መፅሐፈ ሞርሞን

ሌላኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት

መፅሐፈ ሞርሞን

ሌላኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት

በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን
የታተመ
ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ፣ ዩ.ኤስ.ኤ.

የመጀመሪያው የእንግሊዝኛ ቅጂ
በፓልሚራ፣ ኒው ዮርክ፣ ዩ.ኤስ.ኤ. በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ታተመ

ጠቃሚ አስተያየትን ወይም ሀሳቦችን እባካችሁ በ scriptures@ldschurch.org
ወይም ወደ Scriptures Coordination, 50 East North Temple Street Room 2455,
Salt Lake City, UT 84150-3220 USA በደብዳቤ ላኩ

© 2018 by Intellectual Reserve, Inc.
All rights reserved.
Printed in the United States of America 7/2019
English approval: 3/15
Translation approval: 3/15
Translation of Book of Mormon
Amharic

መፅሐፈ ሞርሞን

ከኔፊ ሰሌዳዎች ተወስዶ

በሞርሞን እጅ

በሰሌዳዎች
ላይ የተፃፈ መዝገብ

ስለዚህ፣ ይህ የኔፊ ህዝብ፣ እናም ደግሞ የላማናውያን አጭር ታሪክ ነው—የእስራኤል ቤት ቅሪት ለሆኑት ለላማናውያን፣ እናም ደግሞ ለአይሁድና ለአህዛብ የተፃፈ—በትዕዛዝ መሰረት፣ እናም ደግሞ በትንቢት መንፈስና በመገለጥ የተፃፈ—እንዳይጠፉ ሲባል ተፅፈውና ታሽገው በጌታ የተደበቁ—ለነበረው ትርጉም በእግዚአብሔር ኃይልና ስጦታ ይመጡ ዘንድ—በአህዛብ በኩል በትክክለኛው ጊዜ ይመጡ ዘንድ፣ በሞሮኒ እጅ ታሽጉ፣ እናም ለጌታ የተደበቁ—ትርጉሙም በእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

ጌታ ወደ ሰማይ ለመድረስ ግንብ ሲገነቡ ቋንቋቸውን በደባለቀባቸው ጊዜ የተበተኑት የያሬድ ህዝቦችን ታሪክ ከያዘው ከመፅሐፈ ኤተር የተወሰደ አጭር ታሪክ—ይህም ጌታ ለእስራኤል ቤቶች ቅሪት ለአባቶቻቸው ምን ያህል ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገ ለማሳየት ነው፤ እናም የጌታን ኪዳን ያውቁ ዘንድ፣ ለዘለዓለምም እንደማይጣሉ ያውቁ ዘንድ—እናም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ፣ ዘለዓለማዊ አምላክ እንደሆነ፣ እራሱንም ለሁሉም ሀገሮች እንደገለፀ፣ ለአይሁድና ለአህዛብ እስከማሳመን—እና አሁን፣ ስህተቶች ካሉ ስህተቶቹ የሰዎች ስህተቶች ናቸው፣ ስለዚህ፣ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ያለ እንከን ትሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር የሆኑትን አትኮንኑ።

ከሰሌዳዎቹ የመጀመሪያው የእንግሊዝኛ ትርጉም
በጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ።

ማውጫዎች

መግቢያ 7
የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት 9
የስምንቱ ምስክሮች ምስክርነት 9
የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ምስክርነት 11
አጭር መግለጫ 15
ስዕሎች 17
፩ ኔፊ . . . . . ፩
፪ ኔፊ . . . . . ፻፩
ያዕቆብ . . . . . ፲፫
ኢኖስ . . . . . ፲፯
ጀረም . . . . . ፲፯
ኦምኒ . . . . . ፲፱
የሞርሞን ቃላት . . . . . ፲፱
ሞዛያ . . . . . ፲፳፩
አልማ . . . . . ፪፲፩
ሔለማን . . . . . ፫፲፰
፫ ኔፊ . . . . . ፴፲
፬ ኔፊ . . . . . ፴፲፻፤
ሞርሞን . . . . . ፴፲፰
ኤተር . . . . . ፴፲፰
ሞሮኒ . . . . . ፣፲፣
የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ . . . . . ፩
የዘመን ቅድመ ተከተል . . . . . ፲፣፫
የወንጌሎች ስምምነት . . . . . ፲፣፱

አህፅሮተ ቃላት

ብሉይ ኪዳን

ዘፍጥ.	ኦሪት ዘፍጥረት
ዘፀአ.	ኦሪት ዘፀአት
ዘሌዋ.	ኦሪት ዘሌዋውያን
ዘኁል.	ኦሪት ዘኁልቁ
ዘዳግ.	ኦሪት ዘዳግም
ኢያ.	መፅሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌል
መሳ.	መፅሐፈ መሳፍንት
ሩት	መፅሐፈ ሩት
፩ ሳሙ.	መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
፪ ሳሙ.	መፅሐፈ ሳሙኤል ካልዕ
፩ ነገሥ.	መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ
፪ ነገሥ.	መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ
፩ ዜና	መፅሐፈ ዜና ቀዳማዊ
፪ ዜና	መፅሐፈ ዜና ካልዕ
ዕዝ.	መፅሐፈ ዕዝራ
ነህ.	መፅሐፈ ነህምያ
አስቴ.	መፅሐፈ አስቴር
ኢዮብ	መፅሐፈ ኢዮብ
መዝ.	መዝሙረ ዳዊት
ምሳ.	መፅሐፈ ምሳሌ
መክ.	መፅሐፈ መክብብ
መኃ.	መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን
ኢሳ.	ትንቢተ ኢሳይያስ
ኤር.	ትንቢተ ኤርምያስ
ሰቆ.	ሰቆቃወ ኤርምያስ
ሕዝ.	ትንቢተ ሕዝቅኤል
ዳን.	ትንቢተ ዳንኤል
ሆሴ.	ትንቢተ ሆሴዕ
ኢዩ.	ትንቢተ ኢዩኤል
ዓሞ.	ትንቢተ ዓሞጽ
አብድ.	ትንቢተ አብድዩ
ዮና.	ትንቢተ ዮናስ
ሚክ.	ትንቢተ ሚክያስ
ናሆ	ትንቢተ ናሆም
እንባ.	ትንቢተ እንባቆም
ሶፎ.	ትንቢተ ሶፎንያስ
ሐጌ.	ትንቢተ ሐጌ
ዘካ.	ትንቢተ ዘካርያስ
ሚል.	ትንቢተ ሚልክያስ

አዲስ ኪዳን

ማቴ.	የማቴዎስ ወንጌል
ማር.	የማርቆስ ወንጌል
ሉቃ.	የሉቃስ ወንጌል
ዮሐ.	የዮሐንስ ወንጌል
የሐዋ.	የሐዋርያት ስራ
ሮሜ	ወደ ሮሜ ሰዎች
፩ ቆሮ.	ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፩
፪ ቆሮ.	ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪
ገላ.	ወደ ገላትያ ሰዎች
ኤፌ.	ወደ ኤፌሶን ሰዎች
ፊልጵ.	ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች
ቆላ.	ወደ ቆላስይስ ሰዎች
፩ ተሰ.	ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ፩
፪ ተሰ.	ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ፪
፩ ጢሞ.	ወደ ጢሞቴዎስ ፩
፪ ጢሞ.	ወደ ጢሞቴዎስ ፪
ቲቶ	ወደ ቲቶ
ፊልሞ.	ወደ ፊልሞና
ዕብ.	ወደ ዕብራውያን
ያዕ.	የያዕቆብ መልእክት
፩ ጴጥ.	የጴጥሮስ መልእክት ፩
፪ ጴጥ.	የጴጥሮስ መልእክት ፪
፩ ዮሐ.	የዮሐንስ መልእክት ፩
፪ ዮሐ.	የዮሐንስ መልእክት ፪
፫ ዮሐ.	የዮሐንስ መልእክት ፫
ይሁዳ	የይሁዳ መልእክት
ራዕ.	የዮሐንስ ራዕይ

መፅሐፈ ሞርሞን

፩ ኔፊ	፩ ኔፊ
፪ ኔፊ	፪ ኔፊ
ያዕቆ.	ያዕቆብ
ኢኖስ	ኢኖስ
ጃሬም	ጃሬም
ኦምኒ	ኦምኒ
ቃላት	የሞርሞን ቃላት
ሞዛያ	ሞዛያ
አልማ	አልማ
ሔለ.	ሔለማን
፫ ኔፊ	፫ ኔፊ
፬ ኔፊ	፬ ኔፊ
ሞር.	ሞርሞን
ኤተር	ኤተር
ሞሮኒ	ሞሮኒ

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች

ት. እና ቃ.	ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች
አ.አ.	አስተዳደሪያዊ አዋጅ

የታላቅ ዋጋ ዕንቁ

ሙሴ	ሙሴ
አብር.	አብርሐም
ጆ.ስ.—ማቴ.	ጆሴፍ ስሚዝ—ማቴዎስ
ጆ.ስ.—ታ.	የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክ
እ.አ.	የእምነት አንቀጾች

ሌሎች አህፅሮተ ቃላት እና መግለጫዎች

ጆ.ስ.ት.	የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም
ቅ.መ.መ.	የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ
ዕብ.	የዕብራውያን ቋንቋ አማራጭ ትርጉም።
ግሪ.	የግሪኮች ቋንቋ አማራጭ ትርጉም።
ይህም ማለት	የአነጋገር ዘይቤን እና አስቸጋሪ የቃላት አገባብ መግለጫ።
ወይም	የጥንት መግለጫ ትርጉምን ለመግለጽ አማራጭ ቃላትን ያሳያል።

መግቢያ

መፅሐፈ ሞርሞን ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር የሚመሳሰል ቅዱስ መፅሐፍ ነው። እግዚአ ብሔር በጥንት በአሜሪካ ከኖሩት ህዝቦች ጋር ያደረጋቸው ነገሮች መዝገብ ነው፣ እናም ዘለዓለማዊ የሆነውን የወንጌል ሙላት የያዘ ነው።

መጽሐፉ በብዙ ጥንታዊ ነቢያት በትንቢትና በራዕይ መንፈስ የተፃፈ ነበር። በወርቅ ሰሌዳ ላይ የተፃፉት ቃላቶቻቸው፣ ሞርሞን በተባለ ታሪካዊ ነቢይ የተጠቀሱና ያጠሩ ነበሩ። መዝገቡ ስለ ሁለት ታላላቅ ስልጣኔዎች ይዘግባል። አንደኛው በ፯፱ ም.ዓ. ከኢየሩሳሌም መጣ እና በኋላም ኔፋውያን እና ላማናውያን ወደሚባሉት ሁለት ሀገሮች ተከፈለ። ሌላኛው ይበልጥ ቀድሞ የመጣው ጌታ በባቢሎን ግንብ የህዝቡን ቋንቋ በቀላቀለበት ጊዜ ነው። ይህ ወገን ያሬዳውያን ይባላል። ከሺህ ዓመታት በኋላ፣ ከላማናውያን በስተቀር ሁሉም ጠፉ፣ እናም እነርሱ ከአሜሪካ ሕንዶች ቅድመ አያቶች መካከል አንዳንዶቹ ናቸው።

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የተመዘገበው ታላቁ ድርጊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ በኔፋውያን መካከል ያደረገው የግል አገልግሎት ነው። የወንጌልን ትምህርት ይገልፃል፣ የደህንነትን ዕቅድ ይዘረዝራል፣ እናም በዚህ ህይወት ሰላምን እንዲሁም በሚመ ጣው ህይወት ዘለዓለማዊ ደህንነትን ለማግኘት ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራል።

ሞርሞን ጽሑፉን ካጠናቀቀ በኋላ፣ መዝገቡን ለወንድ ልጁ ለሞሮኒ ሰጠው፤ እርሱም ከራሱ ትንሽ ቃላት በመጨመር በከሞራ ኮረብታ ውስጥ ሰሌዳዎቹን ደበቀ። መስከረም ፳፭፣ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.)፣ ይኸው የከበረው ሞሮኒ፣ ከሞት የተነሳው ሰው፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ታየው፣ እናም ስለጥንታዊው መዝገብ እናም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ መተርጎም ስላ ለው እጣ ፈንታ አስተማረው።

በመጨረሻም ሰሌዳዎቹ በእግዚአብሔር ኃይልና ስጦታ ለተረጎማቸው ለጆሴፍ ስሚዝ ተሰጡ። መዝገቡ አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ እንደ አዲ ስና ተጨማሪ ምስክርነት፣ እናም፤ ወደ እርሱ የሚመጡና የወንጌሉን ህግጋትና ስርዓቶች የሚቀበሉ ሁሉ ይድኑ ዘንድ በብዙ ቋንቋዎች እየተተረጎመ ነው።

ይህንን መዝገብ በተመለከተ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንዲህ ብሏል፥ "ለወንድሞች መፅ ሐፈ ሞርሞን በምድር ካሉ መፅሐፍት በሙሉ የበለጠ ትክክል እንደሆነ፣ እናም የኃይማኖ ታችን የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ፣ እናም ከየትኛውም መፅሐፍ በበለጠ በውስጡ ባሉት አዕምሮአዊ ትእዛዝ በመኖር ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ይችላል ብዬ ነገርኳቸው።"

ከጆሴፍ ስሚዝ በተጨማሪ፣ ጌታ ለራሳቸው የወርቅ ሰሌዳዎቹን እንዲያዩና የመፅሐፈ ሞርሞን እውነተኛነትና መለኮታዊነት ልዩ ምስክር እንዲሆኑ ሌሎች አስራ አንድን መረጠ። የእነዚህ ሰዎች የጽሑፍ ምስክርነት "የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት" እና "የስምንቱ ምስ ክሮች ምስክርነት" ተብሎ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተጨምረው ይገኛሉ።

እኛ ሁሉንም ሰዎች በሁሉም ቦታ መፅሐፈ ሞርሞንን እንዲያነቡት፣ የያዘውን መል ዕክት በልባቸው እንዲያሰላስሉት፣ እናም ዘለዓለማዊውን አባት እግዚአብሔርን በክርስ ቶስ ስም ይህ መፅሐፍ እውነት እንደሆነ እንዲጠይቁት እንጋብዛለን። ይህን ምክር የሚከ ተሉ እናም በእምነት የሚጠይቁ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት የእውነተኛነቱን እን ዲሁም የመለኮታዊነቱን ምስክር ያገኛሉ። (ሞሮኒ ፲፡፣ ፫–፭ን ተመልከቱ።)

ይህንን መለኮታዊ ምስክርነት ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበሉ በዚሁ ኃይል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም አዳኝ እንደሆነ፣ ጆሴፍ ስሚዝ የእርሱ ገላጭ እና በእነዚህ በኋለኛው

ዘመናት ነቢይ እንደሆነ፣ እና ለመሲሁ ዳግም ምፅዓት መዘጋጃም፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የጌታ መንግስት እንደገና በምድር ላይ የተቋቋመ ችበት እንደሆነ ያውቃሉ።

የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት

ይህ ስራ ለሚደርሳቸው ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎች፣ እና ህዝቦች በሙሉ፥ እኛ በእግዚአብሔር አብና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ፣ ይህንን የኔፊ ህዝብ እናም ደግሞ የወንድሞቻቸውን የላማናውያንን፣ እናም ደግሞ ተነግሮበት ከነበረው ግንብ የመጡትን የያሬድ ህዝብ ታሪክ የያዘውን መዝገብ እንዳየን የታወቀ ይሁን። እናም እኛ ደግሞ በእግዚአብሔር ኃይልና ስጦታ እንደተተረጎሙ የእርሱ ድምፅ ነግሮናልና እናውቃለን፤ ስለዚህ ስራው እውነተኛ እንደሆነ በእርግጠኝነት እናውቃለን። እናም ደግሞ በሰሌዳዎቹ ላይ የነበሩትን የተቀረፁ ጽሑፎች እንዳየን እንመሰክራለን፤ እናም እነርሱ ለእኛ የታዩን በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል ነው። እናም እኛ አንድ የእግዚአብሔር መልአክ ወርዶ እናም በዐይኖቻችን ፊት እንዳስቀመጠው፣ በዚያ ላይ የነበሩትን ሰሌዳዎችና የተቀረፁትን እንደተመለከትንና እንዳየን በጥሞና ቃላት እንናገራለን፤ እናም እኛ እነዚህን ነገሮች አይተን እውነት እንደሆኑ የምንመዘግበው በእግዚአብሔር አብ እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ እንደሆነ እናውቃለን። እናም በእኛ አመለካከት ይህ ድንቅ ነው። ይሁን እንጂ፣ የጌታ ድምፅ ስለዚህ ነገር ምስክርነት ቃል እንድንሰጥ አዞናል፤ ስለዚህ፣ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለመታዘዝ፣ ስለእነዚህ ነገሮች ምስክርነት እንሰጣለን። እናም በክርስቶስ ታማኞች ከሆንን፣ ልብሶቻችንን ከሰዎች ሁሉ ደም በማንፃት፣ እናም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ያለ እንከን እንደምንገኝ እናውቃለን፣ እናም ከእርሱ ጋር በሰማያት ለዘለዓለም እንኖራለን። እናም አንድ አምላክ ለሆኑት ለአብ፣ እናም ለወልድ፣ እናም ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ይሁን። አሜን።

ኦሊቨር ካውድሪ
ዴቪድ ዊትመር
ማርቲን ሀርስ

የስምንቱ ምስክሮች ምስክርነት

ይህ ስራ ለሚደርሳቸው ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝቦች በሙሉ፥ ወርቅ የሚመስሉትን ሰሌዳዎች የእዚህ ስራ ተርጓሚ፣ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እንዳሳየን፣ እናም የተባለው ስሚዝ የተረጎማቸውን ብዙዎቹን ገጾች በእጆቻችን እንደዳሰስናቸ የታወቀ ይሁን፤ እናም ደግሞ በዚያም ላይ የተቀረፁትን ተመልክተናል፣ ሁሉም የጥንት ስራ፣ እና በብልሃት የመሰራት ገፅታ አላቸው። እናም የተባለው ስሚዝ ለእኛ እንዳሳየን፣ እናም አይተን እንዳነሳን እናም የተባለው ስሚዝ ያልናቸውን ሰሌዳዎች እንዳለው በእርግጥ ማወቃችንን በጥሞና ቃላት ምስክርነት እንሰጣለን። ያየነውም ለዓለም ሁሉ ምስክር ይሆን ዘንድ ስማችንን ለዓለም እንሰጣለን። እናም አልዋሸንም፣ እግዚአብሔርም ስለዚህ ይመሰክራል።

ክርስቲያን ዊትመር
ጄኮብ ዊትመር
ፒተር ዊትመር፣ ዳግማዊ
ጆን ዊትመር
ሀይረም ፔጅ
ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ
ሀይረም ስሚዝ
ሳሙኤል ሔሪሰን ስሚዝ

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ምስክርነት

የመፅሐፈ ሞርሞንን መምጣት በተመለከተ የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የራሱ ቃላት የሚከተሉት ናቸው፥

“በመስከረም [ፕሬዚዳንት] (እ.አ.አ.) ምሽት ላይ . . . በትህትና ሁሉን ለሚገዛው እግዚአብሔር መፀለይ እና መማጸን ጀመርኩ። . . .

“እግዚአብሔርን በመጥራት ላይ ባለሁበት ጊዜ፣ ብርሃን በክፍሌ ውስጥ ሲመጣ ተመለከትኩ፣ ብርሃኑም ከቀትር ፀሐይ እስኪበልጥ ድረስ መጨመሩን ቀጠለ፣ ወዲያውኑም አንድ ሰው በአልጋዬ አጠገብ እግሩ መሬት ሳይነካ በአየር ላይ ቆሞ ተገለጠልኝ።

“በጣም ያሸበረቀ ነጭ ካባ ለብሶ ነበር። ንጣቱም ምድራዊ ከሆኑ ካየኋቸው ነገሮች በሙሉ የበለጠ ነበር፤ ማንኛውም ምድራዊ ነገር እንደዚህ እጅግ ነጭና ደማቅ መሆን ይችላል ብዬም አላምንም። እጆቹ፣ እናም ደግሞ ክንዶቹ፣ ከፍንጃ ትንሽ ከፍ ብሎ፣ በልብስ አልተሸፈኑም ነበር፤ እግሮቹም ደግሞ እንዲሁ ከቁርጭምጭሚቱ በላይ በልብስ አልተሸፈኑም ነበር። ራሱና አንገቱም የተገለጡ ነበሩ። ካባው ተከፍቶ ደረቱን ማየት እችል ስለ ነበር፣ ከካባው በቀር ሌላ ልብስ እንዳልነበረው ለማወቅ እችል ነበር።

“እጅግም የነጣው ካባው ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን መላ ሰውነቱ መግለፅ ከሚቻለው በላይ ብሩህ ነበር፣ እንዲሁም ፊቱ በእውነት ልክ እንደ መብረቅ ነበር። ክፍሉ እጅግ ብርሃን ነበር፣ ነገር ግን ልክ በእርሱ ዙሪያ እንደነበረው በጣም የደመቀ አልነበረም። በመጀመሪያም ወደ እርሱ በተመለከትኩ ጊዜ ፈርቼ ነበር፣ ነገር ግን ፍርሃቱ ወዲያው ለቀቀኝ።

“በስሜ ጠራኝ፣ እናም እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እኔ የተላከ መልዕክተኛ እንደ ሆነና ስሙም ሞሮኒ እንደሆነ፣ እግዚአብሔርም ለእኔ የምሰራው ስራ እንደነበረው፤ እናም ስሜም በሁሉም ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝብ መካከል በጥሩና በመጥፎ እንደሚነሳ፣ ወይም በሁሉም ህዝብ መካከል ጥሩና መጥፎ እንደሚባልልኝ ነገረኝ።

“እርሱ በዚህ አህጉር ቀድመው ነዋሪ ስለነበሩት ታሪክ እና እነርሱ የመጡበትን ምንጭ ከየት እንደሆነ የሚናገር በወርቅ ሰሌዳዎች ላይ ተፅፎ የተቀበረ መፅሐፍ እንዳለ ተናገረ። ለጥንት ነዋሪዎች በአዳኙ የተሰጠውን የዘለዓለማዊውን ወንጌል ሙሉነትም በውስጡ እንደያዘ ደግሞ ተናገረ፤

“ደግሞ ከሰሌዳዎቹም ጋር የተቀበሩ ሁለት ድንጋዮች በብር ቅስት ውስጥ ነበሩ፣ እናም እነዚህ ድንጋዮች፣ በደረት ኪስ ታስረው፣ ኡሪምና ቱሚም የሚባለውን ይሰራሉ፤ እናም የእነዚህ ድንጋዮች ባለቤትና ተጠቃሚ በጥንት ወይም በድሮ ጊዜ ‘ባለራዕይ’ የሚባሉት ናቸው፤ እናም እግዚአብሔር መጽሐፉን ለመተርጎም ዓላማ እነርሱን አዘጋጅቶ ነበር።. . .

“እንደገናም፣ እርሱ የተናገረኝን ሰሌዳዎች ሳገኝ—እነርሱን የምወስድበት ትክክለኛው ጊዜ ገና እንዳልተሟላና—እኔ ማሳየት እንዳለብኝ ከምታዘዘው በቀር እነዚህን ወይም የደረት ኪሱን ከኡሪምና ቱሚም ጋር ለማንም ሰው ማሳየት እንደሌለብኝ፤ ይህን ካደረግሁ ግን መጥፋት እንዳለብኝ ነገረኝ። እርሱ ከእኔ ጋር ስለሰሌዳዎቹ በሚነጋገርበት ጊዜ ሰሌዳዎቹ የተቀበሩበትን ቦታ ማየት እንድችል ራዕይ ለአዕምሮዬ ተገለፀ፣ እናም ይህም በጣም ግልጽ እና ጉልህ ሆኖ ታይቶኝ ቦታውን በጎበኘሁበት ጊዜ እንደገና አውቄው ነበር።

“ይህን ሁሉ ከሰማሁ በኋላ ብርሃን በክፍሉ ውስጥ ባናገረኝ ሰው ዙሪያ በፍጥነት መሰብሰብ ሲጀምር አየሁ፣ እናም ከእርሱ ዙሪያ በቀር ክፍሉ እንደገና እስኪጨልም ሲቀጥል፣ ወዲያውም መተላለፊያ ቀጥታ ወደ ሰማይ ሲከፈት የተመለከትኩኝ መሰለኝ፣

እናም እርሱ እስኪጠፋ ድረስ አረገ፣ እናም ክፍሉ ይህ ሰማያዊ ብርሃን ከመታየቱ በፊት እንደነበረው ሆነ።

“እኔ ተኝቼ በዚህ እንግዳ ዕይታ በጥንቃቄ አሰብኩ፣ እናም ይህ እንግዳው መልዕክተኛ በነገረኝ ታላቅ አስደናቂ ነገር፤ በሃሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ክፍሌ እንደገና እየደመቀ መም ጣቱን በድንገት ተመለከትኩ፣ እናም ወዲያው ያው የሰማይ መልዕክተኛ በድጋሚ አል ጋዬ አጠገብ መሆኑን ተመለከትኩ።

“እርሱም መናገር ጀመረ፣ እናም እንደገና በመጀመሪያ ጉብኝቱ ያደረጋቸውን አንድ አይነት ነገሮች ምንም ሳይለውጥ ተናገረ፤ ይህንን ካደረገ በኋላ፣ ከታላቅ ጥፋት ጋር በረ ሃብ፣ በሰይፍ፣ እና በቸነፈር፣ ታላቅ ፍርድ በምድር እንደሚመጣ፤ እናም እነዚህ አሳዛኝ ፍርዶች በምድር ላይ በዚህ ትውልድ እንደሚመጡ ገለፀልኝ። እነዚህን ነገሮች ከነገረኝ በኋላ ልክ እንደ በፊቱ በድጋሚ አረገ።

“በዚህ ጊዜ በአዕምሮዬ የተቀረፁት በጣም ጥልቅ ነገሮች ስለነበሩ፣ እንቅልፍ ከዐይ ኖቼ ጠፋ፣ እናም ባየሁትና በሰማሁት በመደነቅ ተሸንፌ ተኛሁ። ነገር ግን ይገርመኝ የነ በረው ነገር በድጋሚ ያንን መልዕክተኛ በአልጋዬ በኩል ሳየው፣ እናም ያንኑ የበፊቱን ነገ ሮች እንደገና ሲደግመው ሰሰማ፣ እናም ሰይጣን ሰሌዳዎቹን ሳገኝ (የአባቴ ቤተሰቦች ድሃ በመሆናቸው ምክንያት) ሀብታም እንድሆንባቸው ሊፈትነኝ እንደሚሞክር ማስጠንቀቂያ ሲጨምርልኝ ነበር። እርሱም፣ ጌታን ከማሞገስ በስተቀር፣ ይኸውም ሰሌዳዎቹን በማግ ኘቴ ሌላ አእምሮዬን የማያነሳሳ ነገር መኖር እንደሌለበት እንዲህ በማለት ከለከለኝ፣ እናም የእርሱን መንግስት ከመገንባት በማንኛውም ሌላ ነገር ተፅዕኖ ሊደርስብኝ እንደማይገባ አለበለዚያ እነርሱን ማግኘት እንደማልችል ተናገረኝ።

“ከዚህ ከሦስተኛው ጉብኝት በኋላ፣ ልክ እንደበፊቱ በድጋሚ ወደ ሰማይ አረገ፣ እናም አሁን ስለአየሁት እንግዳ ነገር በድጋሚ ማሰላሰሌን ቀጠልኩ፤ ልክ የሰማዩ መልዕክተኛ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሰማይ ሲያርግ፣ ዶሮ ጮኸ፣ እናም እየነጋ መሆኑን ተገነዘብኩ፣ ስለ ዚህ ንግግራችንም ያን ምሽት በሙሉ የያዘ እንደነበር ተረዳሁ።

“ከትንሽ ጊዜም በኋላ ከመኝታዬ ተነሳሁ፤ እናም እንደተለመደው፣ ለቀኑ አስፈላጊ ወደ ሆነው ስራ ሄድኩ፤ ነገር ግን በሌላ ጊዜ እንደምሰራው ስሞክር፣ ኃይልን በማጣቴ ያም ለመስራት ፍፁም አላስቻለኝም። አባቴ ከእኔ ጋር ሲሰራ በእኔ በኩል አንድ ችግር እንዳለ አየ፣ እናም ወደ ቤት እንድሄድ ተናገረኝ። ወደ ቤት ለመሄድ ጀመርኩ፤ ነገር ግን እኛ የነበርንበትን የሜዳ አጥር ለማቋረጥ ስሞክር ብርታቴን በሙሉ አጣሁ፣ እናም አቅ ቶኝ በመሬት ላይ ወደቅሁ፣ እናም ለተወሰነ ጊዜ አዕምሮዬን ስቼ ነበር።

“የመጀመሪያው የማስታውሰው ነገር አንድ ድምፅ በስሜም እየጠራኝ ሲያናግረኝ ነበር። ተመለከትኩ፣ እናም የፊተኛው መልዕክተኛ ልክ እንደበፊቱ በብርሃን ተከቦ በጭንቅላቴ በኩል ቆሞ አየሁ። እናም እርሱ ባለፈው ምሽት ለእኔ የተናገረውን ሁሉ እንደገና ተና ገረ፣ እናም ወደ አባቴ በመሄድ ስለራዕዩና ስለተቀበልኩት ትዕዛዛት እንድናገር አዘዘኝ።

“እኔም ተቀበልኩ፤ በሜዳው ወደአለው አባቴም ተመለስኩ፣ እናም ሁሉንም ነገር ለእርሱ ነገርኩት። እርሱም ከእግዚአብሔር ነው ብሎ መለሰልኝ፣ እናም በመልዕክተ ኛው የታዘዝኩትን እንድሄድና እንዳደርግ ነገረኝ። ከሜዳውን ወጣሁ፣ እናም መልዕክተ ኛው ሰሌዳዎቹ ተቀብረዋል ብሎ ወደነገረኝ ቦታ ሄድኩ፤ ያንን በተመለከተ ግልፅ ራዕይ ስለነበረኝ፣ ስፍራው እንደደረስኩ ወዲያው አወቅሁት።

“በኒው ዮርክ፣ በማንቸስተር መንደር፣ በአንታሪዮ የግዛት ክፍል አጠገብ አንድ ትልቅ፣ እናም ከማንኛውም በአቅራቢያው ካሉት ሁሉ የበለጠ ኮረብታ ቆሟል። በኮረብታው በስተ ምዕራብ በኩል ከጫፉ ራቅ ሳይል፣ በትልቅ ድንጋይ ስር ሰሌዳዎቹ በድንጋይ ሳጥን ውስጥ

ተቀብረዋል። ትልቁ ድንጋይ በላይ በኩል ከመሀሉ ወፍራምና ክብ፣ እንዲሁም ወደጠ ርዙም በኩል ቀጭን ነበር፣ ስለዚህ የመካከለኛው ክፍሉ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፤ ነገር ግን ጠርዞቹ በሙሉ በመሬቱ ተሸፍነው ነበር።

“አፈሩን ከቆፈርኩኝ በኋላ፣ ሰቅስቆ ማንሻ አገኘሁ፣ ይህንንም ከድንጋዩ ጠርዝ ላይ ተከልኩኝ፣ እናም በትንሽ ጉልበት አነሳሁት። ወደ ውስጥ ተመለከትኩ፣ እና በእዚያም መልዕክተኛው እንደገለፀው በእርግጥ ሰሌዳዎቹን፣ ኡሪምና ቱሚም፣ እናም የደረት ኪሱን ተመለከትኩ። በውስጡ የተቀመጡበት ሳጥን ሲሚንቶ በሚመስል በተነባበሩ ድንጋዮች የተሰራ ነበር። ከሳጥኑ በታች በኩል ሁለት ድንጋዮች ተቀምጠዋል፣ እናም በእነዚህ ድን ጋዮች ላይ ሰሌዳዎችና ከእነርሱ ጋር ሌሎች ነገሮች ነበሩ።

“እኔ እነርሱን ለማውጣት ሞከርኩ፣ ነገር ግን በመልዕክተኛው ተከለከልኩ፣ እናም እን ደገና የእነርሱ ማውጫ ጊዜ ገና እንዳልደረሰ፣ ከእዚህም ጊዜ ከአራት አመት በኋላ ድረስ እንደማይደርስም አስታወቀኝ፤ ነገር ግን እርሱ ልክ ከእዚያ ጊዜ በአንድ አመት ወደ እዚ ያው ቦታ መምጣት እንዳለብኝ፣ እናም እርሱ እዚያ እንደሚያገኘኝ፣ እናም ሰሌዳዎቹ የምወስድበት ጊዜ እስከሚመጣ ይህን ማድረግ መቀጠል እንዳለብኝ ተናገረኝ።

“በታዘዝኩት መሰረት፣ በየአመቱ መጨረሻ እሄድ ነበር፣ እናም በእያንዳንዱ ጊዜም ያንኑ መልዕክተኛ በእዚያ አገኘሁት፣ እናም በእያንዳንዱ ንግግራችን ጌታ እንደሚያደ ርግ በተመለከተ፣ እናም እንዴትና በምን አይነት ሁኔታ የእርሱ መንግስት በመጨረሻው ቀን እንደሚመራ መመሪያና እውቀት ከእርሱ እቀበል ነበር።. . .

“በመጨረሻም ሰሌዳዎቹን፣ ኡሪምና ቱሚም፣ እና የደረት ኪስን የማገኝበት ጊዜ ደረሰ። መስከረም ሃያ ሁለት በአንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሰባት (እ.አ.አ.)፣ ልክ እንደ ተለመደው በሌላኛው አመት መጨረሻ ወደ ተቀበሩበት ቦታ ስሄድ፣ ያው የሰማይ መል ዕክተኛ እነዚህን ከዚህ ትዕዛዝ ጋር ለእኔ ሰጠኝ፤ ይኸውም ለእነሱ ሀላፊ መሆን እንዳለ ብኝ፣ በቀላሉ ወይንም በራሴ ንዝህላልነት እንዲሄዱ ካደረግሁ እንደምገለል፤ ነገር ግን ራሱ መልዕክተኛው እንድመልስለት እስከሚጠይቀኝ ደረስ ያለኝን ጥረቴን ሁሉ እነሱን ለመጠበቅ ከተጠቀምኩ፣ እነርሱ እንደሚጠበቁ ነበር።

“እኔ እነርሱን በጥንቃቄ እንዳስቀምጥ ለምን ጥብቅ መመሪያ የተቀበልኩትን፣ እናም ከእኔ የተፈለገውን ባደረግሁ ጊዜ እነርሱን እንድመልስለት የሚጠይቅበትን ምክንያት በፍጥነት አገኘሁት። እነርሱ እንዳሉኝ እንደታወቀ፣ ወዲያውኑ ከእኔ እነርሱን ለመው ሰድ ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነ ጥረት ተደረጉ። ይህንንም ዓላማ ለማሳካት የተለያዩ ሥል ቶች ጥቅም ላይ ውለዋል። ስደቱም ከበፊቱ የበለጠ አሰቃቂና መራራ ሆነ፣ እናም ብዙ ህዝብም የሚቻል ከሆነ እነርሱን ከእኔ ለመውሰድ በማድፈጥ መጠበቅ ቀጥለው ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ጥበብ ከእኔ የሚፈለገውን እስከማከናውን ድረስ በጥንቃቄ በእጄ ውስጥ ተቀመጡ። በዕቅዱ መሠረት መልዕክተኛው ሊወስዳቸው ሲመጣ፣ እኔም ለእርሱ ሰጠኋ ቸው፤ እናም እስከዚያ ቀን፣ ግንቦት ሁለተኛው ቀን አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስም ንት (እ.አ.አ.)፣ ድረስም በእርሱ ቁጥጥር ስር።”

ለተሟላ ዘገባ፣ በታላቅ ዕንቁ ዋጋ ውስጥ የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክን ተመልከቱ።

ከተቀበረበት የወጣው ጥንታዊው ታሪክ ልክ ህዝቦች ከመሬት እንደሚናገሩት ድምፅ እናም በእግዚአብሔር ኃይልና ስጦታ በአምላክ እውነትነቱ ተረጋግጦ ወደ ዘመናዊው ቋንቋ የተተረጎመው፣ በመጀመሪያ በ፲፰፻፴ ዓመተ ምህረት (እ.አ.አ.) ለዓለም በእንግሊ ዝኛ The Book of Mormon ተብሎ ታተመ።

ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ

መፅሐፈ ሞርሞን በብረት ሰሌዳዎች ላይ የተቀረጸ እና በጥንታዊት አሜሪካ የነበሩ ህዝቦች ቅዱስ ታሪክ ነው። ይህ መዝገብ የተጠረዘበት ምንጮቹ የሚከተሉት ናቸው፥

፩ ሁለት ዓይነት የነበሩት *የኔፊ ሠሌዳዎች*፥ ትንንሾቹ ሠሌዳዎች እና ትልልቆቹ ሠሌዳዎች። የመጀመሪያው በተለይ በብዛት የተፃፈበት ስለመንፈሳዊ ነገሮችና ስለነቢያት አገልግሎትና ትምህርቶች ሲሆን፣ የኋለኞቹ በአብዛኛው በ(፩ ኔፊ ፱፥፪–፴) ያሉትን ህዝቦች አለማዊ ታሪክ በተመለከተ የተፃፈ ነበር። ሆኖም፣ ከሞዛያ ጊዜ ጀምሮ ትልቁ ሰሌዳ ዋናውን መንፈሳዊ ጠቃሚ ዝርዝሮችን አጠቃሏል።

፪ *የሞርሞን ሠሌዳዎች*፣ ከብዙ ሀተታዎች ጋር ከትልቁ ከኔፊ ሰሌዳዎች ላይ በሞርሞን በማሳጠር የተፃፉትን ይዘዋል። እነዚህ ሰሌዳዎች ደግሞ የሞርሞን ታሪክ ቅጥያ እና የወንድ ልጁ የሞሮኒን ተጨማሪዎችን ይዘዋል።

፫ *የኤተር ሠሌዳዎች*፣ የያሬዳውያንን ታሪክ ያቀርባል። ይህ ታሪክ ያጠረው የራሱን አስተያየት ጨምሮ ከጠቅላላው "መፅሐፈ ኤተር" ከሚባለው ታሪክ ጋር ባቀላቀለው በሞሮኒ ነው።

፬ *የነሀስ ሠሌዳዎች* በሌሂ ህዝቦች በ፮፻ ም.ዓ. ከኢየሩሳሌም የመጡ ናቸው። እነዚህም "አምስቱን የሙሴ መፅሐፍ፣ . . . እናም ደግሞ የአይሁዶችን ታሪክ ከመጀመሪያው ጀምሮ . . . እስከ የይሁዳ ንጉስ ሰዴቅያስ የመጀመሪያ ንግስ ድረስ፤ እናም ደግሞ የቅዱሳን ነቢያትን ትንቢቶችን" ይይዛሉ (፩ ኔፊ ፭፥፣ ፲፩–፲፫)። ከእነዚህ ሰሌዳዎች ብዙ ጥቅሶች፣ ኢሳይያስንና ሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ፣ እና ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ነቢያትን፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ሲጠቅሱ ይታያሉ።

መፅሐፈ ሞርሞን፣ ከአንዱ በስተቀር በልምድም በዋናው ፀሐፊያቸው ስም የሚጠሩ መፅሐፍ ተብለው የሚታወቁ፣ አስራ አምስት ዋና ዋና ክፍሎችን ይዟል። የመጀመሪያው ክፍል (በኦምኒ የሚያልቁ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ መፅሐፍቶች) ከትንሹ የኔፊ ሰሌዳዎች የተተረጎመ ነው። በኦምኒና በሞዛያ መፅሐፍቶች መካከል የሞርሞን ቃላት የተባለ ገብቷል። ይህ በመሀል የገባው በትንሹ ሰሌዳዎች ላይ የተቀረፁትን ታሪኮች ከትልቁ የሞርሞን ታሪክ ጋር ያያይዛል።

ከሞዛያ እስከ ሞርሞን ምዕራፍ ሰባት ያሉት ትልቁ ክፍል፣ ከትልቁ የኔፊ ሰሌዳዎች ላይ ሞርሞን ካጠረው የተተረጎመ ነው። ማጠቃለያው ክፍል፣ ከሞርሞን ምዕራፍ ፰ እስከ መጽሐፉ መጨረሻ፣ በሞርሞን ልጅ በሞሮኒ የተቀረፁ ነበሩ፣ እርሱም የአባቱን ህይወት ከመዘገበ በኋላ የያሬዳውያንን ታሪክ አሳጥሮ (እንደ መፅሐፈ ኤተር) ፃፈ፣ እናም በኋላ መፅሐፈ ሞሮኒ የተባለውን ክፍል ጨመረበት።

በ፬፻፷፭ ዓ.ም. ወይም ገደማ፣ የመጨረሻው የኔፊ ባለታሪክ እና ነቢይ ሞሮኒ፣ በጥንታዊ ነቢያት አማካኝነት እንደተተነበየው በእግዚአብሔር ድምፅ በኋለኛው ቀን እንዲመጣ ቅዱሱን መዝገብ አተመው እናም በጌታ እንዲጠበቅ ደበቀው። በ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.) የቀድሞው ሞሮኒ፣ ከሞት የተነሳው ሰው፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝን ጎበኘው፣ እናም በመጨረሻ ተቀርጾባቸው የተቀበሩትን ሰሌዳዎች ሰጠው።

ስለዚህ ቅጂ፥ የመጀመሪያው የርዕስ ገፅ ወዲያው የሚከተለው የማውጫውን ገፅ ከሰሌዳው የተወሰደ ነው እናም የተቀደሰ ፅሁፍ ክፍል ነው። እንደ ፩ ኔፊ እና ከሞዛያ ምዕራፍ ፱ ወዲያው ተከትለው እንዳሉት አይነት ጠመም ባለ የፊደል አጣጣል የተጻፉ መግቢያዎችም

የተቀደሰ ፅሁፍ ክፍል ናቸው። እንደ ምዕራፍ ርዕስ አይነቶቹ ጠመም ባለ የፊደል አጣ ጣል የተጻፉት መግቢያዎች በፅሁፉ በመጀመሪያ ይገኙ የነበሩ አይደሉም ነገር ግን በጥ ናት እርዳታ ለምንባብ ምቾት እንዲሆኑ የተጨመሩ ናቸው።

በእንግሊዝኛ በታተሙት በመፅሐፈ ሞርሞን የድሮ ቅጂዎች ውስጥ በጽሁፍ አንዳንድ ቀላል ስህተቶች ተቀታትለው የመጡ ነበሩ። ይህ ቅጂ ይህን ጽሁፍ ከመታመቱ በፊት ከነ በረው ጽሁፍ እና በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ከተስተካከሉት ከመጀመሪያ ቅጂዎች ጋር ለማስ ማማት አስፈላጊ የሆኑትን ያስተካክላል።

ስዕሎች



ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
በሃይንሪክ ሆፍማን የተሳለ



ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ
በአልቭን ጊትንስ የተሳለ

“የነቢዮ ጆሴፍ ስሚዝ ምስክርነት፣” ገጽ 11–13 ተመልከቱ

ሉሂ ሊ.ያሆናውን አገኘ

በአርኖልድ ፍራይበርግ የተሳለ

ፎ ኔፊ ፲፯፣ ገጽ ፴፪–፴፭ ተመልከቱ

ሌሂ እና ህዝቡ በቃል ኪዳን ምድር ውስጥ ደረሱ
በአርኖልድ ፍራይበርግ የተሳለ

ᎧᏂᏎᏗᏥ፣ ገጽ ᏯᏂᏯᏑ ተመልከቱ

ኣልማ ሓለፈ ከመይ ጌሩ ወሰደ ኣብ ቀመሓ

በኣርናልድ ፍራይበርግ የሁሳስ

ዝተሳዕሎ ሥዕሊ ፕሮፌሰር ሓመልማሊ ; ፕሮፌሰር ሓመሓ

ላምናውያን ሳሙኤል ተነበየ
በአርኖልድ ፍራይበርግ የተሳለ

ሔለማን ፲፯፡ ገጽ ፫፻፶፯–፫፻ ተመልከቱ

ኢየሱስ ክርስቶስ አሜሪካን ጎበኘ
በጆን ስኮት የተሳለ

ቮ ኔፊ ፲፯፡ ገጽ ፹፱–፹፰ ተመልከቱ

ሞሮኒ የኔፋውያንን መዝገብ ቀበረ

በቶማስ ለቭል የተሳለ

ሞርሞን ፰፣ ገጽ ፬፻፫፪–፬፻፫፭ ተመልከቱ

የመጀመሪያው የኔፊ መጽሐፍ

ንግስ እና አገልግሎቱ

የሌሂና የሚስቱ የሳርያ፣ እንዲሁም የእርሱ አራት ልጆች (ከበኩር ጀምሮ) ላማን፣ ልሙ ኤል፣ ሳምና፣ ኔፊ ተብለው የሚጠሩት መዝገብ። ጌታ ሌሂን ከኢየሩሳሌም ምድር እን ዲወጣ አስጠነቀቀው፣ ምክንያቱም እርሱ የህዝቡን ክፋት በተመለከተ ስለተነበየ እነርሱ ህይወቱን ሊያጠፉ ፈለጉ። ከቤተሰቡም ጋር የሶስት ቀን ጉዞ ወደ ምድረበዳ አደረገ። ኔፊ የአይሁዶችን መዝገብ ለመውሰድ ወንድሞቹን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ምድር ተመለሰ። ስለ ስቃያቸው ታሪክ። እነርሱም የእስማኤልን ሴት ልጆች አገቡ። ቤተሰቦቻቸውንም ይዘው ወደ ምድረበዳ ሄዱ። በምድረበዳ ውስጥ የነበራቸው ስቃያቸውና መከራቸው። የጉዞአቸ ውም አቅጣጫ። ወደ ትልቁ ውሃ መጡ። የኔፊ ወንድሞች በእርሱ ላይ አመፁ። እርሱም እነርሱን ዝም አሰኛቸው፣ እና መርከብን ሰራ። የቦታውንም ስም ለጋስ ብለው ጠሩት። ታላቁን ውሃ ተሻግረው ወደ ቃል ኪዳን ምድር ቀጠሉ። ይህ በኔፊ አመዘጋገብ መሰረት ነው፣ ወይም በሌላ አነጋገር እኔ፣ ኔፊ፣ ይህን ታሪክ ፃፍኩ።

ምዕራፍ ፩

ኔፊ የእርሱን ሕዝብ የሕይወት ታሪክ መመ ዝገብ ጀመረ— ሌሂ የእሳት አምድ በራ ዕይ አየ እናም ከትንቢት መጽሐፍም አነ በበ— እግዚአብሔርንም አወደሰ፣ የመሲ ህን መምጣት አስቀድሞ ተናገረ፣ እንዲ ሁም የኢየሩሳሌምን ጥፋት ተነበየ፣ በአይ ሁዶች ስደት ደረሰበት። ፯፮ ዓ.ዓ. ገደማ።

እኔ [1]ኔፊ፣ [2]ከመልካም ሐወላጆች የተ ወለድኩ በመሆኔ አባቴ ከሚያውቃ ቸው በመጠኑ [3]ተማርኩ፤ እናም በዘመ ኔም ብዙ [4]መከራን ብመለከትም፣ በጊዜዬ ሁሉ ከጌታ ድጋፍን በማግኘቴ፣ አዎን የእ ግዚአብሔርን ቸርነትና [5]ሚስጥሮች ታላቅ ዕውቀት በማግኘቴ፣ በጊዜዬ የተፈፀሙ ድርጊቶቼን [6]እመዘግባለሁ።

፪ አዎን፣ የአይሁዶችን ትምህርት እና የግብፃውያንን [7]ቋንቋ በያዘው በአባቴ ቋንቋ እጽፋለሁ።

፫ የምፅፈው ታሪክ [8]እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፣ በገዛ እጄም እፅፈዋለሁ፣ እናም እንደዕውቀቴም እፅፈዋለሁ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ በይሁዳ ንጉስ [9]ሴዴ ቅያስ [10]በአንደኛ የንግስ ዓመት መጀመ ሪያ (አባቴ ሌሂ በህይወቱ ሁሉ [11]በኢየሩ ሳሌም ውስጥ ኖሯል)፤ እና በዚያም አመት ህዝቡ ንስሀ መግባት እንዳለባቸው አለበ ለዚያ ታላቁ ከተማ [12]ኢየሩሳሌም መጥ ፋት እንዳለባት የሚተነብዩ ብዙ [13]ነቢ ያት ተነሱ።

፭ ስለዚህ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ [14]ሌሂ በወጣ ጊዜ፣ አዎን በሙሉ [15]ልቡ በእርግጥ ስለህዝቡ ወደጌታ ይፀልይ ነበር።

፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኔፊ፣ የሌሂ ልጅ።
ለ ምሳ. ፳፪፡፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፰፡፲፭፣ ፳፰።
ቅ.መ.መ. ወላጆች።
መ ኢሮስ ፩፡፩፤
ሞዛያ ፩፡፪–፫።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
ሠ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ረ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ሰ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
፪ *ሀ* ሞዛያ ፩፡፪–፬፤
ሞር. ፱፡ ፴፪–፴፫።
፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፡፡ ፴፣
ሞዛያ ፩፡፲፤
ኤተር ፭፡ ፩–፫፣
ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲።
፬ *ሀ* ፪ ዜና ፴፯፡ ፲፣
ኤር. ፶፪፡ ፣–፭፣
ኦምኒ ፩፡ ፲፭።
ለ ፭ ፣ ፣ ፣ ዓ.ዓ.፣ በተጨማሪ
ውስጥ የዘመን ቅድመ
ተከተልን ተመልከቱ።
ሐ ፩ ዜና ፱፡ ፣።
መ ፪ ነገሥ. ፲፯፡ ፣–፣ ፭፣
፪ ዜና ፴፯፡ ፣ ፭–፣ ፣
ኤር. ፣፡ ፳፭–፳፯።
ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ሠ ኤር. ፳፯፡ ፣ ፣፣
፪ ኔፊ ፩፡ ፣፣
ሐለ. ፣፡ ፣።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሌሂ፣ የኔፊ አባት።
ለ ያዕ. ፭፡ ፣ ፣።

፤ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ጌታ ሲፀልይ የእሳት ᵐአምድ ወረደና በፊቱ በአለት ላይ አረፈ፣ ብዙ አየ፣ ሰማም፤ እናም ባያቸውና በሰማቸው ነገሮች ምክንያት እጅግ ፈራና ተንቀጠቀጠ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በኢየሩሳሌም ወደ ሚገኘው ቤቱ ተመለሰ፤ እናም በመንፈስና ባያቸው ነገሮች ᵐተዳክሞ እራሱን በአልጋው ላይ ወረወረ።

፮ እና በመንፈስ እንዲህ ተዳክሞ፣ ᵐበራዕይ ተወሰደ፣ እንዲሁም ᶮሰማያት ተከፍተው አየ፤ እግዚአብሔርንም በዙፋኑ ተቀምጦ አምላካቸውን ሲያሞግሱና ሲዘምሩ በሚታዩት ስፍር ቁጥር በሌላቸው መላእክት ተከብቦ ማየቱን ተገነዘበ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ ከሰማይ መካከል አንድ ሰው ሲወርድ አየ፣ ᵐድምቀቱም ከቀትር ፀሐይ ይበልጥ እንደነበር ተመለከተ።

፲ እናም ሌሎች ᵐአስራ ሁለት እሱን ሲከተሉት አየ፣ ብርሃናቸውም ከጠፈር ውስጥ ከዋክብት የሚልቅ ነበር።

፲፩ እነርሱም ወረዱና ወደ ምድር ገፅመጡ፤ አንደኛውም መጣና በአባቴ ፊት ቆሞ፣ ᵐመፅሐፍ ሰጠውና ማንበብ እንዳለበት ነገረው።

፲፪ እንዲህ ሆነ እያነበበ ሳለ በጌታ ᵐመንፈስ ተሞልቶ ነበር።

፲፫ እናም እርሱ እንዲህ ብሎ አነበበ፥ ወዮ፣ ወዮ፣ ᵐለኢየሩሳሌም፣ ያንቺን ᶮርኩሰት አይቻለሁና፣ አዎን እናም አባቴም ኢየሩሳሌም መጥፋት እንዳለባት ብዙ ነገሮችን አንብቧል—ነዋሪዎችዋ ብዙዎቹ በሰይፍ ይጠፋሉ እንዲሁም አብዛኞቹ ወደ ባቢሎን በምርኮ ᶮይወሰዳሉ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ብዙ ታላቅና አስደናቂ ነገሮችን ባነበበና ባየ ጊዜ ለጌታ ብዙ ነገሮችን በመገረም ተናገረ፣ እነኚህም አቤቱ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ስራዎችህ ታላቅና አስደናቂ ናቸው! ዙፋንህ ከፍ ብሎ በሰማይ ነው። እንዲሁም ኃይልህ፣ ቸርነትህና ምህረትህ በምድር ባሉ ፍጡራን ሁሉ ላይ ነው፤ ምክንያቱም አንተ መሀሪ በመሆንህ ወደ አንተ ᵐየሚመጡት እንዲጠፉ አትፈቅድምና! የመሳሰሉትን ነበር።

፲፭ እናም አምላኩን ያመሰግን የነበረበት የአባቴ አነጋገር እንዲህም ነበር፤ ባያቸው ነገሮች፣ አዎን፣ ጌታ ለእርሱ ባሳየውም፣ ነፍሱ ተደስታለች፣ ልቡም በሙሉ በመንፈስ ተሞልታለች።

፲፮ እናም አሁን እኔ ነፊ አባቴ የፃፋቸውን ነገሮች በሙሉ አልመዘግብም፣ በራዕይና በህልም ያያቸውን ብዙ ነገሮች ፅፏልና፤ እና ይኸውም እኔ አጠቃልዬ የማልመዘግባቸውን ᵐየተነበያቸውንና ለልጆቹ የተናገራቸውን ብዙ ነገሮች ደግሞ ፅፏል።

፲፯ ነገር ግን እኔ በዘመኔ የፈፀምኳቸውን እመዘግባለሁ። እነሆም የአባቴን ᵐታሪክ በእጄ በሰራኋቸው ሰሌዳዎች ላይ ᶮአሳጥሬ ፅፌአለሁ፤ ስለዚህ የአባቴን ታሪክ ካሳጠርኩ በኋላ የራሴን የሕይወት ታሪክ እፅፋለሁ።

፲፰ ስለዚህ ጌታ ብዙ ድንቅ ነገሮችን፣ አዎን፣ ስለኢየሩሳሌም ᵐመጥፋትን ስለሚመለከት፣ ለአባቴ ሌሂ ካሳየው በኋላ፣ እነሆ በህዝቡ መካከል ሄደ እናም ስላየውና

፤ ሀ ዘፀአ. ፲፫፡ ፳፭፤
ሐሌ. ፭፡ ፳፬፣ ፵፫፤
ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፲፪፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፯።
፭ ሀ ዳን. ፲፡ ፰፤
፩ ነፊ ፲፯፡ ፵፯፤
ሙሴ ፩፡ ፱–፲፣
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፳።
፰ ሀ ፩ ነፊ ፭፡ ፱።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ሕዝ. ፩፡ ፩፤
የሐዋ. ፯፡ ፶፭–፶፮፤
፩ ነፊ ፲፩፡ ፲፱፤
ሔሌ. ፭፡ ፵፭–፵፱፤
ት. እና ቃ. የ፴፯፡ ፩።
፱ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፯–፲፯።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፲፩ ሀ ሕዝ. ፪፡ ፱።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፯፡ ፲፭።
፲፫ ሀ ፪ ነገሥ. ፳፫፡ ፳፯፤ ፳፬፡ ፪፤
ኤር. ፲፫፡ ፲፫–፲፱፤
፪ ነፊ ፩፡ ፡።
ለ ፪ ነገሥ. ፳፬፡ ፲፰–፳፣
፪ ዜና ፴፮፡ ፲፱።
ሐ ፪ ነገሥ. ፳፡ ፲፯–፲፰፤
፪ ነፊ ፳፭፡ ፲፡
ኦምኒ ፩፡ ፲፭።
፲፡ ሀ አልማ ፭፡ ፴፫–፴፯፤
፫ ነፊ ፱፡ ፲፡።
፲፣ ሀ ፩ ነፊ ፣፡ ፩።
፲፣ ሀ ፩ ነፊ ፣፡ ፩–፫፣ ፲፱፡ ፩–፣፤
፪ ነፊ ፭፡ ፳፱–፴፫፣
ት. እና ቃ. ፲፡ ፴፰–፵፣
ለ ፩ ነፊ ፱፡ ፪–፭።
፲፰ ሀ ፪ ነፊ ፳፭፡ ፱–፲፡
ት. እና ቃ. ፭፡ ፳።

ስለሰማቸው ነገሮች ለእነርሱ ^መተንበይና ማወጅ እንደጀመረ እናንተ እንድታውቁት እፈልጋለሁ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በእነርሱ ላይ በመሰ ከራቸው ነገሮች ምክንያት አይሁዶች ᵐተሳ ለቁበት፣ ምክንያቱም እርሱ በእውነት ስለ ክፋታቸውና ስለእርኩሰታቸው መስክ ሯል፤ እንዲሁም ያያቸውና የሰማቸው ነገሮች፣ ደግሞም በመፅሐፉ ውስጥ ያነበ ባቸው ነገሮች በግልጽ ^ስለመሲሕ መም ጣትና ደግሞም ስለአለም ቤዛነት እንደሚ ገልጹ መሰከረ።

፳ እና አይሁዶች ይህንን በሰሙ ጊዜ በእ ርሱ ተቆጡ፤ አዎን እንዲሁም ልክ ᵐእን ዳሳደዱአቸውና እንደወገሩአቸው፣ እንደ ገደሉዋቸውም የጥንት ጊዜ ነቢያት፤ ይገ ድሉትም ዘንድ የእርሱንም ሕይወት ደግሞ ሊወስዱ ፈለጉ። ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ኔፊ የጌታ ^ምህረቶች ርህራሄ በእምነታቸው ምክንያት ለመዳን ሀይል እስኪኖራቸው ድረስ ሀያል እንዲሆኑ በመረጣቸው ላይ ሁሉ እንደሆነ አሳያችኋለሁ።

ምዕራፍ ፪

ሌሂ ቤተሰቡን በቀይ ባሕር በኩል ወደ ምድረበዳ ወሰደ — ንብረታቸውንም ተዉ — ሌሂ መስዋዕትን ለጌታ አቀረበ፣ እናም ወንዶች ልጆቹን ትዕዛዛትን እንዲ ጠብቁ አስተማረ — ላማን እና ልሙኤል በአባታቸው ላይ አጉረመረሙ — ኔፊ ታዛ ዥና በእምነትም የሚፀልይ ነው፣ ጌታም እርሱን ተናገረው እና በወንድሞቹም ላይ እንዲገዛ ተመረጠ። ፯፲፫ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እናም እንዲህ ሆነ፣ ጌታ ለአባቴ ተናገረው፣ አዎን በህልሙም እንኳን እን ዲህ አለው፥ ሌሂ፣ ባደረግሃቸው ነገሮች ምክንያት የተባረክህ ነህ፣ እንዲሁም አንተ ታማኝ በመሆንህና ለዚህ ሕዝብ ያዘዝኩህን ነገሮች በመግለፅህ ምክንያት እነሆም ሕይ ወትህን ᵐሊያጠፉ ይፈልጋሉ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ጌታ አባቴን ᵐበህ ልሙም ጭምር ቤተሰቡን ይዞ ወደ ምድ ረበዳ ^እንዲሄድ ሐአዘዘው።

፫ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ ለጌታ ቃል ᵐታዛዥ ነበር፣ ስለዚህ ጌታ እንዳዘዘው አደረገ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ምድረበዳ ሄደ። እናም ቤቱን፣ የወረሰውን መሬት፣ ወርቁ ንና ብሩን፣ ውድና የከበሩ ነገሮቹን ተወ፣ እንዲሁም ከቤተሰቡ፣ ከስንቆችና፣ ከድን ኳኖች በስተቀር ከእርሱ ጋር ምንም ሳይወ ስድ ወደ ምድረበዳ ᵐሄደ።

፭ እናም በቀይ ባሕር ወዳለው ዳርቻ መጣ፤ ᵐለቀይ ባሕር ቅርብ በሆነው ዳርቻ በምድረበዳ ውስጥ ተጓዘ፣ እናም በምድ ረበዳ ውስጥ እናቴን ሳርያንና ታላቅ ወን ድሞቹ የነበሩት ^ላማን፣ ልሙኤልና ሳምን ያካተተውን ቤተሰቦቹን ይዞ ወደ ምድረበዳ ተጓዘ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ለሶስት ቀን በም ድረበዳ ከተጓዘ በኋላ፣ የወንዝ ውሃ ባለበት ᵐሸለቆ አጠገብ ድንኳኑን ተከለ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ᵐየድንጋይ ^መሠዊ ያን ሠራ፣ ለጌታም መስዋዕትን አደረገ፣ እናም ለጌታ ለአምላካችን ^ምስጋና አቀ ረበ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ የወንዙንም ስም

፲፰ ^ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
፲፱ ᵐ ፪ ዜና ፴፮፡፲፭–፲፮፤ ኤር. ፳፭፡፱፣ ፤ ፩ ኔፊ ፪፡፲፫፣ ፯፡፲፬። ^ ቅ.መ.መ. መሲህ።
፳ ᵐ ሐሌ. ፲፫፡፳፬–፳፮። ^ አልማ ፴፬፡፴፤ ፡ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፭። ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፳፪ ᵐ ፩ ᵐ ፩ ኔፊ ፯፡፲፬። ^ ቅ.መ.መ. ህልም። ^ ዘፍጥ. ፲፪፡፩፣ ፪ ኔፊ ፲፡፳፣ ኤተር ፩፡፴፪፣ አብር. ፪፡፣ ፣ ሐ ፩ ኔፊ ፳፡፲፣ ፣ ፲፯፡፴፬። ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፴ ᵐ ᵐ ፩ ኔፊ ፣ ፡ ፣ ፲፱፡፳۔
፳ ᵐ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፩۔ ^ ቅ.መ.መ. ላማን።
፲ ᵐ ᵐ ፩ ኔፊ ፱፡ ፩۔
፲ ᵐ ዘፀአ. ፳፡፳፳፣ ዘዳግ. ፳፲፡ ፩–፲۔ ^ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፩–፳፣ ዘፀአ. ፳፱፡ ፱፣ አብር. ፪፡፣ ፣ ሐ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።

ላማን ብሎ ጠራው፣ እና ወደ ቀይ ባሕር ይፈስ ነበር፤ ሸለቆውም በወንዙ ዳርቻ አጠ ገብ ጫፍ ላይ ነበር።

፱ እናም አባቴ የወንዙ ውሃ ወደ ቀይ ባሕር ምንጭ መፍሰሱን ባየ ጊዜ ለላማን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡ አንተ ልክ እንደዚህ ወንዝ የሁሉም ፅድቅ ምንጭ ወደሆነው ያለማቋ ረጥ እንድትፈስ ዘንድ ምን ያህል እመኛለሁ!

፣ እናም ለልሙኤልም ተናገረው፡ አንተ ልክ እንደዚህ እንደሸለቆ የጌታን ትዕዛዝ በመጠበቅ ጠንካራ፣ ፅኑና፣ የማትነቃነቅ እንድትሆን እመኛለሁ!

፤ በላማንና በልሙኤል አንገተ ደንዳ ናነት ምክንያት እርሱ ይህንን ተናግሯል፤ እነሆም እነርሱ [a]በአባታቸው ላይ በብዙ ነገ ሮች [b]አጉረምርመዋል፣ ምክንያቱም እርሱ [c]ባለራዕይ ሰው ስለነበረ፣ እና የውርስ ምድ ራቸውንና ወርቃቸውንና፣ ብራቸውንና፣ የከበሩ ነገሮቻቸውን ትተው በምድረበዳ እንዲጠፉ ከኢየሩሳሌም ምድር እንዲወጡ ስላደረገ ነበር። እናም እርሱ ይህን ያደረገው በከንቱ የልቡ ሀሳብ ምክንያት ነው አሉ።

፥ እናም ላማንና ልሙኤል ታላቅ በመ ሆናቸው በአባታቸው ላይ አጉረመረሙ። እና ይህንን ያጉረመረሙት የዚያን የፈጠ ራቸውን አምላክ ሥራዎች [d]ስላላወቁ ነበር።

፦ እንደ ነቢያት ቃል ታላቋ ከተማ ኢየ ሩሳሌም [e]እንደምትጠፋ አላመኑም ነበር። እናም እነርሱ ልክ በኢየሩሳሌም የአባቴን ሕይወት ለማጥፋት እንደፈለጉት አይሁ ዶች ነበሩ።

፧ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ በልሙኤል ሸለቆ ውስጥ በመንፈስ በመሞላቱ ምክን ያት ሰውነታቸው [f]እስኪንቀጠቀጥ ድረስ [g]በኃይል ተናገራቸው። እናም እርሱን ለማ ናገር ድፍረት እስኪያጡ ድረስ ዝም አሰኛ ቸው፤ ስለዚህ እርሱ እንዳዘዛቸው አደረጉ።

፨ እናም አባቴ በድንኳን ውስጥ ኖረ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ነፊ፣ እጅግ ወጣት ነበርኩ፣ ሆኖም በአቋሜ ትልቅ ነበ ርኩ፣ እናም የእግዚአብሔርን [h]ሚስጥሮች የማወቅ ፍላጎቴ ትልቅ ነበር፣ ስለዚህ፣ ወደ ጌታ ጮህኩ፤ እናም እነሆ እርሱ [i]ጎበኘኝ፣ እኔም [j]አባቴ የተናገራቸውን ቃላት ሁሉ [k]እንዳምን ዘንድ ልቤንም [l]አባባው፤ ስለ ዚህ፣ እኔ እንደ ወንድሞቼ በእርሱ ላይ አላ መፅኩም።

፪ እናም ጌታም በቅዱስ መንፈሱ አማ ካኝነት ለእኔ ስለገለፃቸው ነገሮች እንዲያ ውቅ በማድረግ ሳምን አነጋገርኩት። እናም እንዲህ ሆነ በእኔ ቃላት አመነ።

፫ ነገር ግን እነሆ ላማንና ልሙኤል የእ ኔን ቃላት አላዳመጡም፤ እናም በልባቸው ጠጣርነት የተነሳ [m]አዝኜ ለእነርሱ ወደ ጌታ ጮህኩ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፡ [n]በእምነትህ የተነሳ በትሁት ልብህ አጥብቀህ ፈልገኸኛልና አንተ ነፊ የተባረክህ ነህ።

፭ እና ትዕዛዛቴን እስከጠበቅህ ድረስ [o]ትበለፅጋለህ፣ ወደ [p]ቃል ኪዳንም ምድር፣ አዎን እንዲያውም እኔ ወደ አዘጋጀሁልህ ምድር፣ አዎን ከሌሎች ምድር ሁሉ በላይ ወደተመረጠች ምድር ትመራለህ።

፮ እናም ወንድሞችህ በአንተ ላይ እስከ ዐመፁ ድረስ ከጌታ ፊት [q]ይለያሉ።

፤ ፩ *ሀ* ምሳ. ፰፡፳።
ለ ፩ ነፊ ፤ ፲ ፡ ፲ ፣ ፲ ፣ ፲ ፣

፳፪ እናም አንተ ትዕዛዛቴን እስከጠበቅህ ድረስ በወንድሞችህ ላይ ᵐአለቃና መም ህር ትሆናለህ።

፳፫ እነሆ እነርሱ በእኔ ላይ በሚያምፁ በት ጊዜ በከባድ እርግማን ᵐእረግማቸዋ ለሁ፣ እናም እነርሱ በእኔም ላይ ካላመፁ በቀር፣ በዘሮችህ ላይ ምንም ኃይል አይ ኖራቸውም።

፳፬ እናም እነርሱ በእኔ ላይ የሚያምፁም ከሆነ፣ ለማስታወስ ᵐእንዲያነሳሷቸው፣ ለዘርህ የሚያውኩ ᵃጅራፍ ይሆናሉ።

ምዕራፍ ፫

የሌሂ ወንዶች ልጆች የነሀስ ሰሌዳዎቹን ለማ ግኘት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ— ላባን ሰሌዳዎቹን አልሰጥም አለ— ኔፊ ወንድ ሞቹን ገሰፀ እና አበረታታ— ላባን ንብረ ታቸውን ቀማቸው እናም ሊገድላቸውም ሞከረ— ላማንና ልሙኤል ኔፊንና ሳምን መቷቸው፣ እናም መልአክ ገሰፃቸው። ፭፲–፳፬፲፯፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እና እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊ፣ ከጌታ ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ ወደ አባቴ ድንኳን ተመ ለስኩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ እነሆ ᵐሕልምን አልሜአለሁ፣ በእርሱም ጌታ አንተና ወንድሞችህ ወደ ኢየሩሳሌም እንድትመለሱ አዞኛል።

፫ እነሆም ላባን የአይሁዶችን መዝገብና ደግሞም የቅድመ አባቶቼን ᵐየትውልድ ሐረግ መጽሐፍ አለው፣ እናም እነርሱ በነ ሐስ ሰሌዳ ላይ የተቀረፁ ናቸው።

፬ ስለዚህ አንተና ወንድሞችህ ወደ ላባን ቤት ሄዳችሁ መዝገቦቹን ፈልጋችሁ ወደ ዚህ ወደ ምድረበዳ እንድታመጡዋቸው ሲል ጌታ አዞኛል።

፭ እናም አሁን እነሆ ወንድሞችህ ከእነ ርሱ የፈለግሁትን ነገር ከባድ ነው በማለት አጉረመረሙ፣ ነገር ግን እነሆ ይህን ከእነ ርሱ የፈለኩት እኔ አይደለሁም፣ ነገር ግን ይህ የጌታ ትዕዛዝ ነው።

፮ ስለዚህ ሂድ ልጄ፣ አንተ ᵐስላላጉረመ ረምክ በጌታ የተደገፍክ ትሆናለህ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊ፣ አባቴን እንዲህ አልኩት፥ ᵐእሄዳለሁ፣ ጌታ ያዘዘኝ ንም ነገሮች አደርጋለሁ፣ ምክንያቱም ጌታ ያዘዛቸውን ᵃትዕዛዛት የሚሟሉበትን መን ገድ ᵇካላዘጋጀ በቀር ለሰው ልጆች ትዕዛዛ ትን እንደማይሰጥ አውቃለሁና።

፰ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ እነዚህን ቃላት በሰማ ጊዜ እጅግ ተደሰተ፣ እኔም በጌታ መባረኬን አወቋልና።

፱ እና እኔ፣ ኔፊና ወንድሞቼ ድንኳናች ንን ይዘን ወደ ኢየሩሳሌም ምድር ለመሄድ በምድረበዳ ጉዞአችንን ጀመርን።

፲ እናም እንዲህ ሆነ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ምድር በሄድን ጊዜ እኔና ወንድሞቼ እርስ በእርስ ተመካከርን።

፲፩ እናም ማን ወደ ላባን ቤት መሄድ እን ዳለበት ᵐዕጣ ተጣጣልን። እናም እንዲህ ሆነ ዕጣው በላማን ላይ ወደቀ፤ እናም ላማን ወደ ላባን ቤት ሄደ፣ በቤቱም ተቀምጦ ሳለ እና ገረው።

፲፪ እና ላባንን በነሐስ ሰሌዳዎች ላይ የተ ቀረፁትንና የአባቴን ᵐትውልድ ሐረግ የያ ዙትን መዝገቦች ጠየቀው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ላባን ተናደደ፣ እናም ከፊቱም አባረረው፣ እና መዝገቦ ቹን እንዲወስድ አላደረገውም፣ ስለሆነም

፳፪ ᵐ ዘፍጥ. ፴፯፡፳–፲፩፤
፩ ኔፊ ፫፡፳፱።
፳፫ ᵐ ዘዳግ. ፲፩፡፳፰፤
፩ ኔፊ ፲፪፡፳፪–፳፫፤
ት. እና ቃ. ፵፩፡፩።
፳፬ ᵐ ፪ ኔፊ ፭፡፳፭።
ᵃ ኢያ. ፳፫፡፲፫፤
መሳ. ፪፡፲፪–፳፫።
፫ ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. ህልም።
፫ ᵐ ᵐ ፩ ኔፊ ፭፡፲፬።
፯ ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን
መሪዎችን መደገፍ።
፯ ᵐ ᵐ ፩ ሳሙ. ፲፭፡፴፪፤
፩ ነገሥ. ፲፭፡፲፩–፲፭።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ፤
እምነት፣ ማመን።
ᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
ᵇ ዘፍጥ. ፲፰፡፲፬፤
ፊልጵ. ፬፡፲፫፤
፩ ኔፊ ፲፯፡፫፤ ፶፤
ት. እና ቃ. ፭፡፴፬።
፲፩ ᵐ ነህ. ፲፡፴፬፤
የሐዋ. ፩፡፳፮።
፲፪ ᵐ ᵐ ፩ ኔፊ ፫፡፫፤ ፭፡፲፬።

አለው፡ እነሆ አንተ ወንበዴ ነህ እናም እገ
ድልሀለሁ።

፲፬ ነገር ግን ላማን ከእርሱ ፊት ሸሸ፣
ላባን ያደረገውንም ነገር ለእኛ ነገረን።
እኛም እጅግ አዘንን እና ወንድሞቼ ወደ
አባቴ ዘንድ ወደ ምድረበዳው ለመመለስ
ተዘጋጁ።

፲፭ ነገር ግን እነሆ እኔ ለእነርሱ እንዲህ
አልኳቸው፡ ጌታ ህያው እንደሆነ፣ እኛም
እስካለን ድረስ ጌታ ያዘዘንን ሳናከናውን
ወደአባታችን ወደ ምድረበዳ አንመለስም።

፲፮ ስለዚህ የጌታን ትዕዛዝ በመጠበቅ
ታማኝ እንሁን፣ ስለዚህ ወደ አባታችን
ᵐርስት ምድር እንውረድ፣ እነሆ ወርቅን፣
ብርንና ሁሉን ሀብቶችን ትቷልና። እናም
ይህን ሁሉ ያደረገው በጌታ ^ትዕዛዛት ምክ
ንያት ነው።

፲፯ ኢየሩሳሌም በህዝቡ ክፋት ምክንያት
ᵐመጥፋት እንዳለባት ያውቅ ነበርና።

፲፰ እነሆም እነርሱ የነቢያትን ቃላት
ᵐአልተቀበሉም፣ ስለዚህ አባቴ ከምድሪቱ
እንዲወጣ ^ከታዘዘ በኋላ በዚያ ሀገር ቢቆይ
ኖሮ እነሆ እርሱም ደግሞ ይጠፋ ነበር። ስለ
ዚህ፣ ከምድሪቷ መውጣት ነበረበት።

፲፱ እናም የአባቶቻችንን ቋንቋ ለልጆቻ
ችን እናቆይ ዘንድ እነዚህን ᵐመዝገቦች ማግ
ኘታችን የእግዚአብሔር ጥበብ ነው

፳ እናም ደግሞ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ
እስከ አሁን ጊዜ ድረስ በመንፈስና በእግዚ
አብሔር ኃይል ተሰጥቷቸው በቅዱሳን ነቢ
ያት የተነገሩትን ቃላት ሁሉ ᵐእንድንጠብ
ቅላቸው ዘንድ ነው።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ አይነት አነጋ
ገር ነበር የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጠበቅ
ታማኝ እንዲሆኑ አሳመንኳቸው።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ርስታችን
ምድር ወረድንና ᵐወርቃችንንና፣ ብራች
ንን፣ እንዲሁም የከበሩ ነገሮቻችንን በአ
ንድነት ሰበሰብን።

፳፫ እና እነዚህን ነገሮች ከሰበሰብን በኋላ
ወደ ላባን ቤት ተመልሰን ሄድን።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ላባን ቤት ገባንና
ᵐበነህስ ሰሌዳዎች ላይ የተቀረፁትን መዛ
ግብት እንዲሰጠን ለዚህም ወርቃችንን፣
ብራችንንና፣ ሁሉንም የከበሩ ነገሮቻችንን
እንደምንሰጠው ነገርነው።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ላባን ንብረታችን
እጅግ ታላቅ እንደሆነ ባየ ጊዜ ᵐተመኘው፣
በዚህም ምክንያት ወደ ውጪ አባረረንና
ንብረታችንን ይወስድ ዘንድ አገልጋዮቹን
እንዲገድሉን ላከብን።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ እኛ ከላባን አገል
ጋዮች ፊት ሸሽን ንብረታችንን ከኋላችን
ትተን እንድንሄድ ተገደድን፣ እና ይህም
በላባን እጆች ውስጥ ወደቀ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ምድረበዳ
ሸሽን፣ የላባን አገልጋዮች ሊይዙን አልቻ
ሉም፣ እናም እራሳችንን በአለት ዋሻ ውስጥ
ደበቅን።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማን በእኔም ሆነ
በአባቴ ተናደደ፤ ልሙኤልም እንደዛው
የላማንን ቃላት አድምጦአልና። ስለዚህ
ላማንና ልሙኤልም እኛን ታናናሽ ወንድ
ሞቻቸውን ብዙ ᵐአስፈሪ ቃላት ተናገሩን፣
በበትርም መቱን።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ በበትር
በመቱን ጊዜ፣ እነሆም የጌታ ᵐመልአክ
መጥቶ በፊታቸው ቆመ፣ እንዲህም ብሎ
ተናገራቸው፡ ለምን ታናሽ ወንድማችሁን
በበትር ትመታላችሁ? ጌታ እርሱን በእና
ንተ ላይ ^ገዥ ይሆን ዘንድ እንደመረጠውና
ይህም በአመፃችሁ ምክንያት እንደሆነ አታ

፲፯ ᵐ ፩ ነፌ ፪፡፱።
ለ ፩ ነፌ ፪፡፪፣ ፱፡ ፴፩።
፲፯ ᵐ ፪ ዘና ፴፯፡፲፯–፳፣
ኤር. ፴፱፡ ፩–፱፣
፩ ነፌ ፩፡ ፲፫።
፲፰ ᵐ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ፩ ነፌ ፲፯፡ ፳።

፲፱ ᵐ ኦምኒ ፩፡ ፲፯፣
ሞዛያ ፩፡ ፪–፯።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት—የሚጠበቁ ቅዱስ
መጻፍህት።
፳፪ ᵐ ፩ ነፌ ፪፡ ፱።
፳፭ ᵐ ፩ ነፌ ፫፡ ፫።

፳፭ ᵐ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፳፰ ᵐ ፩ ነፌ ፲፯፡ ፲፯–፲፰።
፳፱ ᵐ ፩ ነፌ ፱፡ ፫፣ ፯፡ ፲።
ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ፩ ነፌ ፪፡ ፳፪።

ውቁምን? እነሆ እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ትመለሳላችሁ፣ እናም ጌታ ላባንን አሳልፎ በእጃችሁ ላይ ይጥለዋል።

፴ እናም [ሀ]መልአኩ ለእኛ ከተናገረ በኋላ ሄደ።

፴፩ እናም መልአኩም ከሄደ በኋላ ላማንና ልሙኤል እንዲህ ሲሉ [ለ]ማጉረምረም ጀመሩ፣ ጌታ ላባንን አሳልፎ በእጃችን ይጥለው ዘንድ እንዴት ይቻላል? እነሆ እርሱ ሀይለኛ ነው፣ እናም አምሳዎችን ሰዎችን ሊያዝ ይችላል፣ አዎን፣ አምሳዎችንም መግደል ይችላል፣ እኛንስ መግደል እንዴት አይቻለውም?

ምዕራፍ ፴

ኔፊ በጌታ ትዕዛዝ ላባንን ገደለ፣ እናም የነሀስ ሰሌዳዎቹን በብልሀት አገኘ— ዞራም ወደ ምድረበዳው በመሄድ ከሌሂ ቤተሰብ ጋር መደባለቅን መረጠ። ከ፯፪–፳፱ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ለወንድሞቼ እንዲህ ስል ተናገርኩ፥ ተመልሰን ወደ ኢየሩሳሌም እንሂድ፣ እናም የጌታን ትዕዛዝ በመጠበቅ [ሁ]ታማኝ እንሁን፣ እነሆም እርሱ ከምድር ላይ ካለው ሁሉ [ሂ]ኃያል ነው፣ ከላባንና ከአምሳዎቹ ሰዎች፣ አዎን፣ ወይንም ከአስር ሺዎቹ እንኳ ለምን የበለጠ ኃያል አይሆንምን?

፪ ስለዚህ እንሂድ፣ ልክ እንደ [ሃ]ሙሴ [ሄ]ጠንካሮች እንሁን፣ እነሆ እርሱ በእውነት [ሆ]የቀይ ባሕርን ውሃ ተናገረው፣ ውሃውም ወዲያና ወዲህ ተከፈለ፣ አባቶቻችንም በውስጡ ተሻግረው ከግዛት በደረቅ ምድር ወጡ፣ እናም የፈርዖን ሰራዊት ተከተሉትና፣ በቀይ ባሕር ውሃ ውስጥ ሰጠሙ።

፫ አሁን እነሆ ይህ እውነት እንደሆነ አውቃችኋል፣ እናም ደግሞ [ሀ]መልአክ እንደተናገራችሁ ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ፣ ልትጠራጠሩ ትችላላችሁን? እንሂድ ጌታ እኛን እንደአባቶቻችን ሊያድነን ላባንን እንደግ ብፃውያን ሊያጠፋ ይቻለዋል።

፬ አሁን እነዚህን ቃላት በተናገርኩ ጊዜ፣ እንደተቆጡና አሁንም ማጉረምረማቸውን እንደቀጠሉ ነበር፣ ይሁን እንጂ እስከ ኢየሩሳሌም ግንብ ውጪ እስከደረስን ድረስ ተከተሉኝ።

፭ እና ይህም በምሽት ነበር፣ እራሳቸውን ከግንቡ ውጪ እንዲደብቁ አደረኳቸው። እነርሱም ራሳቸውን ከደበቁ በኋላ እኔ ኔፊ ወደ ከተማው ሾለኩና፣ ወደ ላባን ቤት ሄድኩ።

፮ እናም ማድረግ ያለብኝን ነገሮች ቀድሜ [ሀ]ሳላውቅ በመንፈስ [ለ]ተመራሁ።

፯ ይሁን እንጂ፣ እኔም ወደፊት ሄድኩ፣ እናም ወደ ላባን ቤት እየቀረብኩ ስሄድ አንድ ሰው አየሁ፣ እና የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ ስለነበረ ከፊቴ በመሬት ላይ ወድቆ ነበር።

፰ እና ወደ እርሱ በመጣሁ ጊዜ ይህም ላባን እንደሆነ አወቅኩኝ።

፱ የእርሱን [ሀ]ጎራዴ አየሁ፣ ከአፎቱም መዘዝኩት፣ የጎራዴውም መያዣ የተሰራው ከንፁህ ወርቅ ነበር፣ አሰራሩም እጅግ ያማረ ነበር፣ እናም ስለቱ በጣም ከከበረ ብረት መሆኑን አየሁ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ላባንን እገድለው ዘንድ በመንፈስ [ሀ]ተገፋፋሁ፣ ነገር ግን በልቤ፣ በማንኛውም ጊዜ የሰው ደም አፍስሼ አላውቅም አልኩ። እና እኔ ተሸማቀቅሁና፣ እርሱን ላለመግደል ፈለግሁ።

፲፩ እናም መንፈስ በድጋሚ እንዲህ

፴ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፴፰።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማጉረምረም።
፴፪ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት፣ እምነት፣ ማመን።
ለ ፩ ኔፊ ፯፡ ፲፩–፲፪።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሙሴ።
ለ ዘዳግ. ፲፩፡ ፳።
ሐ ዘፀአ. ፲፡ ፳፩፣ ፳፭፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፳፯፣ ሞዛያ ፯፡ ፲፱።
፴፬ ሀ ፩ ኔፊ ፫፡ ፳፱–፴፩፣ ፯፡ ፲።
፴፭ ሀ ዕብ. ፲፩፡ ፳።
ለ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፣ መንፈስ ቅዱስ።
፴፮ ሀ ፴፫ ኔፊ ፭፡ ፲፡ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፩።
፲ ሀ አልማ ፲፡ ፲፩።

አለኝ፥ እነሆ ᐸጌታ እርሱን በእጆችህ አሳ
ልፎ ሰጥቶሀል። አዎን፣ እኔም ደግሞ ሕይ
ወቴን ሊወስድ እንደፈለገ አውቃለሁ፤
አዎን የጌታን ትዕዛዝ አያዳምጥም፤ እናም
ንብረታችንንም ደግሞ ᐸወስዷል።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ መንፈስ ለእኔ እን
ደገና እንዲህ አለኝ፥ ግደለው፣ ጌታ በእ
ጆችህ አሳልፎ ሰጥቶሀልና፤
፲፬ እነሆ ጌታ ጻድቃዊ ዓላማውን ያሟላ
ዘንድ ᐸክፉዎችን ᐸይገድላል። አንድ አገር
እምነት በማጣት ከሚመነምንና ከሚሞት
አንድ ሰው ቢሞት ᐸይሻላል።
፲፭ እናም አሁን፣ እኔ፣ ነፌ፣ እነዚ
ህን ቃላት ስሰማ ጌታ በምድረበዳ እንዲህ
ብሎ የተናገረኝን ቃላት አስታወስኩ፥ ዘርህ
ᐸትዕዛዛቴን ᐸእስከጠበቁ ድረስ ᐸበቃልኪ
ዳኑ ምድር ላይ ᐸይበለፅጋሉ።
፲፮ አዎን ሕጉ ከሌላቸው በስተቀር በሙሴ
ህግ መሰረት የጌታን ትዕዛዛት ሊጠብቁ እን
ደማይችሉ ደግሞ አሰብኩ።
፲፯ እናም እኔ ደግሞ ᐸህጉ በነህስ ሰሌዳው
ላይ እንደተቀረፀም አውቃለሁ።
፲፰ እናም እንደገና ጌታ በትዕዛዙ መሰ
ረት መዝገቦቹን አገኝ ዘንድ ላባንን በእጄ
አሳልፎ የሰጠኝ ለዚህ ምክንያት መሆኑን
አወቅሁ።
፲፱ ስለዚህ ለመንፈስም ድምፅ ታዘዝኩ፣
እና ላባንን የራሱን ፀጉር ይዤ በራሱ ᐸጎራዴ
አንገቱን ቆረጥኩት።
፲፱ እናም በራሱ ጎራዴ አንገቱን ከቆረ
ጥኩ በኋላ፣ የላባንን ልብስ ወስጄ ለበስ
ኩት፣ አዎን፣ አንድ ነገር ሳይቀር፣ እናም
የእርሱን ጥሩር በወገቤ ላይ ታጠቅሁት።
፳ ይህን ካደረግሁ በኋላ ወደ ላባን ግምጃ
ቤት ተጓዝኩ። ወደ ላባን ግምጃ ቤት ስሄድ፣
እነሆም የግምጃ ቤቱን ቁልፍ የያዘውን የላ
ባንን ᐸአገልጋይ አየሁ። እናም በላባን ድምፅ
ወደ ግምጃ ቤቱ ከእኔ ጋር እንዲሄድ አዘ
ዝኩት።
፳፩ እናም እርሱ የላባንን ልብስና ጎራ
ዴውን በወገቤ መታጠቁን በማየቱ የእርሱ
አለቃ መሰልኩት።
፳፪ እናም እርሱ አለቃው ላባን ሌሊቱን
ከአይሁድ ሽማግሌዎች ጋር መሆኑን ስለ
ሚያውቅ፣ ስለእነርሱ አነጋገረኝ።
፳፫ እናም እኔ ልክ ላባን እንደሆንኩኝ
አስመስዬ ከእርሱ ጋር ተነጋገርኩ።
፳፬ እኔ ከግንቡ ውጭ ወደ ሚገኙት ታላ
ላቅ ወንድሞቼ ᐸበነህስ ሰሌዳ ላይ የተቀረ
ፁትን ተሸክሜ መውሰድ እንዳለብኝ ተና
ገርኩት።
፳፭ እናም እኔ ደግሞ ሊከተለኝ እንደሚ
ገባው አዘዝኩት።
፳፮ እርሱ የተናገርኩት ስለቤተክርስቲ
ያን ወንድሞች መሰለው፣ እና እውነት እኔ
የገደልኩትን ላባንን መሰልኩት፣ ስለዚህም
ተከተለኝ።
፳፯ እናም እርሱ ከግንቡ ውጭ ወዳሉት
ወንድሞቼ ስጓዝ ብዙ ጊዜ አይሁዶች ሽማ
ግሌዎችን በተመለከተ ተናገረኝ።
፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማን ባየኝ ጊዜ
እጅግ ፈራ፣ እንዲሁም ልሙኤልና
ሳምም። እናም እነርሱም ላባን ነው ብለው
ስላሰቡ እኔንም የገደለኝና የእነርሱንም ህይ
ወት የሚያጠፋ ስለመሰላቸው ከፊቴ ሸሹ።
፳፱ እናም እንዲህ ሆነ እኔም ጠራኋቸው፣
እናም ሰሙኝ፤ ስለዚህ ከፊቴ መሸሻቸውን
አቆሙ።
፴ እናም እንዲህ ሆነ የላባን አገልጋይ
ወንድሞቼን ሲያይ መንቀጥቀጥ ጀመ
ረና፣ ከእኔ ሸሽቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሊመ
ለስ ፈለገ።

፲፩ ሀ ፩ ሳሙ. ፲፯፡ ፴፩–፴፱።
ለ ፩ ነፌ ፫፡ ፳፯።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ለ ፩ ነፌ ፲፯፡ ፴፫–፴፰፤
ት. እና ቃ. ፣፳፡ ፴፩–፴፪።
ሐ አልማ ፴፡ ፴፯።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
ለ ኦምኒ ፩፡ ፯፤
ሞዛያ ፪፡ ፳፪፤
ኤተር ፪፡ ፯–፲፪።
ሐ ፩ ነፌ ፪፡ ፳።
መ ፩ ነፌ ፲፯፡ ፲፫–፲፰፤
ያዕቆ. ፪፡ ፲፪።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፲፡ ሀ ፩ ሳሙ. ፲፯፡ ፶፩።
ሀ ፪ ነፌ ፩፡ ፴።
፳፩ ሀ ፩ ነፌ ፫፡ ፲፪፤ ፲፱–፳፩፤
፭፡ ፣–፳፪።

፴፩ እናም አሁን እኔ፣ ኔፊ፣ በአቋሜ ግዙፍ በመሆኔና ከጌታም Ꮏጥንካሬን በማግ ኘቴ የላባንን አገልጋይ እንዳይሸሽ ያዝኩት።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ ህያው እን ደሆነ እኔም እስካለሁ ድረስ የእኔን ቃላት ከሰማ እንዲሁም ቃላታችንን ለመስማት ፈቃደኛ ከሆነ ሕይወቱን እኛ እንደምናተ ርፍለት ተናገርኩት።

፴፫ እናም እርሱ ከእኛ ጋር ወደ ምድ ረበዳ የሚሄድ ከሆነ መፍራት እንደሌለበት ልክ እንደ እኛ ነፃ ሰው እንደሚሆን Ꮏበመ ሃላ ጭምር ተናገርኩት።

፴፬ እናም እኔ እንዲህ ብዬ ተናገርኩት፡ በእርግጥ ጌታ ይህን እንድናደርግ Ꮏአዞናል፣ እናም የጌታንስ ትዕዛዛት በመጠበቅ መት ጋት የለብንምን? ስለዚህ አንተ ወደ ምድ ረበዳ ወደ አባቴ የምትወርድ ከሆነ ከእኛ ጋር ትኖራለህ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ Ꮏዞራም እኔ በተና ገርኳቸው ቃላት ተበረታታ። ዞራም የአገ ልጋዩ ስም ነበር፤ እናም እርሱ ወደ ምድ ረበዳ ወደ አባታችን እንደሚሄድ ቃል ገባ። አዎን፣ ደግሞም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርሱ ከእኛ ጋር እንደሚቆይ ማለልን።

፴፮ አሁን እርሱ ከእኛ ጋር እንዲቆይ የፈ ለግንበት ለዚህ ምክንያት ነበር፣ አይሁዶች እኛን እንዳያሳድዱን እናም እንዳይጠፉን በመፍራት ወደ ምድረበዳ መሸሸታችንን እንዳያውቁ ዘንድ ነው።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ ዞራም Ꮏመሃላ ሲገ ባልን እርሱን በተመለከተ የነበሩን ፍርሃ ቶች አቆሙ።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ የነህስ ሰሌዳዎችንና የላባንን አገልጋይ ወሰድንና፣ ወደ ምድ ረበዳው ሄድን፣ እንዲሁም ወደ አባታችን ድንኳን ተጓዝን።

ምዕራፍ ፯

ሳርያ በሌሂ ላይ አጉረመረመች— በወን ዶች ልጆቻቸው መመለስ ሁለቱም ተደ ሰቱ—መስዋዕትም አቀረቡ— የነህስ ሰሌ ዳዎቹ የሙሴን እና የነቢያትን ፅህፈቶች ይዘዋል—ሰሌዳዎቹ ሌሂ ከዮሴፍ ትው ልድ መሆኑን ያሳያሉ—ሌሂ ስለዘሮቹና ሰሌዳዎቹን ስለመጠበቅ ተነበየ። ፯፲–፯፲፯፲፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ወደ አባታችን ወደ ምድረበዳ ከመጣን በኋላ እነሆ እርሱ በደ ስታ ተሞላ፣ እንዲሁም እናቴ Ꮏሳርያም እጅግ ተደሰተች፣ በእውነት በእኛ ምክን ያት አዝና ነበርና።

፪ እርሷም እኛ በምድረበዳ ውስጥ እን ደጠፋን አስባ ነበር፤ እና እርሷም በአባቴ ላይ እርሱ ባለራዕይ እንደሆነ በመንገር ቅሬታዋን ገልጻ ነበር፤ እንዲህም አለች፡ እነሆ ከርስት ምድራችን መርተህ አው ጥተንሀል፣ ወንዶች ልጆቼም ከእንግዲህ የሉም፣ እናም እኛም በምድረበዳ ውስጥ እንጠፋለን።

፫ በእንዲህ ዓይነት አነጋገር ነበር እናቴ በአባቴ ላይ ቅሬታዋን የገለጸችው።

፬ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ እንዲህ ብሎ ተናገራት፡ Ꮏባለራዕይ ሰው መሆኔን አው ቃለሁ፣ የእግዚአብሔርን ነገሮች Ꮎበራ ዕይ ባላይ ኖሮ የእግዚአብሔርን ቸርነት አላውቅም ነበር፣ ነገር ግን በኢየሩሳሌም እቆይ ነበር፣ እና ከወንድሞቼ ጋር እጠፋ ነበር።

፭ ነገር ግን እነሆ Ꮏየቃልኪዳኑን ምድር አገኛለሁ፣ በነዚህም ነገሮች እደሰታለሁ፣ አዎን፣ ጌታ የእኔን ወንዶች ልጆች ከላባን እጅ ነፃ እንደሚያወጣቸው እንዲሁም ወደ

፴፩ Ꮏ ሞዛያ ፱፡ ፲፯፣ አልማ ፶፯፡ ፶፯።
፴፫ Ꮏ ቅ.መ.መ. መሀላ።
፴፬ Ꮏ ፩ ኔሬ ፪፡ ፪፣ ፫፡ ፲፯።
፴፭ Ꮏ ፩ ኔሬ ፲፯፡ ፯፣ ፪ ኔሬ ፭፡–፯።
ቅ.መ.መ. ዞራም፣ ዞራማውያን።
፴፯ Ꮏ ኢ.ያ. ፱፡ ፩–፳፩፣ መክ. ፭፡ ፱።
ቅ.መ.መ. መሀላ።
፴፰ ፩ Ꮏ ቅ.መ.መ. ሳርያ።
፱ Ꮏ ፩ ኔሬ ፪፡ ፲፩።
ለ ፩ ኔሬ ፩፡ ፳–፲፫።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፭ Ꮏ ፩ ኔሬ ፪፡ ፳፣ ፲፳፡ ፳፣ ፳፪–፳፫።
ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።

እኛ ወደ ምድረበዳው ዳግመኛ እንደሚያ መጣቸው ^አውቃለሁ።

፲ እናም በዚህ ዓይነት አነጋገር ነበር አባቴ ሌሂ እኛ በምድረበዳ ውስጥ ወደ ኢየሩሳ ሌም ምድር፣ የአይሁዶችን መዝገብ ለማ ግኘት ስንጓዝ፣ እናቴ ሳርያን እኛን በተመ ለከተ ያፅናናት።

፲፩ እናም እኛ ወደ አባቴ ድንኳን ስንመለስ እነሆ የእነርሱ ደስታ የተሟላ ነበር፣ እና ቴም ተፅናናች።

፲፪ እናም እርሷ እንዲህ በማለት ተና ገረች፡ ጌታ ባለቤቴን ወደ ምድረበዳው እንዲሸሽ *እንዳዘዘው አሁን በእርግጥ አወ ቅሁ፣ አዎን እንዲሁም ደግሞ ጌታ ወንዶች ልጆቼን እንደጠበቀልኝ እንዲሁም ከላባን እጆች ነፃ እንዳወጣልኝና፣ ጌታ ያዘዛቸውን ነገር ^ማከናወን እንዲችሉ ኃይልን እንደሰ ጣቸው በእርግጥ አወቅሁ። በእንዲህ ዓይ ነት ነበር እርሷ የተናገረችው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ እነሱ እጅግ ተደሰቱ፣ *መስዋዕት አቀረቡ፣ የሚቃጠል መስዋዕት ለጌታ አቀረቡ፣ እናም የእስራኤል አምላክ ንም ^አመሰገኑ።

፲፬ እናም ለእስራኤል አምላክ ምስጋናውን ካቀረቡ በኋላ፣ አባቴ ሌሂ *በነህስ ሰሌዳዎች ላይ የተቀረፀውን መዝገብ ወሰደው፣ እናም ከመጀመሪያ ጀምሮ መረመራቸው።

፲፭ እናም እርሱም እነርሱ ስለዓለም አፈ ጣጠር፣ እንዲሁም የመጀመሪያ የእኛ ወላ ጆች የሆኑትን የአዳምና የሔዋን ታሪክ የሚ ገልጹትን አምስቱን *የሙሴ መፅሐፍት እንደያዙ አየ፤

፲፮ እናም ደግሞ የአይሁዶችን *መዝገብ፣ ከመጀመሪያው እስከ የይሁዳ ንጉስ ሴዴቅ ያስ የንግሥ ዓምት መጀመሪያ ድረስ ይዘው ነበር፤

፲፯ እናም ደግሞ የቅዱሳን ነቢያት ትንቢ ቶች፣ ከመጀመሪያ እስከ *ሴዴቅያስ የንግስ መጀመሪያ ድረስ እንዲሁም ደግሞ ^በኤ ርምያስ አፍ የተነገሩ ብዙ ትንቢቶችንም ይዘው ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ሌሂ ደግሞ *በነህስ ሰሌዳዎቹ ላይ የአባቶቹን የትውልድ ሐረግ ታሪክ አገኘ፤ ስለዚህ እርሱ ^ከዮሴፍ ትውልድ እንደሆነ አወቀ፤ አዎን፣ በእር ግጥ ዮሴፍ *የያዕቆብ ልጅ የሆነው ወደግ ብፅ *የተሸጠው፣ እናም እርሱ አባቱን ያዕ ቆብንና ሁሉንም ቤተሰዎቹን በረሃብ ከመ ጥፋት ያድናቸው ዘንድ በጌታ እጅ *የተ ጠበቀው ነበር።

፲፱ እናም እነርሱ ደግሞ ከምርኮ ከግብፅ ምድር ከዚህ በፊት በጠበቃቸው አምላክ *ተመርተው የዳኑ ናቸው።

፲፲ እናም እንደዚህ ነበር አባቴ፣ ሌሂ፣ የአባቶቹን የትውልድ ሐረግ ያገኘው። ላባ ንም *የዮሴፍ ትውልድ ነበር፣ ስለዚህ እር ሱና አባቶቹ መዝገቦችን ጠብቀው አቆዩ።

፲፲ እናም አሁን አባቴ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ባየ ጊዜ፣ በመንፈስ ተሞላና፣ ስለዘ ሮቹ መተንበይ ጀመረ—

፲፲ እነዚህ የነህስ ሰሌዳዎች የእርሱ ዘሮች ለሆኑት ለሁሉም ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋ ዎችና ህዝቦች ሁሉ መሄድ ይኖርባቸዋል።

፲፲ ስለዚህ እነዚህ የነህስ ሰሌዳዎች

፭ *ለ* ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፭ *ሀ* ፩ ኔፊ ፪፡፪።
ለ ፩ ኔፊ ፫፡፯።
፱ *ሀ* ሞዛያ ፪፡፫፣
፫ ኔፊ ፱፡፲፱–፳።
ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ለ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፲ *ሀ* ፩ ኔፊ ፡፡ ፳፡ ፴፣
፲፫፡ ፳፫።
ቅ.መ.መ. የነህስ ሰሌዳዎች።
፲፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፳፫።
ቅ.መ.መ. አምስቱ
መጻህፍት።
፲፪ *ሀ* ፩ ዜና ፱፡ ፩።
ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
፲፫ *ሀ* ፪ ነገሥ. ፳፡ ፲፣
ኤር. ፴፯፡ ፩።
ለ ዕዝ. ፩፡ ፩፣
ኤር. ፴፯፡ ፲፯–፴፪፣
፩ ኔፊ ፯፡ ፲፡ ሔሌ. ፣ ፳።
፲፡ *ሀ* ፩ ኔፊ ፫፡ ፫፣ ፲፪።
ቅ.መ.መ. የነህስ ሰሌዳዎች።
ለ ፪ ኔፊ ፫፡ ፡፣ አልማ ፲፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ
ልጅ።
ሐ ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የይስሐቅ
ልጅ።
መ ዘፍጥ. ፴፯፡ ፳፱–፴፯።
ሠ ዘፍጥ. ፴፭፡ ፡–፭።
፲፭ *ሀ* ዘፀአ. ፲፫፡ ፲፯–፲፣
ዓሞ. ፫፡ ፩–፪፣
፩ ኔፊ ፲፯፡ ፳፫–፴፩፣
ት. እና ቃ. ፲፫፡ ፲፯–፲፣
፲፴፯፡ ፳፪።
፲፯ *ሀ* ፩ ኔፊ ፯፡ ፪።

ᵐበፍፁም መጥፋትም ሆነ ከጊዜ ብዛት ሊደ በዝዙም አይገባም አለ። እናም ዘሮቹን በተ መለከተ ብዙ ነገሮችን ተነበየ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ እስከአሁን እኔና አባቴ ጌታ ያዘዘንን ትዕዛዛት ጠበቅን።

፳፩ እናም እኛ ጌታ እንድናገኝ ያዘዘንን መዝገቦች አግኝተናልና መርምረናቸዋል፣ እነሱም ጠቃሚ እንደሆኑ፣ አዎን፣ የጌታን ᵐትዕዛዛት ለልጆቻችን ማቆየት እስኪቻለን ያህል ለእኛ ᵃትልቅ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ አግኝተናቸዋል።

፳፪ ስለዚህ እኛ ወደ ቃልኪዳኑ ምድር በምድረበዳ ውስጥ ስንጓዝ ከእኛ ጋር ይዘ ናቸው እንሄድ ዘንድ የጌታ ጥበብ ነበር።

ምዕራፍ ፯

ኔፊ ስለ እግዚአብሔር ነገሮች ፃፈ—የኔፊ ዓላማ ሰዎችን ወደ አብርሃም አምላክ መጥተው እንዲድኑ ማስረዳት ነው። ከ፯፻–፰፻፶፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እና አሁን እኔ፣ ኔፊ፣ የአባቶቼን የት ውልድ ሀረግ በዚህ ᵐየመዝገቤ ክፍል አል ፅፍም፣ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በዚህ በም ፅፍበት ᵃሰሌዳ ላይ አልፅፈውም፤ ᵇአባቴ ባቆየው መዝገብ ላይ ተፅፏልና፤ ስለዚህ በዚህ ሥራ ውስጥ አልፅፈውም።

፪ እኛ ᵐየዮሴፍ ትውልዶች ነን ማለት ብቻ ይበቃኛል።

፫ ሁሉንም የአባቴን ነገሮች በመፃፍ ጥን ቁቅ መሆኔ ልዩነት አያመጣም፣ ᵐበእነዚህ ሰሌዳ ላይ መፃፍ አይችሉምና፣ እኔ የእግ ዚአብሔርን ነገሮች ለመፃፍ ቦታውን እፈ ልገዋለሁና።

፬ ሙሉ አላማዬም ሰዎችን ወደ አብርሃም አምላክ፣ ወደ ይስሀቅ አምላክና፣ ወደ ያዕ ቆብ አምላክ ᵐእንዲመጡና እንዲድኑ ᵃለማ ሳመን ነውና።

፭ ስለዚህ፣ ለዓለም ᵐአስደሳች የሆኑትን ነገሮች እኔ አልፅፍም፣ ነገር ግን ለእግዚ አብሔርና ከዓለም ላልሆኑት የሚያስደስቱ ነገሮችን እፅፋለሁ።

፮ ስለዚህ ሰሌዳዎቹን ለሰው ልጆች ዋጋ በሌላቸው ነገሮች እንዳይሞሏቸው ለዘሮቼ ትዕዛዝን እሰጣለሁ።

ምዕራፍ ፯

የሌሂ ወንዶች ልጆች ወደ ኢየሩሳ ሌም ተመልሰው እስማኤልንና ቤተሰ ቦቹን አብረዋቸው እንዲጓዙ ጋበዙአ ቸው—ላማንና ሌሙቼ አመፁ—ኔፊ ወንድሞቹን በጌታ እምነት እንዲኖራ ቸው መከራቸው—በገመድ አሰሩት እናም የእርሱን ጥፋት አቀዱ—በእም ነት ሀይል እርሱ ነፃ ሆነ—ወንድሞቹ ይቅ ርታን ጠየቁ—ሌሂና አብረውት የነበሩ ትም የሚቃጠለውን መስዋዕት አቀረቡ። ከ፯፻–፰፻፶፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እና አሁን ይህንን እንድታውቁት እፈ ልጋለሁ፣ አባቴ፣ ሌሂ፣ ስለ ዘሩ ᵐመተንበ ይን ከጨረሰ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ ሌሂ ቤተ ሰቦቹን ብቻ ወደ ምድረበዳ መውሰድ እን ደማይገባው ነገር ግን ወንድ ልጆቹ ᵃሴት ልጆችን ᵇለሚስትነት እንዲወስዱና፣ ለጌታ ዘርን በቃልኪዳኑ ምድር እንዲያሳድጉ ጌታ በድጋሚ ነገረው።

፪ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊና፣ ወንድ ሞቼ፣ ተመልሰን ወደ ኢየሩሳሌም ምድር መሄድ እንዳለብን፣ እናም እስማኤልንና ቤተሰቡን ወደ ምድረበዳ እንድናመጣቸው ጌታ ᵐአዘዘው።

፲፱ ᵐ አልማ ፴፯፡፱–፴፡ ᵃ ፳፩ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፮። ᵃ ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሳት መጻህፍት ዋጋዎች። ᵇ ፯ ᵐ ፪ ኔፊ ፴፡፲፡–፲፭። ᵃ ለ ፩ ኔፊ ፱፡፪።

ሐ ፩ ኔፊ ፩፡፲፯–፲፯፣ ፲፱፡፩–፯። ᵐ ፪ ᵐ ፩ ኔፊ ፭፡፲፡–፲፯። ᵐ ᵐ ያዕቆ. ፯፡፳፯፣ ᵐ ᵐ ᵐ

፲ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊ፣ ᵐእንደገና ከወንድሞቼ ጋር፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ወደ ምድረበዳ ወጣን።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ወደ እስማኤል ቤት ድረስ ሄድን፣ በእስማኤልም ፊት ታላቅ ሞገስን በማግኘታችን፣ የጌታን ቃል ለእርሱ ተናገርን።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ የእስማኤልንና የቤተሰዎቹን ልብ ከማራራቱ የተነሳ ወደ ምድረበዳ ወደ አባታችን ድንኳን ከእኛ ጋር ተጓዙ።

፲፫ እናም በምድረበዳ ስንጓዝ፣ እነሆ ላማንና ልሙኤል፣ ሁለቱ የእስማኤል ሴት ልጆች፣ ሁለቱ የእስማኤል ᵐወንዶች ልጆቹና ቤተሰቦቻቸው በእኛ ላይ አዎን፣ በእኔ፣ በኔፊና፣ በሳም፣ በአባታቸው በእስማኤልና በሚስቱና በሌሎች ሶስት ሴቶች ልጆቹ ላይ አመፁ።

፲፬ እናም በዚህ በአመፃቸው የተነሳ ወደ ኢየሩሳሌም ምድር ለመመለስ ፈለጉ።

፲፭ እና አሁን እኔ፣ ኔፊ፣ በልባቸው ጠማርነት ᵐበማዘን፣ እንዲህ ስል ተናገር ኋቸው፥ አዎን፣ ለላማንና ለልሙኤልም እንኋ፤ እነሆ እናንተ የእኔ ታላቅ ወንድሞቼ ናችሁ፣ እንዴት በልባችሁ ጠማር፣ በአዕምሮአችሁ እውር ሆናችሁ፣ እና እኔ ታናሽ ወንድማችሁ ለእናንተ ልናገርና፣ አዎን፣ እና ምሳሌን ላስቀምጥላችሁ ይገባኛልን?

፲፮ እንዴት ነው የጌታን ቃል ያላዳመጣችሁት?

፲፯ እንዴት ነው የጌታን መልአክ ማየታችሁን ᵐየረሳችሁት?

፲፰ አዎ፣ ጌታ ከላባን እጅ ᵐሲያወጣን፣ እና ደግሞ መዝገቦቹን እንድናገኝ ሲል ምን ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገልንስ እንዴት ረሳችሁት?

፲፱ አዎን፣ ጌታ ለሰዎች ልጆች፣ በእርሱ ᵐታማኝ እስከሆኑ ድረስ፣ ሁሉንም ^ነገሮች በፈቃዱ ለማድረግ እንደሚችል እንዴት እረሳችሁ? ስለዚህ ለእርሱ ታማኞች እንሁን።

፲፲ እኛም ለእርሱ ታማኞች ከሆንን ᵐየቃልኪዳኗን ምድር እናገኛለን፤ እናም ወደ ፊት አንድ ቀን የኢየሩሳሌምን መጥፋት በተመለከተ የጌታ ቃል እንደሚሟላ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ሁሉም ስለኢየሩሳሌም ^መጥፋት ጌታ የተናገራቸው ነገሮች መፈጸም አለባቸውና።

፲፳ እነሆም የጌታ መንፈስ ከእነርሱ ጋር መስራትን በቅርብ ያቆማል፤ እነሆ እነርሱ ነቢያትን ᵐተቃውመዋል፣ ^ኤርምያስን ወደ ወህኒ ጨምረዋል። እናም ከምድሪቱ እስከ ማባረር ድረስም የአባቴን ^ህይወት ለማጥፋት ፈልገዋል።

፲፳፩ አሁንም እነሆ እላችኋለሁ ወደ ኢየሩሳሌም ብትመለሱ እናንተም ደግሞ ከእነርሱ ጋር ትጠፋላችሁ። አሁንም በምርጫችሁ ወደ ምድሪቱም ሂዱ፣ እናም እኔ ለእናንተ የተናገርኩትን ቃላቶች አስታውሱ፣ የምትሄዱ ከሆነ ትጠፋላችሁ፤ ይህንንም እናገር ዘንድ የጌታ መንፈስ ገፋፍቶኛልና።

፲፳፪ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ እነዚህን ቃላት ለወንድሞቼ ስናገር በእኔ ተቆጡ። እነሆም እንዲህ ሆነ በእጃቸው ያዙኝ፣ እነሆ፣ እጅግ ተናደው ነበር፣ እና በምድረበዳ ውስጥ ትተውኝ በዱር አውሬ እንድበላ ዘንድ ህይወቴን ለማጥፋት ስለፈለጉ በገመድም ᵐአሰሩኝ።

፲፳፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ ለጌታ እንዲህ ብዬ ፀለይኩ፥ አቤቱ ጌታ በአንተ ባለኝ እምነት መሰረት ከወንድሞቼ እጅ ታድነኛለህ፤ አዎን የታሰርኩበትንም እስር ᵐእበጣጥሰው ዘንድ ጥንካሬን ስጠኝ።

፲ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፡፪–፲።
፲፩ ᵐ ፪ ኔፊ ፩፡፲።
፲፭ ᵐ አልማ ፳፩፡፪፣
ሙሴ ፯፡፵፯።
፲፰ ᵐ ዘዳግ. ፩፡፱፣
፩ ኔፊ ፲፡፳፱፣ ፩፡፲።
፲፩ ᵐ ፩ ኔፊ ፩።
፲፪ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፡፯፣ ፲፫፡፲፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፡፱፣
አልማ ፳፯፣፡፲፪።
፲፲ ᵐ ፩ ኔፊ ፪፡፳።
ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን
ምድር።
ለ ፪ ነገሥ. ፳፭፡፩–፳፭፣
፪ ኔፊ ፯፡፳፣ ፳፭፡፲፣
ኦምኒ ፩፡፲፭፣
ሔለ. ፳፡፳–፳፩።
፲፡ᵐ ሕዝ. ፭፡፯፣
፩ ኔፊ ፩፡፲፳–፳፣ ፪፡፲፣።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ኤር. ፴፯፡፲፭–፳፩።
ሐ ፩ ኔፊ ፪፡፩።
፲፯ᵐ ፩ ኔፊ ፲፳፡፲፩–፲፭።
፲፯ᵐ አልማ ፲፡፳፯–፳፳።

፲፤ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት በተ
ናገርኩ ጊዜ እስሩ ከእጆቼና ከእግሬ ላይ
ተፈታ፣ እናም ከወንድሞቼ ፊት ቆምኩና፣
እንደገና ተናገርኳቸው።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ እንደገና
በእኔ ላይ ተቆጡ፣ እናም እጃቸውን ሊያ
ሳርፉብኝ ፈለጉ፤ ነገር ግን እነሆ ከእስማ
ኤል ᵐሴት ልጆች አንዷ፣ አዎን፣ ደግ
ሞም እናቷና ከእስማኤል ወንዶች ልጆች
አንዱ፣ የእኔ ወንድሞች ልባቸው እስኪራራ
ድረስ ለመኑዋቸው፤ ህይወቴንም ለማጥ
ፋት መፈለጋቸውን አቆሙ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ በክፋታ
ቸው፣ ምክንያት አዘኑ፣ ስለዚህ በእኔ ላይ
ባደረጉት ነገር ይቅርታ እንዳደርግላቸው
በፊቴ አጎንብሰው ለመኑኝ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ ባደረጉት
ነገር ሁሉ በእውነት ᵐይቅርታ አደረኩላ
ቸው፣ እናም ይቅር ይላቸው ዘንድ ለጌታ
ለአምላካቸው እንዲፀልዩ መከርኳቸው።
እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም እንዲሁ አደ
ረጉ። እናም ወደ ጌታ ከፀለዩ በኋላ እንደገና
ወደአባታችን ድንኳን ጉዞአችንን አደረግን።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ወደ አባታችን ድን
ኳን ወረድን። እናም እኔና ወንድሞቼና የእ
ስማኤል ቤት ሁሉ ወደ አባቴ ድንኳን ከወ
ረድን በኋላ እነርሱ ለጌታ ለአምላካቸው
ᵐምስጋናን አቀረቡ፤ ᶮመስዋዕትንና የሚ
ቃጠለውንም መስዋዕት አቀረቡለት።

ምዕራፍ ፳

*ሌሂ ስለ ሕይወት ዛፍ ራዕይ አየ—ከፍሬ
ውም ተካፈለና ቤተሰቦቹም እንደዚያው
እንዲያደርጉ ፈለገ—የብረት በትር፣ የጠ
በበና የቀጠነ መንገድና ሰዎችን የሚጋርደ
ውን የጨለማ ጭጋግ ተመለከተ—ሳርያ፣
ኔፊና፣ ሳም፣ ፍሬውን ተካፈሉ፣ ላማ
ንና ልሙኤል ግን ተቃወሙ። ከ፲፯–
፳፫ ዓ.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ ከሁሉም ዓይነት
ዘሮች ሁሉንም የእህል ዓይነትና፣ ከሁ
ሉም ዓይነት የፍራፍሬ ዘሮች በአንድነት
ሰበሰብን።

፪ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ በምድረበዳ
በቆየበት ጊዜ እንዲህ ብሎ ተናገረን፥ እነሆ
ህልምን ᵐአልሜአለሁ፣ ወይም በሌላ አባ
ባል፣ ᶮራዕይን አይቻለሁ።

፫ እናም እነሆ ባየሁት ነገር የተነሳ ᵐበኔ
ፊና ደግሞም ስለሳም በጌታ የምደሰትበት
ምክንያት አለኝ፣ እና እነርሱና ብዙዎቹ
ዘሮቻቸው እንደሚድኑ ለመገመት ምክ
ንያት አለኝ።

፬ ነገር ግን እነሆ ᵐላማንና ልሙኤል፣ በእ
ናንተ ምክንያት እጅግ እፈራለሁ፤ እነሆ
በህልሜ ውስጥ ጨለማና የማያስደስት
ምድረበዳ ማየቴን ተረዳሁ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ አንድ ሰው አየሁ፣
ነጭ ᵐልብስ ለብሶ ነበር፤ እናም መጥቶ
በፊቴ ቆመ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ተናገረኝ፣
እናም እንድከተለው ጋበዘኝ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እርሱን እንደተከተ
ልኩት ራሴንም በጭለማ እና በማያስደስት
ባድማ ውስጥ እንደነበርኩ ተመለከትኩ።

፰ እናም ለብዙ ሰዓታት በጨለማ ውስጥ
ከተጓዝኩ በኋላ እንደምህረቱም ብዛት ጌታ
በእኔ ላይ ᵐምህረትን ያደርግ ዘንድ ፀለ
ይኩ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ለጌታ ከፀለይኩ
በኋላ፣ ትልቅና ሰፊ የሆነን ᵐሜዳ ተመለ
ከትኩ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ᵐፍሬዋ አንድን ሰው

፲፱ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፯።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
ለ ፩ ኔፊ ፭፡፱።
፳ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. ህልም፣
ራዕይ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡፲፯።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፫ ሀ ፩ ኔፊ ፳፡፲፱–፲፳።
፬ ሀ ፩ ኔፊ ፳፡፴፭–፴፯።
፭ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴–፴፪።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፱ ሀ ማቴ. ፲፫፡ ፴፳።
፲ ሀ አልማ ፴፪፡ ፵፩–፵፫።

ደስተኛ ለማድረግ መልካም የሆነችን ^ዛፍ ተመለከትኩ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ሄጄ ᵛከፍሬዋ ተካ ፈልኩ፤ ከዚህ በፊት ከቀመስኩት ሁሉ ጣፋጭ እንደሆነች አየሁ። አዎን፣ ፍሬ ዋም ከዚህ በፊት ካየሁትም ንጣት ሁሉ በላይ ^ነጭ የሆነች ፍሬ እንደሆነች ተመ ለከትኩ።

፲፪ ከዚህች ፍሬ ስካፈልም ይህም ነፍሴን ᵛበደስታ ሞላው፣ ስለሆነም ቤተሰቦቼም ደግሞ ይካፈሉት ዘንድ ^መመኘት ጀመ ርኩ፤ ከሌላው ፍሬ ሁሉ በላይ ^አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁና።

፲፫ እናም ቤተሰቤን ደግሞ ማግኘት እችል ዘንድ በዙሪያው ስመለከት፣ ᵛየወንዝ ውሃን ተመለከትኩ፤ ይወርድም ነበር፣ እና እኔ ፍሬውን ከበላሁበት ዛፍ አቅራቢያ ነበር።

፲፬ እናም ከየት እንደመጣም ለማየት ተመለከትኩ፣ ትንሽ ራቅ ብሎም ምን ጩን አየሁ፤ እናታችሁ ሳርያን፣ ሳምንና፣ ኔፊን፣ በዚያው በምንጩ አየሁ፤ እነርሱም ወዴት መሄድ እንዳለባቸው እንደማያውቁ ሆነው ቆሙ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ጠቆምኳቸው፣ ወደ እኔ እንዲመጡና ከሌሎች ፍሬዎች ሁሉ በላይ መልካም የሆነውን ፍሬ፣ እን ዲበሉ በከፍተኛ ድምፅ ነገርኳቸው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ ወደ እኔ መጡና ደግሞ ፍሬውን በሉ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ላማንና ልሙኤ ልም እንዲመጡና ደግሞ ፍሬውን እንዲ በሉ ተመኘሁ፣ ስለሆነም እንዳያቸው ዘንድ አይኖቼን ወደ ወንዙ ምንጭ ጣልኩኝ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እኔ አየሁአቸው፣ ነገር ግን እነርሱ ወደ እኔ ᵛአልመጡም፣ ፍሬውንም አልበሉም።

፲፱ እናም ᵛየብረት በትር ተመለከትኩ፣ በወንዙም ዳርቻ፣ እኔ ወደ ቆምኩበት ዛፍ ድረስ እንዲወስድ የተዘረጋ ነበር።

፳ እናም እኔ ወደ ቆምኩበት ዛፍ ከብ ረት በትሩ ጋር የሚወስድ ᵛየጠበበና የቀ ጠነ መንገድ ተመለከትኩ፣ ይህም ደግሞ በቋቋቴውም ምንጭ፣ ዓለምን ወደሚመ ስለው ትልቅና ሰፊ ^ሜዳ ያመራል።

፳፩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎችን አየሁ፣ እኔ ወደ ቆምኩበት ዛፍ የሚያደርሰውን ᵛመንገድ ለማግኘት አብዛኞቹ ወደፊት ይገፉ ነበር።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ መጡ፣ እና ወደ ዛፉ በሚያመራው መንገድ ወደፊት ተጓዙ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ የጨለማ ᵛጭጋግ ተነሳ፣ አዎን በመንገዱ ጉዞ የጀመሩት መን ገዳቸውን እስኪስቱና ተንከራተው እስኪ ጠፉ ድረስ እጅግ ታላቅ የጨለማ ጭጋግ ተነሳ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ሌሎች ደግሞ ወደ ፊት ሲጋፉ አየሁ፣ እናም እነርሱም ወደፊት መጡና የብረት በትሩን ጫፍ ያዙ፣ የብረ ቱን በትር ተጠግተው በጨለማው ጭጋግ ውስጥ ወደፊት መጥተው የዛፉን ᵛፍሬ እስ ኪካፈሉ ድረስ ወደፊት ገፉ።

፳፭ እናም ከዛፉ ፍሬ ከተካፈሉ በኋላ ᵛያፈሩ በመምሰል አይኖቻቸውን ወደ እዚ ህና ወደ እዚያ ጣሉ።

፳፮ እኔም ደግሞ አይኖቼን በዙሪያው ጣልኩኝ፣ እና ከውሃው ወንዝ ባሻገር፣ ትልቅና ᵛሰፊ ህንፃን ተመለከትኩ፤ ከምድር ከፍ ብሎ በአየር ላይ የቆመ ይመስል ነበር።

፲ ^ለ ዘፍጥ. ፪፡ ፱፣
ራዕ. ፪፡ ፯፣ ፳፪፡ ፪፣
፩ ኔፊ ፲፩፡ ፱፣ ፰–፳፩።
ቅ.መ.መ. የህይወት ዛፍ።
፲፩ ^ሀ አልማ ፭፡ ፴፱።
^ለ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፰።
፲፪ ^ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
^ለ አልማ ፴፯፡ ፳፱።
^ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፯።
፲፫ ^ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፲፯–፲፰፣
፲፭ ^ሀ ፩ ኔፊ ፭፡ ፳–፳፭።
፲፱ ^ሀ ፩ ኔፊ ፰፡ ፱፣
ራዕ. ፲፪፡ ፭፣
ጆ.ስ.ት. ራዕ. ፲፱፡ ፲፭
(ተጨማሪ)፣
፩ ኔፊ ፰፡ ፴፣ ፲፭፡ ፳፭፣
፲፭፡ ፳፣–፳፡።
፳ ^ሀ ማቴ. ፯፡ ፲፡፣
፪ ኔፊ ፴፭፡ ፲፯–፳።
^ለ ማቴ. ፲፣፡ ፴፰።
፳፩ ^ሀ ቅ.መ.መ. መንገድ።
፳፣ ^ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፲፯፣ ፲፭፡ ፳፡።
፳፡ ^ሀ ፩ ኔፊ ፰፡ ፣–፲፪።
፳፫ ^ሀ ሮሜ ፩፡ ፲፯፣
፪ ጢሞ. ፩፡ ፰፣
አልማ ፵፯፡ ፳፩፣
ሞር. ፰፡ ፴፰።
፳፯ ^ሀ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፴፭–፴፯፣
፲፪፡ ፲፰።

፳፯ እናም በአረጋውያን ጎልማሳም፣ በወ
ንድም በሴትም ሰዎች ተሞልቶ ነበር፣ አለ
ባበሳቸውም እጅግ ያማረ ነበር፤ ፍሬውንም
መጥተው ወደበሉት ላይ እጃቸውን እየጠ
ቆሙና [ሀ]እየተሳለቁባቸው ነበር።

፳፰ በእነዚያ በሚያላገጡባቸውም ምክ
ንያት፣ ፍሬውን [ለ]ከቀመሱ በኋላ [ሐ]አፈሩ፤
ወደተከለከለውም መንገድ [መ]ገቡና ጠፉ።

፳፱ እና አሁን እኔ፣ ኔፊ፣ የአባቴን ቃላት
[ሠ]በሙሉ አልናገርም።

፴ ነገር ግን፣ ፅሁፉን ለማሳጠር፣ እነሆ
ብዙ ሌሎችም ወደፊት ሲጋፉ አየ፤ መጥ
ተው [ረ]የብረት በትሩን ጫፍ ያዙ፣ እና ወደ
ፊት መጥተው እስኪወድቁና የዛፉን ፍሬ
እስኪካፈሉና እስኪወድቁ ድረስ መንገዳ
ቸውን ወደፊት በመቀጠል ያለማቋረጥም
የብረቱን በትር አጥብቀው ያዙ።

፴፩ እና ደግሞ ሌሎችም [ሰ]ብዙዎች ወደ
ትልቁና ሰፊው ህንፃ መንገዳቸውን ሲያ
ቀኑ አየ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ብዙዎች ወደ
[ሸ]ፏፏቴው ጥልቅ ሲመጡ፤ እና ብዙዎች
ደግሞ በማይታወቅ መንገድ ገብተው ሲቅ
በዘበዙ ከዕይታው ጠፉ።

፴፫ እና ወደ ማይታወቀው ህንፃ የገቡት
ታላቅ ብዛት ነበራቸው። ወደ ህንፃው ከገ
ቡም በኋላ በእኔና ፍሬውን ይካፈሉ በነበ
ሩት ላይ ደግሞ [ቀ]የጫዝ ጣታቸውን ይጠቁሙ
ነበር፤ ነገር ግን እኛ አላደመጥናቸውም።

፴፬ እነዚህ የአባቴ ቃላት ነበሩ፥ [በ]ያደመ
ጡዋቸው በሙሉ ጠፍተዋል።

፴፭ እና አባቴ [ተ]ላማንና ልሙኤል ፍሬ
ውን አልተካፈሉም አለ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ብዙ የነበ
ሩትን የህልሙን ወይንም የራዕዩን ቃላት
ከተናገረ በኋላ፣ ለእኛ እንዲህ አለን፣ በራ
ዕዩ ባየው ነገር የተነሳ፣ ለላማንና ለልሙ
ኤል በእጅጉ ፈራላቸው፣ አዎ፣ ከጌታ ፊት
እንዳይጣሉ ፈራላቸው።

፴፯ እና ምናልባት ጌታ ለእነርሱም መሐሪ
እንዲሆንላቸውና እንዳይጥላቸው ዘንድ፣
የእርሱን ቃላት እንዲሰሙ በአፍቃሪ [ተ]ወላጅ
ሙሉ ስሜት መከራቸው፤ አዎን፣ አባቴ
ለእነርሱ ሰበከላቸው።

፴፰ እናም ለእነርሱ ከሰበከላቸውና፣ ብዙ
ነገሮችን ለእነርሱ ከተነበየላቸው በኋላ፣
የጌታን ትዕዛዛት እንዲጠብቁ አዘዛቸው፣
እናም ለእነርሱ መናገርን አቆመ።

ምዕራፍ ፱

*ኔፊ በሁለት የተካፈሉ መዝገቦችን
ሰራ—እያንዳንዳቸው የኔፊ ሰሌዳዎች
ይባላሉ—ትልልቆቹ ሰሌዳዎች አለማዊ
ውን ታሪክ ይዘዋል፤ ትንንሾቹም ቅዱሳን
ነገሮችን። ፮፣ ፲–፲፣ ፲፪ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እና አባቴ [ተ]በልሙኤል ሽለቆ፣ ውስጥ
በድንኳን ሲኖር፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉና፣
በእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ ሊፃፉ የማይችሉ
ትን፣ ብዙ ትላልቅ ነገሮችን አየ፣ እንዲ
ሁም ሰማ፣ ተናገረም።

፪ እናም አሁን፣ እነዚህን ሰሌዳዎች በተ
መለከተ እንደተናገርኩት፣ እነሆ እነርሱ
የህዝቤን ታሪክ በሙሉ የፃፍኩባቸው [ሀ]ሰሌ
ዳዎች አይደሉም፤ የእኔን ህዝቦች ታሪክ
በሙሉ የፃፍኩባቸው ሰሌዳዎች ኔፊ የሚል
ስም ሰጥቻቸዋለሁ፤ ስለዚህ፣ እነርሱ በእኔ
ስም የኔፊ ሰሌዳዎች ተብለው ይጠራሉ፤
እናም እነዚህ ሰሌዳዎች ደግሞ የኔፊ ሰሌ
ዳዎች ተብለው ይጠራሉ።

፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፰ *ለ* ፪ ጴጥ. ፪፡ ፲፱–፳፪።
ሐ ማር. ፱፡ ፲፱–፳፡ ፰፡ ፴፰፤
ሉቃ. ፰፡ ፲፭–፲፰፤
ዮሐ. ፲፪፡ ፵፪–፵፫።
መ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፳፱ *ሠ* ፩ ኔፊ ፩፡ ፲፯–፲፱።
፴ *ረ* ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፳፫–፳፬።
፴፩ *ሰ* ማቴ. ፯፡ ፲፫።
፴፪ *ሸ* ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፳፯–፳፱።
፴፫ *ቀ* ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
፴፬ *በ* ዘፀአ. ፳፫፡ ፪።
፴፭ *ተ* ፩ ኔፊ ፰፡ ፲፯–፲፰፤
፪ ኔፊ ፭፡ ፲፱–፳፬።
፴፮ *ቸ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ፣
ወላጆች።
፱ ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፪፡ ፬–፯፣ ፰፣ ፲፬–፲፭፣
፲፯፡ ፯።
፪ *ለ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፪፣ ፴፣
ያዕቆ. ፫፡ ፲፫–፲፴፣
ቃላት ፩፡ ፪–፲፩፣
ት. እና ቃ. ፲፡ ፴፰–፴።
ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።

፫ ሆኖም፣ እኔ ለተለየ ᐸዓላማ ስለህዝቦቼ ᐳአገልግሎት ታሪክ በእነዚህ ሰሌዳዎች በመቅረፅ እንድፅፍ ከጌታ ትዕዛዝ ተቀብ ያለሁ።

፬ ᐸበሌሎቹም ሰሌዳዎች ላይ የንጉሶቹን የንግስ ታሪክ፣ እናም የጦርነትና የእኔ ህዝ ቦች ፀብ መቀረፅ አለበት፤ ስለዚህ እነዚህ ሰሌዳዎች በይበልጥ ስለአገልግሎት የሚ ቀረጹበት፤ እናም ሌሎች ሰሌዳዎች ስለን ጉሶቹ ንግስና የእኔ ህዝቦች ፀብና ጦርነቶች የሚቀረጹበት ናቸው።

፭ ስለዚህ ጌታ እነዚህ ሰሌዳዎች ᐸለብ ልህ ዓላማው እንድሰራው አዘዘኝ፣ ይህ ንም አላማ እኔ አላውቀውም።

፮ ነገር ግን ጌታ ሁሉንም ነገሮች ከመጀ መሪያ ጀምሮ ᐸያውቃል፤ ስለዚህ፣ ሁሉ ንም የእርሱን ስራዎች በሰው ልጆች መካ ከል ለመፈፀም መንገድ ያዘጋጃል፤ እነ ሆም፣ የእርሱ ቃላት በሙሉ የሚያሟ ላበት ሁሉም ᐸኃይል አለው። እናም ይህ ነው። አሜን።

ምዕራፍ ፲

ሌሂ አይሁዶች በባቢሎናውያን በም ርኮ እንደሚወሰዱ ተነበየ—ከአይሁ ዶች መካከል መሲህ፣ አዳኝና፣ መድ ኃኒት እንደሚመጣ ተናገረ—እንዲሁም ሌሂ የእግዚአብሔርን በግ የሚያጠም ቀው እንደሚመጣ ተናገረ—ሌሂ የመ ሲሁን ሞትና ትንሣኤ ተናገረ—እርሱም የእስራኤልን መበተንና መሰባሰብ ከወ ይራ ዛፍ ጋር አነፃፀረ—ኔፊ ስለእግዚ አብሔር ልጅ፣ ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦ ታና፣ ስለፅድቅ አስፈላጊነት ተናገረ። ከ፯፻–፮፻፶፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እና አሁን እኔ፣ ኔፊ፣ ᐸበእነዚህ ሰሌ ዳዎች ላይ የእኔን ድርጊትና ንግስና አገ ልግሎት ታሪኬን በመፃፍ እቀጥላለሁ፤ ስለዚህ፣ በእኔ ታሪክ ለመቀጠል፣ የአባ ቴን ደግሞም የወንድሞቼን ነገሮች በመ ጠኑ መናገር አለብኝ።

፪ እነሆም፣ እንዲህ ሆነ አባቴ ᐸስለህልሙ መናገሩን፣ እናም እነርሱን በሙሉ ትጋት መምከር ከጨረሰ በኋላ፣ አይሁዶችን በተ መለከተ ተናገራቸው—

፫ እነርሱም ከጠፉ በኋላ፣ እንዲሁም ያቺ ታላቂቷ ከተማ ᐸኢየሩሳሌምና ብዙ ዎች ሕዝቦቿ በምርኮ ወደ ᐳባቢሎን ᐸከተ ወሰዱ በኋላ፣ ጌታ በጊዜው መሰረት እን ደገና ᐸይመለሳሉ፣ አዎን፣ ከምርኮ ወጥ ተው ይመለሳሉ፤ እናም ከምርኮም ወጥ ተው ከተመለሱ በኋላ፣ እንደገናም የርስት ምድራቸው ባለቤት ይሆናሉ።

፬ አዎን፣ አባቴ ኢየሩሳሌምን ከለቀቀ ᐸከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ጌታ እግ ዚአብሔር ከአይሁዶች መካከል ᐳነቢይን፣ እንዲሁም ᐸመሲሁን ወይም በሌላ አነጋገር የዓለምን መድኃኒት ያስነሳል።

፭ እናም፣ ደግሞ እርሱ ነቢያትን በተመ ለከተ፣ እርሱ ስለተናገረበት መሲህን ወይም ይህ የአለም አዳኝን በሚመለከት ስለእነዚህ ነገሮች እንዴት ታላቅ ቁጥር ያላቸው ᐸእን ደመሰከሩ ተናገረ።

፮ ስለዚህ በዚህ መድሐኒት ካልታመኑ

፫ ᐸ ት.እና ቃ. ፫፡፲፱።
ᐳ ፩ ኔፊ ፮፡፫።
፬ ᐸ ያዕቆ. ፩፡፪–፱፡
ቃላት ፩፡፲።
፭ ᐸ ፩ ኔፊ ፲፱፡፫፣
ቃላት ፩፡፯፣
አልማ ፴፯፡፪፣ ፲፪፣ ፲፱፡፲፡
፮ ᐸ ፪ ኔፊ ፱፡፳፣
ት.እና ቃ. ፴፳፡፪፣
ሙሴ ፩፡፮፣ ፴፭።
ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
ᐳ ማቴ. ፳፳፡፲፳።

፲ ᐸ ፩ ᐸ ፩ ኔፊ ፱፡፩–፳፡ ፲፱፡፩–፮፣
ያዕቆ. ፩፡፩–፱።
፪ ᐸ ፩ ኔፊ ፳።
፫ ᐸ ፩ ኔፊ ፮፡፮፣
፪ ኔፊ ፮፡፳፣
ሔለ. ፳፡፳–፳፩።
ᐳ ሕዝ. ፳፱፡፪፣
፩ ኔፊ ፩፡፲፫፣
ኦምኒ ፩፡፲፭።
ሐ ፳፻፹፯ ም.ዓ.፣ በተጨማሪ
ውስጥ የዘመን ቅድመ
ተከተልን ተመልከቱ።

፪ ኔፊ ፳፭፡፲።
መ ኤር. ፳፱፡፲፣
፪ ኔፊ ፮፡፳–፱።
፱ ᐸ ፩ ኔፊ ፲፱፡፳፡
፪ ኔፊ ፳፭፡፲፡
ᐳ ፩ ኔፊ ፳፡፩።
ᐸ ያዕቆ. ፮፡፲፩፣
ሞዛያ ፲፫፡፴፫፣
ሔለ. ፳፡፲፱–፳፩፣
፫ ኔፊ ፳፡፳፫–፳፩።

በስተቀር ሁሉም የሰው ዘር በመሳትና ᵐበው ድቀት ላይ ነበሩ፣ እናም ለዘለአለምም ይሆ ናሉ።

፯ እናም ደግሞ እርሱ ከመሲሁ፣ በፊት የጌታን መንገድ ለማቅናት ስለሚመጣው ᵐነቢይ ተናገረ—

፰ አዎን፣ ወደ ምድረበዳው ሄዶ እንዲህ በማለት ይጮሃል፡ የጌታን መንገድ ᵐአቅኑ፣ ጥርጊያውንም አዘጋጁ፣ እናንተ የማታው ቁት አንዱ ከመካከላችሁ ቆሟልና፤ እናም እርሱም የጫማውን ጠፍር ለመፍታት ብቁ ያልሆንኩ ከእኔ የበረታ ነው። እናም ይህ ንን ነገር በተመለከተ አባቴ ብዙ ተናገረ።

፱ እናም አባቴ ከዮርዳኖስ ባሻገር ᵐቤተ ባራ ውስጥ እርሱ እንደሚያጠምቅ ተናገረ፣ ደግ ሞም እርሱ በውሃ ᶮእንደሚያጠምቅ ተና ገረ፤ መሲሁንም ቢሆን በውሃ ያጠምቀዋል።

፲ እናም እርሱ መሲሁን በውሃ ካጠመቀ በኋላ፣ የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግደ ውን የእግዚአብሔርን ᵐበግ ማጥመቁን እርሱ እንዲሁም ይመሰክራል።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ በአይሁዶች መካከል ስለሚሰበከው ወንጌል፣ ደግሞም ስለአይሁ ዶች ᵐእምነት በማጣት ᶮመመንመን ለወን ድሞቼ ነገራቸው። እናም ዳግም የሚመጣ ውን መሲሕ ᵒከገደሉ በኋላና እርሱም ከተ ገደለ በኋላ፣ ከሞት ᵖይነሳል፣ እናም እራ ሱን ᵐበመንፈስ ቅዱስ ለአህዛብ ይገልጣል።

፲፪ አዎን፣ አባቴ አህዛቦችን በሚመለከ ትና የእስራኤልን ቤት በሚመለከት፣ እነ ርሱንም ልክ ቅርንጫፎቹ እንደወደበቁት ᵐወይራ ዛፍ በመነፃፀረና በምድር ላይ ሁሉ ᶮመበታተን እንደሚገባቸው ብዙ ተናገረ።

፲፫ የጌታ ቃል ይፈፀም ዘንድ፣ በምድር ላይ ሁሉ መበተን አለብን፣ ስለዚህ እኛ ወደ ᵐቃልኪዳኑ ምድር በአንድነት ሆነን መሔድ እንደሚያስፈልገን ተናገረ።

፲፬ እናም የእስራኤል ቤቶች ከተበተኑ በኋላ እንደገና በአንድ ላይ ᵐመሰብሰብ አለ ባቸው፤ ወይም ᶮአህዛብ የወንጌልን ሙሉ ነት ከተቀበሉ በኋላ፣ ᵒየወይራው ዛፍ ተፈ ጥሮአዊ ቅርንጫፎች፣ ወይም በአጠቃላይ የእስራኤል ቤት ቅሪት ይጣበቃሉ፣ ወይም የእነርሱ መድሐኒትና ጌታ ወደሆነው እው ነተኛ መሲሕ እውቀት ይመጣሉ።

፲፭ እናም አባቴ በዚህ አይነት አነጋገር ተነበየ፣ እንዲሁም ለወንድሞቼና በዚህ መፅሐፍ ላይ ያልጻፍኳቸውን ሌሎች ብዙ ነገሮች ተናገረ፣ እኔ ግን ለእኔ የሚያስፈ ልጉኝን ነገሮች ᵐበሌላኛው የራሴ መፅሐፍ ፅፌአለሁ።

፲፮ እናም እነዚህ ሁሉ እኔ የተናገርኳቸው ነገሮች የተደረጉት አባቴ በልሙኤል ሸለቆ በድንኳን ተቀምጦ ሳለ ነበር።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊ የአባቴን ᵐቃላት ሁሉ ከሰማሁ በኋላ፣ እርሱ ᶮበራ ዕይ ስላያቸው ነገሮችና ደግሞ በእግዚአ ብሔር ልጅ ባለው እምነት በተቀበለው መንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለተናገራቸው ነገ ሮች፤ እናም የእግዚአብሔር ልጅ የሚመ ጣው የእግዚአብሔር ልጅ ᵒመሲሁ ነው፤

፯ ᵐ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
፯ ᶮ ፩ ነፊ ፲፩፡ ፳፯፤ ፪ ነፊ ፴፩፡ ፴።
፰ ᵐ ኢሳ. ፴፡ ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፣ ።
፱ ᵐ ዮሐ. ፩፡ ፳፰
ᶮ ቅ.መ.መ. መጥምቁ ዮሐንስ።
፲ ᵐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
፲፩ ᵐ ሞር. ፭፡ ፲፡
ᶮ ያዕቆ. ፡ ፣ ።
ᵒ ቅ.መ.መ. መሰቀል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ።
ᵖ መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ᵐ ሠ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፲፪ ᵐ ᵐ ዘፍጥ. ፴፱፡ ፳፪–፳፭፤ ፩ ነፊ ፲፭፡ ፲፪፤ ፪ ነፊ ፣ ያዕቆ. ፭፤ ፯፡ ፩–፯፤ ቅ.መ.መ. የወይራ ዛፍ፤ የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ᶮ ፩ ነፊ ፳፪፡ ፣–፳።
ᶮ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የተበተኑት እስራኤል።
፲፣ ᵐ ᵐ ፩ ነፊ ፪፡ ፳።
ᶮ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፲፡ ᵐ ᶮ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የእስራኤል መሰብሰብ።
ᶮ ᵐ ፩ ነፊ ፲፣፡ ፳፪፤ ት. እና ቃ. ፲፡ ፣ ።
ᵒ ያዕቆ. ፭፡ ፳፡ ፶፪፣ ፶፡ ፣ ።
፲፭ ᵐ ᵐ ፩ ነፊ ፩፡ ፲፯–፲፰።
፲፯ ᵐ ᵐ ኢኖስ ፩፡ ፣ አልማ ፴፯፡ ፣ ።
ᶮ ᵐ ፩ ነፊ ፣ ።
ᵒ ቅ.መ.መ. መሲህ።

እኔም፣ ኔፊ ደግሞ Ꮎበትጋት እርሱን ለፈ
ለጉት ሁሉ እንደ Ꮎጥንት ጊዜው አሁንም
ቢሆን እራሱን ለሰው ልጆች በሚገልጥበት
በእግዚአብሔር ስጦታ Ꮏበመንፈስ ቅዱስ
ኃይል እነዚህን ነገሮች እመለከት እንዲ
ሁም እሰማና አውቅ ዘንድ ፈለግሁ።

፲፰ እርሱ ትናንትም ዛሬም እስከዘለዓለም
ᏽያው ነውና፤ ንስህ የሚገቡና ወደ እርሱ
የሚመጡ ከሆነ፣ መንገዱ ከዓለም መፈጠር
ጀምሮ ለሰዎች ሁሉ ተዘጋጅቷል።

፲፱ በትጋት የሚፈልግ ያገኛልና፣ የእግ
ዚአብሔር ᏽሚስጥሮች ለእነርሱ እንደጥ
ንቱም ጊዜ ቢሆን በሚመጡትም ጊዜያት
ᏽበመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለጥላቸዋል፣
ስለዚህ፣ የጌታ ᏽመንገድ አንድ ዘለዓለማዊ
ዙሪያ ነው።

፳ ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፣ አስታውስ፣
ለሥራህ ሁሉ ᏽወደፍርድ ትቀርባለህና።

፳፩ ስለዚህ ᏽበሙከራ ዘመንህ መጥፎ ነገ
ሮችን ማድረግ ከፈለግህ በእግዚአብሔር
የፍርድ ወንበር ፊት ᏽሳትፀዳ ትገኛለህ፣
እናም ምንም እርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር
ጋር ሊኖር አይቻለውም፣ ስለዚህ ለዘለዓ
ለም ትጣላለህ።

፳፪ እናም መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች
እናገርና እንዳልደብቃቸው ዘንድ ስልጣን
ሰጥቶኛል።

ምዕራፍ ፲፩

*ኔፊ የጌታን መንፈስ አየ እና የህይወት ዛፍ
በራዕይ ታየው—እርሱም የእግዚአብሔ
ርን ልጅ እናት አየ እናም ስለእግዚአብ
ሔር ትህትና ተማረ—እርሱም የእግዚአ
ብሔርን በግ ጥምቀት አገልግሎትና ስቅ
ለት አየ—እናም ደግሞ የአስራ ሁለቱን
የበጉን ሐዋርያት ጥሪና አገልግሎት አየ።
ከ፯፲–፰፲፯፲ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ያየውን ነገ
ሮች ለማወቅ ከፈለግሁ በኋላ፣ እናም ጌታ
ሊያሳውቀኝ እንደሚችል በማመን በልቤ
ᏽእያሰላሰልኩ ተቀምጬ ሳለሁ በጌታ መን
ፈስ፣ አዎን፣ በፊት አይቼው ወደማላውቀ
ውና ከዚህ በፊት በእግሮቼ ቆሜበት ወደ
ማላውቀው እጅግ ከፍ ያለ ᏽተራራ ᏽተወ
ሰድኩ።

፪ እነሆ መንፈስ፣ ምን ትፈልጋለህ?
አለኝ።

፫ እና እኔም አልሁ፥ አባቴ ᏽያያቸውን ነገ
ሮች ማየት እፈልጋለሁ።

፬ እና መንፈስም አለኝ—አባትህ የተናገ
ረውን ᏽዛፍ እንዳየ ታምናለህን?

፭ እናም እኔ አልኩ—አዎን፣ የአባቴን
ቃላት በሙሉ ᏽእንደማምን አንተ ታው
ቃለህ።

፮ እናም እነዚህን ቃላት ስናገር መን
ፈስ በታላቅ ድምፅ እንዲህ ሲል ጮኸ፥
ሆሳዕና ለጌታ ለልዑል እግዚአብሔር፤
እርሱ ᏽበምድር ሁሉ ላይ፣ አዎን፣ ከሁ
ሉም በላይ አምላክ ነው። እናም አንተ፣
ለ ሮሜ ፲፭፡፲፪፤ ት. እና ቃ. ፻፲፫፡፭–፮።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፭፡፱–፲።
መ ወይም ለእርሱ።
፲፩ ᵇ ፪ ኔፊ ፮፡፲፡፤ ፳፭፡፲፯፤ ፳፱፡፩።
፲፪ ᵇ ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ᵃ ኔፊ ፲፭፡፲፭፤ ፲፯፡፩–፩።
ሐ ነህ. ፩፡፱፤ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳፪–፳፭። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፫ ᵇ ኤር. ፫፡፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ።
ሐ በይሁዳ እና ኤፍሬም የተመሩት ጎሳዎች (በ፩ ነገሥ. ፲፪፡፲፯–፳ ድርጊት በኋላ) በታሪክ ጠላቶች ነበሩ። በኋለኛው ቀናት ይህ ጥላቻ ይጠገናል። ሕዝ. ፴፯፡፲፯–፳፪። ቅ.መ.መ. ቅናት።
፲፬ ᵇ ይህም የፍልስጤማውያን ግዛት የሆኑትን በምዕራብ ዳገታማ አቀበተ ማለት ነው።
፲፭ ᵇ ዘካ. ፲፡፲፩።
፲፮ ᵇ ኢሳ. ፴፭፡፰፤ ፹፡ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፳፯።
፳፪ ᵇ ᵃ ኤሳ. ፴፭፡፰፤ ፹፡ ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፳፯።
ᵇ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
ᵇ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፭ ᵇ ት. እና ቃ. ፻፴፯፡፳፯።

ሰርቶአልና፤ ይህም በምድር ሁሉ ታው ቋል።

፮ በፅዮን የምትኖሩ ሁሉ ᐟጩሁ፣ እል ልም በሉ፤ በመካከላችሁ ያለው የእስራኤሉ ቅዱስ ታላቅ ነውና።

ምዕራፍ ፳፫

የባቢሎን ጥፋት በዳግም ምፅአት የሚኖ ረው ጥፋት ምልክት ነው—የቁጣና የበቀል ቀን ይሆናል—ባቢሎን (አለም) ለዘለዓ ለም ትወድቃለች—ኢሳይያስ ፲፫ን አነ ጻፅሩ። ከ፳፻፱፱–፳፻፷፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ የአሞፅ ልጅ ኢሳይያስ የተመለከተው ᐟየባቢሎን ᐟሸክም።

፪ ከፍ ባሉ ተራራ ላይ ᐟአርማን አቁሙ፣ ድምፃችሁንም ወደ እነርሱ ከፍ አድርጉ፣ ወደ ልዑላት ደጃፍ ይሄዱ ዘንድ ᐟጠቁሙ አቸው።

፫ ᐟቅዱሳኖቼን አዝዤአለሁ፣ ኃያላኖች ንም ጠርቻቸዋለሁ፣ ቁጣዬ በእኔ ታላቅነት በሚደሰቱት ላይ አይደለችምና።

፬ በተራሮቹ ያሉት ህዝቦች ጩኸት እንደ በርካታ ሰዎች ነው፣ ከመጠን በላይ የሚ ንጫጩ ሀገሮች ᐟመንግስታት ተከማችተ ዋል፣ የሰራዊት ጌታ የጦር ሰራዊቱን ᐟይሰ በስባል።

፭ እነርሱ፣ አዎን፣ ጌታ እና የእርሱ የቁጣው መሳሪያ ምድርን ሊያጠፉት ከሩቅ ሀገር፣ ከሰማይ ዳርቻም መጥተዋል።

፮ የጌታ ቀን ቀርባለችና አልቅሱ፤ ሁሉን ከሚገዛ እንደጥፋት ትመጣለች።

፯ ስለዚህ ሁሉም እጆች ይዝላሉ፣ የሁ ሉም ሰዎች ልብ ትቀልጣለች።

፰ እናም እነርሱ ይፈራሉ፣ ኃይለኛ ህመ ምና ሀዘንም ይይዛቸዋል፤ አንዱም በሌላው ይደነቃል፤ ፊቶቻቸው በእፍረት እንደነበ ልባል ይሆናሉ።

፱ እነሆ፣ ጨካኝ በሆነ ቁጣና ከኃይለኛ ንዴት ጋር ምድርን ባድማ ሊያደርጋት የጌታ ቀን ይመጣል፤ ኃጢአተኞችንም ከውስጧ ᐟያጠፋል።

፲ የሰማይ ከዋክብትና ህብር ከዋክብቶች ብርሃናቸውን አይሰጡም፤ ᐟፀሐይም በወ ጣች ጊዜ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብር ሃኗን አትሰጥም።

፲፩ እናም ዓለምን በመጥፎ ስራዋ፣ ክፉዎ ችንም ለግፍ ስራቸው ᐟእቀጣለሁ፤ ᐟየትዕ ቢተኞችንም ኩራት አስቆማለሁ፣ የጨካ ኞችንም ኩራት አዋርዳለሁ።

፲፪ ᐟሰውንም ከነጠረ ወርቅ የበለጠ የከበረ አደርገዋለሁ፤ ሰውም ከኦፌር ወርቅ ይልቅ የከበረ ይሆናል።

፲፫ ስለዚህ፣ በሰራዊት ጌታ መዐት እናም በታላቁ ቁጣው ቀን እኔ ሰማያትን አናውጣ ለሁ ምድርንም ከቦታዋ ᐟፈቀቅ አደርጋ ታለሁ።

፲፬ እናም ᐟእንደሚሳደድ ድብ፣ ማንም ሰው እንደማይሰበስባቸው በጎች ይሆናሉ፤ እናም ሁሉም ሰው ወደ ራሱ ህዝብ ይዞ ራል፣ እናም ሁሉም ወደ ራሱ ምድር ይሸ ሻል።

፲፭ የሚኮራ ሰው ሁሉ ይወጋል፣ አዎን፣ ከኃጢአተኞች የተቀላቀለ ሰው ሁሉ በሰ ይፍ ይወድቃል።

፲፮ ልጆቻቸውም በዐይኖቻቸው ፊት ይከ ሰከሳሉ፤ ቤቶቻቸው ይበዘበዛል፣ ሚስቶቻ ቸውም ይደፈራሉ።

፲ *ሀ* ኢሳ. ፶፬፡፩፣ ፭፣ ሶፎ. ፫፡፲፬።
፳፫ ፩ *ሀ* በኢሳ. ፲፫ እና ፲፬ ውስጥ ስለኃጢያተኛዋ ባቢሎን የታሪክ ጥፋት የተተነበየው እንደ አለም በሙሉ መጥፋት ምሳሌ ነው። ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፭፣ ፮፣ ፯፣ ፲፩። ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
ለ ይህም የጥፋት መልእክት ማለት ነው።
፪ *ሀ* ወይም ምልክት። ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ይህም እጅን ማውለብለብ፣ ምልክት መስጠት ማለት ነው።
፫ *ሀ* ይህም ቅዱሳን ማለት ነው።
፬ *ሀ* ዘካ. ፲፬፡፪–፫።
ለ ዘካ. ፲፪፡፫።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
፲፩ *ሀ* ሚል. ፬፡፩።
ለ ት. እና ቃ. ፷፬፡፷፬።
፲፪ *ሀ* ኢሳ. ፬፡፩–፬።
፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።
፲፬ *ሀ* ወይም የተዳነ አጋዘን።

፲፯ እነሆ፣ ብር እና ወርቅ የማይሹት ንና በዚህም የማይደሰቱትን ሜዶናውያ ንን በላያቸው አስነሳለሁ።

፲፰ ፍላፃዎቻቸውም ወጣቶቻቸውን ይጨፈጭፏቸዋል፤ ለማህፀኑም ፍሬ ምህ ረት አይኖራቸውም፤ ዐይኖቻቸውም ህፃ ናትን በህይወት አይተዉም።

፲፱ እናም የመንግስታት ክብር፣ የከለዳ ውያን ᵇቆንጆ ክቡር የሆነችው ባቢሎን እግዚአብሔር ᵃሰዶምንና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደነበረ ትሆናለች።

፳ ለዘለዓለም ᵇየሚቀመጥባት አይገኝም፣ ከትውልድ እስከትውልድም የሚኖርባት አይኖርም—አረባውያንም ቢሆኑ ድንኳ ኑን በዚያ አይተክልም፤ እረኞችም ቢሆኑ እንኳ መንጋቸውን በዚያ አያሰማሩም።

፳፩ ነገር ግን የበረሃ ᵇየዱር አራዊት በዚያ ያርፋሉ፤ ሰንኖችም ቤቶቻቸውን ይሞሉ ታል፣ ጉጉቶችም በዚያ ይኖራሉ፤ ᵃአጋ ንንትም በዚያ ይጨፍራሉ።

፳፪ እናም የደሴቶቹ አውሬዎች በባዶ ᵇቤቶቻቸው፣ ᵃቀበሮዎችም በአስደሳች ስፍራዎቻቸው ይጮሃሉ፤ እናም ጊዜዋ ቀርቧል፣ ቀኗም አይራዘምም። እኔ በፍ ጥነት አጠፋታለሁና፤ አዎን፣ እኔ ለህዝ ቦቼ መሃሪ እሆናለሁና፣ ነገር ግን ኃጢአ ተኞች ይጠፋሉ።

ምዕራፍ ፳፯

እስራኤል ትሰበሰባለች፣ የሺህ ዓመት እረ ፍትን ትደሰትበታለች—ሉሲፈር በአመፅ ምክንያት ከሰማይ ተጥሏል—እስራኤል ባቢሎንን (ዓለምን) ድል ታደርጋታ ለች—ኢሳይያስ ፲፬ን አነጻፅሩ። ከ፩ የ፻፱–፩ የ፻፴፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ጌታ በያዕቆብ ላይ ምህረቱን ያወር ዳልና፣ በድጋሚም እስራኤልን ᵇይመር ጣል፣ በራሳቸውም ምድር ላይ ያኖራቸ ዋል፤ ᵃእንግዳዎቹም ከእነርሱ ጋር ይገና ኛሉ፣ ከያዕቆብም ቤት ጋር ይጣበቃሉ።

፪ ᵇእናም ህዝቡ ይዘው ወደ ራሳቸው ቦታ ያመጧቸዋል፤ አዎን፣ ከሩቅም እስከም ድር ዳርቻም፤ እናም ወደ ᵃቃል ኪዳን ምድራቸውም ይመለሳሉ። የእስራኤልም ቤት ባለቤት ያደርጓቸዋል፣ እናም የጌታ ምድር እንደ ወንድና ሴት ᵃገረዶች ይሆ ናሉ፤ የማረኩአቸውንም ይማርካሉ፤ እናም ጨቋኞቻቸውን ይገዛሉ።

፫ እናም በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል ጌታ ከሀዘናችሁ፣ ከፍርሃታችሁም፣ እናም ከአ ስከፊው እንድታገለግሉ ከተደረጋችሁባት ባርነት ᵇእረፍት ይሰጣችኋል።

፬ እናም በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ይህ ንን ምሳሌ ᵇበባቢሎን ንጉስ ላይ አንስታ ችሁ እንዲህ ትላላችሁ—አስጨናቂው እን ዴት ፀጥ አለ፣ ወርቃማዋስ ከተማ እንዴት አረፈች!

፭ ጌታ የኃጥአንን በትር፣ የመሪዎችንም ዘንግ ሰብሯል።

፮ ህዝቡን ያለማቋረጥ በጭካኔ የመታ፣ ሀገሮችን በቁጣ የመራ፣ ስደት ይሆንበ ታል፣ እናም ማንም አያስጥለውም።

፯ መላው ምድር እረፍት ላይ ነው፣ ፀጥታም ሆኖአል፣ ᵇበዝማሬም ተነስተዋል።

፰ አዎን፣ ᵇጥድና የሊባኖስ ዝግባ አንተ ᵃከተጋደምክ ጀምሮ ማንም ᵃይቆርጠን

፲፱ ᵇ ይህም ከንቱነት ማለት ነው።
ᵃ ዘፍጥ. ፲፱፡፳፭–፳፭፤ ዘዳግ. ፳፱፡፳፫፣ ፪ ኔፊ ፲፫፡፱።
፳ ᵇ ኤር. ፶፡፣ ፣ ፴፱–፴።
፳፩ ᵇ ኢሳ. ፴፡፲–፲፭።
ᵃ ዕብ. ፈየሎቹ፣ ወይም ጋኔን።
፳፪ ᵇ ዕብ. ቤተ መንግስት።
ᵃ ዕብ. (ምናልባት) ቀበሮ፣ ወይም የዱር ውሻዎች።
፳፭ ᵃ ᵇ ዘካ. ፩፡፲፯።
ᵃ ኢሳ. ፳፡፣ ፣–፭፣ ፲።
ᵇ ᵇ ይህም ሌሎች ሀገሮች እስራኤልን ይረዳሉ ማለት ነው።
ᵃ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
ᵃ ኢሳ. ፳፡፲፬።
፲ ᵇ ᵃ ኢያ. ፩፡፲፣ ት. እና ቃ. ፲፡፭፡ ፳፭።
፪ ᵇ ᵃ ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
፯ ᵇ ᵃ ኢሳ. ፶፭፡፲፪።
፰ ᵇ ᵃ ዕብ. ሳይፕረስ።
ᵃ ይህም በሞት ውስጥ ማለት ነው።
ᵃ ᵃ ዕብ. የ(ዛፍ) ቆራጩ በእኛ ላይ አልመጣም።

ዘንድ አልመጣብንም ብለው በአንተ ደስ
አላቸው።
፱ ᵐሲኦል ከበታች አንተ በመምጣትህ
ልትገናኝህ ታወከች፤ ᵃየሞቱትንም የም
ድር ታላላቆች ለአንተ አንቀሳቀሰች፤ የሃገ
ሮችን ነገስታቶች ሁሉ ከዙፋኖቻቸው ለአ
ንተ አስነሳች።
፲ ሁሉም ይናገራሉ ለአንተም እንዲህ
ይላሉ—አንተም ደግሞ እንደ እኛ ደካማ
ሆንክን? አንተ ልክ እንደ እኛ ሆንክን?
፲፩ ውበትህ ወደ መቃብር መጥቷል፤
የበገናህም ድምፅ አይሰማም፤ ብል ከበታ
ችህ ተነጥፏል፣ ትልም ይሸፍንሃል።
፲፪ አቤቱ ᵐሉሲፈር፣ አንተ የንጋት ልጅ
ሆይ! ᵃእንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አንተ ሀገ
ሮችን ያዋረድክ፣ እንዴት ከምድር በታች
ተቆረጥህ!
፲፫ አንተም በልብህ ወደ ሰማይ ᵐአርጋ
ለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክ
ብት በላይ አደርጋለሁ፤ ᵃበሰሜን ዳርቻም
በመሰብሰቢያውም ተራራ ደግሞ እቀመ
ጣለሁ፤
፲፬ ከደመናዎችም ከፍታ በላይ አርጋለሁ፤
እንደ ልዑልም እሆናለሁ ብለሃል።
፲፭ ነገር ግን ወደ ሲያል፣ ወደጥልቁም
ᵐጉድጓድ ትወርዳለህ።
፲፮ የሚያዩህም ᵐያተኩሩብሃል፣ ያስተ
ውሉሀልም፣ እናም ይላሉ—ምድርን ያን
ቀጠቀጠ፣ መንግስታትን ያናወጠ ሰው ይህ
ነውን?
፲፯ እናም ዓለምን ምድረበዳ ያደረገ፣
ከተሞቿንም ያጠፋ፣ የእስረኞቹንም በር
ያልከፈተው ይህ እርሱ አይደለምን?
፲፰ የሁሉም ሀገሮች ንጉሶች፣ አዎን፣
ሁላቸውም፣ እያንዳንዳቸውም ᵐበየቤታ
ቸው በክብር አንቀላፍተዋል።
፲፱ ነገር ግን አንተ ᵐእንደረከሰ ቅርን
ጫፍ፣ በሰይፉም ተወግተው እንደተገደ
ሉት፣ ወደ ጉድጓዱ ᵃድንጋዮች አዘቅት
እንደወረዱት ቅሪቶች በእግሮች ስር እን
ደተረገጠም ሬሳ ከመቃብርህ ተጥለሃል።
፳ ምድርህን አጥፍተሀልና ህዝብህንም
ገድለሀልና፣ ከእነርሱ ጋር በመቃብር አንድ
አትሆንም፣ ᵐየክፉ አድራጊዎች ᵃዘር በፍ
ፁም አይከበርም።
፳፩ እንዳያንሰራሩም ምድሪቷንም እንዳ
ይዙ፣ የምድርንም ገፅ በከተሞቻቸው እን
ዳይሞሉ፣ በአባቶቻቸው ᵐኃጢያት ምክን
ያት ልጆቹን ለማድያ አዘጋጁ።
፳፪ እኔም በእነርሱ ላይ እነሳለሁ ይላል
የሰራዊት ጌታ፣ እናም ከባቢሎን ᵐስምና
ቅሪት ዘርንና ወንድ ልጅንና ᵃየወንድምን
ወይም የእህትን ልጅ እቆርጣለሁ ይላል
ጌታ።
፳፫ የጃርት ᵐመኖሪያ የውሃም መቆሚያ
አደርጋለሁ፤ በጥፋትም ᵃመጥረጊያ እጠ
ርጋታለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ።
፳፬ የሰራዊት ጌታ እንዲህ ሲል ምሏል—
በእርግጥም እኔ እንዳቀድኩት ይሆናል፤ እኔ
እንደወሰንኩትም ይቆማል—
፳፭ ᵐአሶርን በምድሬ አመጣታለሁ፣
ᵃበተራራዬም ላይ በእግሬ ስር እረግጠዋ

፱ ᴴ ቅ.መ.መ. ሲያል።
ᵃ ይህም ሰውነት የሌላቸው
መንፈሶች ማለት ነው።
፲፪ ᴴ ዕብ. የንጋት ኮከብ፣ የጠዋት
ልጅ። የክፉ አለም (ባቢሎን)
ገዢ እንደ አጥቢያ ኮከብ፣
የክፉዎች ሁሉ ገዢ ይባላል።
ቅ.መ.መ. አጥቢያ ኮከብ፣
ዲያብሎስ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፯።
፲፫ ᴴ ሙሴ ፬፡፭–፬።
ᵃ ይህም በባቢሎን እምነት
መሰረት አምላኮች
የሚኖሩበት ማለት ነው።
መዝ. ፵፰፡፪።
፲፭ ᴴ ፩ ኔፊ ፲፡፣ ፫።
፲፮ ᴴ ዕብ. አይን በአንተ ላይ
እጨፍናለሁ እናም በአንተ
ላይ አስተውላለሁ።
፲፰ ᴴ ይህም በቤተሰቡ መቃብር
ማለት ነው።
፲፱ ᴴ ይህም የተወገደ፣ የተከረከመ
እና የተጣለ ቅርንጫፍ ማለት
ነው።
ᵃ ይህም ከሁሉም በታች ማለት
ነው።
፳ ᴴ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ᵃ መዝ. ፳፭፡፣ ፲–፲፭፣ ፴፯፡፳፰።
፳፩ ᴴ ዘፀአ. ፳፡፭።
፳፪ ᴴ ምሳ. ፣፡፯።
ᵃ ኢዮብ ፲፰፡፲፱።
፳፫ ᴴ ኢሳ. ፴፡፣ ፲፭–፲፰።
ᵃ ወይም መጥረጊያ።
፳፭ ᴴ ርዕሱ ወደ አሶር ጥቃት
እና ወደ ይሁዳ መውደቅ፣
በ፯፻ ም.ዓ.፣ ተለወጠ
(ቁጥር ፳፭–፳፯)።
፪ ነገሥ. ፲፱፡ ፴፪–፴፯፣
ኢሳ. ፴፯፡ ፴፣–፴፰።
ᵃ ይህም የይሁዳ እና
የእስራኤል ተራራዎች
ማለት ነው።

ለሁ፤ ከዚያም ሐቀንበሩ ከእነርሱ ላይ ይወ
ርዳል፣ ሸክሙም ከትከሻቸው ይወርዳል።
፳፤ በምድር ላይ ሁሉ የታቀደው ዕቅድ
ᵐይህ ነው፤ እናም በሃገር ሁሉ ላይ የተዘረ
ጋው እጅ ይህ ነው።
፳፣ የሰራዊት ጌታ ይህንን አቅዶአል፣
የሚያከሽፈውስ ማነው? እጁም ተዘርግታ
ለች የሚያስመልሳትስ ማነው?
፳፪ ንጉስ ᵐአካዝ በሞተበት ᵃዘመን ይህ
ሸክም ነበር።
፳፫ እናንተ ፍልስጤም ደስ አይበላችሁ፣
ምክንያቱም እናንተን የመታው በትሩ ተሰ
ብሯል፤ ከእባቡ ስር እፉኝት ይመጣል፣
ፍሬውም የሚበር ቁጡ እባብ ይሆናል።
፳፬ እናም የድሆች በኩር ይመገባል፣ ችግ
ረኞችም በሰላም ይኖራሉ፤ እኔም ስራችሁን
በረሃብ እገድላለሁ፣ እርሱ ደግሞ ቅሪቶቻ
ችሁን ይገድላል።
፳፭ አንተ መግቢያ ሆይ ወዮ በል፤ አንቺ
ከተማ ሆይ አልቅሺ፤ ፍልስጤም ሁላች
ሁም ቀልጣችኋል፤ ጢስ ከሰሜን ይመ
ጣልና፣ እናም በእርሱ ቀነ ቀጠሮ ጊዜያት
ማንም ብቸኛ አይሆንም።
፳፮ እንግዲህ ለሀገር መልዕክተኞች ምን
ይመለሳልን? ጌታ ᵐዕዮንን እንደመሰረ
ተና፣ የሀገሮቹም ᵃድሆች በውስጧ ᵐእን
ደሚጠጉ ነው።

ምዕራፍ ፳፭

ኔፊ በግልፅነት ይደሰታል—የኢሳይያስ ትንቢቶች በመጨረሻው ዘመናት ግልፅ ይሆናሉ—አይሁድ ከባቢሎን ይመለ ሳሉ፣ መሲሁንም ይሰቅላሉ፣ እናም ይበ ተናሉ፣ ይቀሰፋሉም—በመሲሁ ሲያ ምኑ ደግመው ይመለሳሉ—በመጀመሪያ ሌሂ ኢየሩሳሌምን ከለቀቀ ከስድሰት መቶ አመት በኋላ ይመጣል—ኔፋውያን የሙ ሴን ህግ ይጠብቃሉ፣ የእስራኤሉ ቅዱስ በሆነው ክርስቶስም ያምናሉ። ከ፳፪፣፳፭–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን እኔ ኔፊ፣ በኢሳይያስ አፍ ስለተ
ነገሩት፣ እኔ ስለፃፍኳቸው ቃላት በመጠኑ
እናገራለሁ። እነሆም ኢሳይያስ ለብዙ ህዝ
ቦቼ ለመረዳት ᵐአስቸጋሪ የሆኑ ብዙ ነገሮ
ችን ተናግሯል፤ እነርሱም በአይሁድ መካ
ከል ስላለው በትንቢት አነጋገር አያውቁ
ምና።
፪ እኔ ኔፊ ስለአይሁዶች አኳኋን ብዙም
አላስተማርኳቸውምና፤ ᵐስራዎቻቸው
የጨለማ ስራ፣ አድራጎታቸውም የእርኩ
ሰት አድራጎት ነበሩና።
፫ ስለዚህ፣ ለህዝቦቼም ሆነ ከዚህ በኋላ
እነዚህን የምፅፋቸውን ለሚቀበሉ ሁሉ፣
የእግዚአብሔርን ፍርድ፣ በሁሉም ሀገሮች
ላይ እርሱ በተናገረው ቃል መሰረት እንደ
ሚመጡ ያውቁ ዘንድ ይህንን እፅፋለሁ።
፬ ስለዚህ፣ የእስራኤል ቤት የሆናችሁ
ህዝቤ ሆይ፣ አዳምጡኝ፣ ቃላቶቼንም
ለመስማት ጆሮአችሁን ስጡ፣ የኢሳይያስ
ቃላት ለእናንተ ግልፅ አይደሉም፣ ይሁን
እንጂ ᵐበትንቢት ᵃመንፈስ ለተሞሉት ሁሉ
ግልፅ ናቸው። ነገር ግን እኔ በውስጤ ባለው
መንፈስ መሰረት ይህንን ትንቢት እሰጣች
ኋለሁ፤ ስለዚህ ከአባቴ ጋር ኢየሩሳሌምን
ለቅቄ ከወጣሁ ጊዜ ጀምሮ ባለኝ ᵐግልፅነት
እተነብይላችኋለሁ፤ እነሆም ህዝቦቼ ይማሩ
ዘንድ ነፍሴ በግልፅነት ትደሰታለች።
፭ አዎን፣ ነፍሴ ᵐበኢሳይያስ ቃላት ትደ

፳፭ *ሐ* ኢሳ. ፲፡፳፯።
፳፯ *ሀ* ይህም በመጨረሻ አለማዊ
ሀገሮች በሙሉ እንደዚህ
ይጣላሉ ማለት ነው።
፳፰ *ሀ* ፪ ነገሥ. ፲፯፡፳።
ለ ይህም በ፯፻፳ ም.ዓ.
አካባቢ፣ ይሁዳ የተጠበቁ
ሲሆኑ፣ የተተነበየው ሸክም
ወይም የውድቀት መልእክት
ስለፍልስጤማውያን ነበር
ማለት ነው።
፳፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ሶፎ. ፫፡፲፪።
ሐ ወይም በዚህ ውስጥ
መሸሸጊያን ፈልግ
ማለት ነው።
፳፭ ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፭፡፭–፯።
፪ *ሀ* ፪ ነገሥ. ፲፯፡፲፫–፳።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትንቢት፣
መተንበይ።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፭፡፫፣ ፳፫፡፭፣
ያዕቆ. ፬፡፲፫።
፭ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡፳፣
፫ ኔፊ ፳፫፡፩።

ሰታለች፣ እኔ ከኢየሩሳሌም ወጥቻለሁና፣ አይኖቼም ^የአይሁዶችን ነገር አይታለች፣ እናም አይሁድ የነቢዩን ነገሮች እንደተረዱት አውቃለሁ፣ እናም በአይሁዶች ጉዳይ የተማሩ ካልሆኑ በስተቀር ለአይሁዶች የተነገሩትን ነገሮች ከራሳቸው በቀር የሚረዳው ማንም የለም።

፮ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እኔ ኔፊ፣ ልጆቼን የአይሁድ ጉዳዮችን አላስተማርኳቸውም፤ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ራሴ፣ በኢየሩሳሌም ኖሬአለሁ፣ ስለዚህ በዙሪያዬ ስለነበሩት ክልሎች በተመለከተ አውቃለሁ፤ ለልጆቼም ኢሳይያስ በተናገረው ሁሉ መሰረት በአይሁድ መካከል *ሊመጣ ስላለውም የእግዚአብሔር ፍርድ ለልጆቼ ገልጬላቸዋለሁ፣ እናም እኔ አልፅፋቸውም።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ *በግልፅነቴ መሰረት የራሴን ትንቢት እቀጥላለሁ፤ በዚህም ማንም ሰው እንደማይሳሳት አውቃለሁ፣ ይሁን እንጂ፣ የኢሳይያስ ትንቢት በሚፈፀምበት ጊዜ፣ ሆነውም ሲያልፉ፣ ሰዎች እርግጠኛነቱን ያውቃሉ።

፰ ስለዚህ፣ ለሰው ልጆች *ጥቅም አላቸው፣ እናም አይኖራቸውም ብሎ የሚያስብ፣ እኔ እነርሱን በተለይ እናገራቸዋለሁ፣ እናም ^ለህዝቤ ብቻ ቃሉን እናገራለሁ፤ ምክንያቱም ^በመጨረሻ ቀናት ለእነርሱ ታላቅ ዋጋ እንደሚኖራቸው አውቃለሁ፤ በዚያ ቀንም ይረዱአቸዋልና፣ ስለሆነም፣ ለጥቅማቸው ፅፌአቸዋለሁና።

፱ እናም በክፉታቸው የተነሳ ከአይሁዶች መካከል *እንደጠፋው አንድ ትውልድ፣ እንደ ክፉታቸው እነርሱም ከትውልድ እስከ ትውልድም ሊጠፉ ችለዋል፤ እናም በጌታ ነቢያት አማካኝነት ^አስቀድሞ ካልተነገረላቸው በስተቀር ማናቸውም አልጠፉም።

፲ ስለሆነም፣ አባቴ ኢየሩሳሌምን ከለቀቀ ወዲያው በእነርሱ ላይ የሚመጣባቸውን ጥፋት በተመለከተ ተነግሯቸዋል፤ ይሁን እንጂ፣ እነርሱ ልባቸውን አጠጡ፤ እናም በትንቢቴ መሰረት ወደ ባቢሎን በምርኮ *ከተወሰዱት በስተቀር ሌሎች ^ጠፍተዋል።

፲፩ እናም አሁን ይህን የምናገረው በውስጤ ባለው መንፈስ የተነሳ ነው። እናም እነርሱ ቢወሰዱም እንኳን እንደገና ይመለሳሉ፣ የኢየሩሳሌምን ምድርንም ይወርሳሉ፤ ስለሆነም፣ ወደ ርስት ምድራቸው *እንደገና ይመለሳሉ።

፲፪ ነገር ግን፣ እነሆ፣ ጦርነትና የጦርነት ወሬዎች በመካከላቸው ይኖራቸዋል፤ እናም የአብ *አንድያ ልጅ፣ አዎን፣ የሰማይና የምድር አባት የሆነውም እንኳን፣ በስጋ እራሱን የሚገልፅበት ቀን በሚመጣበት ጊዜ፣ እነሆ፣ በክፋታቸውና በልባቸው ጠማርነት እንዲሁም በአንገተ ደንዳናነታቸው ምክንያት አይቀበሉትም።

፲፫ እነሆ፣ *ይሰቅሉታል፤ እናም ከድን ጋይ ከተወቀረው ^መቃብር ውስጥ ^ለሶስት ቀን ከቆየ በኋላ፣ ፈውስን በክንፎቹ ይዞ ከሙታን *ይነሳል፤ እናም በስሙ የሚያምኑ ሁሉ በእግዚአብሔር መንግስት ይድናሉ። ስለሆነም፣ ነፍሴ እርሱን በተመለከተ ለመተንበይ ትደሰታለች፣ ቀኖቹን *አይቻለሁና፣ ልቤም ቅዱስ ስሙን ታመሰግናለች።

፭ *ለ* ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
፮ *ሀ* ፪ ኔፊ ፮፡፳፣
ሐሌ. ፳፡፳–፳፩።
፯ *ሀ* ፪ ኔፊ ፴፪፡፯፣
አልማ ፲፫፡፳፫።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት—የቅዱሣት
መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ኢኖስ ፩፡፲፫–፲፮፣
ሞር. ፭፡፲፪–፲፭፣
ት.እና ቃ. ፫፡፲፮–፳።
ሐ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣
የኋለኛው ቀናት።
፱ *ሀ* ኤር. ፴፱፡፱–፲፣
ማቴ. ፳፫፡፣ ፴፯–፴፰።
ለ ዓሞ. ፫፡፯፣
፩ ኔፊ ፩፡፲፫።
፲ *ሀ* ፪ ነገሥ. ፳፭፡፱፣ ፲፰፣
ኤር. ፶፪፡፫–፲፯።
ለ ፩ ኔፊ ፯፡፲፫፣
፪ ኔፊ ፮፡፳፣
ዕሞኒ ፩፡፲፭፣
ሐሌ. ፳፡፳–፳፩።
፲፩ *ሀ* ዕዝ. ፩፡፩–፬፣
ኤር. ፳፱፡፭–፮።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
፲፫ *ሀ* ሉቃ. ፳፫፡፴፫።
ለ ዮሐ. ፲፱፡፴፩–፴፪፣
፩ ኔፊ ፲፱፡፲።
ሐ ሉቃ. ፳፭፡፯–፯፣
ሞዛያ ፫፡፲።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሠ ፩ ኔፊ ፲፩፡፲፫–፴፪።

፲፬ እናም እነሆ እንዲህ ይሆናል ᐟመሲሁ ከሞት ከተነሳ እናም፣ በስሙ ለሚያምኑ ለብዙዎች ሕዝቦቹ ራሱን ከገለጸ በኋላ፣ እነሆ፣ ኢየሩሳሌም በድጋሚ ᐠትጠፋለች፤ ከእግዚአብሔርና ከቤተክርስቲያኑ ሰዎች ጋር ለሚጣሉ ወዮላቸው።

፲፭ ስለሆነም፣ ᐟአይሁዶች በሀገር ሁሉ መካከል ᐠይበተናሉ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ ᐠባቢሎን ትጠፋለች፤ ስለሆነም፣ አይሁዶች በሌሎች ሀገሮች ይበተናሉ።

፲፮ እናም እነርሱ ከተበተኑና፣ ለብዙ ዘመን ጌታ እግዚአብሔር በሌሎች ሀገሮች ከቀጣቸው በኋላ፣ አዎን፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ፣ እና ለሁሉም የሰው ዘር ያልተገደበውን የኃጢያት ክፍያ ᐟለማመን እስኪገደዱም ድረስ—እናም በክርስቶስ የሚያምኑበትና፣ በፍፁም ልብና በንፁህ እጃቸው አብን በስሙ የሚያመልኩበት፣ እናም ሌላ መሲህ ይመጣል ብለውም የማይጠብቁበት ያ ቀን ሲመጣ፣ በኋላም፣ በዚያን ጊዜ እነዚህን ነገሮች ማመን ለእነርሱ አስፈላጊ የሚሆንበት ቀን ይመጣል።

፲፯ እናም ጌታ ለሁለተኛ ጊዜ ህዝቡን ከጥፋትና ከውድቀት ᐟለመመለስ እጁን ይዘረጋል። ስለዚህ፣ በሰው ልጆች መካከል አስደናቂውንና ᐠድንቅ ስራውን መስራት ይቀጥላል።

፲፰ ስለዚህ፣ ᐟቃሉን ይገልፅላቸዋል፣ እነዚህም ቃላት በመጨረሻውም ቀን ᐠይፈርድባቸዋል፣ ምክንያቱም በእነርሱ ስለተነቀፈው ስለ እውነተኛው መሲህ ዓላማ ᐠለማሳመን ተሰጥቶአቸዋልና፤ እናም ከእንግዲህ መሲሁ ይመጣል ብለው እንዳይጠብቁ ለማሳመን፣ ህዝቡን የሚያታልለው ᐟሀሰተኛው መሲህ ካልሆነ ሌላ ማንም ሊመጣ አይገባውምና፤ በነቢያት የተነገረበት አንድ መሲህ ብቻ ነው ያለውና፣ እናም ያ መሲህ በአይሁዶች የተነቀፈው ነው።

፲፱ በነቢያቶቹ ቃል መሰረት፣ አባቴ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣ ᐟከስድስት መቶ ዓመት በኋላ ᐠመሲሁ ይመጣል፤ እናም እንደ ነቢያቱ ቃል፣ ደግሞም በእግዚአብሔር ᐠመልአክ ቃል መሰረት፣ ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል።

፳ እናም አሁን ወንድሞቼ እንዳትሳሳቱ ዘንድ በግልፅ ነግሬአችኋለሁ። እናም ከግብፅ ምድር እስራኤልን ᐟያወጣና፣ ለሙሴ ህዝቡ በመርዘኛ እባብ ከተነደፉ በኋላ በፊታቸው ከፍ ያደረገውን ᐠእባብ ላይ አይናቸውን ከጣሉ ᐠለመፈወስ ይችል ዘንድ ኃይልን የሰጠው፣ እናም ደግሞ ᐟድንጋዩን መትቶ ውኃ እንዲፈልቅለት ኃይልን የሰጠው ጌታ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ፤ አዎን፣ እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፥ እነዚህ ነገሮች እውነት ናቸው፣ እናም ጌታ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ እኔ እንደተናገርኩበት ከዚህ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ሰው ሊድንበት የሚችል ምንም አይነት ᐟᐟስም ከሰማይ በታች የተሰጠ የለም።

፲፩ ᐟ ቅ.መ.መ. መሲህ።
ᐠ ሉቃ. ፳፩ ፡ ፳፬፤ ፳፡ ፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩ ፡ ፩–፲፰።

፲፭ ᐟ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ᐠ ነሀ. ፩ ፡ ፳–፱፤ ፪ ኔፊ ፲ ፡ ፮።
ᐠᐠ ቅ.መ.መ. ባቢሎን።

፲፯ ᐟ ፪ ኔፊ ፲ ፡ ፮–፱፤ ፴ ፡ ፯፤ ሞር. ፭ ፡ ፲፡።

፲፯ ᐟ ፪ ኔፊ ፳፩ ፡ ፲፩–፲፪፤ ፳፱ ፡ ፩። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ᐠ ኢሳ. ፳፱ ፡ ፲፡፤ ፪ ኔፊ ፳፯ ፡ ፳፯፤ ፫ ኔፊ ፳፳ ፡ ፴፩–፴፫።

፲፳ ᐟ ፪ ኔፊ ፳፱ ፡ ፲፩–፲፪፤ ፴፫ ፡ ፲፡፤ ፲፡–፲፭።
ᐠ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ᐠᐠ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ተቃዋሚ።

፲፱ ᐟ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፡፣ ፫ ፡ ፩፣ ፲፫። ᐠ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
ᐠᐠ ፪ ኔፊ ፲ ፡ ፫።

፳ ᐟ ዘፀአ. ፫ ፡ ፯–፲፣ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፳፡፣ ፴፩ ፡ ፴፩።

፲፳ ᐟ ፪ ኔፊ ፳፱ ፡ ፲፩–፲፪፣ ፴፫ ፡ ፲፡፣ ፲፡–፲፭።
ᐠ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ᐠᐠ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ተቃዋሚ።

፲፱ ᐟ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፡፣ ፫ ፡ ፩፣ ፲፫። ᐠ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
ᐠᐠ ፪ ኔፊ ፲ ፡ ፫።

፳ ᐟ ዘፀአ. ፫ ፡ ፯–፲፣ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፳፡፣ ፴፩ ፡ ፴፩፣ ፲፱ ፡ ፲።
ᐠ ዘኁል. ፳፩ ፡ ፰–፱፣ አልማ ፴፫ ፡ ፲፱፣ ሔሊ. ፰ ፡ ፲፡–፲፭።
ᐠᐠ ዮሐ. ፫ ፡ ፲፡፣ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፴፩።
ᐠᐠᐠ ዘፀአ. ፲፯ ፡ ፮፣ ዘኁል. ፳ ፡ ፲፩፣ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፳፱፣ ፳ ፡ ፳፩።
ᐠᐠᐠᐠ ሆሴ. ፲፫ ፡ ፱፣ የሐዋ. ፱ ፡ ፣–፲፪፣ ሞዛያ ፭ ፡ ፣፣ ሙሴ ፮ ፡ ፶፪። ቅ.መ.መ. አዳኝ።

፳፩ ስለዚህ፣ በዚህ ምክንያት ነው ጌታ እግዚአብሔር እነዚህን ᵐየፃፍኳቸው ነገሮች እንደሚጠበቁና እንደሚቀመጡ፣ እናም ዘሮቼ ምድር እስካለችም ድረስ ᵃእንደማይጠፉ ለዮሴፍ የተገባለት ቃል ኪዳን እንዲሟላ ዘንድ ከትውልድ እስከ ትውልድ ለዘሮቼ እንደሚተላለፉ ቃል የገባልኝ።

፳፪ ስለሆነም፣ እነዚህ ነገሮች ምድር እስካለች ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ፤ እናም እነሱም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ደስታ ይተላለፋሉ፤ እናም እነርሱ ያሏቸውም ሀገሮች በተፃፉት ቃል መሰረት ᵐይፈረድባቸዋል።

፳፫ ለመጻፍ፣ ልጆቻችንን እናም ደግሞ ወንድሞቻችንን በክርስቶስ እንዲያምኑና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ᵐለማሳመን በትጋት እንሰራለንና፤ ምክንያቱም ᵃበጸጋ የምንድነው የምንችለውን ᵐካደረግን በኋላ እንደሆነ እናውቃለንና።

፳፬ እናም በክርስቶስ ብናምንም እንኳን የሙሴን ህግ ᵐእንጠብቃለን፣ እናም ህጉ እስከሚፈፀም ድረስ በፅኑነት ወደፊት ወደ ክርስቶስን እንመለከታለን።

፳፭ ይህ ህግ የተሰጠው ለዚህ አላማ ነበርና፤ ስለሆነም ᵐህጉ ለእኛ ᵃሙት ሆኗል፣ እናም እኛ በእምነታችን ምክንያት በክርስቶስ ህያው ሆነናል፤ ቢሆንም ግን ህጉን በትዕዛዝ ምክንያት እንጠብቃለን።

፳፮ እናም ᵐልጆቻችን ለኃጢአታቸው ᵃስርየት የትኛውን ምንጭ መመልከት እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ፣ ᶜስለክርስቶስ እንናገራለን፣ በክርስቶስ እንደሰታለን፣ ስለክርስቶስ እንሰብካለን፣ ስለክርስቶስ ᵐትንቢት እንናገራለን፣ እናም በትንቢታችን መሰረት እንፅፋለን።

፳፯ ስለዚህ፣ ህጉን በተመለከተ ልጆቻችን የህጉን መሞት ያውቁት ዘንድ እንናገራለን፤ እናም እነርሱ የህጉን ሞት በማወቅ፣ በክርስቶስ የሚመጣውን ህይወት ይጠብቃሉ እናም ህጉ ለምን ዓላማ እንደተሰጠ ያውቃሉ። እናም ህጉ በክርስቶስ ከተፈፀመ በኋላ፣ ህጉ በሚፈፀምበት ጊዜ በእርሱ ልባቸውን ማጠጠር እንደማያስፈልጋቸው እንዲያውቁም ነው።

፳፰ እናም አሁን እነሆ ህዝቦቼ፣ አዎን እናንተ ᵐአንገተ ደንዳና ህዝብ ናችሁ፤ እኔ በግልፅ የተናገርኳችሁ አንዳትደናገሩም ነው። የምናገረው ቃል ᵃእንደምስክር በእናንተ ላይ ይቆማሉ፤ ምክንያቱም እነርሱ ማንኛውንም ሰው ትክክለኛውን መንገድ ᶜለማስተማር በቂ ናቸውና፤ ትክክለኛው መንገድ በክርስቶስ ማመንና እርሱን አለመካድ ነውና፤ ምክንያቱም እርሱን በመካድ እናንተ ደግሞ ነቢያትንና ህጉን ትክዳላችሁና።

፳፱ እናም እነሆ አሁን፣ ትክክለኛው መንገድ በክርስቶስ ማመን ነው እላችኋለሁ፣ እርሱንም አትካዱ፤ እናም ክርስቶስ የእስራኤል ቅዱስ ነው፤ ስለዚህ በፊቱ መስገድና፣ በሙሉ ᵐኃይላችሁ፣ አእምሮአችሁና ጉልበታችሁ እንዲሁም በፍፁም ነፍሳችሁ እርሱን ማምለክ አለባችሁ፤ እናም ይህን ካደረጋችሁ በምንም ሁኔታ አትጣሉም።

፴ እናም አስፈላጊ እስከሆነ፣ ለሙሴም የተሰጠው ህግ እስከሚፈፀም ድረስ የእግዚአብሔርን ስራና ᵐስርዓቱን መጠበቅ አለባችሁ።

፳፩ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፯፡፮–፲፱።
ᵃ ዓሞ. ፭፡፲፭፤
፪ ኔፊ ፲፡፲፮፤
አልማ ፴፯፡፳፬–፳፯።
፳፪ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲፭፤ ፴፲፡፲–፲፭፤
፣ ኔፊ ፳፯፡፳፣–፳፯።
፳፣ ᵐ ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች።
ᵃ ሮሜ ፣፡፳፣–፳፱፤
፪ ኔፊ ፪፡፱–፲፡
ሞዛያ ፲፣፡፴፪፤
አልማ ፴፪፡፲፪–፲፮፤
ት. እና ቃ. ፻፴፯፡፱።
ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ᶜ ያዕ. ፪፡፲፱–፳፯።
ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፳፭ ᵐ ያዕቆ. ፱፡፱–፳፡
ᵃ ሮሜ ፯፡፱–፯።
፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች።
ᵃ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ᶜ ያዕቆ. ፱፡፲፪፤
ኢሬም ፩፡፲፩፤
ሞዛያ ፫፡፲፣።
ᵐ ሉቃ. ፣፡፳፣–፳፱።
፳፰ ᵐ ሞዛያ ፣፡፲፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ᶜ ፪ ኔፊ ፴፣፡፣።
፳፱ ᵐ ዘዳግ. ፮፡፭፤
ማር. ፲፪፡፳፱–፴፩።
፴ ᵐ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።

ምዕራፍ ፳፤

ክርስቶስ ለኔፋውያን ያገለግላል—ኔፊ የህዝቡን መጥፋት አስቀድሞ አየ—ከምድር ውስጥ ይናገራሉ—አህዛብም ሀሰተኛ ቤተክርስቲያንን እናም ሚስጥራዊ ሴራዎችን ይሰራሉ—ጌታ በክህነት የሚ ደረገውን ተንኮል ይከለክላል። ከ፳፻፶፱–፳፻፸፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም ልጆቼና የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ክርስቶስ ከሙታን [ሀ]ከተነሳ በኋላ እራሱን ለእናንተ [ለ]ያሳያል፤ ለእናንተ የሚ ናገራችሁ ቃልም ለእናንተ [ሐ]ህግ ይሆንላ ችኋል።

፪ እነሆም እላችኋለሁ፣ ብዙ ትውልድ እንደሚያልፉ፣ እናም በህዝቦቼ መካከል ታላቅ ጦርነትና ፀብ እንድሚኖር ተመል ክቻለሁ።

፫ እናም መሲሁ ከመጣም በኋላ [ሀ]ስለው ልደቱ፣ እንዲሁም ስለሞቱና ትንሳኤው፤ ለህዝቦቼ [ለ]ምልክቶች ይሰጣል፤ እናም ለኃጢአተኞች ያ ቀን ታላቅና የሚያስ ፈራ ይሆናል፣ ምክንያቱም እነርሱ ይጠ ፋሉና፤ እናም የሚጠፉትም እነርሱ ነቢ ያትንና፣ ፃድቃንን፣ ስለአወጡአቸውና፣ በድንጋይ ስለወገሩአቸው፣ ስለገደሉአቸ ውም ነው። ስለዚህ የቅዱሳን [ሐ]ደም ጩኸት በእነርሱ ላይ ከምድር ወደ እግዚአብሔር ይወጣል።

፬ ስለዚህ፣ ኩራተኞችና፣ አመፅን የሚ ያደርጉ ሁሉ፣ የሚመጣው ቀንም [ሀ]ያቃጥ ላቸዋል፣ ይላል የሰራዊት ጌታ፣ እንደገ ለባ ይሆናሉና።

፭ እናም ነቢያትንና፣ ፃድቃንን፣ የሚገ ድሉ የምድር ጥልቅ [ሀ]ይውጧቸዋል፣ ይላል የሰራዊት ጌታ፤ እናም [ለ]ተራሮች ይጫኗቸ ዋል፣ አውሎ ነፋስም ይወስዳቸዋል፣ ህን ፃዎችም በላያቸው ላይ ይወድቃሉ፣ እናም ይሰባብሩአቸዋል እንዲሁም ወደ ዱቄት ነት ይለውጡአቸዋል።

፮ እናም በነጎድጓድና፣ በመብረቅ፣ በመ ሬት መናወጥና፣ በሁሉም አይነት ጥፋት፣ ይቀጣሉ፣ የጌታም የቁጣ እሳት በእነርሱ ላይ ይነዳልና፣ እናም እነርሱ እንደገለባ ይሆናሉ፣ የሚመጣውም ቀን እነርሱን ይበ ላል፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፯ አቤቱ በህዝቤ ጥፋትና ሞት የተነሳ፣ የነፍሴ ስቃይ! እኔ ኔፊ አይቼዋለሁ፣ እና ይህም በጌታ ፊት ሊያጠፋኝ ደርሷልና፤ ነገር ግን መንገድህ [ሀ]ጻድቅ ነው ብዬ ወደ አምላኬ መጮህ አለብኝ።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ [ሀ]የስደት መከራ ቢደር ስባቸውም የነቢያትን ቃል የሚሰሙ እናም የማያጠፏቸው፣ ነገር ግን የተሰጠውን ምል ክት በመጠባበቅ በእምነት ፀንተው ክርስ ቶስን ወደ ፊት የሚመለከቱ ጻድቃኖች—እነሆ፣ እነርሱም [ለ]የማይጠፉት ናቸው።

፱ ነገር ግን የፅድቅ ልጅ [ሀ]ይገለፅላቸዋል፤ [ለ]ይፈውሳቸዋልም፣ እናም [ሐ]ሶስት ትውልድ እስከሚያልፍ ድረስ በእርሱ [መ]ሰላም ይኖ ራቸዋል፣ [ሠ]ከአራተኛው ትውልድም ብዙ ዎች በፅድቅ ያልፋሉ።

፲ እናም እነዚህ ነገሮች በሚያልፉበት ጊዜ ፈጣን [ሀ]ጥፋት በህዝቤ ላይ ይመጣል፤ ምክ ንያቱም በነፍሴ ስቃይ ቢኖርም፣ ይህን አይ ቼዋለሁ፤ ስለዚህ፣ እንደሚሆንም አውቃ ለሁ፤ እናም እራሳቸውን ያለ ዋጋ ይሸጣሉ፤ ለኩራታቸውና ለሞኝነታቸው ጥፋትን ዋጋ

፳፤ ፩ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፩–፲፪።
ለ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፲፤ ፲፪፡ ፮።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፪–፲።
፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፡–፮።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
ሐ ዘፍጥ. ፡፡ ፡ ፲፤ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳–፲ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲–፲፭ ሞር. ፳፡ ፳፮።
፬ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፡–፳፡ ፡፡ ፡ ፡ ፡፡።
ለ ፫ ኔፊ ፳፡ ፡ ፡

ይቀበላሉና፤ ለዲያብሎስ እጃቸውን ስለ ሰጡ፣ እናም ከብርሃን ይልቅ የጨለማን ስራ ስለመረጡ፣ ስለዚህ ወደ ^ሲኦል ሊወርዱ ይገባቸዋል።

፲፩ የጌታ መንፈስ ሁል ጊዜ ከሰው ጋር ᵛአይቆይም። እናም መንፈስ ከሰው ጋር መስራት ሲያቆም ፈጣን ጥፋት ይመጣል፣ እናም ይህ ነፍሴን ያሳዝነዋል።

፲፪ እናም እኔ ᵛአይሁዶችን ኢየሱስ፣ እን ዲሁም ^ያው ክርስቶስ፣ መሆኑን ሐለማ ሳመን ስናገር፣ አህዛቦችም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን ሊረ ዱት ይገባቸዋል፤

፲፫ እናም እሱ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ እራሱን ᵛበመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገልፃል፤ አዎን፣ ለሁሉም ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋን ቋና ህዝብ እንደ እምነታቸው በሰው ልጆች መካከል አስደናቂ ተአምራትን፣ ምልክ ትን፣ እና ድንቅ ነገርን ይሰራል።

፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ᵛየመጨረሻ ቀና ትን በተመለከተ ጌታ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እነዚህን ነገሮች ^የሚያመጣባቸውን ቀናትም በተመለከተ እተነብይላችኋለሁ።

፲፭ ዘሮቼና የወንድሞቼ ዘሮች ባለማመን ከመነመኑና፣ በአህዛብ ከተመቱ በኋላ፤ አዎን፣ እግዚአብሔር በሰራዊቱ ከከበባ ቸውና፣ የግንብ ከለላ ካደረገላቸው በኋላ፣ ከሚዋጉአቸውም ከከለላቸው፤ እናም እስ ከሚጠፉም እንኳን፣ በትቢያም ዝቅ ካደ ረጋቸው በኋላ፣ ሆኖም የፃድቃን ቃል ይፃ ፋል፣ የታማኞች ፀሎትም ይሰማል፣ እናም ባለማመን የመነመኑትም ሁሉ አይረሱም።

፲፮ እነዚያ የሚጠፉት ከመሬት ᵛይናገ ራሉ ቃላቸውም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወ ጣል፣ ድምጻቸውም ከመሬት እንደሚ ወጣ እንደመናፍስት ጠሪ ድምፅ ይሆናል፤ ጌታ እግዚአብሔር እነርሱን በተመለከተ፣ ከመሬት ውስጥ እንደሆኑ ሁሉ፣ ያንሾካሽክ ዘንድ ኃይልን ይሰጠዋል፤ ቃላታቸውም ከአፈር ወጥተው ያንሾካሽካሉ።

፲፯ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና— በእነርሱ መካከል ስለሚደረጉት ነገሮች ᵛይፅፋሉ፣ እናም ተፅፈውም በመጽሐፍ ይታተማሉ፣ እናም ባለማመን የመነመኑት አያገኟቸውም፣ ምክንያቱም እነርሱ የእግ ዚአብሔርን ነገሮች ለማጥፋት ^ይሻሉና።

፲፰ ስለሆነም፣ እነዚያ የሚጠፉት በፍጥ ነት ጠፍተዋል፤ እናም የጨካኞችም ብዛ ታቸው እንደሚያልፍ ᵛገለባ ይሆናል— አዎን፣ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ ይህም ፈጥኖ፣ በድንገትም ይሆናል—

፲፱ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ባለማመን የመነመኑት በአህዛብ እጅ ᵛይመታሉ።

፳ እናም አህዛብ በአይናቸው ᵛኩራት ምክንያት ^ተሰናክለዋል፣ እናም ᵃᵇᵃᵢᵢᵢᵃᵢᵢᵢᵃᵢᵢᵢ

እንደ ዲያብሎስ ውህደት መሰረት አሁ
ንም ደግሞ ᵐሚስጥራዊ ሴራዎች አለ፣ የነ
ዚህ ሁሉ ነገሮች መስራት እርሱ ነውና፤
አዎን፣ የግድያ እና የጨለማ ስራ መስራት፤
አዎን፣ ለዘለዓለም በጠንካራው ገመድ እስ
ከሚያስራቸው፣ በተልባ ገመድ አንገታቸ
ውን ይስባል።

፳፫ እነሆም፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣
ጌታ እግዚአብሔር በጨለማ አይሰራም እላ
ችኋለሁ።

፳፬ እርሱም ለዓለም ጥቅም ካልሆነ በስ
ተቀር ማንኛውንም አያደርግም፤ ምክንያ
ቱም ሰዎችን ᵐሁሉ ወደ እርሱ ይስብ ዘን
ድም ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ዓለ
ምን ᵃይወዳል። ስለዚህ፣ ማንንም ደህንነ
ቱን እንዳይካፈሉ አያዝም።

፳፭ እነሆ፣ ለሰው ከእኔ ራቁ ብሎ ተና
ግሯልን? እነሆ፣ እኔ እላችኋለሁ፣ አይደ
ለም፤ ነገር ግን እርሱ እንዲህ ይላል—እና
ንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ ወደ እኔ ᵐኑ፣ ያለ
ገንዘብም ያለዋጋም ወተትና ማር ᵃግዙ።

፳፮ እነሆ፣ ከምኩራብ ወይም ከማም
ለኪያ ቤቶች ውጪ መውጣት እንዳለባ
ቸው እርሱ አዟልን? እነሆ፣ እላችኋለሁ
አላለም።

፳፯ ᵐደህንነቱን እንዳይካፈሉ እርሱ አዝ
ዟቸዋልን? እነሆ እኔ እላችኋለሁ—አላዘዛ
ቸውም፤ ነገር ግን እርሱ ለሰዎች ሁሉ በነፃ
ᵃሰጥቶታል፤ እናም እርሱ ህዝቡን ሁሉ
ንም ሰዎች ሐንስህ ለመግባት እንዲያሳምኑ
አቸው አዟል።

፳፰ እነሆ፣ ጌታ ከቸርነቱ እንዳይካ
ፈሉ ያዘዘው አለ? እነሆ እኔ እላችኋለሁ—
የለም፤ ነገር ግን ᵐሁሉም ሰው እንደሌላው
ታድሷል፤ እናም ማንም አልተከለከለም።

፳፱ የክህነት ተንኮል እንዳይኖር አዟል፣
እነሆም፣ ᵐየክህነት ተንኮሎችም ጥቅምና
ᵃሙገሳን ከአለም ያገኙ ዘንድ ሰዎች የሚሰ
ብኳቸውና እራሳቸውን በዓለም ውስጥ በብ
ርሃን የሚያስቀምጡበት ነው፤ ነገር ግን እነ
ርሱ የፅዮንን ደህንነት አይሹም።

፴ እነሆ፣ ጌታ ይህንን ነገር ይከለክላል፤
ስለዚህ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሰው ሁሉ
ለጋስ መሆን እንዳለበት ትዕዛዝን ሰጥቷል፣
ይህም ᵐልግስና ᵃፍቅር ነው። እናም ለጋስ
ነት ከሌላቸው ከንቱ ናቸው። ስለሆነም፣
ልግስና ቢኖራቸው የፅዮን ሰራተኞች እን
ዲጠፉ አይፈቅዱም ነበር።

፴፩ ነገር ግን ᵐበፅዮን ያሉ ሰራተኞች
ለፅዮን ይሰራሉ፤ ምክንያቱም ᵃለገንዘብ
ከሰሩ ይጠፋሉና።

፴፪ እናም ጌታ እግዚአብሔር እንደገና
ሰዎች መግደል እንደሌለባቸው፤ መዋ
ሸት እንደሌለባቸው፤ መስረቅ እንደሌለ
ባቸው፤ የጌታን ስም ᵐበከንቱ መጥራት እን
ደሌለባቸው፤ እንዳይመቀኙ፤ ጥላቻ እን
ዳይኖራቸው፤ አንዱ ከሌላው እንዳይጣላ፤
ዝሙትን እንዳይፈፅሙ፤ እናም ከእነዚህ
ውስጥ ማንኛውንም ማድረግ እንደሌለባ
ቸው ᵃአዝዞአል፤ እነዚህን የሚፈፅሙ ይጠ
ፋሉና።

፴፫ ከእነዚህ ማናቸውም ክፋቶች በጌታ
አይመጡምና፤ እርሱ በሰው ልጆች መካ
ከል መልካም የሆነውን ያደርጋልና፤ እናም
ለሰዎች ልጆች ግልፅ ከሆነው በስተቀር
ምንም አያደርግም፤ እርሱም ከቸርነቱ ይካ
ፈሉ ዘንድ ሁሉም ወደ እርሱ እንዲመጡ
ይጋብዛል፤ እናም ወደ እርሱ የሚመጡ
ትን ማንንም፣ ጥቁርም ነጭም፣ ባሪያው
ንና ነፃውን፤ ሴትና ወንድን ᵐአይክድም፤

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
፳፬ ሀ ፫ ኔሬ ፳፤ ፣ ፲፬–፲፭።
ለ ዮሐ. ፫ ፣ ፲፤።
፳፭ ሀ አልማ ፭ ፣ ፴፫–፴፭ ፤
፫ ኔሬ ፱ ፣ ፲፫–፲፱።
ለ ኢሳ. ፶፭ ፣ ፩–፪።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ለ ኤፌ. ፪ ፣ ፳ ፤
፪ ኔሬ ፳፭ ፣ ፳፫።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
፳፰ ሀ ሮሜ ፪ ፣ ፲፭ ፤
፩ ኔሬ ፲፯ ፣ ፴፫–፴፭።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
ለ ት. እና ቃ. ፲፳፭ ፣ ፴፱–፴፯።
፴ ሀ ሞሮኒ ፯ ፣ ፴፯–፴፰።
ቅ.መ.መ. ልግስና።
ለ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ያዕቆ. ፪ ፣ ፲፯–፲፱ ፤
ት. እና ቃ. ፲፩ ፣ ፯ ፤
፴፰ ፣ ፴፱።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
፴፫ ሀ የሐዋ. ፲ ፣ ፱–፴፭ ፣ ፴፱–፴፭።

ᵃእምነተቢሶችንም ያስታውሳል፤ እናም አይሁድም ሆኑ አህዛብ፣ ᵇሁሉም ለእግዚአብሔር አንድ ናቸው።

ምዕራፍ ፳፯

ጨለማና ክህደት በመጨረሻው ዘመን ምድርን ይሸፍናታል—መፅሐፈ ሞርሞን ይመጣል—ሶስት ምስክሮች ስለ መፅሐፉ ይመሰክራሉ—የተማረው ሰው የታተመውን መጽሐፍ ማንበብ አልችልም ይላል—ጌታ አስደናቂና ድንቅ ስራን ይሰራል—ኢሳይያስ ፳፱ን አነጻፅሩ። ከ፳፱–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ነገር ግን እነሆ፣ ᵃበመጨረሻ ቀናት ወይም በአህዛብ ቀናት—አዎን፣ እነሆ በዚህ ምድር የሚመጡትና በሌላም ምድር፣ አዎን፣ በአለም ምድሮች ሁሉ ላይ የሚሆኑት የአህዛብን እናም ደግሞ የአይሁዶች ሀገሮች፣ እነሆ፣ በክፋቶችና በሁሉም አይነት እርኩሰቶች ይሰክራሉ—

፪ እናም ያ ቀን ሲመጣ የሰራዊት ጌታ በነጎድጓድ፣ በምድር መናወጥና፣ በታላቅ ሁካታ፣ በአውሎ ነፋስና በወጨፎም፣ እንዲሁም በምትበላም እሳት ᵃነበልባል ይጎበኛቸዋል።

፫ እናም ᵃፅዮንን ᵃየሚዋጉ፣ እናም የሚያስጨንቋት ሁሉም ሀገሮች እንደህልምና እንደምሽት ራዕይ ይሆናሉ፤ አዎን፣ ለእነርሱ ተርቦ እንደሚያልም ሰው እንኳን ይሆንላቸዋል፣ እናም እነሆ ይበላል፣ ነገር ግን ይነቃልም ነፍሱ ባዶ ናት፤ ወይም ተጠምቶ እንደሚያልም ሰው ነው፣ እናም እነሆ እርሱ ይጠጣል ነገር ግን ይነቃልም እነሆ የዛለ ነው፣ ነፍሱም አምሮት ይኖረዋል፣ አዎን፣ ከፅዮን ተራራ ጋር የሚዋጋ የሀገሮች ሁሉ ብዛት እንዲህም ይሆናሉ።

፬ እነሆም፣ ክፋትን የምታደርጉ ሁሉ፣ ራሳችሁን ቆጥቡ እናም ተደነቁ፣ ትጮሀላችሁና፤ እናም ታለቅሳላችሁ፤ አዎን፣ እናንተ ትሰክራላችሁ ነገር ግን በወይን አይደለም፣ በሚያሰክር መጠጥ ሳይሆን ትንገዳገዳላችሁ።

፭ እነሆም ጌታ ከባድ የእንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል። እነሆም ዐይኖቻችሁን ጨፍናችኋል ነቢያትንም ተቃውማችኋል፤ እናም በክፋታችሁ የተነሳ ገዠዎቻችሁንና ባለራዕዮችን ሸፍናባችኋል።

፮ እናም እንዲህ ይሆናል ጌታ እግዚአብሔር ᵃየመፅሐፍን ቃል ᵃያመጣላችኋል፣ እናም እነርሱ የሚያንቀላፉት ቃል ይሆናሉ።

፯ እናም እነሆ መጽሐፉ ᵃየታተመ ይሆናል፤ እናም በመጽሐፉም ውስጥ ከዓለም መጀመሪያ እስከ ᵃመጨረሻው ድረስ ያለው የእግዚአብሔር ᵇራዕይ ይኖራል።

፰ ስለሆነም፣ ᵃበታተሙት ነገሮች የተነሳ፣ የታተሙት ነገሮች በህዝቡ በኃጢያትና በመጥፎነት ጊዜ ᵃአይሰጡም። ስለዚህ መጽሐፉ ከእነርሱ ይደበቃል።

፱ ነገር ግን መጽሐፉ ለአንድ ᵃሰው ይሰጣል፣ እናም እርሱ በአፈር ያንቀላፉት ቃል የሆነውን የመጽሐፉን ቃል ይሰጣል፣ እናም እነዚህን ቃላት ᵃለሌሎችም ይሰጣል፤

፲ ነገር ግን የታተሙትን ቃላት እንዲሁም መጽሐፉን አይሰጥም። መጽሐፉ የታተመው በእግዚአብሔር ሀይል በመሆኑ እናም የታተመው ራዕይ እንዲመጣ ዘንድ የጌታ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ በመጽሐፉ ውስጥ ይጠበቃል፤ እነሆም እነርሱ ከዓለም መጀ

፴፫ ᵃ አልማ ፳፯፡፴፯።
ᵇ ሮሜ ፪፡፲፩፣
፩ ኔፊ ፲፯፡፴፭።

፳፯ ፩ ᵃ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
፪ ᵃ ኢሳ. ፳፬፡፮፣
፳፯፡፲፭–፲፯፣
ያዕቆ. ፮፡፲፣
፣ ኔፊ ፳፭፡፩።
፣ ᵃ ሀ ኢሳ. ፳፱፡፯–፳።
ᵃ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፱።
፮ ᵃ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፯–፲፯፣
፳፯፡፲፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ᵃ ጄረም ፩፡፪፣
ሞር. ፭፡፲፪–፲፣።
፯ ᵃ ኢሳ. ፳፱፡፲፩–፲፪፣
ኤተር ፣፡፳፭–፳፯፣
፡፡–፯።
ᵃ ኤተር ፲፣፡፩–፲፪።
ᵇ ሞዛያ ፳፡፲፱።
፡ ᵃ ኤተር ፭፡፩።
ᵃ ፣ ኔፊ ፳፯፡፱–፲፪፣
ኤተር ፡፡–፯።
፱ ᵃ ት. እና ቃ. ፲፯፡፭–፯።
ᵃ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፡–፳፭።

መሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ያሉትን ነገሮች ይገልፃሉ።

፲፩ እናም የታተሙት የመጽሐፉ ቃላት በሰገነት ላይ የሚነበቡበት ጊዜ ይመጣል፤ እነርሱም በክርስቶስ ኃይል ይነበባሉ፤ እናም በሰዎች ልጆች መካከል የነበሩትና፣ እስከ ዓለም ዳርቻ የሚሆኑት፣ ሁሉም ነገሮች ለሰዎች ልጆች ᵐይገለፃሉ።

፲፪ ስለሆነም፣ እኔ ለተናገርኩበት ሰው መጽሐፉ በሚሰጥበት በዚያ ቀን፣ መጽሐፉ ከዓለም ዐይን ይደበቃል፣ በእግዚአብሔር ኃይል፣ ከእርሱ መጽሐፉ ከተሰጠው በተጨማሪ፣ በዚያም ᵐከሶስቱ ካዩት ᵃምስክሮች በስተቀር የማንም ዐይን አያየውም፤ እናም እነርሱ ስለመጽሐፉ እውነታና በውስጡ ስላሉት ነገሮች ይመሰክራሉ።

፲፫ እናም ለሰዎች ልጆች የእርሱን ቃል ምስክርነት ይሰጡ ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከጥቂቶቹ በስተቀር ማንም አያየውም፤ ምክንያቱም ጌታ እግዚአብሔር የታመኑት ቃላት ᵐከሙታን እንደሆነ ይናገራሉ ብሎአልና።

፲፬ ስለሆነም፣ ጌታ እግዚአብሔር የመጽሐፉን ቃል ለማምጣት ይቀጥላል፤ እናም እርሱ ጠቃሚ ናቸው ብሎ በሚያስባቸው ብዙ ምስክሮቹ አፍ የቃሉን እውነትነት ያረጋግጣል፤ እናም የእግዚአብሔርን ቃል ᵐለማይቀበል ለዚያ ሰው ወዮለት!

፲፭ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ ይሆናል፣ መጽሐፉን ለሚሰጠው ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ ያልታተሙትን እነዚህን ቃላት ውሰድና እርሱ ለተማረው እንዲያሳየውና—ይህን ᵐእንድታነበውም እለምና ለሁ እንዲለው ለሌላው ስጠው። እናም የተማረውም እንዲህ ይላል—መጽሐፉን ወደ እኔ አምጣው አነባቸዋለሁ።

፲፮ እናም አሁን፣ ይህን የሚሉት በአለም ክብር የተነሳና ሀብት ᵐለማግኘት እንጂ ለእግዚአብሔር ክብር አይደለም።

፲፯ እናም ሰውየውም እንዲህ ይላል፥ መጽሐፉን ማምጣት አልችልም፣ ምክን ያቱም ታትሟልና።

፲፰ የተማረውም እንዲህ ይላል—ይህንን ለማንበብ አልችልም።

፲፱ ስለዚህ እንዲህ ይሆናል፣ ጌታ እግዚአብሔር መጽሐፉን እና በዚያም ያሉትን ቃላት በድጋሚ ላልተማረው ይሰጣል፤ እናም ያልተማረው ሰው እንዲህ ይላል—እኔ አልተማርኩም።

፳ ከዚያም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፥ የተማሩት አያነቡአቸውም፣ ምክንያቱም እነርሱ አልተቀበሉትምና፣ እናም እኔ የራሴን ስራ መስራት እችላለሁ፤ ስለዚህ አንተ የምሰጥህን ቃላት አንብባቸው።

፳፩ የታተሙትን ነገሮች ᵐአትንካ፣ ምክንያቱም በራሴ ጊዜ አመጣቸዋለሁና፤ ለሰዎች ልጆችም የራሴን ስራ መስራት እንደምችል አሳያቸዋለሁና።

፳፪ ስለሆነም፣ እኔ ያዘዝኩህን ቃላት ስታነብ፣ እናም ቃል የገባሁልህን ᵐምስክርነት ስታገኝ፣ ከዚያም መጽሐፉን በድጋሚ ታትማለህ፣ እናም በራሴ ጥበብ ለሰው ልጆች ሁሉንም ነገሮች መግለጫዬ እስከ ሚደርስ ያላነበብሃቸውን ቃላት እጠብቀው ዘንድ ለእኔ ትሸሽገዋለህ።

፳፫ እነሆም እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እኔም ᵐየተአምራት አምላክ ነኝ፤ እናም ለዓለም እኔ ትናንትም፣ ዛሬም፣ ለዘለዓለም ᵃአንድ መሆኔን አሳያለሁ፤ እናም እንደ እምነታቸው ካልሆነ ᵃᵃበስተቀር በሰዎች ልጆች መካከል አልሰራም።

፲፩ ሀ ሉቃ. ፲፪፡፫፤ ሞር. ፭፡፰፤ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡፳፲–፴፩።
፲፪ ሀ ፪ ኔፊ ፲፩፡፫፤ ኤተር ፭፡፪–፬፤ ት. እና ቃ. ፭፡፲፩፤ ፲፫፤ ፲፯፡፩።
ለ ዘዳግ. ፲፱፡፲፭።
፲፫ ሀ ፪ ኔፊ ፫፡፲፱–፳፤ ፴፫፡፲፣ ፲፫–፲፭፤ ሞሮኒ ፣፡፳፯።
፲፬ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡፳፱–፴፣ ኤተር ፪፡፰–፲፡፲፯።
፲፭ ሀ ኢሳ. ፳፱፡፲፩–፲፪፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፭–፳፮።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
፳፩ ሀ ኤተር ፭፡፩።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
ለ ዕብ. ፲፫፡፰።
ሐ ዕብ. ፲፩፡፲፣ ፲፪–፳፪።

፳፬ እናም በድጋሚ እንዲህ ይሆናል፣ የተ ሰጡትን ቃላት ለሚያነበው ጌታ እንዲህ ይለዋል—

፳፭ ይህ ህዝብ በአፋቸው ወደ እኔ ᵐእስከ ቀረቡ፣ በከንፈሮቻቸውም ᵃእስካከበሩኝ፣ ልባቸውን ግን ከእኔ እስካራቁ፣ እናም ወደ እኔ ያላቸው ፍርሀት በሰዎች አስተያየት የተማሩ እስከሆኑ ʰድረስ—

፳፮ ስለዚህ፣ በዚህ ህዝብ መካከል ᵐድንቅ ስራ፣ አዎን፣ ᵃድንቅ ስራ እና አስገራሚ ነገር መስራቴን እቀጥላለሁ፣ የጥበበኞቻ ቸው እና የተማሯቸው ጥበብ ትጠፋለ ችና፣ እናም የአስተዋዮቻቸውም ማስተ ዋል ትሰወራለች።

፳፯ እናም ምክራቸውን ጥልቅ አድር ገው ከጌታ ለሚሰውሩ ᵐወዮላቸው! ስራ ቸውም በጨለማ ውስጥ ነው፤ እናም ማን ያየናል፣ ማንስ ያውቀናል? ይላሉ። እናም ደግሞ እንዲህ ይላሉ—በእርግጥ ነገሮችን የምታጣምሙት ᵃእንደሸክላ ሰሪ ጭቃ ናቸው። ነገር ግን እነሆ፣ ስራቸውን በሙሉ እንደማውቅ አሳያቸዋለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ። ስራ ሰሪውን አልሰራኸኝም ይለዋ ልን? ወይስ መውጠሪያ የወጠረውን አታ ስተውልም ይለዋልን?

፳፰ ነገር ግን እነሆ፣ የሰራዊት ጌታ እን ዲህ ይላል—ለሰው ልጆች ሊባኖስ እንደ ፍሬያማ መስክ የሚለወጥበት ጊዜ ረጅም እንደማይሆን አሳያቸዋለሁ፤ እናም ፍሬ ያማው መስክ እንደጫካ ይመስላል።

፳፱ ᵐእናም በዚያ ቀን ደንቆሮዎች የመጽ ሐፉን ቃል ይሰማሉ፣ እናም የእውሮችም ዐይኖች ከጭጋግና ከጨለማ ውስጥ ወጥ ተው ያያሉ።

፴ እናም ደግሞ ᵐየዋሆች ይጨምራሉ፣ ᵃደስታቸውም በጌታ ይሆናል፣ እናም በሰ ዎች መካከል ያሉ ድሆችም በእስራኤሉ ቅዱስ ይደሰታሉ።

፴፩ ጌታ ህያው እንደሆነ ᵐአሸባሪዎችም ወደከንቱ እንደሚመጣ ያያሉ፣ የሚያሾ ፉትም ይጠፋሉ፣ እናም ለክፋት የተዘጋጁ ሁሉ ይቆረጣሉና፤

፴፪ እናም ሰውን በነገር ᵐበደለኛ የሚ ያደርጉም፣ እናም ᵃበበርም ለሚገስፀው ወጥመድን የሚያኖሩም፣ ፃድቁንም በከ ንቱ ነገር ʰየሚያስቱም ይቆረጣሉ።

፴፫ ስለዚህ፣ አብርሃምን የተቤዠ ጌታ፣ የያዕቆብን ቤት በተመለከተ እንዲህ ይላል—ያዕቆብ አሁን አያፍርም፣ ፊቱም አሁን አይገረጣም።

፴፬ ነገር ግን በእርሱ መካከል የእጄን ስራ ልጆቼን ᵐባየ ጊዜ፣ ስሜን ይቀድሳሉ፣ እናም የያዕቆብን ቅዱስ ይቀድሳሉ፣ እናም የእስራኤልን አምላክ ይፈራሉ።

፴፭ በመንፈስም ደግሞ ᵐየተሳሳቱ ያስተ ውላሉ፣ እናም የሚያጉረመርሙ ትምህር ትን ᵃይማራሉ።

ምዕራፍ ፳፱

በመጨረሻው ዘመን ብዙ ሀሰተኛ ቤተክ ርስቲያኖች ይሰራሉ—ውሸትን፣ ከንቱ ነትን፣ እና የማይረባ ትምህርትንም ያስ ተምራሉ—በሐሰተኛ አስተማሪዎችም የተነሳ ክህደት ይበዛል—ዲያብሎስ በሰ ዎች ልብ ቁጣን ያመጣል—የተለያዩ ሐሰ ተኛ ትምህርቶችን ሁሉ ያስተምራል። ከ፳፻፲፱–፳፻፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ መን ፈስ እንደገፋፋኝ ተናግሬአችኋለሁ፤ ስለ ሆነም፣ እነዚህ ነገሮች በእርግጥ እንደሚ ሆኑ አውቃለሁ።

፳፭ ሀ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፫።
ለ ማቴ. ፲፭፡ ፰።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፩።
፳፮ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፣
፪ ኔፊ ፳፱፡ ፩–፪።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ለ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፱፣
፪ ኔፊ ፳፭፡ ፲፯።
፳፯ ሀ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፭።
ለ ኤር. ፲፰፡ ፩።
፳፱ ሀ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፰።
ሠ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ት.እና ቃ. ፲፩፡ ፴፯።
፴፩ ሀ ኢሳ. ፳፱፡ ፳።
፴፪ ሀ ኢሳ. ፲፩፡ ፶፱።
ለ ዓሞ. ፭፡ ፲።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፲፯።
፴፫ ሀ ኢሳ. ፳፱፡ ፳፫–፳፬።
፴፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፲፬፣
ት.እና ቃ. ፴፫፡ ፬።
ለ ዳን. ፲፪፡ ፬።

፪ እናም "ከመጽሐፉ ላይ የተፃፉት ነገሮች ለሰው ልጆች፣ እና በተለይም የእስራኤል ቤት ቅሪት ለሆኑት ለእኛ ዘር፣ ታላቅ ^ዋጋ ይኖራቸዋል።

፫ በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ለጌታም ያልሆነው የተሰሩት "ቤተክርስቲያኖች፣ አንዱም ለሌላው ይለዋል—እነሆ፣ እኔ የጌታ ነኝ፤ እናም ሌሎቹም እኔ፣ እኔ የጌታ ነኝ ይላሉ፤ እናም ለጌታ ያልተሰሩት ቤተክርስቲያናት ሁሉ እንደዚህ ይላሉ—

፬ እናም አንዳቸው ከሌላኛው ይከራከራሉ፤ ካህናቶቻቸውም አንዱ ከሌላ ይከራከራሉ፣ እናም ከራሳቸው የሆነውን ትምህርት "ያስተምራሉ፣ የመናገርን ችሎታ የሚሰጠውንም መንፈስ ቅዱስ ይክዳሉ።

፭ እናም የእግዚአብሔርን "ኃይል፣ የእስራኤሉንም ቅዱስ ^ይክዳሉ፤ ለህዝቡም እንዲህ ይላሉ—አድምጡን፣ እናም የእኛን መመሪያ ስሙ፤ እነሆም እግዚአብሔር ዛሬ ^የለምና፣ ጌታና አዳኝ ስራውን ሰርቷል፣ እናም ኃይሉን ለሰዎች ሰጥቷልና።

፮ እነሆ፣ የእኔን መመሪያ አድምጡ፤ በጌታ እጅ የተሰራ ተአምር አለ ካሉ አት መኑአቸው፤ በዛሬ ጊዜ እርሱ "የተአምራት አምላክ አይደለምና፤ እሱ ስራውን ሰርቷል።

፯ አዎን፣ እናም ብዙዎች እንዲህ የሚሉ አሉ፥ "ብሉ፣ ጠጡ፣ እናም ተደሰቱ፣ ነገ እንሞታለንና፤ ይህም ለእኛ መልካም ይሆናል።

፰ እናም ሌሎች ደግሞ እንዲህ የሚሉ ብዙ አሉ፥ ብሉ፣ ጠጡ፣ እናም ተደሰቱ፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔርን ፍሩ—ትንሽ ኃጢያትን ብንሰራ "ጥፋተኛ አያደርገንም፤ አዎን፣ ትንሽም ^ዋሹ፣ በቃሉ የተነሳ በሌላ ላይ ዕድል ተጠቀሙ፣ በጎረቤታችሁም ላይ ^ጉድጓድን ቆፍሩ፤ በዚህ ምንም ጉዳት የለም፤ እናም እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርጉ፣ ነገ እንሞታለንና፤ እናም ምንም እንኳን ጥፋተኛ ብንሆን፣ እግዚአብሔር በትንሹ ይቀጣናል፣ እናም በመጨረሻ በእግዚአብሔር መንግስት እንድናለን።

፱ አዎን፣ እናም እንደዚህ ውሸትና ከንቱና "የማይረባ ^ትምህርትን የሚያስተምሩ፣ እናም በልባቸውም የታበዩና፣ ምክራቸውን ጥልቅ አድርገው ከጌታ ለመሰወር የሚፈልጉ ብዙዎች ይኖራሉ፤ እናም ስራቸውም በጨለማ ውስጥ ይሆናል።

፲ እናም የቅዱሳን "ደም ከምድር በእነርሱ ላይ ይጮሃል።

፲፩ አዎን፣ ሁላቸውም "መንገዳቸውን ስተዋል፤ ^ተበላሽተዋልም።

፲፪ "በኩራትና፣ በሐሰተኛ አስተማሪዎች፣ እንዲሁም በሀሰት ትምህርት የተነሳ፣ ቤተክርስቲያናቸው ተበላሽቷል፣ እናም ቤተክርስቲያኖቻቸው ከፍ ብለዋል፤ በኩራትም የተነሳ ተወጥረዋል።

፲፫ በመልካሙ ቅዱስ ስፍራ የተነሳ "ድሆችን ^ይበዘብዛሉ፤ በመልካም ልብሳቸውም የተነሳ ድሆችን ይበዘብዛሉ፤ እናም ትሁታንንና በልባቸው ድሆች የሆኑትን ያሳድዳሉ፣ ^በኩራታቸው የተነሳ ተወጥረዋልና።

፲፬ "አንገተ ደንዳና እና ትምክህተኞች

ሯ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፡–፴፪፤ ፳፯፡ ፱፤ ፫ ኔፊ ፳፩፡ ፲፡–፲፫።
ሯ ሀ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፣–፲፫፤ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፫፤ ፩ ኔፊ ፩፡ ፳፭–፳፱፤ ሞር. ፰፡ ፳፰፣ ፴፪–፴፰።
፯ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፰።
፰ ሀ ፪ ጢሞ. ፫፡ ፭።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳።
ሐ አልማ ፴፡ ፳፰።
፲ ሀ ሞር. ፰፡ ፳፯፤ ፱፡ ፲፭–፳፯።
፲፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፴፪፤ አልማ ፴፡ ፲፯–፲፰።
፲፪ ሀ ሞር. ፰፡ ፴፩።
ለ ት.እና ቃ. ፲፡ ፳፭፤ ሙሴ ፩፡ ፩። ቅ.መ.መ. ሐሰት።
ሐ ምሳ. ፳፯፡ ፳፯፤ ፩ ኔፊ ፲፡ ፫።
፲፫ ሀ ሕዝ. ፲፫፡ ፫፤ ሔሌ. ፲፫፡ ፳፱።
ለ ማቴ. ፲፭፡ ፱።
፲፬ ሀ ራዕ. ፮፡ ፱–፲፩፤ ፪ ኔፊ ፳፯፤ ሞር. ፰፡ ፳፯፤ ኤተር ፰፡ ፳፪–፳፩፤ ት.እና ቃ. ፹፯፡ ፯።
፲፩ ሀ ሔሌ. ፮፡ ፴፩።
ለ ሞር. ፰፡ ፳፰–፴፩፤ ት.እና ቃ. ፴፫፡ ፱።
፲፪ ሀ ምሳ. ፳፰፡ ፳፩።
፲፫ ሀ ሔሌ. ፱፡ ፲፪።
ለ ሕዝ. ፴፬፡ ፰።
ሐ አልማ ፭፡ ፶፫።
፲፬ ሀ ምሳ. ፳፩፡ ፱።

ናቸው፤ እናም አዎን፣ ከጥቂት ትሁት የክርስቶስ ተከታዮች በስተቀር በኩራታ ቸው፣ በክፋታቸው፣ በእርኩሰታቸውና በዝሙት የተነሳ ሁሉም ^ባክነዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ተመርተዋል፣ በብዙ መንገድ የተ ሳሳቱበት ምክንያትም በሰዎች አስተያየቶች ስለተማሩ ነው።

፲፭ አቤቱ በልባችሁ ^ኩራት የተወጠሩ ^ጥበበኞች፣ የተማሩና፣ ሀብታሞች፣ እናም ሀሰተኛ ትምህርትን የሚያስተምሩ ሁሉና፣ ዝሙትን የሚፈጽሙ ሁሉ፣ እናም ትክክ ለኛውን የጌታን መንገድ የሚያጣምሙ፣ ወዮ፣ ወዮ፣ ለእነርሱ ^ሐዘኖላቸው ወደ ሲያ ልም ይጣላሉና ይላል ሁሉን የሚገዛ ጌታ እግዚአብሔር።

፲፮ ፃድቁንም በከንቱ ነገር ^ዞር የሚይደ ርጉና ጥሩ የሆነውን የሚሰድቡ፣ እናም ዋጋ የለውም ለሚሉ ወዮላቸው! ጌታ እግዚአብ ሔር የምድር ነዋሪዎቹን የሚጎበኝበት ቀን በፍጥነት ይመጣልና፤ እናም በዚያን ቀን በጥፋት ^ፈጽመው የበሰሉትም ይጠፋሉ።

፲፯ ነገር ግን እነሆ፣ የምድር ነዋሪዎች ለክፋታቸውና ለእርኩሰታቸው ንሰሀ ከገቡ አይጠፉም ይላል የሠራዊት ጌታ።

፲፰ ነገር ግን እነሆ፣ ያቺ ታላቋና የርኩሰት ቤተክርስቲያን የምድር ሁሉ ^ጋለሞታም ወደ አፈር ^ትወድቃለች፣ እናም አወዳ ደቋም ታላቅ ይሆናል።

፲፱ የዲያብሎስ መንግስት ^መናወጥ አለ በት፣ እናም የእርሱ የሆኑትም ለንስሀ መነ ቃቃት ይገባቸዋልና፣ አለበለዚያ ^ዲያ ብሎስ በዘለዓለማዊ ^ሰንሰለቱ ይይዛቸ ዋል፣ እናም እነርሱ ለቁጣ ይነሳሳሉም፣ ይጠፋሉም፤

፳ እነሆም፣ በዚያን ቀን በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ^ይቆጣል፣ እናም ጥሩ በሆነውም ላይ ለቁጣ ያነሳሳቸዋል።

፳፩ እናም እርሱ ሌሎችን ^ያረጋጋልና፣ ቀስ ብሎም ወደ ስጋዊ ደህንነት አባብሷ ቸው እንዲህ ይላሉ፥ በፅዮን ሁሉም መል ካም ነው፤ አዎን፣ ፅዮን ትለመልማለች፤ ሁሉም መልካም ነው—^ዲያብሎስም ነፍ ሳቸውን እንዲህ ያታልላል፣ እናም በጥን ቃቄ ወደ ሲኦል ይመራቸዋል።

፳፪ እናም እነሆ፣ ሌሎችን እያሞገሰ ያስ ታቸዋል፣ እናም ^ሲኦል የለም ብሎ ይነ ግራቸዋል፤ እናም ይላቸዋል፥ እኔ ዲያ ብሎስ አይደለሁም፣ እርሱ የለምና—እናም ማላቀቅ በማይቻለው በመጥፎው ^ሰንሰለቱ እስከሚያስራቸው ድረስ በጆሮአቸው እን ዲህ ያንሾካሹካል።

፳፫ አዎን፣ በሞትና በሲኦል ተይዘዋል፤ እናም ሞትና ሲኦል እንዲሁም ዲያብሎ ስና በእነርሱም የተያዙት ሁሉ በእግዚአብ ሔር ዙፋን ፊት መቆም አለባቸው፣ እናም እንደስራቸው ^ይፈረድባቸዋል፣ ከዚያም ለእነርሱ በተዘጋጀው ቦታ ወደማያቋርጥ ስቃይ ወደሆነው፣ እንዲሁም ወደ እሳትና ወደ ዲኑ ^ባህር መሄድ አለባቸው።

፳፬ ስለዚህ፣ በፅዮን ለሚዝናናው ወዮለት!

፳፭ ሁሉ መልካም ነው! ብሎ ለሚጮህ ወዮለት!

፳፮ አዎን፣ የሰዎችን አስተያየት ^ለሚያ ዳምጥና፣ የእግዚአብሔርን ኃይልና የመን ፈስ ቅዱስ ስጦታን ለሚክድ ወዮለት!

፳፯ አዎን፣ እኛ ተቀብለናል፣ እናም ሌላ ^አንፈልግም ለሚልም ወዮለት።

፳፰ እናም በአጠቃላይ ለሚንቀጠቀጡ ሁሉና፣ በእግዚአብሔር እውነት ምክን ያት ^ለሚቆጡ ወዮላቸው! እነሆም ^በአለት

፲፬ ^ለ ኢሳ. ፶፫፡፮።
፲፭ ^ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
^ለ ምሳ. ፫፡፭–፮።
^ሐ ፫ ኔፊ ፳፭፡፭።
፲፯ ^ሀ ኢሳ. ፳፱፡፳፫።
^ለ ኤተር ፪፡፱–፲።
፲፰ ^ሀ ራዕ. ፲፱፡፪።
^ለ ፩ ኔፊ ፲፬፡፫፣ ፲፯።
፲፱ ^ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳፫።
^ለ አልማ ፴፬፡፴፭።
^ሐ አልማ ፲፪፡፲፭።
፳ ^ሀ ት.እና ቃ. ፲፡፳–፳፯።
፳፩ ^ሀ ሞር. ፰፡፴፩።
^ለ ፪ ኔፊ ፱፡፴፱።
፳፪ ^ሀ ቅ.መ.መ. ሲያል።
^ለ አልማ ፴፯፡፲፰።
፳፫ ^ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ፣ ፍርድ፣ የመጨረሻው።
^ለ ፪ ኔፊ ፱፡፲፣ ፲፱፣ ፳፯።
፳፯ ^ሀ ፪ ኔፊ ፱፡፳፱።
፳፯ ^ለ አልማ ፲፪፡፲–፲፭።
፳፰ ^ሀ ዕብ. ፲፡፴፡፳–፳፯።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
^ለ ማቴ. ፯፡፳፭–፳፯።
ቅ.መ.መ. አለት።

ላይ የሰራ ይህን በደስታ ይቀበላል፤ እናም በአሸዋ መሰረት ላይ የሰራው ግን በፍርሃት እወድቃለሁ ብሎ ይንቀጠቀጣል።

፳፪ የእግዚአብሔርንም ቃል ተቀብለ ናል፣ እናም የእግዚአብሔርንም ቃል ከዚህ በተጨማሪ ᵐምንም ᵃአንፈልግም፣ ምክንያ ቱም በቂ አለንና ለሚሉት ወዮላቸው!

፳፫ እነሆም፣ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል—ለሰው ልጆች በትዕዛዝ ላይ ትዕ ዛዝ፣ ᵐበስርዐት ላይ ስርዐት፣ ጥቂት በዚህ፣ ጥቂት በዚያ እሰጣለሁ፤ ትምህርቴን የሚ ሰሙ፣ እናም ምክሬን የሚያደምጡ የተባ ረኩ ናቸው፣ ᵃጥበብን ይማራሉና፤ ᵇለሚ ቀበልም ᶜተጨማሪ እሰጣለሁና፤ እና ይበ ቃናል ለሚሉም፣ ያላቸውም እንኳን ቢሆን ይወሰድባቸዋል።

፳፬ ᵐእምነቱን በሰው የሚያደርግ፣ ወይም ስጋን ክንዱ የሚያደርግ፣ ወይም አስተያ የታቸው በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካኝ ነት ካልተሰጠ በስተቀር የሰውን ትምህርት የሚሰማ የተረገመ ነው።

፳፭ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለአህዛብ ᵐወዮላቸው ይላል! ክንዴን ከቀን ወደቀን ብዘረጋትም እንኳን ይክዱኛልና፣ ይሁን እንጂ፣ ንስሀ የሚገቡና ወደ እኔ የሚመጡ ከሆነ እምራቸዋለሁ ይላል ጌታ እግዚአ ብሔር፤ ᵃክንዴ ቀኑን ሁሉ ትዘረጋለችና ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

ምዕራፍ ፳፱

ብዙ አህዛብ መፅሐፈ ሞርሞንን አይቀ በሉም—ሌላ መፅሐፍ ቅዱስ አያስፈል ገንም ይላሉ—ጌታ ለብዙ ሀገሮች ይናገ ራል—በመጽሐፍት ላይ በሚፃፉት ዓለምን ይፈርዳል። ከ፳፫፻፶–፳፻፷ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ነገር ግን እነሆ፣ ከሰው ልጆች ጋር የገ ባሁትን ᵐቃልኪዳኔን አስብ ዘንድ፣ የእስ ራኤል ቤት የሆኑትን ህዝቤን ደግሜ ለመሰ ብሰብ ክንዴን ᵃለሁለተኛ ጊዜ አነሳ ዘንድ፤

፪ እናም ደግሞ ዘርህንም አንደማስ ታውስ፤ እናም የዘርህ ᵐቃል ከአፌ ወደ ዘርህ እንደሚያልፍ፤ ቃሌም የእስራኤል ቤት ለሆኑት ህዝቦቼ ᵃአርማ ይሆን ዘንድ ወደ ምድር ዳርቻ ᵇእንደሚያፏጭ፤ ለአ ንተ ኔፊና ደግሞ ለአባትህ የገባሁትን ቃል ኪዳን አስታውሰው ዘንድ፤ በዚያን ቀን በእ ነርሱ መካከል ᶜድንቅ ስራን መስራት ስቀ ጥል፣ ብዙዎች ይኖራሉ—

፫ እናም ቃሎቼ ወደፊት ስለሚያፏጩ— ብዙ አህዛብ እንዲህ ይላሉ፣ ᵐመፅሐፍ ቅዱስ! መፅሐፍ ቅዱስ! መፅሐፍ ቅዱስ አለን፣ እናም ሌላ መፅሐፍ ቅዱስ ሊኖር አይችልም።

፬ ነገር ግን ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ ሞኞች ሆይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይኖ ራቸዋል፤ እናም ከእኔ የጥንት የቃል ኪዳን ህዝቦቼ ᵐከአይሁዶች ይወጣል። እናም ከአ ይሁዶች ስለተቀበሉት ᵃመፅሐፍ ቅዱስ እንዴት አድርገው ያመሰግናሉ? አዎን፣ አህዛብስ ምን ማለታቸው ነው? ችግርን፣ የጉልበት ስራንና፣ የአይሁዶችን ስቃይ፣ እንዲሁም ለአህዛብ ደህንነትን ለማምጣት ለእኔ ያላቸውን ትጋት ያስታውሳሉ?

፭ እናንተ አህዛብ ሆይ፣ የጥንት የቃል

፳፱ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፬፤ ኤተር ፪፡፳።
ᵃ ፪ ኔፊ ፳፱፡፫–፲።
ᵇ ᵃ ኢሳ. ፳፳፡፱–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፶፳፡፲፪።
ᶜ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ᵈ ሉቃ. ፳፡፲፳።
ᵉ አልማ ፲፪፡፲፤ ት. እና ቃ. ፱፡፳፭።
ᵐ ᵃ ት. እና ቃ. ፩፡፲፱–፳።
ᵇ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፡፲–፲፪፡፭።
ᶜ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፡፲–፲፪፡፭።
ᵈ ᵃ ያዕቆ. ፫፡ ፴፯፤ ፮፡፱።

፳፭ ᵃ ᵃ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ᵇ ᵃ ፪ ኔፊ ፮፡፲፱፤ ፳፭፡፲፩–፲፪፣ ፳፭፡፲፯።
ᶜ ᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ᵈ ᵃ ᵇ ᵃ ፪ ኔፊ ፫፡፲፳–፳፭።
ᵉ ᵃ ፩ ኔፊ ፳፭፡፳፪።
ᶠ ᵃ ቅ.መ.መ. ምልክት።
ᵍ ᵃ ኢሳ. ፭፡፳፮፤ ᵇ ᵃ ፪ ኔፊ ፲፡፲፭፣ ሞሮኒ ፣፡፳፯።

ᵐ ᵃ ᵇ ᵃ ፪ ኔፊ ፳፯፡፳፮። ᶜ ᵃ ᵇ ᵃ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ᵈ ᵃ ᵇ ᵃ ᵃ ᵃ

ኪዳን ህዝቦቼ አይሁዶችን ታስታውሳላ ችሁ? አታስታውሱም፤ ነገር ግን እናንተ ረግማችኋቸዋልና፣ ᵇጠልታችኋቸዋል፣ እናም እነሱን ለመመለስም አልፈለጋች ሁም። ነገር ግን እነሆ፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በራሳችሁ ላይ አደርጋለሁ፤ ምክንያ ቱም እኔ ጌታ ህዝቤን አልረሳሁምና።

፲፮ እናንት ሞኞች፣ ᵇመጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አለን፣ እናም ሌላ መጽ ሐፍ ቅዱስ አንፈልግም የምትሉ። በአይ ሁዶች ካልሆነ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስን አግኝታችኋልን?

፲፯ ከአንድ በላይ ሀገር እንዳለ አታውቁ ምን? እኔ ጌታ አምላካችሁ፣ ሰዎችን ሁሉ ᵇእንደፈጠርኩ፣ እናም እኔ በባህር ᵃደሴ ቶች ያሉትን እንደማስታውስና በላይ በሰ ማይ እንዲሁም በታች በምድር እንደም ገዛ፣ ለሰው ልጆች ቃሌን፣ አዎን፣ ለሁ ሉም የምድር ሀገሮችም እንኳን እንደማ መጣ አታውቁምን?

፲፰ ስለዚህ ቃሌን በይበልጥ ስለተቀበላችሁ ታጉረመርማላችሁ? እኔ እግዚአብሔር ስለ መሆኔ፣ አንዱን ሀገር እንደሌላኛው እንደ ማስታውሰው፣ ᵇየሁለት ሀገሮች ᵃምስክር ነት ለእናንተ ምስክር መሆኑን አታውቁምን? ስለሆነም፣ ለአንዱ ሀገር እንደተናገርኩት ለሌላኛውም አንድ አይነት ቃል እናገራ ለሁ። እናም ሁለቱ ሀገሮች ሲገናኙ የሁለቱ ᶜሀገሮች ምስክርነትም ደግሞ ይገናኛሉ።

፲፱ እናም ይህን የማደርገውም ለብዙዎች እኔ ትናንትም፣ ዛሬና ለዘለዓለም ᵇአንድ መሆኔን፤ ቃሌንም በፈቃዴ መሰረት እን ደምናገር አረጋግጥ ዘንድ ነው። እናም አንድ ᵃቃል በመናገሬ ሌላ መናገር አይ ችልም ብላችሁ ትገምታላችሁ፤ ምክንያ ቱም ስራዬ ገና አላለቀም፤ ወይም ይህ እስከ ሰው ዘር መጨረሻ፣ ከዚያም እስከ ዘለዓ ለም ድረስ አያልቅም።

፲ ስለሆነም፣ እናንተ መፅሐፍ ቅዱስ ስላ ላችሁ የእኔን ᵇቃል ሁሉ ይፈል ብላችሁ አታስቡ፤ እኔን ሌላም እንዲፃፍ አላደር ግም ብላችሁ አታስቡ።

፲፩ በምስራቅና በምዕራብና፣ በሰሜን፣ እናም በደቡብና፣ በባህሩ ደሴት ያሉትን ሰዎች ᵇሁሉ እኔ የተናገርኳቸውን ቃላት ሁሉ ᵃይፅፋ ዘንድ አዛቸዋለሁና፤ ᶜበመ ፅሐፉ ውስጥ በተፃፉትም፣ ማንኛውንም ሰው እንደስራው፣ በተፃፈው መሰረት ዓለ ምን ᵐእፈርዳለሁ።

፲፪ እነሆም፣ ᵇለአይሁዶች እናገራለሁ እናም ይፅፉታል፤ ለኔፋውያንም ደግሞ እናገራለሁ፣ እናም ᵃይፅፉታል፤ እኔ መርቼ ያወጣኋቸው የእስራኤል ቤት ለሆኑት ለሌ ሎቹ ነገዶችም ደግሞ እናገራለሁ፣ እናም ይፅፉታል፤ እኔም ᶜለሁሉም የምድር ሀገሮ ችም ደግሞ እናገራለሁ፣ እናም ይፅፉታል።

፲፫ እናም እንዲህ ይሆናል ᵇአይሁዶች የኔፋውያን ቃል ይኖራቸዋል፣ ኔፋውያ ንም የአይሁዶች ቃል ይኖራቸዋል፤ እናም ኔፋውያንና አይሁዶች ᵃየጠፉት የእስራኤል ነገዶች ቃል ይኖራቸዋል፤ እናም የጠፉት የእስራኤል ነገዶችም የኔፋውያንና የአይሁ ዶች ቃል ይኖሩዋቸዋል።

፲፬ እናም እንዲህ ይሆናል ᵇከእስራኤል ቤት የሆኑት ህዝቤ በርስተ ምድራቸው ይሰ በሰባሉ፤ እናም ቃሌም ደግሞ ᵃበአንድ ይሰ

፭ ሀ ፫ ኔፊ ፳፱፡፣ ፳፡
፮ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፡
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፱።
፡ ሀ ሕዝ. ፴፯፡ ፲፭–፴፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፡–፴፩፣ ፪ ኔፊ ፫፡ ፲፪።
ለ ማቴ. ፲፡ ፣ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ምስክር።
ሐ ሆሴ. ፩፡ ፲፩።
፱ ሀ ዕብ. ፲፫፡ ፡።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—እንደሚመጡ የተተነበዩ ቅዱሣት መጻህፍት።
፲፩ ሀ አልማ ፳፱፡ ፡።
ለ ጢሞ. ፫፡ ፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
መ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፪፣ ፴፫፡ ፲፩፣ ፲፴–፲፭።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፲፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፳፣–፳፱።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፡–፴፪፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፯።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፣።
፲፣ ሀ ሞር. ፭፡ ፲፪–፲፡።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ነሳዎች።
፲፡ ሀ ኤር. ፣ ፡ ፲፯–፲፡።
ለ ሕዝ. ፴፯፡ ፲፯–፲፯።

በሰባል። ከቃሌና ሐየእስራኤል ቤት ከሆ ኑት ህዝቤ ጋር የሚጣሉትን፣ እኔ እግዚ አብሔር መሆኔንና፣ ለአብርሃም ሙለዘለ ዓለም ሚዘሩን እንደማስታውስ ረቃል መግ ባቴን አሳያቸዋለሁ።

ምዕራፍ ፴

የተለወጡት አህዛብ ከቃል ኪዳን ህዝብ ጋር ይቆጠራሉ—ብዙ ላማናውያንና አይ ሁዶች በቃሉ ያምናሉ እናም ያማሩ ይሆ ናሉ—እስራኤል ዳግም ትመለሳለች፣ እናም ኃጢአተኞች ይጠፋሉ። ከ፩፻፺፱–፩፻፻፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ እናገራችኋለሁ፤ እኔ ኔፊ እናንተ አህዛቦች ከሚሆኑት የበለጠ ፃድቃን እንሆ ናለን ብላችሁ እንድታስቡ አልፈቅድም። እነሆም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ካልጠ በቃችሁ በተመሳሳዩ ሁላችሁም ትጠፋላ ችሁ፤ እናም በተነገረው ቃል ምክንያት አህ ዛብ በሙሉ ጠፍተዋል ብላችሁም አታስቡ።

፪ እነሆም፣ እላችኋለሁ ንሰሃ የሚገቡት አህዛቦች የጌታ ሀቃል ኪዳን ህዝብ ናቸው፤ እናም ንሰሃ የማይገቡት ለአይሁዶችም ይጣ ላሉ፤ ምክንያቱም ጌታ ሏንስህ በሚገቡት እና የእስራኤል ቅዱስ በሆነው በልጁ ከሚ ያምኑት በስተቀር ለማንም ቃል ኪዳን አል ገባምና።

፫ እናም አሁን፣ በይበልጥ ስለአይሁዶችና ስለአህዛብ በመጠኑ ትንቢት እናገራለሁ። እኔ የተናገርኳችሁ መፅሐፍ ከመጣ፣ እናም ለአህዛቦች ከተፃፈና፣ በድጋሚ ወደ ጌታ ከታተመ በኋላ፣ በተፃፉት ቃላት ሀየሚ ያምኑ ብዙዎች ይኖራሉ፤ እና ለእነርሱም ለቀሩት ዘሮቻችን ያደርሱአቸዋል።

፬ እናም ከዚያ በኋላ የእኛ ዘሮች ቅሪት እኛን በተመለከተ፣ እንዴት አድርገን ከኢየሩሳሌም እንደወጣን፣ እናም እንዴ ትስ እነርሱ የአይሁድ ትውልድ እንደሆኑ ያውቃሉ።

፭ እናም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሀበእ ነርሱ መካከላቸው ይሰበካል፤ ስለሆነ፣ ለእነ ርሱም ወደ አባቶቻቸው እውቀት፣ እናም ደግሞ በአባቶቻቸው መካከል ወደ ነበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ሏእውቀት ይመለሳሉ።

፮ እናም ከዚያ በኋላ ይደሰታሉ፤ ምክ ንያቱም ይህ ከእግዚአብሔር እጅ የተሰ ጣቸው በረከት እንደሆነ ያውቃሉ፤ እናም የጨለማው ቅርፊት ከዐይናቸው መውደ ቅም ይጀምራል፤ እናም ንፁህና ሀአስደሳች ህዝቦች እስኪሆኑ ድረስ ብዙ ትውልድ ከእ ነርሱ አያልፍም።

፯ እናም እንዲህ ይሆናል የተበተኑት ሀአይሁዶች ደግሞ በክርስቶስ ማመን ለይጀምራሉ፤ በምድር ፊትም ላይ መሰብ ሰብ ይጀምራሉ፤ እናም በክርስቶስ የሚያ ምኑ ብዙዎችም አስደሳች ህዝብ ይሆናሉ።

፰ እናም እንዲህ ይሆናል ጌታ እግዚአብ ሔር በምድር ላይ የህዝቡን ዳግም መመ ለስ ለማምጣት በሁሉም ሀገሮች፣ ወገኖች፣ ቋንቋና ህዝብ መካከል ስራውን ይጀምራል።

፱ እናም ሀጌታ እግዚአብሔር ድሆችን በፅ ድቅ ለይፈርዳል፣ የምድር ሏትሁታንም በእ ኩልነት ይገስጻል። እናም ምድርን በአፉ በትር ይመታል፤ በከንፈሩም ትንፋሽ ኃጢ አተኞችን ይገድላል።

፲ ጌታ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል

፲፡ሐ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳–፳፱።
መ ዘፍጥ. ፲፯፡፯።
ሠ ት.እና ቃ. ፱፴፪፡፴።
ረ ዘፍጥ. ፲፪፡፩–፫፣
፩ ኔፊ ፲፯፡፣ ፣
፫ ኔፊ ፳፡፳፯፣
አብር. ፪፡፱።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፴ ፪ ሀ ገላ. ፫፡፳፯–፳፱።
ለ ማቴ. ፳፡፲–፲፫።
ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፯፡፯–፯።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪፡፡–፱።
፭ ሀ ፫ ኔፊ ፳፩፡፫–፯፣ ፳፬–፳፯።
ለ ት.እና ቃ. ፫፡፳።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፬፣
፪ ኔፊ ፫፡፣ ፲፪፣
ሞር. ፯፡፩፣ ፱–፲።
፯ ሀ ት.እና ቃ. ፴፱፡፳፤ ፲፪፡፡፳፭።
፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲፫–፲፱።
ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፯–፲፯።
፱ ሀ ኢሳ. ፲፩፡፱–፱።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡፲፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።

ታላቅ ᵐክፍፍል የሚያደርግበት ᵃጊዜ በፍ ጥነት ይመጣል፣ እናም በደለኞችን ያጠ ፋል፤ እናም ህዝቡን ᵃይምራል፣ አዎን፣ በደለኞችን በእሳት ᵐማጥፋት ቢኖርበትም።

፲፩ እናም ᵐፅድቅነትም የወገቡ መታጠቅ ያው፣ ታማኝነትም የጎኑ መቀነትይሆናል።

፲፪ ᵐእናም ተኩላ ከበጉ ጋር ይኖራል፤ አቦሸማኔውም ከፍየል ግልገሎች ጋር፣ ጥጃውም የአንበሳ ደቦልም፣ ከፍሪዳውም ጋር በአንድ ላይ ይተኛሉ፤ እናም ትንሽ ልጅም ይመራቸዋል።

፲፫ እናም ላምና ድብ አብረው ይመገባሉ፤ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ይተኛሉ፤ እናም አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል።

፲፬ እናም የሚጠባው ህፃን በመርዛማው እባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታል፣ እናም ጡት የጣለውም ህፃን በእፉኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል።

፲፭ በተቀደሰው ተራራዬ ላይ ሁሉ አይ ጎዱም፣ አይጠፉምም፤ ውሃ ባህርን እን ደሚሸፍን ሁሉ ምድር በጌታ እውቀትም ትሞላለችና።

፲፮ ስለሆነም፣ ᵐየሁሉም ሀገሮች ነገሮች ይታወቃሉ፤ አዎን፣ ሁሉም ነገሮች ለሰው ልጆች ᵃይገለጣሉ።

፲፯ ᵐያልተገለጠ፣ ሚስጥር የሆነ ምንም የለም፤ በብርሃን የማይወጣ የጨለማ ስራ የለም፤ እናም የማይፈታ በምድር ላይ የሚ ታተም ምንም ነገር አይኖርም።

፲፰ ስለሆነም፣ ለሰው ልጆች ተገልጠው የነበሩት ሁሉም ነገሮች በዚያ ቀን ይገለ ጣሉ፤ እናም ከእንግዲህ ወዲህ ሰይጣን በሰ ዎች ልጆች ልብ ላይ ᵐምንም ስልጣን ለብዙ ጊዜ አይኖረውም። እናም አሁን የተወደ ዳችሁ ወንድሞቼ ንግግሬን እፈፅማለሁ።

ምዕራፍ ፴፩

ኔፊ ክርስቶስ ለምን እንደተጠመቀ ይና ገራል—ሰዎች ለመዳን ክርስቶስን መከ ተል፣ መጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስን መቀ በል እናም እስከመጨረሻው መፅናት ይኖ ርባቸዋል—ንስሀ መግባትና ጥምቀት የጠ ባቡና ቀጭኑ ጎዳና መግቢያ ናቸው—የዘ ለዓለም ህይወት ከጥምቀት በኋላ ትዕዛ ዛትን ለሚጠብቁት ይመጣል። ከ፩፤፯–፲፬ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ እኔ ኔፊ፣ ለእናንተ ᵐትንቢት መና ገሬን እጨርሳለሁ። እናም በእርግጥ መም ጣት አለበት ብዬ ከማውቀው ጥቂት ነገ ሮችን በስተቀር መፃፍ አልችልም፤ የወ ንድሜ ያዕቆብንም ጥቂት ቃላት ብቻ ነው መፃፍ የምችለው።

፪ ስለሆነም፣ እኔ የፃፍኳቸው ነገሮች ስለ ክርስቶስ ᵐትምህርት መናገር ካለብኝ በስተ ቀር ለእኔ በቂ ናቸው፤ ስለሆነም፣ በትንቢቴ ግልፅነት መሰረት በግልፅ እናገራችኋለሁ።

፫ ነፍሴ በግልፅነት ትደሰታለችና፤ ጌታ እግዚአብሔርም በሰዎች ልጆች መካከል የሚሰራው በእንዲህ ያለ ሁኔታ ነውና። ጌታ እግዚአብሔር ለመረዳት ᵐብርሃንን ይሰጣ ልና፤ ለሰዎችም በሚረዱት፣ እንደ ᵃቋን ቋቸው ይናገራቸዋልና።

፬ ስለሆነም፣ እናንተ የተናገርኳችሁ የዓለ ምን ኃጢያት የሚያስወግደውን የእግዚአ ብሔርን ᵐበግ የሚያጠምቀውን ᵃነቢይ በተ መለከተ ጌታ ያሳየኝን በተመለከተ ያሳየኝን እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ።

፭ እናም አሁን የእግዚአብሔር በግ፣ ቅዱስ ሆኖ፣ ፅድቅን ሁሉ ለመፈፀም በውሃ

፲ ሀ ት. እና ቃ. ፳፫፡–፴፫፡–፴፬፡።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ሙሴ ፯፡፳፭፡።
መ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፫–፲፮፣ ፳፫፡።
ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
፲፩ ሀ ኢሳ. ፲፩፡፭–፱፡።
፲፪ ሀ ኢሳ. ፳፭፡፳፭፡።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፭፡፴፪–፴፭፣ ፲፳፭፡፳፳–፳፱፡።
ለ ኤተር ፬፡፯–፲፡።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡፪–፫፡።
፲፰ ሀ ራዕ. ፳፡፩–፫፣ ኤተር ፳፡፳፯፡።
፴፩ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡፩–፩፡።
፪ ሀ ፪ ኔፊ ፲፩፡፣ ፲፭፡፣ ፲፱፡፣ ፳፯፡።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡፳፱፡።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡፣ ፣ ፲፩፡፣ ፳፯፣ ቅ.መ.መ. መጥምቁ ዮሐንስ።

᐀መጠመቅ ካስፈለገው፣ አቤቱ ቅዱስ ያል ሆንነው፣ አዎን፣ እኛ በውሃ እንኳን መጠ መቅ ምን ያህል ያስፈልገናል!

፯ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ እጠይቃችኋለሁ—የእግዚአብሔር በግ በውሃ በመጠመቅ ፅድቅን ሁሉ የፈፀ መው እንዴት ነበር?

፰ ቅዱስ እንደነበር አታውቁምን? ነገር ግን ቅዱስም እንኳን ቢሆን፣ በስጋ መሰረት ለሰው ልጆች በአብ ፊት እራሱን እንዳዋረደ አሳይቷል፣ እናም ትዕዛዛቱን በመጠበቅ ለእ ርሱ ᐟታዛዥ መሆኑን ለአባቱ መስክሯል።

፱ ስለሆነም፣ እርሱ በውሃ ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ᐟበእርግብ ᐠአምሳል በላዩ ላይ አረፈ።

፲ እናም እንደገና፣ እርሱ በፊታቸው ምሳሌ በመሆን፣ ለሰዎች ልጆች የኃዳና ውን ቀጥተኝነትና፣ እነርሱ በዚያ መግባት ያለባቸው ᐟበሩን ጥበት አሳይቷቸዋል።

፲፩ እናም ለሰዎች ልጆች፣ እኔን ᐟተከተ ሉኝ አለ። ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ የአብን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ፈቃደ ኞች ከመሆን በስተቀር ኢየሱስን ᐠልንከ ተለው እንችላለን?

፲፪ እናም አብ እንዲህ ይላል፥ ንስሀ ግቡ፣ ንስሀ ግቡ፣ እናም በተወደደው ልጄ ስም ተጠመቁ።

፲፫ እናም ደግሞ፣ የወልድ ድምፅ ወደ እኔ መጥቶ እንዲህ አለኝ፥ በስሜ የተጠመቀ፣ አብ እንደ እኔ መንፈስ ቅዱስን ᐟይሰጠዋል፤ ስለሆነም፣ ᐠተከተሉኝ፣ እናም እኔ ስሰራ ያያችሁትን ስሩ።

፲፬ ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ በሙሉ ልባችሁ አላማ፣ በእግዚአብሔር ፊት ባለማስመሰልና ያለግብዝነት፣ ነገር ግን በእውነት ፍላጎት፣ ለኃጢአታችሁ ንስሀ በመግባት፣ ᐟበጥምቀት የክርስቶስን ስም ለእራሳችሁ መውሰዳችሁን ለአብ በመመ ስከር ወልድን ብትከተሉ—አዎን፣ እንደ ቃሉ ጌታችሁንና አዳኛችሁን ወደ ውኃው ብትከተሉ፣ እነሆ፣ ከዚያም መንፈስ ቅዱ ስን ትቀበላላችሁ፤ አዎን፣ ᐠየእሳትና የመን ፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይመጣል፤ እናም ከዚያ በኋላ በመላዕክት ᐠልሳን መናገርና ለእስ ራኤል ቅዱስም በምስጋና መጮህ ትችላ ላችሁ።

፲፭ ነገር ግን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ የወልድ ድምፅ እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፥ ለኃጢአታችሁ ንስሀ ከገባች ሁና፣ በውኃ በመጠመቅ ትዕዛዛቴን ለመ ጠበቅ ፈቃደኛ እንደሆናችሁ ለአብ ከመ ሰከራችሁ፣ እና የእሳትንና የመንፈስ ቅዱ ስን ጥምቀት በመቀበላችሁ፣ እናም በአዲስ ልሳን፣ አዎን፣ እንዲያውም በመላዕክት ልሳንም ለመናገር ከቻላችሁ በኋላ፣ ከዚ ህም በኋላ ᐟየምትክዱኝ ከሆነ፣ ፈፅሞ ባታ ውቁኝ ምንኛ ᐠይሻላችሁ ነበር።

፲፮ እናም ከአብ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ፥ አዎን፣ የተወደደው ልጄ ቃላት እውነትና የታመኑ ናቸው። እስከመጨረ ሻው የሚፀና እርሱ ይድናል።

፲፯ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ የህያው እግዚአብሔርን ልጅ ᐟምሳ ሌን በመከተል ሰው እስከመጨረሻው ᐠየማ ይፀና ከሆነ፣ መዳን እንደማይችል በዚህ አውቃለሁ።

፭ ᐟ ማቴ. ፫፡፲፩–፲፯።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
፯ ᐟ ዮሐ. ፭፡፴።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፰ ᐟ ቅ.መ.መ. የርግብ
መልእክት።
ᐠ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፯።
፱ ᐟ ፪ ኔፊ ፱፡፴፩፣
፫ ኔፊ ፲፱፡፲፫–፲፭፣
ት. እና ቃ. ፳፪፡፱።
፲ ᐟ ማቴ. ፬፡፲፱፣ ፳፡፳፪፣ ፱፡፱።
ᐠ ሞሮኒ ፯፡፲፩፣
ት. እና ቃ. ፶፯፡፪።
፲፩ ᐟ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ
ስጦታ።
ᐠ ሉቃ. ፱፡፶፯–፷፪፣
ዮሐ. ፲፪፡፳፮።
፲፫ ᐟ ገላ. ፫፡፳፯–፳፰።
ᐠ ቅ.መ.መ. እሳት፣
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፪፡፪–፫።
፲፬ ᐟ ማቴ. ፲፡፴፱፣ ፴፡፳፪፣ ፱፡፱።
ᐠ ᐟ ዮሐ. ፲፡፳–፳፯፣
ት. እና ቃ. ፴፮፡፳–፳፩።
ᐠ ᐟ ዮሐ. ፲፡፳–፳፯፣
ት. እና ቃ. ፴፮፡፳–፳፩።
ᐠ ᐟ ᐟ ᐟ

፲፯ ስለዚህ፣ ጌታችሁና አዳኛችሁ ሲያ
ደርግ እንዳየሁ የነገርኳችሁን ነገሮች አድ
ርጉ፤ መግቢያችሁን ታውቁት ዘንድ፣ ለዚ
ህም ነው እነዚህን ነገሮች የታዩኝ። የምትገ
ቡበትም በር ንስሀና የውኃ [ሀ]ጥምቀት ነው፤
እና ከእዚያም የኃጢአታችሁ [ለ]ስርየት በእ
ሳትና በመንፈስ ቅዱስ ይመጣሉ።
፲፰ እና ከእዚያም እናንተ ወደ ዘለዓለማ
ዊው ህይወት በሚመራው በዚህ [ሐ]በቀጭ
ኑና ጠባቡ [መ]ጎዳና ላይ ናችሁ፤ አዎን፣ በበሩ
ገብታችኋል፤ በአብና በወልድ ትዕዛዛት
መሰረትም አድርጋችኋል፤ እናም በትክክ
ለኛው መንገድ ከገባችሁ ትቀበላላችሁ ያለ
ውን የተስፋውንም ቃል በመፈፀም፣ ስለ
አብና ስለወልድ [ሠ]የሚመሰክረውን መንፈስ
ቅዱስ ተቀብላችኋል።
፲፱ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቼ፣ በጠባቡና በቀጭኑ ጎዳና ከገባችሁ
በኋላ፣ ሁሉ [ረ]ተደርጓልን? ብዬ እጠይ
ቃችኋለሁ። እነሆ፣ አይደለም፣ እላችኋ
ለሁ፤ በክርስቶስ ቃል በማይናወጥ [ሰ]እም
ነት ለማዳን ኃያል በሆነው መልካም ስራ
ሙሉ በሙሉ [ሸ]በመተማመን ባይሆን ኖሮ
እስከዚህ አትመጡም ነበር።
፳ ስለሆነም ፍጹም የሆነ [ቀ]የተስፋ ብር
ሃን፣ እናም የእግዚአብሔርና የሰዎች
ሁሉ [በ]ፍቅር እየኖራችሁ በክርስቶስ ባላ
ችሁ ፅኑነት [ተ]መቀጠል አለባችሁ። ስለሆ
ነም አብም፣ የክርስቶስን ቃል በመመገብ፣
እናም እስከመጨረሻው [ቸ]በመፅናት የምት
ቀጥሉ ከሆነ፣ እነሆ አብ እንዲህ ይላል፥ የዘ
ለዓለም ህይወት ይኖራችኋል።
፳፩ እናም አሁን፣ እነሆ የተወደዳችሁ
ወንድሞቼ፣ [ሀ]መንገዱ ይህ ነው፤ ሰው በእ
ግዚአብሔር መንግስት መዳን የሚችል
በት ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ [ለ]ምንም
መንገድም ሆነ [ሐ]ስም የለምና። እናም
አሁን፣ እነሆ፣ ይህ የክርስቶስ [መ]ትምህር
ትና፣ መጨረሻ የሌለው [ሠ]አንድ አምላክ፣
[ረ]የአብ፣ የወልድና፣ የመንፈስ ቅዱስ ብቸኛ
ውና እውነተኛው ትምህርት ነው። አሜን።

ምዕራፍ ፴፪

*መላዕክት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይናገ
ራሉ—ሰዎች መፀለይ እናም እውቀትን
ከመንፈስ ቅዱስ ማግኘት አለባቸው።
ከ፳፻፲፱–፳፻፳፭ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን፣ እነሆ፣ የተወደዳችሁ
ወንድሞቼ፣ እናንተ በጎዳናው ከገባችሁ
በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ በመ
ጠኑ በልባችሁ እንደምታሰላስሉ እገምታ
ለሁ። ነገር ግን፣ እነሆ፣ ስለምን እነዚህን
ነገሮች በልባችሁ ታሰላስላላችሁ?
፪ መንፈስ ቅዱስን [ሀ]ከተቀበላችሁ በኋላ
በመላዕክት [ለ]ልሳን መናገር እንደምትችሉ
የተናገርኳችሁን አታስታውሱም? እናም
አሁን፣ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በመላዕ
ክት ልሳን መናገር እንዴት ትችላላችሁ?
፫ [ሀ]መላዕክት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይና
ገራሉ፤ ስለዚህ፣ የክርስቶስን ቃል ይናገ
ራሉ። ስለሆነም፣ የክርስቶስን ቃል [ለ]ተመ
ገቡ እላችኋለሁ፤ እነሆ የክርስቶስ ቃል
ማድረግ ያለባችሁን ነገሮች በሙሉ ይነግ
ራችኋልና።
፬ ስለሆነም፣ አሁን እነዚህን ቃላት ከተና

፲፯ *ሀ* ሞዛያ ፲፰፡-፲።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፲፰ *ሀ* ፩ ኔፊ ፰፡-፳።
ለ ምሳ. ፬፡-፲፰።
ቅ.መ.መ. መንገድ።
ሐ የሐዋ. ፭፡-፳፱–፴፪።
፲፱ *ሀ* ሞዛያ ፬፡-፲።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ት.እና ቃ. ፫፡-፳።
፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ለ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሐ ቅ.መ.መ. መራመድ፣
ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
መ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፳፩ *ሀ* የሐዋ. ፬፡-፲–፲፪፣
፪ ኔፊ ፱፡-፴፩፣
አልማ ፴፯፡-፴፯፣
ት.እና ቃ. ፲፴፪፡-፳፪፣ ፳፭።
ለ ሞዛያ ፫፡-፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
መ ማቴ. ፯፡-፳፭፣
ዮሐ. ፯፡-፲፯–፲፯።
ሠ ፫ ኔፊ ፲፩፡-፳፯፣ ፴፭–፴፯።
ቅ.መ.መ. አንድነት።
ረ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
፴፪ *ሀ* ፫ ኔፊ ፱፡-፳።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡-፲፫።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ኤር. ፲፭፡-፲፯።

ገርኩ በኋላ፣ መረዳት ካልቻላችሁ፣ ይህም
ᵐስላልጠየቃችሁ፣ ወይም ስላላንኳኳችሁ
ነው፤ ስለሆነም፣ ወደ ብርሃኑ አልመጣች
ሁም፣ ነገር ግን በጨለማው ትጠፋላችሁ።
፭ እነሆም፣ በድጋሚ እላችኋለሁ በመ
ንገዱ የምትገቡ፣ እናም መንፈስ ቅዱስን
የምትቀበሉ ከሆነ፣ ማድረግ ያለባችሁን ነገ
ሮች ሁሉ ያሳያችኋል።
፮ እነሆ፣ ይህ የክርስቶስ ትምህርት ነው፣
እናም ለእናንተ በስጋ እራሱን ᵐእስከሚገ
ልፅ ድረስ ሌላ ትምህርት አይሰጥም። እናም
እርሱ ራሱን በስጋ ለእናንተ በሚገልፅበት
ጊዜ፣ የተናገራችሁን ነገሮች በትጋት ታደ
ርጋላችሁ።
፯ እናም አሁን እኔ ኔፊ፣ ብዙ ማለት አል
ችልም፤ መንፈስ እንዳልናገር አደረገኝ፣
እናም በሰዎች ᵐባለማመን፣ ክፋትና፣ ባለ
ማወቅ፣ እንዲሁም አንገተ ደንዳናነት የተነሳ
አዝናለሁ፤ ምክንያቱም እውቀትን አልፈ
ለጉም፣ ወይም ታላቁን እውቀት ᵃበግልፅ፣
እንዲሁም ቃል መግለጽ እስከሚቻልበት
ያህል፣ በተሰጣቸውም ጊዜ አልተረዱምና።
፰ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቼ፣ አሁንም በልባችሁ እንደምታሰላስሉ
አስተውላለሁ፤ እናም ይህን ነገር በሚመ
ለከት መናገር ስላለብኝ ያሳዝነኛል። ሰዎ
ችን ᵐእንዲፀልዩ የሚያስተምረውን መን
ፈስ ካዳመጣችሁት መፀለይ እንዳለባችሁ
ታውቃላችሁ፤ ᵃእርኩስ መንፈስ ሰዎችን
ፀሎት አያስተምርምና፣ ነገር ግን መፀለይ
እንደሌለባቸው ያስተምራቸዋል።
፱ ነገር ግን እነሆ፣ ሳትታክቱ ዘወትር
ᵐመጸለይ እንዳለባችሁ፤ በመጀመሪያ ወደ
አብ በክርስቶስ ᵃስም ካልፀለያችሁ ምንም
ነገር ለጌታ ማከናወን እንደማይገባችሁ፣
እርሱም ስራችሁን ቅዱስ እንደሚያደር
ግላችሁ፣ ስራችሁም ለነፍሳችሁ ᵃደህን
ነት እንደሚሆን እነግራችኋለሁ።

ምዕራፍ ፴፫

*የኔፊ ቃላት እውነት ናቸው—ስለክርስ
ቶስ ይመሰክራሉ—በክርስቶስ የሚያምኑ
በፍርድ ወንበር ፊት ምስክር ሆኖ በሚ
ቆመው በኔፊ ቃላት ያምናሉ። ከ፳፻፶፱–
፳፻፸፯ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን እኔ ኔፊ፣ በህዝቤ መካ
ከል የተነገሩትን ትምህርቶች በሙሉ መፃፍ
አልችልም፤ እንደመናገሬ አይነት በፅህ
ፈት ᵐነበዝ አይደለሁም፤ ምክንያቱም ሰው
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ᵃሲናገር የመንፈስ
ቅዱስ ኃይል ነው ወደ ሰዎች ልጆች ልብ
የሚያደርሰው።
፪ ነገር ግን እነሆ፣ በቅዱስ መንፈስ ላይ
ልባቸውን ᵐአጠጥረው በእነርሱ ውስጥ ቦታ
የሌላቸው ብዙዎች አሉ፣ ስለዚህ እነርሱ
የፃፉትንና ጠቃሚ አይደለም ብለው የገ
መቱአቸውን ብዙ ነገሮች ይጥላሉ።
፫ ነገር ግን እኔ ኔፊ፣ መፃፍ ያለብኝን
ፅፌአለሁ፣ እና ይህም በልዩ ለህዝቤ ታላቅ
ᵐዋጋ አለው ብዬ የምገምተው ነው። በእነ
ርሱ የተነሳ ያለማቋረጥም በቀን ᵃእፀልያ
ለሁ፣ እናም በሌሊት እምባዬ ትራሴን ያረ
ጥባል፤ ወደ ጌታም በእምነት እጮሀለሁ፣
ጩኸቴንም እንደሚሰማ አውቃለሁ።
፬ እናም ጌታ እግዚአብሔር ፀሎቴን ለህ
ዝቤ ጥቅም እንደሚቀድሰው አውቃለሁ።
እናም በድካም የፃፍኳቸው ቃላትም በእነ
ርሱ ዘንድ ᵐብርቱ ይሆናሉ፤ መልካምም
ያደርጉ ዘንድ ᵃያሳምናቸዋልና፤ ስለአባ
ቶቻቸውም ያሳውቃቸዋል፤ ስለክርስቶ
ስም ይናገራል፤ እናም ᵃዘለዓለማዊ ህይ

፩ ሀ ቅ.መ.መ. ለምን።
፪ ሀ ቮ ኔፊ ፲፩፡ ፰።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፪–ቮ፣ ያዕቆ. ፩፡ ፲ቮ።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ሞዛያ ፩፡ ፲፩። ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፱ ሀ ቮ ኔፊ ፳፡ ፩፣ ት. እና ቃ. ሮጌ፡ ፲፩።
ለ ሙሴ ፭፡ ፰።
ሐ አልማ ፴፩፡ ፳፯።
፴ቮ ፩ ሀ ኤተር ፲፪፡ ፳ቮ–፳፩።
ለ ት. እና ቃ. ፮፡ ፯–፰።
፪ ሀ ሔለ. ፯፡ ፴፭–፴፯።
ቮ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሳት መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ኢኖስ ፩፡ ፱–፲፪፣ ቃላት ፩፡ ፰።
፩ ሀ ኤተር ፲፪፡ ፳፯–፳፯።
ለ ሞሮኒ ፯፡ ፲ቮ።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።

ወት በሆነው በእርሱ እንዲያምኑና፣ እስ
ከመጨረሻውም እንዲፀኑ ያሳምናቸዋል።
፲ እናም በእውነት ᵐበግልፅነት መሰረት፣
ስለኃጢያት ᵃበፅኑ በመቃወም ይናገራል፤
ስለዚህ፣ ከዲያብሎስ መንፈስ ካልሆነ በቀር
እኔ በፃፍኩት ቃላት የሚናደድ ማንም ሰው
አይኖርም።
፲፩ በግልፅነት እደሰታለሁ፤ በእውነት እደ
ሰታለሁ፣ በእኔ ኢየሱስ እደሰታለሁ፣ ነፍ
ሴን ከሲኦል ᵐአድኗታልና።
፲፪ ለህዝቤ ᵐልግስና፣ እናም በፍርድ ወን
በር ብዙ እንከን የለሽ ነፍሳት እንደማገኝ
በክርስቶስ ታላቅ እምነት አለኝ።
፲፫ ለአይሁድ ልግስና አለኝ—ᵐአይሁድ
እላለሁ፣ ምክንያቱም እኔ የመጣሁበትን
ዘር ማለቴ ነው።
፲፬ ᵐለአህዛብም ደግሞ ልግስና አለኝ። ነገር
ግን እነሆ፣ በክርስቶስ ᵃካልታረቁ፣ እናም
ᵇበጠባቡ በር ካልገቡ፣ እናም ወደ ህይ
ወት በሚያመራው ᶜበቀጭኑ ጎዳና ᶜካል
ተራመዱ፣ እናም እስከሙከራ ቀናቸውም
መጨረሻ ድረስ በጎዳናው ጉዞአቸውን ካል
ቀጠሉ፣ በማናቸውም ላይ ተስፋ አላደር
ግም።
፲፭ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቼ፣ እናም ደግሞ አይሁድና፣ በምድር
ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ፣ እነዚህን ቃላት አድ
ምጡም፣ በክርስቶስም ᵐእመኑ፤ እንዲሁም
በእነዚህ ᵃቃላት የማታምኑ ከሆነ በክርስቶስ
እመኑ። እናም በክርስቶስ የምታምኑ ከሆነ
በእነዚህ ᵇቃላት ታምናላችሁ፣ እነርሱ የክ
ርስቶስ ቃላት ናቸውና፣ እነርሱንም ለእኔ
ሰጠኝ፤ እናም ሰዎች ሁሉ መልካም እንዲ
ሰሩ ᶜያስተምራሉ።
፲፮ እናም የክርስቶስ ቃላት ካልሆኑም
ፍረዱ—በመጨረሻው ቀን የእርሱ ቃል
መሆናቸውን ክርስቶስ ᵐበኃይልና በታላቅ
ክብር ያሳያቸኋል፤ እናም እኔና እናንተ
በፍርድ ᵃወንበር ፊት ለፊት እንቆማለን፤
እናም ምንም እንኳን ደካማ ብሆንም እነ
ዚህን ነገሮች እንድፅፍ በእርሱ እንደታዘ
ዝኩ ታውቃላችሁ።
፲፯ እናም ሁላችንም እንኳን ባንሆን ብዙ
ዎቻችን በታላቁና በመጨረሻው ቀን ᵐበመ
ንግስቱ እንድን ዘንድ በክርስቶስ ስም ለአብ
እፀልያለሁ።
፲፰ እናም አሁን፣ የእስራኤል ቤት ሁሉ
የሆናችሁ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እናም
በምድር ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ፣ ከመሬት
ᵐእንደሚጮህ ድምፅ እናገራችኋለሁ፥ ያ
ታላቁ ቀን እስኪመጣ መልካም ይሁንላ
ችሁ።
፲፱ እናም ከእግዚአብሔር ቸርነት የማ
ትካፈሉ፣ እናም የአይሁዶችንም ᵐቃላት፣
ደግሞም የእኔን ᵃቃላት፣ እንዲሁም ከእግ
ዚአብሔር በግ አፍ የሚወጣውን ቃል የማ
ታከብሩ፣ እነሆ፣ ዘለዓለማዊ ስንብት እላ
ችኋለሁ፣ እነዚህ ቃላት በመጨረሻው ቀን
ᵇይከንኗችኋልና።
፲፭ በምድር ያተምሁት፣ ᵐበፍርድ ወንበር
በእናንተ ላይ ይቀርባል፤ ጌታ እንዲህ አዞ
ኛልና፣ መታዘዝ አለብኝ። አሜን።

፭ ሀ ፪ ኔፊ ፴፩፡፫፣
ያዕቆ. ፩፡፲፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፡፩–፫፣
፪ ኔፊ ፱፡፴።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ልግስና።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ፪ ኔፊ ፱፡፳፩።
መ ሔለ. ፫፡፳፱–፴፣
ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፪።
ሠ ቅ.መ.መ. መራመድ፣
ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ሐ ሞሮኒ ፣ ፳፯–፳፱።
መ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፰።
፲፩ ሀ ኤተር ፭፡፱፣
ሞሮኒ ፯፡፴፭።
ለ ራዕ. ፳፡፲፪፣
ሞሮኒ ፣ ፴፩።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
፲፫ ሀ ኢሳ. ፳፱፡፱፣
፪ ኔፊ ፳፯፡፲፯።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲፩፣
ኤተር ፱፡፳–፣።
፲፭ ሀ ቃላት ፩፡፲፩።

መፅሐፈ ያዕቆብ

የኔፊ ወንድም

ለወንድሞቹ የሰበካቸው ቃላት። እርሱ የክርስቶስን ትምህርት ለማጥፋት የተመኘውን ሰው አሳፈረው። የኔፊን ህዝብ ታሪክ በተመለከተ ጥቂት ቃላት።

ምዕራፍ ፩

ያዕቆብና ዮሴፍ ሰዎች በክርስቶስ እንዲ ያምኑና ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ ለማሳመን ሞከሩ—ኔፊ ሞተ—ክፋት በኔፋውያን መካከል ተስፋፋ። ፭፻፸፬–፭፻፸፭ ም.ዓ. ገደማ።

[1] ነሆም እንዲህ ሆነ፣ ሌሂ ኢየሩሳሌ ምን ለቆ ከወጣ ሃምሳ አምስት ዓመ ታት አለፉ፤ ስለዚህ፣ ኔፊ፤ ለእኔ [a]ለያዕ ቆብ እነዚህ ነገሮች የተፃፉበትን [b]ትንሹን ሰሌዳ በተመለከተ [c]ትዕዛዝን ሰጠኝ።

[2] እናም እኔ ያዕቆብ፣ በጣም የከበሩ ናቸው ብዬ የማስባቸውን ጥቂት ነገሮች በእ ነዚህ ሰሌዳዎች ላይ እንድፅፍ፤ የኔፊ ህዝብ ተብለው ስለሚጠሩት ታሪክም ባጭሩ ካል ሆነ በስተቀር መፃፍ እንደሌለብኝም ትዕዛ ዝን ሰጠኝ።

[3] እርሱም የህዝቡን ታሪክ በሌላኛው የእ ርሱ ሰሌዳ ላይ መፃፍ እንዳለበት፣ እና እኔ እነዚህን ሰሌዳዎች ማቆየትና ለዘሮቼም፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ እን ዳለብኝ ተናግሯል።

[4] እናም ቅዱስ የሆነ ሰበካ፣ ወይም ታላቅ የሆነ ራዕይ፣ ወይም ትንቢት፣ ካለ በእነ ዚህ ሰሌዳዎች ላይ [d]ዋና ዋናዎቹን መቅ ረፅ፣ እስከተቻለም ድረስ ለክርስቶስ እና ለህዝባችን ስል መጻፍ አለብኝ።

[5] በእምነትና በታላቅ ጭንቀት የተነሳ ህዝባችንን በተመለከተ፣ ምን ነገሮች በእ ነርሱ ላይ [e]መሆን እንዳለባቸው በእውነት ለእኛ ተገልፆልናል።

[6] እናም ደግሞ እኛ ብዙ ራዕይና ብዙ የት ንቢት መንፈስ ነበረን፣ ስለዚህ [f]ስለክርስ ቶስ እና ስለሚመጣው መንግስቱም እና ውቅ ነበር።

[7] ስለሆነም የእስራኤል ልጆች [g]በምድ ረበዳው በነበሩበት ወቅት በፈተናው ጊዜ [h]በአመጽ እንደነበሩ ወደ እረፍቱ [i]እንዳ ይገቡ በማንኛውም መንገድ ቢሆን በቁጣው እንዳይምል፣ ህዝቦቻችን ወደ [j]እረፍ ቱም ይገቡ ዘንድ ወደ ክርስቶስ [k]እንዲ መጡ እናም የእግዚአብሔርን በጎነት እን ዲካፈሉ እናሳምናቸው ዘንድ በትጋት ሠራን።

[8] ስለዚህ፣ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ [l]ለቁጣ የሚቀሰቅሰውን አመፅ [m]እንዳያ ምፁ፣ ነገር ግን ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ እን ዲያምኑና፣ ሞቱን ይገነዘቡ ዘንድ፣ እናም [n]የመስቀሉን ስቃይና የዓለምን መሳለቅ ይቀበሉ ዘንድ ለማሳመን እንድንችል የእ ግዚአብሔርን እርዳታ እንፈልጋለን፤ ስለ ሆነም፣ እኔ ያዕቆብ፣ የወንድሜ ኔፊን ትዕ ዛዛት ለመፈፀም ኃላፊነቱን ወሰድኩ።

[9] እንግዲህ ኔፊ መሸምገል ጀመረ፣ እናም በቅርቡ [o]እንደሚሞት ተገነዘበ፤ ስለዚህ፣

---

[a] ፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የሌሂ ልጅ።
ለ ፪ ኔፊ ፭፡፳፯–፴፫፤ ያዕቆ. ፫፡፲፫–፲፭። ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ሐ ያዕቆ. ፯፡፳፯።

[b] ፩ *ሀ* ይህም ከሌላ የሚልቅ፣ አስፈላጊ እቃዎች ማለት ነው።

[c] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፪።

[d] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፡፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[e] ፩ *ሀ* ዘኍል. ፳፯፡፳፭፤ ፩ ኔፊ ፣፣፯፡፣ ፳፣–፳፩።
ለ ዕብ. ፣፡፡፳።
ሐ ዘኍል. ፣፡፡፣ ፳፣፡፣ ዘዳግ. ፩፡፴፩–፴፣፤ ት. እና ቃ. ፹፡፡፡፣ ፳፣–፳፭።
መ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፡፴፩፤ ኦምኒ ፩፡፳፣፣፤ ሞሮኒ ፣፡፴፪።

[f] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፣፡፤ ፴፤
አልማ ፣፪፡፴፣–፴፣፤ ሔሌ. ፣፡፣፡።
ለ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ሐ ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፣፣፡፤ ፳፭–፳፣ (ተጨማሪ)፤ ሉቃ. ፣፡፡፡፣ ፳፣፡።

[g] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፩፡፣፡፡፤ ፣፡፡–፣፡፡።

[h] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፪፡፡–፣፡፡።

[i] ፩ *ሀ* ዘኍል. ፳፣፡፣ ፳፣፡፣ ፩ ኔፊ ፣፣፡፣ ፣፡–፣፡፡።
ለ ዕብ. ፣፡፡፣ ፳፡።
ሐ ዘኍል. ፣፡፡፣ ፳፣፡፣ ዘዳግ. ፩፡፴፩–፴፣፤ ት. እና ቃ. ፹፡፡፡፣ ፳፣–፳፭።
መ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፡፴፩፤ ኦምኒ ፩፡፳፣፣፤ ሞሮኒ ፣፡፴፪።

[j] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡፡፣ ፣፡፡–፣፡፡።

[k] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[l] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[m] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[n] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[o] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

አንድ ሰው አሁን በህዝቡ ላይ ^ንጉሥና መሪ እንዲሆን፣ በመሣፍንቱ አገዛዝ መሰ ረት ሓቀባው።

፤ ህዝቡ ኔፌን እጅግ በመውደዱ፣ እር ሱም ለእነርሱ ታላቅ ጠባቂ በመሆኑ፣ የላ ባንንም ^ጎራዴ ለእነርሱ ለመከላከያ በመ ጠቀሙ፣ እናም ለደህንነታቸው በጊዜው ሁሉ በመስራቱ—

፤፩ ስለሆነም፣ ህዝቡ ስሙን በማስታወስ ለመቆየት ፈለጉ። እናም በነገስታት አገዛዝ መሠረት በእርሱ ምትክ የሚነግሱት ሁሉ ሁለተኛው ኔፌ፣ ሶስተኛው ኔፌና፣ ወዘተ ተብለው በህዝቡ ተሰየሙ፤ እናም ስማቸው ምንም ቢሆን፣ በህዝቡ እንዲህም ተሰየሙ።

፤፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ኔፌ ሞተ።

፤፫ አሁን ^ላማናውያን ያልነበሩት ህዝቦች ኔፋውያን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ፣ ^ኔፋው ያን፣ ያዕቆባውያን፣ ዮሴፋውያን፣ ^ዞራማ ውያን፣ ላማናውያን፣ ልሙኤላውያን እና እስማኤላውያን ተብለው ይጠሩ ነበር።

፤፬ ነገር ግን፣ እኔ ያዕቆብ፣ ከእንግዲህ በኋላ እነርሱን በዚህ ስም አልለያቸውም፣ ነገር ግን የኔፌን ህዝቦች ለማጥፋት የሞ ከሩትን፣ ላማናውያን፣ ብዬ ^እጠራቸ ዋለሁ፣ እናም በነገስት አገዛዝ መሰረት፣ ለኔፌ ወዳጅ የሆኑትን፣ ^ኔፋውያን፣ ወይም ^የኔፌ ህዝብ፣ ብዬ እጠራቸዋለሁ።

፤፭ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የኔፌ ህዝብ፣ በሁለተኛው ንጉስ የንግሥ ዘመን ልባቸውን ማደንደን ጀመሩ፣ እናም በጥቂቱ እራሳ ቸውን እንደ ጥንቱ ዳዊት እንዲሁም እንደ ልጁ ሰለሞን ብዙ ^ሚስቶችና ዕቁባቶችን በማድረግ በክፉ ልማድ የእራሳቸውን ፍላ ጎት ማሟላት ጀመሩ።

፤፮ አዎን፣ እናም ደግሞ እነርሱ ብዙ ወርቅና ብር መፈለግ ጀመሩ፣ እናም በኩ ራት እራሳቸውን ከፍ ማድረግ ጀመሩ።

፤፯ ስለዚህ፣ እኔ ያዕቆብ፣ መጀመሪያ ^መልእክቴን ከጌታ ካገኘሁ በኋላ ^በቤ ተመቅደስ ውስጥ ሳስተምራቸው እነዚህን ቃላት ሰጠኋቸው።

፤፰ እኔ ያዕቆብ፣ እናም ወንድሜ ዮሴፍ፣ ለዚህ ህዝብ ካህናትና መምህራን እንድን ሆን በኔፌ እጅ ^ተቀብተን ነበር።

፤፱ እናም ኃላፊነቱንም በመውሰድ፣ የእ ግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ትጋት ካላስተ ማርናቸው የህዝቡን ኃጢኣት በራሳችን ላይ በመቀበል ^ኃላፊነታችንን ለጌታ ^አኃላን፤ ስለሆነም፣ ^ደማቸው ልብሳችንን እንዳይ በክል ባለን ኃይል ሰራን፤ አለበለዚያ ደማ ቸው ልብሳችንን ይበክላልና፣ እናም በመ ጨረሻው ቀን እንከን የለሽ ሆነን አንገኝም።

ምዕራፍ ፪

ያዕቆብ የሀብትን ፍቅር፣ ኩራትና፣ ምን ዝርናን አወገዘ—ሰዎች ወገናቸውን ለመ ርዳት ሀብትን ሊሹ ይችላሉ—ጌታ ከኔ ፋውያን መካከል ማንኛውም ሰው ከአንድ በላይ ሚስት እንዳይኖረው አዘዘ—ጌታ በሴቶች ንፁህነት ይደሰታል። ከ፳፻፸፬–፳፻፸፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ የኔፌ ወንድም ያዕቆብ፣ ኔፌ ከሞተ በኋላ ለኔፌ ህዝብ የተናገራቸው ቃላት—

፪ አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እኔ ያዕቆብ እግዚአብሔር በሰጠኝ ሀላፊነት መሰረት፣ ሀላፊነቴን በጥሞና ለመወጣት፣ እናም ኃጢአታችሁንም ከመጎናፀፊያዬ

፤ለ ፪ ኔፌ ፤፯፡፪፣ ጂረም ፩፡፲። ሐ ቅ.መ.መ. መቀባት።
፤ሀ ፩ ኔፌ ፡፡፡፣ ፪ ኔፌ ፡፡፡፣ ቃላት ፩፡ ፤፲፣ ሞዛያ ፩፡ ፤፲፯፣ ት.እና ቃ. ፤፲፯፡ ፩።
፤፲ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፤፲፣ ት.እና ቃ. ፫፡ ፤፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. ኔፋውያን።
ሐ ፩ ኔፌ ፡፣ ፴፩፣ ፡ ኔፌ ፩፡ ፴፯–፴፯።
፤፲፡ ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፤፪፣ አልማ ፪፡ ፤፩።
ለ ፪ ኔፌ ፡፣ ፤፩።
ሐ ፪ ኔፌ ፩፡ ፡፡
፤፲፩ ሀ ት.እና ቃ. ፲፴፪፡ ፴፰–፴፡፡
፤፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ለ ፪ ኔፌ ፩፡ ፤፲፯።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
፤፲፰ ሀ ፪ ኔፌ ፩፡ ፳፯።
፤፡፡ ሀ ት.እና ቃ. ፲፯፡ ፣፡፡–፪።
ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፳፩ እናም አሁን ቤተክርስቲያኗ በምድ ሪቱ ላይ ከተመሰረተች በኋላ—በዲያብሎስ ላይ ᵇድል ካገኘች፣ እናም በንፅህና በም ድሪቱ ላይ የጌታ ቃል አንድ ላይ ከተሰ በከ በኋላ፣ እናም ጌታ በህዝቡ ላይ በረከትን አፈሰሰ—በኔፊ ህዝብ ላይ አስራ አራተኛው የመሣፍንት የንግስ ዘመን በዚሁ ተፈፀመ።

ለእግዚአብሔር ቃል በመንግስቱ የነበራ ቸውን መብት የናቁት፣ እናም ላማናው ያንን ለመስበክ ወደኔፊ ምድር የሄዱት የሞዛያ ልጆች፣ የስቃያቸውና የመዳናቸው ታሪክ—አልማ እንደመዘገበው።

ምዕራፍ ፲፯ እስከ ፳፯ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፲፯

የሞዛያ ልጆች የትንቢትና የራዕይ መንፈስ አላቸው—ቃሉን ለላማናውያን ለማወጅ ወደ ተለያዩ መንገዶች ተጓዙ—አሞን ወደ እስማኤል ምድር ተጓዘ፣ እናም የን ጉስ ላሞኒ አገልጋይ ሆነ—አሞን የንጉሱን መንጋዎች አዳነ፣ እናም ጠላቶቹን በሴቡስ ወንዝ ገደለ። ከቁጥር ፩–፮፣ በ፭–፯ ም.ዓ. ገደማ፣ ቁጥር ፬፣ ከ፣ ፩–፭–፭ ም.ዓ. ገደማ፤ እናም ከቁጥር ፮–፳፪፣ በ፣ ፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ከጌዴ ዎን ምድር ከደቡብ በኩል ወደ ማንቲ ምድር ሲጓዝ፣ እነሆ በመገረም ᵇከሞዛያ ልጆች ጋር ወደ ዛራሔምላ ሲጓዙ ᵃተገናኘ።

፪ እንዲሁም የሞዛያ ልጆች መልአኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ᵇሲገለጥለት ከአልማ ጋር ነበሩ፤ ስለዚህ አልማ ወንድሞቹን በመመ ልከቱ እጅግ ተደሰተ፤ እናም ደስታውን ይበልጥ የጨመረው አሁንም በጌታ ወን ድሞቹ በመሆናቸው ነበር፤ አዎን፣ እናም እውነትን በማወቅ የጠነከሩ ነበሩ፤ ትክክ ለኛ ማስተዋል የነበራቸው፣ የእግዚአብሔ ርን ቃል ያውቁ ዘንድ ቅዱሳን መጻሕፍትን በትጋት ᵃየሚያጠኑ ሰዎች ነበሩ።

፫ ነገር ግን ይህ ብቻም አይደለም፤ እራ ሳቸውን በብዙ ᵇጸሎትና ፆም አተጉ፤ ስለ

፲፯ ለ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
፲፯ ሀ ያዕቆ. ፭፡ ፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ሐ አልማ ፲፪፡ ፴፯፤ ፲፫፡ ፣–፲፫።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።
ለ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሐ አልማ ፲፭፡ ፣፫።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፱–፭።
ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፱፤ ፣ ኔፊ ፲፩፡ ፭–፲፱።
፳፩ ሀ አልማ ፲፭፡ ፣፲፯።
ለ አልማ ፳፭፡ ፣፲፯።
፪ ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፴፱።
ለ አልማ ፳፭፡ ፣፲፯።
፪ ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፣፩–፣፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት፤ ጾም፣ መጾም።

ዚህ የትንቢት መንፈስና፣ የራዕይ መን ፈስ ነበራቸው፣ እናም ^በሚያስተምሩ በት ጊዜም በእግዚአብሔር ኃይልና ስል ጣን አስተማሩ።

፩ እናም የእግዚአብሔርን ቃል በላማናው ያን መካከል ለአስራ አራት ዓመታት አስተ ማሩ፤ እናም ብዙዎችን ወደ እውነት ᵛበማ ምጣት አጥጋቢ ^ውጤት አግኝተው ነበር፤ አዎን በቃላቸው ኃይልም ስሙን ለመጥ ራትና በፊቱም ኃጢአታቸውን ^ለመና ዘዝ ብዙዎች በእግዚአብሔር መሰዊያ ፊት ቀረቡ።

፪ አሁን የጉዞአቸው ሁኔታ ይህን ይመ ስል ነበር፣ በብዛት ተሰቃይተው ነበርና፤ በአካልም ሆነ በአዕምሮ በረሃብ፣ በጥማ ትና በድካም ብዙ ተሰቃዩ፣ እናም ደግሞ በመንፈስ ብዙ ᵛሰሩ።

፫ አሁን ጉዞአቸውም እነዚህ ነበሩ፥ በመ ሣፍንቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ አባታ ቸው ለእነርሱ ለመስጠት የፈለገውን መን ግስት፣ እናም ደግሞ ይህ የህዝቡ ምኞት ነበር፣ ᵛከተቃወሙ በኋላ አባታቸው ሞዛ ያን ^ተሰናበቱ፤

፬ ይሁን እንጂ ከዛራሔምላ ምድር ወጥ ተው ሄዱ፣ እናም ጎራዴአቸውንና ጦራ ቸውን፣ ቀስቶቻቸውንና፣ ሻምላቸውን፣ እንዲሁም ወንጭፎቻቸውን ወሰዱ፤ እናም በምድረበዳ ባሉበት ጊዜ ምግባቸውን ያዘ ጋጁ ዘንድ ይህን አደረጉ።

፭ እናም ወደ ኔፊ ምድር የእግዚአብሔ ርን ቃል ለላማናውያን ለመስበክ ለመሄድ ከመረጧቸው ጋር ወደ ምድረበዳው ሄዱ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በምድረበዳው ውስጥ ለብዙ ቀናት ተጓዙ፣ እናም ጌታ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ዘንድ መንፈሱን ይሰጣቸው ዘን ድና፣ ከእነርሱ ጋር ይቆዩ ዘንድ፣ ወንድሞ ቻቸው ላማናውያኖችን ወደ እውነት ለማ ምጣት፣ የሚቻል ከሆነም ትክክል ያልሆ ነውን፣ የአባቶቻቸውን ᵛወግ መጥፎነቱን ይረዱት ዘንድ በእግዚአብሔር እጅ ^መሳ ሪያ እንዲሆኑ በርትተው ᵖሙ እንዲሁም ^ፀለዩ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ ᵛበመንፈሱ ^ጎበ ኛቸውና፣ እንዲህ አላቸው፥ ^ተፅናኑ። እነ ርሱም ተፅናኑ።

፰ እናም ደግሞ ጌታ እንዲህ አላቸው፥ ወደ ወንድሞቻችሁ ወደ ላማናውያን ሂዱ፣ ቃሌንም መስርቱ፤ ይሁን እንጂ በእኔ ለእነ ርሱ መልካም ምሳሌ ታሳዩ ዘንድ በስቃያ ችሁ ፅናትና ᵛትእግስት ይኑራችሁ፣ እናም ለብዙ ነፍስ መዳኛ በእጆቼ መሳሪያ አደር ጋችኋለሁ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ የሞዛያ ልጆችና፣ ደግሞ ከእነርሱ ጋር የነበሩት፣ ልብ የጌ ታን ቃል ወደ ላማናውያን በመሄድ ለመ ናገር ድፍረትን አገኙ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ በላማናውያን ምድር ዳርቻ በደረሱ ጊዜ፣ ᵛበመኸራቸው ወቅ ትም በኋላ በድጋሚ እንደሚገናኙ በጌታ በማመን እርስ በርስ ^ተለያዩና፣ አንዱ ከሌ ላኛው ተከፈሉና ተለዩ፤ ለመስራት በእራ ሳቸው ላይ የወሰዱት ስራ ታላቅ እንደሆነ ገምተዋልና።

፲፩ እና በእርግጥም ታላቅ ነበር፣ ምክን ያቱም የጌታን ቃል ᵛዱር፣ ልበ ጠጣሮ ችና፣ አስፈሪ ለሆኑ ሰዎች ለመስበክ በእ ራሳቸው ላይ ወስደውታልና፤ ህዝቡም ኔፋ ውያንን በመግደልና በመስረቅ እንዲሁም በመዝረፍ የሚደሰት ነበር፤ እናም ልባቸው በሀብት ላይ፣ እንዲሁም በወርቅና በብር፣ እናም በከበሩት ድንጋዮች ላይ የተደገፈ ነበር፤ ይሁን እንጂ እነዚህን ነገሮች በእ

፫ ^ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ—በመንፈስ ማስተማር።
፩ ᵛ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
^ አልማ ፳፱፡፲፡፡
^ ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
፭ ᵛ አልማ ፳፡፲፡
፮ ᵛ ሞዛያ ፳፱፡፫፡
^ ሞዛያ ፳፡፭፡ ፭–፱።
፱ ᵛ አልማ ፫፡ ፲–፲፪።
^ ሞዛያ ፳፫፡፲፣ አልማ ፳፮፡፫።
^ አልማ ፳፮፡፲፮፡ ^ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲ ᵛ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
^ አልማ ፳፮፡፳፮።
^ ት.እና ቃ. ፭፡፲፮።
፲፩ ᵛ አልማ ፳፡፳፱።
ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፲፫ ᵛ ማቴ. ፱፡ ፴፯።
^ አልማ ፳፭፡ ፭።
፲፩ ᵛ ሞዛያ ፲፡ ፲፪።

ጃቸው ሳይሰሩ በግድያና በዝርፊያ ማግኘ ትን ተመኙ።

፲፭ እነርሱ እንደዚህ ከንቱ ሰዎች ነበሩ፣ ብዙዎቻቸው ጣዖትን አምላኪዎች ነበሩ፣ እናም በአባቶቻቸው [a]ባህል የተነሳ [b]የአም ላክ እርግማን በእነርሱ አርፎ ነበር፤ ይህም ቢሆን ንስሃ እስከገቡ ድረስ የጌታ ቃል ኪዳን ለእነርሱ ተዘርግተውላቸዋል።

፲፮ ስለዚህ፣ እነርሱም ወደ ንስሃ፣ እናም ምናልባትም የቤዛነትን ዕቅድ ወደማወቅ ያመጡአቸው ዘንድ፣ ለዚህም [c]ምክንያት ነበር የሞዛያ ልጆች ስራውን በእራሳቸው ላይ የወሰዱት።

፲፯ ስለዚህ እራሳቸውን ከሌላኛው ለዩ፣ እናም ከመካከላቸው ለእነርሱ በተሰጠው በእግዚአብሔር ቃልና ኃይል መሰረት እያ ንዳንዱ ሰው ብቻውን ሄደ።

፲፰ እንዲሁም አሞን ከመካከላቸው ዋና ስለነበር፣ ወይም እነርሱን ረዳቸው፣ እናም እንደጥሪአቸው መሰረት [d]ከባረካቸውና የጌ ታን ቃል ካካፈላቸው፣ እናም ከመሄዱም በፊት ከረዳቸው በኋላ ከእነርሱ ተለየ፤ እን ደዚህም የተለያዩ ጉዞአቸውን በምድሪቱ አደረጉ።

፲፱ እናም አሞን ወደ እስማኤል ምድር ሄደ፣ ምድሪቱም የተጠራችው ላማናው ያን በሆኑት [e]በእስማኤል ልጆች ስም ነበር።

፳ እናም አሞን በእስማኤል ምድር በገባ ጊዜ፣ በእጃቸው የወደቁትን ኔፋውያን ሁሉ ማሰር፣ እናም በንጉሱ ፊት መውሰ ዳቸው ባህል ስለነበር፣ ላማናውያን ወሰዱ ትና አሰሩት፤ እናም እንደ ፈቃዱና ደስ ታው ለመግደል፣ ወይም በምርኮ ለማቆ የት፣ ወይም ወደ ወህኒ ለመጣል፣ ወይም ከራሱ አገር ለማስወጣት፣ ንጉሱ እንደ ፍላጎቱ ያደርግ ዘንድ እንደዚህ ይተው ለት ነበር።

፳፩ እናም አሞን በእስማኤል ምድር በነ ገሰው ንጉስ ፊት ተይዞ ቀረበ፤ ስሙም ላሞኒ ይባል ነበር፣ እርሱም የእስማኤል ዝርያ ነበር።

፳፪ እናም በምድሪቱ ከላማናውያን፣ ወይም ከእርሱ ህዝቦች፣ ጋር ለመኖር ፈቃዱ እንደሆነ አሞንን ንጉሱ ጠየቀው።

፳፫ እናም አሞን እንዲህ አለው፥ አዎን፣ ከዚህ ህዝብ ጋር ለተወሰነ ጊዜ፣ አዎን፣ እናም ምናልባት እስከምሞትባት ቀን ድረስ ለመኖር እፈልጋለሁ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ላሞኒ በአ ሞን እጅግ ተደሰተና፣ የታሰረበት እንዲ ፈታ አደረገ፤ እናም አሞን ከሴት ልጆቹ አንዷን እንዲያገባለት ፈለገ።

፳፭ ነገር ግን አሞን እንዲህ አለው፥ አይ ሆንም፣ ነገር ግን አገልጋይህ እሆናለሁ። ስለዚህ አሞን ለንጉስ ላሞኒ አገልጋይ ሆነ። እናም እንዲህ ሆነ በላማናውያን ባህል መሰ ረት የላሞኒን መንጋዎችን ለመጠበቅ ከሌ ሎች አገልጋዮች ጋር ተሰማራ።

፳፮ እናም ለሶስት ቀናት ንጉሱን ካገለ ገለ በኋላ፣ የሴቡስ ውሃ ተብሎ ወደሚጠ ራው ውሃ ወዳለበት ስፍራ ከብቶቻቸውን ከላማናውያን አገልጋዮች ጋር ውሃ ለማጠ ጣት ሄደ፣ እናም ላማናውያን በሙሉ ከብ ቶቻቸው ውሃ እንዲያገኙ ወደ እዚህ ቦታ መርተዋቸው ነበር—

፳፯ ስለዚህ፣ አሞንና የንጉሱ አገልጋዮች መንጋዎቻቸውን ወደዚህ የውሃ ስፍራ እየ ነዱ በወሰዱ ጊዜ፣ እነሆ ወደውሃው ከመን ጋዎቻቸው ጋር የነበሩት የተወሰኑ ላማናው ያን ቆሙ፣ እናም የአሞንንና የንጉሱ አገል ጋዮች መንጋዎችን በታተኑአቸው፣ እናም በብዙ አቅጣጫ እስከሚበታተኑም አባረ ሩአቸው።

፳፰ እንግዲህ የንጉሱ አገልጋዮች እን ዲህ በማለት ማጉረምረም ጀመሩ፥ እንግ ዲህ ንጉሱ እነዚህ ሰዎች በክፋታቸው መን ጋዎቻቸውን በመበተናቸው ምክንያት በወ ንድሞቻችን ላይ እንዳደረገው ይገድለናል።

፲፭ *a* አልማ ፱፡፲፮–፳፩፤ ፲፰፡፭–፮።
b አልማ ፫፡፯–፲፱፤ ፫ ኔፊ ፪፡፲፭–፲፯።

፲፯ *c* ሞዛያ ፳፰፡፭–፮–፫።
፲፰ *d* ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።

፲፱ *e* ፩ ኔፊ ፯፡፭–፮–፯።

እናም እንዲህ በማለት በሀይል አለቀሱ፥ እነሆ መንጋዎቻችን ተበትነዋል።

፳፩ እንግዲህ መገደላቸውን ፈርተው አለቀሱ። እንግዲህ አሞን ይህንን በተመ ለከተ ጊዜ ልቡ በደስታ ተሞላ፤ እንዲ ህም አለ፥ ለንጉሱ እነዚህን ከብቶች በመ መለስ፣ የአገልጋይ ጓደኞቼን ልብ አሸንፍ ዘንድ፣ በቃሌም እንዲያምኑ እመራቸው ዘንድ ለእነዚህ ከእኔ ጋር አገልጋዮች ለሆ ኑት ኃይሌን፣ ወይንም በውስጤ ያለውን ሀይል አሳያቸዋለሁ።

፳፪ እናም አሁን፣ እነዚህ ወንድሞቼ በማ ለት የጠራቸውን ስቃይ በተመለከተ ጊዜ፣ ይህ የአሞን ሀሳብ ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ እንዲህ በማለት በቃሉ አበረታታቸው፥ ወንድሞቼ፣ አት ፍሩም መንጋዎቹን ለመፈለግም እንሂድ፣ እናም በአንድ ላይ እንሰበሰባቸዋለን፣ ወደ ውሃው ስፍራ እንመልሳቸዋለንም፣ እንደ ዚህም መንጋዎቹን ለንጉሱ እንጠብቃለን፣ እርሱም አይገድለንም።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ መንጋዎቹን ፍለጋ ሄዱ፣ አሞንንም ተከተሉት፣ እናም በፍ ጥነት ሮጡና፣ የንጉሱን መንጋዎች መለ ሱአቸው፤ በአንድ ላይ ወደ ውሃው በድ ጋሚ ሰበሰቡአቸው።

፳፫ እናም እነዚያ ሰዎች በድጋሚ ከብ ቶቹን ለመበታተን ተነሱ፤ ነገር ግን አሞን ለወንድሞቹ እንዲህ አላቸው፥ መንጋዎቹ እንዳይሸሹ ክበቡአቸው፤ እናም እኔ እሄ ዳለሁና፣ ከብቶቻችንን ከሚያባርሩት ጋር እጣላለሁ።

፳፮ ስለዚህ፣ አሞን እንዳዘዘው አደረጉ፤ እርሱም ሄደና በሴቡስ ውሃ አጠገብ የነበሩ ትን ለመጣላት ተነሳ፤ እናም እነርሱ በቁጥ ራቸው ብዙ ነበሩ።

፳፯ ስለዚህ ከእነርሱ አንዱ ሰው እርሱን እንደፈለገው ለመግደል ይችላል በማለት በመገመታቸው አሞንን አልፈሩትም ነበር፣ ጌታ ለሞዛያ ልጆቹን ከእጃቸው [ሀ]እንደሚ ያወጣ ቃል መግባቱን አላወቁምና፣ ስለጌ ታም ቢሆን ምንም አያውቁም ነበር፤ ስለ ዚህ በወንድሞቻቸው ጥፋት ተደሰቱ፤ እናም በዚህ ምክንያት የንጉሱን ከብቶች ለማባረር ተነስተዋል።

፳፯ ነገር ግን [ሁ]አሞን ተነሳ እናም በወ ንጭፉ ድንጋይ በእነርሱ ላይ መወርወር ጀመረ፤ አዎን፣ በታላቅ ሀይል ድንጋይ በመካከላቸው በወንጭፉ ወረወረ፤ እናም [ሂ]የተወሰኑትን በመግደሉ በሀይሉ መደነቅ ጀምሩ፤ ይሁን እንጂ ወንድሞቻቸው ስለ ተገደሉባቸው ተቆጡና፣ እርሱ እንዲወ ድቅ ቆርጠው ነበር፣ ስለዚህ በድንጋዮቻ ቸው [ሃ]ሊመቱት እንዳልቻሉ በመመልከታ ቸው ሊገድሉት ዱላቸውን ይዘው መጡ።

፳፱ ነገር ግን፣ እነሆ አሞንን ለመምታት ዱላውን ያነሳ ማንኛውንም ሰው አሞን በጎ ራዴው እጆቻቸውን መትቶ ቆረጠ፤ እስ ኪገረሙ ድረስ በጎራዴው ጫፍ እጃቸውን በመምታት ምታቸውን ተቋቋመውና፣ ከፊቱ መሸሽ ጀመሩ፤ አዎን፣ እናም በቁ ጥር ጥቂት አልነበሩም፤ እናም በክንዱ ጥን ካሬም እንዲሸሹ አደረገ።

፳፰ አሁን በወንጭፉ ስድስት ሰዎች ወደቁ፣ ነገር ግን ከመሪያቸው በስተቀር ማንንም በጎራዴው አልገደለም፤ እናም በእርሱ ላይ የተነሱትን እጅ ሁሉ መትቶ ቆረጠ፣ እናም እነርሱ ጥቂት አልነበሩም።

፳፱ እንግዲህ አርቆ ካሸሻቸው በኋላ ተመ ለሰ፣ እናም ከብቶቻቸውን ውሃ አጠጡ አቸውና ወደንጉሱ ግጦሽ መለሱአቸው፣ እናም እርሱን ሊገድሉ የፈለጉትን በአሞን ጎራዴ የተቆረጡትን እጆች ይዘው ወደን ጉሱ ሄዱና፣ ላደረጉአቸው ነገሮች ምስክር እንዲሆኑ ወደ ንጉሱ ተወሰዱ።

ምዕራፍ ፲፯

ንጉስ ላሞኒ አሞን ታላቁ መንፈስ እንደ ሆነ ገመተ—አሞን ንጉሱን ስለፍጥረት፣

[ሀ] ሀ ሞዛያ ፳፯፡፲፣ ፲፣ አልማ ፲፱፡፳፪–፳፫።

[ሁ] ሀ ኤተር ፲፪፡፲፭። [ሂ] ለ አልማ ፲፯፡፲፯።

[ሃ] ሐ አልማ ፲፯፡፲።

እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ስላለው አድራጎትና፣ በክርስቶስ ስለሚመጣው ቤዛነት አስተማረው—ላሞኒ አመነ፣ እናም በምድሪቱ ላይ የሞተ በመምሰል ወደቀ። በ፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ላሞኒ አገልጋዮቹ በፊቱ እንዲቆሙና ስለሁሉም ነገሮች ድርጊቱን በተመለከተ እንዲመሰክሩ አደረገ።

፪ እናም ሁሉም ስለተመለከቱአቸው ነገሮች ሁሉ በመሰከሩ ጊዜና፣ ንጉሱ አሞን መንጋዎቹን በመጠበቁ፣ እናም ደግሞ እርሱን ለመግደል ከፈለጉት ጋር ለመጣላት ባለው ታላቅ ኃይል ታማኝነቱን በተማረ ጊዜ፣ እጅግ ተደነቀ፣ እናም እንዲህ አለ፥ በእርግጥ ይህ ከሰው በላይ ነው። እነሆ፣ ይህ በግድያቸው የተነሳ ታላቅ ቅጣት በህዝቡ ላይ የላከው ታላቅ መንፈስ አይደለምን?

፫ እናም ለንጉሱ እንዲህ ሲሉ መለሱለት፥ እርሱ ታላቅ መንፈስም ይሁን ሰው አናውቅም፣ ነገር ግን፣ የምናውቀው ይህን ያህል ነው፣ በንጉሱ ጠላቶች "መገደል አይቻልም፤ በባለሙያነቱና በታላቅ ጥንካሬው የተነሳ ከእኛም ጋር እስካለ ድረስ የንጉሱን ከብቶች ለመበታተን አይችሉም፤ ስለዚህ፣ የንጉሱ ወዳጅ መሆኑንም እናውቃለን። እናም እንግዲህ፣ ንጉስ ሆይ፣ ሰው እንደዚህ ታላቅ ኃይል ይኖረዋል ብለን አናምንም፣ ምክንያቱም እርሱ እንደማይገደል እናውቃለንና።

፬ እናም አሁን፣ ንጉሱ እነዚህን ቃላት በሰማ ጊዜ፣ እንዲህ አላቸው፥ አሁን ይህ ታላቁ መንፈስ እንደሆነ አውቃለሁ፤ እናም በወንድሞቻችሁ እንዳደረግሁት "እንዳልገድላችሁ በዚህን ጊዜ ህይወታችሁን ለማቆየት የመጣ ነው። እንግዲህ አባቶቻችን የተናገሩት ታላቁ መንፈስ ይህ ነው።

፭ አሁን ይህ "ታላቁ መንፈስ መኖሩን ላሞኒ ከአባቶቹ የተቀበለው ወግ ነው። ምንም እንኳ በታላቁ መንፈስ ያመኑ ቢሆንም፤ ያደረጉት ማንኛውም ነገር ትክክል እንደሆነ ገምተዋል፤ ይሁን እንጂ፣ አገልጋዮቹን በመግደል ስህተት እንደሰራ በመፍራት ላሞኒ በእጅጉ መፍራት ጀመረ፤

፮ በውሃው ስፍራ ወንድሞቻቸው መንጋዎቻቸውን በማባረራቸው ብዙዎችን ገድሏልና፣ እናም ከብቶቻቸውንም ስላስበተኑ የንጉሱ አገልጋዮች ተገደሉ።

፯ ይህም በእነርሱ መካከል የመዝረፍ ልምድ ሆኖ፣ አሁን በዚያም የተበተኑትን ወደምድራቸው ለመንዳት ይችሉ ዘንድ፣ ላማናውያን በሴቡስ ውሃ አጠገብ በመቆም የሰዎችን ከብቶች ማባረር ልምዳቸው ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ላሞኒ አገልጋዮቹን እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፥ እንደዚህ ዓይነት ታላቅ ኃይል ያለው ሰው የት ነው?

፱ እናም እንዲህ አሉት፥ እነሆ እርሱ ፈረሶችህን እያበላ ነው። አሁን ንጉሱ ከብቶቻቸውን ውሃ ከማጠጣታቸው በፊት፣ ፈረሶቹንና ሰረገላዎቹን እንዲያዘጋጁ፣ እናም ወደኔፊ ምድር እንዲወስዱት አገልጋዮቹን አዝዞ ነበር፤ የምድሪቱ ሁሉ ንጉስ በሆነው የላሞኒ አባት በኔፊ ምድር ላይ ታላቅ ግብዣ ተመድቦ ነበርና።

፲ እንዲሁም ንጉስ ላሞኒ አሞን ፈረሶቹንና ሰረገላዎቹን ማዘጋጀቱን በሰማ ጊዜ ይበልጥ በአሞንም ታማኝነት ተደንቆ፣ እንዲህ አለ፥ በእርግጥ እንደዚህ ሰው ከአገልጋዮቼ ሁሉ መካከል ታማኝ አገልጋይ የለም፣ ትዕዛዛቴንም ሁሉ እንኳን ለመፈፀም አስተውሏልና።

፲፩ አሁን በእርግጥ ይህ ታላቁ መንፈስ እንደሆነ አውቃለሁ፤ እናም እርሱ ወደ እኔ እንዲመጣ እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን አልደፍርም።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ አሞን ለንጉሱና ለአገልጋዮቹ ፈረሶቹንና ሰረገላዎቹን ካዘ

፤፲፯ ፲ *ሀ* አልማ ፲፯፡ ፴፱–፴፯።
፩*ሀ* አልማ ፲፯፡ ፳፯–፴፩።
፭ *ሀ* አልማ ፲፱፡ ፳፭–፳፯።
አምላክ።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣

ጋጀ በኋላ፣ ወደ ንጉሱ ገባ፣ እናም የንጉሱ ፊት እንደተለወጠ ተመለከተ፤ ስለዚህ እር ሱም ከፊቱ መመለስ ጀመረ።

፲፫ እናም ከንጉሱ አገልጋዮች አንዱ እን ዲህ አለው፡ ራባና፣ ማለትም ሲተረጎም ኃያል ወይንም ታላቅ ንጉስ ነው፤ ንጉሳ ቸው ኃያል እንደሆነ ይቆጥሩታልና፤ እናም እንዲህ አለው፡ ራባና፣ ንጉሱ እንድትቆይ ይፈልጋል።

፲፬ ስለሆነም አሞን ወደ ንጉሱ በመዞር እንዲህ አለው፡ ንጉስ ሆይ ለአንተ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ? እናም ንጉስ እን ደነርሱ ሰዓት ለአንድ ሰዓት ያህል ምንም አልመለሰለትም፣ ምክንያቱም ለእርሱ ምን ማለት እንዳለበት አላወቀምና።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አሞን በድጋሚ አለው፡ ከእኔ ምን ትፈልጋለህ? ነገር ግን ንጉሱ ምንም አልመለሰለትም።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ አሞን በእግዚአብ ሔር መንፈስ በመሞላቱ የንጉሱን ᵐሀሳብ አስተዋለ። እናም እንዲህ አለው፡ ከብቶች ህንና አገልጋዮችህን እንደጠበቅኩኝ፣ አገ ልጋዮችህንና መጋዎችህን ለመከላከል ሰባ ቱን ወንድሞቻቸውን በወንጭፍና በጎራዴ እንደገደልኩኝ፣ እናም የሌሎችን እጅ የቆ ረጥኩትን በመስማትህ ነው፤ እነሆ፣ ለአስ ደናቂ ነገሮችህ መንስኤስ ይህ ነውን?

፲፯ እንዲህ እልሃለሁ፣ ድንቅ ነገሮችህ ታላቅ የሆኑት እንዴት ነው? እነሆ፣ እኔ ሰው ነኝ፣ እናም የአንተ አገልጋይ ነኝ፤ ስለዚህ፣ አንተ የፈለከውን ማንኛውንም ትክክል ነገር አደርጋለሁ።

፲፰ አሁን ንጉሱ እነዚህን ቃላት በሰማ ጊዜ አሞን ሃሳቡን ᵐእንደተረዳ ስለተመ ለከተ በድጋሚ ተደነቀ፤ ነገር ግን ቢሆ ንም፣ ንጉሱ ላሞኒ አፉን በመክፈት እን ዲህ አለው፡ አንተ ማን ነህ? ሁሉንም ነገ ሮች ᵃየሚያውቅ ታላቁ መንፈስ ነህን?

፲፱ አሞን፣ እኔ አይደለሁም በማለት መለሰ።

፳ እናም ንጉሱ እንዲህ አለው፡ ታዲያ የልቤን ሀሳብ እንዴት ልታውቅ ቻልህ? አንተ በድፍረት ተናገርና፣ እነዚህን በተ መለከተ ንገረኝ፣ እናም ደግሞ በምን ኃይል ከብቶቼን የበተኑትን ወንድሞቼን እጆች እንደመታሃቸው ንገረኝ—

፳፩ እናም አሁን እነዚህን ነገሮች በተመለ ከተ የምትናገረኝ ከሆነ፣ የፈለግኸውን ሁሉ አሰጥሃለሁ፤ እናም አስፈላጊ ከሆነ፣ በሠራ ዊቶቼ እጠብቅሀለሁ፤ ነገር ግን አንተ ከሁ ሉም በላይ ኃያል እንደሆንክ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ከእኔ የፈለግኸውን ማንኛ ውንም እሰጥሀለሁ።

፳፪ እንግዲህ አሞን ብልህ ቢሆንም፣ የሚ ጎዳም ባለመሆኑ፣ ለላሞኒ እንዲህ አለው፡ በምን ሀይል እነዚህ ነገሮች ለማድረግ እንደ ምችል ብነግርህ ቃሌን ትሰማኛለህን? እናም ይህም ከአንተ የፈለግሁት ነገር ነው።

፳፫ እናም ንጉሱ እንዲህ ሲል መለሰለት፡ አዎን፣ ቃልህን በሙሉ አምናለሁ። እናም እርሱ እንደዚህ ነበር በብልህነት የተያዘው።

፳፬ እናም አሞን ᵐበድፍረት ለእርሱ መና ገር ጀመረና፣ እንዲህ አለው፡ እግዚአብ ሔር እንዳለ ታምናለህን?

፳፭ እናም እንዲህ ሲል መለሰለት፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም።

፳፮ እናም አሞን እንዲህ አለው፡ ታላቅ መንፈስ እንዳለ ታምናለህን?

፳፯ እናም እርሱ አዎን አለ።

፳፰ እናም አሞን፣ ይህ እግዚአብሔር ነው አለ። እናም አሞን በድጋሚ አለው፡ ይህ እግዚአብሔር የሆነው ታላቅ መንፈስ በሰ ማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈ ጠረ እንደሆነ ታምናለህን?

፳፱ እርሱም አዎን፣ በምድር ላይ ያሉ ትን ነገሮች ሁሉ እንደፈጠረ አምናለሁ፤ ነገር ግን የሰማያትን አላውቅም።

፴ እናም አሞን እንዲህ አለው፡ ሰማያት እግዚአብሔርና ቅዱሳን መላዕክቱ የሚኖ ሩበት ቦታ ነው።

፲፯ ᵃ አልማ ፲፪፡፲። ፲፰ ᵃ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ። ᵃ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ። ፳፩ ᵃ አልማ ፴፰፡፲፪።

፴፩ እናም ንጉስ ላሞኒ እንዲህ አለ፡ ይህ ከመሬት በላይ ነውን?

፴፪ እናም አሞንም አለ፡ አዎን፣ እናም የሰው ልጆችን ሁሉ ወደታች ይመለከታል፤ የልባቸውን [ሀ]ሀሳብና መሻት በሙሉ ያውቃልም፤ ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮ ሁሉም በእጁ ተፈጥረዋልና።

፴፫ እናም ንጉስ ላሞኒ እንዲህ አለ፡ አንተ የተናገርካቸውን እነዚህን ነገሮች ሁሉ አምናለሁ። አንተ ከእግዚአብሔር የተላክህ ነህን?

፴፬ አሞን እንዲህ አለው፡ እኔ ሰው ነኝ፤ እናም በመጀመሪያ [ሀ]ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል፣ እናም እነዚህን ነገሮች ይህ ህዝብ ትክክልና እውነት ወደ ሆነው እውቀት ይመጡ ዘንድ [ለ]እንዳስተምር በቅዱስ መንፈሱ ተጠርቻለሁ።

፴፭ እናም [ሐ]እውቀትንና፣ ደግሞ ኃይልን በእግዚአብሔር ላይ ባሉት እምነቴና ፍቃዴ የሚሰጠኝ [ሀ]የመንፈሱ ክፍል ከእኔ ጋር ይኖራል።

፴፮ አሁን አሞን እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ከዓለም መፈጠርና ደግሞ ከአዳም መፈጠር ጀምሮ፣ እናም የሰው መውደቅን በተመለከተ ሁሉም ነገሮች ነገረው፣ እናም አባታቸው ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ድረስ እንኳ የነበሩትን ታሪኮቹንና [ሀ]በነብያት የተነገሩትን የህዝቡን [ለ]ቅዱሳት መጻሕፍትን [ሐ]መተረክና መዘርዘር ጀመረ።

፴፯ እናም ደግሞ ለእነርሱ (ይህም ለንጉሱና ለአገልጋዮቹ ነበርና) በምድረበዳ ውስጥ የነበሯቸውን የአባቶቻቸውን ጉዞና የእነርሱን ረሃብና ጥማት እንዲሁም ድካምና ሌሎችንም ሁሉ ስቃያቸውን ነገራቸው።

፴፰ እናም ደግሞ ስለላማንና ልሙኤል፣ ደግሞም ስለእስማኤል ልጆች አመፅ ተናገረ፣ አዎን፣ አመፃቸውን ሁሉ ተረከላቸው፤ እናም ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ያሉትን መዛግብቱና ቅዱሳት መጻሕፍት ገለፀላቸው።

፴፱ ነገር ግን ይህ ብቻም አይደለም፣ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ተዘጋጅቶ ስለነበረው [ሀ]የቤዛነትን ዕቅድ አብራራላቸው፤ እናም ስለክርስቶስ መምጣትም አስታወቃቸውና፣ የጌታን ስራዎች ሁሉ እንዲያውቁት አደረገ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከተናገረ በኋላ፣ እናም ለንጉሱ አብራራቸው፣ ንጉሱም የተናገረውን በሙሉ አመነው።

፴፩ እናም ወደ ጌታ እንዲህ ሲል መጮህ ጀመረ፡ አቤቱ ጌታ [ሀ]ምህረትህን አድርግ፤ በኔ፣ ህዝብ ላይ ያደረከውን የበዛ ምህረትን፣ በእኔና በህዝቤ ላይ አድርግ።

፴፪ እናም አሁን፣ ይህንን በተናገረ ጊዜ እንደሞተ ሰው በመሬት ላይ ወደቀ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዮቹ ወሰዱት፣ ወደ ሚስቱ ተሸክመው ወሰዱትና፣ በአልጋው ላይ አስተኙት፤ እናም ለሁለት ቀንና ምሽት እንደሞተ ሰው ተኛ፤ ሚስቱ፣ ወንድና ሴት ልጆቹም በሃዘን ተቀመጡ፣ እንደ ላማናውያንም በሆነ ወግ ስለእርሱ እጅግ አለቀሱ።

ምዕራፍ ፲፱

ላሞኒ የዘለዓለማዊውን ህይወት ብርሃን አገኘ፣ እናም አዳኙን ተመለከተ—ቤተ ሰዎቹም ተመሰጡ፣ እናም ብዙዎች መላ ዕክትን ተመለከቱ—አሞን ተአምራት ሁኔታ ተጠበቀ—ብዙዎችን አጠመቀ፣ እናም በመካከላቸው ቤተክርስቲያኗን አቋቋመ። በ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፴፪ *ሀ* ዓሞ. ፪፡ ፲፫፣
፫ ኔፊ ፳፰፡ ፭፣
ት. እና ቃ. ፭፡ ፲፯።
፴፬ *ሀ* ሞዛያ ፯፡ ፳፯፣
ኤተር ፫፡ ፲፫–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ—በመንፈስ
ማስተማር።
፴፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣
መነሳሳት።
፴፮ *ሀ* የሐዋ. ፫፡ ፲፰–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
ሐ ሞዛያ ፩፡ ፬፣
አልማ ፳፪፡ ፲፪፣ ፴፯፡ ፱።
፴፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
፴፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ከሁለት ቀናትና ከሁ
ለት ምሽት በኋላ ሙታኖቻቸውን ለመቅበር
ባዘጋጁት ስፍራ ሰውነቱን በመውሰድ በመ
ካነ መቃብር ሊያሳርፉት ነበር።

፪ እንዲሁም ንግስቲቱ የአሞንን ዝና በመ
ስማቷ፣ መልዕክተኛ ላከች እናም ወደ እርሷ
እንዲመጣ ፈለገች።

፫ እናም እንዲህ ሆነ አሞን እንደታዘዘው
አደረገና፣ ወደ ንግስቲቱ ሄደ፣ እርሱ ምን
እንዲያደርግ እንደምትፈልገው ለማወቅም
ፈለገ።

፬ እናም እርሷም አለችው፡ የባለቤቴ አገ
ልጋዮች አንተ "የቅዱሱ አምላክ ነቢይ መሆ
ንህን አሳወቁኝ፣ እናም አንተ ብዙ ተአም
ራትን የማድረግ ኃይል እንዳለህም ነገሩኝ፤

፭ ስለዚህ፣ ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ ባለቤ
ቴን ሄደህ እንድትመለከተው እፈልጋለሁ፣
ምክንያቱም እርሱ ለሁለት ቀናትና ለሁለት
ሌሊት በአልጋው ላይ ተኝቷልና፤ እናም
አንዳንዶች አልሞተም ይላሉ፣ ነገር ግን
ሌሎች ሞቷል እንዲሁም ሸቷል፤ እናም
በመቃብሩ ማረፍ አለበት ይላሉ፤ ነገር ግን
እንደ እኔ፣ ለእኔ አልሸተተኝም።

፮ እንግዲህ፣ ይህ አሞን የፈለገው ነበር፣
ምክንያቱም ንጉስ ላሞኒ በእግዚአብሔር
ኃይል ስር እንደሆነ ያውቅ ነበርና፤ እር
ሱም ያለማመን ጥቁር "መጋረጃው ከአዕ
ምሮው እንደተወሰደ ያውቅ ነበር፣ እናም
የእግዚአብሔር የክብር ^ብርሃን የሆነው፣
የቸርነቱ አስገራሚ ብርሃን የነበረው ብር
ሃን በአዕምሮው ውስጥ በርቷል—አዎን፣
ይህ ብርሃን በነፍሱ ውስጡ እንደዚያ ያለን
ደስታ አምጥቷል፤ የጨለማው ዳመና ተበ
ትኗል፣ እናም የዘለዓለማዊው ህይወት ብር
ሃን በነፍሱ ውስጡ ተቀጣጥሏል፤ አዎን፣
ይህ እራሱን እንዲስት እንዳደረገው አው
ቋል፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ተወስ
ዷል—

፯ ስለዚህ፣ ንግስቲቱ ከእርሱ የፈለገችው
የእርሱን ፍላጎት ብቻ ነበር። ስለዚህ፣ ንግ
ስቲቱ እንደፈለገችው ንጉሱን ለመመልከት
ሄደ፤ እናም ንጉሱን ተመለከተና ንጉሱ እን
ዳልሞተም አውቆ ነበር።

፰ እናም ለንግሥቲቱም አላት፡ እርሱ
አልሞተም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ተኝ
ቷል፣ እናም በማግስቱ በድጋሚ ይነሳል፤
ስለዚህ አትቅበሩት።

፱ አሞንም አላት፡ ይህን ታምኚአለሽን?
እርሷም አለችው፡ ከአንተ ቃልና ከአገል
ጋዮቻችን ቃል በስተቀር ምንም ማረጋገጫ
የለኝም፤ ይሁን እንጂ አንተ የተናገርከው
እንደሚሆን አምናለሁ።

፲ አሞንም አላት፡ አንቺ በታላቁ እም
ነትሽ የተባረክሽ ነሽ፤ እኔም እልሻለሁ፣
አንቺ ሴት፣ በኔፋውያን ሁሉ መካከል እን
ደዚህ ያለ ታላቅ "እምነት አልነበረም።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ከዚያ ሰዓት ጀምሮ
አሞን ይነሳል ብሎ እስካለበት ሰዓት እስከ
ሚቀጥለው ቀን ድረስ የባሏን መኝታ ጠበ
ቀች።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ አሞን በተናገረው
መሰረት ተነሳ፤ እናም በተነሳም ጊዜ እጁን
በሴቲቱ ላይ ዘረጋና፣ አለ፡ የእግዚአብሔር
ስም የተባረከ ነው፣ እንዲሁም አንቺም የተ
ባረክሽ ነሽ።

፲፫ አንቺ ልክ በህይወት እንዳለሽ፣ እነሆ፣
አዳኜን አይቻለሁ፤ እናም እርሱ ይመጣል፣
"ከሴትም ^ይወለዳል፣ እናም በስሙ የሚ
ያምኑትን የሰው ዘር ሁሉ ያድናል። እን
ግዲህ፣ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣
ልቡ በሀሴት ተሞላ፣ እንደገናም በደስታ
ተዋጠ፣ እናም ንግስቲቱ ደግሞ በመንፈሱ
በመሸነፏ ሰመጠች።

፲፬ እንግዲህ አሞን በወንድሞቹ በላማና
ውያን፣ በኔፋውያን መካከል እንዲሁም
በእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ መካከል በክ

፲፱ ፱ሀ ቅ.መ.መ. ነቢይ።
፲፯ሀ ፪ ቆሮ. ፱፡ ፲–፱።
ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፲ ሀ ሉቃ. ፲፡ ፱።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፲፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፲፫–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ስለኢየሱስ
ክርስቶስ መወለድ እና ሞት
ትንቢቶች።

ፋታቸውና ᵐበባህላቸው ታላቅ ሀዘን እን ዲሆን ባደረጉት ላይ ᵃበፀሎት የጌታ መን ፈስ በእነርሱ ላይ መሆኑን በተመለከተ ጊዜ ተንበረከከ፣ እናም እግዚአብሔር ለወንድ ሞቹ ባደረገው በትጋት ፀለየ፣ እንዲሁም በምስጋና ነፍሱን አፍስሶ አቀረበ፤ እና እር ሱም ደግሞ ᵃᵃበደስታ ተዋጠ፤ ሶስቱም ወደ ምድር ᵐᵐወደቁ።

፲፭ እንግዲህ፣ የንጉሱ አገልጋዮች እን ደወደቁ በተመለከቱ ጊዜ ወደ ጌታ መጮህ ጀመሩ፤ የጌታ ፍርሃት በእነርሱ ላይ ሆኗ ልና፤ ᵐበንጉሱ ፊት ቆመው ስለአሞን ታላቅ ኃይል የመሰከሩት እነርሱ ናቸውና።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ አባቷም በነበረው ታላቅ ራዕይ መሠረት ለብዙ ዓመታት ወደ ጌታ ከተለወጠችው አቢሽ ከተባለች ላማና ዊት ሴት በስተቀር ሁሉም ወደ ምድር እስ ኪወድቁ ድረስ ባላቸው ሀይል በፀሎታቸው የጌታን ስም ጠሩ—

፲፯ ወደ ጌታ የተለወጠች በመሆኗና፣ እንዲታወቅ ባለማድረጓ የላሞኒ አገልጋ ዮች በሙሉ በመሬት ላይ መውደቃቸውን፣ እናም ደግሞ እመቤቷም፣ ንግስቲቱምና፣ ንጉሱ፣ እንዲሁም አሞን በመሬቱ ላይ መዘ ረሩን በተመለከተች ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን አውቃ ነበር፤ እናም ይህን ገምታ፣ ህዝቡን በመካከላቸው ምን እንደ ደረሰ በማሳወቅ ይህን አጋጣሚ ሰዎቹ ሲመ ለከቱ በእግዚአብሔር ኃይል ᵐእንዲያምኑ ያደርጋቸዋል ብላ ገመተች፣ ስለዚህ ይህን ለህዝቡ ለማሳወቅ ከቤት ወደ ቤት ሮጠች።

፲፰ እናም ህዝቡ በንጉሱ ቤት ራሳቸውን በአንድ ላይ መሰብሰብ ጀመሩ። እናም ብዙዎች መጡና፣ ለመገረማቸው፣ ንጉ ሱን፣ ንግሥቲቱንና አገልጋዮቻቸው በመ ሬት ላይ እንደተዘረጉና፣ ሁሉም እንደሞተ በመሬት ላይ ተዘርግተው እንደነበር ተመ ለከቱ፤ ደግሞም አሞንን ተመለከቱት፣ እናም እርሱ ኔፋዊያን እንደነበረ ተመለ ከቱ።

፲፱ እናም አሁን ህዝቡ እርስ በርስ ማጉረ ምረም ጀመሩ፣ ጥቂቶች በእነርሱ ላይ እን ዲሁም በንጉሱ ላይ እና በቤቱ ላይ እርሱ ኔፋውያን በምድሪቱ ላይ ᵐእንዲቀሩ ስለ ፈቀደ የመጣ ታላቁ ክፋት ነው አሉ።

፳ ነገር ግን ሌሎች እንዲህ በማለት ወቀ ሱአቸው፥ ንጉሱ ይህን ክፉ ነገር በቤቱ ላይ ያመጣው ራሱ ነው፣ ምክንያቱም ᵐበሲበስ ውሃ አካባቢ ከብቶቹን የተበተነባቸውን አገ ልጋዮቹን ገድሏልና።

፳፩ እናም ደግሞ እነርሱም የንጉሱ የሆ ኑትን ከብቶች ᵐያባረሩት በውሃው አጠገብ በቆሙት ተወቀሱ፣ እናም በሲበስ ወንዝ አጠገብ የንጉሱን ከብቶች በሚጠብቅበት ጊዜ ብዙ ወንድሞቻቸውን ስለገደለባቸው በአሞን ተቆጥተውት ነበር።

፳፪ እንግዲህ፣ በአሞን ጎራዴ ወን ድሙ ᵐከተገደለበት አንዱ በአሞን በመቆ ጣቱ አሞንን ለመግደል ጎራዴውን አው ጥቶ ሊያሳርፍበት ወደ እርሱ ሄደ፤ እናም ሊመታው ጎራዴውን ባነሳ ጊዜ፣ እነሆ፣ ሞቶ ወደቀ።

፳፫ አሁን ᵐጌታ ለአባቱ ለሞዛያ፣ አድነ ዋለሁ፣ እናም እንደ እምነትህም ይሆንለ ታል ብሎታልና፣ አሞን ሊገደል እንደማ ይችል እንመለከታለን—ስለዚህ ሞዛያ እር ሱን ለጌታ ᵃበአደራ ሰጥቷል።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ አሞንን ለመግደል ጎራዴውን ያነሳውን መሞቱን ህዝቦቹ በተ መለከቱ ጊዜ፣ በሁሉም ላይ ፍርሃት ወደ ቀባቸው፣ እናም፣ እርሱን ወይም እነዚያን የወደቁትን ለመንካት አልደፈሩም፤ የዚህ የታላቁ ኃይል መንስኤም ምን ሊሆን እን ደሚችል፣ ወይም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ምን ማለት ሊሆኑ እንደሚችሉ በድጋሚ እርስ በርስ መገረም ጀመሩ።

፲፭ ᵐ ሞዛያ ፩፡፲፭።
ᵃ ት.እና ቃ. ፸፪፡፲፭።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. ደስታ።
ᵐᵐ አልማ ፳፯፡፲፯።
፲፭ ᵐ አልማ ፲፰፡፩–፪።

፲፯ ᵐ ሞዛያ ፳፯፡፲፭።
፲፱ ᵐ አልማ ፲፯፡፳፪–፳፫።
፳ ᵐ አልማ ፲፯፡፳፯፣ ፲፰፡፯።
፳፩ ᵐ አልማ ፲፯፡፳፯፣ ፲፰፡፫።
፳፪ ᵐ አልማ ፲፯፡፴፰።

፳፫ ᵐ ሞዛያ ፳፰፡፯፣
አልማ ፲፯፡፴፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. መታመን።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ አሞን "ታላቅ መንፈስ ነው የሚሉ ብዙዎች በመካከላቸው ነበሩ፣ እናም ሌሎች በታላቁ መንፈስ ተልኳል ይሉ ነበር፤

፳፪ ነገር ግን ሌሎች እንዲህ በማለት ይወቅሱታል፣ እርሱም ከኔፋውያን እነርሱን ለመቅጣት የተላከ ጭራቅ ነበር።

፳፫ እናም ጥቂቶች አሞን በታላቁ መንፈስ በክፋታቸው የተነሳ እነርሱን ለማሰቃየት የተላከ ነው፤ እናም ሁልጊዜ ኔፋውያንን የሚጠብቅ፣ ከእጃቸው ምንጊዜም የሚያስለቅቃቸው ታላቅ መንፈስ ነው፤ እናም ይህ ታላቁ መንፈስ በጣም ብዙ የላማናውያን ወንድሞቻቸውን ያጠፋ ነው ይሉ ነበር።

፳፬ እናም ፀቡ በመካከላቸው እጅግ የከፋ መሆን ጀመረ። እናም በሚጣሉበት ጊዜ፣ ህዝቡ በአንድነት ተሰብስቦ እንዲመጣ ያደረገችው "ሴት አገልጋይ መጣችና፣ በህዝቡ መካከል ፀብ መሆኑን በተመለከተች ጊዜ እምባ እስኪወጣት እንኳን እጅግ አዝና ነበር።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ሄደችና ከመሬት ንግስቲቱ ትነሳ ዘንድ በእጇ አነሳቻት፤ እናም እጇን እንደነካቻት ተነሳችና፣ በእግሮችዋ ቆመች፣ በሀይለኛ ድምፅ እንዲህም ስትል ጮኸች፤ አቤቱ "ከመጥፎ ሲኦል ያዳንከኝ የተባረከው ኢየሱስ! አቤቱ የተባረከህ እግዚአብሔር ሆይ፣ በዚህ ህዝብ ላይ ^ምህረትን አድርግ!

፳፮ እናም እርሷ ይህንን በተናገረች ጊዜ፣ በደስታ ተሞልታ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮች በመናገር አጨበጨበች፤ ይህንንም ባደረገች ጊዜ ንጉስ ላሞኒን በእጆችዋ ያዘችው፣ እናም እነሆ ተነሳና በእግሮቹ ቆመ።

፳፯ እናም ወዲያው በህዝቡ መካከል ያለውን ፀብ በተመለከተ ጊዜ ሄደ፣ እነርሱንም ወቀሰና በአሞን አንደበት ተነግሮ የሰማውን ማስተማር ጀመረ፤ እናም "ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑና፣ ወደ ጌታ ተለወጡ።

፳፰ ነገር ግን ከእነርሱ መካከል ቃሉን መስማት ያልፈለጉ ብዙዎች ነበሩ፤ ስለ ዚህ በመንገዳቸው ሄዱ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ አሞን በተነሳ ጊዜ ደግሞ እነርሱን አገለገለ፣ ደግሞም የላሞኒ አገልጋዮች ሁሉም እንዲህ አደረጉ፤ እናም ሁሉም ልባቸው "እንደተለወጠ፣ ^ክፉ ለማድረግም ከእንግዲህ ፍላጎት እንደሌላቸው ለህዝቡ አንድ ዓይነት ነገር አወጁ።

፴ እናም እነሆ ብዙዎች ለሰዎቹ "መላዕክትን እንደተመለከቱ ከእነርሱም ጋር እንደተነጋገሩ ተናገሩ፣ እና እንደዚህም የእግዚአብሔርን ነገሮች፣ ፃድቅነቱንም ነገሩአቸው።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ ቃላቸውን ያመኑ ብዙዎች ነበሩ፤ እናም ብዙ ያመኑት "ተጠመቁ፤ ፃድቅ ሰዎችም ሆኑና፣ በመካከላቸው ቤተክርስቲያኗን አቋቋሙ።

፴፪ እናም የጌታ ስራ በላማናውያን መካከል ተጀመረ፤ እንደዚህም ጌታ መንፈሱን በእነርሱ ላይ ማፍሰሱን ጀመረ፤ እናም ንስሃ በሚገቡ ሰዎችና በስሙ ለሚያምኑት "ህዝብ ሁሉ ክንዱ መዘርጋቱን እንመለከታለን።

ምዕራፍ ፳፩

ጌታ አሞንን የታሰሩትን ወንድሞቹን ከእስር እንዲያስለቅቅ ወደ ሚዶኒ ላከው—አሞንና ላሞኒ በምድሪቱ ላይ ንጉስ የሆነውን የላሞኒን አባት አገኙት—አሞን አዛውንቱን ንጉስ የወንድሞቹን መለቀቅ እንዲያፀድቅለት አስገደደው። በ፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ቤተክርስቲያንን ካቋቋሙ በኋላ፣ አሞንን ለአባቱ

፳፭ ሀ አልማ ፲፰፡፪–፭።
፳፰ ሀ አልማ ፲፱፡ ፲፯።
፳፱ ሀ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፴፩ ሀ አልማ ፲፰፡ ፴፯–፴፱።

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጻግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።
ለ ሞዛያ ፭፡ ፪፤ አልማ ፲፫፡ ፲፪።

፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፴፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫፤ አልማ ፭፡ ፴፫።

ለማሳየት ከእርሱ ጋር ወደ ኔፊ ምድር ይሄድ ዘንድ ንጉስ ላሞኒ ፈለገ።

፪ እናም የጌታ ድምፅ ወደ አሞን እን ዲህ ሲል መጣ፥ እነሆም ንጉሱ ህይወት ህን ሊያጠፋ ይፈልጋልና ከእርሱ ጋር ወደ ኔፊ ምድር አትሂድ፤ ነገር ግን ወደ ሚዶኒ ምድር ሂድ፤ እነሆ፣ ወንድምህ ኦሮን፣ ደግሞም ሙሎቂና አማ በወህኒ ቤት አሉና።

፫ እንግዲህ እንዲህ ሆነ አሞን ይህንን በሰማ ጊዜ፣ ለላሞኒ እንዲህ አለው፥ እነሆ፣ ወንድሜ እናም ወንድሞቻችንን በሚዶኒ በወህኒ ናቸው፣ እናም ላስለቅቃቸው ወደ ዚያው እሄዳለሁ።

፬ አሁን ላሞኒ ለአሞን አለው፥ "በጌታ ጥንካሬ ሁሉንም ነገሮች ማድረግ እንደም ትችል አውቃለሁ። ነገር ግን እነሆ፣ ከአ ንተ ጋር ወደ ሚዶኒ ምድር እሄዳለሁ፤ አን ቲዮምኖ የተባለው የሚዶኒ ንጉስ ጓደኛዬ ነውና፤ ስለዚህ ወደ ሚዶኒ ምድር እሄዳ ለሁ፣ ወንድሞችህን እንዲለቅ ንጉሱን አባ ብለዋለሁ። አሁን ላሞኒ እንዲህ አለው፥ ወንድሞችህ [a]በወህኒ ቤት እንደሆኑ ማን ነገረህ?

፭ እናም አሞን እንዲህ አለው፥ ከእግዚ አብሔር በቀር ማንም አልነገረኝም፣ እን ዲህም አለኝ—ሂድና ወንድሞችህን አስለ ቅቅ፣ ምክንያቱም እነርሱ በሚዶኒ ምድር በወህኒ ናቸውና።

፮ እናም ላሞኒ ይህን በሰማ ጊዜ አገል ጋዮቹ "ፈረሶቹንና ሰረገላዎቹን እንዲያዘ ጋጁ አደረገ።

፯ እናም ለአሞን እንዲህ አለው፥ ና እኔ ወደ ሚዶኒ ምድር ከአንተ ጋር እሄዳለሁ እናም ንጉሱ ወንድሞችህን ከወህኒ እንዲ ለቃቸው እለምናለሁ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ አሞንና ላሞኒ ወደ ዚያ ቦታ በተጓዙ ጊዜ፣ "በምድሪቱ ሁሉ ላይ ንጉስ የሆነውን የላሞኒን አባት አገኙት።

፱ እናም እነሆ፣ የላሞኒ አባት እንዲህ አለው፥ ለልጆቼና ለህዝቤ "በዓል በማደ ርግበት ታላቅ ቀን በዚያ በዓል ላይ ለምን አልመጣህም?

፲ እናም ደግሞ እንዲህ አለው፥ ከእዚህ "ከሃሰተኛ ልጆች አንዱ ከሆነው ከኔፋዊ ጋር ወዴት ትሄዳለህ?

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ላሞኒ እርሱን ማበ ሳጨትን ፈርቶ ወዴት እንደሚሄድ በዝር ዝር ነገረው።

፲፪ እናም ደግሞ በራሱ መንግስት የዘገየ ባቸውንና አባቱ ወደ አዘጋጀው በዓል ያል ሄደበትን ምክንያቶች ሁሉ ነገረው።

፲፫ እናም አሁን ላሞኒ እነዚህን ሁሉ ነገ ሮች በዝርዝር በተናገረ ጊዜ፣ እነሆ፣ አባቱ በእርሱ ተቆጥቶ ስለነበር ተቆጣ፣ እናም እንዲህ አለ፥ ላሞኒ፣ እነዚህን የውሸት ልጆች የሆኑትን ኔፋውያን ልታስለቅቃቸው ነው። እነሆ፣ እነርሱ አባቶቻችንን ዘርፈ ዋል፤ እናም አሁን ልጆቼ በማታለልና፣ በውሸታቸው እኛን ለማጭበርበር ንብረ ታችንን በድጋሚ ለመዝረፍ መጥተዋል።

፲፬ አሁን የላሞኒ አባት አሞንን በጎራዴው እንዲገድለው ላሞኒን አዘዘው። እናም ወደ ሚዶኒ ምድርም ደግሞ እንዳይሄድ፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ወደ "እስማኤል ምድር እን ዲመለስ አዞት ነበር።

፲፭ ነገር ግን ላሞኒም አለው፥ አሞንን አልገድለውም፣ ወደ እስማኤል ምድርም አልመለስም፣ ነገር ግን የአሞንን ወንድ ሞች ለማስለቀቅ ወደ ሚዶኒ ምድር እሄዳ ለሁ፣ ምክንያቱም እነርሱ ትክክለኛ ሰዎ ችና የእውነተኛው አምላክ ነቢያት እንደ ሆኑ አውቃለሁና።

፲፮ አሁን አባቱ እነዚህን ቃላት በሰማ ጊዜ ተቆጥቶት ነበር፣ እናም መሬት እስከሚ ወድቅ ድረስ ለመምታት ጎራዴውን መዘ ዘበት።

፲፯ ነገር ግን አሞን ወደፊት በመምጣት ቆመ፣ እናም እንዲህ አለው፥ እነሆ ልጅ

፳ ፩ *ሀ* አልማ ፳፯፡፲፪።
ለ አልማ ፳፡፳፫–፴።
፯ *ሀ* አልማ ፲፫፡፱–፲።
፳ *ሀ* አልማ ፳፪፡፩።
፱ *ሀ* አልማ ፲፫፡፱።
፲ *ሀ* ሞዛያ ፲፡፲፪–፲፯።
፲፩ *ሀ* አልማ ፲፯፡፲፱።

ህን አትግደል፤ ይሁን እንጂ፣ ከአንተ ይልቅ እርሱ ᵐቢወድቅ ይሻላል፣ ምክን ያቱም እነሆ እርሱ ለኃጢአቱ ᵃንስሃ ገብ ቷል፤ ነገር ግን በዚህን ጊዜ በቁጣህ አንተ ብትወድቅ ነፍስህ መዳን አትችልም።

፲፰ እናም በድጋሚ፣ ከማድረግ ብትቆ ጠብ መልካም ነው፤ ልጅህን ᵐብትገ ድል፣ የንፁህ ልጅ ደም ከምድር ወደ ጌታ ወደ አምላኩ ለበቀል ይመጣ ዘንድ ይጮህ ነበር፤ እናም ምናልባትም ᵃበነፍስም ትሞ ታለህና።

፲፱ አሁን አሞን እነዚህን ቃላት በተናገ ረው ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰለት፥ ልጆ ቼን መግደል ካለብኝ የንፁህን ደም ማፍሰ ሴን አውቃለሁ፤ እርሱን ለማጥፋት የፈለ ግኸው አንተ ነህና።

፳ እናም አሞንን ለመግደል እጁን ዘረጋ። ነገር ግን አሞን ምቱን ተቋቋመው፣ እናም ደግሞ መጠቀም እንዳይችል ክንዱን መታው።

፳፩ እንግዲህ አሞን ሊገድለው እንደሚ ችል ንጉሱ በተመለከተ ጊዜ፣ ህይወቱን እንዲያተርፍለት አሞንን ለመነው።

፳፪ ነገር ግን አሞን ጎራዴውን አነሳ፣ እናም አለ፥ እነሆ፣ ወንድሞቼ ከወህኒ ቤት እንዲወጡ አድርገህ ካልሰጠኸኝ እመታህ ለሁ።

፳፫ እንግዲህ ንጉሱ ህይወቱን አጣለሁ ብሎ በመፍራቱ እንዲህ አለ፥ እኔን ካዳ ንኸኝ ከመንግስቴም እኩሌታውን እንኳን ቢሆን የጠየቅኸውን ሁሉ እሰጥሃለሁ።

፳፬ እንግዲህ አሞን እንደፍላጎቱ በሸመገ ለው ንጉስ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው በተመለ ከተ ጊዜ እንዲህ አለው፥ ወንድሞቼን ከወ ህኒ ለቀህ የምትሰጠኝ ከሆነ፣ እናም ደግሞ ላሞኒ መንግስቱን ባለበት ካቆየ፣ እናም አንተ በእርሱ የማትከፉ ከሆንክ፣ ነገር ግን ᵐበማንኛውም ነገር እንዳሰበው፣ እንደ ፍላጎቱ እንዲሰራ የምትሰጠው ከሆነ አድ ንሃለሁ፣ አለበለዚያ መትቼ በመሬት ላይ እጥልሃለሁ።

፳፭ አሁን አሞን እነዚህን ቃላት በሚ ናገርበት ጊዜ፣ ንጉሡ ህይወቱ በመትረፉ መደሰት ጀመረ።

፳፮ እናም አሞን እርሱን የማጥፋት ፍላ ጎት እንደሌለው በተመለከተ ጊዜና፣ ለልጁ ለላሞኒ ያለውን ታላቅ ፍቅርም ደግሞ በተ መለከተ ጊዜ፣ እጅግ ተገረመ፣ እናም እን ዲህ አለ፥ ይህ ሁሉ አንተ የፈለከው በመ ሆኑ፣ ወንድሞችህን እለቃለሁ፣ እናም ልጄ ላሞኒ መንግስቱን ይዞ እንዲቆይ እፈቅዳ ለሁ፤ እነሆ፣ ልጄ መንግስቱን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከዘለአለም እንዲያቆይ እፈቅድ ልሀለሁ፤ እናም ከእንግዲህ ወዲህ እኔ አላ ስተዳድረውም—

፳፯ እናም ደግሞ ወንድሞችህ ከወህኒ ቤት እንዲለቀቁ አደርጋለሁ፣ እናም አን ተና ወንድሞችህ በመንግስቴ ወደ እኔ ለመ ምጣት ትችላላችሁ፤ ምክንያቱም አንተን ለመመልከት በሀይል እፈልጋለሁ። ንጉሱ አሞን በተናገራቸው ቃላትና ደግሞ ልጁ ላሞኒ በተናገራቸው ቃላት ተገረመ፣ ስለ ዚህ እነርሱን ᵐለመረዳት ፈልጎ ነበር።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ አሞንና ላሞኒ ወደ ሚዶኒ ምድር ጉዞአቸውን ቀጠሉ። እናም ላሞኒ በምድሪቱ ንጉስ ፊት ሞገስን አገኘ፤ ስለዚህ የአሞን ወንድሞች ከወህኒ ቤት ወጡ።

፳፱ እናም አሞን ራቁታቸውን በመሆና ቸው፣ በሲባጎ በጥብቅ በመታሰራቸው፣ ቆዳቸው ቆስሎ ባገኛቸው ጊዜ፣ እጅግ አዝኖ ነበር። እናም በረሃብ፣ በጥምና በሁ ሉም ዓይነት ስቃዮች ተሰቃይተዋል፤ ይሁን እንጂ፣ በስቃያቸው ሁሉ ᵐትዕግ ስት ነበራቸው።

፴ እናም፣ ይህ በመሆኑ የበለጠ ጠግርና አንገተ ደንዳና በሆኑ ሰዎች እጅ መውደቅ ዕድላቸው ነበር፤ ስለዚህ ቃላቸውን አላዳ

፲፯ ሀ አልማ ፴፰፡ ፳፫።
ለ አልማ ፲፱፡ ፲፭–፲፫።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ግድያ።
ለ ት.እና ቃ. ፴፭፡ ፲፰።
፳፩ ሀ አልማ ፳፩፡ ፳፩–፳፪።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፳፱ ሀ አልማ ፲፯፡ ፲፩።

መጡም፣ ጣሉአቸውም፣ መቱአቸውም፣ እናም ወደ ሚዶኒ ምድር እስከሚደርሱም እንኳን ከየቤታቸው ወደቤትና፣ ከቦታ ቦታ አስወጡአቸው፤ ከእዚያም ተወሰዱና ወደ ወህኒ ቤት ተጣሉም፣ በጠንካራ ᐸገመድ ታሰሩም፣ እናም ለብዙ ቀናት በወህኒ ቤት ቆዩና በላሞኒና በአሞን ተለቀቁ።

አሮንና፣ ሙሎቂ፣ እና ወንድሞቻቸው ለላ ማናውያን የሰበኩበት ታሪክ።

ከምዕራፍ ፳፩ እስከ ፳፯ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፳፩

አሮን አማሌቂውያንን ስለክርስቶስና ስለ ኃጢያት ክፍያው አስተማረ—አሮንና ወንድሞቹ በሚዶኒ ታሰሩ—ከዳኑ በኋላ፣ በምኩራቦች አስተማሩ፣ እናም ብዙዎችን ለወጡ—ላሞኒ በእስማኤል ምድር ለሚ ኖሩ ህዝቦች የኃይማኖት ነፃነትን ሰጣቸው። ከ፣–ፖ፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ አሞንና ወንድሞቹ በላማና ውያን ምድር ዳርቻ ᐸበተለያዩ ጊዜ፣ እነሆ አሮን በላማናውያን ኢየሩሳሌም ተብላ ወደ ምትጠራበት፣ እንደ አባቶቻቸው የትው ልድ ሥፍራ ስም ወደተጠራችው ስፍራ ጉዞውን አደረገ፤ እናም ስፍራውም ራቅ ያለና በሞርሞን ዳርቻ ነበር።

፪ ላማናውያንና አማሌቂውያን፣ እናም ᐸየአሙሎን ሰዎች፣ ኢየሩሳሌም በመባል የታወቀች ታላቅ ከተማን ገንብተው ነበር።

፫ እንግዲህ ላማናውያን እጅግ ጠጣር ነበሩ፤ ነገር ግን አማሌቂውያን እናም አሙሎናውያን ይበልጥ ጠጣሮች ነበሩ፣ ስለዚህ ላማናውያንም ልባቸውን እንዲያ ጠጥሩ፣ በክፋታቸውና በእርኩሰታቸውም እንዲጠናከሩ አደረጉአቸው።

፬ እናም እንዲህ ሆነ አሮን ወደ ኢየሩሳ ሌም ከተማ መጣ፣ እናም በመጀመሪያ ለአ ማሌቂውያን መስበክ ጀመረ። እናም በም ኩራባቸው መስበክ ጀመረ፣ ምክንያቱም ᐸእንደኔሆራውያን አሠራር ምኩራብ ሰር ተዋልና፤ ብዙ አማሌቂውያንና አሙሎና ውያን የኔሆርን ስርዓት የሚከተሉ ነበሩና።

፭ ስለዚህ፣ አሮን በአንደኛው ምኩራብ ህዝቡን ለማስተማር በገባ ጊዜ፣ እናም ለእነርሱ በሚናገር ጊዜ፣ እነሆ አንድ አሙሌቃዊ ተነሳና፣ ከእርሱም ጋር እን ዲህ በማለት መጣላት ጀመረ፥ አንተ የመ ሰከርከው ያ ምንድነው? ᐸመልአክን ተመ ልክተሃልን? መላዕክት ለምን ለእኛ አይገ ለጡልንም? እነሆ እነዚህ ሰዎች እንደ አንተ ሰዎች መልካም አይደሉምን?

፮ ደግሞም ንስሃ ካልገባን እንጠፋለን ብለ ሃል። የልባችንን ሃሳብና መሻት እንዴት አወቅህ? ንሰሃ ለመግባት ምክንያት እን ዳለን እንዴት አወቃችሁ? የጽድቅ ሰዎች አለመሆናችንንስ እንዴት አወቃችሁ? እነሆ ቅዱሳን ስፍራዎችን ሰርተናል፣ እናም እግ ዚአብሔርን ለማምለክ እራሳችንን በአንድ ላይ እንሰበስባለን። ጌታ ሰዎችን ሁሉ እን ደሚያድን እናምናለንና።

፯ አሁን አሮንም እንዲህ አለው፥ የእግ ዚአብሔር ልጅ የሰው ልጆችን ከኃጢአ ታቸው ለማዳን እንደሚመጣ ታምናለህን?

፰ እናም ሰውየው አለው፥ እንደዚህ ያለ ምንም ነገር ታውቃለህ ብለን አናምንም። በእነዚህ የሞኝ ባህሎች አናምንም። ወደፊት ᐸስለሚመጡ ነገሮች እንደምታውቅ አናም ንም፣ አባቶችህ እናም ደግሞ አባቶቻችን ይመጣሉ ብለው የተናገሯቸውን በተመለ ከተ ያውቃሉ ብለን አናምንም።

፱ አሁን አሮን የክርስቶስን መምጣት በተ መለከተ እናም ደግሞ የሙታንን ትንሳኤ በተመለከተና በክርስቶስ ሞት፣ እና ስቃ ይና በደሙ ᐸየኃጢያት ክፍያ ካልሆነ በቀር

፴ᐸ አልማ ፳፯፡፳፱።
፳፩ ፩ᐸ አልማ ፲፯፡፲፣ ፲፯።
፪ᐸ ሞዛያ ፳፪፡ ፩፣
፫ᐸ አልማ ፳፭፡፪–፱።
፬ᐸ አልማ ፩፡፪–፲፭።
፭ᐸ ሞዛያ ፳፯፡ ፲፩–፲፭።
፮ᐸ ያዕቆ. ፯፡ ፩–፰።
፱ᐸ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።

ለሰው ዘር ምንም ^ቤዛ እንደማይኖር ለማ ስረዳት ቅዱሳት መጻሕፍትን ገለጠላቸው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች ማብ ራራት በጀመረ ጊዜ፣ በእርሱ ተቆጥተው ነበር፣ ያሾፉበትም ጀመሩ፤ እናም የተና ገራቸውን ቃላት ለመስማት አልፈለጉም።

፲፩ ስለዚህ፣ የሚናገረውን መስማት አለ መፈለጋቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ ከምኩ ራባቸው ወጥቶ ሄደና፣ አኒ-አንቲ ወደም ትባል መንደር ሄደ፣ እናም በዚያ ሙሎቂ ቃሉን ለእነርሱ ሲሰብክላቸው፣ ደግሞም አማንና ወንድሞቹንም አገኘ። እናም ቃሉን በተመለከተ ከብዙዎች ጋር ተከራከሩ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡ ልቡን እን ዳጠጠረ ተመለከቱ፣ ስለዚህ ሄዱና ወደ ሚዶኒ ምድር መጡ። እናም ለብዙዎች ቃሉን ሰበኩ፣ ያስተማሩትን ቃላት ያመ ኑትም ጥቂት ነበሩ።

፲፫ ይሁን እንጂ፣ አሮንና የተወሰኑ ወን ድሞቹ ተወሰዱና፣ ወደ ወህኒ ቤት ተጣሉ፣ እናም ቀሪዎቹ ከሚዶኒ ምድር በዙሪያው ወዳሉ ሥፍራዎች ሸሹ።

፲፬ እናም ወደ ወህኒ ቤት የተጣሉት በብዙ ነገሮች ^ተሰቃይተዋል፤ እናም በላሞኒና አሞን እጅ ተለቀቁ፣ እናም በእነርሱ ምግ ብና ልብስ ተሰጣቸው።

፲፭ እናም ቃሉን ለማወጅ በድጋሚ ሄዱና፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወህኒ ተለ ቀቁ፤ እናም እንደዚህ ተሰቃይተው ነበር።

፲፮ እናም ^በጌታ መንፈስ በሚመሩበት በማንኛውም ቦታ በአማሌቂውያን እያንዳ ንዱ ምኩራብ፣ ወይም ለመግባት በሚችሉ በት በማንኛውም የላማናውያን ጉባኤ የእግ ዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ሄዱ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ ይባርካቸው ጀመረ፣ ይህም ሆኖ ብዙዎችን እውነትን ወደ ማወቅ አመጡ፤ አዎን፣ ብዙዎችን ኃጢአታቸውንና ትክክል ያልሆነውን የአ ባቶቻቸውን ወግ ^ያስረዱአቸው ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ አሞንና ላሞኒ ከሚ ዶኒ ምድር የወርሳው ምድር ወደ ሆነው ወደ እስማኤል ምድር ተመለሱ።

፲፱ እናም ንጉስ ላሞኒ አሞን እንዲያገለ ግለውም ሆነ አገልጋዩ እንዲሆንም አል ፈቀደም።

፳ ነገር ግን በእስማኤል ምድር ምኩራብ እንዲሰራ አደረገ፤ እናም ህዝቡ ወይም በአ ገዛዙ ስር ያለው ህዝብ እራሳቸውን በአንድ ላይ እንዲሰበስቡ አደረገ።

፳፩ እናም በእነርሱ ተደሰተ፣ ብዙ ነገሮ ችንም አስተማራቸው። እናም ህዝቡ በእ ርሱ ስር እንደነበሩና፣ ነፃ ህዝብ እንደነበሩ፣ በአባቱ ከንጉሱም ጭቆና ነፃ እንደሆኑም ነገራቸው፤ ምክንያቱም አባቱ በእስማኤል ምድርና በዙሪያው ባሉት ምድር በሚኖ ሩት ሰዎች ላይ ይገዛ ዘንድ ሰጥቶታልና።

፳፪ እናም በንጉስ ላሞኒ አገዛዝ ስር የሆነ ምድር ከሆነ እንደፍላጎታቸው በማንኛውም ባሉበት ቦታ ጌታ አምላካቸውን ለማምለክ ^ነፃነት እንዳላቸውም ደግሞ አወጀላቸው።

፳፫ እናም አሞን ለንጉስ ላሞኒ ህዝብ ሰበከ፤ እናም እንዲህ ሆነ፣ ስለፅድቅ የሆ ኑትን ነገሮች በተመለከተ ሁሉንም ነገሮች አስተማረ። በሙሉ ትጋትም በየቀኑ መከ ራቸው፤ እናም ቃሉን አዳመጡትና የእ ግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ቀናኢ ሆነው ነበር።

ምዕራፍ ፳፪

አሮን ስለፍጥረት፣ ስለአዳም መውደቅ፣ በክርስቶስም ስላለው የቤዛነት ዕቅድ የላሞኒን አባት አስተማረ—ንጉሱ እና ቤተሰቦቹ በሙሉ ተለወጡ—በኔፋውያንና በላማናውያን መካከል የመሬት ክፍፍሉ ተገልጿል። ከ፣ቅ–ፍ.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ አሞን ያለማቋረጥ የላሞኒን ሰዎች በማስተማር ላይ እያለ፣ ወደ አሮን

፩ ^ለ ሞዛያ ፭፡፳፣ አልማ ፴፰፡፱።
፲፩ ^ሀ አልማ ፳፡፳፱።
፲፯ ^ሀ አልማ ፳፡፲፩–፲፣ ^ሀ ት.እና ቃ. ፲፰፡፴፩።
፳፪ ^ሀ ት.እና ቃ. ፲፴፬፡፩–፬፣ ^ሀ አልማ ፳፪፡፩።
፲፭ ^ሀ ት.እና ቃ. ፲፡፲–፲፣ ^ሀ ት.እና ቃ. ፲፩፡፲–፲፪፣ ^ሀ ^ለ ^ሀ ^ሀ
ኤ.አ. ፩፡፲፩።
ቅ.መ.መ. መብት።

እና ወንድሞቹ ታሪክ እንመለሳለን፤ እርሱ ከሚዶኒ ወጥቶ ከሄደ በኋላ በመን ፈስ ወደኔፊ ምድር፣ እንዲሁም ᵐከእስማ ኤል ምድር በስተቀር በምድሪቱ ላይ ሁሉ ንጉሥ ወደ ሆነውም ቤት እንኳን ᵃተመር ቷል፤ እናም እርሱም የላሞኒ አባት ነበር።

፪ እናም እንዲህ ሆነ አሮን ከወንድሞቹ ጋር ወደ ንጉሱ ቤተመንግስት ሄደና፣ ከን ጉሱ ፊት ሰገደ፣ እናም እንዲህ አለው፡ እነሆ፣ ንጉስ ሆይ፣ አንተ ከወህኒ ቤት ᵐየለ ቀቅኸን፣ የአሞን ወንድሞች ነን።

፫ እናም አሁን፣ ንጉስ ሆይ፣ ነፍሳችንን የምታተርፍ ከሆነ፣ አገልጋዮችህ እንሆና ለን። እናም ንጉሱ እንዲህ አላቸው፡ ተነሱ ህይወታችሁን እሰጣችኋለሁ፣ አገልጋዮቼ እንድትሆኑም አልፈቅድም፤ ነገር ግን እን ድትሰብኩልኝ እጠይቃችኋለሁ፤ ምክንያ ቱም በጥቂቱም እንኳን ቢሆን በወንድማ ችሁ አሞን ደግነትና በቃሉ ታላቅነት አዕ ምሮዬ ታውኳልና፤ እናም እርሱ ከሚዶኒ ወጥቶ ከእናንተ ጋር ለምን እንዳልመጣም ምክንያቱን ለማወቅ እፈልጋለሁ።

፬ እናም አሮን ለንጉሱ እንዲህ አለው፡ እነሆ የጌታ መንፈስ ወደሌላ ቦታ እንዲ ሄድ ጠርቶታል፤ እርሱም የላሞኒን ህዝብ ለማስተማር ወደ እስማኤል ምድር ሄዷል።

፭ አሁን ንጉሱ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡ ስለጌታ መንፈስ የተናገራችሁት ይህ ምን ድን ነው? እነሆ እኔን የሚያውኪኝ ነገር ይህ ነው።

፮ እናም ደግሞ አሞን—ᵐንስሃ የምትገቡ ከሆነ ትድናላችሁ፣ እናም ንስሃ ካልገባችሁ በመጨረሻው ቀን ትጣላላችሁ በማለት የተ ናገረው ይህ ምንድን ነው?

፯ እናም አሮንም መለሰለትና፣ እንዲህ ሲል ተናገረው፡ እግዚአብሔር መኖሩን ታምናለህን? እናም ንጉሱም እንዲህ አለ፡ አማሌቂውያን እግዚአብሔር አለ እንደ ሚሉ አውቃለሁ፣ እርሱን ለማምለክ እራ ሳቸውን በአንድነት ይሰበስቡ ዘንድ ቅዱስ ሥፍራን እንዲሰሩ ፈቃድ ሰጥቻቸዋለ ሁም። እናም አንተ አሁን እግዚአብሔር አለ የምትል ከሆነ እነሆ እኔ ᵐአምናለሁ።

፰ እናም አሁን አሮን ይህን በሰማ ጊዜ ልቡ ሃሴት ማድረግ ጀመረች፣ እናም እን ዲህ አለ፡ እነሆ አንተ ህያው እንደሆንክ፣ ንጉስ ሆይ፣ እግዚአብሔርም አለ።

፱ እናም ንጉሱም እንዲህ አለ፡ አባቶቻች ንን ከኢየሩሳሌም ምድር ያወጣው ያᵐታላቁ መንፈስ እግዚአብሔር ነውን?

፲ እናም አሮን እንዲህ አለው፡ አዎን እርሱ ያ ታላቁ መንፈስ ነው፣ እናም በሰ ማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ ᵐፈጥ ሯል። ይህንን ታምናለህን?

፲፩ እናም እንዲህ አለ፡ አዎን ታላቁ መን ፈስ ሁሉን ነገሮች እንደፈጠረᵐአምናለሁ፣ እነዚህን ሁሉ በተመለከተ እንድትነግረኝም እፈልጋለሁ፣ እናም ቃልህን አምናለሁ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ አሮን ንጉሡ ቃሉን እንደሚያምነው በተመለከተ ጊዜ፣ ከአዳም መፈጠር ጀምሮ ያሉትን ከቅዱሳት መጻሕ ፍት ለንጉሡ ᵐያነብለት ጀመረ—እግዚአ ብሔር ሰውን በአምሳሉ እንዴት እንደፈ ጠረ፣ እናም እግዚአብሔርስ እንዴት ትዕዛ ዛትን እንደሰጠው፣ እናም በመተላለፉ የተ ነሳም ሰው እንደወደቀ አነበበ።

፲፫ እናም አሮን ቅዱሳት መጻሕፍ ትን ᵐከአዳም መፈጠር ጀምሮ፣ የሰዎችን መውደቅ በፊቱ በማኖር፣ በስጋ ያሉበትን ሁኔታ፣ እናም ደግሞ ᵃከዓለም መፈጠር ጀምሮ፣ በክርስቶስ በኩል፣ በስሙ ለሚ ያምኑ ሁሉ የተዘጋጀውን ᶜየቤዛነት ዕቅድ አስረዳው።

፲፬ እናም ሰው ᵐበመውደቁ የተነሳ ስለ

ሯ፪ ፩ᵇ አልማ ፳፩፡ ፳፩–ሯ፪።
ᵃ አልማ ፳፩፡ ፲፯–፲፯።
ᵇ አልማ ፳፡ ፳፯።
ᶜ አልማ ፳፡ ፲፯–፲፰።
ᵈ ት.እና ቃ. ፵፯፡ ፲፫–፲፩።
ᵉ አልማ ፲፰፡ ፲፰–ሯ፰።

ᶠ ᵐ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ᵍ ᵐ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ʰ ᵐ ፩ ኔፊ ፭፡ ፣–፲፰፤ አልማ ፴፯፡ ፱።
ⁱ ᵐ ዘፍጥ. ፩፡ ሯ፯–ሯ፰።

ᵃ ᵐ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፰።
ᶜ ᵐ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ᵈ ᵐ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።

ራሱ በማንኛውም ነገር ^ብቁ ለመሆን አይ
ችልም፤ ነገር ግን የክርስቶስ ስቃዩና ሞቱ
በእምነታቸውና በንስሃቸውና በሚመሳሰ
ሉት አማካይነት ለኃጢአታቸው ^ክፍያ
ይሆናል፣ እናም እርሱም የሞትን እስ
ራት በጣጥሷል፤ ^ሞትም ድል አይኖረ
ውም፣ እናም የሞት መውጊያ በክብር ተሰፋ
ይዋጣል፤ እናም አሮን እነዚህን ነገሮች ሁሉ
ለንጉሱ አስረዳ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አሮን እነዚህን
ነገሮች በሙሉ ለንጉሱ ካስረዳው በኋላ፣
ንጉሱ እንዲህ ሲል ተናገረ፥ አንተ የተና
ገርከውን ይህን ዘለዓለማዊ ህይወት እንዳ
ገኝ ^ምን ማድረግ አለብኝ? አዎን፣ ^ከእ
ግዚአብሔር እንድወለድ፣ እናም ይህ እር
ኩስ መንፈስ ከደረቴ እንዲነቀልና፣ መን
ፈሱን ተቀብዬ በደስታ እሞላ ዘንድ፣ በመ
ጨረሻው ቀንም እንዳልጣል፣ ምን ማድ
ረግ አለብኝ? እነሆ፣ ያለኝን ^ሁሉ እተዋ
ለሁ፣ አዎን ይህን ታላቁን ደስታም እቀበል
ዘንድ መንግስቴን እለቃለሁ።

፲፮ ነገር ግን አሮን እንዲህ አለው፥ ይህንን
ነገር ^ከፈለግህ፣ በእግዚአብሔር ፊት ከሰገ
ድህ፣ አዎን፣ ለኃጢያትህ ሁሉ ንስሃ ከገባ
ህና፣ በእግዚአብሔር ፊት ከሰገድህ፣ እናም
እንደምትቀበል በማመን ስሙን በእምነት
ከጠራህ የፈለከውን ^ተስፋ ታገኛለህ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ አሮን እነዚህን
ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ንጉሱ በጉልበቱ ተን
በርክኮ በጌታ ፊት ^ሰገደ፣ አዎን፣ በመ
ሬትም ላይ እራሱን ዘረጋ፣ እናም እንዲህ
በማለት በኃይል ^ጮኸ፥

፲፰ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ አሮን
እግዚአብሔር እንዳለ ነግሮኛል፤ እናም
እግዚአብሔር ካለና፣ አንተ እግዚአብሔር
ከሆንክ፣ አንተንም እንዳውቅ ታደርጋለ
ህን፣ እናም ከሞት እነሳ ዘንድና፣ በመጨ
ረሻው ቀን እድን ዘንድ፣ አንተን ለማወቅ
ኃጢአቴን በሙሉ እተዋለሁ። እናም እን
ግዲህ ንጉሱ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣
እንደሞተ አይነት ወደቀ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዮቹ ሮጡና፣
በንጉሱ ላይ የሆነውን ሁሉ ለንግስቲቱ ነገ
ሯት። እናም እርሷ ወደንጉሱ መጣች፤ እን
ደሞተ መውደቁን ባየችም ጊዜና፣ ደግሞ
አሮንና ወንድሞቹ ለመውደቁ እንደምክ
ንያት በመሆን መቆማቸውን በተመለከተች
ጊዜ፣ በእነርሱ ተቆጣች፣ እናም አገልጋ
ዮችዋ፣ ወይም የንጉሱ አገልጋዮች፣ እነ
ርሱን ወስደው እንዲገድሉአቸው አዘዘች።

፳ አሁን አገልጋዮቹ ንጉሱ የወደቀበ
ትን መንስኤ ያውቃሉ፣ ስለዚህ በአሮንና
በወንድሞቹ ላይ እጃቸውን ለመጫን አል
ደፈሩም፤ እናም ንግስቲቱን እንዲህ በማ
ለት ተማፀኗት፥ እነሆ ከእነዚህ አንዱ ከሁ
ላችንም በላይ ^ኃያል የሆኑትን ሰዎች እን
ድንገድል ለምን ታዝዘናለሽ? ስለሆነም በፊ
ታቸው እንወድቃለን።

፳፩ እንግዲህ ንግስቲቱ የአገልጋዮቹን
ፍርሃት በተመለከተች ጊዜ በእርሷም ላይ
ክፉ የሆነ ነገር እንዳይመጣባት እጅግ መፍ
ራት ጀመረች። እናም አገልጋዮቿ አሮንና
ወንድሞቹን እንዲገድሉ ህዝቦችን እንዲ
ጠሩ አዘዘች።

፳፪ እንግዲህ አሮን የንግስቲቱን ፅኑ
ውሳኔ በተመለከተ ጊዜ፣ የህዝቡንም ልበ
ጠጣርነት የሚያውቅ በመሆኑ፣ ብዙዎች
እራሳቸውን በአንድነት ከሰበሰቡ፣ እናም
ታላቅ ፀብና ረብሻ በመካከላቸው ይኖራል
ብሎም ፈራ፤ ስለዚህ አሮን እጁን አን
ስቶ ንጉሱን ከመሬት አነሳውና፣ እንዲህ
አለው፥ ቁም። እናም ብርታትን አግኝቶ
በእግሩ ቆመ።

፳፫ እንግዲህ ይህ የተደረገው በንግሥቲ

፲፬ *ለ* ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫፣ አልማ ፵፪፡ ፲–፳፭።
ሐ አልማ ፴፡፡ ፳–፲፯።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
መ ኢሳ. ፳፭፡ ፳፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፭።
፲፭ *ሀ* የሐዋ. ፪፡ ፴፯።
ለ አልማ ፭፡ ፲፡ ፣ ፵፱።
ሐ ማቴ. ፲፫፡ ፵፪–፵፭፣ ፲፱፡ ፲፯–፳፪።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
ለ ኤተር ፲፪፡ ፡ ።
፲፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፭፡ ፳፡ ።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳ *ሀ* አልማ ፲፰፡ ፩–፫።

ቱና በብዙዎቹ አገልጋዮች ፊት ነበር። እናም ይህንንም በተመለከቱ ጊዜ እጅግ ተገረሙና መፍራት ጀመሩ። እናም ንጉሱ ተነሳን፣ [ሀ]ይሰብክላቸው ጀመር። ለእነርሱም ሰበከና፣ እንዲህም ሆኖ ቤተሰቦቹ በሙሉ ወደጌታ [ለ]ተለወጡ።

፳፬ እንግዲህ በንግስቲቱ ትዕዛዝ መሰረት ብዙዎች በአንድነት ተሰብስበው ነበር፣ እናም በአሮንና ወንድሞቹም የተነሳ በመካከላቸው ብዙዎች ማጉረምረም ጀምረው ነበር።

፳፭ ነገር ግን ንጉሱ በመካከላቸው ቆመና፣ አገለገላቸው። እናም በአሮንና ከእርሱ ጋር በነበሩት መረጋጋትን አገኙ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ የህዝቡን መረጋጋት በተመለከተ ጊዜ፣ አሮንና ወንድሞቹ በህዝቡ መካከል እንዲቆሙና ቃሉን እንዲሰብኩ አደረገ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ በምድሪቱ ሁሉ ባሉት ሰዎች መካከል፣ በዙሪያውም ባለው ክልል በባህሩም ዳርቻ፣ በምስራቅና በስተምዕራብ፣ ከዛራሔምላ ምድር በምድረበዳው ከምስራቁ ባህር ጀምሮ እስከምዕራብ በሚከፍለው በቀጭኑ መንገድ፣ እናም በባህሩም ዳርቻና በምድረበዳው ዳርቻ፣ [ሀ]በዛራሔምላ በስተሰሜን በኩል በማንቲ ዳርቻ በሲዶም ወንዝ ምንጭ በኩል፣ ከምስራቅ ወደምዕራብ በሚፈሰው በኩል [ለ]አዋጅ ላከ—እናም ይህም ላማናውያንና ኔፋውያን የተከፈሉበት ነው።

፳፰ እንግዲህ፣ ብዙዎቹ የላማናውያን [ሀ]ስራ ፈቶች በምድረበዳው ውስጥ ኖሩ፣ እናም በድንኳን ኖሩ፤ በኔፊ ምድር ውስጥ በስተምዕራብ ምድረበዳው በኩልም ተዘረጉ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ በዛራሔምላ ምድር በስተምዕራብ በኩል፣ በባህሩ ዳርቻና፣ በኔፊ ምድር በስተምዕራብ በመጀመሪያው የአባቶቻቸው የርስት ሥፍራ እናም በባህሩ ዳርቻ ነበሩ።

፳፱ እናም ደግሞ ኔፋውያን ካባረሩአቸው አካባቢ በባህሩ ዳርቻ በስተምስራቅ በኩል ብዙ ላማናውያን ነበሩ። እናም በዚያም ኔፋውያን ሙሉ በሙሉ በላማናውያን ሊከበቡ ተቃርበው ነበር፤ ይሁን እንጂ ኔፋውያን በምድረበዳው ወሰን በስተሰሜን በኩል፣ በሲዶም ወንዝ መነሻ፣ ከምስራቅ እስከምዕራብ፣ በምድረበዳው ዙሪያ ያሉትን ሥፍራዎች ተቆጣጥረዋል፣ በስተሰሜን በኩል፣ [ሀ]ለጋስ ብለው በሚጠሩት ምድር እስከሚመጡም ድረስ እንኳን ተቆጣጥረዋል።

፴ እናም ይህም ወደ ሰሜን የሚርቅ ሆኖ፣ የዛራሔምላ ህዝቦች በመጀመሪያ [ሀ]ያረፉበት ስፍራ በመሆኑ ያገኙበት [ለ]ስለአጥንታቸው የተናገርንባቸው ሰዎች ኖረውበት እናም ተደምሰሰውበት ወደነበረው ምድር ውስጥ እየገባ፣ [ሐ]የወደመ ስፍራ ብለው የሚጠሩትን ያዋስን ነበር።

፴፩ እናም እነርሱም በምድረበዳው በስተደቡብ በኩል መጡ። በስተሰሜን በኩል ያለው ቦታም [ሀ]የወደመው ስፍራ ተብሎ ይጠራ ነበር፣ እናም በስተደቡብ በኩል ያለው ምድር ለጋስ ተብሎ ይጠራል፣ ይህም በተለያዩ የዱር አውሬዎች ተሞልቶ የነበረ፣ ከፊሎቹም ምግብ ፍለጋ ከሰሜን በኩል የመጡ ነበሩበት፣ ምድረበዳው ነበር።

፴፪ እናም አሁን፣ ለኔፋውያን እስከ ለጋሱ ምድርና እስከ ወደመው ስፍራ ከባህሩ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ርቀቱም የአንድ ቀን ተኩል [ሀ]ጉዞ ብቻ ነበር፤ እናም የኔፊና የዛራሔምላ ምድር ከሞላ ጎደል በውሃ የተከበበ ነበር፤ በስተሰሜንና በስተደቡብ ምድር መካከል [ለ]ቀጭን ሥፍራ ነበር።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን ለጋስን

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ፣ ማስተማር፣ አስተማሪ፣ አገልግሎት።
ለ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፳፯ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፫–፲፯።
ለ አልማ ፳፫፡ ፩–፬።
፳፰ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡ ፳፪–፳፭።
፳፱ ሀ አልማ ፶፪፡ ፱፣ ፳፫፡ ፭።
፴ ሀ ሔለ. ፯፡ ፲።
ለ ሞዛያ ፳፡ ፯–፲፪፣ ፳፰፡ ፲፩–፲፱።
ሐ አልማ ፶፡ ፴፬፣ ሞር. ፱፡ ፩–፫።
፴፩ ሀ ሔለ. ፫፡ ፭–፯።
፴፪ ሀ ሔለ. ፱፡ ፯።
ለ አልማ ፶፡ ፴፩።

ምድር፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራቡ ባህር፣ ይኖሩበት ነበር፤ እናም ኔፋውያን ላማናውያን በስተሰሜን ምንም ሀብት እንዳይኖራቸው፣ በስተሰሜንም ያለውን ሥፍራ እንዳያጥለቀልቁት በብልሃታቸው ከጠባቂዎቻቸውና ከወታደሮቻቸው ጋር በስተደቡብ ባለው ሥፍራ አገዱአቸው።

፴፬ ስለዚህ በኔፊ ምድር እና በዙሪያው ካለው ምድረበዳ በስተቀር ላማናይቶች ምንም ይዞታዎች ሊኖራቸው አልቻሉም። ላማናውያን ለእነርሱ ጠላት በመሆናቸው፣ በየትኛውም አቅጣጫ አንዳያሰቃዩአቸው፣ እናም ደግሞ እንደፍላጎታቸው የሚሸሹበትን ሃገር ያገኙ ዘንድ እንግዲህ በኔፋውያን ይህ ብልህነት ነው።

፴፭ እናም አሁን እኔ፣ ይህን ካልኩኝ በኋላ፣ ወደ አሞንና አሮን፣ ኦምነርና ሂምኒ፣ እናም ወንድሞቻቸው ታሪክ በድጋሚ እመለሳለሁ።

ምዕራፍ ፴፫

የኃይማኖት ነፃነት ታወጀ—በሰባት ምድሮች እና ከተሞች ያሉ ላማናውያን ተሰወጡ—እራሳቸውንም አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች-ሌሂ ብለው ጠሩ፣ እናም ከእርግማኑ ነፃ ወጥተዋል—አማሌቂውያንና አሙሎናውያን እውነትን አልተቀበሉም። ከ፣ ፳–፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እንግዲህ እንዲህ ሆነ የላማናውያን ንጉስ በአሞን፣ በአሮን፣ በኦምነር፣ በሂምኒ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በማንኛውም ቦታ በየትኛውም በምድሪቱ ክፍል ለመስበክ በሚሄዱት ወንድሞቻቸው ላይ እጃቸውን እንዳይጭኑ በህዝቦቹ ሁሉ መካከል [ሀ]አዋጅ ላከ።

፪ አዎን፣ ለማሰር እጃቸውን በእነርሱ ላይ በማድረግ ወይንም በወህኒ ቤት እንዳይጥሏቸው፣ ወይም እንዳይተፉባቸውም፣ እንዳይመቱአቸውም፣ ከምኩራባቸው እንዳያባርሩአቸውም፣ እንዳይገርፉአቸውም፣ ድንጋይም እንዳይወረውሩባቸውም፣ ነገር ግን ወደቤቶቻቸው እናም ደግሞ ወደ ቤተመቅደሶቻቸውና ወደተቀደሱት ስፍራዎቻቸው ውስጥ ለመግባት ነጻ ፍቃድ እንዲኖራው በመካከላቸው አዋጅ ላከ።

፫ እናም እንደዚህ እንደፍላጎታቸውም የጌታን ቃል እንደፍላጎታቸው ለመስበክ ይሄዱ ዘንድ፣ ምክንያቱም ንጉሱና ቤተሰቦቹ ወደጌታ ተለውጠዋልና፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሚከላከለው እንዳይኖርበት ነገር ግን በምድሪቱ ላይ በሙሉ እንዲሆን፣ ህዝቡም መጥፎውን የአባቶቻቸውን [ሁ]ወግ ለማሳመን፣ እናም ሁሉም የእርስበርስ ወንድሞች መሆናቸውን እንዲያምኑ፣ ወይም እንዳይገድሉ፣ ወይም እንዳይዘርፉና፣ ወይም እንዳይሰርቁ፣ ወይም ዝሙትንም እንዳይፈፅሙ፣ ወይም ክፉ የሆኑትንም ነገሮች እንዳይፈፅሙ በምድሪቱ ላይ ሁሉ ለህዝቡ አዋጁን ላከ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ አዋጁን በላከ ጊዜ፣ አሮንና ወንድሞቹ ከከተማ ወደ ከተማ ተጓዙና፣ ከአንዱ ማምለኪያ ቦታ ወደ ሌላኛው በመጓዝ፣ ቤተክርስቲያኖችን በማቋቋም፣ እናም ካህናትንና መምህራን በላማናውያን ምድር በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ቀደሱአቸው፤ እናም እንደዚህ ታላቅ ስኬትንም ማግኘት ጀመሩ።

፭ እናም በሺህ የሚቆጠሩ ጌታን ወደማወቅ መጡ፣ አዎን፣ በሺህ የሚቆጠሩት በኔፋውያን [ሂ]ባህል ወደማመንም መጡ፤ እናም እስከአሁኑ ጊዜ የተላለፉትን [ለ]መዝገቦችና ትንቢቶችም ተማሩ።

፮ እናም ጌታ ህያው እንደሆነ፣ በርግጥም ብዙዎች እንዳመኑትም፣ ወይም በራዕይና በትንቢት መንፈስ፣ እናም በውስጣቸው ድንቅ ስራን በሚሰራው በእግዚአብሔር ኃይል መሰረት በአሞንና በወንድሙ ሰበብ ብዙዎች እውነቱን ወደ ማወቅ የሚ

[ሀ] ሀ አልማ ፴፪፡፴፯። [ለ] ለ አልማ ፴፫፡፲፱። ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
[ሁ] ሁ አልማ ፴፮፡፳፩። [ሂ] ሂ አልማ ፴፫፡፲፪።

መጡት—አዎን እንዲሁም እላችኋለሁ፣ ጌታ ህያው እንደሆነ፣ በስብከታቸው አም ነው የነበሩ ላማናውያን ሁሉ፣ እናም ወደ ጌታ ᵐተለውጠው የነበሩ፣ መንገዳቸውንም ᵃአልሳቱም ነበር።

፲፯ እነርሱም ፃድቃን ህዝቦች ሆኑ፣ ከእንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም ከወን ድሞቻቸው ጋር እንዳይጣሉ የአመፅ መሣ ሪያቸውን ጣሉ።

፲፰ አሁን፣ ወደጌታም ᵐየተለወጡት እነ ዚህ ናቸው፡፡

፲፱ በእስማኤል ምድር የነበሩት የላማናው ያን ሕዝቦች፣

፲ እናም ደግሞ በሚዶኒ ምድር የነበሩት የላማናውያን ሕዝቦች፣

፲፩ እናም ደግሞ በኔፊ ከተማ የነበሩት የላ ማናውያን ሕዝቦች፤

፲፪ እናም ደግሞ በሼለም ምድር የነበሩ ትና፣ በሼምሎን ምድር የነበሩት፣ እናም በልሙኤል ከተማና፣ ᵐበሻምሎንም ከተማ የነበሩት የላማናውያን ሕዝቦች።

፲፫ እናም እነዚህ ወደጌታ ᵐየተለወጡት የላማናውያን ከተሞች ስም ነበሩ፤ እናም የአመፃቸውን መሳሪያዎች፣ አዎን፣ ሁሉ ንም የጦር መሳሪያዎቻቸውን የጣሉት እነዚህ ናቸው፤ እናም ሁሉም ላማናውያን ነበሩ።

፲፬ እናም ከአንዱ በስተቀር አማሌቂው ያን ᵐአልተለወጡም ነበር፤ ᵃከአሙሎና ውያንም ማንም አልተለወጠም፤ ነገር ግን ልባቸውን፣ ደግሞም በዚያ በከፊል በምድ ሪቱ፣ አዎን እናም መንደሮቻቸውን ሁሉና ከተሞቻቸውን ሁሉ የሚኖሩት ላማናውያን ልብም አጠጥረውት ነበር።

፲፭ ስለሆነም፣ ንስሃ የገቡባቸውንና እው ነትን እንዲያውቁ የተደረጉባቸውን እናም የተለወጡባቸውን የላማናውያን ከተሞች ሁሉ ሰይመናቸው።

፲፮ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱና የተ ለወጡት ከወንድሞቻቸው ተለይተው ይታ ወቁ ዘንድ ስም እንዲኖራቸው ፈለጉ፤ ስለ ዚህ ንጉሱ ከአሮንና ከብዙ ካህናቶቻቸው ጋር እነርሱ እንዲለዩ የሚሰጣቸውን ስም በተመለከተ ተመካከሩ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ስማቸውንም ᵐአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች በማለት ጠሩአቸው፤ እናም በዚህ ስም ተጠሩና፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ላማናውያን ተብለው አልተጠሩም።

፲፰ እናም ታታሪ ሰዎች መሆን ጀመሩ፤ አዎን፣ እናም ከኔፋውያን ጋር ወዳጅ ነበሩ፤ ስለዚህ ከእነርሱም ጋር ጓደኝነትን ጀመሩ፣ እናም የእግዚአብሔር ᵐእርግማን ከዚያን ጊዜ በኋላ አልተከተላቸውም።

ምዕራፍ ፳፫

ላማናውያን የእግዚአብሔር በሆኑት ሰዎች ላይ መጡ—አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች በክርስቶስ ተደሰቱ፣ እናም በመልአክት ተጎበኙ—እራሳቸውን ከመከላከል ይልቅ በሞት መሰቃየትን መረጡ—በርካታ ላማናውያን ተለወጡ። ከ፣ቀ–ፀ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ አማሌቂውያንና፣ አሙሎናውያንም፣ በአሙሎን ምድር፣ ደግሞ በሔላም ምድር የነበሩት ላማናውያ ንም፣ እናም ᵐበኢየሩሳሌም ምድርና፣ በአ ጠቃላይ በምድሪቱ ሁሉ የነበሩት፣ ያልተ ለወጡት፣ እናም ᵃየአንቲ-ኔፊ- ሌሂን ስም ያልወሰዱት፣ በአማሌቂውያንና በአሙሎ ናውያን በወንድሞቻቸው ላይ ለማስቆጣት ተነሳስተው ነበር።

፪ እናም ጥላቻቸው በእነርሱ ላይ መሪር ነበር፤ እንዲህም ሆኖ በንጉሳቸውም ላይ እስከሚያምፁ ድረስ፣ እርሱ ንጉሳቸው እንዲሆን አልፈለጉም ነበር፤ ስለዚህ በአ ንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ህዝብ ላይም የጦር መሳ ሪያዎቻቸውን አነሱ።

፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
ᵃ አልማ ፳፯፡፳፯።
፳ ᵐ አልማ ፳፯፡፲፣ ፴፩።
፲፪ ᵐ ሞዛያ ፳፪፡፳፡ ፲፩።
፲፫ ᵐ አልማ ፳፫፡፲።
፲፬ ᵐ አልማ ፳፬፡፳፱።
ᵃ አልማ ፳፫፡፴፩–፴፱።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።
፲፰ ᵐ ፩ ኔፊ ፪፡፳፫፣
፪ ᵐ ᵃ ኔፊ ፴፡፭–፮፣
፫ ᵐ ᵃ ኔፊ ፪፡፲፴–፲፯።
፳፬ ᵐ ᵃ አልማ ፳፬፡፩።
ᵃ አልማ ፳፭፡፩፣ ፲፫።

፲ እንግዲህ ንጉሱ በልጁ ላይ መንግስቱን አፀደቀ፣ እናም ስሙን አንቲ-ኔፊ- ሌሂ በማለት ጠራው።

፡ እናም ንጉሱ ላማናውያን በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ለጦርነት ዝግጅት በጀመሩበት ዓመት ሞተ።

፲፪ እንግዲህ አሞንና ወንድሞቹ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የመጡት ሁሉ ላማናውያን ወንድሞቻቸውን ለማጥፋት መዘጋጀ ታቸውን በተመለከቱ ጊዜ፣ ወደ ምድያም ምድር መጡ፣ እናም እዚያ አሞን ወንድሞቹን በሙሉ ተገናኘ፤ እናም እራሳቸውን ከላማናውያን ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከላሞኒና ደግሞ ከአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ጋር ᵐለመወያየት ወደ እስማኤል ምድር መጡ።

፲፫ እንግዲህ ወደ ጌታ ከተለወጡት ሰዎች መካከል በወንድሙ ላይ የጦር መሣሪያን የሚያነሳ አንድም ሰው አልነበረም፤ ለጦርነትም ቢሆን ምንም ዓይነት ዝግጅት ማንም አያደርግም፤ አዎን እናም ደግሞ ንጉሳቸው ለጦርነት እንዳይዘጋጁ አዟል።

፲፬ እንግዲህ፣ ይህንን በተመለከተ ለህዝቡ የተናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፥ የተወደዱትንም ሕዝቦቼን፣ ታላቁ አምላካችን በቸርነቱ እነዚህን ኔፋውያን ወንድሞቻችን ለእኛ እንዲሰብኩ፣ እናም የአባቶቻችንን ክፉ ᵐባህሎች እንዲያሳምኑን ስለላካቸው እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፭ እናም እነሆ፣ ከእነዚህ ከኔፋውያን ወንድሞችም ጋር ጓደኝነት እንድንጀምር፣ ልባችንን ለማራራት የመንፈሱን ክፍል ስለላከልን ታላቁ አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፮ እናም እነሆ፣ ይህንን ጓደኝነት በመጀመር ᵐኃጢአታችንንና ብዙ ግድያዎችን መፈፀማችንን ስላመንን ደግሞ አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፯ እናም ለእነዚህን ነገሮች ንስሃ እንድንገባ ስለፈቀደልንና፣ ደግሞ ለፈፀምናቸው ኃጢአቶችና ግድያዎች ᵐይቅር ስላለን፣ እናም ᴬጥፋታችንን በልጁ አማካኝነት ከልባችን ስለወሰደው አምላኬን፣ አዎን ታላቅ የሆነውን አምላኬን አመሰግነዋለሁ።

፲፰ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ (ከሰው ዘር ሁሉ በላይ የጠፋን እኛ በመሆናችን) ለኃጢአታችን ሁሉ እንዲሁም በር ካታ ግድያዎችን ለፈፀምንበት ንስሃ ለመግባት፣ እናም እነዚህን እግዚአብሔር ከልባችን ᵐእንዲያስወግድልን ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ ይህ ብቻ ስለነበረ፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት በበቂ ሁኔታ ንስሃ ገብተን እርሱም ጥፋታችንን ሊወስድ በሚችልበት ሁሉ ልናደርግ የምንችለው ሁሉ ይህ ነበርና፤

፲፱ እንግዲህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እግዚአብሔር እንከናችንን በመውሰዱ፣ እናም ጎራዴዎቻችን ስላበሩ፣ ከእንግዲህ ጎራዴዎቻችንን በወንድሞቻችን ደም አናጎድፋቸው።

፲፲ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ አይሆንም፣ በወንድሞቻችን ደም እንዳይጎድፉ ዘንድ ጎራዴዎቻችንን እናስቀምጣቸው፤ ምናልባትም ጎራዴዎቻችንን በድጋሚ ካጎ ደፍናቸው ለኃጢአታችን ክፍያ በሚሆነው በታላቁ አምላካችን ልጅ ደም ከእንግዲህ ᵐሊነፁ አይችሉም ይሆናልና።

፲፰ እናም ታላቁ አምላክ በእኛ ላይ ምህረትንና፣ እንዳንጠፋ እነዚህን ነገሮች እና ድናውቃቸው አድርጓል፤ አዎን፣ እናም ᵐነፍሶቻችንን ልጆቻችንን ከመውደዱ ያህል ድረስ ስለሚወድ አስቀድሞ እነዚህን ነገሮች እንድናውቃቸው አድርጓል፤ ስለዚህ፣ ᴬየደህንነት ዕቅድ ለእኛ እንዲሁም ለወደፊቱ ትውልድ እንዲታወቅ በምህረቱ በመላዕክቱ ጎብኝቶናል።

፲፳ አቤቱ አምላካችን እንዴት መሀሪ

ᵉ ᴮ አልማ ፳፯፡ ፱–፲፫።
ᶠ ᴮ ሞዛያ ፩፡ ፫።
ᵍ ᴮ ት.እና ቃ. ፲፰፡ ፴፱።
ʰ ᴮ ዳን. ፱፡ ፱።
ᴬ ቅ.መ.መ. በደል።
ᴮ ᴮ ኢሳ. ፶፫፡ ፱–፯።
ᶜ ᴮ ራዕ. ፩፡ ፭።
ᵈ ᴮ ቅ.መ.መ. ነፍስ—የነፍሶች ዋጋ።
ᴱ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።

ነው! እናም አሁን እነሆ፣ ጉድፋችንን ከራ
ሳችን ለማስወገድ ይህን ያህል ብቻ ማድ
ረግ በመቻላችን እናም ጎራዴዎቻችን እን
ዲያበሩ በመደረጋቸው፣ ቃሉን ለእኛ ከሰ
ጠንና በዚህም ንጹህ ካደረገን በኋላ ጎራዴ
ያችንን በወንድሞቻችን ደም እንዳልበከልን
በመጨረሻው ቀን፣ ወይም በፊቱም እንዲ
ፈረድብን በምንቆምበት ቀን ለአምላካችን
ምስክር እንዲሆኑ፣ ጎራዴዎቻችን እያበሩ
እንድንጠብቃቸው እንደብቃቸው።

፲፯ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ወንድሞ
ቻችን ሊያጠፉን ከፈለጉ፣ እነሆ፣ ጎራዴ
ዎቻችንን እንደብቃቸዋለን፤ አዎን፣ በመ
ጨረሻው ቀንም እንዳልተጠቀምንባቸው
ምስክር ይሆኑ ዘንድ አንፀባራቂ እንዲሆኑ
በመሬቱ ውስጥ እንደብቃቸዋለን፤ እናም
ወንድሞቻችን የሚያጠፉን ከሆነ፣ እነሆ፣
ወደ አምላካችን [ሀ]እንሄዳለንም፣ እንድና
ለንም።

፲፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱ ይህ
ንን አባባል በጨረሰና፣ ህዝቡም በአንድ
ላይ በተሰበሰበ ጊዜ፣ ጎራዴያቸውን፣ እናም
የሰው ደም ለማፍሰስ የሚያገለግሉትን መሳ
ሪያዎች ሁሉ ወሰዱና፣ በመሬት ውስጥም
[ለ]ቀበሩአቸው።

፲፱ እናም ይህንን ያደረጉት ከእንግዲህ
መሳሪያዎቹን የሰው ልጆችን ደም ለማፍ
ሰስ [ሐ]በድጋሚ እንደማይጠቀሙበት በእ
ነርሱ አመለካከት ለእግዚአብሔርና ለሰ
ዎች ምስክር እንዲሆን ነበር፤ እናም ይህን
ያደረጉት የወንድሞቻቸውን ደም ከማፍሰስ
ህይወታቸውን [መ]አሳልፈው እንደሚሰጡና፣
ከወንድም ከመውሰድ ይልቅ ለእርሱ መስ
ጠት እንደሚሻል ነበር፤ እናም ስራ በመ
ፍታት ጊዜያቸውን ከማሳለፍ በእጆቻቸው
ብዙ እንደሚሰሩ ለማረጋገጥና ከእግዚአብ
ሔርም ጋር [ሠ]ቃል ኪዳን ለመግባት ነው።

፲፱ እናም እነዚህ ላማናውያን እንዲያም
ኑና እውነትን እንዲያውቁ በመጡ ጊዜ፣
[ረ]የፀኑ እንደነበሩ፣ እናም ኃጢያትን ከመፈ
ፀም ሞት እንደሚሻላቸው እንደዚህ ተመ
ልክተናል፤ የሰላም መሳሪያዎቻቸውን እን
ደደበቁ፣ ወይም የጦርነት መሳሪያዎቻቸ
ውንም ለሰላም ሲሉ እንደደበቁ ተምልክ
ተናል።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ወንድሞቻቸው
ላማናውያንም ለጦርነት ተዘጋጁና፣ ንጉሱን
ለማጥፋትና፣ ሌላውንም በቦታው ለመተ
ካት፣ እናም ደግሞ የአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች
ህዝቦችንም ከምድሪቱ ለማጥፋት ወደ ኔፊ
ምድር መጡ።

፳፩ እናም ህዝቡ ላማናውያን በእነርሱ ላይ
መምጣታቸውን በተመለከቱ ጊዜ ከእነርሱ
ጋር ለማገናኘት ሄዱና፣ በፊታቸውም ወደ
መሬት [ሠ]ዝቅ አሉላቸው፣ እናም የጌታን ስም
መጥራት ጀመሩና፤ ላማናውያን በእነርሱ
ላይ በመጡና በጎራዴው እነርሱን መግደል
በጀመሩ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ነበሩ።

፳፪ እናም የሚቋቋማቸውን ሳያገኙ አንድ
ሺህ አምስት የሚሆኑትን ገደሉ፤ እናም እነ
ርሱ ከአምላካቸው ጋር ለመኖር በመሄዳ
ቸው የተባረኩ እንደሆኑ እናውቃለን።

፳፫ እናም ላማናውያን ወንድሞቻቸው
ከጎራዴው እንዳልሸሹ እንዲሁም ወደ
ቀኝም ሆነ ወደግራ ፈቀቅ አለማለታቸ
ውን፣ ነገር ግን እንደወደቁና እንደጠፉ፣
እናም በጎራዴው [ሰ]እየጠፉ እያለ አምላካ
ቸውን ማመስገናቸውን በተመለከቱ ጊዜ—

፳፬ እናም ላማናውያን ይህንን በተመለ
ከቱ ጊዜ እነርሱን ከመግደል [ሸ]ተገቱ፤ እናም
በጎራዴው ለወደቁት ወንድሞቻቸው በው
ስጣቸው ልባቸውም [ቀ]ያዘኑ ብዙዎች ነበሩ፣
ስላደረጓቸውም ነገሮች ንስሃ ገብተዋልና።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ የጦር መሳሪያዎ
ቻቸውን ጣሉና፣ በድጋሚ አይወሰዱአቸ
ውም፣ ምክንያቱም በፈፀሟቸው ግድያ
ዎች ተፀፅተዋልና፤ እናም እነርሱን ለመ
ግደል ክንዶቻቸውን በእነርሱ ላይ በሚያ

፲፯ ሀ አልማ ፴፡ ፲፩–፲፭።
፲፯ ለ ሔለ. ፲፭፡ ፱።
፲፰ ሀ አልማ ፶፫፡ ፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳፩ ሀ አልማ ፳፯፡ ፫።
፳፫ ሀ አልማ ፳፯፡ ፴፪።
፳፭ ሀ አልማ ፳፭፡ ፩።
ለ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።

ነሱት ምህረት በመተማመን እንደ ወንድ ሞቻቸው ተንበረከኩ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ከተገደሉት በበለጠ የእግዚአብሔር የሆኑት በዚያን ቀን ተጨመሩ፤ እናም እነዚያ የተገደሉትም ፃድቃን ነበሩ፣ ነገር ግን እነርሱ ᵐእንደዳኑ ስለዚህ ለጥርጣሬ ምንም ምክንያት አልነበረንም።

፳፯ እናም ከእነርሱ መካከል ኃጢአተኛ የሆነ የተገደለ አልነበረም፤ ነገር ግን ከሺ ዎች የሚበልጡ እውነትን ወደማወቅ መጥ ተዋል፤ ስለዚህ ጌታ ለህዝቡ ደህንነት በብዙ ᵐመንገድ እንደሚሰራ እንመለከታለን።

፳፰ አሁን ብዙዎቹን ወንድሞቻቸውን የገደሉት ብዙ ቁጥር ያላቸው ላማናውያን አማሌቂውያን እና አሙሎናውያን ነበሩ፣ ብዙዎቹም ᵐየኔሆር ᵃስርዓትን የሚየሚከ ተሉ ነበሩ።

፳፱ እንግዲህ፣ የጌታን ሰዎች ከተቀ ላቀሉት መካከል፣ አማሌቂውያንም ሆነ አሙሎናውያን የተባሉ፣ በኔሆር ስርዓ ትም የሚጓዙ ᵐአልነበሩም፣ ነገር ግን እነ ርሱ የላማንና የልሙኤል ዝርያዎች ነበሩ።

፴ እናም ህዝቡ በጌታ መንፈስ አንዴ ᵐከታነፁ፣ እናም ፅድቅን በሚመለከቱ ነገ ሮች ታላቅ ᵃእውቀትን ካገኙ በኋላ፤ እናም ወደ ኃጢያትና መተላለፍ ᵃበመውደቃቸው ይበልጥ ጠጣሮች መሆናቸውንና፣ ሁኔታች ውም እነዚህን ነገሮች በጭራሽ የማያውቁ ከሚመስለው ᵐይበልጥ የከፋ እንደሆነ በዚህ በግልጽ ለመለየት ይቻለናል።

ምዕራፍ ፳፭

የላማናውያን ወረራ ተስፋፋ—አቢናዲ እንደተነበየው የኖህ ካህናት ዝርያዎች ጠፉ—ብዙ ላማናውያን ተለወጡ፣ እናም ከአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎችን ጋር ተቀላ ቀሉ—በክርስቶስ አመኑ እናም የሙሴን ህግ ጠበቁ። ከ፣–ሮ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እነሆ፣ አሁን እንዲህ ሆነ ላማና ውያን ወንድሞቻቸውን በመግደላቸው ይበልጥ ተናደዱ፤ ስለዚህ በኔፋውያን ላይ ለበቀል ማሉ፤ እናም በዚያን ጊዜ ᵐየአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎችን ለመግደል ሙከራ አላደረጉም ነበር።

፪ ነገር ግን ወታደሮቻቸውን ወሰዱና፣ ወደ ዛራሔምላ ምድር ዳርቻ ሄዱ፣ እናም በአሞኒህ ምድር ያሉትን ሰዎች አጠቁአ ቸው፣ እናም ᵐአጠፉቸው።

፫ እናም ከዚያን በኋላ ከኔፋውያን ጋር ብዙ ውጊያ ነበራቸው፣ በዚህም ተባረሩ በትና ተገደሉበት።

፬ እናም ከተገደሉት ላማናውያን መካ ከል ᵐየአሙሎንና የወንድሞቹ ዘሮች፣ የኖህ ካህናት የነበሩት ናቸው፣ እናም በኔፋውያን እጅ ነበር የተገደሉት፤

፭ እናም ቀሪዎቹ፣ በስተምስራቅ በኩል በምድረበዳው ከሸሹ በኋላ፣ እናም በላ ማናውያን ላይ ኃይላቸውንና ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመያዛቸው፣ በርካታ ላማናው ያን በእምነታቸው የተነሳ በእሳት ᵐእንዲ ጠፉ ተደረገ—

፮ ᵐለብዙዎቹ፣ ብዙ ጥፋት ከደረሰባቸው እናም ከተሰቃዩ በኋላ፣ አሮንና ወንድሞቹ በምድራቸው የሰበኩትን ᵃቃል ማስታወስ ጀመሩ፤ ስለዚህ የአባቶቻቸውንም ᵃወግ አለማመንና፣ በጌታ በማመን፣ እናም ለኔፋ ውያን ታላቅ ኃይልን እንደሰጣቸው ማመን ጀመሩ፤ እናም እንደዚህ ብዙዎች በምድ ረበዳው ውስጥ ተለውጠው ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ᵐየአሙሎን ልጆች

፳፮ ᴴ ራዕ. ፲፬፡ ፲፫።
፳፯ ᴴ ኢሳ. ፶፭፡ ፳–፴፣ አልማ ፴፯፡ ፮–፯።
፳፰ ᴴ አልማ ፩፡ ፲፭፣ ፪፡ ፩፣ ፳። ᵃ አልማ ፳፩፡ ፬። ᵐ ፳፱ ᴴ አልማ ፳፫፡ ፲፬። ᵐ ፴ ᴴ ማቴ. ፲፪፡ ፣ ᵃ ዕብ. ፲፡ ፳፮፣ አልማ ፴፯፡ ፣ ᵃ ሐ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲፬፣ አልማ ፱፡ ፲፱። ᵐ ᵃ ᵐ ᵃ ᵐ ᵃ

ቅሪት የሆኑት ገዝዎች፣ እነርሱ፣ አዎን፣ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚያምኑት ᵃእንዲ ገደሉ አደረጉ።

፳ እንግዲህ ይህ ሰማዕት ብዙዎች ወን ድሞቻቸውን በቁጣ እንዲታወኩ አደረገ፤ እናም በምድረበዳው ፀብ ተጀመረ፤ ላማና ውያንም የአሙሎንን ዘር ᵇማደንና፣ መግ ደል ጀመሩ፤ እናም በምድረበዳው በስተ ምስራቅ በኩል ሸሹ።

፳፩ እናም እነሆ በዚህን ጊዜ እነርሱ በላ ማናውያን ታደኑ። ስለዚህ አቢናዲ በእሳት እንዲሞት ዘንድ ስላደረጉት የካህናቱ ዘሮች በተመለከተ የተናገረው ቃል ተፈፀመ።

፲ በእኔ ላይ ᵇየምታደርጉት ነገር ወደፊት ሊመጣ ያለው ነገር ምሳሌ ነው በማለት ተና ግሮአቸው ነበርና።

፲፩ እናም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ባለው እምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ሞትን ᵇበእሳት እንዲቀጣ የተደረገው አቢናዲ ነበር፤ አሁን እርሱ ይህን ማለቱ ነበር፣ እርሱ እንደተሰ ቃየው ብዙዎች በእሳት ሞት ይሰቃያሉ።

፲፪ እናም ለኖህ ካህናትም ዘሮቻቸው እር ሱን እንዳደረጉት ብዙዎችን በእሳት እን ደሚገድሉ፣ እናም ልክ እረኛ የሌላቸው በጎች እንደሚባረሩትና በዱር አውሬዎች እንደሚበሉት ወደሌላ ሀገርም እንደሚበ ታተኑና እንደሚገደሉ ነገራቸው፤ እናም አሁን እነሆ፣ ዘሮቻቸው በላማናውያን በመ ባረራቸው፣ በመታደናቸውና በመመታታ ቸው እነዚህ ቃላት ተረጋግጠው ነበር።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ኔፋ ውያንን ማሸነፍ አለመቻላቸውን በተመ ለከቱ ጊዜ ወደራሳቸው ምድር ተመለሱ፤ እናም ብዙዎች በእስማኤል ምድርና በኔፊ ምድር ለመኖር ሄዱ፣ እናም ᵇአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ከነበሩትም የእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ።

፲፬ እናም ወንድሞቻቸው እንዳደረጉት የጦር መሳሪያዎቻቸውን ᵇቀበሩና፣ ፃድቃን ህዝብም መሆን ጀመሩ፤ እናም በጌታ ጎዳና ተራመዱና፣ ትዕዛዛቱንና ህግጋቱን ጠበቁ።

፲፭ አዎን፣ እናም የሙሴን ህግ ጠብቀ ዋል፤ በአሁኑም ጊዜ ሁሉም ስላልተፈ ፀመ የሙሴን ህግ መጠበቅ አስፈላጊ ነበ ርና። ነገር ግን ᵇየሙሴ ህግ ቢኖርም የክ ርስቶስን መምጣት ይጠባበቁ ነበር፣ ምክ ንያቱም የሙሴ ህግ የመምጣቱ ᵃምልክት መሆኑን አስበው ስለነበር፣ እናም ክርስቶ ስም ለእነርሱ እስከሚገለጥ ድረስ ᵃየው ጪአዊውን ሥርዓታቸውን ማከናወን እን ዳለባቸው ስለሚያምኑ ነው።

፲፮ እንግዲህ ᵇደህንነትም በሙሴ ህግ እን ደሚመጣ አልገመቱም፤ ነገር ግን ᵃየሙሴ ህግ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት ያጠ ነክራል፤ እናም እነዚያ ነገሮች ይመጣሉ ብሎ በተናገረው በትንቢት መንፈስ ᵃተስፋ በማድረግ፣ በእምነታቸው የዘለዓለማዊውን ደህንነት ተስፋ ያደርጋሉ።

፲፯ እናም አሁን እነሆ አሞንም፣ አሮ ንም፣ ኦምነርም፣ ሒምኒም፣ እናም ወን ድሞቻቸው በላማናውያን መካከል ድልን ስላገኙ፣ ጌታም ᵇእንደፀሎታቸው ስለሰ ጣቸውና ቃሉን ደግሞ በዝርዝር ስላረጋገ ጠላቸው እጅግ ተደሰቱ።

ምዕራፍ ፳፯

አሞን በጌታ ተመካ—ታማኞች በጌታ ይጠነክራሉ፣ እናም እውቀት ይሰጣቸ ዋል—ሰዎች በእምነት ሺህ ነፍሳትን ወደ ንስሃ ያመጣሉ—እግዚአብሔር ሁሉም ዓይነት ስልጣን አለው እናም ሁሉንም ያውቃል። ከ፣–ፍ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ አሞን ለወንድሞቹ የተ

፣ ᵃ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፳ ᵇ ሞዛያ ፲፯፡ ፲፳።
፲ ᵇ ሞዛያ ፲፫፡ ፲።
፲፩ ᵇ ሞዛያ ፲፣፡ ፲፫።
፲፫ ᵇ አልማ ፳፫፡ ፲፣–፲፣።
፲፬ ᵇ አልማ ፳፬፡ ፲፭፣ ፳፣፡ ፴፪።
፲፭ ᵇ ያዕቆ. ፪፡ ፭፣ ጄረም ፩፡ ፲፩። ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᵃ ሞዛያ ፫፡ ፲፬–፲፭፣ ፲፣፡ ፲፬።
ᵃ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፪–፴፪።
፲፣ ᵇ ሞዛያ ፲፪፡ ፴፩–፴፣፣ ፲፫፡ ፳፯–፴፫።
ᵃ ᵇ ሄለ ፪ ተሰ. ፭፡ ፳–፴።
ᵃ ᵇ ኔፊ ፲፩፡ ፬።
ᵃ ᵇ ፲፣ ᵇ አልማ ፲፣፡ ፴።

ናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፣ እንዲህም ይላሉ፥ ወንድሞቼ፣ እነሆ እንዲህ ብዬ እና ገራችኋለሁ፣ ለደስታችን እንዴት ታላቅ ምክንያት አለን፤ ከዛራሔምላ ምድር [ሀ]በጀ መርን ጊዜ እግዚአብሔር ታላቅ በረከትን ሊሰጠን እንደሚችል መገመት እንችላለን?

፪ እናም አሁን፣ እርሱ ምን ዓይነት ታላቅ በረከት በእኛ ላይ አድርጓል? ብዬ እጠይቃ ችኋለሁ፣ ይህንን ለመናገርስ ትችላላችሁን?

፫ እነሆ፣ እኔ እመልስላችኋለሁ፤ ወን ድሞቻችን፣ ላማናውያን በጨለማ ነበሩ፤ አዎን፣ እንዲያውም በጨለማው ገደል፤ ነገር ግን እነሆ፣ [ለ]ስንቶቹ ናቸው ድንቁን የእግዚአብሔር ብርሃን የተመለከቱት! እናም ይህንን ታላቅ ስራም ለመፈፀም በእ ግዚአብሔር እጅ [ሐ]መሳሪያ መሆናችን፣ ይህ በእኛ ላይ የወረደው በረከት ነው።

፬ እነሆ፣ [መ]ሺዎቹም ተደሰቱ፣ እናም ወደ እግዚአብሔር በረትም መጡ።

፭ እነሆ፣ [ሠ]እርሻው ተዘጋጅቶ ነበር፣ እናም እናንተ [ረ]ስላጨዳችሁና፣ በጉልበ ታችሁ ስለሰበሰባችሁ፣ አዎን፣ ቀኑን ሁሉ ስለሰራችሁ የተባረካችሁ ናችሁ፤ እናም [ሰ]የነዶዎቻችሁን ቁጥር ተመልከቱ! እናም እንዳይባክኑ በየጎተራዎቹ ይሰበሰባሉ።

፮ አዎን፣ እነርሱም በመጨረሻው ቀን በውሽንፍሩ አይመቱም፤ አዎን፣ [ሀ]በአ ውሎ ንፋሱም አይበታተኑም፤ ነገር ግን ውሽንፍሩ ሲመጣ ሁሉም በቦታቸው በአ ንድ ላይ ይሰበሰባሉ፣ ውሽንፍሩም ዘልቆ ሊገባ አይቻለውም፤ አዎን፣ በሃያሉ ነፋስ ጠላታቸው ሊወስዳቸው ወደሚፈልግበ ትም የትኛውም ቦታ ቢሆን አይገፉም።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ እነርሱ [ለ]በአውድማው ጊታ እጅ ናቸው፣ እናም የእርሱ ናቸው፤ እርሱም በመጨረሻው ቀን [ሐ]ያስነሳቸዋል።

፰ የአምላካችን ስም የተባረከ ይሁን፤ [መ]በመዝሙር እናወድሰው፤ አዎን ለቅዱስ ስሙ [ሠ]ምስጋና እናቅርብ፤ ምክንያቱም እርሱ ለዘለዓለም ፅድቅን አድርጓልና።

፱ ከዛራሔምላ ምድር ባንመጣ ኖሮ፣ እነዚህ የተወደዱ ወንድሞቻችን፣ እኛንም እጅግ የሚወዱን፣ ለእኛ ያላቸው [ረ]ጥላቻ የከፋ ይሆን ነበር፣ አዎን እናም ደግሞ እነ ርሱ ለእግዚአብሔር ባዕዳን በሆኑ ነበር።

፲ እናም እንዲህ ሆነ አሞን እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ወንድሙ አሮን እንዲህ በማለት ወቀሰው፥ አሞን ደስታህ ወደኩ ራት ይወስድሃል ብዬ እፈራለሁ።

፲፩ ነገር ግን አሞን እርሱን እንዲህ አለው፥ በራሴ ጉልበት እንዲሁም በጥ በቤ [ሀ]አልኮራም፤ ነገር ግን እነሆ፣ [ለ]ደስ ታዬ ሙሉ ነው፣ አዎን፣ ልቤ በደስታ ይሞ ላል፣ እናም በአምላኬ ሐሴት አደርጋለሁ።

፲፪ አዎን፣ እኔ ምንም እንዳልሆንኩ አው ቃለሁ፤ ጉልበቴን በተመለከተ ደካማ ነኝ፤ ስለዚህ በራሴ [ሀ]አልኮራም፣ ነገር ግን በአ ምላኬ እኮራለሁ፣ ምክንያቱም በእርሱ [ለ]ኃይል ሁሉንም ነገር ማድረግ እችላለሁና፤ አዎን፣ እነሆ፣ በዚህ ምድር ብዙ አስደናቂ ተዓምራትን አድርገናል፣ ለዚህም ስሙን ለዘለዓለም እናወድሳለን።

፲፫ እነሆ፣ ስንት ሺህ ወንድሞቻችንን ነው እግዚአብሔር [ሀ]ከሲኦል እስራት የፈታው፣ እናም [ለ]የቤዛነትን ፍቅር እንዲዘምሩ ተደ ረጉ፣ እናም ለዚህም ምክንያቱ በውስጣችን ባለው በቃሉ ኃይል የተነሳ ነበር፣ ስለዚህ ለመደሰትስ ታላቅ ምክንያት አይኖረንምን?

፳፯ ፩ *ሀ* ሞዛያ ፳፰፡ ፱፤
አልማ ፲፯፡ ፯–፲፩።
፫ *ሀ* አልማ ፳፫፡ ፳–፲፫።
ለ ፪ ቆሮ. ፬፡ ፭፤
ሞዛያ ፳፫፡ ፲።
፬ *ሀ* አልማ ፳፫፡ ፭።
፭ *ሀ* ዮሐ. ፬፡ ፴፭–፴፯፤
ት.እና ቃ. ፬፡ ፬።
ለ ኢዩ. ፫፡ ፲፫።
ሐ ት.እና ቃ. ፴፫፡ ፯–፲፩፤
ሮ፭፡ ፪፤ ፭።
፯ *ሀ* ሔስ. ፭፡ ፲፪፤
፫ ኔፊ ፲፡ ፳፬–፳፯።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መከር።
ለ ሞዛያ ፳፫፡ ፳፪፤
አልማ ፴፯፡ ፳፳።
፳ *ሀ* ት.እና ቃ. ፳፭፡ ፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፴ *ሀ* ሞዛያ ፳፳፡ ፭–፪።
፲፩ *ሀ* ፪ ቆሮ. ፯፡ ፲፡
ለ ት.እና ቃ. ፲፳፡ ፲፡–፲፯።
ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፪ *ሀ* ኤር. ፱፡ ፳፬፤ አልማ ፳፱፡ ፱።
ለ መዝ. ፲፳፡ ፴፪–፴፣
ፊልጵ. ፬፡ ፲፫፤
፩ ኔፊ ፲፯፡ ፫።
፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሲያል።
ለ አልማ ፭፡ ፳፯።

፲፬ አዎን፣ ልዑል እግዚአብሔር በመ ሆኑ እርሱን ለዘለዓለም ለማወደስ ምክን ያት አለን፣ እናም ወንድሞቻችንን ከሲኦል ᵐሰንሰለት አስለቅቋልና።

፲፭ አዎን፣ እነርሱም በዘለአለማዊው ጨለማና ጥፋት ተከበው ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ወደ ዘለአለማዊው ᵐብርሃን፣ አዎን፣ ወደ ዘለአለማዊው ደህንነት አመጣቸው፤ እናም ወደር በሌለው ፍቅሩም ተከበዋል፤ አዎን እናም ይህን ታላቅና ድንቅ ስራ በመ ስራታችን በእጆቹ መሳሪያ ሆነን ነበር።

፲፮ ስለዚህ፣ እኛ ᵐእንደነቃለን፤ አዎን በጌታ ᵃእንደነቃለን፤ አዎን፣ ደስታችን ሙሉ በመሆኑ ሐሴት እናደርጋለን፤ አዎን አምላካችንን ለዘለዓለም እናወድሳለን። እነሆ፣ በጌታ ከመጠን በላይ ለመደነቅ የሚ ችል ማን ነው? አዎን፣ ስለታላቁ ኃይሉና፣ ᵃᵃስለምህረቱ፣ እናም ለሰው ልጆች ስላለው ፅናት አብዝቶ መናገር የሚችል ማን ነው? እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ ከተሰማኝ ጥቂቱን ለመናገር አልችልም።

፲፯ አምላካችን ከአሰቃቂው ከኃጢያትና ከተበላሸው ሁኔታችን ሲያስለቅቀን እንደ ዚህ መሃሪ እንደሚሆንልን ማን ለመገመት ይቻለዋል?

፲፰ እነሆ፣ በቁጣም ቢሆን ቤተክርስቲ ያኗን በኃይል በማስፈራራት ᵐለማጥፋት ሄድን።

፲፱ አቤቱ እንግዲህ፣ ወደአሰቃቂው ጥፋት ለምን አልተወንም፣ አዎን፣ የፍ ርዱ ጎራዴስ በእኛ ላይ እንዲወድቅ፣ እናም ወደዘለዓለማዊው ጥፋት እንዲጥለን ለምን አላደረገም?

፳ አቤቱ ይህም ሀሣብ ነፍሴን እንድት ኮበልል አድርጓት ነበር፤ እነሆ፣ እግዚአ ብሔር ፍርዱን በእኛ ላይ አላደረገም፣ ነገር ግን በታላቁ ምህረቱ ᵐከዘለዓለማዊው ሞትና ስቃይ አሳልፎን፣ እንዲሁም ወደ ነፍሳችን ደህንነት አምጥቶናል።

፳፩ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ እነ ዚህን ነገሮች የሚያውቅ ᵐተፈጥሯዊው ሰው ማን ነው? ንስሃ ከገባው በስተቀር እነዚህን ነገሮች ᵃየሚያውቅ ማንም የለም እላችኋ ለሁ።

፳፪ አዎን፣ ᵐንስሃ ለሚገቡ፣ ᵃእምነትን ለሚለማመደውና፣ መልካምን ለሚሰ ራው፣ እንዲሁም ሳያቋርጡ ለሚፀልየው፣ ለእንደእነዚህ ዓይነቶቹ ᵃᵃየእግዚአብሔርን ሚስጥር እንዲያውቁ ይሰጣቸዋል፤ አዎን፣ ለእንደነዚህ አይነቶቹ ተገልፀው የማያው ቁት ነገሮች እንዲገለፁላቸው ይሰጣቸዋል፤ አዎን እናም ለእነዚህ በሺህ የሚቆጠሩትን ነፍሳት ለንስሃ እንዲያመጡ ይሰጣቸዋል፣ እኛም ወንድሞቻችንን ለንስሃ እንድናመ ጣቸው እንደተሠጠን እንዲሁ ይሆናል።

፳፫ እናም ወንድሞቼ በዛራሔምላ ምድር ላሉት ወንድሞቻችን ወደኔፊ ምድር ለወን ድሞቻችን ለላማናውያን ለማስተማር እንሄ ዳለን እንዳልናቸው፣ እናም በማሾፍ እንደ ሳቁብን ታስታውሳላችሁን?

፳፬ እንዲህ ብለውናልና፥ ላማናውያ ንን እውነትን ወደማወቅ ማምጣት እንደ ሚቻላችሁ ትገምታላችሁን? እንደ ᵐአን ገተ ደንዳና ህዝቦች እንደነበሩት፤ በደም መፍሰስ ልባቸው እንደተደሰተው፤ ጊዜያ ቸውንም በክፋት እንዳሳለፉት፣ አቅጣጫ ቸውም ከመጀመሪያው ጀምሮ ሕጉን እን ደሚተላለፉት የሆነውን ላማናውያንን የአ ባቶቻቸው ᵃወግ ትክክል እንዳልነበር ለማ ሳመን ይቻለናል ብላችሁ ትገምታላችሁን? አሁን ወንድሞቼ ይህ የእነርሱ አነጋገር እን ደሆነ አስታውሱ።

፲፬ ᵐ አልማ ፲፪፡፲፭።
፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፲፮ ᵐ ሮሜ ፲፭፡፲፯፣
ᵃ ፪ ቆሮ. ፭፡፴፩።
ᵃᵃ ፪ ቆሮ. ፣ ፡ ፲፭–፲፰፣
ት.እና ቃ. ፫፯፡፰፩።
ᵃᵃᵃ መዝ. ፴፯፡፭–፮።
፲፰ ᵐ ሞዛያ ፳፯፡፳–፲።
፳ ᵐ ᵃ ኔፊ ፭፡፲፫፣
ሌለ. ፫፡፳፱–፴።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
ᵃ ፭ ቆሮ. ፪፡፱–፲፮፣
ያዕቆ. ፬፡ ፰።
፳፪ ᵐ አልማ ፴፮፡፬–፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፳፫ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡፳፱።
ᵃ ሞዛያ ፣ ፡ ፲፭–፲፯።

፳፭ እናም በተጨማሪ እንዲህ አሉ፡ እነ ርሱንና ክፋታቸውን ከምድሪቱ እንድና ጠፋ፣ እኛንም እንዳይወሩን እናም እንዳ ያጠፉን መሳሪያዎቻችንን በእነርሱ ላይ እን ታጠቅ።

፳፮ ነገር ግን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ ወደ ምድረበዳው የመጣነው ወን ድሞቻችንን ለማጥፋት ባለ ዓላማ አይደ ለም፣ ነገር ግን ጥቂት ነፍሳትን ለማዳን ባለ ዓላማ ነው።

፳፯ እናም ልባችን በተጨነቀ ጊዜና፣ ወደ ኋላችን ለመመለስ በተዘጋጀን ጊዜ፣ እነሆ፣ ጌታ [a]አፅናናን፣ እናም እንዲህ አለን፡ በወ ንድሞቻችሁ በላማናውያን መካከል ሂዱና፣ [b]ስቃያችሁን [c]በትዕግስት ያዙት፣ እናም መልካም ውጤትን እንድታገኙ አደርጋ ችኋለሁ።

፳፰ እናም አሁን እነሆ፣ እኛ መጥተና ልና፣ ከእነርሱ መካከል ሆነናል፤ እናም በስቃያችን ትዕግስተኞች ነበርንም፣ በማ ንኛውም የህይወት ውጣውረዶች ተሰቃ ይተናልም፤ አዎን፣ የዓለምን ምህረት ላይ ተስፋ በማድረግ ከቤት ወደቤት ተጉዘ ናል—በዓለም ምህረት ብቻ ሳይሆን በእ ግዚአብሔርም ምህረት ተስፋ አድርገናል።

፳፱ እናም በየቤቶቻቸው ገባንና፣ አስተ ማርናቸውም፣ በጎዳናዎቻቸው ላይ አስ ተማርናቸውም፤ አዎን፣ በኮረብታዎቻቸ ውም ላይ አስተማርናቸው፤ እናም፣ በቤ ተመቅደሶቻቸውና በምኩራባቸው ገባንም፣ አስተማርናቸውም፤ ተባረርንና፣ ተሳለቁ ብንም፣ ተፉብንም፣ ፈታችንንም መቱት፤ እናም በድንጋይ ተወገርንና ተወስደን በጠ ንካራ ገምዶች ታሰርን፣ ወደ ወህኒ ቤት ተጣልንም፤ እናም በእግዚአብሔር ኃይ ልና ጥበብ በድጋሚ ተለቀቅን።

፴ እናም በሁሉም ዓይነት ስቃይ ተሰቃ ይተናል፣ እናም ይህ ሁሉ የሆነውም ምና ልባት ጥቂት ነፍሳትን የምናድንበት መን ገድ እንድንሆን ነበር፤ እናም ምናልባት ጥቂቶችን ለማዳን ምክንያት ለመሆን ከቻ ልን [d]ደስታችን ሙሉ ይሆናል ብለን ገም ተን ነበር።

፴፩ እናም እነሆ፣ የስራችንን ፍሬ መመ ልከት እንችላለን፤ እናም እነርሱ ጥቂት ናቸውን? እኔ ግን አይደሉም እላችኋለሁ፤ እነርሱ [e]ብዙ ናቸው፤ አዎን ለወንድሞቻ ቸውና ደግሞ ለእኛ ባላቸው ፍቅር የተነሳ ከልባቸው መሆኑን እንመሰክራለን።

፴፪ እነሆም የጠላቶቻቸውን ነፍስ እንኳን ከማጥፋት ህይወታቸውን [f]መስዋዕት ማድ ረጉ ይሻላቸዋል፤ እናም ለወንድሞቻቸው ባላቸው ፍቅር የተነሳ የጦር መሳሪያዎቻ ቸውን በምድር ውስጥ በጥልቅ [g]ቀበሩት።

፴፫ እናም አሁን እንዲህ እላችኋለሁ፣ በምድሪቱ ሁሉ እንደዚህ ያለ ታላቅ ፍቅር አለን? እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በኔፋ ውያን መካከልም እንኳን የለም።

መቀደስ፣ ቅዱስ ማድረግ፣ ወይም ጻድቅ መሆን። የቅድስና ህግ ወንዶች እና ሴቶች ጊዜአ ቸው፣ ችሎታቸውን፣ እና የንብረት ሀብታቸውን የእግዚአብሔር መንግስትን ለመመስረትና ለመገ ንባት በምርጫ የሚቀድሱበት መለኮታዊ መመ ሪያ ነው።

ዛሬ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ቅዱስ አድርጉ፣ **ዘፀአ.** ፴፪፡፡፳፱።

የሚያምኑት ሁሉ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት ያዙ፣ **የሐዋ.** ፪፡፡፴፬–፴፭።

ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአቸው፣ ስለዚህ ድሃና ሃብታም አልነበራቸውም፣ ፬ ኔፊ ፩፡፡፣።

ጌታ የቅድስና መሰረታዊ መመሪያን ገለጸ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፡፴–፴፱ (ት. እና ቃ. ፶፩፡፡፪–፣፱፣ ፶፯፡፡፴፭–፴፯)። አንድ ሰው ከሌላ በላይ ንብረት አይኑረው፣ ት. እና ቃ. ፵፱፡፡፳። እያንዳንዱ ሰው በቤተሰቡ መሰረት በድርሻው እኩል ይሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፡፣። ቅዱሳን በሰማያዊና በምድራዊ ነገሮች በእኩል እንዲተሳሰሩ ዘንድ ስነስርዓት ተመ ስርቶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፡፬–፭። እያንዳንዱ ሰው በሚፈልገውና በሚያስፈልገው መሰረት እኩል ይገባኛል አለው፣ ት. እና ቃ. ፲፪፡፡፣–፲፱። ፅዮን በሰለስቲያል ህግ መሰረታዊ መርሆች ብቻ መገን ባት ትችላለች፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፡፭።

፲፯ የሌኖክ ህዝቦች የአንድ ልብ እና የአንድ አእ ምሮ ስለነበሩ፣ እና በጽድቅ ስለኖሩ፣ እና በመካከ ላቸውም ማንም ድሀ አልነበረም፣ **ሙሴ** ፣፡፡፲፯።

መቃብር። ደግምም ትንሳኤ ተመልከቱ

የምድራዊ ሰውነት መቀበሪያ ቦታ። በኃጢያት ክፍያ ምክንያት፣ እያንዳንዱ ሰው ከመቃብር በት ንሳኤ ይነሳል።

ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ፣ መቃብሮች ተከ ፈቱ እና ብዙ ሰውነቶች ተነሱ፣ **ማቴ.** ፳፯፡፡፶፪–፶፫ (፫ ኔፊ ፳፫፡፡፱–፣፫)። ሲኦል ሆይ፣ ድል መንሣትህ የት አለ፣ ፩ ቆሮ. ፣፭፡፡፶፭።

መቃብርም የያዘቻቸውን አካላት ማስረከብ አለ ባት፣ ፪ ኔፊ ፱፡፡፣፭–፣፫።

በመቃብራቸው የሚያነቀላፉትም ይመጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፡፣–፣፯። የማጥመቂያም ገንዳ የመቃብር ምሳሌ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፡፣–፣፫።

መቆጠር። ደግምም ማክበር፤ ክብር ተመልከቱ

ሰውን ወይም አንድ ነገርን፣ በተለይ በወንጌል አስተያየት፣ ብቁነት እና ዋጋ እንዳለው መመል ከት።

ከሰውም የተጠላ ነው፣ እኛም አላከበርነውም፣ **ኢሳ.** ፶፣፡፡፣–፬።

በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኵሰት ነው፣ **ሉቃ.** ፣፣፯፡፡፣፭። እያንዳንዱ ባልን ጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቀሥ ጠር፣ **ፊልጵ.** ፪፡፡፫።

ጌታ ሁሉንም ሕዝብ በአንድ ዐይን ይመለከታል፣ ፩ ኔፊ ፣፯፡፡፴፭። እያንዳንዱ ሰው ጎረቤቱን እን ደራሱ ያክብር ዘንድ ጥብቅ ትዕዛዝ ነበር፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡፬ (ት. እና ቃ. ፴፯፡፡፳፯–፳፭)።

በሰላም ቀናቸው ምክሬን ትንሽ ዋጋ እንዳለው ተመለከቱት፣ ት. እና ቃ. ፣፭፡፡፳።

መበለት። ባል የሞተባት *ተመልከቱ*

መበርታት፣ ብርቱነት። ደግምም እምነት፣ *ማመን፤ ፍርሀት ተመልከቱ*

በልዩም ትክክለኛውን ለማድረግ አለመፍራት።

ጽኑ፡ አይዞአችሁ፣ **ዘዳግ.** ፴፩፡፡፣ (ኢ.ያ. ፩፡፡፣–፣)። የተጻፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ፣ **ኢ.ያ.** ፳፣፡፡፣።

እግዚአብሔር የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም፣ ፪ ጢሞ. ፩፡፡፣።

ይህን ሲሰማ ልቡ በረታ፣ **አልማ** ፣፭፡፡፬ (አልማ ፳፪፡፡፩)። የሔለማን ልጆች በድፍረትም ጀግኖች ነበሩ፣ **አልማ** ፴፣፡፡፳–፳፩። እንዲህ ያለን ታላቅ ድፍረትን በጭራሽ አላየሁም፣ **አልማ** ፴፣፡፡፴፭።

በርቱ፣ ወንድሞች፣ እና ወደ ድል ሂዱ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፡፳፪።

መበተን። እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል *ተመልከቱ*

መበደል

መለኮታዊ ህግን መተላለፍ፣ ኃጢያት መስራት፣ ወይም ችግር ወይም ጉዳት እንዲገኝ ማድረግ ነው፤ ደግሞም ማስከፋት ወይም ማናደድ ነው።

የተበደለ ወንድም እንደ ጸናች ከተማ ጽኑ ነው፣ ምሳ. ፲፰፡፲፱።

ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፣ ማቴ. ፭፡፳፱። ከእነዚህ ከታናናሾቹ አን ዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአ ንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር፣ ማቴ. ፲፰፡፮ (ት. እና ቃ. ፱፳፭፡፲፱–፳፪)።

ወንድሞቻችሁ ወይም እህቶቻችሁ ቢያስቀይሟ ችሁ፣ ከተናገዘ ወይም ከተናገዘችም ትታረቃላ ችሁ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፹፰። የእርሱ እጅ እን ዳለበት ከማይመሰክሩ እና ትእዛዙን ከማያከብሩ በቀር፣ በምንም ሰው እግዚአብሔርን አያስቀይመ ውም፣ ወይም በማንም ላይ ቁጣው አይቀጣጠልም፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፳፭።

መባህ። በኩራት *ተመልከቱ*

መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት። *ደግምም ህግ፣ ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፣ አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት፣ የፓትሪያርክ በረከቶች፣ ጸጋ ተመልከቱ*

መለኮታዊ ድጋፍን ለአንድ ሰው መስጠት። ለእውነተኛ ደስታ፣ ለደህንነት፣ ወይም ለብል ፅግና ተጨማሪ ምክንያት የሚሆነው ማንኛውም ነገር በረከት ነው።

በረከቶች ሁሉ በዘለአለማዊ ህግጋት ላይ የተመ ሰረቱ ናቸው (ት. እና ቃ. ፲፬፡፳–፳፩)። እግዚአ ብሔር ልጆቹ በእዚህ ህይወት ደስታን እንዲያገኙ እልስሚፈልግ (፪ ኔፊ ፪፡፳፭)፣ ለትእዛዛቱ ታዛ ዥነታቸው ውጤታ (ት. እና ቃ. ፹፪፡፲)፣ ለጸ ሎት መልስ ወይም ለክህነት ስልጣን ስነስርዓት (ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፯፣ ፲፯፡፳፭–፳፯)፣ ወይም በጸጋው በኩል (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫) በረከቶችን ይሰ ጣቸዋል።

ክርስቶስ ስለመባረክ የተናገራቸው አረፍት ነገ ሮች ታዋቂ የሆኑ ስለብሩክነት መግለጫ የተዘረዘረ ነው (ማቴ. ፭፡፩–፲፪፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፲፪)።

አጠቃላይ፣ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባ ርክሃለሁ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡፪–፫ (፩ ኔፊ ፲፭፡፲፰፣ አብር. ፪፡፱–፲፩)። በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው፣ ምሳ. ፲፡፮። የታመነ ሰው እጅግ ይባረካል፣ ምሳ. ፳፰፡፳። ጌታ የሰማይ መስኮትን ይከፍታል እና በረ ከቶችን ያፈስልሀል፣ ሚል. ፫፡፣ ፲ (፫ ኔፊ ፳፬፡፣)።

ክርስቶስ ስለተባረኩ የተናገራቸው አረፍት ነገ ሮች የበረከቶች የተስፋ ቃል ይሰጣሉ፣ ማቴ. ፭፡፩–፲፪ (፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፲፪)። ወደ በጉ ሰርግ እራት የተ ጠሩ ብፁዓን ናቸው፣ ራዕ. ፲፱፡፱።

ጻድቅ የሆነ በእግዚአብሔር የተወደደ ነው፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፩ (ሞዛያ ፲፡፲፫)። ካዳመጣችሁ፣ በረከት እተውላችኋለሁ፣ ፪ ኔፊ ፩፡፳፰። ለእና ንተ አንድ አይነት በረከት እተውላችኋላሁ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፱። ወዲያው ባረካችሁ፣ ሞዛያ ፪፡፳፩። በእርሱ ላይ እምነታቸውን ለሚያሳርፉ ጌታ ባረካቸውም አበለጸጋቸውም፣ ሔሌ. ፲፪፡፩።

ስራዬን ለማምጣት እርዳታ ስጥ፣ እናም ትባረካ ለህ፣ ት. እና ቃ. ፮፡፱። ሁልጊዜም ጸልይ፣ እናም በረከትህ ታላቅ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፰። ተጠመቅ፣ እናም መንፈሴን እንዲሁም ከምታ ውቀው በላይ ታላቅ የሆነን በረከት ትቀበላለህ፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡፲። ከብዙ ፈተናዎች በኋላ በረከ ቶች መጡ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፱። ሰዎች ትእዛዛትን አያከብሩም፣ እመነጥቃለሁ እና በረከቶችን አይ ቀበሉም፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፴፱። አብ ያዘጋጀላ ችሁ በረከት እንዴት ታላቅ እንደሆነ አልገባችሁም፣ ት. እና ቃ. ፷፰፡፲፯። በሊቀ ካህናት በኩል በቤተክ ርስትያኗ ላይ የስነስርዓቶች መከናወን እና በረከቶች መጡ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፭–፴፮። ሁሉም በረከ ቶች የሚሞረከዙበት ህግ አለ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፳። በእጆቹ በረከቶችን የሚያገኙ በህግጋቱ ይኖራሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፭። በረከቶች ጌታን ለሚወዱት ተጠብቀው ተይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፹፪።

አብርሐም የአባቶችን በረከቶችና እነዚህን የማ ስተዳደር መብት ፈለገ፣ አብር. ፩፡፪።

ልጆችን መባረክ፣ አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው፣ ማር. ፣ ፲፮።

ህጻናቶቻቸውን አንድ በአንድ ወሰደ፣ እናም ባረ ካቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፩።

ሽማግሌዎች ልጆችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይባርኩ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፷።

መብት። *ደግምም* ባርነት፣ ነጻ ምርጫ፣ ነጻ፣ *ነጻነት ተመልከቱ*

በነጻነት ለመስራት እና ለማሰብ የሚኖር ችሎታ። በወንጌል መሰረታዊ መርሆች ታዛዥ መሆን ከኃጢ ያት መንፈሳዊ ባርነት ሰውን ነጻ ያደርጋል (ዮሐ. ፰፡፴፩–፴፮)።

ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና አስፍቼ እሄዳለሁ፣ መዝ. ፻፲፱፡፴፭።

የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ፣ ፪ ቆሮ. ፫፡፣ ፲፯። ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባ ርነት ቀንበር አትያዙ፣ ገላ. ፭፡፩ (ት. እና ቃ. ፹፰፡፹፱)።

ሰዎች ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመ ምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯። ይህ ምድር የነ

ፃነት ምድር ይሆናል፣ ᎦᏬᎤ ᏥᏅᏏ። ሞሮኒ በኔፋ ውያን መካከል የነፃነት ዓርማው እንዲሰቀል አደ ረገ፣ *አልማ* ᏯᏆᏂᏥᏍᏆᏂ።

ጌታ እና አገልጋዮቹ ለታሰሩት ነጻነትን አወጁ፣ ት. እና ቃ. ᏧᏍᏆᏍᏥᏍᏆᏍ፣ ᏍᏆᏅᏅ፣ ᏯᏅᏑ።

መተርጎም

በአንድ ቋንቋ የተሰጠውን ትርጉም እና ሀሳብ በሌላ ቋንቋ በእኩል ሁኔታ መግለፅ (ሞዛያ ᏍᏥᏍᏥ–ᏍᏥᏂ፣ እ.አ. ᏅᏍᏥᏍᏥ)። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ይህም እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ይጠቆማል (አልማ ᏫᏍᏅᏅᏂ፣ ት. እና ቃ. ᏥᏂ፣ ᏫᏍᏂ–ᏫᏍ)። አንዳ ንዴም ይህ በቋንቋ የተተረጎመውን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ማለትም ወይም የጠፉትን ቃላት በዳ ግም መመለስም ሊሆን ይችላል (ት. እና ቃ. ᏯᏅᏂᏍᏥᏍ–ᏍᏥᏅᏂ)። ጆሴፍ ስሚዝ የንጉስ ጄምስ መፅ ሐፍ ቅዱስን በመነሳሳት እንዲተረጉም ታዝዞ ነበር (ት. እና ቃ. ᏯᏅᏑᏍᏯᏂᏍ፣ ᏫᏅᏂᏍᏥᏅᏂᏍ)።

ጆሴፍ ስሚዝ በእግዚአብሔር ምህረት፣ በእ ግዚአብሔር ኃይል መጽሐፈ ሞርሞንን የመተር ጎም ኃይል ነበረው፣ ት. እና ቃ. ᏅᏍᏅᏅᏫᏫ። የመተ ርጎም ስጦታ አለህ፣ ት. እና ቃ. ᏅᏍᏫᏫ። ከእኔ የም ትፈልግ ከሆነ እንድትተረጉም ስጦታን እሰጥሃ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ᏂᏍᏅᏅᏂ። እግዚአብሔር ለጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ለመተርጎም ከላይ ሀይ ልን ሰጠው፣ ት. እና ቃ. ᏅᏍᏍᏥᏍ።

በኡሪምና ቱሚም ጥቅም አንዳንዶቹን ፊደ ኖች ተረጎመ፣ ጆ.ስ.—ታ. ᏅᏍᏅᏅᏑ (ሞዛያ ᏍᏥᏍᏥ፣ ᏅᏍᏥᏍᏥᏍᏥᏍ)።

መተኛት

ሰው የማይንቀሳቀስ ወይም ሩሁን የሳተበት የእረ ፍት ሁኔታ። ጌታ ቅዱሳኑን ከሚያስፈልጋቸው በላይ እንዳይተኙ መክሯል (ት. እና ቃ. ᏯᏍᏥᏍ᏶ᏍᏥᏅᏅᏫ)። *መተኛት የመንፈስ ሞት* (ᏅᏅᏂᏥᏍᏆᏂ ᏑᏅᏅ ᏅᏍᏥᏍᏥ) ወይም የስጋዊ ሞት (ሞር. ᏫᏍᏥᏍᏥ) ምልክ ትም ሊሆን ይችላል።

መታመን። *ደግሞም ልበ ሙሉነት፣ እምነት፣ ማመን ተመልከቱ*

በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ላይ መመካት ወይም እምነትን መጣል። በመንፈሳዊ ነገሮች፣ ማመን በእግዚአብሔር እና በመንፈሱ መመካት ነው።

ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃ ለሁ፣ ኢዮብ ᏥᏍᏥᏍᏥᏅᏂ። በፍጹም ልብህ በእግዚአ ብሔር ታመን፣ ምሳ. ᏍᏥᏍᏅᏂ። እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን አገልጋዮች አዳነ፣ ዳን. ᏍᏥᏍᏫᏫᏂ–ᏅᏍᏅᏂ።

ለዘለዓለም በአንተ እታመናለሁ፣ ᏑᏅᏅᏫᏫᏂᏫᏫᏂ። ተደሰቱ፣ እናም በእግዚአብሔር እምነታቸሁን አድርጉ፣ ሞዛያ ᏅᏍᏫᏫᏂ። እምነቱን በእርሱ ያደረገ በመጨረሻው ቀን ከፍ ይላል፣ ሞዛያ ᏅᏍᏥᏍᏥᏅᏅᏑᏂ። እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ያደረጉ ሁሉ፣ በፈተናቸውይደገፋሉ፣ *አልማ* ᏯᏅᏂᏍᏥᏍᏅᏂ።

በስጋ ክንድ አትመካ፣ ት. እና ቃ. ᏅᏍᏫᏫᏂ። ወደ መልካም በሚመራው መንፈስ ላይ እምነትህን አድ ርግ፣ ት. እና ቃ. ᏥᏅᏍᏥᏍᏥᏑᏂ። በእኔ ይመን እናም ግራ አይጋባ፣ ት. እና ቃ. ᏫᏫᏫᏍᏥᏅᏂᏍ።

መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን

የብሉይ ኪዳን መፅሀፍ። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን የተነሳሳ ጽሁፍ አይ ደለም ብሎ አስተምሯል።

መነሳሳት። *ህያው ማድረግ ተመልከቱ*

መነሳሻ፣ መነሳሳት። *ደግሞም መንፈስ ቅዱስ፣ ራዕይ ተመልከቱ*

ለሰው በእግዚአብሔር የተሰጠው መኮታዊ አመ ራር። መነሳሳት ከመንፈስ የሚመጣው በተለያዩ መንገዶች ወደ ሰው አዕምሮና ልብ ነው።

ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ፣ ᏂᏅᏅᏥ ᏥᏍᏥᏍᏥᏍ

ቋንቋ ማን-ሁ) ብለው ጠሩት—ይህም “ምንድን ነው?” ማለት ነው—ምክያቱም ምን እንደሆነ አላ ወቁምና (ዘፀአ. ፲፮፡፲፭)። ደግሞም ይህ “የመላእ ክት ምግብ” እና “የሰማይ እንጀራ” ተብሎ ይታወ ቃል (መዝ. ፹፰፡፳፡፳፭፣ ዮሐ. ፮፡፴፩)። ይህም የህይወት እንጀራ የሚሆነው የክርስቶስ ምሳሌ ነበር (ዮሐ. ፮፡፴፩–፴፭)።

መናቅ። መጥላት፣ ጥላቻ *ተመልከቱ*

መናዘዝ። *ደግሞም መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፣ ይቅርታ ማድረግ ተመልከቱ*

ቅዱሳት መጻህፍት *መናዘዝን* በሁለት መንገዶች ተጠቅመውበታል። በሌላ አባባል፣ መናዘዝ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ መናዘዝ አይነት በአንድ ነገር የእራስን እምነት ሁኔታ መግለፅ ነው (ማቴ. ፲፡፴፪፣ ሮሜ ፲፡፱፣ ፩ ዮሐ. ፬፡፩–፫፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፡፲፬)።

መናዘዝ፣ እንደ ኃጢያት መናዘዝ አይነት፣ ለራስ ወንጀለኛነት ተቀባይ መሆን ማለት ነው። ሁሉም ሰው ኃጢያቶቻቸውን ሁሉ ለጌታ መናዘዝ እና የእርሱን ምህረት የማግኘት ሀላፊነት አላቸው (ት. እና ቃ. ፶፮፡፶፪–፶፫)። አስፈላጊም ሲሆን፣ ኃጢያቶች ለተሰራበት ወይም ለተሰራባቸው ሰዎች መናዘዝ ያስፈልጋል። ሀይለኛ ኃጢያቶች ለቤተክር ስቲያኗ ባለስልጣናት (በብዙም ጊዜ ለኤጲስ ቆጶስ) መናዘዝ ይገባል።

የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል፣ **ዘሌዋ.** ፭፡፭። ኃጢአታቸውንም ይናዘዛሉ፣ **ዘሌዋ.** ፳፮፡፵–፵፪። ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፡ ለእርሱም ተናዘዝ፣ **ኢያ.** ፯፡፲፱። ሰዎች ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር፣ **ማቴ.** ፫፡፭–፮። ኃጢያታቸውን የተናዘዙት ተላላፊዎች ይቅርታ ይሰጣቸዋል፣ **ሞዛያ** ፳፮፡፳፱። ኃጢያትህን ተናዘዝ አለበለዚያም ቅጣቶችን ትሰ ቃያለህ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፳። ንስሀ የሚገቡ ኃጢ ያቶቻቸውን ይናዘዛሉ እናም ይተዉአቸዋልም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፶፫። ጌታ ኃጢያቶችን በትሁት ልብ ለሚናዘዙት መሀሪ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡፪። ጌታ ለሚናዘዙና ይቅርታን ለሚጠይቁ ኃጢያቶችን ይቅርታ ያደርጋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፬፡፲። ፡

መንገድ። *ደግሞም መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ሰው የሚከተለው መንገድ ወይም አቅጣጫ። ኢየሱስ መንገዱ ነኝ አለ (ዮሐ. ፲፬፡፩–፮)።

በመንገዱም እንድትሄድ የእግዚአብሔርን ትእ ዛዝ ጠብቅ፣ ዘዳግ. ፭፡፲። ልጅን በሚሄድበት መን ገድ ምራው፣ ምሳ. ፳፪፡፮ (፪ ኔፊ ፱፡፳)። መን ገዴ ከመንገዳችሁ ከፍ ያለ ነው፣ ኢሳ. ፶፭፡፰–፱። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መን ገዱም የቀጠነ ነውና፣ **ማቴ.** ፯፡፲፫–፲፬ (፫ ኔፊ ፲፬፡፲፫–፲፭፣ ፳፯፡፲፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፳፪፡፳፭)። እግዚአብሔር ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፲፫።

ጌታ ያዘዛቸውን ትዕዛዛት የሚሟሉበትን መንገድ ካላዘጋጀ በቀር ለሰው ልጆች ትዕዛዛትን አይሰጥም፣ ፩ ኔፊ ፫፡፯ (፩ ኔፊ ፱፡፯፣ ፲፯፡፣ ፲፫)። በመግቢ ያው ካልሆነ በቀር ምንም ሌላ መንገድ የለም፣ ፪ ኔፊ ፱፡፶፩። በራሳችሁ ዘለዓለማዊውን ሞት ወይም የዘ ለዓለማዊውን ህይወት መንገድ እራሳችሁ ለመም ረጥ ነጻነት አላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፲፡፳፫። መንገዱ ይህ ነው፤ የተሰጠ ሌላ መንገድም ሆነ ስም የለምና፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፳፩ (ሞዛያ ፫፡፲፯፣ አልማ ፴፯፡፱፣ ሔለ. ፭፡፱)። እግዚአብሔርም በልጁ ስጦታም ይበ ልጥ የተመረጠውን መንገድ አዘጋጅቷል፣ **ኤተር** ፲፪፡፲፩ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፴፩)።

ሁልም ሰው በራሱ መንገድ ይጓዛል፣ **ት. እና ቃ.** ፩፡፲፮። ይህም በእኔ መንገድ መደረግ አለበት፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፲፮።

መንግስት። *ደግሞም ህገ መንግስት ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ፣ የጻድቅ መንግስት ይመሰርታል።

አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፱፡፮ (፪ ኔፊ ፲፱፡፮)።

እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር አስረክቡ፣ **ማቴ.** ፳፪፡፳፩ (ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፮)። ለባለ ሥልጣ ኖች ይገዛ፣ **ሮሜ** ፲፫፡፩ ለነገሥታትና ለመኳን ንትም ሁሉ ጸልይ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፩–፪ ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ ሁኑ፣ ቲቶ ፫፡፩ ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፣ ፩ ጴጥ. ፪፡፲፫–፲፰ የዓለም መንግሥት የክርስቶስ ትሆናለች፣ ራዕ. ፲፩፡፲፭።

ፃድቅ ሰው የእናንተ ንጉስ ይሁን፣ ሞዛያ ፳፫፡፳ በህዝቡም ድምፅ ጉዳያቸሁን ፈፅሙ፣ ሞዛያ ፳፱፡፳፯።

ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የእኛ ገዢ ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፩፡፱። የእግዚአብሔርን ህግጋትን የሚጠብቅ የምድርን ህግጋት የመጣስ ፍላጎት አይ ኖረውም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፳፩። ክፉው ሲያስተ ዳድር ህዝቡ ያዝናል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፱–፲። መን ግስቶች እግዚአብሔር ለሰው ጥቅም የመሰረታቸው ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፬፡፩–፭። ሰዎች መንግ ስቶች ለመቀበል እና ለመደገፍ ግዴታ አላቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፬፡፭።

፲፪ ለንጉሶች፣ ለፕሬዘደንቶች፣ ለመሪዎች፣ እናም ለዳኛዎች ታዛዦች በመሆን፣ በህግ በመ

ታዘዝ፣ በማክበርና በመደገፍ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፪።

መንፈሳዊ ሞት። ደግሞም ሲያል፤ ኩነኔ፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፤ የጥፋት ልጆች፤ ደህንነት፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ

ከእግዚአብሔር እና ከተፅዕኖው መለየት፤ ጻድቅን ከሚነኩ ነገሮች መሞት። ሉሲፈር እና ከሰማይ ሰራዊት አንድ ሶስተኛቹ ከሰማይ በሚወረወሩበት ጊዜ በመንፈስ ሞቱ (ት. እና ቃ. ፹፱፡-፹፯)።

መንፈሳዊ ሞት ወደ አለም የተዋወቀው በአዳም ውድቀት ምክንያት ነው (ሙሴ ፮፡፶፯)። ክፉ ሀሳቦች፣ ቃላት፣ እና ስራዎች ያላቸው ስጋዊ ሰዎች በምድር ላይ በህይወት እያሉ በመንፈስ የሞቱ ናቸው(፩ ጢሞ. ፭፡፮)። በኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል እና ለወንጌሉ መሰረታዊ መርሆችና ስነስርዓቶች ታዛዥ በመሆን፣ ወንዶች እና ሴቶች ከኃጢያት ንጹህ ለመሆንና መንፈሳዊ ሞትን ለማሸነፍ ይችላሉ።

መንፈሳዊ ሞት ደግሞም የስጋዊ ሰውነት ሞትን በመከተል ለደርስ ይችላል። ከሞት የተነሱ ሰዎች እና ዲያብሎስና መላእክቱ ይፈረድባቸዋል። በወንጌሉ ብርሀን እና እውነት ላይ በፈቃደኝነት የሚያምጹ በመንፈሳዊ ሞት ይሰቃያሉ። ይህ ሞት ብዙም ጊዜ ሁለተኛ ሞት ይባላል (አልማ ፲፪፡፲፯፤ ሔለ. ፲፩፡፲፯-፲፱፤ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴፯-፴፰)።

ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉ፤ መዝ. ፴፯፡፱።

ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው፣ ሮሜ ፰፡፮ (፪ ኔፊ ፱፡፴፱)። ምኞት ሰዎችን በፈተና እና በወጥመድም ያጠፋቸዋል፣ ፩ ጢሞ. ፮፡፱። ኃጢአት ሞትን ትወልዳለች፣ ያዕ. ፩፡፲፭። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም፣ ራዕ. ፪፡፲፩። ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፣ ራዕ. ፳፡፮፣ ፲፪-፲፬። ኃጢያተኞች ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፣ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው፣ ራዕ. ፳፩፡፰ (ት. እና ቃ. ፹፫፡፲፮-፲፰)።

ሰዎች ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመምረጥ፣ ወይም እንደዲያብሎስ ምርኮና ሀይል ምርኮንና ሞትን ለመምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯ (፪ ኔፊ ፲፡፳፫፣ አልማ ፳፱፡፮፣ ሔለ. ፲፩፡፴-፴፩)። እግዚአብሔር ከሞትና ከሲኦል የምናመልጥበት መንገድ አዘጋጅቷል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲። እናም የዲያብሎስ መልዕክተኛ በመሆን የሁለተኛው ሞት ከሆነው እሳትና ዲን ራሳችሁን እንዳትጥሉ ከሲያል ህመም ራሳችሁን ፍቱ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፩። ፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ነው፣ ሞዛያ ፫፡፲፱። በሁለተኛ ሞትም እንዳትሰቃዩ፣ ጌታ ንስሃን ይስጣችሁ፣ አልማ ፲፫፡፴። አልማ በዘለአለማዊው የሞት ሰንሰለት ተከብቦ ነበር፣ አልማ ፴፮፡፲፯። ኃጢያተኞች ጻድቅ ለሆኑት ነገሮች ይሞታሉ፣ አልማ ፴፡፳፯ (አልማ ፲፪፡፲፯)። ውድቀት በሰው ዘር በሙሉ የመንፈስ ሞትን አመጣ፣ አልማ ፴፪፡፱ (ሔለ. ፲፬፡፲፯-፲፰)።

አዳም ሲወድቅ፣ በመንፈስ ሟች ሆነ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴-፴፩፣ ፴፬።

መንፈሳዊ ስጦታ። ደግሞም ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት ተመልከቱ

በአጠቃላይ አስተሳሰብ፣ የእግዚአብሔር ሀይል ስጦታ። ብቁ የቤተክርስቲያኗ አባላት ዘለአለማዊነትን ለማግኘት የሚያስፈልጋቸውን መመሪያና የቅዱስ ክህነት ቃል ኪዳኖች በሚሰጣቸው በቤተመቅደስ ስነስርዓቶች በኩል የሀይል ስጦታን ይቀበላሉ። መንፈሳዊ ስጦታ ስለደህናነት አላማ መመሪያንም ይጨምራል።

በእዚያም ከላይ የኃይል መንፈሳዊ ስጦታም ይሰጣችኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፪፣ ፴፪ (ሉቃ. ፳፬፡፵፱፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፯)። ቤት ገንቡ፣ በዚህ ቤትም የመረጥኳቸውን ከላይ መንፈሳዊ ስጦታ ለመስጠት አቅጃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፰። ታላቅ መንፈሳዊ ስጦታ እና በረከት አዘጋጅቻለሁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፲፪፣ ፲፰፣ ፴፫። አገልጋዮቼ በተቀበሉት መንፈሳዊ ስጦታ ምክንያት የብዙዎች ልብ በታላቅ ይደሰታሉ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፣፡፱። ግርማ፣ ክብር፣ እና መንፈሳዊ ስጦታ፣ በቅዱስ ቤቴ ስነ ስርዓት የተሾሙ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፣፲፳፱፡፴፱። በአብ እንደ አሮን የተጠሩ በክህነት ስልጣን ቁልፎች ይበለፅጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፣፴፪፡፣፴፱።

መንፈሳዊ ጭለማ። ደግሞም ክፉ፣ ክፋት ተመልከቱ

ጥፋተኛነት ወይም ስለመንፈሳዊ ነገሮች አላዋቂነት።

ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ኢሳ. ፭፡፳ (፪ ኔፊ ፲፭፡፳)። ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፣ ኢሳ. ፷፡፪።

ኢየሱስ ብርሃኑም በጨለማና ተቀምጠው ላሉት ያበራል፣ ሉቃ. ፩፡፷፱። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፡ ጨለማም አላሸነፈውም፣ ዮሐ. ፩፡፭ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፣)። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ፣ ሮሜ ፣፲፡፡፲፪። ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፣ ኤፌ. ፭፡፣-፲፩።

ስላልጠየቃችሁ፣ ወይም ስላላንኳኳችሁ ነው፣ ስለሆነም፣ ወደ ብርሃኑ አልመጣችሁም፣ ነገር ግን በጨለማው ትጠፋላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፴፪፡፱። ሰይጣን የጨለማ ስራን ያሰራጫል፣ ሔለ. ፣፡፳-፴፩።

የጨለማ ሀይሎች በምድር ላይ ይሰራጫል፣ ት. እና ቃ. ፴፣፡፣ ፣፲፩-፲፪። አለም በሙሉ

በጨለማና በኃጢያት ስር ይቃሰታሉ፣ ት. እና ቃ. ፷፫፡ ፶፱–፶፩። ለክብሬ ዐይናችሁ ቀና ብትሆን፣ በእናንተም ምንም ጭለማ አይኖርም፣ ት. እና ቃ. ፷፫፡ ፷፯፡ ፷፯።

እንደዚህም የጭለማ ስራዎች በሰው ልጆች ሁሉ መካከል መሳካት ጀመረ፣ ሙሴ ፮፡ ፶፭።

መንፈስ። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ ስጋዊ ሞት፤ ትንሳኤ፤ ነፍስ ተመልከቱ*

ከምድራዊ ውልደት በፊት የነበረው፣ በስጋዊ ሰውነት ውስጥ በምድራዊ ህይወት ጊዜ የሚኖር፣ እናም ከሞት በኋላም እስከ ትንሳኤ ድረስ ተለይቶ የሚኖረው የህያው ሰው ክፍል። ሁሉም ህያው ነገሮች፣ የሰው ዘር፣ እንስሳት፣ እና ተክል፣ በምድር ላይ ምንም አይነት ህይወት ከመኖሩ በፊት መንፈሶች ነበሩ (ዘፍጥ. ፪፡ ፬–፭፤ ሙሴ ፫፡ ፬–፯)። የመንፈስ ሰውነት ከስጋ ሰውነት ጋር አንድ ይመስላሉ (፩ ኔፊ ፲፭፡ ፲፩፤ ኤተር ፫፡ ፲፭–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፷፯፡ ፪፤ ፲፯፱)። መንፈስ ንጥረ ነገር ነው፣ ነገር ግን ከምንም ንጥረ ነገር በላይ የጠራ እና ንጹህ ነው (ት. እና ቃ. ፲፴፩፡ ፯)።

በምድር ላይ ወደ ሟች ወላጆች ከመወለዳቸው በፊት ለሰማይ ወላጆች እንደ መንፈስ የተወለደው እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔር ወንድ ወይም ልጅ ነው (ዕብ. ፲፪፡ ፱)። በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ከስጋ እና አጥንት ሰውነት በተጨማሪ የማይሞት የመንፈስ ሰውነት አለው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ አንዳንዴ ትርጉም እንደሚሰጣቸው፣ መንፈስ እና ስጋዊ ሰውነት በአንድነት ነፍስን ይሰራሉ (ዘፍጥ. ፪፡ ፯፤ ት. እና ቃ. ፸፯፡ ፲፭፤ ሙሴ ፫፡ ፯፤ ፱፡ ፲፱፤ አብር. ፭፡ ፯)። መንፈስ ያለስጋዊ ሰውነት ለመኖር ይችላል፣ ነገር ግን ስጋዊ ሰውነት ያለመንፈስ ለመኖር አይችልም (ያዕ. ፪፡ ፳፮)። ስጋዊ ሞት የመንፈስ ከሰውነት መለየት ነው። በትንሳኤ ጊዜ፣ ከሁለት ታላቅ ልዩ ጋር፣ መንፈስ በሟች ነት እንደነበረው ምድራዊ የስጋ እና የአጥንት ሰውነት ጋር እንደገና አንድ ይሆናል፥ ሁለቱም እንደገና አይለያዩም፣ እና ስጋዊ ሰውነት ዘለአለማዊ እና ፍጹም ይሆናል (አልማ ፲፩፡ ፵፭፤ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፲፯–፲፯)።

በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም፣ ሉቃ. ፳፬፡ ፴፱። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፣ ሮሜ ፰፡ ፲፮። በሥጋችሁ፣ እናም በመንፈሳችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፣ ፩ ቆሮ. ፮፡ ፳።

ይህ ሰውነት መንፈሳዊው ሰውነቴ ነው፣ ኤተር ፫፡ ፲፮።

ሰው መንፈስ ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡ ፴፫። ክርስቶስ ለጻድቃን መንፈሶች በገነት አስተማረ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፳፯–፴ (፩ ጴጥ. ፫፡ ፲፰–፲፱)።

ወደ ምድር በውሃ፣ ደምና፣ መንፈስ ተወለድክ፣ ሙሴ ፮፡ ፶፱። መንፈስ ከሦኑት መካከል ቆሞ ነበር፣ አብር. ፫፡ ፳፫።

ክፉ መንፈሶች፣ ኢየሱስ ዲያብሎሶች አወጣ፣ ማር. ፩፡ ፳፯፣ ፴፬፣ ፴፱። አንተ ርኵስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ፣ ማር. ፭፡ ፪–፲፫።

እርኩስ መንፈስ ሰዎችን መፀለይ እንደሌለባቸው ያስተምራቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፴፪፡ ፰። ፣በኢየሱስ ስም ዲያብሎስን እንዲሁም እርኩስ መንፈስን አስወጥቷል፣ ፫ ኔፊ ፯፡ ፲፱።

ብዙ የሀሰት መንፈሶች አለምን በማታለል ሄደ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፡ ፪፣ ፴፭–፴፪። ጆሴፍ ስሚዝመንፈስ ከእግዚአብሔር ይሁን ወይም ከዲያብሎስ ለይቶ ለማወቅ የሚቻልበት ሶስት ዋና መንገዶችን ገልጿል፣ ት. እና ቃ. ፳፭፱።

መንፈስ ቅዱስ። *ደግሞም መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ ራዕይ፤ ቅዱስ የተስፋ መንፈስ፤ አፅናኝ፤ እግዚአብሔር፤ አምላክ፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፤ የርግብ መልእክት፤ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ ተመልከቱ*

የአምላክ ሶስተኛው አባል (፩ ዮሐ. ፭፡ ፯፤ ት. እና ቃ. ፳፡ ፳፰)። እርሱም የስጋ እና አጥንት ሰውነት የሌለው የመንፈስ ሰው ነው (ት. እና ቃ. ፲፴፡ ፳፭)። መንፈስ ቅዱስ በብዙ ጊዜ እንደ መንፈስ ወይም እንደ እግዚአብሔር መንፈስ ይጠቆማል።

መንፈስ ቅዱስ በደህንነት አላማ ውስጥ የተለያዩ አስፈላጊ ሀላፊነቶች አለው። (፩) ስለአብ እና ወልድ ምስክር ይሰጣል (፩ ቆሮ. ፲፪፡ ፫፤ ፣ ፣ ፣

መከራ ፳፯

ሐዋሪያት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ታዝዘዋል፣ **ማቴ.** ፳፰፡፲፱። መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ **ዮሐ.** ፲፬፡፳፮። ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፣ ፪ **ጴጥ.** ፩፡፳፩።

ኔፊ በመንፈስ ተመራ፣ ፩ **ኔፊ** ፬፡፮። የእግዚአብሔር ሚስጥር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለጥላቸዋል፣ ፩ **ኔፊ** ፲፡፲፯–፲፱። መንፈስ ቅዱስ ማድረግ ያለባችሁን ነገሮች ሁሉ ያሳያችኋል፣ ፪ **ኔፊ** ፴፪፡፭። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሁሉንም ነገር እውነታ ታውቁታላችሁ፣ **ሞሮኒ** ፣፡፭።

መንፈስ ቅዱስ በአዕምሮህ እና በልብህ ይነግር ሃል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፪። መንፈስ ወደ መልካም ይመራል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፲፪። መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፭፡፲፱። መንፈስ ቅዱስ የመንግስተ ሰማይን የሰላም ነገሮችን ያስተምራል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡፪ (**ት. እና ቃ.** ፴፱፡፯)። መንፈስን ካልተቀበላችሁ፣ አታስተምሩም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፲፡ መንፈስ ቅዱስ ስለአብ እና ስለወልድ ይመሰክራል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፲፯ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፫፣ ፣ ኔፊ ፲፭፡፴፪፣ ፴፭–፴፯)። ለአንዳንዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲያውቁ በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፯፡፲፣ በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሣት መጻህፍት ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፯፡፭። ለምትሉት ማንኛቸውም ነገሮች ሁሉ ምስክር ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ ይላካል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፡፳፡ መንፈስ ቅዱስም የሁልጊዜ ጓደኛህ ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፭፡፶፭–፶፯።

መከራ። ጭንቀት *ተመልከቱ*

መከር

አንዳንድ ጊዜ ቅዱስ መጻህፍቶች *መከር* ሰዎችን በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግስት ወደሆነችው ወደ ቤተክርስቲያኗ እንደ ማምጣት፣ ወይም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት አይነት ፍርድ ጊዜ እንደ ማምጣት ምሳሌአዊነት ይጠቀሙበታል።

መከሩ አልፎአል፡ በጋው ሄዶአል፡ እኛም አልዳንም፣ **ኤር.** ፰፡፳ (**ት. እና ቃ.** ፶፯፡፲፯)።

መከሩስ ብዙ ነው፡ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፣ **ማቴ.** ፱፡፴፯። መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፣ **ማቴ.** ፣፣፡፴፱። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል፣ **ገላ.** ፮፡፯–፱ (**ት. እና ቃ.** ፮፡፴፣)።

የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ ለመከር ዝግጁ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፬፡፬። መከሩ ያልፋል፣ እና መንፈሳችሁም አይድኑም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፭፡፪። የመከር ጊዜ መጥቷል፣ እና ቃሌም መፈጸም አለበት፣ **ት. እና ቃ.** ፻፩፡፳፬።

መኩራት። ኩራት *ተመልከቱ*

መክሊት

የጥንት የክብደት መለኪያ ወይም ታላቅ ዋጋ ያለው ገንዘብ። ይህም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አይነት ታላቅ ዋጋ ስላለው ነገር ምሳሌ ሊያገለግልም ይችላል (ማቴ. ፳፭፡፲፡–፳፱፣ ኤተር ፲፪፡፴፭፣ ት. እና ቃ. ፴፡፪፣ ፣፣፣)።

መኮነን፣ ኩነኔ። *ደግሞም ዳኛ፣ ፍርድ፣ ፍርድ፣ የመጨረሻው ተመልከቱ*

መፍረድ ወይም በእግዚአብሔር እንደ ወንጀለኛ መፈረድ።

ተንኰለኛውን ሰው ግን ይቀሥፈዋል፣ **ምሳ.** ፲፪፡፪።

በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን፣ ፩ **ቆሮ.** ፲፩፡፴፪።

ቃላቶቻችን፣ ስራዎቻችን፣ እና ሀሳቦቻችን ያስኮንኑናል፣ **አልማ** ፲፪፡፲፡ ነገሮችን በማወቅና ባለማከናወን፣ ሰዎች በኩነኔ ስር ናቸው፣ **ሔለ.** ፲፡፡፲፱። እንስራ፣ መስራት ካቆምን እንኮነናለን፣ **ሞሮኒ** ፱፡፮።

ለወንድሙ ይቅርታ የማይሰጥ በጌታ ፊት ይኮነናል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፱፡ በታላቅ ብርሀን ላይ ኃጢያት የሚሰራው የባሰውን ፍርድ ይቀበላል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፪፡፫፡ ንስሀ እስከሚገቡና መፅሐፈ ሞርሞንን እስከሚያስታውሱ ድረስ ቤተክርስቲያኗን ሁሉ በፍርድ ላይ ናት፣ **ት. እና ቃ.** ፹፡፱፡–፹፯።

መወለድ። *ደግሞም አንድያ ልጅ፣ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፣ የክርስቶስ ልጆች፣ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ*

መወለድ ወደ ህይወት ማምጣት በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ እነዚህ ቃላቶች ብዙም ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ከእግዚአብሔር የመወለድን ለማለት ነው። ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ የአብ አንድያ ልጅ ቢሆንም፣ ሁሉም ሰዎች እርሱን በመቀበል፣ ትእዛዛቱን በማክበር፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል አዲስ ሰዎች በመሆን ከክርስቶስ የተወለዱ ለመሆን ይችላሉ።

እኔ ዛሬ ወለድሁህ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ **መዝ.** ፪፡፯ (የሐዋ. ፣፣፡፣፣፣ ዕብ. ፩፡፭–፮፣ ፭፡፭)።

አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር ነው፣ **ዮሐ.** ፩፡፲፡ (፪ ኔፊ ፳፭፡፲፪፣ አልማ ፲፪፡፴፣–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፡፳፣)። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል፣ **ዮሐ.** ፣፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፳፡፳፩)።

ክርስቶስ ህዝቦቹን በመንፈስ ወልዷቸዋል፣ **ሞዛያ** ፭፡፯።

በጌታ በኩል የተወለዱት የበኩር ቤተክርስቲያን ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፲ ፡ ፲ ፪።

መዘመር። *ደግሞም መዝሙር፤ ሙዚቃ ተመልከቱ*

እግዚአብሔርን በመዝሙር እና በሙዚቃ ግጥም ማምለክ እና ማመስገን።

ለጌታ ዘምሩ፣ ፤ ዜና ፣ ፡ ፲ ፭–፲ ፮ (መዝ. ፣ ፡ ፲ ፭)። ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡ አመስግኑ፣ መዝ. ፡ ፡ ፡ ። ለእግዚአብሔር እልል በሉ፣ መዝ. ፡ ፡ ። መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ።

መንፈስ ቅዱስ እንዲዘምሩ ይመራቸዋል፣ ሞሮኒ ፣ ፡ ፡ ።

የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጸሎት ነው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ፡ ፡ ። ደስተኛ ከሆናችሁ፣ ጌታን በዘፈን አም ልኩ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ።

መዝሙረ ዳዊት። *ደግሞም ሙዚቃ፤ ዳዊት ተመልከቱ*

የተነሳሳ ግጥም ወይም መዝሙር

መዝሙረ ዳዊት፣ ብዙዎቹ ስለክርስቶስ የሆኑ፣ የመዝሙር ጥርቅሞችን የያዘ የብሉይ ኪዳን መፅ ሐፍ። መዝሙረ ዳዊት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ጊዜ ተጠቅሷል።

ዳዊት ብዙዎቹን መዝሙሮች ፅፏል። መዝሙ ሮቹ እግዚአብሔርን ለማሞገስ የተጻፉ ነበሩ። ብዙ ዎቹ በሙዚቃ የተዘጋጁ ነበሩ።

መዝሙር። *ደግሞም መዘመር፤ ሙዚቃ ተመልከቱ*

እግዚአብሔር የሚሞገስበት መዝሙር።

ጌታ ወደ ጌቴሴማኒ ከመሄዱ በፊት አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት መዝሙር ዘመሩ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ።

ጌታ ኤማ ስሚዝ ቅዱስ መዝሙሮችን ለመምረጥ አዘዛት፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ። የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጸሎት ነው፣ በረከት በራሳቸው ላይ በማድ ረግ ይመለስላቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ። ጌታን በመዝሙርና በሙዚቃ አምልኩ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ።

መድኃኒት። *ደግሞም አዳኝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ሁሉንም ከሞት እስርና ንስሀ የሚገቡትን ከኃጢ ያት ቅጣቶች ስለሚያድን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃ ኒት (ቤዛ) ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር ታላቅ ቤዛ ነው፣ ምክንያቱም በኃጢያት ክፍያው በኩል እርሱ የሰው ዘር ኃጢያት ዋጋን ከፈለ እናም የሁሉ ንም ሰዎች ትንሳኤ ሊሆን እንዲቻል አደረገ።

እግዚአብሔር ዓለቴ አምባዬ መድኃኒቴ ነው፣ ፤ ሳሙ. ፣ ፡ ፤ (መዝ. ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፡ ፡)። የሚ ቤዣኝ ሕያው እንደ ሆነ ያውቃል፣ ኢዮብ ፣ ፡ ፡ ። አንተ ረዳቴና መድኃኒቴ ነህ፣ መዝ. ፡ ፣ ፣ (መዝ. ፡ ፡ ፡)። እረዳሃለሁ፡ ይላል እግ ዚአብሔር፣ የሚቤዥህም የእስራኤል ቅዱስ ነው፣ ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ (ኢሳ. ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡)። እኔ እግዚአብሔር መድኃኒትሽና ታዳጊሽ ነኝ፣ ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ (ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡)።

እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ። የሰው ልጅ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ መጣ፣ ማቴ. ፡ ፡ ፡ ፡ (፣ ጢሞ. ፣ ፡ ፡–፣)። የእስራኤል ጌታ አምላክ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአል፣ ሉቃ. ፣ ፡ ፡ ፡ ። ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን፣ ሮሜ ፣ ፡ ፣ ። መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ሮሜ ፣ ፡ ፡ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓመፅ ሁሉ እንዲ ቤዣን፣ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል፣ ቲቶ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአታችንም በደሙ አጠበን፣ ራዕ. ፣ ፡ ፣ ።

ቤዛነት የሚመጣው በቅዱስ መሲሕ በኩል ነው፣ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፣ ፡ ፣ ። ወልድ በእራሱ ላይ የሰውን ኃጢያት እና መተላለፍ ወሰደ፣ አዳናቸው፣ እናም የፍትህን ፍላጎት አሟላ፣ ሞዛያ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፣ ፡ ፡–፣ ፡ ። ክርስቶስ ወደ ንስሀ መግባት የሚጠመቁትን ሁሉ ለማዳን መጣ፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ህዝቡን ለማዳንና ወደ ዓለም ይመጣል፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ቤዛነት በንስሃ አማካይነት ይመጣል፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ኢየሱስ አለምን ለማዳን መጣ፣ ሔለ. ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ክርስቶስ የሰው ዘርን ከስጋዊ እና ከመን ፈሳዊ ሞት ለማዳን መጣ፣ ሔለ. ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። በክ ርስቶስ ቤዛነት ይመጣል፣ ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ህዝቤን ለማዳን የተዘጋጀሁ እኔ ነኝ፣ ኤተር ፣ ፡ ፣ ፡ ።

ጌታ አዳኞችሁ የስጋ ሞትን ሞተ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፡ ። ክርስቶስ ንስሀ ከገቡ ለሁሉም ተሰቃይ ቷል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ፡–፡ ። ህፃናት ከአ ለም መጀመሪያ ጀምሮ በአንድያ ልጁ ድነዋል፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ። አንድያ ልጁን ለአለም ቤዛነት ወደ አለም ልኬአለሁ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፣ ፡ ። ክር ስቶስ የአለም ብርሀን እና አዳኝ ነው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ። ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለሙታን ቤዛነት ራዕይ አየ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ቅዱሳን የእግዚ አብሔርን ልጅ እንደ ቤዛቸውና እንደ መድሀኒታ ቸው እንደሆነ ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ።

የሰው ዘሮች ሁሉ በክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል መዳን እንደሚችሉ እናምናለን፣ እ.አ. ፣ ፡ ፣ ።

መጀመሪያ። *ደግሞም መፍጠር፣ ፍጥረት፣ ቅድመ ምድራዊ ህይወት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በአጠቃላይ ስለ ስጋዊ ህይወት—ይህም ማለት

ስለቅድመ ምድራዊ ህይወት ይናገራል። አንዳንዴ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጀመሪያ ይጠቀሳል።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፣ ዘፍጥ. ፩፡፩ (ሙሴ ፪፡፩)።

በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ዮሐ. ፩፡፩።

እኔ አለፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ነኝ፣ ፣ ኄሬ ፱፡፲፯።

ክርስቶስ መጀመሪያው እና መጨረሻው ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፩። አዲሱ እና ዘለአለማዊው ቃል ኪዳን ከመጀመሪያው ጀምሮ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፩። ሰው በመጀመሪያም ከሰው ጋር ነበር፣ ት. እና ቃ. ፣፲፣፡፳፣፣ ፳፱። የተከበሩና ታላቅ መን ፈሳት ከመጀመሪያም መሪዎች እንዲሆኑ ተመር ጠው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፣፲፭።

አንድያ ልጄ ከመጀመሪያ ጀምሮ ከእኔ ጋር ነበር፣ ሙሴ ፪፡፳፯።

መገሰጽ፣ ተግሳጽ። *ደግምም ጭንቀት ተመልከቱ*

ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ለማሻሻል ወይም ለማጠናከር ለመርዳት የሚሰጥ ማስተካከያ ወይም ቅጣት።

ሁሉን የሚችለውን የአምላክን ተግሣጽ አትናቅ፣ ኢዮብ ፭፡፣፲፯ (ምሳ. ፫፡፣፲፩)። አቤቱ. . . አንተ የገሠጽኸው . . . ሰው ምስጉን ነው፣ መዝ. ፣፻፱፡፣፲፪።

ሁሉም ቅዱሣት መጻህፍት ለትምህርትና ለተ ግሣጽ የተሰጠ ነው፣ ፪ ጢሞ. ፫፡፣፲፮። ጌታ የሚወ ደውን ይቀጣዋል፣ ዕብ. ፣፲፪፡፭–፣፲፩።

ጌታ ህዝቡን መግሰፅ ተገቢ መሆኑን አየ፣ ሞዛያ ፳፫፡፣፳፩–፳፪። ጌታ ህዝቡን ካልገሰጸ፣ አያስታው ሱትም፣ ሔሌ. ፣፲፪፡፫። ጌታ የያሬድ ወንድምን አነ ጋገረው፣ እናም ገሰፀው፣ ኤተር ፪፡፣፲፬።

ንስህ ይገቡ ዘንድ ተገሰጹ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፳፯፲፯። የምወዳቸውንም ኀጥያታቸውን ለመሰረይ እገስጻ ቸዋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፩። በግሰጻው የማይጸኑት ሁሉ ሊቀደሱ አይችሉም፣ ት. እና ቃ. ፣፲፩፡፪–፭። ህዝቦቼ ታዛዥነትን እስከሚማሩ ድረስ መገሰጽ ያስ ፈልጋቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፣፯። መገሰፅን ለመ ቀበል የማይችል ለመንግስቴ ብቁ አይደለም፣ ት. እና ቃ. ፣፲፴፣፡፴፩።

መገፋፋት፣ ጥብቅ ትእዛዝ። *ደግምም መንፈስ ቅዱስ ተመልከቱ*

አንድ ነገርን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ፣ በል ዩም በመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ ወይም ሀይል፣ በጥብቅ መገፋፋት።

በውስጤም ያለ መንፈስ አስገድዶኛልና፣ ኢዮብ ፴፪፡፣፲፰።

የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል፣ ፪ ቆሮ. ፭፡፣፲፬።

ላባንን እገድለው ዘንድ በመንፈስ ተገፋፋሁ፣ ፩ ኔፊ ፬፡፣፲። መንፈስ ገፋፋኝ፣ አልማ ፣፲፬፡፣፲፩። በኪዳን መሰረት እገፋፋለሁ፣ አልማ ፣፰፡፴፬። አማሮን በመንፈስ ቅዱስ በመገፋፋቱ፣ መዛግብ ትን ደበቀ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፴፣፴፣።

ከላይ የሚመጣው በመንፈስም ቁጥጥር መናገር አለበት፣ ት. እና ቃ. ፣፳፫፡፣፳፬።

መጋረጃ። *ዐይነ-እርግብ ተመልከቱ*

መጋቢ፣ መጋቢነት። *ደግምም ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት ተመልከቱ*

የሌላን ጉዳይ ወይም ንብረት የሚያስተዳድር ሰው። መጋቢ የሚያስተዳድረው መጋቢነት ይባ ላል። በምድር ያሉት ነገሮች ሁሉ የጌታ ናቸ፣ እኛም የእርሱ መጋቢዎች ነን። ለጌታ ሀላፊዎች ነን፣ ነገር ግን በመጋቢነታችን በእግዚአብሔር ስልጣን ለተ ሰጣቸው ወኪሉ ሀተታ ለመስጠት እንችላለን። ከጌታ ወይም ስልጣን ካላቸው አገልጋዮቹ የአገ ልግሎት ጥሪ ስንቀበል፣ ያም መጋቢነት በመንፈ ሳዊ እና በምድራዊ ጉዳዮች ላይ ለመሆን ይችላል (ት. እና ቃ. ፳፪፡፣፴፩)።

በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፣ ማቴ. ፳፭፡፣፲፱–፳፫። ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፣ ሉቃ. ፣፲፪፡፣፣፳ (ት. እና ቃ. ፣፲፪፡፣፫)። ኢየሱስ ጻደቅ ስላልሆነው መጋቢ ምሳሌ ሰጠ፣ ሉቃ. ፣፲፮፡፣፩–፣፳።

ታማኝ ሀላፊ ሆኖ የተገኘውም ወደ ጌታው ደስታ ይገባል፣ ት. እና ቃ. ፣፲፩፡፣፲፪። እያንዳንዱ ሰው የመ ጋቢነቱን መግለጫ ይስጥ፣ ት. እና ቃ. ፣፳፪፡፣፫–፣፭። ታማኝ እና ጥበባዊ ሀላፊው ሁሉንም ነገሮች ይወርሳል፣ ት. እና ቃ. ፣፳፣፡፣፳፪። ጌታ እያንዳን ዱን ሰው እንደ ምድራዊ በረከቶች መጋቢነቱ መግ ለጫ እንዲሰጥ ያደርገዋል፣ ት. እና ቃ. ፣፲፬፡፣፲፩–፣፲፯ (ት. እና ቃ. ፣፲፪፡፣፲፪)። ጥበባዊ ሀላፊነት እን ድትሆን ዘንድ ተጉ ሁን፣ ት. እና ቃ. ፣፲፴፯፡፣፳፯።

መግለጫ። *ደግምም ውድሩፍ፣ ውልፈርድ፣ ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ*

በፕሬዘደንት ውልፈርድ ውድሩፍ በ፲፣፣፲፣ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ ውስጥ ቤተክርስቲያኗና አባ ላቷ በምድር ህግ ታዛዥ እንደሚሆኑና ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን እንደሚያቆሙ በግልፅ የሚና ገር አስተዳደራዊ አዋጅ (እ.አ. ፩)። ፕሬዘደንት ውድሩፍ መግለጫውን የሰጡት ከእግዚአብሔር ራዕይ ከተቀበሉ በኋላ ነበር።

መግረዝ። *ደግምም የአብርሐም ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ዘመናት ለእስራኤል ወንዶች

የነበረ የአብርሐም ቃል ኪዳን ምልክት (ዘፍጥ. ፲፯፡፣–፲፩፣ ፳፫–፳፯፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፣ ፲፩ [ተጨማሪ])። ግርዘት የወንድ ህጻናትን እና ጎልማሳዎችን “የቀ·ልፈተ ሥጋ” በመቁረጥ የሚ ፈጸም ነበር። ይህን የሚያደርጉት የቃል ኪዳን መብት ነበራቸው እናም የዚህን ሀላፊነት ይቀበ ላሉ። ግርዘት በክርስቶስ ተልዕኮ እንደ ቃል ኪዳን ምልክት የተወገደ ነበር (ሞሮኒ ፰፡፰፡ ት. እና ቃ. ፷፬፡፣–፯)።

መግደላዊት ማርያም

የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ደቀ መዝሙር የሆነች የአዲስ ኪዳን ሴት። መግደላዊ ማርያም የመጣች በትን ቦታ፣ መጌዶልን፣ የሚጠቁም ነበረ። ይህም የተገኘው በገሊላ ባህር በምዕራብ ባህር ዳር ነበር።

በመስቀሉ አጠገብ ነበረች፣ **ማቴ.** ፳፯፡፣–፴፯ (ማር. ፲፭፡፣–፵፣ ዮሐ. ፲፱፡፣–፳፭)። ክርስቶስ በሚቀበርበትም ጊዜ ነበረች፣ **ማቴ.** ፳፯፡፣–፳፩ (ማር. ፲፭፡፣–፵፯)። ከሞት በተነሳበት ጠዋትም በመቃብሩ አጠገብ ነበ ረች፣ **ማቴ.** ፳፰፡፣–፩ (ማር. ፲፮፡፣–፩፣ ሉቃ. ፳፬፡፣–፲፣ ዮሐ. ፳፡፣–፩፣ ፲፩)። ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለመ ጀመሪያ ጊዜ የታየው በእርሷ ነበር፣ **ማር.** ፲፮፡፣–፱ (ዮሐ. ፳፡፣–፲፱–፲፳)። ሰባት አጋንንት ወጡላት፣ **ሉቃ.** ፰፡፣–፪።

መግደል። የሞት ቅጣት፣ ግድያ *ተመልከቱ*

መጠራት እና መመረጥ። *ደግሞም መመረጥ ተመልከቱ*

ጻድቅ የክርስቶስ ተከታዮች የዘለአለማዊነትን መረጋገጫ ከሚያገኙት ምርጦች መካከል ለመቆ ጠር ይችላሉ። ይህ መጠራት እና መመረጥ የሚጀ መረው ንስሀ በመግባት እና በጥምቀት ነው። የሚ ፈጸመውም “በክርስቶስ ባላችሁ ፅኑነት መቀጠል፣ . . .እናም እስከመጨረሻም መፅናት” ሲችሉ ነው (፪ ኔፊ ፴፩፡፣ ፲፱–፳)። ቅዱሣት መጻህፍት ይህን ሂደት መጠራታችንን እና መመረጣችንን ማረጋገጥ ብለው ይጠሩታል (፪ ጴጥ. ፩፡፡–፲፩፣ ት. እና ቃ. ፲፴፩፡፣–፯)

እናንተም የካህናት መንግሥት ትሆኑልኛላችሁ፣ **ዘፀአ.** ፲፱፡፣–፮ (ራዕ. ፩፡፣)።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ጀምሮ ምርጥ የሆኑ ትንን ለደህንነት መርጧል፣ ፪ ተሰ. ፪፡፣ ፲፣። መጠ ራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ትጉ፣ ፪ ጴጥ. ፩፡፣ ፲።

ጌታ የእርሱ እንድትሆኑ ያትማችኋል፣ **ሞዛያ** ፭፡፣ ፲፭። ከአንተ ጋር ዘለአለማዊ ህይወት እንዲኖ ርህ ቃል ኪዳን እገባለሁ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፣ ፳።

ታማኝ የክህነት ባለስልጣኖች የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያንና መንግስት እንዲሁም ምርጦቹ ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፱፡፱፡ ፴፣–፴፴። ተጨማሪ እርግጠኛ የትንቢት ቃል ማለት . . . ሰው በዘለ አለም ህይወት እንደታተመ አውቋል ማለት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፩፡፣–፯። በአንተም ላይ ዘለአለማ ዊነትህን አትምብሀለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፣ ፵፱።

መጠበቅ፣ ጠባቂ። *ደግሞም ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ ተመልከቱ*

ንቁ መሆን፣ መጠበቅ። የሚጠብቅና ታዛዥ የሆነ እናም የተሰጋጀ ሰው። ጠባቂዎች በጌታ ወኪሎች ለሌሎች ጥቅም ልዩ ሀላፊነት እንዲኖራቸው የተ ጠሩ መሪዎች ናቸው። መሪዎች እንዲሆኑ የተጠ ሩትም በአለም ላሉት ሌሎች ጠባቂ የመሆን ሀላፊ ነት አላቸው።

ጠባቂ አድርጌሃለሁ፣ **ሕዝ.** ፫፡፣ ፲፣–፳፩። የማስ ጠንቀቂያ ድምፅ የሚያነሱ ጠባቂዎች ነፍሳቸውን ያድናሉ፣ **ሕዝ.** ፴፫፡፣ ፣–፱። ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁ ምና እንግዲህ ንቁ፣ **ማቴ.** ፳፬፡፣ ፴፪–፴፫ (ማቴ. ፳፭፡፣ ፲፫፡ ማር. ፲፫፡፣ ፴፭–፴፯፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፣ ፣–፲፩)። ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፣ **ማቴ.** ፳፮፡፣ ፴፩ (ፍ ኔፊ ፲፯፡፣ ፣ ፲፣ ፲፯)።

ራሳችሁን፣ እናም ሀሳባችሁን፣ እናም ቃላች ሁን፣ እናም ድርጊታችሁን የማታስተውሉ ከሆና ችሁ፣ መጥፋት ይገባችኋል፣ **ሞዛያ** ፬፡ ፴፡ አልማ ቤተክርስቲያኗን እንዲመሩና እንዲቆጣጠሩ ካህና ትን እና ሽማግሌዎችን ሾመ፣ **አልማ** ፮፡ ፩።

አዳኝን የማይጠብቀውም ተለይቶ ይጠፋል፣ ት. እና ቃ. ፴፩፡፣ ፴፬። ኤጲስ ቆጶስና ሌሎች ቤተ ክርቲያኗን እንዲጠብቁ ተጠሩት እና ተሾሙ፣ ት. እና ቃ. ፴፮፡፣ ፳፯። ጌታ በወይን አትክልት ስፍራው ላይ ጠባቂዎች አስቀመጠ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፴፬–፴፯።

መጠነኛነት። *ደግሞም ትሁት፣ ትሕትና ተመልከቱ*

ትሁት፣ መጠነኛ፣ እና ጨዋ የሆነ ጸባይ እና አመ ለካከት። መጠነኛ የሆነ ሰው ከመጠን በላይ የሆኑትን እና ሽንገላን ያስወግዳል።

እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሔዋን የቁ ርበትን ልብስ አደረገላቸው፣ **ዘፍጥ.** ፫፡ ፳፩ (ሙሴ ፬፡ ፳፯)።

ሴቶች በሚገባ ልብስ ሰውነታቸውን ይሸልሙ፣ ፩ **ጢሞ.** ፪፡ ፱። ራሳቸውን የሚገዙ፡ ንጹሐች፡ በቤት የሚሠሩ ሁኑ፣ ቲቶ ፪፡ ፭።

ብዙዎች በልብሳቸው ውድነት አንገታቸውን አደንድነዋል፣ **ያዕቆ.** ፪፡ ፲፣።

ልብሶችህ ያላጌጠ ይሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፴።

በንፁህነት፣ በምግባረ ጥሩነት፣ በመሆን እናም ናለን፣ ኤ.ኧ. ፩፡ ፲፣።

መጠጣት፣ ጠጥቷል። የጥበብ ቃል *ተመልከቱ*

መጣላት። ጸብ *ተመልከቱ*

መጥላት፣ ጥላቻ። *ደግሞም* በቀል፤ ጠላትነት፤ ፍቅር *ተመልከቱ*

ጥላቻ አንድን ሰው ወይም ነገር አለመውደድ ነው።

እኔ እግዚአብሔር በሚጠሉኝ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣው፣ **ዘፀአ.** ፳፡፭። እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፣ **ምሳ.** ፮፡፲፮። ሰነፍ ልጅ ግን እና ቱን ይንቃል፣ **ምሳ.** ፲፭፡፳። የተናቀ ከሰውም የተ ጠላ ነው፣ **ኢሳ.** ፶፫፡፫። ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ **ማቴ.** ፭፡፵፬። ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛው ንም ይንቃል፣ **ማቴ.** ፮፡፳፬። በሁሉም ስለ ስሜ የተ ጠላችሁ ትሆናላችሁ፣ **ማቴ.** ፲፡፳፪። ክፉ የሚያ ደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፣ **ዮሐ.** ፫፡፳። ማንም ታናሽነትህን አይናቀው፣ **፩ ጢሞ.** ፬፡፲፪።

ሀብታም በመሆናቸው ድሆችን ይጠላሉ፣ **ፍ ኔፊ** ፱፡፴። የእግዚአብሔርን ራዕይ አትናቁ፣ **ያዕቆ.** ፪፡፯። ከእኛ ዘለዓለማዊ የሆነ ጥላቻ ነበራቸው፣ **ያዕቆ.** ፯፡፳፪።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ምክር ከንቱ ያደርጋሉ እናም ቃሉንም ይንቃሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፫፡፯።

ራዕይ አይቻለሁ በማለቱ ተጠላሁ እናም ተሰቃ የሁ፣ **ጆ.ስ.—ታ.** ፩፡፳፭።

መጥምቁ ዮሐንስ። *ደግሞም* አሮናዊ ክህነት፤ ኢሊያ *ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የዘካሪያስ እና የኤልሳቤጥ ልጅ። ዮሐንስ ህዝብን ለመሲህ ለማዘጋጀት ተልኮ ነበር (**ዮሐ.** ፩፡፲፱–፳፯)። የአሮናዊ ክህነት ቁል ፎች የያዘ ነበር እናም ኢየሱስ ክርስቶስን ጠመቀ።

ኢሳይያስ እና ሌሎች ስለዮሐንስ ሚስዮን ተነ በየ፣ **ኢሳ.** ፵፡፫ (ሚል. ፫፡፩፣ ፩ ኔፊ ፲፡፯–፲፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፱)።

ወደ እስር ቤት ተሰደደ እናም ተሰየፈ፣ **ማቴ.** ፲፬፡፫–፲፪ (ማር. ፮፡፲፯–፳፱)። ገብርኤል የዮሐ ንስን መወለድ እና አገልግሎት ለዘካሪያስ አስታ ወቀ፣ **ሉቃ.** ፩፡፭–፳፭። ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ታላቅ ነቢይ እንደነበረ አስተማረ፣ **ሉቃ.** ፯፡፳፱–፳፰። ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ልጅ አወቀው፣ **ዮሐ.** ፩፡፳፱–፴፩። የዮሐንስ ደቀ መዛሙርቶች የኢ የሱስ ደቀ መዛሙርቶች ሆኑ፣ **ዮሐ.** ፩፡፳፭–፳፱፣ ፴፭–፴፯ (የሐዋ. ፩፡፳፭–፳፪)። ምንም ተአምራት አልሰራም፣ **ዮሐ.** ፲፡፴፭።

ከሞት እንደተነሳ ሰው፣ ጆሴፍ ስሚዝን እና ኦሊ ቨር ካውደሪን ወደ አሮናዊ ክህነት ለመሾም ተላከ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፫ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፭–፰፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፰–፳፱)። በስምንት ቀን እድሜውም፣ በመል አክ ተሹሞ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፩፣ ፳፰።

መጨረሻ የሌለው። ማለቂያ የሌለው *ተመልከቱ*

መጸጸት፣ ንስሀ መግባት። *ደግሞም* መናዘዝ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ስርየት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የተሰበረ ልብ፤ ይቅርታ ማድረግ *ተመልከቱ*

ወደ እግዚአብሔር፣ ወደ እራስ፣ እና በአጠቃ ላይም ወደ ህይወት አዲስ አስተሳሰብ የሚያመጣ የአዕምሮና የልብ ቅያሬ። ንስሀ መግባት ሰው ከክ ፋት መዞሩን እና ልቡንና ፍላጎቱን ወደ እግዚአብ ሔር ማዞሩን፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛትና ፍላጎት እራስን እንዳስገዛ እና ኃጢያትን እንደተወ ያስ መለክታል። እውነተኛ ንስሀ መግባት የሚመጣው ለእግዚአብሔር ባለው ፍቅር እና የእርሱን ትእዛ ዛት ለማክበር ባለው ልባዊ ፍላጎት ነው። ተጠያቂ ነት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ኃጢያት ሰርተዋል እናም ወደ ደህንነት ወደፊት ለመጓዝ ንስሀ መግባት አለ ባቸው። ንስሀችን ውጤታማና በእግዚአብሔር ተቀ ባይነት የሚያገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል ብቻ ነው።

ለእግዚአብሔር ተናዘዙ፣ **ዕዝ.** ፲፡፲፩። የሥራች ሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፤ ክፉ ማድረግን ተዉ፣ **ኢሳ.** ፩፡፲፮። ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅ ፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመ ለሱ፣ **ሕዝ.** ፲፰፡፴–፴፩።

መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ፣ **ማቴ.** ፫፡፪። ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል፣ **ሉቃ.** ፲፭፡፯። እግዚአብሔር በየ ቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፣ **የሐዋ.** ፲፯፡፴ (፪ ኔፊ ፱፡፳፫፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፴–፴፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፲፯)። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኅዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋል፣ **፪ ቆሮ.** ፯፡፲።

እንግዲህ ኃጢያት ለመፈፀም ምንም ፍላጎት እንዳይኖረን ታላቅ ለውጥ በልባችን ውስጥ ሁሉን በሚገዛው በጌታ መንፈስ አምጥቷል፣ **ሞዛያ** ፭፡፪። ኃጢአቱን ከተናዘዘ፣ እናም ንስሃ ከገባ እር ሱን ይቅር ትለዋለህ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፳፱። አልማ ለህ ዝቡ መናገሩን ከጨረሰ በኋላ ብዙዎች ንስሃ ገቡ፣ **አልማ** ፲፭፡፩። የንስሃ ቀናችሁን አታዘግዩ፣ **አልማ** ፴፡፲፡ ፴፫። አልማ ሔለማንን ስለንስሀ መግባቱ እና መቀየሩ አስተማረው፣ **አልማ** ፴፯ (ሞዛያ ፳፯፡፲–፴፴)። ቅጣት ከሌለ በስተቀር ለሰዎች ንሰሃ ሊመጣ አይችልም፣ **አልማ** ፴፪፡፲፯። ኃጢያትህ ብቻ በዚያ ወደ ንሰሃ በሚያመጣህ ጭንቀት ያስጨን ቅህ፣ **አልማ** ፴፪፡፳፱። ለእኔም መስዋእት የተሰበረ ልብ እናም የተዋረደ መንፈስ ታቀርባላችሁ፣ ፫ ኔፊ

፱፡፳። ንስሃ የሚገባን እናም እንደ ህፃን ልጅ ወደ እኔ የሚመጣንም እቀበለዋለሁ፣ ፤ ኔፊ ፱፡፳፪። በምድር ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ ንስሃ ግቡ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፡፳። ንስሃ ሁል ጊዜም ከገቡ፣ ይቅር ይባላሉ፣ ሞሮኒ ፮፡፰።

ለዚህ ትውልድ ከንስሃ በቀር ሌላ ምንም አት በሉ፣ ት. እና ቃ. ፮፡፱ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፱)። ንስሃ በሚገባ ነፍስ ሃሴቱ እንዴት ታላቅ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፲፫። እያንዳንዱ ሰው ንስሃ መግባት አለበት ወይም ይሰቃያል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፭። ኃጢያ ትን የሚያደርግና ንስሃ የማይገባ ወደ ውጭ ይጣ ላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፯። ለኃጥያቱ ንስሀ የሚ ገባ እና ለሚተዋቸውም፣ ይቅርታ ይደረግለታል፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፵፪–፵፫። ንስሀ የገቡ ሙታንም ይድናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፶፯፡፶፰።

ንስሐ በመግባት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፬።

መፅሐፈ መሳፍንት

የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። መፅሐፈ መሳፍንት ከኢያሱ ሞት እስከ ሳሙኤል መወለድ ድረስ ስለ እስራኤል ይናገራል።

ምዕራፍ ፩–፫ የመፅሐፈ መሳፍንት መቅድም ናቸው። እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ስላላስወጡ (መሳ. ፩፡፣፲፯–፴፭)፣ እምነት ማጣት፣ ከማያምኑት ጋር መጋባት፣ እና ጣዖት ማምለክ በሆኑት ውጤ ቶች እስራኤላውያን መሰቃየት እንዳለባቸው ይገል ጻሉ። ምዕራፍ ፬–፭ እስራኤልን ከከነዓናውያን ስላ ዳኑት የዲቦራና የባርቅ አጋጣሚዎችን ይናገራሉ። ምዕራፍ ፮–፰ ጌታ እስራኤልን ከምድያም ስላዳ ነው ስለጌዴዎን እምነት የሚያሳድግ አጋጣሚዎች ናቸው። በምዕራፍ ፱–፲፪ ውስጥ፣ ብዙዎቹም እስ ራኤላውያን በክህደት ላይ እያሉ እና በባእድ ገዢ ዎች በሚገዙበት ጊዜ፣ የተለያዩ ሰዎች እንደ እስ ራኤል ዳኛ አገለገሉ። ምዕራፍ ፲፫–፲፮ ስለመጨ ረሻው ዳኛ ሶምሶን መነሳት እና ውድቀት ይናገ ራሉ። የመጨረሻው ምዕራፍ፣ ፲፯–፳፩፣ የእስራ ኤል ኃጢያቶች ጥልቀትን እንደሚገልፅ ተጨማሪ ፅሑፍ ለመመልከት ይቻላል።

መፅሐፈ መክብብ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የህይወት ጥልቅ ፈተናዎች ላይ ማሰላሰሊያን የያዘ መፅሐፍ።

የመፅሐፉ ጸሀፊ፣ ሰባኪው፣ አብዛኛውን የጻ ፈው የወንጌል እውቀት በሌላቸው አስተሳሰብ በኩል ነው። የጻፈውም በአለም ህዝቦች ስሜቶች መሰረት ነው—ይህም ማለት፣ “በጸሀይ ስር” ለነበሩት (መክ. ፩፡፣፱)። ከመፅሐፉ አብዛኛው መጥፎ ነገሮችን የሚ ጠቁምና ክፉ አሳቢዎች ያሉበት ይመስላል (መክ. ፱፡፣፭፣ ፲)። ጌታ ህይወትን እንደዚህ እንድናስብበት አይፈልግም ነገር ግን ሰባኪዎች በምድር ላይ ላሉ ላልተብራሩ ሰዎች ነገሮች እንደሚታዩአቸው የተ መለከቱበት ነው። በመፅሐፉ ውስጥ ከሁሉም በላይ መንፈሳዊ ክፍሎች የሚገኙት በምዕራፍ ፲፩ እና ፲፪ ውስጥ ነው፣ በዚህም ጸሀፊው እስከ መጨረሻ ድረስ ዋጋ የሚኖረው ብቸኛ ነገር ቢኖር ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥነት ነው ብሎ ደምድሟል።

መፅሐፈ ምሳሌ

አጭር የምግባረጥሩ አባባል ወይም ምክር።

መፅሐፈ ምሳሌ፣ አንዳንዶቹ በሰለሞን የተጻፉ ብዙ ምሳሌዎች፣ አባባሎች፣ እና ግጥሞች የያዘ የብ ሉይ ኪዳን መፅሐፍ። መፅሐፈ ምሳሌ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ጊዜ ተጠቅሷል።

ምዕራፍ ፩–፱ የእውነተኛ ጥበብ መግለጫን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፲–፳፪ ስለትክክለኛ ወይም ትክክል ስላልሆነ የመኖር መንገድ አባባል ጥርቅምን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፳፫–፳፱ የይሁዳ ንጉስ ሕዝቅ ያስ ሰዎች የመዘገቡትን የሰለሞን ምሳሌዎችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፴–፴፩ የምግባረ ጥሩ ሴት መግ ለጫ ያለበት ነው።

መፅሐፈ ሞርሞን

ደግምም ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ፣ ሰሌዳዎች፣ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፣ ቀኖና፣ ቅዱሳት መጻህፍት፣ ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር፣ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች፣ የወርቅ ሰሌዳዎች ተመልከቱ

በየጓለኛው ቀን ቅዱስና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስትያን ተቀባይ ከሆኑት አራት የቅዱስም መጻ ህፍት ጥራዞች አንዱ። ይህም የአሜሪካዎች የጥ ንት ነዋሪዎች መዝገቦች ሞርሞን ተብሎ በሚጠ ራው በጥንት ነቢይ የታጠረ ነው። የተጻፈውም ኢየ ሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ለመምስከር ነበር። ይህን መዝገብ በሚመለከት ይህን በእግዚአብሔር ስጦታ እና ሀይል የተረጎመው ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለወንድሞች መጽሐፈ ሞርሞን በምድር ካሉ መጽ ሐፍት በሙሉ የበለጠ ትክክል እንደሆነ፣ እናም የኃይማኖታችን የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነና ከማን ኛውም ሌላም መጽሐፍ በበለጠ በውስጡ ባሉት አስ ተያየቶች በመኖር ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ እንደሚችል ነገርኳቸው ብሏል (በመፅሐፈ ሞርሞን መጀመሪያ ያለውን መግቢያ ተመልከቱ)።

መፅሐፈ ሞርሞን ከጥንቱ አለም ወደ አሜሪካ ክፍለ አህጉሮች የሄዱት የሶስት ቡድኖች ሀይማኖ ታዊ መዝገብ ነው። እነዚህ ቡድኖች የሀይማኖታ ቸውን እና የአለማዊ ታሪኮቻቸውን በብረት ሰሌዳ ዎች ላይ በጻፉ ነቢያት ይመሩ ነበር። መፅሐፈ ሞር ሞን ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በአሜሪ ካዎች ውስጥ የሚገኙትን ህዝቦች እንደጎበኘ መዝ ግቧል። የክርስቶስን ጉብኝት የሁለት መቶ አመት ሰላም ዘመን ተከተለ።

ከኔፋውያን ነቢያት የመጨረሻው ሞሮኒ የእነዚህ

ህዝቦችን የታጠሩ መዝገቦችን ዘጋ እና በ፱፻፳፩ ዓ.ም. አካባቢ ደበቃቸው። በ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.)፣ ከሞት የተነሳው ሞሮኒ ጆሴፍ ስሚዝን ነበኝ እና በጓላም እነዚህን ጥንታዊ እና ቅዱስ መዝገቦች እንዲተረጎሙ እና እንደ ሌላኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት እንዲመጡ ሰጠው።

ዮሴፍ ትንሹ የፍሬ ዛፍ ነው፣ አረጎቹ በቅጥር ላይ ያድጋሉ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፳፪–፳፮። እውነት ከምድር በቀለች፣ መዝ. ፹፭፡፲፩ (ሞር. ፰፡፲፯፣ ሙሴ ፯፡፳፪)። ለአሕዛብም በሩቅ ምልክትን ያቆማል፣ ከምድርም ዳርቻ በፉጨት ይጠራቸዋል፣ ኢሳ. ፭፡፳፮። ድምፅም ከመሬት ላይ ሆኖ ይናገራል፣ ኢሳ. ፳፱፡፬ (፪ ኔፊ ፳፯፡፲፩–፲፭)። ራእዩም ሁሉ እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃል ይሆናል፣ ኢሳ. ፳፱፡፲፩ (ኢሳ. ፳፱፡፱–፲፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፯–፳፯)። የዮሴፍ እና የይሁዳ በትሮች በጌታ እጅ ውስጥ አንድ ይሆናሉ፣ ሕዝ. ፴፯፡፲፭–፳።

ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፣ ዮሐ. ፣፡፲፣ (፣ ኔፊ ፲፭፡፲፣–፳፬)።

መፅሐፈ ሞርሞን እና መፅሐፍ ቅዱስ አብረው ያድጋሉ፣ ፪ ኔፊ ፣፡፲፪–፳፩። የጌታ ቃላት ወደ ምድር ዳርቻ ያፏጫሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፱፡፪። ጌታ መፅሐፈ ሞርሞንን ወደ ላማናውያን ለማምጣት ከኢኖስ ጋር ቃል ኪዳን ገባ፣ ኢኖስ ፩፡፲፭–፲፣። መፅሐፈ ሞርሞን የተጻፈው እኛ በመፅሐፍ ቅዱስ እንድና ምን ዘንድ ነው፣ ሞር. ፣፡፱። በመጨረሻው ቀንም መፅሐፈ ሞርሞን በዓለም ላይ ለምስክርነት ይቆማል፣ ኤተር ፭፡፪። እነዚህ ነገሮች ሀሰት እንደሆኑ እግዚአብሔርን ጠይቁ፣ ሞሮኒ ፣፡፪።

ክርስቶስ መፅሐፈ ሞርሞን እውነት እንደ ሆነ መሰከረ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፣። መፅሐፈ ሞርሞን ሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የያዘ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፱ (ት. እና ቃ. ፳፡፳–፲፪፣ ፴፪፡፲፪)።

መፅሐፈ ሞርሞን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፳።

መፅሐፈ ትእዛዛት። *ደግሞም ራዕይ*፣ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች *ተመልከቱ*

በ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.)፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተቀበላቸው ብዙ ራዕያት A Book of Commandments for the Government of the Church of Christ በሚል በተሰጠር ርዕስ ለህተማ ተዘጋጅተው ነበር። ጌታ ከአገልጋዮቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል፣ እና ከሁለት አመት በኋላ የተስፋፉ የራዕዮች ጥርዝ እንድ ት. እና ቃ. ታተመ።

ት. እና ቃ. ፩ ለመፅሐፈ ትእዛዛቱ መቅድም የሰጠው ነው፣ ት. እና ቃ. ፩፡፣። ጌታ ጥበባዊ ሰውን በመፅሐፈ ትእዛዛቱ ውስጥ ያለውን ታናሽኛውን ራዕዩን አመሳስሎ ለመጻፍ የሚችል እንዳለ ጠየቀ፣ ት. እና ቃ. ፳፣፡፩–፱። እነዚህን ራዕያት እንዲያትሙ መጋቢዎች ተመድበው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፫፡፩–፭።

መፅሐፈ ነገሥት

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ሁለት መፅሐፎች። እነዚህ መፅሐፎች ከንጉስ ዳዊት አራተኛ ወንድ ልጅ ከአዶንያስ አመጽ (በ፲፻፲፭ ም.ዓ. አካባቢ.) እስከ ይሁዳ መጨረሻ ምርኮ ድረስ (፭፻፹፯ ም.ዓ. አካባቢ.) የእስራኤል ታሪክን ይዘረዝራሉ። እነዚህም ከተለያዩበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሰሜን አገሮች ሶርያዎች በምርኮ እስከሚወስዷቸው ድረስ የሰሜን መንግስት (የእስራኤል አስር ጎሳዎች) ታሪኮችን በሙሉ ጨምረው ይዘረዝራሉ። ደግሞም የዘመን ቅድመ ተከተል በተጨማሪ ውስጥ ተመልክቱ።

መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ፣ ምዕራፍ ፩ የንጉስ ዳዊት የመጨረሻ ቀናትን ገልጿል። ምዕራፍ ፪–፲፩ የሰለሞን ህይወትን መዝግበዋል። ምዕራፍ ፲፪–፲፮ ስለሰለሞን ወራሾች፣ ሮብዓም እና ኢዮርብዓም ተናግረዋል። ኢዮርብዓም የእስራኤል መንግስት መከፋፈል ምክንያት ነበር። ደግሞም ሌሎች ንጉሶችም ተጠቅሰዋል። ምዕራፍ ፲፯–፳፩ የኤልያስ አገልግሎት ክፍልን፣ የእስራኤል ንጉስ አክዓብ ሲገስጽ፣ መዝግበዋል። ምዕራፍ ፳፪ አክዓብ እና የእስራኤል ንጉስ ኢዮሣፍጥ ሀይላቸውን አንድ ያደረጉበትን ከሶሪያ ጋር ጦርነትን መዝግቧል። ነቢዩ ሚክያስ ንጉሶችን በመቃወም ተነበየ።

መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ፣ ምዕራፍ ፩፡፩–፪፡፲፩ የኢልያስን ህይወት፣ በተጨማሪም በእሳት ሰረገላ ወደሰማይ ያረገበትን፣ ታሪክ ቀጥለዋል። ምዕራፍ ፪–፱ የኤልሳዕን የእምነት እና የታላቅ ሀይል አገልግሎትን ተናግረዋል። ምዕራፍ ፣ ስለንጉሱ ኢዩ እና የአክዓብ ቤትን እና የብዔል ቄሶችን እንዴት እንዳጠፋ ተናግሯል። ምዕራፍ ፲፩–፲፫ የኢዮአስምን ጻድግ ዘመነ መንግስት እና የኤልሳዕን ሞት መዝግበዋል። ምዕራፍ ፲፡–፲፯ በእስራኤል እና በይሁዳ ውስጥ፣ በብዙ ጊዜ በኃጢያተኛነት፣ ስለነገሱ የተለያዩ ንጉሶች ተናግረዋል። ምዕራፍ ፲፰ አሶር የእስራኤል አስር ጎሳዎችን ስለመማረካቸው መዝግቧል። ምዕራፍ ፲፱–፳ የይሁዳ ንጉስ የሕዝቅያስን እና የነቢዩ ኢሳይያስን ጻድቅ ህይወት መዝግቧል። ምዕራፍ ፳፩–፳፫ ስለንጉሶች ምናሴና ኢዮስያስ ተናግረዋል። በባህል መሰረት፣ ምናሴ ለኢሳይያስ ሰማዕት ሀላፊ ነበር። ኢዮስያስ በአይሁዳ መካከል ህግን የመሰረተ ጻድቅ ንጉስ ነበር። ምዕራፍ ፳፬–፳፭ ስለባቢሎን ምርኮ መዝግበዋል።

መፅሐፍ ቅዱስ። *ደግሞም ቀኖና*፣ ቅዱሳት መጻህፍት፣ ብሉይ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳን፣ አፖክርፋ፣ ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም

የኤፍሬም በትር፤ ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ—
የይሁዳ በትር *ተመልከቱ*

መለኮታዊ ራዕያትን የያዙ የእብራውያን እና የክርስቲያን ፅሑፎች የተሰበሰበበት። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባይብል ማለር “መፅሐፍት” ማለት ነው። መፅሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ የተሰሩ የብዙ ነቢያት እና የተነሳሱ ጸሬዎች ስራ ነው (፪ ጴጥ. ፩፡፳፩)።

የክርስትያን መፅሐፍ ቅዱስ እንደ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን የሚታወቁ ሁለት ክፍሎች አሉት። ብሉይ ኪዳን በጌታ በፍልስጥኤም አይሁዶች መካከል በስጋዊ አገልግሎቱ ጉዞ የሚጠቀሙባቸው ቅዱስ መጻሕፍትን የሚያካትት ነው። አዲስ ኪዳን በሐዋሪያት ዘመን የነበሩትን ፅሑፎች የያዘ እና እንደ አይሁዳዊ ቅዱሣት መጻህፍት አንድ አይነት ቅድስና እና ስልጣን እንዳለው የሚመለከት ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከብዙ መቶ አመቶች የተዘረጋ ከዜጋዊ ፅሁፎችን የተወሰጹ እና በሙሉ በእብራውያን ቋንቋ የተጻፉ ነበሩ፣ ይህም ሲሆን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የአንድ ትውልድ ስራዎች ናቸው እና በአብዛኛው የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ *ኪዳን* የሚባለው ቃል “ቃል ኪዳን” የሚለውን የእብራዊያን ቋንቋ ቃል ያመለክታል። የድሮው ቃል ኪዳንም እስራኤል የእግዚአብሔር ህዝብ ከስጋዊ ህይወት ጀምሮ የነበራቸውን የወንጌሉን ሙሉነት ባስወገዱበት ጊዜ ለሙሴ የተሰጠው ህግ ነው። አዲሱ ቃል ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ወንጌል ነው።

በእብራውያን መፅሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳን) መፅሐፎቹ በሶስት ክፍሎች የተከፋፈሉ ናቸው፥ ህግ፣ ነቢያት፣ እና ፅህፈቶች። ክርስቲያናት የሚጠቀሙበት መፅሐፍ ቅዱስ መፅሀፎችን እንደ ታሪካዊ፣ ግዋም፣ እና ትንቢታዊ በሚለው ርእስ መሰረት ይከፋፍሏቸዋል።

የአዲስ ኪዳን መጻህፍት በብዙ ጊዜ በዚህ መሰረት ናቸው፥ አራቱ ወንጌሎች እና የሐዋርያት ስራዎች፤ የጳውሎስ መልእክቶች፤ የያዕቆብ፣ የጴጥሮስ፣ የዮሐንስ፣ እና የይሁድ አጠቃላይ መልእክቶች፤ እና የዮሐንስ ራዕይ።

የጓሌኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስትያን አባላት ቅዱሣት መጻህፍትን ያወድሳሉና ያከብራሉ እናም በመጨረሻው ቀናት እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር ያለውን የግንኙነት ታሪክን ለማረጋገጥና ለመደገፍ ተጨማሪ ራዕዮችን ጌታ በመስጠት እንደሚቀጥል ያረጋግጣሉ።

የይሁዳ በትር (መፅሐፍ ቅዱስ) እና የዮሴፍ በትር (መፅሐፈ ሞርሞን) በጌታ እጅ አንድ ይሆናሉ፣ ሕዝ. ፴፯፡፲፭–፳።

የመፅሐፍ ቅዱስ እውነትነት በጓለኛ ቀን ቅዱሣት መጻህፍት ይረጋገጣል፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴–፴፡ መፅሐፍ ቅዱስ ከመፅሀፈ ሞርሞን ጋር የሀሰት ትምህርትን ለማዋረድ ይገናኛሉ፣ ፪ ኔፊ ፫፡፲፪። መፅሐፍ ቅዱስ! መፅሐፍ ቅዱስ! መፅሐፍ ቅዱስ አለን፣ ፪ ኔፊ ፳፱፡፣ ፣–፲። በመፅሐፍ ቅዱስ የሚያምኑት ሁሉ በመፅሐፈ ሞርሞን ያምናሉ፣ ሞር. ፯፡፳–፲።

ሽማግሌዎች በመፅሐፍ ቅዱስ እና በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ያሉትን የወንጌሌን መሰረታዊ መመሪያ ያስተምራሉ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፪።

በትክክል እስከተተረጎመ ድረስ፣ መፅሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፳።

መፅናት። *ደግሞም መፈተን፣ ፈተና፤ ትዕግስት፣ ጭንቀት ተመልከቱ*

ፈተና፣ ተቃዋሚነት፣ እና መከራ ቢኖርም ለእግዚአብሔር ትእዛዛት እውነት ለመሆን ፅኑ ውሳኔ ማድረግ።

እስከ መጨረሻ የሚጸና ይድናል፣ ማቴ. ፣፡፳፪ (ማር. ፣፣፡፣፣)። ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፣ ማር. ፬፡፣፣። ፍቅር በሁሉ ይጸናል፣ ፩ ቆሮ. ፣፣፡፣፯። አብርሐም ከታገሰ በኋላ ተስፋውን አገኘ፣ ዕብ. ፮፡፣፭።

እስከ መጨረሻ የሚፀኑ ከሆነ በመጨረሻው ቀን ከፍ ይደረጋሉ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፡፴፯። ለትዕዛዛቱ ታዛዥ ከሆናችሁ እናም እስከመጨረሻው ከፀናችሁ ትድናላችሁ፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፴፩ (አልማ ፭፡፣፣)። የክርስቶስን ቃል በመመገብ፣ እናም እስከመጨረሻው በመፅናት የምትቀጥሉ ከሆነ፣ የዘለዓለም ህይወት ይኖራችኋል፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፳ (፣ ኔፊ ፣፭፡፤ ት. እና ቃ. ፣፴፡፣)። ስሜን በራሱ ላይ የወሰደ፣ እናም እስከመጨረሻው የፀና፣ እርሱ ይድናል፣ ፣ ኔፊ ፳፣፡፣። በቤተክርስቲያኔ እስከመጨራሻው የሚጸና በአለቱ ላይ የምመሰርተው እሱን ነው፣ ት. እና ቃ. ፣፡፳፤። በእምነት የሚጸና አለምን ያሸንፋታል፣ ት. እና ቃ. ፳፣፡፳፣ ፴፣። ዙፋናት እና አለቅነት ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በጉብዝና ለጸኑትም ሁሉ ይሰጧቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፣፳፭፡፳፤።

መፈተን፣ ፈተና። *ደግሞም መፅናት፤ ነጻ ምርጫ፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

የሰው መልካምን ከመጥፎ በላይ የመምረጥ ችሎታ ፈተና፤ ኃጢያት ለመስራት እና እግዚአብሔርን ሳይሆን ሰይጣንን ለመከተል መባበል።

ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፣ ማቴ. ፮፡፣፣ (፣ ኔፊ ፣፣፡፣፣)። ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ እግዚአብሔር አይፈቅድም፣ ፩ ቆሮ. ፣፡፣፣። ኢየሱስ እንደ እኛ የተፈተነ ነው፣ ዕብ. ፬፡፣፡–፣፭። ፈተናን የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፣ ያዕ. ፩፡፣፪–፣፡።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙ የጠላት ፈተናዎች ሊያሸንፏቸው አይችሉም፣ ፤ ኤፌ ፲፭፡፳፬ (ሉሌ. ፭፡፲፪)። ሰው በአንዱ ወይም በሌለኛው ካልተሳሰር በስተቀር ለራሱ ማድረግ አይቻለውም፣ ፤ ኤፌ ፪፡፲፭–፲፮። ያለማቋረጥ እንድትተጉ እንዲሁም እንድትፀልዩ፣ ከሚቻላችሁ በላይም እንዳ ትፈተኑም፣ **አልማ** ፲፫፡፳፰። ማንኛውንም የዲያብሎስ ፈተና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት እንዲቋቋሙ አስተምራቸው፣ **አልማ** ፴፯፡፴፫። ዘወትር መፀለይ አለባችሁ፤ አለበለዚያ በዲያብሎስ ትፈተናላችሁ፣ ፤ ኤፌ ፲፰፡፲፭፣ ፲፰ (ት. እና ቃ. ፳፡፴፫፣ ፴፭፡፲፪፣ ፳፭፡፴፱)።

ወደ ፈተና እንዳትግባ ትዕቢትን ተጠንቀቅ፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፭። አዳም ለፈተና እራሱን አሳ ልፎ በመስጠቱ ምክንያት በሰይጣን ፈቅድ ተገዢ ሆነ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፱–፴፩።

ነገር ግን ወጣትነቴን በሚያስታውሱት እና በሀገ ራዊ ደስተኛ ጸባዬን በሚያውቁት ይህ አስገራሚ ላይሆን ይችላል፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፰።

መፈወስ፣ ፈውሶች። *ደግምም ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፣ መቀባት ተመልከቱ*

እንደገና በስጋ እናም በመንፈስ ደህና ማድረግ ወይም ጤና መስጠት። ቅዱሳት መጻህፍት የጌታ ንና የአገልጋዮቹን ተአምራት ፈውሶች ብዙ ምሳ ሌዎችን የያዙ ናቸው።

እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ፣ **ዘፀአ.** ፲፭፡፳፮። ናዕማን እራሱን በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ለሰባት ጊዜ ጠለቀ እናም ተፈወሰ፣ ፤ ነገሥ. ፭፡፩–፲፬። በእር ሱም ቀኑል እኛ ተፈወስን፣ **ኢሳ.** ፶፫፡፭ (ሞዛያ ፲፬፡፭)። የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች፡ ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል፣ **ሚል.** ፬፡፪።

ኢየሱስ ህማምን ሁሉ ፈወሰ፣ **ማቴ.** ፬፡፳፫ (ማቴ. ፱፡፴፭)። ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው፣ **ማቴ.** ፣፡፩። ልባቸው የተሰበ ረውም እንድፈውስ ልኮኛል፣ **ሉቃ.** ፬፡፣፳፰።

እነርሱም በእግዚአብሔር በግ ኃይል ተፈወሱ፣ ፤ ኤፌ ፲፩፡፴፩። በክርስቶስ ቤዛነት ካመንህ መፈ ወስ ትችላለህ፣ **አልማ** ፲፭፡፳፡ እርሱም እያንዳን ዳቸውን ፈወሳቸው፣ ፣ ኤፌ ፲፯፡፱።

ለመፈውስ በእኔ እምነት ያለው ይፈወሳል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፴፯። በስሜም የታመሙትን ይፈ ውሳሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፳፡፳፰።

በመፈወስ ስጦታዎችም እናምናለን፣ ኢ.አ. ፩፡፯።

መፋታት። *ደግምም ጋብቻ፣ መጋባት ተመልከቱ*

በህዝባዊ ወይም በቤተክርስቲያን ህግ መሰረት ከጋብቻ መለያየት። በአዲስ ኪዳን መሰረት፣ በሰዎች ልብ ደንዳናነት ምክንያት እግዚአብሔር መፋታትን በአንዳንድ ጉዳዮች ይፈቅዳል፤ ነገር ግን፣ ኢየ ሱስ እንደገለጸው፣ “ከመጀመሪያው እንዲህ አል ነበረም” (ማቴ. ፲፱፡፫–፲፪)። በአጠቃላይ ቅዱሣት መጻህፍት ከጋብቻ መፋታት እንዲወገዱ ምክር ይሰ ጣሉ እናም ባሎችና ሚስቶችን እርስ በርስ በጻድቅ እንዲፈቃቀሩም ይመክራሉ (፩ ቆሮ. ፯፡፣–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፪)።

መፍረድ፣ ፍርድ። *መኮነን፣ ኩነኔ ተመልከቱ*

መፍጠር፣ ፍጥረት። *ደግምም መጀመሪያ፤ ምድር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የመንፈስ ፍጥረት፤ የሰንበት ቀን ተመልከቱ*

ማደራጀት። እግዚአብሔር፣ በልጁ በኩል በመ ስራት፣ በፍጥረት ውስጥ ያሉትን ንጥረ ነገሮች በማ ደራጀት ሰማያትንና ምድርን ሰራ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ሰውን በመልካቸው ፈጠሩ (ሙሴ ፪፡፳፯–፳፯)።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፣ **ዘፍጥ.** ፩፡፩። ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፣ **ዘፍጥ.** ፩፡፳፯ (ሙሴ ፪፡፳፯–፳፯፣ አብር. ፬፡፳፯)።

ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ **ዮሐ.** ፩፡፫፣ ፣። በሰማይ ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል፣ **ቆላ.** ፩፡፲፮ (ሞዛያ ፫፡፴፣ ሔለ. ፲፬፡፲፪)። እግዚአብሔር አለማትን በልጁ ፈጠረ፣ **ዕብ.** ፩፡፪።

በመጀመሪያ ሰው ተፈጠረ፣ **ሞዛያ** ፣፡፳፯። ሰማ ያትንና ምድርን እንዲሁም ሁሉንም ነገሮች ፈጠ ርኩ፣ ፣ ኔፊ ፱፡፲፭ (ሞር. ፱፡፲፩፣ ፲፯)። ሁሉም ሰዎች በመጀመሪያ በራሴ ምስል ተፈጥረዋል፣ **ኤተር** ፣፡፲፭።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፱። ሰውን፣ ወንድንና ሴትን፣ በመ ልኩ ፈጠረ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፣፲፰።

ለመቁጠር የማይቻል አለሞችንም ፈጠርኩኝ፣ **ሙሴ** ፩፡፴፣። በአንድያ ልጄ ሰማይን ፈጠርኩኝ፣ **ሙሴ** ፪፡፩። እኔ እግዚአብሔር አምላክም የተና ገርኩባቸውን ነገሮች ሁሉ ከምድር ፊት በፍጥረ ታዊ አካል ከመፈጠራቸው በፊት በመንፈሳዊ አካል ፈጥሬአቸዋለሁ፣ **ሙሴ** ፣፡፩። እንደዚህ አይነት ሚልዮን ምድሮችን የአንተን ለፈጠርካቸው የመ ቆጠሪያ መጀመሪያም አይሆንም፣ **ሙሴ** ፯፡፴። አምላኮች ወረዱና ሰማያትን መሰረቱም ሰሩም፣ **አብር.** ፬፡፩።

ሙሌቅ። *ደግሞም ሴዴቅያስ ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን ንጉስ ሴዴቅያስ ልጅ (በ፳፪ቸ፱ ም.ዓ. አካባቢ)። መፅሐፍ ቅዱስ የሴ ዴቅያስ ልጆች በሙሉ እንደተገደሉ ይመዘግባል (፪ ነገሥ. ፳፭፡፣)፣ ነገር ግን መፅሐፈ ሞርሞን ሙሌቅ እንደዳነ ይገልጻል (ሔለ. ፰፡፳፩)።

ዛራሔምላ የሙሌቅ ትውልድ ነበር፤ ሞዛያ ፳፭፡፪። የሙሌቅ ህዝቦች ከኔፋውያን ጋር አንድ ሆኑ፣ ሞዛያ ፳፭፡፲፫። ጌታ ሙሌቅን በምድሪቱ በሰሜን በኩል አምጥቷቸዋል፣ ሔለ. ፮፡፲። ከሙሌቅ በስተቅር የሴዴቅያስ ወንድ ልጆች ሁሉ ተገድለው ነበር፣ ሔለ. ፰፡፳፩።

ሙሴ። *ደግምም መለወጥ—የክርስቶስ መለወጥ፤ አምስቱ መጻህፍት፤ አስሩ ቃላት፤ አሮን፣ የሙሴ ወንድም፤ የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

እስራኤላውያንን ከግብጻዊ ባርነት ያወጣ እና ከእግዚአብሔር የተገለጹ የሀይማኖት፣ የህብረተ ሰባዊ፣ እና የምግብ ህግጋት የሰጣቸው የብሉይ ኪዳን ነቢይ።

የሙሴ አገልግሎት ከስጋዊ ህይወቱ በጓላም የተ ዘረጋ ነው። ጆሴፍ ስሚዝ ከኤልያስ ጋር ወደ መቀየ ሪያ ተራራ ላይ እንደመጣ እና ለጴጥሮስ፣ ለያዕቆ ብና፣ ለዮሐንስ የክህነት ቁልፎችን እንደሰጠ አስ ተምሯል (ማቴ. ፲፯፡፫–፬፤ ማር. ፱፡፬–፱፤ ሉቃ. ፱፡፴፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፩)።

በሚያዝያ ፫፣ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ሙሴ በጆሴፍ ስሚዝ እና በኦሊቨር ካውደሪ በከርትላንድ ኦሀዮ ቤተመቅደስ ውስጥ ታየ እናም በእነርሱም ላይ እስ ራኤልን የመሰብሰብ ቁልፎችን ሰጠ (ት. እና ቃ. ፴፲፡፲፩)።

የጓለኛው ቀን ራዕይ ሙሴን በሚመለከት ብዙ ይናገራሉ። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል፣ እናም በትምህርት እና ቃል ኪዳ ኖች ውስጥ ስለአገልግሎቱ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፳–፳፯) እናም ከአማቱ ዮቶር ክህነትን እንደተቀበለ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፮)። እንማራለን።

የጓለኛው ቀን ራዕይ ደግሞም በእስራኤል ልጆች መካከል ስለነበረው አገልግሎቱ የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪክን ያረጋግጣል እናም የብሉይ ኪዳን የመጀ መሪያ አምስት መፅሐፎች ጸሀፊም እንደሆነ ያረጋ ግጣል (፩ ኔፊ ፭፡፲፩፣ ሙሴ ፩፡፴–፴፩)።

የፈርዖን ሴት ልጅ አዳነችው፣ ዘፀአ. ፪፡፩–፲፡ ወደ ምድያን ሸሸ፣ ዘፀአ. ፪፡፲፩–፳፪። የጌታ መላእክ ለእርሱ በሚነድ ቁጥቋጥ ታየው፣ ዘፀአ. ፫፡፩–፲፭። በግብጻውያን ላይ የሚመጣውን ወረር ሽኝ አሳወቀ፣ ዘፀአ. ፯–፲፩። ጌታ ፋሲካ መከበርን አስጀመረ፣ ዘፀአ. ፲፪፡፩–፴። የእስራኤል ልጆ ችን በቀይ ባህር አሻገረ፣ ዘፀአ. ፲፬፡፭–፴፩። በበ ረሀ ውስጥ ጌታ መና ላከ፣ ዘፀአ. ፲፮። በሞሬብ ድንጋይን መታ እናም ውሀም ከዚህ ፈለቀ፣ ዘፀአ. ፲፯፡፩–፯። ኢያሱ አመሌቅን እንዲያሸንፍ አሮን እና ሆር እጆቹን ከፍ አድርገው ያዙ፣ ዘፀአ. ፲፯፡፰–፲፭። ዮትር መከረው፣ ዘፀአ. ፲፰፡፲፫–፳፮። በሲና ተራራ ላይ ለጌታ መታየት ህዝቡን አዘጋጀ፣ ዘፀአ. ፲፱። ጌታ አስር ትእዛዛትን ገለጸለት፣ ዘፀአ. ፳፡፩–፲፯። እርሱ እና ሰባ ሽማግሌዎች እግዚአብ ሔርን አዩ፣ ዘፀአ. ፳፬፡፱–፲፩። የምስክር ጽላቶ ችን ሰበረ እናም የወርቅ ጥጃውን አጠፋ፣ ዘፀአ. ፴፪፡፲፱–፳። ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ተነ ጋገረ፣ ዘፀአ. ፴፫፡፱–፲፩።

ኢየሱስ በተቀየረበት ጊዜ ታየ፣ ማቴ. ፲፯፡፩–፲፫ (ማር. ፱፡፪–፲፫፣ ሉቃ. ፱፡፳፯–፴፯)።

ልክ እንደ ሙሴ ጠንካሮች እንሁን፣ ፩ ኔፊ ፪፡፪። ጌታ የሚያስነሳው እንደሙሴ አይነት የሆነው ነቢይ ክርስቶስ ነው፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳–፳፩ (ዘዳግ. ፲፰፡፲፩፣ ፲ ኔፊ ፳፡፳፫)።

እስራኤልን በራዕይ መራ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፲። ከልዑል መንፈሶች መካከል ታይቶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፻፴፯፡፵፩።

እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየ፣ ሙሴ ፩፡፪፣ ፴፩። እንደ አንድያ ልጁ ምሳሌ ነበር፣ ሙሴ ፩፡፮፣ ፲፫። ስለፍጥረት በሚመለከት ለእርሱ የተገለጹ ነገ ሮችን ይጽፋል፣ ሙሴ ፪፡፩።

መፅሐፈ ሙሴ፣ በየታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ የኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ ሰባት ምዕራፎችን ጆሴፍ ስሚዝ በመነሳሳት የተረጎማቸው የሚገኝ በት መፅሐፍ።

ምዕራፍ ፩ ሙሴ የደህንነት አላማን በሙሉ የገ ለፀለትን እግዚአብሔር ያየበትን ራዕይ ይገልጻል። ምዕራፍ ፪–፭ የፍጥረት እና የሰው ውድቀት ታሪክ ናቸው። ምዕራፍ ፮–፯ የሔኖክ እና በምድር አገል ግሎቱ ራዕይን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፰ የኖኅ እና የታላቅ ጎርፍ ራዕይን የያዘ ነው።

የሙሴ አምስት መጻህፍት፣ ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘዳግም፣ *ተመልከቱ* የብሉይ ኪዳን የመጀመ ሪያ አምስት መጻህፍት የሙሴ መፅሐፎች ተብለው ይጠራሉ። ኔፊ ከላባን የወሰደው የናስ ሰሌዳ የሙሴ መጻህፍትን የያዘ ነበር (፩ ኔፊ ፫፡፲፩)።

ኔፊ በሙሴ መጻህፍቶች ውስጥ የተጻፉትን ብዙ ነገሮችን አነበበ፣ ሙሴ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፳፫።

ሙሽራ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደ ወንድ ሙሽራ ተመስሏል። ቤተክርስትያኗ እንደ ሴት ሙሽራዋ ተመስላለች።

አስር ቆነጃጅት መሽራውን ለመቀበል ወጡ፣ ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫። ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፣ ዮሐ. ፫፡፳፯–፴። ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው፣ ራዕ. ፲፱፡፭–፲።

በሙሽራው መምጫ ጊዜ ዝግጁ ሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፯። ለሙሽራው መምጫ ተዘ ጋጁ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፫።

ሙዚቃ። ደግሞም መዘመር፤ መዝሙር
ተመልከቱ

ከመፅሐፍ ቅዱስ ጊዜዎች ጀምሮ ደስታን፣ ሙገሳን፣ እና ማምለክን ለመግለጽ የሚጫወቱት ቃና ዎች እና የሙዚቃ ምቶች (፪ ሳሙ. ፮፡፭)። ይህም የጸሎት አይነት ለመሆን ይችላል። መዝሙረ ዳዊት በቀላል ቃናዎች እና በመሳሪያዎች እጀባ የተዘመሩ ነበሩ።

የአሮን እና የሙሴ እኅት ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች፤ እናም እርሷና ሴቶችም ጨፈሩ፣ **ዘፀአ.** ፲፭፡፳ ። መዘምራንም የነበሩት ሌዋውያን ሁሉ፥ ጸናጽልና በገና መሰንቆም እየመቱ ነበር፣ ከእነር ሱም ጋር መቶ ሀያ ካህናት መለከት ይነፉ ነበር፣ ፪ ዜና ፭፡፲፪ ።

ኢየሱስና ሐዋሪያት ከመጨረሻው እራት በኋላ መዝሙርም ዘመሩ፣ **ማቴ.** ፳፮፡፴ ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ አስተ ምሩ፣ **ቄላ.** ፫፡፲፮ ።

የቢዛነት የፍቅር ዜማ ለመዘመር ተሰምቷችኋል፣ **አልማ** ፭፡፳፮ ።

የጌታ ነፍስ በልብ መዝሙር ትደሰታለች፣ አዎ የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጸሎት ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡፲፪ ። ጌታን በዘፈን፣ በመዝሙ ቃ፣ እና በእስክ ስታ አምልኩ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፯፡፳፯ ።

ሚልክያስ

በ፱፻፴ ም.ዓ. አካባቢ የጻፈና የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ።

ትንቢተ ሚልክያስ፣ የሚልክያስ መፅሐፍ ወይም ትንቢት የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ መፅሐፍ ነው ። ይህም የሚቀጥሉት አራት ጭብጥ መልእክቶች ነበሩት፥ (፩) የእስራኤል ኃጢያቶች—ሚልክያስ ፩፡፲–፪፡፲፯ ፣ ፫፡፰–፬፡ ፣ (፪) ታዛዥ ባለመሆናቸው ምክንያት በእስራኤል ላይ የሚመጣው ፍርድ—ሚልክያስ ፩፡፲፬ ፣ ፪፡፪–፫ ፣ ፲፪ ፣ ፫፡፭ ፣ (፫) ለታ ዛዥነት ቃል ኪዳን—ሚልክያስ ፫፡፲–፲፪ ፣ ፲፯–፲፰ ፣ ፬፡፪–፫ ፣ እና (፬) እስራኤልን በሚመለከት ትንቢ ቶች ሚልክያስ ፫፡፩–፭ ፣ ፬፡፩ ፣ ፭–፮ (ት. እና ቃ. ፪ ፣ ፲፳፰ ፣ ፲፯ ፣ ፳.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፯–፴፱)።

በትንቢቶቹ ውስጥ፣ ሚልክያስ ስለመጥምቁ ዮሐንስ (ሚል. ፫፡፩ ፣ ማቴ. ፲፩፡፲)፣ ስለአስራት ህግ (ሚል. ፫፡፯–፲፪)፣ ስለጌታ ዳግም ምፅዓት (ሚል. ፬፡፭)፣ እናም ስለኤልያስ መመለስ (ሚል. ፬፡፭–፮ ፣ ት. እና ቃ. ፪ ፣ ፲፳፰ ፣ ፲፯ ፣ ፳.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፯–፴፱) ጻፈ። አዳኝ የሚልክያስን ምዕራፍ ፫ እና ፬ ለኔፋውያን ጠቀሰ (፫ ኔፊ ፳፬–፳፭)።

ሚሳቅ። *ደግሞም ዳንኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ሶስቱ የእስራኤል ወጣ ቶች ሲድራት፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ከዳንኤል ጋር ወደ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት የተ ወሰዱት ነበሩ። የሚሳቅ ዕብራውያን ስም ሚሳኤል ነበር። አራቱ ወጣት ሰዎች ከንጉሱ ስጋና ወይን በመካፈል እራሳቸውን አንበክልም አሉ (ዳን. ፩)። ሲድራት፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ወደ እሳት እቶን ተወርውረው ነበር እናም በተአምራት ድነው ነበር (ዳን. ፫)።

ሚስጥራዊ ህብረት። የሚስጥር ስብሰባ
ተመልከቱ

ሚስጥራዊ ውህደት። የሚስጥር ስብሰባ
ተመልከቱ

ሚካኤል። *ደግሞም አዳም፤ የመላእክት አለቃ ተመልከቱ*

ከምድራዊ ህይወት በፊት አዳም ይታወቅበት የነበረው ስም። እርሱም የመላእክት አለቃ ተብሎ ይጠራ ነበር። በአይሁዳ ቋንቋ ስሙ "እንደ እግዚ አብሔር አይነት የሆነ" ማለት ነው ።

ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል፣ ዳንልን ለመርዳት መጣ፣ ዳን. ፲፡፲፫ ፣ ፳፩ (ት. እና ቃ. ፹፰፡፲ ፣ ፲፯)። በመጨረሻው ቀናት ታላቁ አለቃ ሚካ ኤል ይነሣል፣ ዳን. ፲፪፡፩ ።

የመላእክት አለቃ ሚካኤል ከዲያብሎስ ጋር ተከ ራከረ፣ ይሁዳ ፩፡፱ ። ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶ ውን ተዋጉ፣ ራዕ. ፲፪፡፯ (ዳን. ፯)።

ሚካኤል አዳም ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፯፡፲፩ (ት. እና ቃ. ፻፯፡፹–፹፯ ፣ ፻፳፰፡፳፩)። የጌታ የመላእክቶቹ አለቃ ሚካኤል መለክቱን ይነፋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፳፯ ። ሚካኤል ሰራዊቶቹን ይሰ በስባል እናም ከሰይጣን ጋር ይዋጋል፣ **ት. እና ቃ.** ፸፰፡፲ ፣ ፲፲፪–፲፲፭ ። የሚካኤል ድምፅም ዲያብሎስን ሲመረምር ተሰምቶ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፰፡፳ ።

ሚክያስ

የብሉይ ኪዳን ነቢይ ። ከይሁዳ ሀገር ውስጥ፣ ከሞሬሼትጌት ተወላጅ ነበር፣ እናም ሕዝቅያስ ንጉስ በነበረበት ጊዜ ተነበየ (ሚክ. ፩፡፩–፪)።

ትንቢተ ሚክያስ፣ ከብሉይ ኪዳን መፅሐፎች ውስጥ መሲህ የሚወለድበት ከተማ ቤተልሔም እንደሆነ የሚገልጸው የሚክያስ መፅሐፍ ብቻ ነው (ሚክ. ፭፡፪)። በመፅሐፉ ውስጥ ጌታ ህዝቡን መከረ እናም ለእነርሱ ያደረገውን የበፊት በጎ ድርጊቱን ዘረዘረ፤ ከእነርሱም ፍትህ፣ ምህረት፣ እና ትሁት ነትን ጠየቀ (ሚክ. ፮፡፰)።

ማህበርተኛነት። ጓደኝነት *ተመልከቱ*

ማለቂያ የሌለው። *ደግሞም እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልከቱ*

ዘለአለማዊነቱን የሚያሳይ ከእግዚአብሔር

ስሞች አንዱ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፲–፲፪፣ ሙሴ ፭፡፮፣ ፯፡፴፭)።

ማመን። መታመን ተመልከቱ

ማመንዘር። *ደግምም ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፣ ንጹህነት፣ ዝሙት መፈጸም፣ ግብረ ሰዶማዊ ጸባይ ተመልከቱ*

የወንዶች እና ሴቶች ህጋዊ ያልሆነ የፍትወተ ስጋ ግንኙነት። ምንም እንኳን ማመንዘር ያገባ ወንድ ወይም ሴት ከሚስቱ ወይም ከባሏ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር የፍትወተ ስጋ ግንኙነት ስለማድረግ ሀሳብ የሚያቀርብ ቢሆንም፣ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ስላልተጋቡትም ሀሳብ ያቀርባል።

አንዳንዴ ማመንዘር ከጌታ መንገዶች ወይም የሁሉም ህዝቦች ክህደትን ለማመሳሰል ይጠቀሙበታል (ዘኍል. ፳፭፡፩–፪፣ ኤር. ፫፡፮–፣ ሕዝ. ፲፮፡፲፭–፴፱፣ ሆሴ. ፬)።

ዮሴፍ ይህን ታላቅ ትልቅ ክፉ ነገር አያደርግም፣ እና በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያት አይሰራም፣ **ዘፍጥ.** ፴፱፡፯–፣፲፪። አታመንዝር፣ **ዘፀአ.** ፳፡፣፲፬።

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፣ **ማቴ.** ፭፡፳፰። አመንዝሮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ የእግዚአብሔርን መንግሥት እይወርሱም፣ **፩ ቆሮ.** ፮፡፱–፣። ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል፣ **ዕብ.** ፣፲፫፡፬።

ማመንዘር የንፁሃንን ደም ከማፍሰስ ወይም መን ፈስ ቅዱስን ከመካድ በቀር ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ይበልጥ አስከፊ ነው፣ **አልማ** ፴፱፡፣–፳።

የሚያመንዝር፣ እናም ንሰሃ የማይገባ፣ ወደ ውጭ ይጣላል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፳፣–፳፯፣። ማንም በልባቸው ካመነዘሩ፣ መንፈስ አይኖራቸውም፣ **ት. እና ቃ.** ፳፣፡፡፡–፲፲፪።

ማምለክ። *ደግምም እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልከቱ*

ፍቅር፣ አምልኮ፣ አገልግሎት፣ እና ለእግዚአብ ሔር ታማኝነት (ት. እና ቃ. ፳፡፣፲፱)። አምልኮ በተ ጨማሪም ጸሎት፣ ጾም፣ የቤተክርስቲያን አገልግ ሎት፣ በወንጌል ስነስርዓቶች መሳተፍ፣ እና ለእ ግዚአብሔር ያለን ታማኝነት እና ፍቅር የማሳየት ሌሎች ልብዶች ነው።

ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፣ **ዘፀአ.** ፳፡፣ (ዘፀአ. ፴፪፡፩–፳፡፣ ፣፲፱–፴፭፣ መዝ. ፹፭፡፱–፱)።

ለአብ በመንፈስና በእውነት ስገዱ፣ **ዮሐ.** ፬፡፳፭፣። ሰማይንና ምድርንም ለሠራው ስገዱለት፣ **ራዕ.** ፣፲፬፡፣ (ት. እና ቃ. ፣፲፴፣፡፴፣–፴፱)።

እርሱን በሙሉ ኃይላችሁ፣ አእምሮአችሁ እና ጉልበታችሁ ማምለክ አለባችሁ፣ **፪ ኔፊ** ፳፭፡፳፱። በክርስቶስ አምነዋል እናም አብንም በስሙ አምል ከዋል፣ **ያዕቆ.** ፬፡፭። ሰዎች በሁሉም በታዎች መጸ ለይ እና ማምለክ እንደሚገባቸው ዜኖስ አስተማረ፣ **አልማ** ፴፣፡፡–፣፲፭። ላችሁበት ስፍራ ሁሉ በመን ፈስና በእውነት እግዚአብሔርን አምልኩ፣ **አልማ** ፴፬፡፴፣፡፡። ህዝቡም በኢየሱስ እግር ስር ወደቁ፣ እናም አመለኩት፣ **፣ ኔፊ** ፣፲፭፡፣፲፯።

ሁሉም ሰው ንስሀ መግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማመን፣ እናም አብን በእርሱ ስም ማምለክ አለ ባቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፣፳፱። እነዚህን አባባል የም ሰማችሁ እንድትረዱ እና እንዴት እንደምታመልኩ እንድታውቁ፣ እና ምን እንደምታመልኩ እንድታ ውቁ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፣፣፣፡፣፲፱።

ይህን አንድ እግዚአብሔር አመልካለሁ፣ **ሙሴ** ፭፡፣፲፪–፳፡ ሁሉን የሚችለው እግዚአብሔርን የማ ምለክ መብት እንዳለን እናረጋግጣለን፣ **እ.አ.** ፭፡፣፲፭።

ማሰላሰል። *ደግምም ራዕይ፣ ጸሎት ተመልከቱ*

በቅዱስ መጻህፍቶች እና በሌሎች የእግዚአብሔር ነገሮች መመሰጥ እና በጥልቅ ማሰብ። ከጸሎት ጋር ሲጣመር፣ የእግዚአብሔር ነገሮችን ማሰላሰል ራዕ ይን እና ማስተዋልን ያመጣል።

ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር፣ **ሉቃ.** ፪፡፣፲፱።

በልቤ እያሰላሰልኩ ተቀምጬ ሳለሁ ተወሰድኩ፣ **፩ ኔፊ** ፣፲፭፡፩። ልቤ ታሰላስላቸዋለች፣ **፪ ኔፊ** ፬፡፣፲፭። ኔፊ ጌታ ያሳየውን ነገሮች በልቡ እያሰላሰለ ወደ ራሱ ቤት መንገዱን አቀና፣ **ሔለ.** ፣፡፪–፣። ወደ ቤታ ችሁ ሂዱ፣ እናም ስለተናገርኳችሁ ነገሮች አሰላ ስሉ፣ **፣ ኔፊ** ፣፲፣፡፣። ጌታ ምን ያህል መሃሪ እን ደነበረ አስታውሱ፣ እናም በልባችሁ ይህን አሰላ ስሉ፣ **ሞሮኒ** ፣፡፣።

ስለተቀብልካቸው ነገሮች አሰላስል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፡፣። እነዚህ ነገሮች ላይ እያሰላሰልን እያለን፣ ጌታ የመረጃ አይኖቻችንን ነካን፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፣፲፱። በቅዱሣት መጻህፍት ላይ በክፍሌ ቁጭ ብዬ አሰላ ስል ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፣፲፴፯፡፩–፣፲፩።

ይህን ደጋግሜ አሰብኩበት፣ **ጆ.ስ.—ታ.** ፩፡፣፲፪።

ማሰናከል። *መበደል ተመልከቱ*

ማሳደድ፣ መሳደድ። *ደግምም ጭንቀት ተመልከቱ*

ሌሎችን በእምነታቸው ወይም በማህበራዊ ሁኔ ታቸው ምክንያት ሌሎችን ማስጨነቅ ወይም ማሳ ዘን፣ ማስፈራራት ወይም መጨቆን።

ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፣ **ማቴ.** ፭፡፣፲ (፣ ኔፊ ፣፲፪፡፣)። ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፣ **ማቴ.** ፭፡፴፬ (፣ ኔፊ ፣፲፪፡፴፬)።

ሀብታም በመሆናቸው፣ ትሁቶችን ያሳድዳሉ፣ ፤ ኤፌ ፱፡፴ (፤ ኤፌ ፭፡፲፪–፲፫)። የስደት መከራ ቢደርስባቸውም ክርስቶስን ወደ ፊት የሚመለከቱ ጻድቃኖች የማይጠፉት ናቸው፣ ፤ ኤፌ ፭፡፭–፮።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለአንተ ልምድ ይሰጡሀል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፭–፮።

ማስተማር፣ አስተማሪ። ደግምም መንፈስ ቅዱስ ተመልከቱ

ለሌሎች፣ በልዩም ስለወንጌል እውነት፣ እውቀትን መስጠት እናም ወደ ጽድቅ መምራት። ወንጌልን የሚያስተምሩ በመንፈስ መመራት ይገባቸዋል። ሁሉም ወላጆች በቤተሰቦቻቸው መካከል አስተማሪዎች ናቸው። ቅዱሳን ከጌታ እና ከእርሱ መሪዎች ትምህርቶችን መፈለግ እና መቀበል ይገባቸዋል።

ልጆቻቸውንም ያስተምሩ፣ ዘዳግ. ፬፡፭–፱። በትጋት ለልጆችህም አስተምረው፣ ዘዳግ. ፮፡፯ (ዘዳግ. ፲፩፡፲፭–፲፱)። ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ ምሳ. ፳፪፡፮። ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፣ ኢሳ. ፶፬፡፲፣ (፣ ኔፊ ፳፪፡፲፣)።

መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን፣ ዮሐ. ፣፡፪። እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን፣ ሮሜ ፪፡፳፩።

አባቴ ከሚያውቃቸው በመጠኑ ተማርኩ፣ ፤ ኔፊ ፩፡፩ (ኢኖስ ፩፡፩)። ካህናትና መምህሮች በትጋት ያስተምሩ ወይም የህዝቡን ኃጢኣት በራሳችን ላይ ይቀበላሉ፣ ያዕቆ. ፩፡፲፭–፲፱። እኔን አዳምጡ፣ እናም ትሰሙኝ ዘንድ ጆሮአችሁን ክፈቱ፣ ሞዛያ ፪፡፱። ፣ልጆቻችሁ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ እንዲሁም አንደኛው ሌላኛውን እንዲያገለግል ታስተምሯቸዋላችሁ፣ ሞዛያ ፬፡፲፭። ማንም የእናንተ መምህርም ሆነ አገልጋይ እንዲሆን አትፍቀዱ፣ ሞዛያ ፳፣፡፲፬። ጌታ የሰው ልጆችን ቃልን ለመቀበል ልባቸውን እንዲያዘጋጁ በምድሪቱ ላይ ሁሉ መንፈሱን አፈሰሰ፣ አልማ ፲፯፡፲፯። በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን አስተማሩ፣ አልማ ፲፯፡፪–፣። በእናቶቻቸውም ተምረዋል፣ አልማ ፶፯፡፳፯ (አልማ ፶፯፡፳፭)።

ጥበብን እስከፈለጉ ድርስ እንዲያስተምሯቸው፣ ት. እና ቃ. ፭፡፳፭። በሾምኳችሁ ስልጣን መሰረት እርስ በእርስ ተማማሩ፣ ት. እና ቃ. ፴፡፳፡፳፣። በመጻሐፍ ቅዱስ እና በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኙትን የወንጌሌን መርሆች ያስተምራሉ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፪። ከበላይም መማር ይገባቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፵፣፡፲፭–፲፯። ወላጆች ልጆቻቸውን ያስተምራሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፡፳፭–፳፡፳። እርስ በራስ የመንግስትን ትምህርት አስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፡፳፡፫–፫፡፳፣ ፣፲፡፳። ከመካከላች ሁም አስተማሪ መድቡ፣ ት. እና ቃ. ፲፡፳፡፣፲፭፪። ልጆችህን ብርሀን እና እውነት አላስተማርክም፣ እና ይህም የስቃይህ ምክንያት ነው፣ ት. እና ቃ. ፣፣፡፡ ፣፣፪–፣፣፪።

እነዚህን ነገሮች ለልጆቻችሁ አስተምሩ፣ ሙሴ ፮፡፣፣፮–፳፭።

በመንፈስ ማስተማር፣ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፡ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም፣ ማቴ. ፣፡፣፣–፭። መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፪። ወንጌሉ የሚሰበከው በመንፈስ ሀይል ነው፣ ፤ ቆሮ. ፪፡፩–፣፣፡፡

የተናገረውም በሀይል እና ከእግዚአብሔር በመጣ ስልጣን ነው፣ ሞዛያ ፣፣፡፡ ፭–፱ (አልማ ፲፯፡፣፡ ሔለ. ፭፡፲፯)።

ሰዎችን ለማሳመኛ መንፈሴን ትቀበላለህ፣ ት. እና ቃ. ፣፩፡፳፭፪። በአጽናኙ የምታስተምራቸው ነገሮች ሁሉ ትሰማለህ፣ ት. እና ቃ. ፳፳፡፩ (ት. እና ቃ. ፱፪፡፱)። መንፈስን ካልተቀብላቹ አታስተምሩም፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፣፡ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፮)። በመንፈሴ ሀይል ለሰዎች ልጆች አስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፵፣፡፣፭። ሽማግሌዎች ወንጌልን በመንፈስ ያስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፯፡፣፣–፳፪። በዚያች ሰዓት የምትናገሩት ይሰጣችኋል፣ ት. እና ቃ. ፲፡፩፡፲፭ (ት. እና ቃ. ፣፡፩–፳)።

ማስተዋል። ደግምም እውቀት፣ እውነት፣ ጥበብ ተመልከቱ

እውቀትን ማግኘት ወይም በህይወት እንዴት እንደሚጠቀሙበት ከማወቅ በተጨማሪ፣ የአንዳንድ እውነትን ትርጉም መገንዘብ።

በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፣ ምሳ. ፣፡፭። ከሀብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ፣ ምሳ. ፩፡፯።

ኢየሱስ በምሳሌ ተናገረ እናም አንዳንዱ አልገባቸውም፣ ማቴ. ፲፣፡፣፪–፣፣፯። ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፭።

እነዚህን ቃላት መረዳት ካልቻላችሁ፣ ይህም ስላልጠየቃችሁ፣ ፤ ኔፊ ፲፭፡፲ (፣ ኔፊ ፲፯፡፣)። መዝገቦቹ የተጠበቁት እንድናነባቸው እና እንድናስተውላቸው ነው፣ ሞዛያ ፩፡፪–፭። ባለማመናቸው የእግዚአብሔርን ቃል ሊረዱት አልቻሉም ነበር፣ ሞዛያ ፳፯፡፣፡ ትክክለኛ ማስተዋል የነበራቸው፣ አልማ ፲፯፡፪–፣። ቃሉ ግንዛቤዬን ያበራልኝ ጀምሯል፣ አልማ ፴፪፡፳፭።

እንዲገባችሁም እንወቃቀስ፣ ት. እና ቃ. ፣፡፣–፣፪፣ ፣፣፩–፳፣። ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያስተውሉ አስተምሯቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፳፡፳፭። የእግዚአብሔር ስራዎች እና ሚስጥሮች ለመገባት የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፣ ት. እና ቃ.

ᎾᏬᏕ፡ᏥᏁᏕ–ᏥᏁᏕ። ይጣን ልቦቻቸውን ከእውነቱ ለማዞር ይፈልጋል፣ ት. እና ቃ. ᏬᏥᏂ፡Ꭲ። የክርስቶስ ብርሀን የምትረዱበትን ያነሳሳል፣ ት. እና ቃ. ᏠᏥᏂ፡ᏁᏕ።

ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ። *ደግሞም መጠበቅ፣ ጠባቂ ተመልከቱ*

ማስታወቂያ ወይም ማስጠንቀቂያ መስጠት ነቢያት፣ መሪዎች፣ እና ወላጆች ሌሎችን ለጌታና ለሚ ያስተምረው ታዛዥ እንዲሆኑ ያስጠነቅቃሉ።

ያዕቆን የኔፊን ህዝብ ስለእያንዳንዱ አይነት ኃጢያት ማስጠንቀቂያ ሰጠ፣ ያዕቆ. ᏅᏁᏕᏥ።

የማስጠንቀቂያው ድምጽ ለሁልም ህዝብ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ᏕᏁᏕ። ስብከታችሁ የማስጠንቀቂያ ድምጽ ይሁን፣ ት. እና ቃ. ᏬᏕᏂ፡ᏬᏕᏕ። ይህ የማስጠንቀቂያ ቀን ነው፣ ት. እና ቃ. ᏕᏅᏂ፡ᏭᏕᏕ። የተጠነቀቀ ሰው ጎረቤቱን ማስጠንቀቁ አስፈላጊ ነው፣ ት. እና ቃ. ᏥᏕᏂ፡ᏥᏕᏕ። በራዕይ ይህን የጥበብ ቃል ለእናንተ በመስጠት አስጠንቅቄአችኋለሁ፣ እናም ከቀደም ጊዜ በፊትም አስጠነቅቄአች ኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ᏥᏅᏅ፡ᏅᏕ።

ማረጋገጫ። *እጅን መጫን ተመልከቱ*

ማሪያም። *ደግሞም ሙሴ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሙሴ እህት (ዘኁል. ᏕᏁᏕ፡ᏭᏅᏕ)።

የደንገል ሣጥንን ትጎበኘው ነበር፣ ዘፀአ. ᏅᏕ፡ᏕᏕ–ᏕᏕ። በከበሮ ሴቶችን መራች፣ ዘፀአ. ᏥᏕ፡ᏕᏕ–ᏕᏕᏕ። በሙሴ ላይ አጉረመረመች እናም በለምፅ ተመታች፣ ከእዚያም ተፈወሰች፣ ዘኁል. ᏥᏅᏕ፡ᏕᏕ–ᏥᏕᏕ (ዘዳግ. ᏕᏕᏕ፡ᏅᏕ)።

ማራከስ። *ደግሞም መስደብ ተመልከቱ*

ለቅዱስ ነገሮች ክብር አለመኖር ወይም ንቀት።

የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ ዘፀአ. ᏕᏁᏕ (ᏅᏕᏕ ᏕᏕᏕ፡ᏬᏅᏅ፣ ሞዛያ ᏥᏅ፡ᏥᏕᏕ፣ ት. እና ቃ. ᏅᏬᏕ፡ᏕᏕᏕ)። የአባቶቻችንን ቃል ኪዳን ለምን እንነቅፋለን፣ ሚል. ᏅᏁᏕ።

ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፣ ማቴ. ᏥᏅᏕ፡ᏬᏕᏕ–ᏬᏕᏕ። ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፣ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም፣ ያዕ. ᏅᏁᏕ።

ቃላቶቻችን ይፈርዱብናል፣ **አልማ** ᏥᏅᏕ፡ᏥᏕᏕ (ሞዛያ ᏕᏕ፡ᏬᏕ)።

ሁሉም ሰዎች እንዴት ስሜን በከንፈሮቻቸው እንደሚይዙ ይጠንቀቁ፣ ት. እና ቃ. ᏕᏅᏅ፡ᏕᏕᏕ–ᏕᏕᏅ።

ማርሽ፣ ቶማስ ቢ

በᏥᏕᏅᏬ (እ.አ.አ.) ከቤተክርስቲያኗ ዳግም መመለስ በኋላ የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን የመጀመሪያ ፕሬዘደንት። አስራ ሁለቱን በሚመለከት የመንግስትን ቁልፍ ይዞ ነበር (ት. እና ቃ. ᏅᏥᏅ፡ᏥᏅ) እናም፣ በᏥᏕᏅᏬᏕᏕ (እ.አ.አ.) የጌታን ቃል እንዲያትም ታዝዞ ነበር (ት. እና ቃ. ᏅᏥᏕ፡Ꮕ)። ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ክፍል ᏬᏅ ስለእርሱ የተሰጠ ነበር። ማርሽ በᏥᏕᏅᏬᏬ (እ.አ.አ.) ከቤተክርስቲያኗ ተወገዘ ነገር ግን በሐምሌ ᏥᏕᏅᏬᏬ (እ.አ.አ.) እንደገና ተጠመቀ።

ማርቆስ። *ደግሞም ወንጌሎች ተመልከቱ*

የማርያም ልጅ ነበር (የሐዋ. ᏥᏅ፡ᏥᏅ)፤ ደግሞም የበርናባስ ዘመድ ሳይሆን አይቀርም (ቄላ. Ꮕ፡Ꭲ)። ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር በመጀመሪያው ጉዞ አቸው ከኢየሩሳሌም ሄደ እናም በጴርጌም ከእነርሱ ተለየ (የሐዋ. ᏥᏅ፡ᏕᏕ፣ ᏥᏅ፡Ꭴ፣ ᏥᏅ)። በጓላም ከበርናባስ ጋር ወደ ቆጵሮስ ሄደ (የሐዋ. ᏥᏕ፡ᏬᏕ–ᏬᏅᏅ)። በሮሜ ውስጥ ከጳውሎስ ጋር ነበር (ቄላ. Ꮕ፡Ꭲ፤ ፊልሞ. Ꭴ፡ᏕᏅ)፣ እናም ከጴጥሮስ ጋር በባቢሎን (ምናልባት በሮሜም) ውስጥ ነበር (Ꭴ ጴጥ. Ꭴ፡ᏥᏅ)። በመጨረሻም ከጢሞቴዎስ ጋር በኤፌሶን ነበር (ᏅᏅ ጢሞ. Ꮕ፡ᏥᏅ)።

የማርቆስ ወንጌል፣ የአዲስ ኪዳን ሁለተኛ መፅሐፍ። የማርቆስ ወንጌል ምናልባት የተጻፈው በጴጥሮስ አመራር ስር ነበር። አላማው ጌታን በሰዎች መካከል እንደኖረና እንደሰራ የእግዚአብሔር ልጅ ለመግለፅ ነበር። ማርቆስ፣ በሀይል እና በትሁትነት፣ ሌሎች ኢየሱስን እንዴት እንደተመለከቱት ገለጸ። ባህል እንደሚገልጸው ከጴጥሮስ ሞት በኋላ፣ ማርቆስ ግብፅን ጎበኝ፣ የእስክንድርያን ቤተክርስቲያን አደራጀ፣ እናም በሰማዕትነት ሞተ።

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለጹትን የአዳኝ ህይወት ድርጊቶችዝርዝር፣ የወንጌሎች ስምምነትን ተመልከቱ።

ማርታ። *ደግሞም አልዓዛር፤ የቢታንያ ማርያምን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአልዓዛር እና የማርያም እህት (ሉቃ. Ꭲ፡ᏬᏕ–ᏬᏅᏅ፤ ዮሐ. ᏥᏅ፡Ꭴ–ᏬᏥᏅ፤ ᏥᏅᏅ፡Ꮕ)።

ማርያም፣ የማርቆስ እናት። *ደግሞም ማርቆስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የማርቆስን ወንጌል የጻፈው የዮሐንስ ማርቆስ እናት (የሐዋ. ᏥᏅ፡ᏥᏅ)።

ማርያም፣ የኢየሱስ እናት። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ዮሴፍ፣ የማርያም ባለቤት ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በስጋ ልጁ ለሆነው እናት እንድትሆን በእግዚአብሔ አብ የተመረጠች ድን

ግል። ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ፣ ማርያም ሌሎች ልጆች ወለደች (ማር. ፮፡፫)።

እርሷ ለዮሴፍ ታጨች፣ **ማቴ.** ፩፡፲፰ (ሉቃ. ፩፡፳፯)። ዮሴፍ ማርያምን እንዳይፈታ ወይም ከታጨችበት እንዳይለቃት ተነገረው፣ **ማቴ.** ፩፡፲፰–፳፩። ሰብአ ሰገል ማርያምን ጎበኙ፣ **ማቴ.** ፪፡፲፩። ማርያም እና ዮሴፍ ከሕጻኑ ኢየሱስ ጋር ወደ ግብፅ ሸሹ፣ **ማቴ.** ፪፡፲፫–፲፬። ከሄሮድስ ሞት በኋላ፣ ቤተሰቡ ወደ ናዝሬት ተመለሱ፣ **ማቴ.** ፪፡፲፱–፳፫። መልአኩ ገብርኤል ጎበኛት፣ **ሉቃ.** ፩፡፳፯–፴፯። ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ጎበኘች፣ **ሉቃ.** ፩፡፴፯፣ ፴–፴፭። ማርያም ለጌታ የምስ ጋና መዝሙር አቀረበች፣ **ሉቃ.** ፩፡፴፯–፴፭። ማርያም ከዮሴፍ ጋር ወደ ቤተ ልሔም ሄደች፣ **ሉቃ.** ፪፡፬–፭። ማርያም ኢየሱስን ወለደች፥ በግ ርግም አስተኛችው፣ **ሉቃ.** ፪፡፮። እረኞች ህጻኑ ክርስቶስን ለመጎብኘት ወደ ቤተልሔም ሄዱ፣ **ሉቃ.** ፪፡፲፮–፳። ማርያም እና ዮሴፍ በኢየሩሳ ሌም ውስጥ ወደ ቤተመቅደስ ኢየሱስን ወሰዱ፣ **ሉቃ.** ፪፡፳፭–፴፰። ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ወደ ፋሲካ ወሰዱ፣ **ሉቃ.** ፪፡፴፩–፴፪። ማርያም በቃና ጋብቻ ላይ ነበረች፣ **ዮሐ.** ፪፡፪–፭። አዳኝ፣ በመስቀል ላይ እያለ፣ ዮሐንስን እናቱን እንዲጎከ ባከብ ጠየቀ፣ **ዮሐ.** ፲፱፡፳፭–፳፮። ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ማርያም ከሐዋሪያት ጋር ነበረች፣ **የሐዋ.** ፩፡፲፬።

ማርያም ከሌሎች ድንግሎች በላይ በጣም ውብ እና ቆንጆ የነበረች ድንግል ነበረች፣ ፮ ኄሬ ፲፩፡፲፫–፳። የክርስቶስ እናት ማርያም ተብላ ትጠራለች፣ **ሞዛያ** ፫፡፳። ማርያም ድንግል፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሸፈን፣ የተከበረች እንዲሁም የተመረ ጠች ዕቃ ትሆናለች፣ **አልማ** ፯፡፲።

ማተም፣ ማስተሳሰር። *ደግሞም ስነስርዓቶች፤ ኤልያስ፤ ክህነት ተመልከቱ*

በሰማይ በምድር ላይ በክህነት ስልጣን የተከና ወኑትን ስነስርዓቶች ማረጋገጥ። ስነስርዓቶች የሚ ታተሙት ቅዱስ የተስፋ መንፈስ በሆነው መንፈስ ቅዱስ ተቀባይነትን ሲቀበሉ ነው።

በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታ ሰረ ይሆናል፣ **ማቴ.** ፲፮፡፲፱ (ማቴ. ፲፰፡፲፰፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፯፣ ፲፣ ፲፱፡፴–፴፮)። በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፣ **ኤፌ.** ፩፡፲፣ ፲፣ ፲፫፡፲፬።

በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆን ዘንድ ስልጣን ይኖርሃል፣ **ሔሊ.** ፲፡፯።

ለእነሱ በምድርም ሆነ በሰማይ የማሰር ኃይል ተሰጥቷቸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፭፡፳። በሰለስቲያል ክብር ያሉት በቅዱስ የተስፋ መንፈስ ታትመ ዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፯፡፭–፳። ኤልያስ የማስተሳ ሰር ሀይል ቁልፎችን ወደ ጆሴፍ ስሚዝ እጆች አሳ ለፈ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፣ ፲፫–፲፮። ይህም የሚያትም እና የሚያሳስር ሀይል ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፯፡፲፡። ተጨማሪ እርግጠኛ የትንቢት ቃል ማለት ሰው በዘ ለአለም ህይወት እንደታተመ አውቋል ማለት ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፭። በተቀደሰ ቅዱስ የተስፋ መን ፈስ ያልተሰሩ ሰዎች ሲሞቱ መጨረሻ አላቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፪። በቤተመቅደስ የሚደረግ ታላቅ ስራ ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር ማስተሳ ሰርን ይጨውራል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፴–፴፯–፴፰።

ማቴሳላ። *ደግሞም ሔኖክ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሔኖክ ልጅ። ማቴሳላ ለ፱፻፷፱ አመት ኖረ (ዘፍጥ. ፭፡፳፭–፳፯፣ ሉቃ. ፫፡፴፯፣ ሙሴ ፰፡፯)። የሔኖክ ከተማ ወደ ሰማይ በተወሰደችበት ጊዜ በምድር ላይ የቀረ ጻድቅ ነቢይ ነበር። በምድር የቀረውም ኖኅ የሚመጣበትን ትው ልድ ለመስጠት ነበር (ሙሴ ፰፡፫–፱)።

ማቴዎስ። *ደግሞም ወንጌሎች ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ እና የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያ መፅሐፍ ጸሀፊ። በቅፍርናሆም ውስጥ ለሮሜ ቀረጥ ይሰበስብ የነበረው አይሁድ ማቴዎስ ሄሮድስ አንቲጳስን የሚያገለግል ነበር። ከመቀየሩ በፊት እንደ እልፍዮስ ወንድ ልጅ ሌዋ ይታወቅ ነበር (ማር. ፪፡፲፬)። የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንዲ ሆን ከመጠራቱ በፊት፣ ጌታ የተገኘበት ድግስ ደገሰ (ማቴ. ፱፡፱–፲፫፣ ማር. ፪፡፲፬–፲፯፣ ሉቃ. ፭፡፳፯–፴፪)። ማቴዎስ ምናልባት የብሉይ ኪዳን ቅዱሣት መጻህፍቶች የተስፋፋ እውቀት ይኖረው ነበር እናም በጌታ ህይወት ውስጥ የትንቢት መሟላአትን ለማየት ችሏል። ስለሐዋሪያው የጓለኛው ህይወት የሚታወ ቀው ትንሽ ነው። አንድ ባህል እርሱ እንደ ሰማዕት ሞቷል ይላል።

የማቴዎስ ወንጌል፣ የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያ መፅሐፍ። የማቴዎስ ወንጌል ምናልባት ለመጀመ ሪያ ጊዜ የተጻፈው በፍልስጥኤም ለሚገኙት አይ ሁዶች ጥቅም ነው። ከብሉይ ኪዳን ብዙ ጥቅሶችን ተጠቁሟል። የማቴዎስ ዋና አላማ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ነብያት የተናገሩበት መሲህ እንደሆነ ለማሳ የት ነበር። ደግሞም ኢየሱስ የሰዎች ንጉስና ዳኛ እን ደሆነ ትኩረት ሰጥቷል።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተገለጹትን የአዳኝ ህይወት ድርጊቶችዝርዝር፣ የወንጌሎች ስምምነ ትን ተመልከቱ።

ማትያስ። *ደግሞም ሐዋሪያ—የሐዋሪያት መመረጥ ተመልከቱ*

በአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አባልነት የአ ስቆሮቱ ይሁዳ ቦታን እንዲወስድ የተመረጠ ሰው (የሐዋ. ፩፡፲፭–፳፮)። በኢየሱስ ምድራዊ አገልግ

ሎት በሙሉ ደቀመዛሙርት ነበር (የሐዋ. ፩፡፳፩–፳፪)።

ማክበር። *ደግምም ክብር፤ ፍርሀት ተመልከቱ*

ለቅዱስ ነገሮች ጥልቅ ክብር መኖር፤ ድንቅ

በቅዱስ ምድር ላይ ስለቆመ፣ ጌታ ሙሴን ጫማ ዎቹን እንዲያወልቅ አዘዘው፣ **ዘፀአ.** ፫፡፬–፭። እግ ዚአብሔር ክቡር ነው፤ ግሩም ነው፣ **መዝ.** ፹፱፡፯። እግዚአብሔርን በማክበርና በፍርሃት እግዚአብ ሔርን እናገልግል፣ **ዕብ.** ፲፪፡፳፰።

ሞሮኒ በመሬት ላይ ሰገደ፣ በኃይል ፀለየ፣ **አልማ** ፴፯፡፲፫። ህዝቡ በምድር ላይ ወደቁ እናም ለክርስ ቶስ ሰገዱ፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፲፪–፲፱።

እራሱን ዝቅ ያድርግ፣ **ት. እና ቃ.** ፭፡፳፭። በዙ ፋኑ ፊትም ሁሉም ነገሮች በትህትና ይሰግዳሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፣ ፻፫። የተቀበላችሁትን እንደተራ ስለተቀበላችሁት፣ አዕምሮአችሁ ባለማመን ምክ ንያት ጨልሞባችሁ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፹፱፡ ፻፱–፻፯። ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ይናዘ ዛል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፯፡ ፻፱። ለኃያል ጌታ ስም ክብር ወይም አምልኮ፣ ቤተክርስቲያና ክህነትን የመልከ ጼዴቅ ክህነት ወይም በመልከ ጼዴቅ ስም ጠሩት፣ **ት. እና ቃ.** ፻፯፡፯። ጌታ በቤቱ ለሚያከብሩት ሁሉ በረከቶች ያፈሣል፣ **ት. እና ቃ.** ፻፱፡ ፳፭።

ማዘን። ርህራሄ *ተመልከቱ*

ማዳመጥ። *ደግምም ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፤ ጆሮ ተመልከቱ*

የጌታን ድምፅ ወይም ትምህርትን

ጌታ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እር ሱንም ታደምጣለህ፣ **ዘዳግ.** ፲፰፡፲፭። ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል፣ ፩ ሳሙ. ፲፭፡፳–፳፫። የጌታ ባሪያዎችህን ነቢያትን አልሰ ማንም፣ ዳን. ፱፡፮። የነቢያትን ቃል የሚሰሙ ጻድቃኖች፣ እነርሱም የማይጠፉት ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፳፮፡፲፡ ፳። የመልካሙን እረኛ ድምፅ የማትሰሙ ከሆነ፣ እናንተ የእርሱ በግ አይደላችሁም፣ **አልማ** ፭፡ ፴፳ (ሔሊ. ፯፡፲፳)።

አቤቱ፣ እናንተ የቤተክርስቲያኔ ሰዎች ሆይ አድ ምጡ፣ **ት. እና ቃ.** ፩፡፩። የመንፈስን ድምፅ የሚ ያዳምጠውን ሰው ሁሉ ያብራራለታል እናም ወደ አብም ይመጣል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፱፡ ፴፯–፴፯። የጌታ አምላካቸውን ድምፅ ለማድመጥ ይዘገዩ ነበር፣ ስለ ዚህ፣ ጌታ አምላካቸው ጸሎታቸውን ለማድመጥ ዘግይቷል፣ **ት. እና ቃ.** ፻፩፡፣ ፯–፱። ትእዛዛትን ያላ ዳመጡትም ተገስጸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፻፫፡ ፱ (ሙሴ ፱፡ ፱)።

ማድረግ። *ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ ተመልከቱ*

ማጉረምረም። *ደግምም አመጽ ተመልከቱ*

የእግዚአብሔርን እቅዶች፣ አላማዎች፣ እና አገ ልጋዮች ላይ መነጫነጭ እና ቅሬታን መግለፅ።

ህዝቦች በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፣ **ዘፀአ.** ፲፭፡ ፳፫–፲፯፡ ፫።

አይሁድ ስለ ኢየሱስ አጉረመረሙ፣ **ዮሐ.** ፮፡ ፴፭።

ላማን እና ላሞኤል በብዙ ነገሮች ላይ አጉረመ ረሙ፣ ፩ ኔፊ ፪፡ ፲፩–፲፪ (፩ ኔፊ ፣ ፡ ፴፩፣ ፲፯፡ ፲፣)።

ስላላየሻቸው ነገሮች አታጉረምርሚ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡ ፱።

ማንግ። *ደግምም የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ ጎግ ተመልከቱ*

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በጥቁር ባህር አካባቢ የሚገኝ ምድርና ህዝብ። ከክርስቶስ ዳግም ምፅ ዓት በፊት በሚኖረው ታላቅ ጦርነት ንጉሳቸው፣ ጎግ፣ የማጎግ ሰራዊትን ይመራል (ሕዝ. ፴፰፡ ፪፣ ፴፱፡ ፯)። በአንድ ሺህ አመት መጨረሻም ላይ በእግ ዚአብሔር ሀይሎች እና በክፉ ሀይሎች መካከል ስለ ሚኖረው ስለጎግና ሜጎግ ሌላ ታላቅ ጦርነትም ይናገ ራሉ (ራዕ. ፳፡ ፯–፱፣ **ት. እና ቃ.** ፹፰፡ ፲፭–፲፮)።

ማጠብ፣ የታጠበ፣ የሚታጠቡ። *ደግምም የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ ተመልከቱ*

በስጋዊ ወይም በመንፈሳዊ ማጽዳት። በምሳሌ፣ ንስሀ የገባ ሰው በኃጢያት እና በዚህ ውጤታ ሸከም ከነበረበት ህይወት በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ መስዋዕት በኩል ለመጽዳት ይችላሉ። በት ክክለኛው ክህነት በኩል የሚከናወኑ መታጠብ እንደ ቅዱስ ስነስርዓት ለማገልገል ይችላሉ።

ካህኑም ልብሱን ያጥባል፥ ገላውንም በውኃ ይታ ጠባል፣ **ዘኁል.** ፲፱፡ ፯። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ፣ **መዝ.** ፶፩፡ ፪፣ ፯። ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፤ ክፉ ማድረግን ተዉ፣ **ኢሳ.** ፩፡ ፲፮–፲፰። ኢየሱስ የሐዋሪያቱን እግሮች አጠበ፣ **ዮሐ.** ፲፫፡ ፬–፲፭ (ት. እና ቃ. ፹፱፡ ፲፱–፲፱)። ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአት ህም ታጠብ፣ **የሐዋ.** ፳፪፡ ፲፮ (አልማ ፯፡ ፲፬፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡ ፣)።

ማንም ሰው ልብሱ ነጭ ሆኖ ካልታጠበ በቀር መዳን አይችልም፣ **አልማ** ፭፡ ፳፭ (፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፱)። በክርስቶስ ደም ልብሳቸው እስከሚነጣ ታጥበው ነበር፣ **አልማ** ፲፫፡ ፲፭ (ኤተር ፲፫፡ ፣)።

ትእዛዛትን በማክበርም ከጎጥያታቸው ሁሉ ይታ ጠቡ እና ይጽዱ፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡ ፻፫። መቀባ ታችሁ፣ እና መታጠባችሁ፣ በቅዱስ ቤቴ ስነስር ዓት የተሾሙ ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፻፳፬፡ ፴፱–፴፭።

ማጥለቅ። ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ *ተመልከቱ*

ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን። *ደግምም ቅድስና፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ ተመልከቱ*

ከቅጣት ምህረት ማግኘት እና ከበደል ነጻ መሆንን ማወጅ። ሰው በኢየሱስም ጸጋ በእርሱ እምነት በኩል ይጻደቃል። ይህም እምነት የሚታየው ንስሀ በመግባት እና ለወንጌሉ ህግጋት እና ስነስርዓቶች ታዛዥ በመሆን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ የሰው ዘር ንስሀ እንዲገባና ከበደል ነጻ እንዲ ሆን ወይም ይህ ካልሆነ ከሚቀበሉት ቅጣት ምህረት እንዲያገኙ ያስችላል።

የእስራኤልም ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ይጸድ ቃሉ፣ **ኢሳ.** ፵፭፡፳፭።

ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም፣ **ሮሜ** ፪፡፲፫። ሰው በክርስቶስ ደም ጸድቋል፣ **ሮሜ** ፭፡፩–፪፣ ፱። እናንተም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸድቃ ችኋል፣ **፩ ቆሮ.** ፮፡፲፩። በጸጋው ጸድቀን ወራ ሾች እንሆናለን፣ **ቲቶ** ፫፡፯። አባታችን አብር ሃም በሥራ የጸደቀ አልነበረምን፣ **ያዕ.** ፪፡፳፭። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ ጸድቋል፣ **ያዕ.** ፪፡፲፬–፳፮።

በህግ ማንም ስጋ አይጸድቅም፣ **፪ ኔፊ** ፪፡፭። ጻድቁ ባሪያዬም ብዙዎችን ያጸድቃል፣ ኃጢአ ታቸውንም ይሸከማልና፣ **ሞዛያ** ፲፬፡፲፩ (ኢሳ. ፶፫፡፲፩)። ልብሳችሁ በክርስቶስ ደም ጠርቷል ለማለት ትችላላችሁ፣ **አልማ** ፭፡፳፯።

በጌታችንና አዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ በኩል የምናገኘው ፅድቅ እውነተኛ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፴–፴፩ (ት. እና ቃ. ፲፰፡፴፡፴፱)።

በመንፈሱም ትጸድቃለህ፣ **ሙሴ** ፮፡፳።

ሜዳ። እርሻ *ተመልከቱ*

ምላስ። *ደግምም የልሳኖች ስጦታ ተመልከቱ*

የንግግር ምሳሌ። ቅዱሳን ልሳናቸውን ይቆጣ ጠሩ፣ ይህም ማለት ንግግራቸውን ይቆጣጠሩ። ይህም ቋንቋዎችን ወይም ህዝቦችን ሊያመለክት ይችላል። በመጨረሻም፣ እያንዳንዱ ጉልበት ይን በረከካል እናም ምላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያም ናል (ኢሳ. ፵፭፡፳፫፣ ሮሜ ፲፡፡፲፩)።

አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ **መዝ.** ፴፬፡፲፫ (፩ ጴጥ. ፫፡፲)። አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ነፍ ሱን ከመከራ ይጠብቃል፣ **ምሳ.** ፳፩፡፳፫።

አንደበቱን ሳይገታ ማንም ቢኖር የእርሱ አም ልኮ ከንቱ ነው፣ **ያዕ.** ፩፡፳፮። በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር ፍጹም ሰው ነው፣ **ያዕ.** ፫፡፩–፲፫። ወንጌሉ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰበካል፣ **ራዕ.** ፲፡፡፮–፯ (፪ ኔፊ ፳፯፡፲፣ ሞዛያ ፫፡፲፣ ፳፡ ት. እና ቃ. ፲፡፡፲፣ ፲፲፪፡፩)።

ጌታ ለሀገሮች ሁሉ ቃሉን እንዲያስተምሩ የራ ሳቸውን ሀገር እና ቋንቋ ሰጥቷል፣ **አልማ** ፳፱፡፰። እነዚህ ሰሌዳዎች ለሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ህዝብ ይሄዳሉ፣ **አልማ** ፴፯፡፱።

ቃሌን ለማግኘት ፈልግ፣ እናም ከዚያ አንደ በትህ ይፈታል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፩፡፳፩። በእራሱ ልሳን እያንዳንዱ ሰው የወንጌልን ሙላት ይሰማል፣ **ት. እና ቃ.** ፣፡፲፩።

ምልክት። *ደግምም ተአምራት፣ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች፣ የጊዜዎች ምልክቶች ተመልከቱ*

ሰዎች እንደ አንድ ነገር ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ የሚመለከቱት ድርጊት ወይም አጋጣሚ። ምል ክት በልምድ ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ታዕምራቶች ናቸው። ሰይጣን በአንዳንድ ጉዳዮች ምልክትን የመ ስጠት ሀይል አለው። ቅዱስና የመንፈስ ስጦታዎችን መፈለግ ይገባቸዋል ነገር ግን ለማወቅ የሚጓጉትን ለማግኘት ወይም እምነታቸውን ለመደገፍ ምልክቶ ችን መፈለግ አይገባቸውም (ት. እና ቃ. ፱፳፡፳፱)።

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ሰዎች በአላማ አን ድነት እና በማንነት አብረው የሚሰበሰቡበት አርማ ወይም መሰረት። በጥንት ጊዜዎች ምልክት በጦር ነት ላይ ላሉ ወታደሮች እንደ መሰብሰቢያ ይሆናል። መፅሐፈ ሞርሞን እና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክር ስቲያን ለአለም ሀገሮች በሙሉ እንደ ምሳሌ ምል ክቶች ናቸው።

ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል፣ **ኢሳ.** ፭፡፳፮ (፪ ኔፊ ፲፭፡፳፮)። ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣ **ኢሳ.** ፣፡፣፲ (፪ ኔፊ ፲፣፡፣፲)። የእሴይን ሥር ለአ ሕዛብ ምልክት ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፲፩፡፲ (፪ ኔፊ ፳፩፡፣፣ ት. እና ቃ. ፲፣፲፡፣)። እግዚአብሔር በሰ ማይና በምድርም ተአምራትንና ድንቅን ይሠራል፣ **ዳን.** ፮፡፳፯።

ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፣ **ማቴ.** ፲፪፡፴፱ (ማቴ. ፲፮፡፬፣ ሉቃ. ፲፩፡፳፱)። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፣ **ማር.** ፲፮፡፣፣ (ሞር. ፱፡፳፬፣ ኤተር ፬፡፣፲፳፣ ት. እና ቃ. ፲፡፬፡፳፭)።

ሼረም ምልክት እንዲሰጠው ጠየቀ፣ **ያዕቆ.** ፣፡፣፲–፳። ቆሪሆር ምልክት እንዲሰጠው ጠየቀ፣ **አልማ** ፴፡፴፯–፴። ከሰማይ ምልክትን ካሳየኸን፣ ከዚያም እናምናለን፣ **አልማ** ፴፪፡፲፣። በምልክ ቶች እንዲሁም በአስገራሚ ነገሮች ማመን ጀመሩ፣ ፫ ኔፊ ፭፡፳፪። ሰዎቹ እነዚያን ምልክቶች እናም አስገራሚ ነገሮች መርሳት ጀመሩ፣ ፫ ኔፊ ፪፡፭። እምነታችሁ እስከሚፈተን ድረስ ምስክርነትን አት ቀበሉም፣ **ኤተር** ፲፪፡፣። ፣

፲፮ ዲያብሎስን ከማስወጣት፣ የታመሙትን ከመፈወስ እናም ከምራዝ እፉኝት፣ እናም ገዳይ መርዝን ከመቋቋውም በስተቀር፣ እኔ ካላዘዝኳችሁ ተአምራትን አትፈልጉ፣ ት. እና ቃ. ፷፬፡፲፫። እም ነት የሚመጣው በምልክቶች አይደለም፣ ነገር ግን ምልክቶች የሚያምኑትን ይከተላል፣ ት. እና ቃ. ፷፫፡፯–፲፩። የሰላም ምልክት ያንሱ፣ ት. እና ቃ. ፱፭፡፴፱።

በእነዚያ ቀናት ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተ ኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ታላቅ ምልክቶችና ድንቆ ችን ያሳያሉ፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፭፡፳፪።

ምሳሌ

መንፈሳዊ እውነት ወይም መሰረታዊ መመሪያ ለማሳየት እና ለማስተማር የሚጠቀሙበት ታሪክ። ምሳሌ ልዩ ያልሆነ ነገርን ወይም የእውነት ድርጊ ቶችን በማነጻጸር ላይ የተመሰረተ ነው፣ እናም የም ሳሌ ዋና መልእክት ይህን ለመቀበል በመንፈስ ላል ተዘጋጁት አዳማጮች የተደበቀ ነው (ማቴ. ፲፫፡፲–፲፯)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ በምሳሌዎች አስተ ማረ። የወንጌሎች ስምምነትን በተጨማሪ ውስጥ ተመልከቱ።

ምሳሌዎች

አንድ ነገርን እንደ ሌላ ነገር ተመሳሳይነት ወይም ምስል መጠቀም። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ምሳሌዎችን የተለመዱ እቃዎችን፣ ድርጊቶችን፣ ወይም ጉዳዮችን የወንጌል መሰረታዊ መርሆችን ወይም ትምህርቶችን ለመወከል ይጠቀሙባቸዋል። ለምሳሌ፣ የመፅሐፈ ሞርሞን ነቢይ አልማ የእግ ዚአብሔር ቃልን ለመወከል ዘርን ተጠቅሞበታል (አልማ ፴፪)።

በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ በሙሉ ነቢያት ምሳ ሌዎችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለማስተማር ተጠቅመ ዋል። የተጠቀሙባቸው አንዳንዶቹ ምሳሌዎች በተ ጨማሪም ስርዓቶች (ሙሴ ፮፡፳፫–፳፰)፣ መስዋዕቶች (ዕብ. ፱፡፲፭–፲፭፤ ሙሴ ፭፡፯–፳)፣ ቅዱስ ቁር ባን (ጆ.ስ.ት.፣ ማር. ፲፬፡፳–፳፬፤ ሉቃ. ፳፪፡፲፫–፳)፣ እና ጥምቀት። (ሮሜ ፮፡፩–፮፣ ት. እና ቃ. ፲፳፳፡፲፪–፲፫) ነበሩ። ብዙዎቹ የመፅሐፍ ቅዱስ ስሞች ምሳሌዎች ነበሩ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የድንኳን ስነስርዓቶች እና የሙሴ ህግ የዘለአለም እውነቶችን ይወክላሉ(ዕብ. ፰–፲፣ ሞዛያ ፲፫፡፳፱–፴፪፣ አልማ ፳፭፡፲፭፣ ሔለ. ፰፡፲፱–፲፭)። ለሌሎች ምሳሌዎች ማቴዎስ ፭፡፲፫–፲፮፣ ዮሐ. ፫፡፲፬–፲፭፣ ያዕቆ. ፬፡፭፣ አልማ ፴፯፡፴፯–፴፭ ተመልከቱ።

ምስክር። *ደግምም ምስክርነት ተመልከቱ*

አንድ ነገር እውነት እንደሆነ መረጃ መስጠት። ምስክርም በግል እውቀት እንደዚህ አይነት መረ ጃን የሚሰጥ ሰውም ሊሆን ይችላል፣ ይህም ማለት ምስክር የሚሰጥ ነው።

በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ ዘፀአ. ፳፡፲፮።

ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግ ሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል፣ ማቴ. ፳፬፡፲፬ (ጆ.ስ.—ማቴ. ፭፡፴፭)። ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፣ የሐዋ. ፩፡፰። ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰ ክራል፣ ሮሜ ፰፡፲፮ (፩ ዮሐ. ፭፡፮)።

ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ምስክር በመሆን ቁሙ፣ ሞዛያ ፲፰፡፰–፱። ቅዱሣት መጻህፍትን የምንወስደው ሁልጊዜ ትእዛዛቱን ለማክበር እና ኢየሱስን ሁልጊዜ እንድናስታውስ ዘንድ ነው፣ ፮ ኔፊ ፲፡፲–፲፩ (ሞሮኒ ፱–፭፣ ት. እና ቃ. ፭፡፳–፳፱)። እምነታችሁ እስከሚፈተን ድረስ ምስክርነ ትን አትቀበሉም፣ ኤተር ፲፪፡፮።

የምስክሮች ህግ፥ በሁለት ወይም በሶስት አፍ ምስክርነት ሁሉም ቃል ይጸናል፣ ት. እና ቃ. ፮፡፳፰ (ዘዳግ. ፲፯፡፮፣ ማቴ. ፲፰፡፲፮፣ ፪ ቆሮ. ፲፫፡፩፣ ኤተር ፭፡፱፣ ት. እና ቃ. ፲፳፰፡፫)። ሐዋ ሪያት ትሆኑ እናም የስሜ ልዩ ምስክር እንድት ሆኑ ሾምኳችሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፫)። ፳፭ ሰባዎቹ ለአህዛብና በአለም በሙሉ ልዩ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭። መዝጋቢ ይኑር፣ እና እርሱም ለጥሞቀቶ ቻችሁ የአይን ምስክር ይሁን፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፮ (ት. እና ቃ. ፲፡፴–፴፪)።

ምስክርነት። *ደግምም መመስከር፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ምስክር ተመልከቱ*

በመንፈስ ቅዱስ ብኩል የሚሰጥ እውቀት እና ምስክር። ምስክር ሰው እንደ እውነት ስለሚመለ ከተው በይፉ ወይም በህግ የሚያውጀው ሊሆንም ይችላል (ት. እና ቃ. ፲፪፡፳፯)።

እኔን ግን የሚቤዝኝ ሕያው እንደ ሆነ አውቃ ለሁ፣ ኢዮብ ፲፱፡፳፭–፳፮።

በጌታችን ምስክርነት አትፈር፣ ፪ ጢሞ. ፩፡፰። የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነው፣ ራዕ. ፲፱፡፲።

በሁሉም ጊዜዎች እንደ እግዚአብሔር ምስክር ቁሙ፣ ሞዛያ ፲፰፡፱። በእነርሱ ላይ ንጹሁን ምስ ክር በግድ ከመገፋፋት በስተቀር እነርሱን መልሶ የሚያገኝበት ሌላ መንገድ የለም፣ አልማ ፱፡፲፱–፳። እነዚህ ነገሮች እውነት ለመሆናቸው ለምስክር ነት ሁሉም ነገር አሉኝ፣ አልማ ፴፡፴፭–፴፱። እም ነታችሁ እስከሚፈተን ድረስ ምስክርነትን አትቀበ ሉም፣ ኤተር ፲፪፡፮።

ይህንን ነገር በተመለከተ በአምሮህ ሰላምን አልተናገርኩም? ከዚህ የተሻለ ከእግዚአብሔር

ምን አይነት ምስክርነትን ታገኛለህ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፳፪–፳፫። ስለእርሱ ከተሰጡት ብዙ ምስክሮች በኋላ፣ ይህም በመጨረሻ ስለእርሱ የምንሰጠው ምስክር ነው፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፪–፳፬። የላኳ ችሁ እንድትመሰክሩ እና ሰዎችን እንድታስጠነ ቅቁ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፩–፲፪። መስካሪ ዎቹ ሞተዋል፣ እና ምስክራቸውም ተፅዕኖ አለው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፭፡፬–፭።

ሔኖክ መላእክቶች የአብና ወልድ ምስክር ይዘው ከሰማይ ሲወርዱ አየ፣ ሙሴ ፯፡፳፯። ምንም እንኳን ራዕይ አይቻለሁ በማለቱ ብጠላና ብሰቃይም፣ ይህ ግን እውነት ነበር፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፬–፳፭።

ምስጋና። አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት *ተመልከቱ*

ምርኮ። ነጻ፣ ነጻነት *ተመልከቱ*

ምርጥ። መምረጥ፣ መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)፣ ነጻ ምርጫ *ተመልከቱ*

ምርጦች

ምርጦች እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው የሚ ወዱና እርሱን ለማስደሰት ህይወታቸውን የሚኖሩ ናቸው። እንደዚህ አይነት የደቀ መዛሙርት ህይወት የሚኖሩት አንድ ቀን ከተመረጡት ልጆቹ መካከል እንዲሆኑ በጌታ ይመረጣሉ።

ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ያታልሏቸውዋል፣ ማቴ. ፳፬፡፳፬። ዮሐንስ የምርጥ ሴታ ልጆች እውነትኛ እና ታማኝ ስለሆኑ ተደሰተ፣ ፪ ዮሐ. ፩።

ኃጢያትሽ ተሰርዮልሻል፣ እናም የተመርጥሽ ሴት ነሽ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፫። በእኔ የተመረጡት ድምጼን ይሰማሉ እና ልባቸውን አያደንድኑም፣ ት. እና ቃ. ፳፬፡፲። ምርጦቼን ከአራቱም የም ድር ማዕዘናት ቢሆንም እሰበስባለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲። ቅዱሣት መጻህፍት ለምርጦቼ ደህንነት ይሰጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳–፳፩። የክህነት ጥሪ አቸውን የሚያጎሉ የእግዚአብሔር ምርጥ ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፴፫–፴፡።

ለምርጦች የፈተና ቀናት ያጥራሉ፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፳።

ምናሴ። *ደግሞም* ኤፍሬም፣ እስራኤል፣ ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአስናት እና ወደ ግብፅ የተሸጠው ዮሴፍ ታላቅ ልጅ (ዘፍጥ. ፵፩፡ ፶–፶፩)። እርሱና ወንድሙ ኤፍሬም የያዕቆብ (የእስራኤል) የልጅ ልጆች ነበሩ ነገር ግን እነርሱ የእርሱ አደረጋ ቸው እናም ልክ እንደ እርሱ ልጆች እንደሆኑ ባረካ ቸው (ዘፍጥ. ፵፰፡ ፩–፭)።

የምናሴ ጎሳ፣ የምናሴ ትውልዶች ከእስራኤል ጎሳዎች መካከል የተቆጠሩ ነበሩ (ዘኁል. ፩፡ ፴፬–፴፭፣ ኢያ. ፲፫፡ ፳፱–፴፩)። ደግሞም ለኤፍሬ ምና ለምናሴ ተሰጥቶ የነበረው ለዮሴፍ ጎሳ የተ ሰጠው የሙሴ በረከት በኦሪት ዘዳግም ፴፫፡ ፲፫–፲፯ ውስጥ ተመዝግቧል። የተመደበላቸው ምድር ከዮርዳኖስ ወደ ምዕራብ በኩልና ከኤፍሬም አጠ ገብ ነበር። በዮርዳኖስ ምስራቅ በበሳን እና በገለዓድ ጥሩ የግጦሽ መሬት ውስጥም ሰፍረው ነበር። በመ ጨረሻው ቀናት፣ የምናሴ ጎሳ የኤፍሬም ጎሳን የተ በተኑትን እስራኤል በመሰብሰብ ይረዳሉ (ዘዳግ. ፴፫፡ ፲፫–፲፯)። የመፅሐፈ ሞርሞን ነቢይ ሌሂ የም ናሴ ትውልድ ነበር (አልማ ፲፡ ፫)።

ምኞት። *ደግሞም* ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት *ተመልከቱ*

ለአንድ ነገር ትክክል ያልሆነ ጠንካራ ፍላጎት መኖር

ውበትዋን በልብህ አትመኝው፣ ምሳ. ፮፡ ፳፭።

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፣ ማቴ. ፭፡ ፳፰ (ቮ ኔፊ ፲፪፡ ፳፰)። እንዲሁም ወንዶች እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፣ ሮሜ ፩፡ ፳፯። እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማ ቻሉ፣ ፪ ጢሞ. ፬፡ ፫–፬።

ላባን ንብረታችን ባየ ጊዜ ተመኘው፣ ፩ ኔፊ ፫፡ ፳፭። በዓይንህ ምኞት ከእንግዲህ አትጓዝ፣ አልማ ፴፱፡ ፫–፬፣ ፴።

ሴትን በምኞት የሚመለከት እምነትን ይክዳል፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡ ፳፫። ከፍተኛ ፍላጎታችሁን ሁሉ አቁሙ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲፭፩።

ምኩራብ። *ደግሞም* አይሁዶች *ተመልከቱ*

ለሀይማኖት አላማዎች የሚጠቀመባቸው የመሰ ብሰቢያ ቦታዎች። በአዲስ ኪዳን ጊዜዎች፣ የምኩ ራብ እቃዎች የህግ እና ሌሎች ቅዱስ ጽሁፎች የነ በረባቸውን ጥቅልል የያዘ ታቦት፣ የማንበቢያ ጠረ ጴዛ፣ እና የሚያመልኩት የሚቀመጡበት ያለው ብቻ ነበር።

የአካባቢው የሽማግሌዎች ሸንጎ እያንዳን ዱን ምኩራብ ያስተዳድራሉ። እነርሱ ማን መግ ባት እንደሚችል እና ማን መግባት እንደማይችል ይወስናሉ (ዮሐ. ፱፡ ፳፪፣ ፲፪፡ ፴፪)። በጣም አስፈ ላጊ የሆነው ባለስልጣን የምኩራቡ አስተዳዳሪ ነው (ማር. ፭፡ ፳፪፣ ሉቃ. ፲፫፡ ፲፬)። እርሱም በአጠቃ ላይ ጸሀፊ፣ ህንጻውን የሚጠብቅ፣ እና አገልግሎ ትን የሚያስተዳድር ነበር። አጃቢዎችም የጸሀፊ ሀላ ፊነቶችን ይፈጽማሉ (ሉቃ. ፬፡ ፳)።

አይሁዶች በሚኖሩበት፣ በፍልስጥኤም ይሁን በሌላ፣ በእያንዳንዱ ከተማ ውስጥ ምኩራቦች ይገኙ ነበር። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማሰራ

ጨት ታላቅ እርዳታ ነበር ምክንያቱም የቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ ሚስዮናውያን በምኩራብ ውስጥ ለመናገር ይችሉ ነበር (የሐዋ. ፲፫፡፭፣ ፲፬፡፲ ፲፬፡፩፣ ፲፯፡፩፣ ፲፣ ፲፰፡፬)። እንደዚህ አይነት ነገሮች በመ ፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ይገኙ ነበር (አልማ ፲፯፡፲፫፣ ፳፩፡፩–፭፣ ፴፪፡፩)

በዚህ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያንም እንደዚህ ይደረግ ነበር (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፣ ፳፳፡፩)።

ምክር (ስም)። *ደግምም ነቢይ ተመልከቱ*

ከጌታ እና ከተሾሙ መሪዎቹ የሚመጡ ግሰጻ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ምክር፣ እና ትምህርት።

እመክርሃለሁ፣ **ዘፀአ.** ፲፰፡፲፱። እግዚአብሔር በምክሩ መራኝ፣ **መዝ.** ፷፫፡፳፩። መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ሕዝብ ይወድቃል፣ **ምሳ.** ፲፩፡፲፬።

ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ፣ **ሉቃ.** ፯፡፴።

የእግዚአብሔርን ምክር የሚያዳምጡ ከሆኑ መማር ጥሩ ነው፣ **ፊ ኔፊ** ፱፡፳፱።

የሾማችሁን ምክር ስሙ፣ **ት. እና ቃ.** ፷፳፡፪። ከመደብኩት ምክር ተቀበሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፡፩። ከመደብኩት ምክር በላይ የእራሱን ምክር ለመመ ስረት ተነሳስቷል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፱፡፣ ፲፲፡። የአ ገልጋዩን ጆሴፍ ምክር አድምጡ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፱፡፣ ፲፲፡። ማንም ሰው ምክሬን ካልፈለገ፣ ምንም ሀይል አይኖረውም፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፯፡፣ ፲፱፡።

ምዙሪ። *አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ተመልከቱ*

ምድር። *ደግምም መፍጠር፣ ፍጥረት፣ አለም ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሰው በስጋዊ ሙከራ ጊዜው እንዲጠቀሙበት የተ ፈጠረ የምንኖርበት ፕላኔት። የመጨረሻ እጣ ፈንታዋ የምትከበርና ከፍ የተደረገች መሆን ነው (ት. እና ቃ. ፷፯፡፩–፪፣ ፲፴፡፳–፴፡)። ምድር ለሰለ ስቲያል ክብር ብቁ ሆነው ለኖሩት ዘለአለማዊ ውርስ ትሆናለች(ት. እና ቃ. ፲፳፡፲–፲፩–፳፯)። እነርሱም በአብና ወልድ ፊት በመኖር ይደሰታሉ (ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፡፳፪)።

ለሰው የተፈጠረች ነች፣ እግዚአብሔር በም ድር ላይ ገዝር አደረጋቸው፣ **ዘፍጥ.** ፩፡፳፰ (ሙሴ ፪፡፳፰)። ምድሪቱ የእግዚአብሔር ነች፣ **ዘፀአ.** ፱፡፳፱ (መዝ. ፳፬፡፩)። ምድርን ጌታ ለሰው ልጆች ሰጣት፣ **መዝ.** ፲፣፲፭፡፣ ፲፯፡። እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ፣ **ኢሳ.** ፴፭፡፣ ፲፪፡።

ሰው በቃሉ ኃይል ወደ ምድር ፊት መጥቷል፣ *ያዕቆ.* ፪፡፱።

ምድር መንፈስ ቅዱስን እንደ መሪያቸው ለወሰዱት ትሰጣለች፣ **ት. እና ቃ.** ፴፭፡፣ ፶፯–፶፡ (ት. እና ቃ. ፲፫፡፣ ፲)። ወንጌሌን ያከበሩ የም ድር ጥሩ ነገሮች የእነርሱ ደመወዛቸው ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፱፡፣ ፫። ድህውና የዋሁ ምድርን ይወ ርሳሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፫፡፣ ፲፣ (ማቴ. ፭፡፭፣ ፣ ፲ ኔፊ ፲፪፡፭)።

ምድርን እንሰራለን፣ እናም እንፈትናቸዋለን፣ **አብር.** ፫፡፳፭–፳፮።

ሀያው አካል፣ ምድር ግን ለዘላለም ነው፣ **መክ.** ፩፡፬።

የብርጭቆ ባሕር ምድር በተቀደሰ፣ በማይጠፋ፣ እና ዘለአለማዊ ሁኔታዋ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፩። ለሰለስቲያል ክብር እንድትዘጋጅ ዘንድ፣ ምድር መንጻት አለባት፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፡፣ ፲፳–፲፱።

ምድር በታላቅ ድምፅ አለቀሰች፣ **ሙሴ** ፯፡፴፯።

የምድር መከፋፈል፣ ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብ ሰብ፣ **ዘፍጥ.** ፩፡፱። ምድር በፋሌቅ ዘመን ተከፍላ ለች፣ **ዘፍጥ.** ፣፡፳፭።

ውኃውም ከምድሪቱ ገፅ ከሸሸ በኋላ ከሁሉም መሬት በላይ የተመረጠች ምድርሆነች፣ **ኤተር** ፲፣፡፪።

ምድርም ከተከፋፈለችበት ቀን በፊት እንደነበ ረችም አይነት ትሆናለች፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፣፡፳፱።

ምድርን ማፅዳት፣ ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ ዘነበ፣ **ዘፍጥ.** ፯፡፬።

ምድር እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ለእሳት ቀርታ ተጠብቃለች፣ ፪ ጴጥ. ፣፡፯።

ከዛሬ በኋላ እንደ እሳት የሚነድ ቀን ይመጣል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፣ ፳፱፡።

ምድር እድፍ ለመነጻት ፈለገች፣ **ሙሴ** ፯፡፴፯።

የምድር የመጨረሻ ሁኔታ፣ ምድርም እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ትጠቀለላለች እናም ታልፋ ለች፣ ፣ ኔፊ ፳፯፡፣ ፣ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፣ ፳፣)። አዲስ ሰማይ እና አዲስ ምድር ይኖራል፣ **ኤተር** ፲፣፡፣ ፱ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፣ ፳፣)።

የብርጭቆ ባሕር ምድር በተቀደሰ፣ በማይጠፋ፣ እና ዘለአለማዊ ሁኔታዋ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፩። ለሰለስቲያል ክብር እንድትዘጋጅ ዘንድ፣ ምድር መንጻት አለባት፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፡፣ ፲፳–፲፱። ይህች ምድር በጥራት ትሰራለች እና እንደ ኡሪምና ቱሚም ትሆናለች፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፡፣ ፳–፱።

ለአንድ ሺህ አመት ምድር ታርፋለች፣ **ሙሴ** ፯፡፳፩። ምድርም ትታደሳለች፣ **እ.አ.** ፩፡፣ ፣።

ምግባረ ጥሩነት። *ማመንዘር፣ በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፣ ንጹህነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

ምዕዋት፣ የምዕዋት ስጦታ። *ደግምም*

በኩራት፣ በጎ ድርገት፣ ደሀ፣ ጾም፣ መጾም ተመልከቱ

ደሀዎችን ለመርዳት የሚሰጥ በኩራት።

ምጽዋታችሁን በሰዎች ፊት እንዳታድርጉ፣ **ማቴ.** ፮፡፩–፬ (ቮ ኔፊ ፲፫፡፩–፪)። ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሀ መበለት አብልጣ ጣለች፣ **ማር.** ፲፪፡፴፩–፴፪። ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው፣ **የሐዋ.** ፳፡፴፭–፴፮።

የራሳችሁን ነገር ለድሃ እንድትሰጡ. . .እፈልጋለሁ፣ **ሞዛያ** ፪፡፳፤ የቤተክርስቲያኑ አባላት እያንዳንዳቸው ያላቸውን እንዲያካፍሉ፣ ማለት እያንዳንዱ እንዳለው ባለው መጠን ያካፍል፣ **ሞዛያ** ፲፰፡፳፤ ፳፯።

ሞርሞን (ሞርሞኖች)። *ደግሞም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልከቱ*

ምርሞን የተባለው ቅፅል ስም የተሰጠው የቤተ ክርስቲያኗ አባል ያልሆኑት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትን ለመጠቆም ነበር። ስሙም የመጣው በጥንት ነቢይ ሞርሞን የተዘጋጀና መፅሐፈ ሞርሞን ከተባለው ቅዱሣት መጻህፍት ነው። ጌታ የቤተክርስቲያኗ አባላት እንዲጠሩበት የተሰጣቸው ስም “ቅዱሳን” ነው። የቤተክርስቲያኗ ትክክለኛ ስምም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው።

ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን ተመልከቱ*

የኔፋውያን ህዝብ ነቢይ፣ የወታደሮች ጄነራል፣ እና የመፅሐፈ ሞርሞን መዝገብ ጠባቂ። ሞርሞን በ፫፻፲፭–፫፻፷፭ ም.ዓ. አካባቢ ይኖር ነበር (ሞር. ፩፡፪፣ ፯፣ ፯፡፭–፯፣ ፰፡፪–፫)። ከአስራ አምስት አመቱ ጀምሮ በብዙ ህይወቱ የወታደሮች መሪ ነበር (ሞር. ፪፡፩–፪፣ ፫፡፰–፲፪፣ ፭፡፩፣ ፰፡፪–፫)። አማሮን ሞሮኒን በመዝገቦቹ ሀላፊነት ለመው ሰድና መዝገቦችን ለመጠበቅ እንዲዘጋጅ መመሪያ ሰጠው (ሞር. ፩፡፪–፭፣ ፪፡፣ ፲፯–፲፰)። የህይወቱን ታሪክ ከመዘገበ በኋላ፣ ሞርሞን የኔፊን ታላቅ ሰሌዳ በሞርሞን ሰሌዳዎች ላይ በማሳጠር ጻፈ። በኋላም ይህን ቅዱስ መዝገብ ለልጁ ለሞሮኒ አሳልፎ ሰጠ። እነዚህ ሰሌዳዎች ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን የተረጎመባቸው ሰሌዳዎች ክፍል ነበሩ።

የሞርሞን ቃላት፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ትንሹ መፅሐፍ። በመፅሐፈ ኦምኒ ውስጥ አማሌቅ የመጨረሻ ቃላት እና በመፅሐፈ ሞሳያ የመጀመሪያ ቃላት መካከል፣ የመዝገቦቹ በሙሉ አዘጋጁ ሞርሞን ይህን ትንሽ ተጨማሪ ጻፈ። (“ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ” በመፅሐፈ ሞርሞን መጀመሪያ ውስጥ ተመልከቱ።)

መፅሐፈ ሞርሞን፣ መፅሐፈ ሞርሞን ተብሎ በሚታወቀው ቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የሚገኝ የተለየ መጽሐፍ። ምዕራፍ ፩–፪ የኔፋውያን ነቢይ አማሮን ሞርሞን ሰሌዳዎችን መቼና የት እንደሚያገኛቸው ስላስተማረው ይናገራሉ። ደግሞም፣ ታላቁ ጦርነት ተጀመረ፣ እናም ሶስቱ ኔፋውያን በህዝብ ክፋት ምክንያት ተወሰዱ። ምዕራፍ ፫–፪ ሞርሞን ለህዝቦቹ ንስህ ስለመግባት መስበኩ ይናገራሉ። ነገር ግን ስሜት የሚሰማቸው አልነበሩም እናም በእስራኤል ውስጥ ከነበረው ክፋት ሁሉ በላይ ታላቅ ክፋት ተባዛ። ምዕራፍ ፭–፯ በኔፋውያን እና በላማናውያን መካከል የመጨረሻ ጦርነት ይመዘግባሉ። ሞርሞን ከብዙዎቹ የኔፋውያን ህዝቦች ጋር ተገደለ። በምዕራፍ ፯ ውስጥ፣ ከመሞቱ በፊት፣ ሞርሞን እዚያ ያሉትን እና የወደፊት ህዝቦቹን ንስሀ እንዲገቡ ጠራ። ምዕራፍ ፰–፱ በመጨረሻም የሞርሞን ልጅ ሞሮኒ ብቻ በህይወት እንደቀረ ይመዘግባል። የኔፋውያን ህዝብ መጨረሻን የሚጨምር የመጨረሻውን የሞትና የጭፍጨፋ ትእይንትን መዘገበ፣ እናም ለወደፊት ትውልዶችና ይህም መዝገብ ለሚያነቡት መልእክት ጻፈ።

ሞሮኒ፣ ሻምበል። *ደግሞም የነፃነት አርማ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በ፪ ም.ዓ. አካባቢ የኖረ ጻድቅ የኔፋውያን የወታደሮች አዛዥ።

ሞሮኒ በኔፋውያን ወታደሮች ላይ ሙሉ በሙሉ አዛዥ ነበር፣ **አልማ** ፵፫፡፲፯–፲፯። የተነሳሱ የኔፋውያን ወታደሮች ለነጻነታቸው ተዋጉ፣ **አልማ** ፵፫፡፴፤–፴። በኮቱ ቁራጭ ላይ የነፃነት አርማ ሰራ፣ **አልማ** ፵፮፡፲፪–፲፫። የእግዚአብሔር ሰው ነበር፣ **አልማ** ፵፭፡፲፩–፲፤። የሀገራቸውን ነፃነት በተመለከተ በመንግስቱ ግዴለሽነት ተቆጥቶ ነበር፣ **አልማ** ፶፬፡፲፣ ፶፫።

ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፣ ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ ተመልከቱ*

በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ የመጨረሻው የኔፋውያን ነቢይ (በ፬፻፷፭ ዓ.ም. አካባቢ)። ከሞርሞን ሞት በፊት፣ የሞርሞን ሰሌዳዎች ተብለው የሚጠሩትን የታሪክ መዝገቦች ለልጁ ሞሮኒ ሰጠ (ቃላት ፩፡፩)። ሞሮኒ የሞርሞን ሰሌዳዎችን ማዘጋጀትን ጨረሰ። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ምዕራፍ ፰ እና ፱ን ጨመረ (ሞር. ፰፡፩)። መፅሐፈ ኤተርን አሳጥሮ ጻፋቸውና ጨመራቸው (ኤተር ፩፡፩–፪) እናም መፅሐፈ ሞርሞን የሚባለውን የእርሱን መፅሐፍ ጨመረ (ሞሮኒ ፩)። ሞሮኒ ሰሌዳዎችን አተመ እና በከሞራ ኮረብታ ውስጥ ደበቃቸው (ሞር. ፰፡፲፭፣ ሞሮኒ ፲፡፪)። በ፲፰፻፷፫ (እ.አ.አ.) ሞሮኒ ከሞት እንደተነሳ ሰው መፅሐፈ ሞርሞንን ለጆሴፍ ስሚዝ እንዲገልፅ ትልኮ ነበር። (ት.እና ቃ. ፳፯፡፩፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴–፴፪፣ ፴፯)። ወጣቱን ነቢይ ከ፲፰፻፷፫ እስከ ፲፰፻፷፯ (እ.አ.አ.) አስተማረው

መፅሐፈ ሞዛያ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኝ መፅሐፍ። ምዕራፍ ፩–፯ ንጉስ ቢንያም ለሕዝቡ የሰጠውን ሀይለኛ ስብከት የያዙ ናቸው። የጌታ መንፈስ ልባቸውን ነካቸው እና ህዝቡም ተቀየሩ፣ እንዲሁም ክፉ ለማድረግ ምንም ፍላጎት አይሰማቸውም። ምዕራፍ ፯–፰ በላማናውያን ምድር ለመኖር ስለሄዱ የኔፋውያን ቡድን ይናገራሉ። የሚፈልጓቸው ቡድን መሪ አሞን አገኛቸው እናም በላማናውያን ጭቆና ስር ስለነበራቸው ፈተናዎች ታሪክ ተማረ። ምዕራፍ ፱–፳፪ ያን ጭቆና እና እንዴት መሪአዎቻቸው ዜኒፍ፣ ኖኅ፣ እና ሊምሂ በላማናውያን ስር እንደ ኖሩ ይገልጻሉ። አቢናዲ ተብሎ የሚጠራው ነቢይ ሰማዕትም ተመዝግቧል። አልማ አቢናዲ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ተቀየረ። ምዕራፍ ፳፭–፳፰ የአልማ ልጅ እና የንጉስ ሞዛያ አራት ልጆች እንዴት እንደተቀየሩ ታሪክን ይነግራሉ። በምዕራፍ ፳፱ ውስጥ ንጉስ ሞዛያ የመሳፍንት መንግስት ንጉሶችን እንዲ ተኩ ሀሳብ አቀረበ። የአልማ ልጅ አልማ ዋና ዳኛ እንዲሆን ተመረጠ።

ሞዛያ፣ የቢንያም አባት። *ደግሞም* ቢንያም፣ የሞዛያ አባት፤ ዛራሔምላ *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በዛራሔምላ ህዝብ ላይ ንጉስ እንዲሆን የተደረገ የኔፋውያን ነቢይ።

ከኔፊ ምድር እንዲወጣ ተጠነቀቀ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፪። የዛራሔምላ ህዝብን አገኘ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፰–፲፭። የዛራሔምላ ህዝብ የእርሱን ቋንቋ እንዲማሩ አደረገ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፭። በአንድነት የተዋሃዱ ህዝብ ንጉስ እንዲሆን ተመደበ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፱። ከሞተ በኋላ፣ ልጁ ቢንያም በምትኩ ነገሰ፣ **ኦምኒ** ፩፡፳፫።

ሚኪ አባት። *ደግሞም* ቤተሰብ፤ ወላጆች፤ የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ፤ የፓትሪያርክ በረከቶች *ተመልከት*

ልጅን ለወለደ ወይም በጉዲፈቻ ላሳደገ ሰው የሚሰጥ ቅዱስ ርዕስ።

አባትህንና እናትህን አክብር፣ **ዘፀአ.** ፳፡፲፪ (ዘዳግ. ፭፡፲፮፣ ማቴ. ፲፱፡፲፱፣ ሞዛያ ፲፫፡፳)። አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚገሥጽ፣ **ምሳ.** ፫፡፲፪።

አባቶች ሆይ፡ አታስቆጡአቸው፣ **ኤፌ.** ፮፡፩–፬።

አባቴ ከሚያውቃቸው በመጠኑ ተማርኩ፣ **ፊ ኔፊ** ፩፡፩። አባቴ ፃድቅ ሰው ነበር—አስተማሮኛልና፣ **ኢኖስ** ፩፡፩። አልማ ለልጁ ጸለየ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፲፬። አልማ ለልጆቹ ትእዛዛትን ሰጠ፣ **አልማ** ፴፯–፴፱። ሔለመን ልጆቹን የቅድመ አያቶቹን ስም ሰጣቸው፣ **ሔለ.** ፭፡፮–፲፪። ሞርሞን ልጁን በጸሎቱ ሁልጊዜ ያስታውሳል፣ **ሞሮኒ** ፰፡፪–፫።

(ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፩) እና በመጨረሻም በ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) ሰሌዳዎችን ለእርሱ ሰጠው (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፩)። መተርጎምን ከጨረሰ በኋላ ጆሴፍ ስሚዝ ሰሌዳዎችን ለሞሮኒ መለሰ።

መፅሐፈ ሞሮኒ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የመጨረሻው መፅሐፍ። የተጻፈው በኔፋውያን የመጨረሻ ነቢይ ሞሮኒ ነበር። ምዕራፍ ፩–፫ ስለኔፋውያን የመጨረሻ መደምሰስ ይናገራሉ፣ መንፈስ ቅዱስን እና ክህነትን ስለመስጠት መመሪያ ይሰጣሉ። ምዕራፍ ፬–፭ የቅዱስ ቁርባንን ማስተዳደር ዘዴን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፮ የቤተክርስቲያናን ስራ በማጠቃላል ይገልጻል። ምዕራፍ ፯–፰ ከሞርሞን የእምነት፣ ተስፋና፣ ልግስና ትምህርት እና ጥሩን ከመጥፎ ስለመፍረድ መንገድ በተጨማሪ የወንጌልን ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆች (ሞሮኒ ፯)፣ እናም ትንሽ ልጆች በክርስቶስ ሀያው የሆኑና ጥምቀት እንደማያስፈልጋቸው ሞሮኒ የገለጸበት (ሞሮኒ ፰) ስብከቶች ናቸው። ምዕራፍ ፱ የኔፋውያን ህዝቦች በስነምግባር የጎደለ እንደነበረ ይገልጻል። ምዕራፍ ፲ የሞሮኒ የመጨረሻ መልእክት ነው እናም በተጨማሪ መፅሐፈ ሞርሞን እውነት እንደሆነ የሚታወቅበትን መንገድ ይገልጻል (ሞሮኒ ፲፡፫–፮)።

ሞሮኒሀ፣ የሻንበል ሞሮኒ ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ጻድቅ የኔፋውያን አዛዥ (በ፰ ዓ.ዓ. አካባቢ)።

ሞሮኒ ሞሮኒሀ ተብሎ ለሚጠራው ልጁ የሠራዊቱን መሪነት አሳልፎ ሠጠ፣ **አልማ** ፰፡፭፡፴፫። የዛራሔምላን ከተማ በድጋሚ ወሰደ፣ **ሔለ.** ፩፡፴፫። ኔፋውያን ንስሀ እንዲገቡ አደረገ እናም በምድር ግማሽ ላይ ቁጥጥርን በዳግም አገኘ፣ **ሔለ.** ፬፡፲፬–፳።

ሞአብ። *ደግሞም* ሎጥ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ጊዜ በሙት ባህር በስተምስራቅ በኩል የሚገኝ ምድር። ሞዓባውያን የሎት ትውልዶች ነበሩ እናም ከእስራኤላውያን ጋር ዘመድ ነበሩ። ከዕብራውያን ቋንቋ ጋር የሚመሳሰል ቋንቋ ነበራቸው። በሞአባውያንና በእስራኤላውያን መካከል የማይቆም ጦርነት ነበረ (መሳ. ፫፡፲፪–፴፣ ፲፩፡፲፣ ፲፯፡፲፣ ፪ ሳሙ. ፰፡፪፣ ፪ ነገሥ. ፫፡፭–፳፯፣ ፪ ዜና ፳፡፩–፳፭፣ ኢሳ. ፲፭)።

ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ። *ደግሞም* ቢንያም፣ የሞዛያ አባት፤ የሞዛያ ልጆች *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፋውያን ጻድቅ ንጉስ እና ነቢይ። ሞዛያ የአባቱን ጻድቅ ምሳሌ ተከተለ (ሞዛያ ፤፡፩–፯)። የያሬዳውያን መዝገቦችን የያዙትን ሀያ አራት የወርቅ ሰሌዳዎች ተረጎመ (ሞዛያ ፳፰፡፲፯)።

ታላላቅ ነገሮች ከአባቶቻቸው እጅ ይጠበቃል፣ ት. እና ቃ. ፯፤፱፡፳፯። ቤተሰቡን የማስተዳደር ሀላፊነት እያንዳንዱም ሰው አለበት፣ ት. እና ቃ. ፹፭፡፳፯።

ወደ አባቴ እንድሄድ አዘዘኝ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፭፡፳፱።

ሩት። *ደግምም ቦኤዝ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ እስራኤላውያን ለሆኑት ኑኃሚ እና አቢሜሌክ አማች የነበረች የሞአብ ሴት። ከባሏ ሞት በኋላ፣ ሩት የኒኃሚን ዘመድ ቦዔዝን አገባች። ልጃቸው ኢዮቤድ የዳዊት እና የክርስቶስ ትውልድ ነበር። የሩት ታሪክ እስራኤላዊ ያልሆነችውን ወደ እስራኤል እቅፍ መቀየርን በደንብ ያሳያል። ሩት የድሮ ጣዖቷን እና የድሮ ህይወቷን የእስራኤል እግዚአብሔርን ከሚያገለግል የእምነት ቤት ጋር አንድ ለመሆን ተወች (ሩት ፩፡፲፮)።

መፅሐፈ ሩት፣ ምዕራፍ ፩ በሞአብ ውስጥ የነበራቸውን የአቢሜሌክ እና የቤተሰቡን ህይወት ይገልጻል። ከባላቸው ሞት በኋላ፣ ኑኃሚ እና ሩት ወደ ቤተልሔም ሄዱ። ምዕራፍ ፪ ሩት ከቦዔዝ ሜዳ ውስጥ እንደ ቃረመች ይገልጻል። ምዕራፍ ፫ ኑኃሚ ሩትን ወደ አውድማ እንድትሄድ እና በቦዔዝ እግር ስር እንድትወድቅ እንዳስተማረቻት ይናገራል። ምዕራፍ ፬ የሩት እና የቦዔዝ ጋብቻ ታሪክ ነው። ኢዮቤድ የሚባል ወንድ ልጅ ወለዱ፣ በእርሱም ትውልድ ዳዊት እና ክርስቶስ ተወለዱ።

ሪግደን፣ ስድኒ

በ፲፰፻፱ እና በ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ መካከል በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ በመጀመሪያ የተቀየረ እና መሪ የነበረ ሰው። ስድኒ ሪግደን ለአንድ ጊዜ በቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ውስጥ የጆሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ አማካሪ ነበር (ት. እና ቃ. ፴፭፣ ፴፰፡፱፣ ፴፱፣ ፵፫፡፴፭–፴፮፣ ፹፭፡፲፭–፲፰፣ ፲፱–፳፫፣ ፶፡፮፣ ፶፭፡፴፬፣ ፹፬፡፲–፲፭)። በኋላም ወደቀ እናም በመስከረም ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) ተወገዘ።

ራሔል። *ደግምም ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ ሚስት (ዘፍጥ. ፳፱–፴፭፣ ፴፯)። ደግሞም የዮሴፍ እና የቢንያም እናት ነች።

ራሜዩምጵቶም

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ሀይማኖትን የካዱት ኔፋውያን የሆኑት ዞራማውያን የጸለዩበት ከፍ ያለ የመቆሚያ ቦታ (አልማ ፴፭፡፳–፲፱፣ ፳፭)።

ራዕይ። *ደግምም ህልም፤ መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ መንፈስ ቅዱስ፤ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፤ ትንቢት፣ መተንበይ፤ የመጀመሪያው ራዕይ፤ የእግዚአብሔር ቃል፤ ድምፅ ተመልከቱ*

እግዚአብሔር በምድር ላይ ካሉት ልጆቹ ጋር የሚነጋገርበት። በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል የአንድ ድርጊት፣ ሰው፣ ወይም ነገር የሚታይ ራዕይ። ራዕይ በክርስቶስ ብርሀን ወይም በመንፈስ ቅዱስ በኩል በማነሳሳት፣ በራዕዮች፣ በህልሞች፣ ወይም በመላእክት በመትብገት ሊመጣ ይችላል። ራዕይ ታማኝን በሰለስቲያል መንግስት ወደ ዘለአለማዊ ደህናነት ለመምራት የሚችል መመሪያን ይሰጣል።

ጌታ ስራውን ለነቢያቱ ይገልጻል እናም ለነቢያቱ የተሰጡት ራዕዮች እውነት እንደሆኑም ለሚያምኑት ያረጋግጣል (ዓሞ. ፫፡፯)። በራዕይ በኩል፣ ጌታ ለሚፈልገው እና እምነት ላለው፣ ንስሀ ለገባው፣ እንዲሁም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ታዛዥ ለሆነው ለእያንዳንዱ ሰው መመሪያ ይሰጣል። ጆሴፍ ስሚዝ እንዳለው፣ "መንፈስ ቅዱስ ገላጭ ነው፣ ማንም ሰው ራዕይን ሳይቀበል መንፈስ ቅዱስን መቀበል አይችልም።"

በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ የቀዳሚ አመራር እና የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም ነቢያት፣ ባለራዕዮች፣ እና ገላጮች ናቸው። ጌታ ለቤተክርስቲያኗ ራዕይ ለመቀበል ስልጣን የሰጠው ለቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት ብቻ ነው (ት. እና ቃ. ፳፯፡፪–፭)። እያንዳንዱ ሰው ለእራሱ ጥቅም ራዕይ ለመቀበል ይችላል።

ሕዝቅኤል ስለመጨረሻው ቀናት ያየው ራዕይ (ሕዝ. ፴፯–፴፱)፣ እስጢፋኖስ ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል ቆሞ ያየው ራዕይ (የሐዋ. ፯፡፶፭–፶፮)፣ የመጨረሻው ቀናትን በሚመለከት ዮሐንስ ያየው ራዕይ (ራዕ. ፩–፳፩)፣ ሌሂ እና ኔፊ ስለህይወት ዛፍ ያዩት ራዕይ (፩ ኔፊ ፰፣ ፲–፲፪)፣ ዳግማዊ አልማ የጌታ መልአክን ያየበት ራዕይ (ሞዛያ ፳፯)፣ የያሬድ ወንድም የአለምን ኗሪዎችን ሁሉ ያየበት ራዕይ (ኤተር ፫፡፳፭)፣ የክብሮች ራዕይ (ት. እና ቃ. ፹፯) በክርትላንድ ቤተመቅደስ ውስጥ ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ የተሰጣቸው ራዕይ (ት. እና ቃ. ፻፲)፣ ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለሙታን ቤዛነት ያዩት ራዕይ (ት. እና ቃ. ፻፴፯)፣ ስለእግዚአብሔር እና ስለፍጥረቶቹ ለሙሴ የተሰጠ ራዕይ (ሙሴ ፩)፣ ስለእግዚአብሔር ሔሞክ ያየው ራዕይ (ሙሴ ፮–፯)፣ እና የጆሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ራዕይ (ጆ.ስ.—ታ. ፩)።

ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት ይኖራል፣ ዘዳግ. ፰፡፫ (ማቴ. ፬፡፬፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፩)። ጌታ በትንሽ የዝምታ ድምፅ ይናገራል፣ ፩ ነገሥ. ፲፱፡፲፪። ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ምሳ. ፳፱፡፲፰። ጕበዞቻችሁም

ራዕይ ያያሉ፣ ኢዩ. ፪፡፳፰ (የሐዋ. ፪፡፲፯)። በእ ውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም፣ ዓሞ. ፫፡፯።

የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፣ ማቴ. ፲፮፡፲፫–፲፱። መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚመጣውንም ይነግራች ኋል፣ ዮሐ. ፲፮፡፲፫። ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ እግዚአብሔርን ይለምን፣ ያዕ. ፩፡፭።

በራዕይ እውቀትን ሰጥቶኛል፣ ፤ ኔፊ ፬፡፳፫። ሁሉም ነገሮች ይገለፃሉ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፡፲፩። ለሰው ልጆች በስርዐት ላይ ስርዐት እሰጣለሁ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፡፴፡ ያልተገለጠ፣ ሚስጥር የሆነ ምንም የለም፣ ፤ ኔፊ ፴፡፲፯። መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን ሁሉ ያሳያ ችኋል፣ ፤ ኔፊ ፴፤፡፭። ለእርሱ ካልተገለፀለት በቀር ማንም ሰው የእግዚአብሔርን መንገድ አያውቅም፣ ያዕቆ. ፬፡፰። አልማ ለራዕይ ለብዙ ቀናት ያመ እንዲሁም ፀለየ፣ አልማ ፭፡፴፯። ተገልፀው የማያው ቁት ነገሮች ለታማኞች ይገለጻሉ፣ አልማ ፳፯፡፳፤ ራዕይን የሚክዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አያ ውቁም እናም ቅዱሳት መጻህፍት አልተረዱም፣ ሞር. ፱፡፯–፰። እምነታችሁ እስከሚፈተን ድረስ ምስክርነትን አትቀበሉም፣ ኤተር ፲፤፡፯።

ቃሌ ይፈጸማል፣ ት. እና ቃ. ፩፡፴፰። ይህ ንን ነገር በተመለከተ በአምሮህ ሰላምን አልተናገ ርኩም፣ ት. እና ቃ. ፯፡፳፤–፳፫። በአዕምሮህ እና በልብህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፰፡፭–፮። ትክ ክለኛ ከሆነ በውስጥህ ልብህ እንዲቃጠል አደርጋ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ፱፡፰። የራዕይ መንፈስንም አት ካድ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፩። ከጠየቃችሁ፣ በራዕይ ላይ ራዕይን ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፤፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት የጌታ ፈቃድም ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፳፰፡፱። እግዚአብሔር እው ቀቱን ይሰጣችኋል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡፳፯።

ጆሴፍ ስሚዝ አብን እና ወልድን አየ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯። እርሱም ከእግዚአብሔር ፊት የተላከ መል እክተኛ ነበር፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፫። በትንቢቶች፣ ራዕዮች እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፯። እግዚአብሔር እንደገለጸ እና ወደፊትም እንደሚገልፅ እናምና ለን፣ እ.አ. ፩፡፯፣ ፱።

ራጉኤል። ዮቶር *ተመልከቱ*

ራፋኤል። *ደግሞም መላእክት ተመልከቱ*

በሁሉም ነገሮች በዳግም መመለስ የተሳተፈ የእ ግዚአብሔር መልአክ (ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፳፩)።

ርህራሄ። *ደግሞም ልግስና፣ መሀሪ፣ ምህረት፣ ፍቅር ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ርህራሄ ማለት "ከሌላ ጋር መሰቃየት" ማለት ነው። ደግሞም የሀ ዘን ተካፋይነትን፣ የሀዝን ስሜትን፣ እና ምህረትን ማሳየት ማለት ነው።

ጌታ ህዝቡ ሩህሩህ እንዲሆኑ ጠራቸው፣ ዘካ. ፯፡፰–፲።

ኢየሱስ አዘነላቸው፣ ማቴ. ፱፡፴፮ (ማቴ. ፳፡፴፬፣ ማር. ፩፡፴፩፣ ሉቃ. ፯፡፲፫)። አንድ ሳም ራዊ አዘነለት፣ ሉቃ. ፲፡፴፫። አንዳችሁ ለሌላችሁ ርኅሩኆችና ሁኑ፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፰።

ክርስቶስ ለሰዎች ልጆች በርህራሄ ይሞላል፣ ሞዛያ ፲፭፡፱። አንጀቴ ለእናንተ በርህራሄ ተሞ ልቷል፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፮።

ጆሴፍ ስሚዝ ለጌታ ርህራሄ ጸለየ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፫–፭።

ርብቃ። *ደግሞም ይስሐቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የአባቶች አለቃው ይስሐቅ ባለቤት (ዘፍጥ. ፳፬–፳፯)። ርብቃ የዔሳው እና የያዕ ቆብ እናት ነበረች (ዘፍጥ. ፳፭፡፳፫–፳፯)።

ርኩስ። ንጹህ እና ርኩስ *ተመልከቱ*

ሮሜ። *ደግሞም የሮሜ ግዛት ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በጣሊያን ውስጥ በጥብር ያዶስ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ የሮሜ መንግስት ዋና ከተማ (የሐዋ. ፲፰፡፪፣ ፲፱፡፳፣ ፳፫፡፲፩)። ጳው ሎስ የሮሜ መንግስት እስረኛ በነበረ ጊዜ ወንጌሉን በሮሜ ውስጥ አስተማረ (የሐዋ. ፳፰፡፲፩–፴፩፣ ሮሜ ፩፡፯፣ ፲፭–፲፮)።

ሮቤል። *ደግሞም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ የመ ጀመሪያ ልጅ (ዘፍጥ. ፳፱፡፴፪፣ ፴፭፡፳–፳፪፣ ፳፱፣ ፴፪፡፳፪፣ ፴፯)። ሮቤል በኩር ቢሆንም፣ በኃ ጢያት ምክንያት በኩሩን አጣ (ዘፍጥ. ፴፭፡፳፪፣ ፴፱፡፫–፴)።

የሮቤል ጎሳ፣ ያዕቆብ ለሮቤል የሰጣቸው በረ ከቶች በኦሪት ዘፍጥረት ፴፱፡፫ እና ኦሪት ዘዳግም ፴፫፡፮ ውስጥ ይገኛሉ። የጎሳው ቁጥር ጥቂት በጥ ቂት እየቀነሰ መጣ፣ እናም ምንም እንኳን ጎሳው ቢኖርም፣ በፖለቲካ አስፈላጊነታቸው ታናሽ ነበር። የሮቤል በኩራት ለዮሴፍ እና ለልጆቹ ሆነ ምክንያ ቱም ዮሴፍ የያዕቆብ ሁለተኛ ሚስት የራሔል በኩር ስለነበረ ነው (፩ ዜና ፭፡፩–፪)።

ሮብዓም። *ደግሞም ሰለሞን ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የንጉስ ሰለሞን ልጅ። አባቱን ተካ እናም በኢየሩሳሌም ውስጥ ነገሰ (፩ ነገሥ. ፲፩፡፴፫፣ ፲፬፡፳፩፣ ፴፩)። በሮብዓም ዘመነ መንግስት፣ መንግስቱ በሰሜን ወደ እስራ

ኤል መንግስት እና በደቡብ ወደ ይሁዳ መንግስት ተከፋፈለ (፩ ነገሥ. ፲፩፡፴፭–፴፯፣ ፲፪፡፲፱–፳)። ሮብዓም የይሁዳ መንግስትን ገዛ።

ሰለሞን። *ደግምም* ቤርሳቤህ፣ ዳዊት *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የዳዊት እና የቤርሳቤህ ልጅ (፪ ሳሙ. ፲፪፡፳፬)። ሰለሞን ለጊዜ የእስራ ኤል ንጉስ ነበር።

ዳዊት ሰለሞንን እንደ ንጉስ መደበ፣ ፩ ነገሥ. ፩፡፲፩–፶፣ ዳዊት ሰለሞንን በጌታ መንገዶች በቅ ንነት እንዲራመድ አዘዘው፣ ፩ ነገሥ. ፪፡፩–፱። ጌታ የማስተዋል ልብ እንደሚኖረው ቃል ኪዳን ሰጠው፣ ፩ ነገሥ. ፫፡፭–፲፭። በሁለት እናቶች መካከል ፈረደ እናም የልጁን እውነተኛ እናትን አረጋገጠ፣ ፩ ነገሥ. ፫፡፲፮–፳፰። ምሳሌዎችንና መኃልዩንም ተናገረ፣ ፩ ነገሥ. ፬፡፴፪። ቤተመቅደስን ገነባ፣ ፩ ነገሥ. ፮፣ ፯፡፲፣–፶፩። ቤተመቅደስን ቀደሰ፣ ፩ ነገሥ. ፰። በሳባ ንግስት ተጎበኘ፣ ፩ ነገሥ. ፣፡፩–፣፣፡። ሰለሞን ከእስራኤል ውጪ አገባ፣ እናም ሚስቶቹም የሀሰት መላእክቶችን ወደማምለክ ልቡን አዞሩ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፩–፰። ጌታ በሰለሞን ላይ ተቆጣ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፱–፣፣፡። ሞተ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፴፣፡። ዳዊት ስለ ሰለሞን ጋዛት ግርማ ተነበየ፣ መዝ. ፷፪።

ሰለሞን ብዙ ሚስቶች እና እቁባቶችን ተቀበለ፣ ነገር ግን አንዳንዶቹ ከጌታ የተቀበላቸው አልነበ ሩም፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፰ (ያዕቆ. ፪፡፳፭)።

ሰላም። *ደግምም* ሰላም የሚሰራ፣ አንድ ሺህ አመት፣ እረፍት *ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ሰላም ከጸብ እና ብጥበጣ ነጻ መሆን ወይም ለታማኝ ቅዱሳኑ እግዚ አብሔር በሚሰጠ መንፈስ የሚመጡ የውስጥ መረ ጋጋት እና ምቾት ማለት ነው።

ከጥላቻ እና ከብጥበጣ ነጻ መሆን፣ ጦርንም ይቄርጣል፣ መዝ. ፴፮፡፱። ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም፣ ኢሳ. ፪፡፬።

ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፣ ራሳችሁ አት በቀሉ፣ ሮሜ ፲፪፡፣፡–፳፩።

በምድሪቱ ሠላም ሰፈነ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፬፣ ፣፲–፳።

ጦርነትን አስወግዱና ሰላም አውጁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፡፣፣ ፣፣፮። የሰላም ምልክት ያንሱ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፩፡፴፱።

ለታዛዥ ከእግዚአብሔር የሚመጣ ሰላም፣ አዳኝ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፣ ኢሳ. ፱፡፮። ለክፉ ዎች ሰላም የላቸውም፣ ኢሳ. ፴፣፡፳፪።

ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር እግዚአ ብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአ ርያም ይሁን ሰላምም በምድር አሉ፣ ሉቃ. ፪፡፣፣–፣፬። ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ዮሐ. ፣፬፡፳፯። የእ ግዚአብሔር ሰላም አሳባችሁን ይጠብቃል፣ ፊልጵ. ፬፡፯።

የንጉስ ቤንያምህዝብ የሀሊና ሰላምን ተቀበሉ፣ ሞዛያ ፪፡፣። በተራራው ላይ ሰላምን የሚያውጁት እግራቸው እንዴት ያማረ ነው፣ ሞዛያ ፣፲፡፣፬–፣፣ (ኢሳ. ፶፪፡፯)። አልማ ወደ ጌታ ጮኸ እናም ሰላ ምን አገኘ፣ አልማ ፴፣፡፣። የዓድቃኖች መንፈስ ወደ ሰላም ቦታ ይገባሉ፣ አልማ ፴፣፡፲፪።

ይህንን ነገር በተመለከተ በአምሮህ ሰላምን አል ተናገርኩም፣ ት. እና ቃ. ፣፯፡፣፣። ከእኔ ተማር፣ እናም ቃላቴን አድምጥ፣ በመንፈሴ በትህትና ተጓዝ፣ እናም በእኔ ሰላምን ታገኛለህ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፱፡፣፣። የጻድቅ ስራ የሚሰራው ሰላም ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፣፣። የፍጹምነትና የሰላም ማሰ ሪያ በሆነው በልግስና ማሰሪያ ራሳችሁን አልብሱ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፣ ፣፣፣፩። ልጄ፣ በነፍስህ ሰላም ይኑርህ፣ ት. እና ቃ. ፣፣፣፩፡፣። ታላቅ ሰላም እንዳሉም ስላወኩኝ፣ የአባቶችን በረከቶች ለማግኘት ፈለኩኝ፣ አብር. ፩፡፪።

ሰላም የሚሰራ። *ደግምም* ሰላም *ተመልከቱ*

ሰላምን የሚያመጣ ወይም የሚያበረታታ ሰው (ማቴ. ፭፡፱፣ ፣ ኔፊ ፣፪፡፱)። የሰላም የሚሰራ ወን ጌልን የሚያውጅ ሊሆንም ይችላል (ሞዛያ ፣፲፩፡፣፩–፣፣)።

ሰሌዳዎች። *ደግምም* መፅሐፈ ሞርሞን፣ የወርቅ ሰሌዳዎች *ተመልከቱ*

መፅሐፈ ሞርሞን እንደነበረው፣ በጥንት ጊዜ አን ዳንድ ባህሎች ታሪካቸውንና መዝገባቸውን በብ ረት ሰሌዳዎች ላይ ይጽፉ ነበር። ለተጨማሪ መዝገ ቦች፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ማስተዋወቂያ ገጾች ውስጥ "ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ" የሚለውን ተመልከቱ።

ሰማርያ። *ደግምም* ሳምራዊ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሰሜን እስራኤል መን ግስት ዋና ከተማ (፩ ነገሥ. ፣፮፡፳፣–፳፬)። በኮረ ብታ ላይ በነበራት ጠንካራ ወታደራዊ ቦታ፣ አሶር እስከ ሶስት አመት በጦር ከበባ ድረስ እርሷን ለመ ያዝ አልቻሉም ነበር (፪ ነገሥ. ፣፯፡፭–፮)። ሄሮድስ እንደገና ገነባት እና ሰባስቴ ብሎ ጠራት። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ውስጥ፣ ሰማርያ በዮርዳኖስ በስተምዕ ራብ ለሚገኘው የፍልስጥኤም አውራጃ በሙሉ የተ ሰጠ ስም ነው።

ሰማዕት፣ ሰማዕትነት

ክርስቶስን፣ ወንጌልን፣ ወይም ጻድቅ እምነቱን ወይም መሰረታዊ መርሆቹን ከመካድ ህይወቱን አሳ ልፎ የሚሰጥ ሰው።

ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ደም

ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ በክፉዎች ላይ ይመሰክራሉ፣ ማቴ. ፳፫፡፴፭ (ሉቃ. ፲፩፡፶)። ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያድናታል፣ ማር. ፰፡፴፭ (ት. እና ቃ. ፶፰፡፲፫)። እስጢፋኖስን ወገሩት፣ የሐዋ. ፯፡፶፱ (የሐዋ. ፳፪፡፳)። ኑዛዜ ያለ እንደሆነ የተናዛዥን ሞት ማርዳት የግድ ነው፣ ዕብ. ፱፡፲፮–፲፯።

አቢናዲ በእሳት ሞቶ ወደቀ፣ ሞዛያ ፲፯፡፳። የተቀየሩት አሞኒሀውያን ወደ እሳት ተጣሉ፣ አልማ ፲፭፡፳–፲፩። ብዙዎች ስለእነዚህ ነገሮች በመመስከራቸው ተገድለዋል፣ ፫ ኔፊ ፲፡፲፭።

ለምክንያቱ ህይወቱን የሚሰጥም ስለአለማዊ ህይወትን ያገኘዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፲፫–፲፭። ጆሴፍ ስሚዝ እና ሐይረም ስሚዝ በዳግም ለተመለሰው ወንጌል ሰማዕት ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፭። ጆሴፍ ስሚዝ ምስክሩን በደሙ አተመ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፮፡ ፴፱።

ሰማይ። *ደግሞም የሰለስቲያል ክብር፤ የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት፤ ገነት ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ሰማይ ሁለት ትርጉሞች አሉት። (፩) እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ እና የቅዱሳን የወደፊት ቤት (ዘፍጥ. ፳፰፡፲፪፤ መዝ. ፲፩፡፬፤ ማቴ. ፮፡፱)። (፪) ምድርን የሚከብ ሰፊና ገላጣ ቦታ (ዘፍጥ. ፩፡፩፤ ፲፯፤ ዘፀአ. ፳፬፡፲)። ሰማይ በዚህ ምድር ላይ በፅድቅ በመሆን የኖሩ እናም የሞቱ ታማኝ መንፈሶች ለጊዜአዊ የሚገኙበት ቦታ የሆነው ገነት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ገነትን ጎበኘ፣ ነገር ግን በሶስተኛው ቀን ወደ አብ ገና እንዳልሄደ ለማርያም ነግሯት ነበር (ሉቃ. ፳፫፡፴፱–፴፪፤ ዮሐ. ፳፡፲፯፤ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፲፩–፴፯)።

የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን አየሁ፣ መዝ. ፰፡፫። በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፣ መዝ. ፴፫፡፮። አንተ የንጋት ልጅ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ፣ ኢሳ. ፲፬፡፲፪ (፪ ኔፊ ፳፬፡፲፪)። ሰማያትም እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ፣ ኢሳ. ፴፬፡፬። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ፣ ኢሳ. ፷፭፡፲፯። እግዚአብሔር የሰማይንም መስኮት ይከፍታል፣ ሚል. ፫፡፲።

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ ማቴ. ፮፡፱ (፫ ኔፊ ፲፫፡፱)። ጻውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፣ ፪ ቆሮ. ፲፪፡፪። ዝምታ በሰማይ ሆነ፣ ራዕ. ፰፡፩ (ት. እና ቃ. ፹፰፡፯–፲፰)።

እስከ መጨረሻው በታማኝነት ከዘለቁ፣ ሰማይ ትቀበላቸዋለች፣ ሞዛያ ፪፡፴፭። በሰማይ ያለው የአባታችሁ ልጆች እንድትሆኑም ያደርጋልና፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፴፭።

በሰማይ ደመና እመጣለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፯። ኤልያስ ሞትን ሳይቀምስ ወደሰማይ ተወሰደ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፫። የክህነት መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡፴፯። ሁለት አይነት የሰማይ ፍጥረቶች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፩።

ፅዮን ወደ ሰማይ ተወሰደች፣ ሙሴ ፯፡፳፫።

ሰቆቃመ ኤርምያስ

በኤርምያስ የተጻፈ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። ግጥም ወይም ኢየሩሳሌም እና የእስራኤል ሀገር በወደቁበት ምክንያት የተጻፉ የሀዘን መዝሙሮች። መፅሐፉ የተጻፈው በ፭፻፸፯ ም.ዓ. አካባቢ ከተማዋ ከወደቀች በኋላ ነበር።

ሰባ። *ደግሞም ሐዋሪያ፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ ወንዶች ሊሾሙበት የሚችሉ ሀላፊነት። ዛሬ፣ የሰባ ቡድኖች የቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ባለስልጣኖች እና የክልል አመራሮች ናቸው። ሰባዎች በቀዳሚ አመራር እና በአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አመራር ስር በጌታ ስም ያገለግላሉ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፱)። ሙሉ ጊዜ አቸውን ለማስተማር ይሰጣሉ።

ከጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፣ ሉቃ. ፲፡፩።

ሰባዎቹ ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ እና ልዩ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭–፳፯። ሰባዎች፣ በአስራ ሁለቱ አመራር በኩል ቤተክርስቲያኗን በመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ በመቆጣጠር በጌታ ስም ሰሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፱። ስራው የሚያስፈልገው ከሆነ ሌሎች ሰባዎች፣ እንዲሁን ሰባት ጊዜ ሰባ፣ ምረጥ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፫–፶፯። የሰባዎች ቡድን የተመሰረተው የሚጓዙ ሽማግሌዎች በአለም ሁሉ ስለ ስሜ እንዲመሰክሩ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፴፯–፲፴፱።

ሰው፣ ሰዎች። *ደግሞም መንፈስ፤ ሴት፤ ሴቶች፤ እህት፤ እግዚአብሔር፤ አምላክ፤ ወንድሞች፤ ወንድም፤ የመንፈስ ፍጥረት፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች ተመልከቱ*

ስለሁሉም የሰው ዘር፣ ወንድ እና ሴቶች፣ የሚናገር ነው። ሁሉም ወንዶችና ሴቶች የሰማይ አባት የመንፈስ ልጆች ናቸው። በሚሞት ሰውነት ሲወለዱ፣ ስጋዊና ሟች ሰውነቶችን ተቀበሉ። እነዚህ ሰውነቶች የተፈጠሩት በእግዚአብሔር መልክ ነበር (ዘፍጥ. ፩፡፳፯–፳፯)። አስፈላጊ የሆኑትን ስነስርዓቶች ለመቀበል ብቁ የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች፣ ቃል ኪዳኖችን በማክበር፣ እናም የእግዚአብሔር ትእዛ

ዛትን በማክበር ወደዘለአለማዊነታቸው ለመግባትና እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ይችላሉ።

እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ ዘፍጥ. ፩፡፳፯ (ሞዛያ ፯፡፳፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡፲፣–፲፰)። ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው፣ መዝ. ፰፡፬–፮። በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ርጉም ነው፣ ኤር. ፲፯፡፭ (፪ ኔፊ ፱፡ ፡፡፡፣ ፳፰፡፳፯፣ ፳፯፣ ፡፡፩)።

ኅልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ፣ ፮ ቆሮ. ፲፫፡፲፩።

ሰዎች የሚኖሩትም ደስታም እንዲኖራቸው ዘንድ ነው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፭። ፲፱ ተፈጥሮአዊው ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ነው፣ ሞዛያ ፫፡፲፱። እናንተ ምን ዐይነት ሰዎች መሆን ይገባችኋል፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፳፯።

የሰው ስራ እንጂ የእግዚአብሔር ስራ አይሰናከልም፣ ት. እና ቃ. ፫፡፫። ሰውን ከእግዚአብሔር አስበልጠህ መፍራት አልነበረብህም፣ ት. እና ቃ. ፫፡፯ (ት. እና ቃ. ፡፡፡፣ ፲፳፪፡፱)። ሁሉም ነገሮች የተፈጠሩት ለሰው ጥቅም ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፰።

ሰው ምንም እንዳልሆነ አወቅኩኝ፣ ሙሴ ፩፡፲። የእግዚአብሔር ስራና ክብር የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት ማምጣት ነው፣ ሙሴ ፩፡ ፡፡፡።

ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ፣ እነርሱም በግምባራቸው ወድቀው፣ አምላክ ሆይ፥ አንተ የሰው ሁሉ ነፍስ አምላክ ነህ አሉ፣ ዘኁል. ፲፮፡፳፪ (ዘኁል. ፳፯፡፲፮)። እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፣ ዘዳግ. ፲፬፡፩። አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፣ መዝ. ፹፪፡፮። የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ፣ ሆሴ. ፩፡፲። ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን፣ ሚል. ፪፡፲።

የእግዚአብሔር ዘመዶች ነን፣ የሐዋ. ፲፯፡፳፱። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን መንፈስ ይመስክራል፣ ሮሜ ፰፡፲፮። ለመናፍስት አባት ልንገዛ ተገባን፣ ዕብ. ፲፪፡፱።

የሰዎች መንፈስ ሁሉ ህይወትን ወደ ሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፣ አልማ ፴፡፲፩።

የአለሞች ኗሪዎችም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፱። ሰው ደግሞ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፫፣ ፳፱።

እግዚአብሔር አምላክም ከምድር ፊት በፍጥረታዊ አካል ከመፈጠራቸው በፊት በመንፈሳዊ አካል ፈጥሮአቸዋል፣ ሙሴ ፫፡፭–፯። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ አለምንና ስጋ ከማግኘታቸው በፊት ሰዎችን የፈጠርኩኝ ነኝ፣ ሙሴ ፮፡፶፭።

የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመ ሆን ያለው ችሎታ፣ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፣ ማቴ. ፭፡፴፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፴፰)። አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን፣ ዮሐ. ፲፡፴፬ (ት. እና ቃ. ፷፮፡፶፰)። የእግዚአብሔር ወራሾች ነን ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፣ ሮሜ ፰፡፲፯። ልጅ ነህ፣ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ፣ ገላ. ፬፡፯። ሲገለጥ፣ እርሱን እንመስላለን፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፪። ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ፣ ራዕ. ፫፡፳፩።

ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሰጠ ኋቸው፣ ፫ ኔፊ ፩፡፲፯።

ሰለስቲያል መንግስትን የሚወርሱ አማልክቶች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፷፮፡፹፣ ፹፰። ከእዚያም እነርሱም አምላኮች ይሆናሉ፣ ምክንያቱም ሀይል ስለሚኖራቸው፣ ት. እና ቃ. ፪፴፪፡፳።

ሰውነት። *ደግሞም ስጋዊ ሞት፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ትንሳኤ፣ ነፍስ ተመልከቱ*

በእግዚአብሔርም ምስል ተፈጥሮ ከመንፈስ ጋር በመጣመር ህያው ሰውን የሚሰራ ስጋዊ፣ የስጋና የአጥንት የሰውነት አካል። የወንድ እና ሴት ሰዎች አካላዊ ሰውነቶች በትንሳኤ ከመንፈሳቸው ጋር ለዘለአለም ተመልሰው ይጣመራሉ። ቅዱሣት መጻህፍት አብረው የተጣመሩትን ሰውነት እና መንፈስ እንደ ነፍስ ይጠሩታል (ዘፍጥ. ፪፡፯፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፭፣ ሙሴ ፫፡፯፣ ፬፣ ፲፬፣ አብር. ፭፡፯)።

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ ዘፍጥ. ፪፡፯ (ሙሴ ፫፡፯)።

መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፱። ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፣ ፩ ቆሮ. ፱፡፳፯። ፍጥረታዊ አካል አለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፴፩። ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ነው፣ ያዕ. ፪፡፳፮።

የሚሞተው ሰውነት ወደ ማይሞተው ሰውነት ይነሳል፣ አልማ ፲፭፡፴፫–፴፭። ማንኛውም የሰውነት ክፍል ወደ ቀድሞው ይመለሳል፣ አልማ ፴፭፡፪። ኢየሱስ ከሞት የተነሳውን ሰውነቱን ለኔፋውያን አሳየ፣ ፫ ኔፊ ፲፡፲፭–፲፱፣ ፲፭፡፲፫–፲፭።

አብ እንደ ሰው ተጨባጭ የሆነ የስጋ እና አጥንቶች ሰውነት አለው፣ ወልድም ደግሞ እንዲሁ አለው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡፳፪።

እግዚአብሔር በእርሱ ሰውነት አምሳል ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ሙሴ ፮፡፱ (ዘፍጥ. ፱፡፮)።

ሰዎች። *ሰው፣ ሰዎች ተመልከቱ*

ሰይጣን። *ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ሰዱቃውያን። ደግምም አይሁዶች ተመልከቱ

በአይሁዶች መካከል ትንሽ ነገር ግን በፖለቲካ ሀይለኛ የነበሩ ቡድን። ምናልባት በደንብ የሚታ ወቁበት ነገር የሙሴን ህግ በማይለወጥ አስተሳሰብ በቃላቱ በማመናቸው እና የመንፈሳትንና የመላእ ክትን እውነትነት እንዲሁም የትንሳኤን እና የዘ ለአለም ህይወት ትምህርቶችን በመካዳቸው ነበር (ማር. ፲፪፡፲፰–፳፯፤ የሐዋ. ፬፡፩–፮፣ ፳፫፡፯–፱)።

ሰዶም። ደግምም ገሞራ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ በጌታ የተደመሰሰ ኃጢ ያተኛ ከተማ (ዘፍጥ. ፲፱፡፲፪–፳፱)።

ሲያል። ደግምም መንፈሳዊ ሞት፤ ኩነኔ፤ የጥፋት ልጆች፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ

የኋለኛው ቀን ራዕይ ስለሲያል በሁለት አስተ ያየት አለው። መጀመሪያ፣ ይህ በሟችነት ትእ ዛዝ አክባሪ ያልሆኑት ለጊዜ የሚኖሩበት የመንፈስ አለም ነው። በዚህ አስተያየት፣ ሲያል መጨረሻ አለው። በእዚያ ያሉት መንፈሶች ወንጌሉን ይማ ራሉ፣ እናም ንስሀ ከገቡ በኋላም ብቁ ወደ ሆኑበት የክብር ደረጃ በትንሳኤ ይነሳሉ። ንስሀ የማይገቡት፣ ግን የጥፋት ልጆች ያልሆኑት፣ በአንድ ሺህ አመት በሙሉ በሲያል ይቆያሉ። ከእነዚህ አንድ ሺህ አመ ቶች ስቃይ በኋላ፣ ወደ ቲለስቲያል ክብር በትንሳኤ ይነሳሉ (ት. እና ቃ. ፹፯፡፴፯–፴፱፤ ፴፰፡፲–፲፩)።

ሁለተኛ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ያልዳኑት በቋሚነት የሚኖሩበት ቦታ ነው። በዚህ አስተያየት፣ ሲያል ዘላቂ ነው። ይህም ለእነዚያ “ረክሰው ለቀሩት” ነው (ት. እና ቃ. ፴፰፡፴፫፣ ፲፪)። ይህም ሰይጣን፣ መላእክቱ፣ እና አብ ከገለ ጸው በኋላ ወልድን የካዱ የጥፋት ልጆች ለዘለአ ለም የሚኖሩበት ነው (ት. እና ቃ. ፹፯፡፴፣–፴፯)።

ቅዱሣት መጻህፍት አንዳንዴ ሲያልን እንደ ድቅ ድቅ ጨለማ ይገልጹታል።

የዳዊት ነፍስ በሲኦል አትተውም፣ መዝ. ፲፮፡፲ (መዝ. ፴፮፡፲፣)።

እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ወደማይ ጠፋ እሳት ሂድ፣ ማር. ፱፡፵፣ (ሞዛያ ፪፡፴፯)። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አየ፣ ሉቃ. ፲፮፡፳፪–፳፫ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፣)። ሞትና ሲኦ ልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፣ ራዕ. ፳፡፲፣።

የተዘጋጀ ቦታ፣ አዎን፣ እንዲሁም አሰቃቂው ገሀነም አለ፣ ፮ ኔፊ ፲፭፡፴፭። በስጋ ፈቃድ የዲ ያብሎስን መንፈስ ወደ ሲኦል እንዲወስደን ሀይል ይሰጠዋል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፱። ክርስቶስ ከሞት እና ሲያል የምንድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲–፲፪። ረክሰው የቀሩት ወደዘለአለም ስቃይ ይሄዳሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፯። ዲያብሎስ ነፍሳቸውን እንዲህ ያታልላል፣ እናም በጥንቃቄ ወደ ሲኦል ይመራቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፩። ኢየሱስ ነፍሴን ከሲኦል አድኗታል፣ ፪ ኔፊ ፴፫፡፯። ከሲያል ህመም ራሳችሁን ፍቱ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፩። በዲያብሎስ ምርኮ መወሰድ፣ እናም እስከሚጠፉም በፈቃዱ መመራት የሲኦል ሰንሰለትም ማለት ነው፣ አልማ ፲፪፡፲፩። ክፉዎች ወደ ድቅድቅ ጨለማ እስከትንሳኤው ድረስ ይጣላሉ፣ አልማ ፴፣፡፲፣–፲፬። የረከሱት ከእግዚአ ብሔር ጋር መኖር በሲያል ከመኖር በላይ አሰቃቂ ነው፣ ሞር. ፱፡፭።

ከእጁ የሚሰጠው ቅጣት መጨረሻ የሌለው ቅጣት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፣–፲፪። ሲያል ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ የተዘጋጀ ቦታ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፰። እግዚአብሔርን በእምነት የሚቀበሉ ከሞት እና ከሲያል ሰንሰለት ይድናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፰፡፳፣፡፣

ሲድራቅ። ደግምም ዳንኤል ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ሶስቱ የእስራኤል ወጣ ቶች ሲድራቅ፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ከዳንኤል ጋር ወደ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት የተ ወሰዱት ነበሩ። የሲድራቅ የእብራውያን ስም ሐና ንያ ነበር። አራቱ ወጣት ሰዎች ከንጉሱ ስጋና ወይን በመካፈል እራሳቸውን አንበክልም አሉ (ዳን. ፩)። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ወደ እሳት እቶን ተወርውረው ነበር እናም በተአምራት ድነው ነበር (ዳን. ፫)።

ሲፓራ። ደግምም ሙሴ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሙሴ ባለቤት እና የዮቶር ሴት ልጅ (ዘፀአ. ፪፡፳፩፣ ፲፰፡፪)።

ሳሌም። ደግምም መልከ ጼዴቅ፤ ኢየሩሳሌም ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መልከ ጼዴቅ የገዛት ከተማ። በዚህ ቀን በኢየሩሳሌም ቦታ ላይ የምትገኝ ይሆን ነበር። ሳሌም በእብራውያን ቋንቋ “ሰላም” ከሚለው ቃል ጋር የምትመሳሰል ነች።

የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወ ይን ጠጅን አወጣ፣ ዘፍጥ. ፲፬፡፲፰።

የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፣ ዕብ. ፯፡፩–፪።

መልከ ጼዴቅ የሳሌም ምድር ሁሉ ንጉስ ነበር፣ አልማ ፲፫፡፲፣–፲፰።

ሳሙኤል፣ የብሉይ ኪዳን ነቢይ

የሕልቃና እና የሐና ወንድ ልጅ፣ ሳሙኤል የተ ወለደው እንደ እናቱ የጸሎት መልስ ነበር (፩ ሳሙ. ፩)። በልጅነቱ በሴሎ ድንኳን ውስጥ ሊቀ ካህን በሆ ነው ዔሊ እንዲጠብቀው ተሰጠ (፩ ሳሙ. ፪፡፲፩፣ ፫፡፩)። ጌታ በወጣትነቱ ነቢይ እንዲሆን ጌታ

ጠራው (፩ ሳሙ. ፫)። ኤሊ ከሞተ በኋላ፣ ሳሙኤል ታናቅ ነቢይ እና የእስራኤል ዳኛ ሆነ እናም ህግን ስርዓር፣ እና ደንበኛ የሀይማኖት አምልኮን በምድር ውስጥ እንዲገኝ በዳግም መለሰ (፩ ሳሙ. ፬፡፲፩–፲፰፣ ፯፡፣ ፣–፲፣)።

፩ ሳሙ. ፰፡፡–፩–፰ ሳሙኤል በሳያል ጥያቄ ምክንያት የዓይንዶር መናፍስትን የምትጠራ አንዲትን ሴት ከሞት ያመጣበትን ታሪክ የያዘ ነው። ይህም ከእግዚአብሔር የመጣ ራይይም አልነበረም፣ ምክንያቱም መናፍስትን የምትጠራ ሴት ወይም ሌላ ከመናፍስት የሚናገሩት በነቢይ ላይ ተጽእኖ ኖሯቸው በእርሱ ወይም በእርሷ ጥያቄ ሊታይ አይች ልም።

የ፩ እና ፪ ሳሙኤል መፅሐፎች፣ በአንዳንድ መፅሐፍ ቅዱሶች ውስጥ መፅሀፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ እና ካዕል አንድ መፅሀፍ ናቸው። በሌሎች ውስጥ ሁለት መፅሀፎች ናቸው። መፅሐፎቹ ከሳሙኤል መወለድ እስከ ንጉስ ዳዊት መሞት በፊት ድረስ የ፤፡ አመ ታት ጊዜን የሚሸፍኑ ነበሩ።

መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ ምዕራፍ ፩–፣ ጌታ የኤሊ ቤተሰብን እንደረገመና እንደቀጣ እንዲ ሁም ሳሙኤል ሊቀ ካህን እና ዳኛ እንዲሆን እንደ ጠራ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፡–፤ የኪዳን ታቦት በፍ ልስጥኤም እጆች እንደወደቀ ይናገራሉ። ምዕራፍ ፣–፡ የሀሰት አማልክት እና ኃጢያተኛ ንጉስ መኖ ርና ሳሙኤል የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ይመዘግ ባሉ። ምዕራፍ ፤–፲፩ የሳያል መንግስት እና የን ጉስነቱን ግዛት ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፲፪–፴፩ የዳዊ ትን እና ሀይል ያገኘበትን ታሪክ ይነግራሉ—ሳሙ ኤል ጎልያድን የገደለውን ዳዊት ቀባ። ሳያል ዳዊ ትን ጠላ፣ ነገር ግን ዳዊት ምንም እንኳን ይህን ለማ ድረግ እድል ቢኖረውም ሳያልን ለመግደል ፈቃ ደኛ አለነበረም።

መፅሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣ ይህ መፅሐፍ የዳዊ ትን እንደ ይሁዳ እናም በመጨረሻ እንደ እስራ ኤል ሁሉ ንጉስ ዘመነ መንግስት የያዘ ነው። ምዕ ራፍ ፩–፡ በይሁዳ ከተዘወደ በኋላ፣ በዳዊት ተከ ታዮች እና በሳያል ተከታዮች መካከል የነበረውን ትግል ያሳያሉ። ምዕራፍ ፣–፤ ዳዊት በብዙ ምድ ሮች ላይ ሁሉ ሀይለኛ እንደሆነ ያሳያሉ። ምዕራፍ ፤፩–፲፪ ዳዊት በኃጢያቶቹ እና በቤተሰቡ አመፅ ምክንያት መንፈሳዊ ጥንካሬው መዳከሙን ያሳ ያሉ። ምዕራፍ ፳፪–፳፡ ዳዊት ከጌታ ጋር ለመታረቅ የሞከረበትን ይገልጻሉ።

ሳም። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂ ሶስተኛ ወንድ ልጅ (፩ ኔፊ ፪፡፣ ፣)። እርሱም ጌታን ለመከተል የመ ረጠ ጻድቅ እና ቅዱስ ሰው ነበር (፩ ኔፊ ፪፡ ፤፲፣ ፪ ኔፊ ፣፡፣–፣፣ አልማ ፣፡፣)።

ሳምራዊ። *ደግሞም ሰማርያ ተመልከቱ*

የሰሜን የእስራኤል መንግስት በአሶር ከተያ ዘች በኋላ በሰማርያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የመፅሐፍ ቅዱስ ህዝቦች። ሳምራዊዎች በክፍል አይሁዶች እናም በክፍል አህዛብ ነበሩ። ሀይማኖታቸውም የአይሁድ እና የጣዖት አምላኪ እምነትንና ስራን የሚከልስ ነበር። በሉቃ. ፤፡ ፳፣–፴፣ ውስጥ የሚ ገኘው የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ሳምራዊ የእ ስራኤላውያን ሀይማኖት ስለካዱ አይሁዶች ለሳ ምራዊን ስላላቸው ጥላቻ ያሳያል። ጌታ ሐዋሪ ያት ወንጌልን ለሳምራዊ እንዲያስተምሩ መመ ሪያ ሰጠ (የሐዋ. ፩፡ ፤–፣)። ፊልጶስ የክርስቶስ ወንጌልን ለሳምራዊ ህዝብ በውጤታማነት ሰበከ እናም በመካከላቸውም ብዙ ታዕምራቶችን አከ ናወነ (የሐዋ. ፣፡ ፣–፴፱)።

ሳራ። *ደግሞም አብርሐም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአብርሐም የመጀመ ሪያ ሚስት። እድሜዋ በገፋበት ጊዜ የይስሐቅ እናት ሆነች (ዘፍጥ. ፲፣፡ ፤–፲፣፣ ፣፣፩፡ ፤)።

ሳርያ። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂ ባለቤት (፩ ኔፊ ፣፡ ፩–፣፣፣ ፣፡ ፣፲፤–፲፤፣ ፲፣፡ ፣፤)እና የላማን፣ ላሙ ኤል፣ ሳም፣ ኔፊ፣ ያዕቆብ፣ የዮሴፍ፣ እና የሴት ልጆች እናት (፩ ኔፊ ፤፡ ፣፣ ፤ ኔፊ ፣፡ ፣)።

ሳንሀድሪን። *ደግሞም አይሁዶች ተመልከቱ*

የአይሁድ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት እና በህዝባዊ እና በሀይማኖታዊ ነገሮች ውስጥ የአይሁድ ታላቅ ፍርድ ቤት። ሳንሀድሪን ከዋና ካህናት፣ ጸሀፊዎች፣ እና ሽማግሌዎች መካከል የተመረጡ ሰባ አንድ አባላት ያለው ነው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ይህም ሽንጎ ተብሎ ይጠራል (ማቴ. ፳፮፡ ፤፤፤፣ ማር. ፲፬፡ ፤፣፣ የሐዋ. ፣፡ ፴፴)።

ሳያል፣ የእስራኤል ንጉስ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ከመከፋፈሏ በፊት የእ ስራኤል የመጀመሪያ ንጉስ። ምንም እንኳን በግ ዛቱ መጀምሪያ ላይ ጻድቅ ቢሆንም፣ በኋላም በት ዕቢት ተሞላ እና በእግዚአብሔር ታዛዥ የማይሆን ነበረ (፩ ሳሙ. ፤–፴፩)።

ሴም። *ደግሞም ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የኖኅ ጻድቅ ወንድ ልጅ እና፣ በባህል መሰረት፣ አረብ፣ ዕብራውያን፣ ባቢ ሎናውያን፣ አሶር፣ እና ፎኒሲያውያን አባል የሆ ኑባቸው የሴማውያን ወይም የሴም ህዝብ ቅድም አባት (ዘፍጥ. ፣፡ ፣፣፤–፣፣፪፣ ፣ ፣፣ ፣ ፣፣ ፣ ፤ ፣፣ ፣ ፣

ውስጥ ሴም “ታላቁ ሊቀ ካህን” ተብሎ ተጠቁሟል (ት. እና ቃ. ፗ፴፯፡ፗ፩)።

ሴት። *ደግሞም አዳም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአዳምና የሔዋን ጻድቅ ወንድ ልጅ።

ሴት ፍጹም ሰው ስለነበረ፣ እና በምሳሌ መል ኩም እንደ አባቱ መልክ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፗ፲፯፡ፗ፪–ፗ፲ (ዘፍጥ. ፭፡፫)። በመንፈስ አለም ውስጥ፣ ሴት ከሀይለኞቹ አንዱ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፗ፴፯፡ፗ።

እግዚአብሔር እራሱን ለሴት ገለጸ፣ ሙሴ ፤፡፩–፲፣ ፯–፲፱።

ሴት፣ ሴቶች። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ እህት፤ ወንድሞች፣ ወንድም ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ሴት ልጅ የሆነች ጎልማሳ ሴት። ሴትን አንዳንድ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደ ክብር ርዕስ ይጠቀሙበታል (ዮሐ. ፲፱፡፳፤ አልማ ፲፱፡፲)።

እግዚአብሔርም ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራ ቸው፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፯ (ሙሴ ፪፡፳፯፤ ፤፡፱፣ አብር. ፬፡፳፯)። የምግባረ ጥሩ ሴት ዋጋ ከቀይ ዕንቁ በላይ ታላቅ ነው፣ ምሳ. ፴፩፡፲–፴፩።

ሴት የወንድ ክብር ናት፣ ፩ ቆሮ. ፲፩፡፯። ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም፣ ፩ ቆሮ. ፲፩፡፲፩። ሴቶች በሚገባ ልብስ ሰውነታቸውን ይሸልሙ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፱–፲።

እኔ ጌታ እግዚአብሔር በሴቶች ንፅህና እደሰታ ለሁ፣ ያዕቆ. ፪፡፳፯፡፳።

ኃጢያትሽ ተሰርዮልሻል፣ እናም አንቺ የተመር ጥሽ ሴት ነሽ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፲። ሴቶች፣ በባሎ ቻቸው የመደገፍ መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፪።

ሴዴቅያስ። *ደግሞም ሙሌቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይሁዳ የመጨረሻ ንጉስ (፪ ነገሥ. ፳፬፡፲፯–፳፣ ፳፭፡፪–፯)። ሴዴቅያስ ነቢዩ ኤርምያስን አሰረ (ኤር. ፴፪፡፩–፭)፣ እናም ኤር ምያስ ስለሴዴቅያስ በምርኮ መያዝ ተነበየ (ኤር. ፴፬፡፪–፳፣ ፳፭)። ሄሂ እና ቤተሰቡ በሴዴቅያስ ዘመነ መንግስት የመጀመሪያ አመት ጊዜ በኢየ ሩሳሌም ውስጥ ይኖሩ ነበር (፩ ኔፊ ፩፡፱)። ከአ ንዱ በስተቀር ሁሉም የሴዴቅያስ ልጆች ተገድለው ነበር፣ ልጁ ሙሌቅ ወደ ምዕራብ ክፍለ አለም አመ ለጠ (ኤር. ፶፪፡፲፣ ኦምኒ ፩፡፲፩፣ ሔሌ. ፲፡፳፩)።

ስህተት። *በደል ተመልከቱ*

ስልጣን። *ደግሞም ሀይል፣ መሾም፣ ሹመት፣ ክህነት፣ የክህነት ቁልፎች፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ስራን ለማከናወን በምድር ላይ ለእግዚአብሔር አብ ወይም ለኢየሱስ ክርስቶስ እና በስማቸው ለመስራት ለተጠሩት ወይም ለተሾሙት ሰዎች የተሰጠ ፈቃድ።

ልኬሀለሁ፣ ዘፀአ. ፫፡፲፪–፲፭። ያዘዝሁህን ነገር ሁሉ አንተ ትነግረዋለህ፣ ዘፀአ. ፯፡፪።

አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ሥልጣን ሰጣ ቸው፣ ማቴ. ፲፡፩። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እና ንተ አልመረጣችሁኝም፣ እና ሾምኋችሁ፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፮።

ኔፊና ሌሒ በታላቅ ኃይልና ስልጣን ሰበኩ፣ ሔሌ. ፭፡፲፤ የሔሌመን ወንድ ልጅ ኔፊ የእግዚአብሔር ሰው፣ ታላቅ ኃይልና ስልጣን ከእግዚአብሔር የተ ሰጠው ነበር፣ ሔሌ. ፲፩፡፲፤ (፫ ኔፊ ፯፡፲፯)። ኢየ ሱስ ለአስራ ሁለቱ ኔፋውያን ሀይልና ስልጣን ሰጣ ቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፪።

ጆሴፍ ስሚዝ በእግዚአብሔር ተጠርቶና ተሹሞ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪። ካልተሾመ፣ እና ስልጣን እንዳለው በቤተክርስቲያኗ የሚታወቅ ካልሆነ በስ ተቀር፣ ለማንም ወንጌሌን እንዲሰብክ ወይም ቤተ ክርስቲያኔን እንዲገንባ አይሰጠውም፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፩። ሽማግሌዎች በስልጣን እየሰሩ ወንጌሉን ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳። የመልከ ጼዴቅ ክህነት በመንፈሳዊ ነገሮች ለማስተዳደር ስልጣን አለው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፣ ፲፯–፲፱። በመለኮ ታዊ ስልጣን የተደረገው ህግ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፳፡፱።

የሚሰብክ ወይም ለእግዚአብሔር የሚያገለግል ስልጣን ባላቸው በእግዚአብሔር መጠራት አለ በት፣ ኢ.ኢ. ፩፡፭።

ስሚዝ፣ ሀይረም። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

የጆሴፍ ስሚዝ ታላቅ ወንድም እና ታማኝ ጓደኛ። በየካቲት ፱፣ ፲፰፻፱ (እ.አ.አ.) ተወልዶ ነበር። የቤ ተክርስቲያኗ ሁለተኛ ፓትሪያርክ ከመሆን በተ ጨማሪ፣ እርሱ በቤተክርስቲያኗ አመራር ውስጥ እንደ ጆሴፍ ረዳት አገለገለ። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.)፣ በካርቴጅ እስር ቤት ውስጥ ከጆሴፍ ጋር ሰማዕት ሆነ።

እግዚአብሔር ለሀይረም በወንድሙ ጆሴፍ በኩል መመሪያዎች ገለጸለት፣ ት. እና ቃ. ፲፩፣ ፳፫፡፫። አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ በልቡ ቅንነት የተባረከ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፭። ሀይረም የቤ ተክርስቲያኗን የፓትሪያርክ ሀላፊነትን እንዲወስድ ታዛዛ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፩–፲፯፣ ፲፳፭። ጆሴፍ እና ሀይረም በካርቴጅ እስር ቤት ውስጥ ሰማዕት ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳። ሀይረም እና ሌሎች ምርጥ መን

ፈሶች በዘመን ሙላት እንዲመጡ ተጠብቀው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፶፫።

ስሚዝ፣ ሉሲ ማክ። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ፤ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እናት እና የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ባለቤት (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬፡፬፣ ፣ ፳)። የተ ወለዱት በሐምሌ ፳፣ ፲፯፻፳፯ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በግንቦት ፭፣ ፲፰፻፶፯ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

ጆሴፍ እናቱን በራዕይ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፭።

ስሚዝ፣ ሳሙኤል ኤች። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ታናሽ ወንድም (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬)። ሳሙኤል የተወለደው በ፲፰፻፷ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በ፲፰፻፸፬ (እ.አ.አ.) ሞተ። ከመፅሐፈ ሞርሞን ስምንት ምስክሮች አንዱ ነብር እናም በዳ ግም ለተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥም እንደ መጀመሪያው ሚስዮን አገለገለ (ት. እና ቃ. ፭፣ ፡፪፣ ፡፲፪፡፡፲፭፣ ፡፲፮፡፡፲–፲፣ ፡፲፭፡፡፲፣ ፡፲፮፡፡፲–፲፣ ፡፲፰፡፡፲)።

ስሚዝ፣ ኤማ ሄል። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነብዩ የጆሴፍ ስሚዝ ባለቤት። ጌታ ለቤተክ ርስቲያኗ መዝሙር እንድትመርጥኤማን አዘዛት። እርሷም እንደ የሴቶች መረዳጃ ማህበር የመጀመ ሪያ ፕሬዘደንት አገለገለች።

ጌታ ለኤማ ስሚዝ ያለውን ፍላጎት ራዕይ ተሰ ጥቶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፭፭፡፡ ጌታ ኤማ ስሚዝን ጋብቻን በሚመለከት ምክር ሰጣት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፡፲፩–፲፲፮፡፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ሉሲ ማክ፣ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አባት። በሐምሌ ፲፪፣ ፲፯፻፳፭ (እ.አ.አ.) የተወለዱ ነበሩ። ሉሲ ማክን አገቡ፣ እናም እነርሱም ዘጠኝ ልጆች ወለዱ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬)። ጆሴፍ በ፯ላኛው ቀን ዳግም መመለስ ታማኝ ሰው እና የቤተክርስቲያኗ የመጀ መሪያ ፓትሪያርክ ሆኑ። በመስከረም ፲፬፣ ፲፰፻፶ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

እግዚአብሔር በልጁ ጆሴፍ በኩል መመሪያ ሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፬፣ ፭፲፣ ፭። የሚሸመግለው አገልጋዩ፣ አሁን በሚኖርበት ቦታ ከቤተሰቡ ጋር ይቀጥል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፭። የሚሸመግለው አገል ጋዩ ጆሴፍ ከአብርሐም ጋር በቀኝ እጁ በኩል ተቀ ጥሞ ጧል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፬፡፡፲፬። ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ አባቱን በራዕይ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፭።

መላእኩ ወደ አባቱ በመሄድ ስለመጀመሪያው ራዕይ እንዲነግረው ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን አዘዘ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፬–፶፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ኤፍ

የቤተክርስቲያኗ ስድስተኛ ፕሬዘደንት፣ የሀይረም እና የሜሪ ፊልዲንግ ስሚዝ ብቸኛ ወንድ ልጅ። የተወለዱት በህዳር ፲፫፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ነበር እና በህዳር ፲፱፣ ፲፱፻፲፰ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ የሙታን ደህንነትን ራዕይ ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ። *ደግሞም* መፅሐፈ ሞርሞን፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፤ የመጀመሪያው ራዕይ፤ የታላቅ ዋጋ ዕንቁ፤ የወንጌል ዳግም መመለስ፤ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.) *ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያንን በምድር ላይ በዳግም ለመመለስ የተመረጠ ነቢይ። ጆሴፍ ስሚዝ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በቨርሞንት ስቴት ውስጥ ተወለደ እናም ከ፲፰፻፭ እስከ ፲፰፻፸፬ (እ.አ.አ.) ድረስ በህይወት ኖረ።

በ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.)፣ እግዚአብሔር አብ እና ኢየ ሱስ ክርስቶስ በጆሴፍ ታዩ፣ እናም በምድር ካሉት ቤተክርስቲያኖች መካከል ማንኛቸውም እውነተኛ እንዳልሆኑ ተማረ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፩–፳)። በኋላም በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ላይ ይኖሩ የነበሩ የጥንት ህዝቦችን መዝገብ የያዘውን የወርቅ ሰሌዳ የተደ በቀበትን ቦታ በገለጸለት በመልአክ ሞሮኒ ተነበኝ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፱–፴፪)።

ጆሴፍ የወርቅ ሰሌዳዎችን ተረጎመ እናም በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) እንደ መፅሐፈ ሞርሞን አተማ ቸው (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፯–፳፱፣ ፫፳)። በ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.)፣ ክህነትን ከመጥምቁ ዮሐንስ፣ እናም ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብ፣ እና ከዮሐንስ ተቀበሉ። (ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፳፯፡፡፲፪፣ ፲፳፯፡፡፳፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፡፳–፫)።

በእግዚአብሔር እንደተመራም፣ በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ እና ብዙ ሌሎች ዳግም የተ መለሰችውን የኢየሱስ ክርቶስ ቤተክርስቲያን አደ ራጁ። (ት. እና ቃ. ፳፡፩–፪)። በጆሴፍ አመራር፣ በካናዳ፣ በእንግሊዝ፣ እና በዮናይትር ስቴትስ በም ስራቅ ክፍሎች፣ በልዩም በኦሀዮ፣ በምዙሪ፣ እናም በኢሊኖይ ውስጥ፣ ቤተክርስቲያኗ አደገች። ጠን ካራ መሳደድ ጆሴፍን እና ቅዱሳንን የትም በሚ ሰፍሩበት ቦታዎች ሁሉ ተከተሏቸው። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ ጆሴፍ እና ወንድሙ ሀይረም በካርቴጅ ኢሊኖይ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜ ሪካ ውስጥ ሰማዕት ሆኑ።

የያዕቆብ ልጅ ጆሴፍ ስለ ጆሴፍ ስሚዝ ተነበየ፣ ፪ ኔፊ ፫፡፭–፲፭።

ጌታ በምድር ነዎሪዎች ላይ የሚመጣውን መቅሰፍት በማወቁ፣ ጌታ አገልጋዩን ጆሴፍ ስሚዝን ጠራ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፫)። ጆሴፍ ስሚዝ የዚህ ቤተክርስቲያን መጀመሪያ ሽማግሌና የኢየሱስ ክርስቶስ ሀዋሪያ እንዲሆን ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፪። ጆሴፍ ሐዋሪያ እንዲሆን በጴጥሮስ፣ እና እብያእቆብ፣ እና በዮሃንስ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪። ጆሴድ እና ስድኒ ሪግደን የአብ አንድያ ልጅ እንዳዩ መሰከሩ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፫። ከኦሊቨር ካውደሪ ጋር፣ ጆሴፍ ስሚዝ ጌታን በራዕይ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፩–፱። ጌታ ጆሴፍን አስተዳዳሪ ሽማግሌ፣ ተርጓሚ፣ ገላጭ፣ ባለ ራዕይ፣ እና ነቢይ እንዲሆን ጠራው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፳፭። ጆሴፍ ስሚዝ፣ ከኢየሱስ በስተቀር፣ በዚህ አለም ውስጥ ለሰዎች ደህንነት ከኖሩ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በላይ አድርጓል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፭–፲፡

በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የመጡ ቅዱሣት መጻህፍት፣ ጆሴፍ በመልአክ ሞሮኒ የተሰጡትን የወርቅ ሰሌዳዎችን ክፍል ተረጎመ፣ ይህም ትርጉም በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) እንደ መፅሐፈ ሞርሞን ታተመ። መሰረታዊ ትምህርቶችን እና የቤተክርስቲያኗን ድርጅቶች ዋና ሀሳቦችን የሚሰጡ ብዙ ራዕዮችንም ከጌታ ተቀበለ። ከእነዚህ ራዕዮች ብዙዎቹ አሁን ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ተብለው በሚታወቁት ውስጥ ተካለሱ። የሙሴ፣ የአብር ሐም፣ እና የማቴዎች የተነሳሱ ትርጉሞችን፣ ከእራሱ ታሪክና ምስክሮች ክፍሎችን፣ እና የቤተክርስቲያኗን ትምህርት እና እምነት የያዙ አስራ ሶስት መረጃዎችን የያዘውን የታላቅ ዋጋ ዕንቁንም የማምጣት ሀላፊ የሆነ ነበር።

ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት። *ደግምም ማመንዘር፣ ምኞት፣ በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፣ ንጹህነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

ሳድቅ ላልሆነ የሰውነት ደስታን፣ በልዩም የወሲብ የስነ ምግባር ጉድለትን፣ ማፍቀር ወይም መውደድ።

የጌታው ሚስት በዮሴፍ ላይ ዓይንዋን ጣለች፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፯።

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፣ ማቴ. ፭፡፳፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፳፰)። ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ራቁ፣ ፩ ጴጥ. ፪፡፲፩። የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ከአባት አይደሉም፣ ፩ ዮሐ. ፪፡፲፮።

በዓይንህ ምኞት ከእንግዲህ እንዳትጓዝ፣ **አልማ** ፴፱፡፱።

ቅዱስ ህጎችን በመተላለፍ ሰዎች ስጋዊ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳። ማንም በልባቸው ካመነዘሩ፣ መንፈስም አይኖራቸውም፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፲፮። ከፍተኛ ፍላጎታችሁን ሁሉ አቁሙ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፪–፭።

ሰዎችም ስጋዊ፣ ስሜታዊና ዲያብሎሳዊ መሆን ጀመሩ፣ **ሙሴ** ፭፡፲፫ (ሞዛያ ፲፮፡፫፣ ሙሴ ፮፡፴፱)።

ስሜት። *ደግምም መንፈስ ቅዱስ ተመልከቱ*

የመንፈስ መነሳሻን መሰማት።

እናንተ ደንዝዛችኋል፣ ስለዚህ ቃሉ ሊሰማችሁ አልቻለም፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፭። ይህ ዕድገት በልባችሁ ውስጥ ሲሰማችሁ፣ በውስጣችሁ እንዲህ ማለት ትጀምራላችሁ፣ **አልማ** ፴፪፡፳፰።

ትክክል እንደሆነ ይሰማሃል፣ ት. እና ቃ. ፱፡፰። በጌታ ቤት መግቢያ በር ላይ የሚገቡት ህዝቦች ሁሉ ሀይልህ ይሰማቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፫።

ስምዖን። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ሁለተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፳፱፡፴፣ ፴፭፡፳፣ ዘፀአ. ፩፡፪)። ሴኬማውያንን በመግደል ከሌዋ ጋር ተባበረ (ዘፍጥ. ፴፬፡፳፭–፴፩)። በዘፍጥረት ፴፱፡፩–፲ ውስጥ ስምዖንን በተመለከተ የያዕቆብ ትንቢት ይገኛል።

የስምዖን ጎሳ፣ የስምዖን ትውልዶች በብዙ ጊዜ ከይሁዳ ጎሳ ጋር በይሁድ መንግስት ድንበር ውስጥ ይኖሩ ነበር (ኢያ. ፲፱፡፩–፱፣ ፩ ዜና ፬፡፳–፴፫)። የስምዖን ጎሳ ከይሁዳ ጋር በመተባበር ከከነዓናውያን ጋር ተዋጉ (መሳ. ፩፡፫፣ ፲፯)። በኋላም የዳዊት ሰራዊት አባል ሆኑ (፩ ዜና ፲፪፡፳፭)።

ስምዖን ጴጥሮስ። *ጴጥሮስ ተመልከቱ*

ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ

ሰነፍ እና በጽድቅ ስራዎች የማይሳተፍ።

እግዚአብሔር የታቦትን ንድፍ ለሙሴ ገለጸ (ዘፀአ. ᏣᏦ–ᏣᏩ)፣ እናም የእስራኤል ልጆች በን ድፉ መሰረት ገነቡት (ዘፀአ. ᏭᏣ–Ꮿ)። ታቦቱ በተፈ ጸመ ጊዜ ዳመና ድንኳኑን ሸፈነ፣ እናም የጌታ ክብር ታቦቱን ሞላው (ዘፀአ. Ꮿ፡ᏭᏫ–ᏭᏭ)። ዳመናው የእ ግዚአብሔር መገኘት ምልክት ነበር። በምሽት፣ የእ ሳት አመለካከት ነበረው። ዳመናው በድንኳኑ ላይ ሲቀር፣ የእስራኤል ልጆች ይሰፍራሉ። ይህም ተነ ስቶ ሲሄድ፣ እነርሱም ከእዚህ ጋር አብረው ሄዱ (ዘፀአ. ᏯᏩ፡ᏭᏩ፣ ዘኁል. ᏬᏫ፡ᏥᏩ–ᏥᏣ)። የእስ ራኤል ልጆች በበረሀ ውስጥ በሚንቀዋለሉበት ጊዜ እና ቀነዓንን በሚያሸንፉበት ጊዜ ታቦቱን ተሸክ መው ይሄዱ ነበር። ጦርነቱን ካሸነፉ በኋላ፣ ጌታ በመረጠበ በሴሎ ታቦቱ ተቀመጠ (ኢያ. ᏥᏣ፡Ꭾ)። የእስራኤል ልጆች የሰለሞን ቤተመቅደስን ከገነቡ በኋላ፣ ታቦቱ ከታሪክ በሙሉ ጠፋ።

ጌታ እና ኢሳይያስ ታቦትን በጌታ ዳግም ምፅዓት ጊዜ እንደሚገኙት እንደ ፅዮን ከተማዎች እና ኢየሩ ሳሌም ምሳሌ ተጠቅመውበት ነበር (ኢሳ. ᏭᏫ፡ᏣᏫ፣ ሙሴ ᏦᏫ፡ᏣᏬ)።

ተአምራት። ደግምም ምልክት፣ እምነት፣ ማመን ተመልከት

በእግዚአብሔር ሀይል የተደረገ አስደናቂ ድር ጊት። ታዕምራቶች በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ናቸው። እነዚህም በተ ጨማሪ ፈውሶችን፣ ሙታንን ወደ ህይወት ዳግም መመለስ፣ እና ትንሳኤ ናቸው። ታዕምራቶች የኢ የሱስ ክርስቶስ ወንጌል ክፍሎች ናቸው። ታዕምራ ቶች እንዲታዩ ዘንድ እምነት አስፈላጊ ነው (ማር. ᏦᏫ፡ᏩᏫ፣ ሞር. ᏯᏫ፡ᏀᏫ፣ ኤተር ᏀᏬᏫ፡ᏀᏬᏫ)።

ፈርዶን ሲናገር፣ ተአምራትን አሳዩኝ፣ **ዘፀአ.** ᏦᏫ፡ᏯᏫ።

በስሜ ተአምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መና ገር የሚችል ማንም የለም፣ **ማር.** ᏯᏫ፡ᏭᏯᏫ። ኢየሱስ የምልክቶች መጀመሪያ ቃና አደረገ፣ **ዮሐ.** ᏬᏫ፡ᏀᏩᏫ።

እኔ የተአምራት አምላክ ነኝ፣ ᏬᏦ **ኔፊ** ᏣᏦ፡ᏣᏫ። ድንቅ ስራን የሚሰራው በእግዚአብሔር ኃይል መሰ ረት ነው፣ **አልማ** ᏣᏫ፡ᏦᏫ። ክርስቶስ በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ውስጥ ለሚገኙት በነበራቸው ታላቅ እም ነት ታላቅ ተአምራቶችን ለማሳየት ችሏል፣ ᏫᏦ **ኔፊ** ᏀᏯ፡ᏭᏣᏫ። እግዚአብሔር የተአምራት አምላክ መሆ ኑን አላቆመም፣ **ሞር.** ᏯᏫ፡ᏀᏣᏫ።

እኔ ካላዘዝኳችሁ በስተቀር ተአምራትን አት ፈልጉ፣ ት. እና ቃ. ᏣᏯ፡ᏀᏫ–ᏀᏯᏫ። ለአንዳንዶቹ ተአምራትን ማድረግ ተሰጥቷቸዋል፣ ት. እና ቃ. ᏯᏦᏫ፡ᏣᏕ (ሞሮኒ ᏀᏫ፡ᏀᏬᏫ)።

ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ። ደግምም ህግ፣ መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)፣ መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት፣ ማዳመጥ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዛት፣ ደስታ ተመልከቱ

በመንፈሳዊ አስተያየት፣ ታዛዥነት የእግዚአብ ሔር ፍላጎትን ማድረግ ነው።

ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ፣ ዘፍጥ. ᏦᏫ፡ᏣᏬᏫ። አብርሐም ለጌታ ታዛዥ ሆነ፣ ዘፍጥ. ᏣᏬᏫ፡ᏀᏣ–ᏀᏥᏫ። እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፣ ዘፀአ. ᏣᏯ፡ᏦᏫ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ይህን ታደርጋት ዘንድ ጠብቅ፤ ዘዳግ. ᏦᏫ፡ᏕᏫ–ᏮᏫ። እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ፤ ዘዳግ. ᏭᏫ፡ᏣᏫ። መታ ዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል፣ ᏕᏫ ሳሙ. ᏀᏣᏫ፡ᏣᏬᏫ። እግዚአብሔርን ፍራ፥ ትእዛዙንም ጠብቅ፤ መክ. ᏀᏬᏫ፡ᏀᏮ–ᏀᏯᏫ።

በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ሁሉም ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፤ ማቴ. ᏦᏫ፡ᏣᏕ (ᏫᏦ **ኔፊ** ᏀᏯ፡ᏣᏕ)። ፈቃ ዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትም ህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ያውቃል፣ **ዮሐ.** ᏦᏫ፡ᏀᏦᏫ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፣ **የሐዋ.** ᏕᏫ፡ᏣᏯᏫ። ልጆች ሆይ፥ ለወላጆ ቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤ **ኤፌ.** ᏦᏫ፡Ꮥ (ቄላ. ᏫᏫ፡ᏣᏫ)።

ጌታ ያዘዘኝንም ነገሮች በመሄድ አደርጋለሁ፣ ᏕᏦ **ኔፊ** ᏫᏫ፡ᏦᏫ። የመንፈስ ድምፅ ታዛዥ እሆናለሁ፣ ᏕᏦ **ኔፊ** ᏯᏫ፡ᏦᏫ–ᏀᏣᏫ። የሰዎች ልጆች የእግዚአብሔ ርን ትዕዛዝ ከጠበቁ እርሱ ይመግባቸዋል፣ ᏕᏦ **ኔፊ**

ቴአንኩም

፲፯፡፫። ለክፉ መንፈስ ታዛዥ እንዳትሆኑ ዘንድ ተጠንቀቁ፣ ሞዛያ ፪፡፴፪–፴፫፣ ፴፯ (ት. እና ቃ. ፰፱፡፣፴፩)። ሰዎች በሚታዘዙበት መንፈስ መሰረት ዋጋቸውን ይቀበላሉ፣ አልማ ፫፡፰፯–፰፯።

ሰዎች በእራሳቸው ነጻ ፍላጎት ብዙ ነገሮችን ያድርጉ፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፳፯–፳፱። በሁሉም ነገሮች ውስጥ የእርሱ እጅ እንዳለበት ከማይመሰክሩ እና ትእዛዙን ከማያከብሩ በቀር፣ በምንም ሰው እግዚአብሔርን አያስቀይመውም፣ ወይም በማንም ላይ ቁጣው አይቀጣጠልም፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፳፭። እኔ ጌታ የምለውን ስታደርጉ እገደዳለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፪፡፲። ድምጼን የሚያከብር እያንዳንዱ ነፍስ ሁሉ ፊቴን ያያል እና እኔ እንደሆንኩም ያውቃል፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፩። ህዝበቼ ታዛዥነት እስከሚ ማሩ ድረስ፣ መገሰፅ ያስፈልጋቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፯። ከእግዚአብሔር ምንም በረከት ስናገኝ፣ ይህን የምናገኘው የተመሰረተበትን ህግ በማክበር ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፳፩።

አዳምም ታዛዥ ነበር፣ ሙሴ ፭፡፭። ጌታ አም ላክ የሚያዛቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ሁሉ እን ደሚያደርጉ ለማየት፣ በዚህ እንፈትናቸዋለን፣ አብር. ፫፡፳፭።

ቴአንኩም

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ታላቁ የኔፋውያን የጦ ርነት መሪ (አልማ ፯፡፴፭፣ ፶፩–፶፪፣ ፳፭–፳፪)።

ቴይለር፣ ጆን

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሶስተኛ ፕሬዘደንት።

በአስራ ሁለት ሐዋሪያት ሸንጎ እንዲያገለ ግል ተጠሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፳፡፤ (ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፣፲፳፰–፲፳፱)። በሰማዕት ጊዜ በጥይት ቆስለው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፪። በጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ በመንፈስ አለም ውስጥ ከታዩት ታላቆች መካከል አንዱ ነበሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፳፡፲፫–፲፤።

ትሁት፣ ትሕትና፡ *ደግምም ኩራት፣ የተሰበረ ልብ፣ ደሀ፣ ደካማነት፣ ገር፣ ገርነት ተመልከቱ*

የዋህ እና ለማስተማር የሚቻል ማድረግ፣ ወይም የዋህ እና ለማስተማር የሚቻል የመሆን ጉዳይ። ትህ ትና በእግዚአብሔር እንደምንመካ ማወቅን እና ለእ ርሱ ፍላጎት ተቀባይ ለመሆን መፈለግን በተጨ ማሪ ይይዛል።

አምላክህ እግዚአብሔር ሊያስጨንቅህ በእ ነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ መራህን፣ ዘዳግ. ፰፡፪፡፪። ነፍሴንም በጾም አደከምኋት፣ መዝ. ፴፭፡፣፲፫። ድሀና ጠቢብ ብላቴና ከማያውቅ ከሰነፍ ሽማግሌ ንጉሥ ይሻላል፣ መክ. ፬፡፲፫። ጌታ የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር ይቀመጣል፣ ኢሳ. ፶፯፡፣፲፭።

እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው፣ ማቴ. ፲፰፡፬። ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል፣ ማቴ. ፳፫፡፣፲፪ (ሉቃ. ፲፬፡፣፲፩፣ ፲፰፡፣፲፬)። ኢየሱስ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም እንኳ የታዘዘ ሆነ፣ ፊልጵ. ፪፡፰ (ሉቃ. ፳፪፡፣፳፪፣ ፳፫፡፣፳፯)። እግዚአ ብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፣ ፤ ጴጥ. ፭፡፭–፯ (፪ ኔፊ ፱፡፣፴፪)።

በመቆም በጥልቅ ትህትና እንኳን ራሳችሁን አዋ ርዱ፣ ሞዛያ ፬፡፲፩ (፪ ኔፊ ፱፡፣፴፡፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፪)። በሚገባ ትሁት ናችሁ፣ አልማ ፭፡፳፯–፳፰። ትሁት የሆኑት በትህትና እየጠነከሩ ሄዱ፣ ሔሊ. ፫፡፴፫–፴፭። ሰዎች ትሁት እንዲሆኑ ድካምን እሰጣቸዋ ለሁ፣ ኤተር ፲፪፡፳፯፣፴፯።

ትሁትነት ለጥምቀት ብቁ የሚያደርግ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴፣፴። በፊቴ ትሁት ከሆናችሁ፣ መጋረጃውም ይገፈፋል እናም አይታችሁኝ እኔ ማን እንደሆንኩም ታውቃላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፰፲፯፡፣፲። ትሁት ሁን፤ እና ጌታ ለጸሎቶችህም መልስ ይሰ ጥሀል፣ ት. እና ቃ. ፲፣፲፪፡፣፲። ደንቆሮው እራሱን ትሁት በማድረግ ጥበብን ይማር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፡፴፪። ትሁቱን ለማስረዳት መንፈስ ተል ኳል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፡፴፣።

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፡ *ደግምም መፅሐፈ ትእዛዛት፤ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፤ ቀኖና፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

የኋለኛው ቀን መለኮታዊ ራዕያትና የተነሳሱ አዋጆች መፅሐፍ። ጌታ እነዚህን የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ በእነዚህ በመጨረሻ ቀናት ለመመስረት እና ለማስተዳደር ለጆሴፍ ስሚዝ እና ለተለያዩ የእርሱ ምትኮች ሰጠ። ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ይፋ ከሆኑት የቤተክርስቲያኗ ጽሁ ፎች ከመጻሐፍ ቅዱስ፣ ከመጻሐፈ ሞርሞን፣ እና የታላቅ ዋጋ ዕንቁ መካከል አንዱ ነው። ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ግን ልዩ ነው፣ ምክንያቱም ይህ የጥንት መዝገብ ትርጉም አይደለም፣ ጌታ እነዚህን ራዕዮች እርሱ ለመረጣቸው ነቢያት በእዚህ ዘመን መንግስቱን በዳግም ለመመስረት መሰረት የሰጣቸው ናቸው። በራዕዮች ውስጥ ሰው የጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስን ለስላሳ ቢሆንም ፅኑ የሆነውን ድምፅ ይሰማል (ት. እና ቃ. ፲፰፡፣፴፫–፴፮)

የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚለው ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች በእነዚህ የመጨረሻው ቀኖች የቤተ ክርስቲያኗ መሰረት፣ እና ለአለምም ጥቅም ነው (ት. እና ቃ. ፫፡ማስተዋወቂያ)። በውስጡ ያሉት ራዕዮች አለም ከተጀመረች ጊዜ ጀምሮ በነቢያት የተነገሩትን ቃላት በማሟላት ለጌታ ዳግም ምፅዓት መንገድ የሚዘጋጅበት ስራን ያስጀምራሉ።

ትምባሆ። የጥበብ ቃል ተመልከቱ

ትንሳኤ። ደግሞም መንፈስ፣ ሰውነት፣ ስጋዊ ሞት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ የማይሞት፣ አለሟችነት ተመልከቱ

ከሞት በኋላ የመንፈስ ሰውነት ስጋ እና አጥንት ካለው ከስጋዊ ሰውነት ጋር እንደገና መገና ኘት። ከትንሳኤ በኋላ፣ መንፈስ እና ሰውነት እንደ ገናም አይለያዩም፣ እናም ሰውም የማይሞት ይሆ ናል። በምድር ላይ የተወለደ ሰው በሙሉ በኢየ ሱስ ክርስቶስ ምክንያት ሞትን ያሸንፋል (፩ ቆሮ. ፲፭፡፳–፳፪)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ ከሞት ለመ ነሳት የመጀመሪያው ነበር (የሐዋ. ፳፮፡፳፫፣ ቁላ. ፩፡፲፰፣ ራዕ. ፩፡፭)። አዲስ ኪዳን ኢየሱስ በስ ጋዊ ሰውነቱ እንደተነሳ ብዙ መረጃዎችን ይሰጣል፡ መቃብሩ ባዶ ነበር፣ አሳ እና ማር በላ፣ የስጋ እና አጥንት ሰውነት ነበረው፣ ሰዎች ነኩት፣ እና መላእ ክት ተነስቷል አሉ (ማር. ፲፮፡፩–፮፣ ሉቃ. ፳፬፡፩–፲፪፣ ፴፮–፴፱፣ ዮሐ. ፳፡፩–፲፳)። የኋለኛው ቀን ራዕይ የክርስቶስና የሰው ዘር ሁሉ ትንሳኤን እውነ ተኛነት አረጋገጠ (አልማ ፲፩፡፴–፴፭፣ ፴፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፩–፲፯፣ ት. እና ቃ. ፍ፯፣ ሙሴ ፮፡፶፪)።

ሁሉም ሰዎች ወደ አንድ አይነት ክብር ከሞት አይነሱም (፩ ቆሮ. ፲፭፡፴፱–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፍ፯፡፣ ፹፱–፺፭)፣ ወይም በአንድ ጊዜ ሁሉም ከሞት አይነሱም (፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፪–፳፫፣ አልማ ፴፡፶፣ ት. እና ቃ. ፍ፯፡፡–፡፡፣ ፹፭፣ ፹፭፡፣ ፺፯–፺፪)። ብዙ ቅዱሳን ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ ከሞት ተነ ስተው ነበር (ማቴ. ፳፯፡፶፪)። ጻድቃን ከኃጢያ ተኞች በፊት ከሞት ይነሳሉ እናም በመጀመሪያው ትንሳኤ ይመጣሉ (፩ ተሰ. ፬፡፲፯)፣ ንስሀ ያልገቡት ኃጢያተኞች በመጨረሻው ትንሳኤ ይመጣሉ (ራዕ. ፳፡፭–፲፫፣ ት. እና ቃ. ፍ፯፡፣ ፹፭)።

ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፡ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃ ለሁ፣ ኢዮብ ፲፱፡፳፯ (ሙሴ ፭፡፲)። መቃብራ ችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም አወጣችኋ ለሁ፣ ሕዝ. ፴፯፡፲፪።

መቃብሮችም ተከፈቱ፡ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፣ ማቴ. ፳፯፡፶፪–፶፫ (፫ ኔፊ ፳፫፡፱)። ጌታ በእውነት ተነሥቶአል፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፬። መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና፣ እኔን ዳስሳችሁ እዩ፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፱። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ ዮሐ. ፲፩፡፳፭። አስራ ሁለት ሐዋሪያት ኢየሱስ እንደተነሳ አስተማሩ፣ የሐዋ. ፩፡፳፭–፳፪ (የሐዋ. ፪፡፴፪፣ ፫፡፲፭፣ ፬፡፴፫)። በክ ርስቶስ ሁሉም ህያው ይሆናሉ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፩–፳፪። በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፣ ፩ ተሰ. ፬፡፲፯። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፣ ራዕ. ፳፡፮።

ክርስቶስ በስጋ ሞተ እናም ህይወቱን እንደገና በማንሳት ሙታን እንዲነሱ አደረገ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፰ (ሞዛያ ፲፫፡፴፭፣ ፲፭፡፳፣ አልማ ፴፫፡፳፪፣ ፴፡፣ ሔለ. ፲፬፡፲፭)። ያለትንሳኤ፣ ለሰይጣን ተገዥዎች እንሆናለን፣ ፪ ኔፊ ፱፡፮–፱። ትንሣኤ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ያልፋል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፳፪። አቢናዲ ስለመ ጀመሪያው ትንሳኤ አስተማረ፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፭–፳፮። ለኃጢአተኞች የሞት እስር ከመፈታት በስተ ቀር ቤዛነት እንዳልተፈፀመ ሆነው ይቆያሉ፣ አልማ ፲፭፡፴፭–፴፭። አልማ በሞት እና በትንሳኤ መካከል ስላለው የነፍስ ሁኔታ ገለጸ፣ አልማ ፴፡፮፣ ፲፭–፳፱።

በጌታ መምጣት፣ የሞቱት ሙታን ወደፊትም ይመጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፫ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፭–፴፮፣ ፹፯፡፣ ፹፯–፹፡፣ ፻ፍ፡፡–፡ፍ)። በተ ለይ የክብር ትንሳዔ ተስፋ ለሌላቸው አልቅሱ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፴፭። ህግን የማያውቁትም በፊ ተኛው ትንሳኤ ክፍል ይኖራቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፱። ከሞት ይነሳሉ እናም ከዚህም በኋላ አይም ቱም፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፱። የሙታን ትንሳኤ የነ ፍስ ቤዛነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፡፡–፡፲። መን ፈሶች እና ንጥረ-ነገሮች ሳይለያዩ የተያያዙ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፫፡፣ ፻፲፫። በትንሳኤ የተነሱ መላእክቶች የስጋ እና የአጥንት ሰውነት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፻ፍ፱፡፭። በዚህ ህይወት የምናገኘው ማንኛውም የመረዳት ችሎታ ደረጃ፣ ይህም ከሞት ስንነሳ አብ ሮን ይነሳል፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡፲፫–፲፱።

ትንቢት፣ መተንበይ። ደግሞም ራዕይ፣ ባለራዕይ፣ ነቢይ፣ ነቢይት ተመልከቱ

ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ ራዕይ በኩል ሰው የሚ ቀበላቸው በመለኮታዊ የተነሳሱ ቃላት ወይም ፅሁ ፎችን የያዘ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር የት ንቢት መንፈስ ነው (ራዕ. ፲፱፡፣)። ትንቢት ስላለ ፈው፣ ስለአሁኑ፣ ወይም ወደፊት ስለሚመጣው ነገር ግንኙነት ያለው ነው። ሰው ሲተነብይ፣ ለእ ራሱ ጥቅም ወይም ለሌሎች ጥሩ ጥቅም እግዚአብ ሔር እንዲያውቅ የሚፈልገውን ይናገራል ወይም ይፅፋል። ግለሰቦች ትንቢቶችን ወይም ራዕዮችን ለእራሳቸው ህይወት ለመቀበል ይችላሉ።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፣ ዘኁል. ፲፩፡፳፱። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ኢዩ. ፪፡፳፰ (የሐዋ. ፪፡፲፯–፲፰)። ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ይናገራል፣ ዓሞ. ፫፡፯።

በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ ፪ ጴጥ. ፩፡፳።

ኔፋውያን ብዙ ራዕዮች እና የመንፈስ ትንቢት ነበራቸው፣ ያዕቆ. ፬፡፮፣ ፲፫። አልማ እና አሙሌቅ

የዚኤዝሮም ልቡን ሀሳብና መሻት አውቀው ነበር፣ **አልማ** ፲፪፡፯፡፯። ጌታ በትንቢት አይሰራም ለሚል ወዮለት፣ ፮ ኔፊ ፳፱፡፯፣ ፮። የኢሳይያስን ትንቢት መር ምሩ፣ **ሞር.** ፰፡ ፳፣፮።

ትንቢቶች ይሟላሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፩፡ ፴፯–፴፰።

ወንድ ሰው በትንቢት መጠራት አለበት፣ **ኢ.አ.** ፩፡ ፩።

ትዕቢት። ኩራት *ተመልከቱ*

ትዕግስት። *ደግሞም መፅናት፤ ገር፣ ገርነት ተመልከቱ*

በጸጥተኛ መፅናናት፤ ስቃይን፣ ስድብን፣ ወይም ጉዳትን ያለማማረር ወይም ያለመበቀል የመፅናት ችሎታ።

ለእግዚአብሔር ተገዛ ተስፋም አድርገው፣ **መዝ.** ፴፯፡፯–፰። ትዕግሥተኛ ሰው ብዙ ማስተዋል አለው፣ **ምሳ.** ፲፬፡ ፳፱።

በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፣ **ሉቃ.** ፳፩፡ ፲፱። በመጽናትና በትእግስት ተስፋ ይሁንልን፣ **ሮሜ** ፲፭፡ ፬። በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን ተከታዮች ሁኑ፣ **ዕብ.** ፮፡ ፲፪–፲፭። ትዕግሥትም ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፣ **ያዕ.** ፩፡ ፪–፬። ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፣ **ያዕ.** ፭፡ ፲፩።

በደስታና በትዕግስት ለጌታ ፈቃድ ተቀባይ እን ዲሆኑ ጌታ ብርታትን ሰጥቷቸዋል፣ **ሞዛያ** ፳፬፡ ፲፭። ጌታ ካንተ ጋር በመሆኑ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በትዕ ግስት ጸንተህል፣ **አልማ** ፴፯፡ ፬–፭።

ፍጹም እስክትሆኑ ድረስ በትግስት ቀጥሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፯፡ ፲፫።

ትጋት

የማይቋረጥ፣ ደፋር ጥረት፣ በልዩም ጌታን በማ ገልገልና ቃላቱን በማክበር።

በትጋት አድምጡኝ፣ **ኢሳ.** ፶፭፡ ፪።

እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ ይሰ ጣል፣ **ዕብ.** ፲፩፡ ፮። ትጋትን ሁሉ አሳዩ፣ በእምነ ታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ ፪ ጴጥ. ፩፡ ፭።

የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት አስተምር፣ **ያዕቆ.** ፩፡ ፲፱። ቅዱሳን መጻሕፍትን በትጋት የሚያጠኑ ሰዎች ነበሩ፣ **አልማ** ፲፯፡ ፪። ባላቸው ትጋት ሁሉ የጌታን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ፈቃደኞች ነበሩ፣ ፮ ኔፊ ፯፡ ፲፱። እኛ ተግተን እንስራ፣ **ሞሮኒ** ፱፡ ፮።

ጥሩ ስራን በጉጉት እናከናውን፣ **ት. እና ቃ.** ፶፯፡ ፳፯። ስራ ሳትፈቱ፣ በአቅማችሁ ሁሉ እየ ሰራችሁ እንድትሄዱ ፍላጎቴ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፫፩፡ ፮። ለዘለአለም ህይወት ቃላቶችም በትጉ ነት አዳምጡ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፬፡ ፴፮። እያንዳንዱ ሰው ሀላፊነቱን ይማር፣ እናም በትጋትም ይስራ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡ ፲፱።

ቶማስ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ በአዳኝ ከተመረጡት ቀዳሚ አስራ ሁለት ሐዋ ሪያት መካከል አንዱ (ማቴ. ፲፡ ፪–፫፣ ዮሐ. ፲፬፡ ፭፣ ፳፡ ፳፭–፳፱፣ ፳፩፡ ፪)። ምንም እንኳን የኢየሱስን ትንሳኤ አዳኝን በሰውነት እስከሚመለከት ድረስ ቢጠራጠርም፣ የግል ጸባይ ጥንካሬው ከጌታው ጋር መሰደድን እና ሞትን ለመቋቋም ፈቃደኛ እንዲሆን አደረገው (ዮሐ. ፲፩፡ ፲፮፣ ፳፡ ፲፱–፳፭)።

ኃጢያተኛ፣ አመፃ። *ደግሞም ኃጢያት፤ እድፍ፣ እድፍነት፤ እግዚአብሔርን የሚጠላ፤ ክፉ፣ ክፋት፤ ጻድቅ፣ ጽድቅ ተመልከቱ*

ክፉ፣ ጻድቅ ያልሆነ፤ እግዚአብሔርን ወይም የእ ግዚአብሔርን ነገሮች የማይደግፉ እና የእርሱን ምክ ንያት የማያፈቅሩ ሰዎች።

ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወ ርሱም፣ ፩ ቆሮ. ፮፡ ፱–፲። በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን ይቀ በላሉ፣ ፪ ተሰ. ፪፡ ፲፪። ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን ይችላል፣ ፩ ዮሐ. ፩፡ ፱።

ፃድቅ ያልሆነ ንጉስ የፃድቃንን መንገድ በሙሉ እንደዚህ ያጣምማል፣ **ሞዛያ** ፳፱፡ ፳፫። የዚህ ህዝብ ጥፋት መሰረቱ ፃድቃን ባልሆኑት ጠበቆቻችሁና ዳኞቻችሁ መጣል ጀምሯል፣ **አልማ** ፲፡ ፳፯።

ጻድቅ ላልሆነው ስራዎቻቸው ዓለምን እንዲ ወቅሱ ልኬአችኋለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፬፡ ፴፯። ነፍስ ጻድቃን ካልሆኑት ሁሉ መንጻት አለባት፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡ ፲፯–፲፰። በቶሎ ጻድቅ ባልሆነ ሁኔታ ስልጣናቸውን እንደሚጠቀሙበት፣ የም ንም ያህል ሰዎች ሁሉ ፍጥረት እና ባህሪይ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፸፭፡ ፴፱።

ኃጢያት። *ደግሞም ኃጢያተኛ፣ አመፃ፤ መበደል፣ አመጽ፣ አስጸያፊ፣ አስከፊ፣ አሰቃቂ፣ ርኩሰት፤ እድፍ፣ እድፍነት፤ እግዚአብሔርን የሚጠላ፤ ክፉ፣ ክፋት ተመልከቱ*

ለእግዚአብሔር ትእዛዛት በፈቃደኛነት ታዛዥ አለመሆን

ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፣ **ምሳ.** ፳፰፡ ፲፫። ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፣ **ኢሳ.** ፩፡ ፲፰። ኃጢያተኞች ይሞታሉ፣ እናም ጻድቃን ይድናሉ፣ **ሕዝ.** ፲፰፡ ፳፡ ፳፩፡ ፳፪፡ ፳፫፡ ፳፭፡ ፳፮፡ ፳፰፡ ፳፱፡ ፴፡ ፴፩፡ ፴፪፡ ፴፫፡ ፴፭፡ ፴፮፡ ፴፯፡ ፴፰፡ ፴፱፡ ፵፡ ፵፩፡ ፵፪፡ ፵፫፡ ፵፭፡ ፵፮፡ ፵፯፡ ፵፰፡ ፵፱፡ ፶፡ ፶፩፡ ፶፪፡ ፶፫፡ ፶፭፡ ፶፮፡ ፶፯፡ ፶፰፡ ፶፱፡ ፷፡ ፷፩፡ ፷፪፡ ፷፫፡ ፷፭፡ ፷፮፡ ፷፯፡ ፷፰፡ ፷፱፡ ፸፡ ፸፩፡ ፸፪፡ ፸፫፡ ፸፭፡ ፸፮፡ ፸፯፡ ፸፰፡ ፸፱፡ ፹፡ ፹፩፡ ፹፪፡ ፹፫፡ ፹፭፡ ፹፮፡ ፹፯፡ ፹፰፡ ፹፱፡ ፺፡ ፺፩፡ ፺፪፡ ፺፫፡ ፺፭፡ ፺፮፡ ፺፯፡ ፺፰፡ ፺፱፡ ፻፡ ፻፩፡ ፻፪፡ ፻፫፡ ፻፭፡ ፻፮፡ ፻፯፡ ፻፰፡ ፻፱፡ ፲፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ፲፭፡ ፲፮፡ ፲፯፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ፳፡ ፳፩፡ ፳፪፡ ፳፫፡ ፳፭፡ ፳፮፡ ፳፯

ኃጢያትን በምመለከትበት ወቅት በጥላቻ ታን ቀጠቅጠኛለህን፣ ፤ ኔፊ ፬፡፴፭። በኃጢአታቸው ለሚሞቱ ሁሉ ወዮላቸው፣ ፤ ኔፊ ፱፡፴፯። ኃጢ ያትን ከመጥላት በቀር ሊመለከቱትም አልቻሉም፣ አልማ ፲፫፡፲፪። ከኃጢያት ወደ ደስታ እመለሳለሁ ብለህ አትገምት፣ አልማ ፴፭፡፱–፲። ጌታ ኃጢያትን በትንሹም ቢሆን ሊቀበለው አይቻለውም፣ አልማ ፴፭፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፩፡፴፭)። ህፃናት ኃጢያትንም ለመፈፀም አይችሉም፣ ሞሮኒ ፰፡፰።

ንስሀ ለመግባት፣ ሰዎች ይናዘዛሉ እናም ይተ ዋቸዋልም፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፴፪–፴፫። ይቅርታ የማይሰጠውም በእርሱ ታላቁ ኃጢያት ይቀራል፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፱። በታላቅ ብርሀን ላይ ኃጢያት የሚሰራው የባሰውን ፍርድ ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲። ኃጢያት ለሚሰራው ነፍስ የድሮው ኃጢ ያት ይመለስበታል፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፯። ኃጢያ ታችንን ለመሸፈን ስንሞክር፣ ሰማያት እራሳቸውን ይለያሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፭፩፡፴፯።

ኅብረት። ቅዱስ ቁርባን *ተመልከቱ*

ነህምያ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በባቢሎን የነበረ በአርጤክ ስስ ቤተ መንግስት ውስጥ ጠጅ አሳላፊው የነበረ፣ ከእርሱም የኢየሩሳሌም ግንብን እንደገና ለመገ ንባት ንጉሳዊ ፈቃድ ያገኘ እስራኤላዊ መኳንን (እርሱ ምናልባት ሌዋውያን ወይም የይሁዳ ነሳ አባል ነበር)።

መፅሐፈ ነህምያ፣ ይህ መፅሐፍ ከመፅሐፈ ዕዝራ የሚቀጥል ነው። ይህም አይሁዶች ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሱ በኋላ በእስራኤል የነበረው ስራ ድርጊቶ ችን እና ችግሮችን ታሪክ የያዘ ነው። ምዕራፍ ፩–፯ ነህምያ ኢየሩሳሌምን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበኘበ ትና፣ ምንም እንኳን ብዙ ተቃዋሚዎች ቢኖሩም ስለከተማዋ ግንቦች በድጋሚ መገንባት ይናገራሉ። ምዕራፍ ፰–፲ ነህምያ በተግባር ላይ ለማዋል ስለሞ ከረው የሀይማኖት እና የህብረተሰብ መሻሻል ይገ ልጻሉ። ምዕራፍ ፲፩–፲፫ ብቁ የሆኑትን ሰዎች ስም ይሰጣሉ እናም ስለግንቡ መቀደስ ታሪክም ይነግ ራሉ። በምዕራፍ ፲፫ ቁጥሮች ፩–፴፩ ውስጥ ነህምያ ለአስራ ሁለት አመት ከእዚያ ከሄደ በኋላ፣ ኢየሩ ሳሌምን ለሁለተኛ ጊዜ ስለነበኘበት ይመዘግባሉ።

ነቢይ፡ *ደግምም ራዕይ፣ ባለራዕይ፣ ትንቢት፣ መተንበይ፣ ፕሬዘደንት ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር የተጠራ እናም እርሱን በመወከል የሚናገር ሰው። እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ፣ ነቢይ ትእዛዛትን፣ ትንቢቶችን፣ እና ራዕዮችን ከእ ግዚአብሔር ለመቀበል ይችላል። የእርሱም ሀላፊነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና እውነተኛ ጸባይ ለሰው ዘር ለማሳወቅ እና እርሱ ከእነርሱ ጋር ያለውን ግን ኙነት ትርጉም ማሳየት ነው። ነቢይ ኃጢያትን ይወ ቅሳል እናም የዘህን ውጤቶች አስቀድሞ ይነግራል። እርሱም የጽድቅ ሰባኪ ነው። አንዳንዴም፣ ነቢያት ለሰው ዘር ጥቅም ስለወደፊት አስቀድመው ይናገ ራሉ። የእርሱ ዋና ሀላፊነት ግን ስለኢየሱስ ክርስ ቶስ መመስከር ነው። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየ ሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት ዛሬ በም ድር ላይ ያለ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው። ቀዳሚ አመራር እና አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት እንደ ነቢያት፣ ባለራዕዮች፣ እና ገላጮች ይደገፋሉ።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፣ ዘኁል. ፲፩፡፳፱። ነቢይ ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር በራዕይ እገለጥለታለሁ፣ ዘኁል. ፲፪፡፮። እግዚአብ ሔርም በነቢዩ ሁሉ በእስራኤል መሰከረ፣ ፤ ነገሥ. ፲፯፡፲፫ (፤ ዜና ፴፮፡፲፭–፲፮፣ ኤር. ፯፡፳፭)። ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ፣ ኤር. ፩፡፭፣ ፮። ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ነገረ፣ ዓሞ. ፫፡፯።

በቅዱሳን ነቢያት አፍ ተናገረ፣ ሉቃ. ፩፡፷ (የሐዋ. ፫፡፳፩)። ሐዋሪያት በሙሉ ስለክርስቶስ መሰከሩ፣ የሐዋ. ፲፡፴፫። እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን ነቢያትን አድርጎአል፣ ፤ ቆሮ. ፲፪፡፳፰ (ኤፌ. ፬፡፲፩)። ቤተክርስቲያኗ በሐዋሪያትና በነ ቢያት መሰረት ተገንብታለች፣ ኤፌ. ፪፡፲፱–፳። ህዝብ የነቢያትን ቃላት አስወገዱ፣ ፤ ኔፊ ፫፡፲፯–፲፰ (፤ ኔፊ ፳፯፡፣ ፫)። በመንፈስ ሁሉም ነገሮች ለነ ቢያት ታውቀዋል፣ ፤ ኔፊ ፳፪፡፩–፪። ክርስቶስ ወደ ኔፋውያን የመጣው በቅዱስ ነቢያት አፍ የተነገረ ውን ለማሟላት ነው፣ ፫ ኔፊ ፩፡፲፫ (ት. እና ቃ. ፴፪፡፴፱)።

ለነቢያት ቃላት ትኩረት የማይሰጡ፣ ከሰዎች መካከል የሚቆረጡበት የሚገለሉበት ቀን ይመ ጣል፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፩። የነቢያትን ቃላቶች ያመ ኑት ሁሉ ዘለአለማዊ ህይወት ያገኛሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፯። የነቢያትን ቃል ልክ ከእኔ አፍ እንደወጣ አድርጋችሁ ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፩–፯። ለቤተክርስቲያኗ ራዕዮች እና ትእዛዛት የሚመ ጡት በተመደቡት በኩል ብቻ ነው፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፩–፲፩። የከፍተኛው የክህነት ፕሬዘደንት ሀላ ፊነት ቤተክርስቲያኗን በሙሉ ለመምራት፣ እና እንደሙሴ አይነት ነቢይ ለመሆን ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፩–፶፪።

በነቢያት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፯።

ነቢይት፡ *ደግምም ትንቢት፣ መተንበይ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር የተቀበለች እና የራ ዕይ መንፈስን የምትደሰትበት ሴት። ነቢይት ክህ ነትን ወይም ቁልፎቹን አትይዝም። ምንም እንኳን በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ነቢይት ተብለው የተ

ጠሩ ሴቶች ጥቂት ቢሆኑም፣ እንደ ርብቃ፣ ሀና፣ ኤልሳቤጥ፣ እና ማርያም ተንብየዋል።

ማሪያምም ነቢይት ነበረች፣ **ዘፀአ.** ፲፭፡፳ሸ። ዲቦራ ነቢይት ነበረች፣ **መሳ.** ፬፡፬። ሕልዳና ነቢይት ነበረች፣ ፪ **ነገሥ.** ፳፪፡፲፬ (፪ ዜና ፴፬፡፳፪)። ሐና ነቢይት የምትባል ነበረች፣ **ሉቃ.** ፪፡፴፮።

ነነዌ። *ደግሞም* አሶር፣ ዮናስ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአሶር ዋና ከተማ እና ለሁለት መቶ አመት በታይግረስ ወንዝ በስተምስራቅ ዳር ዋና የንግድ ቦታ ነበር። በ፯፻፹፯ ም.ዓ. በአሶር ግዛት ውድቀት ጊዜ ወደቀ።

የአሶር ንጉስ ሰናክሬ በነነዌ ውስጥ ይኖር ነበር፣ ፪ **ነገሥ.** ፲፱፡፴፮። ዮናስ ከተማውን ንስሀ እንዲገቡ ለመጥራት ተላከ፣ **ዮና.** ፩፡፩–፪ (ዮና. ፫፡፩–፬)። የነነዌ ህዝብ ንስሀ ገቡ፣ **ዮና.** ፫፡፭–፲። ኢየሱስ በአይሁዶች ፊት ነነዌን እንደ ንስሀ መግባት ተጠቀመባቸው፣ **ማቴ.** ፲፪፡፳፩።

ነይ። *ኑ ተመልከቱ*

ነጻ ምርጫ። *ደግሞም* መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፣ ነጻ፣ ነጻነት *ተመልከቱ*

እግዚአብሔር ለመምረት እና በራሳቸው ለመስራት ለሰዎች የሰጣቸው ችሎታ እና እድል።

ከዛፍ ሁሉ ለመብላት ነጻ ነህ፣ **ዘፍጥ.** ፪፡፲፮። የምታገለግለውን ዛሬ ምረጡ፣ **ኢያ.** ፳፬፡፲፭ (አልማ ፴፡፳፡ ሙሴ ፮፡፴፫)።

ሰው ካልተፈተነ በስተቀር ለራሱ ማድረግ አይቻለውም፣ ፪ **ኔፊ** ፪፡፲፭–፲፮። ሰዎች ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ **ኔፊ** ፪፡፳፯። እናንተ ነፃ ናችሁ፣ ለራሳችሁ እንድትሰሩ ተፈቅዶላችኋል፣ **ሔለ.** ፲፡፭፡ ፴።

አንድ ሶስተኛውን የሰማይ ሰራዊቶች በነጻ ምርጫቸው ምክንያት እንዲተዉ አደረገ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፴፯። ዲያብሎስ የሰዎችን ልጆች ይፈትን ዘንድ ግድ ነው፣ ካልሆነ በራሳቸው ለራሳቸዉ መምረጥ አይችሉም፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፴፱። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ይምረጥ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡፭። ሁሉም ሰው በሰጠሁት ስነምግባር መሰረት ይስራ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፩፡፫፲፯።

ሰይጣን የሰው ነጻ ምርጫ ለማጥፋት ፈለገ፣ **ሙሴ** ፭፡፫። ጌታ ለሰው ነጻ ምርጫውን ሰጠው፣ **ሙሴ** ፮፡፴፪።

ነጻ፣ ነጻነት። *ደግሞም* መብት፣ ባርነት፣ ነጻ ምርጫ *ተመልከቱ*

ያለመገደድ የግል ምርጫዎችን ለመምረጥ ያለ ሀይል ወይም ችሎታ። በመንፈሳዊ አስተያየት፣ ንስሀ የገባና የእግዚአብሐእርን ፍላጎት የሚያከብር ሰው ከኃጢያት እስር በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል ነጻ ነው (ሞዛያ ፭፡፯)።

እውነትም አርነት ያወጣችኋል፣ **ዮሐ.** ፰፡፴፪። ከኃጢያት ነጻ የሚሆኑት የዘለአለም ህይወትን ይቀበላሉ፣ **ሮሜ** ፮፡፲፱–፳፫። ፃድቃን የሆነ የእስራኤል ቤት ቅርንጫፍን ከተ ደበቀው ጨለማና ምርኮ ወደ ነፃነት ይመጣል፣ ፪ **ኔፊ** ፫፡፭። ለነጻነታቸው ወደ ጌታ ጮሁ፣ **አልማ** ፶፫፡፶፰–፶፡ ሞሮኒ በሀገሩ መብትና ነጻነት ተደ ሰተ፣ **አልማ** ፶፰፡፲፭። የእግዚአብሔር መንፈስ የነፃነት መንፈስ፣ **አልማ** ፰፭፡፲፭።

ተከተሉኝ፣ እናም ነፃ ህዝብም ትሆናላችሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፰፡፳፪።

ነፍስ። *ደግሞም* መንፈስ፣ ሰውነት *ተመልከቱ*

ቅዱሳት መጻህፍት ስለነፍስ በሶስት መንገዶች ያናገሩባቸዋል፥ (፩) ከምድረ ህይወት በፊት እና ከምድረ ህይወት በኋላ ያሉ መንፈሶች (አልማ ፴፡፲፭–፲፰፤ አብር. ፫፡፳፫)፣ (፪) በአለሟች ነት አንድ የሆነ መንፈስ እና ሰውነት (ት. እና ቃ. ፸፰፡፲፭)፤ አብር. ፭፡፲)፤ እናም (፫) መንፈሱና ሰውነቱ እንደገና ለመለየት በማይቻል ሁኔታ አንድ የሆኑለት የማይሞት፣ ከሞት የተነሳ ሰው (፪ ኔፊ ፱፡፲፫፤ ት. እና ቃ. ፸፰፡፲፭–፲፯)።

ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያል፣ **ዘሌዋ.** ፲፯፡፲፭። ነፍሴን መለሳት፣ **መዝ.** ፳፫፡፩–፫። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ **ማቴ.** ፳፪፡፴፯ (ማር. ፲፪፡፴)።

ዲያብሎስ ነፍሳቸውን ያታልላል፣ ፪ **ኔፊ** ፳፰፡፳፡ ፳፭። መላ ነፍሳችሁን ለእርሱ እንደ መስዋዕትነት አቅርቡ፣ **ኦምኒ** ፩፡፳፯። ቃሉ በነፍሴ ውስጥ ማደግ ጀመሯል፣ **አልማ** ፴፪፡፳፡ ነፍሱ አትራብም እንዲሁም አትጠማም፣ ፫ **ኔፊ** ፳፡፡ የቅዱስ ቁርባን ዳቦ እና ውሀ ለሚበሉትና ለሚጠጡት የተቀደሱ ናቸው፣ **ሞሮኒ** ፱–፲ (ት. እና ቃ. ፳፡ ፫፲፯–፫፱)።

በመንግስት ውስጥ የሚያገለግሉት በአገልግሎታቸው በኩል ለነፍሳቸው ደህንነት ያመጣል፣ **ት. እና ቃ.** ፩፡፪፣ ፩። የነፍሶች ዋጋ ታላቅ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፰፡፲።

ወደ ምድር በውሃ፣ ደምና፣ መንፈስ ተወለድክ፣ እናም በዚህም ህያው ነፍስ ሆንክ፣ **ሙሴ** ፮፡፶፱።

የነፍሶች ዋጋ፣ ሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ስለእያንዳንዱ ልጆቹ ሀሳብ አለው እናም እያንዳንዱንም እንደ አስፈላጊ ይመለከታቸዋል። ልጆቹ ስለሆኑም፣ እንደ እርሱ የመሆን ችሎታ አላቸው። ስለዚህ፣ ታላቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው።

ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ደስታ ይሆ ናል፣ ሉቃ. ፲፭፡፲፡ በእግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል፣ ዮሐ. ፫፡፲፮።

የማንም የሰው ነፍስ መጥፋቱን ሊቀበሉት አል ቻሉም፣ ሞዛያ ፳፯፡፫። በዚህን ጊዜ ያለው ነፍስ በመምጫው ጊዜ እንደሚኖረው ነፍስ ለእግዚአ ብሔር ውድ የሆነ አይደለምን፣ አልማ ፴፪፡፲፯።

ለአንተ ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር፣ ነፍሶችን ወደ እኔ ታመጣ ዘንድ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፮። የነፍ ሶች ዋጋ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ እንደሆነ አስ ታውሱ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲–፲፭።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥ ቶም የማሳለፍ ስራዬ እና ክብሬ ይህም ነው፣ ሙሴ ፩፡፴፱።

ኑ። *ደግሞም ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፣ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ፣ በአብዛኛው ጊዜ “ወደ ክርስቶስ ኑ እናም በእርሱም ፍጹማን ሁኑ” (ሞሮኒ ፲፡፴፪) በሚለው አይነት መግለጫ አን ድን ሰው በመከተል ወይም ታዛዥ በመሆን መቅ ረብ ነው።

ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ፣ ኢሳ. ፶፭፡፫።

እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፡ ወደ እኔ ኑ፣ ማቴ. ፲፩፡፳፰። ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፣ ማቴ. ፲፱፡፲፬። በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ፣ ሉቃ. ፱፡፳፫። ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ ዮሐ. ፮፡፴፭።

ክርስቶስ ሁሉም ወደ እርሱ እንዲመጡ ይጋብ ዛል፣ ፪ኔፊ ፳፮፡፴፣ ወደ እኔ ኑ እናም ዳኑ፣ ፫ኔፊ ፲፪፡፳። ወደ ክርስቶስ ኑ፣ ሞሮኒ ፲፡፴፪።

ሁሉንም ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ጋብዙ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፶፱። ወደ እኔ ኑ፣ እናም ነፍሳችሁ ይኖራል፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፵፮።

ኑኃሚ። *ደግሞም ሩት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ጻድቅ ሴት እና የአ ቤሜሌክ ሚስት (ሩት ፩–፬)። አቤሜሌክ እና ኑኃሚ ከረሀብ ለማምለጥ ቤተሰባቸውን ወደ ሞአብ ወሰዱ። አቤሜሌክ እና ሁለቱ ወንድ ልጆቿ ሞቱ፣ ኑኃሚ ወደ ቤተልሔም ከልጇ ሚስት ሩት ጋር ተመለሰች።

ኒቆዲሞስ። *ደግሞም ፈሪሳዊያን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ጻድቅ የአይሁዳ ገገር (ምናልባት የሳንሀድሪን አባል) እና ፈራሲዋ (ዮሐ. ፫፡፩)።

በምሽት ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ፣ ዮሐ. ፫፡፩–፳፩። ከፈራሲዋን ጋር ለኢየሱስ ተከራከረ፣ ዮሐ. ፯፡፣–፴፣። ለኢየሱስ መቃብር ሽቱ አመጣ፣ ዮሐ. ፲፱፡፴፱–፴፡

ና። *ኑ ተመልከቱ*

ናሆም

ትንቢቶቹን በ፯፻፴፪ እና በ፯፻፯ ም.ዓ. መካከል ትንቢቶቹን የመዘገበ የብሉይ ኪዳን የገሊላ ነቢይ።

ትንቢተ ናሆም፣ ምዕራፍ ፩ በዳግም ምፅዓት የም ድር መነደድ እና ስለጌታ ምህረት እና ሀይል ይና ገራል። ምዕራፍ ፪ በኋለኛው ቀናት ስለሚመጡት አስቀድሞ የሚነግረው ስለነነዌ መደምሰስ ይናገ ራል። ምዕራፍ ፫ ስለነነዌ አሰቃቂ መደምሰስ አስ ቀድሞ መንገርን ይቀጥላል።

ናቡከደነፆር። *ደግሞም ባቢሎን፣ ዳንኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ይሁዳን ያሸነፈ (፪ ነገሥ. ፳፬፡፩–፭) እና ኢየሩሳሌምን በጦር ሀይል የከበበ (፪ ነገሥ. ፳፭፡፣–፲፩) የባቢሎን ንጉስ። ነቢዩ ሌሂ በ፯፻ ም.ዓ. ንጉስ ናቡከደነፆር ንጉስ ሴዴቅያስ ንና ህዝቡን በሚወስድበት ጊዜ በምርኮ ወደ ባቢ ሎን መወሰድን ለማስወገድ ከኢየሩሳሌም እንዲ ሸሽ ታዘዘ፣ (፩ ኔፊ ፩፡፭–፲፣) (፪ ነገሥ. ፳፭፡፩፣ ፳–፲፯፣ ፳–፳፪) ዳንኤል ናቡከደነፆር ህልምን ተረ ጎመ (ዳን. ፪፣ ፭)።

ናታን። *ደግሞም ዳዊት ተመልከቱ*

በንጉስ ዳዊት ዘመን የነበረ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። ለጌታ ቤተመቅደስ ለመገንባት ዳዊት ሀሳብ ሲያቅ ርብ፣ ጌታ ናታን ዳዊትን እንዳይገነባ እንዲነግረው አዘዘ። ናታን ዳዊት ከእርሱ ጆግናዎች አንዱ የሆ ነው የኦሪዮ ሞት ምክንያት ስለሆነ እናም የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህ ስላገባ ገሰጸው (፪ ሳሙ. ፲፪፡፩–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፲፯፴፪፡፴፯–፴፱)። ሳዶቅ፣ ከና ታን ጋር፣ የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን እንደ ንጉስ ቀቡ (፩ ነገሥ. ፩፡፴፯–፴፱፣ ፵፭)።

ናትናኤል። *ደግሞም በርተሎሜዎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እና የፊልጶስ ጓደኛ (ዮሐ. ፩፡፵፭–፶፩)። በገሊላና ውስጥ ከቃና መጣ (ዮሐ. ፳፩፡፪)። ክርስቶስ ናትና ኤል ተንኮል የሌለው እስራኤላውያን ነው አለ (ዮሐ. ፩፡፵፯)። እርሱና በርተሎሜዎስ በአጠቃላይ አንድ ሰው ናቸው ተብሎ ይታሰባል (ማቴ. ፲፡፫፣ ማር. ፫፡፲፰፣ ሉቃ. ፮፡፲፬፣ ዮሐ. ፩፡፵፫–፵፭)።

ናዕማን። *ደግሞም አልሳዕ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሶርያ ንጉስ ሰራዊት ወታደር። ደግሞም ለምጻም ነበር። በእስራኤላዊ ገደር ታማኝነት ምክንያት ወደ እስራኤል ነቢይ

ኤልሳዕን ለማየት ሄደ። እራሱን ትሁት በማድረግ እና ነቢዩ ኤልሳዕ እንደነገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ እራሱን ለሰባት ጊዜ በማጠብ ከለምጻምነቱ ዳነ (፪ ነገሥ. ፭፡፩–፲፬፤ ሉቃ. ፬፡፳፯)።

ናዝሬት። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በገሊላ ባህር በስተምዕራብ በኮረብታዎች መካከል የምትገኝ መንድር። ናዝሬት የክርስቶስ የመጀመሪያ መኖሪያ ቦታ ነበር (ማቴ. ፪፡፳፫)። ኢየሱስ በናዝሬት በምኩራብ ውስጥ አስተማረ፣ እናም በኢሳይያስ ፡፡፩፡፩–፪ ውስጥ ያለውን ትንቢት እንዳሟላ አወጀ (ማቴ. ፲፫፡፶፭–፶፰፤ ማር. ፮፡፩–፮፤ ሉቃ. ፬፡፲፮–፴)።

ናሹ፣ ኢለኖይ (ዮ.ኤስ.ኤ.)

በ፲፡፲፱፴፱ (እ.አ.አ.) በኢለኖይ ግዛት ውስጥ በጓለኛው ቀን ቅዱሳን የተመሰረተ ከተማ። የሚገኘው ከሴንት ሉውስ ከተማ ፪፲ ማይል (፫፲፯ ኪሎ ሜትር) ከወንዙ በላይ በምስስፒ ወንዝ አጠገብ ነው።

በምዙሪ ግዛት በተሰደዱበት ምክንያት፣ ቅዱሳን ወደ ፪፲ ማይል (፫፲፯ ኪሎ ሜትር) ወደ ሰሜን ምስራቅ አካባቢ፣ የምስስፒ ወንዝን በመሻገር፣ ጥሩ ሁኔታዎችን ወደሚያገኙበት ወደ ኢለኖይ ሄዱ። ከጊዜ በኋላም፣ ቅዱሳን ገና ባልለመለመ ኮሜርስ ከተማ አጠገብ ምድር ገዙ። ከአንዳንድ ህንጻዎች በስተቀር፣ ይህ ምድር አረንቋማ ነበር ቅዱሳን ከም ድሩ ውሀውን አደረቁ እና ቤቶቻቸውን መሰረቱ። ጆሴፍ ስሚዝ ቤተሰቡን በእንጨት በተሰራ ትንሽ ቤት ውስጥ አስገባ። ኮሜርስ የሚባለው የከተማው ስም ወደ ናሹ ተቀየረ፣ ይህም ከዕብራውያን “ወብ ታማ” ከሚባለው ቃል ነው።

የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ብዙ ክፍሎች የተመዘገቡት በናሹ ውስጥ ነው (ት. እና ቃ. ፲፰፡–፲፰፱፤ ፲፡፴፱፤ ፲፡፴፭)። ቅዱሳን በናሹ ቤተመቅደስ እንዲገነቡ ተነገራቸው (ት. እና ቃ. ፲፰፡፡–፲፰፮–፲፰፯)። ከቤቶቻቸው በ፲፡፲፱፴፯ (እ.አ.አ.) ተነድተው ከመሰደዳቸው በፊት ቤተመቅደስን ሰሩ እናም የፅዮን ካስማዎችን አደራጁ። በመሳደዳቸው ምክንያት፣ ቅዱሳን ከእዚያ ቦታ ወጡና ወደ ምዕራብ ተጓዙ።

ኔሆር። *ደግሞም የካህን ተንኮል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የነበረ ክፉ ሰው። ኔሆር በኔፋውያን መካከል የካህናት ተንኮል ከሰሩት የመጀመሪያው ነበር። የህሰት ትምህርትን ካስተማረና ጌዴዎንን ከገደለ በኋላ፣ ኔሆር ለወንጀሉ በሞት ተቀጣ (አልማ ፤)። የኔሆር ተከታዮች ኔሆር ከሞተ ከረጅም ጊዜ በኋላ የክፉ ስራውንና ትምህርቱን ቀጠሉ።

አልማና አሙሌቅ በኔሆር ተከታይ ዳኛ ወደ እስር ቤት ተሰድደው ነበር፣ **አልማ** ፲፡፡–፲፡–፲፡፡። የተገ ደሉት የኔሆርን ኃይማኖት ተከታዮች ነበሩ፣ **አልማ** ፲፮፡፲፩። ብዙ የኔሆርን ስርዓት የሚከተሉ ነበሩ፣ **አልማ** ፷፩፡፡። ብዙዎቹን ወንድሞቻቸውን የገ ደሉት የኔሆር ስርዓት የሚከተሉ ነበሩ፣ **አልማ** ፷፡፡፡፷፡፡።

ኔፊ፣ የሔለማን ልጅ። *ደግሞም ሔለማን፣ የሔለማን ልጅ፣ ሌሂ፣ የኔፋውያን ሚስዮን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ታላቅ ኔፋውያን ነቢይና ሚስዮን።

የሔለማን ታላቅ ልጅ ነበር፣ **ሔለ.** ፫፡፷፩። ዋና ዳኛ እንዲሆን ተመደበ፣ **ሔለ.** ፫፡፴፯። እርሱና ወንድሙ ሌሂ ብዙ ላማናውያንን ወደ ወንጌል አመጣቸው፣ **ሔለ.** ፭፡፣፲–፣፲፱። በእሳት ተከበበ እናም ከእስር ቤት ተለቀቀ፣ **ሔለ.** ፭፡፷–፶፪። በአትክልት ስፍራ ግንብ ላይ ጸለየ፣ **ሔለ.** ፯፡፯–፣፡። የዋና ዳኛውን መገደል ገለጸ፣ **ሔለ.** ፡፡፡፡–፡፡፡፣ ፲፡፩–፴፡፡። በጌታ ሀይል ተሰጠው፣ **ሔለ.** ፣፡፫–፣፩። ጌታ ረሃብን እንዲያመጣ እና ረሀብ እንዲቆም ጠየቀ፣ **ሔለ.** ፣፩፡፫–፣፡፡።

ኔፊ፣ የሌሂ ልጅ። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት፣ ኔፋውያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂና የሳርያ ጻድቅ ልጅ ነው (፩ ኔፊ ፩፡፩–፴፣ ፪፡፲)። ኔፊ በእግዚአብሔር ቃል ታላቅ እምነት ነበረው (፩ ኔፊ ፫፡፣) እና ታላቅ ነቢይ፣ መዝገብ ጠባቂ፣ እና የህዝቡ መሪ ሆነ።

ታዛዥ ነበር እናም በእምነት ጸለየ፣ ፩ ኔፊ ፪፡፣፲፩። የህሰስ ሰሌዳዎችን ለማምጣት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፣ ፩ ኔፊ ፫–፴። የእስማኤል ቤተሰብን ወደ ምድረበዳ ለማምጣት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፣ ፩ ኔፊ ፣፡። ሌሂ የተቀበለውን አንድ አይነት ራዕይ ተቀበለ፣ ፩ ኔፊ ፣፡፣፲–፣፪፪፣ ፣፩። በራዕይ በህዝቡ ላይ ወደፊት የሚደርሰውንና የወንጌል ዳግም መመለስን ተመለከተ፣ ፩ ኔፊ ፣፪–፣፣፣። በህይወት ዛፍ ራዕይን ተረጎመ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፡፡–፡፡፩–፴፣፩። ቀሰቱን ሰበረ ነገር ግን በእምነት ምግብን ለማግኘት ቻለ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፩፡፣፣፡–፴፪። መርከብን ሰራ እና ወደ ቃል ኪዳን ምድር ተጓዘ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፩–፣፣፡። ኔፋውያን እና ላማናውያን ተለያዩ፣ ፪ ኔፊ ፡፡። የመጨረሻ ምስክሩን ሰጠ፣ ፪ ኔፊ ፴፣፡።

፩ ኔፊ መፅሐፍ፣ ምዕራፍ ፩ እስከ ፣፡፡፡፡ በም ድረበዳ በህር ውስጥ ወደ ባህር እስከሚደርሱ ድረስ ተጓዙ። ፩ ኔፊ ፣፡፡፡፡–፡፡፣ በጌታ እንደተመሩት፣ ምንም እንኳን ላማን እና ላሙኤል ቢያምጹም ወደ ቃል ኪዳን ምድር ስለተጓዙበት ጉዞ ይናገራሉ። ምዕራፍ ፣፣፩–፡፡፪ ኔፊ መዝገቦችን ስለጠበቀበት አላማ ይናገራሉ (፩ ኔፊ ፪፣ ፣፣፩፡፣፣፡)፣ ይህም ሁሉም ጌታ

ቤዛቸውን እንዲያስታውሱ ለማሳመን ነው። ኢሳይ ያስን ጠቀሰ (፩ ኔፊ ፳–፳፩) እናም በተስፋ ሁሉም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ቤዛቸው ለማ የት እንደሚችሉ የሚገልጸውን የኢሳይያስን ምል እክት ተረጎመ (፩ ኔፊ ፳፪፡፲፪)።

፪ የኔፊ መፅሐፍ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ለልጆቹና ለት ውልዶቻቸው ከተሰጣቸው በረከቶች በተጨማሪ፣ ከመሞቱ በፊት የሰጣቸውን የሌሂን የመጨረሻ ትም ህርቶች እና ትንቢቶች የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፭ ኔፋያን ከላማናውያን ጋር የተለያዩበትን ምክንያት ይገልጻል። ኔፋውያን ቤተመቅደስ ሰሩ፣ የሙሴ ህግን አስተማሩ፣ እናም መዝገቦችን ጠበቁ። ምዕ ራፍ ፮–፲ የኔፊ ታናሽ ወንድም የያዕቆብ ቃላትን የያዙ ናቸው። ያዕቆብ የይሁዳን ታሪክ ገመገመ እና ስለመሲህ ተነበየ፣ አንዳንዶቹም ከነቢዩ ኢሳይያስ ፅሁፎች የተወሰዱ ነበሩ። በምዕራፍ ፲፩–፴፫ ውስጥ ኔፊ ስለክርስቶስ ስለነበረው ምስክር፣ ስለያዕቆብ ምስክር፣ ስለኋለኛው ቀናት ትንቢቶች፣ እና ከብ ሉይ ኪዳን መፅሐፈ ኢሳይያስ ውስጥ አንዳንድ ምዕ ራፎችን ይመዘግባል።

የኔፊ ሰሌዳዎች፣ ሰሌዳዎች ተመልከቱ

ኔፊ፣ የኔፊ ልጅ፣ የሔለማን ልጅ። *ደግሞም ኔፊ፣ የሔለማን ልጅ፤ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ከሞት በተነሳው ኢየ ሱስ ክርስቶስ ከተመረጡት አስራ ሁለት ደቀመዛ ሙርቶች መካከል አንዱ (፫ ኔፊ ፩፡፪–፫፤ ፲፱፡፱)። ይህ ነቢይ ለህዝቡ ጥቅም በሀይል ወደ ጌታ ጸለየ። ኔፊ የጌታን ድምፅ ሰማ (፫ ኔፊ ፩፡፲፩–፲፭)። ደግ ሞም ኔፊ በመላእክት ተነበገ፣ ዲያብሎሶችን አስ ወጣ፣ ወንድሙን ከሞት አስነሳ፣ እናም ለመካድ የማይቻል ምስክር ሰጠ (፫ ኔፊ ፯፡፲፭–፲፱፤ ፲፱፡፱)። ኔፊ የቅዱሣት መጻህፍት መዝገቦችን ጠበቀ (፫ ኔፊ ፩፡፪–፫)።

፫ የኔፊ መፅሐፍ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፊ ልጅ በሆነው ኔፊ የተጻፈ መፅሐፍ። ምዕራፍ ፩–፲ ስለጌታ መምጣት የተተነበዩትን መሟላት ያሳያሉ። የክርስቶስ መወለድ ምልክት ተሰጡ፤ ህዝቡ ንስሀ ገቡ፤ ነገር ግን ወደ ክፋታቸው ተመለሱ። በመጨ ረሻም አውሎ ንፋስ፤ የምድር መንቀጥቀጥ፣ ሀይ ለኛ ማዕበል፣ እና ታላቅ ድምሳሴ የክርስቶስን ሞት በምልክት ሰጡ። ምዕራፍ ፲፩–፳፰ ክርስቶስ ወደ አሜሪካ የመጣበትን ይመዘግባሉ። ይህም የ፫ ኔፊ መፅሐፍ ዋና ክፍል ነው። ብዙዎቹ የክርስቶስ ቃላት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሰጣቸው ስብከቶች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው (ለምሳሌ፣ ማቴ. ፭–፯ እና ፫ ኔፊ ፲፪–፲፫)። ምዕራፍ ፳፱–፴ ለኋለኛው ቀን ሀገሮች ሞርሞን የተናገራቸውቃላትናቸው።

፬ የኔፊ መፅሐፍ፣ ይህ መፅሐፍ አርባ ዘጠኝ ቁጥ ሮች ብቻ ነው ያሉት፣ ነገር ግን የኔፋውያን ሶስት መቶ አመት ታሪክን የሚሸፍን ነው። በዚህ መዝ ገብ የጻፉ ከኔፊ በተጨማሪ ብዙ የጸሀፊ ትውልዶች ነበሩ። ቁጥሮች ፩–፲፱ በትንሳኤ ከተነሳው ጌታ ጉብ ኝት በኋላ፣ ኔፋውያንና ላማናውያን በሙሉ ወደ ወንጌሉ ተቀየሩ። ሰላም፣ ፍቅር፣ እና ስምምነት ነገሰ። ክርስቶስ እስከ ዳግም ምፅዓቱ ድረስ በም ድር እንዲቀሩ የፈቀደላቸው ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቱ (፫ ኔፊ ፳፯፡፱–፳) ህዝብን አገለገሉ። ኔፊ መዝገቡን ለልጁ አሞጽ አሳልፎ ሰጠ። ቁጥሮች ፲፱–፴፯ የአሞጽን (፳፡፱ አመታት) እና የልጁ የአ ሞጽን (፴፲፪ አመታት) አገልግሎትን መዝግበዋል። በ፴፪ ዓ.ም. ውስጥ፣ ትዕቢት እራሳቸውን በመደብ መከፋፈል እና ገንዘብ ለማግኘት የሀሰት ቤተክር ስቲያኖችን በጀመሩት ህዝብ መካከል ችግር መፍ ጠር ጀመረ (፱ ኔፊ ፩፡፳፱–፴፪)።

የ፴ ኔፊ የመጨረሻው ቁጥሮች ህዝቡ እንደገና ወደ ክፋት እንደተመለሱ ያሳያሉ (፱ ኔፊ ፩፡፴፩–፴፱)። በ፫፲፭ ም.ዓ. የአሞፅ ልጅ አሞፅ ሞተ እናም ወንድሙ አማሮን ለጥበቃ ቅዱስ መዝገቦችን ደበቀ። አማሮን በኋላም መዝገቡን የእራሱ የህይወት ጊዜ ብዙ ድርጊቶችን ለመዘገበውና ከእዚያም አሳጥሮ ለጻፋቸው ሞርሞን በእምነት አሳልፎ ሰጠ (ሞር. ፩፡፪–፬)።

ኔፋውያን። *ደግሞም ላማናውያን፤ መፅሐፈ ሞርሞን፤ ኔፊ፣ የሌሂ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ያሉ፣ ብዙዎቹ የሌሂ ልጅ የነቢዩ ኔፊ ትውልዶች የሆኑ ህዝብ። ከላማና ውያን ጋር ተለያዩ እናም በአጠቃላይ ከላማናውያን በላይ ጻድቅ ነበሩ። ነገር ግን፣ በኋላም በኃጢያተኛ ነት ምክንያት በላማናውያን ተደመሰሱ።

ኔፋውያን ከላማናውያን ተለያዩ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፭–፲፯። ላማናውያን ያልነበሩት ህዝቦች ኔፋውያን ነበሩ፣ ያዕቆ. ፩፡፲፫። ኔፋውያን ከሁሉም በሚበ ልጥ ምክንያት ተነሳስተው ነበር፣ **አልማ** ፴፫፡፲–፴፣ ፴፭። ኔፋውያን በሞሮኒ ዘመን አይነት ያለ ደስታ አልነበራቸውም፣ **አልማ** ፶፡፳፫። ኔፋውያን በጻድቅ ጻሎቶች ምክንያት ድነው ነበር፣ **አልማ** ፶፪፡፶፡ ኔፋውያን ባለማመን መነሙኑ፣ **ሔለ.** ፲፡፴፱–፴፭። ኢየሱስ በኔፋውያን መካከል አስተማረም አገለገ ለም፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፩–፳፯፡፲፪። ወደ ጌታ የተለወጡ ሁሉ፣ ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአቸው፣ ፬ ኔፊ ፩፡፪–፫። በህዝቡ ልብ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሳ በምድሪቱ ፀብ አልነበረም፣ ከሁሉም በላይ ደስተኛ የሆኑ ህዝብ ነበሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፲፭–፲፯። ኔፋውያን መኩራትና ከንቱ መሆን ጀመሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፴፫። በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ደም መፋሰስ እናም እልቂት ሆነ፣ ሞር. ፪፡፲። ኔፋውያን በክፋት አደጉ እናም ሞርሞን እነርሱን ለመምራት እምቢ አለ፣

ሞር. ፫፡፱–፲፩። ከሀያ አራት በስተቀር፣ ኔፋውያን ሁሉ ተገደሉ፣ ሞር. ፮፡፮–፲፭። ክርስቶስን የማይክዱትን እያንዳንዱ ኔፋውያን ተገደሉ፣ ሞሮኒ ፩፡፪።

ኔፋውያን በኃጢያታቸው እና በእርኩስነታቸው የተነሳ ጠፉ፣ ት. እና ቃ. ፫፡፲፯። ኩራትን ተጠን ቀቁ፣ አለበለዚያም እንደ ኔፋውያን ትሆናላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፱።

ኔፋውያን ደቀመዛሙርት። *ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቶች ተመልከቱ*

ንድፍ

ሰው አንዳንድ ውጤቶችን ለማግኘት የሚከተለው ሞዴል። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ንድፍ በብዙ ጊዜ በአንዳንድ መንገድ ለመኖር ወይም አንድ ነገርን ለመገንባት ምሳሌ ማለት ነው።

ጌታ ለሙሴ በተሰጠው ንድፍ መሰረት እስራኤል ድንኳን እንዲገነቡ አዘዘ፣ **ዘፀአ.** ፳፭፡፰። ዳዊት ለሰለሞን የቤተመቅደስ ህንጻ ንድፍን ሰጠው፣ ፩ ዜና ፳፰፡፣ ፲፩–፲፫።

በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድ ሆን ኢየሱስ ክርስቶስ አሳያቸው፣ ፩ ጢሞ. ፩፡፲፮።

እንዳትታለሉም ለሁሉም ነገሮች ንድፍ እሰጣ ችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡፲፬።

ንጹህ፣ ንጹህነት። *ደግምም ቅድስና፣ ንጹህ እና ርኩስ ተመልከቱ*

ከኃጢያት ወይም ጥፋት ነጻ መሆን፣ ታማኝ። ሰው ንጹህ የሚሆነው ሀሳቦቹ እና ስራዎቹ በሁሉም መንገድ የጸጹ ሲሆኑ ናቸው። ኃጢያት የሰራ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት፣ ንስሀ በመግባት፣ እና የወንጌልን ስነስርዓቶችን በመቀበል ንጹህ ለመሆን ይችላል።

እጆቹ የነጹ፡ ልቡም ንጹሕ የሆነ የጌታን በረከት ይቀበላል፣ መዝ. ፳፬፡፫–፭። እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፣ ንጹሐን ሁኑ፣ ኢሳ. ፶፪፡፲፩ (ት. እና ቃ. ፲፯፫፡፩–፩)።

ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣ ማቴ. ፭፡፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፰)። ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፡ እነ ዚህን አስቡ፣ ፊልጵ. ፬፡፰ (እ.አ. ፩፡፲፫)።

በልባችሁ ንፁህ የሆናችሁ ሁሉ፣ ራሳችሁን አቅኑ እናም አስደሳቹን የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ፣ ያዕቆ. ፫፡፪–፫። በዚያን ቀን በንፁህ ልባችሁና በን ፁህ እጆችሁ እግዚአብሔርን ለመመልከት ትችላላ ችሁን፣ አልማ ፭፡፲፱። በአምላክ ፊት ንፁህና እን ከን የለሽ ከሆኑ፣ ኃጢያትን ከመጥላት በቀር ሊመ ለከቱትም አልቻሉም፣ አልማ ፲፫፡፲፪። ክርስቶስ ንጹህ እንደሆነ ንጹህ ሁኑ፣ ሞሮኒ ፯፡፴፰ (ሞር. ፱፡፮)።

ክርስቶስ ንጹህ ህዝቦችን ለእራሱ ያቆያል፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፩። ጌታ ንጹህ የሆኑት እግዚአ ብሔርን የሚያዩበት ቤት በፅዮን እንዲገነባ አዘዘ፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፣ ፲–፲፯። ይህም ፅዮን ነውና—ልበ ንጹህ፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፳፩።

ንጹህ እና ርኩስ። *ደግምም ንጹህ፣ ንጹህነት፣ እድፍ፣ እድፍነት፣ የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ጌታ ለሙሴ እና ለጥንት እስራኤላውያን አንዳንድ ምግቦች ንጹህ፣ ወይም በሌላ አባባል፣ ለመብላት ብቁ እንደሆኑ ገለጸላ ቸው። እስራኤላውያን በንጹህ እና በርኩስ ምግ ቦች መካከል የሰጡት ልዩነት በህይማኖታቸውና በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ነበ ራቸው። አንዳንድ እንስሳት፣ ወፎች፣ እና አሳ ለምግብ ንጹህ እና ተቀባይ ነበሩ፣ ሎሎችም ርኩስ እና የተከለከሉ ነበሩ (ዘሌዋ. ፲፩፣ ዘዳግ. ፲፬፡፫–፳)። አንዳንድ በሽተኛ ሰዎች እንደ ርኩስ ይቆ ጠሩ ነበር።

በመንፈሳዊ አመለካከት፣ ንጹህ መሆን ከኃጢ ያት እና ከኃጢያታዊ ፍላጎቶች ነጻ መሆን ነው። በዚህ አስተያየትም ያሉ ምግባረ ጥሩና ንጹህ ልብ ያለውን ሰው ይገልጻል (መዝ. ፳፬፡፬)። የእግዚአብ ሔር የቃል ኪዳን ህዝቦች ንጹህ ለመሆን ልዩ መመ ሪያ አላቸው (፫ ኔፊ ፳፡፴፩፣ ት. እና ቃ. ፴፳፡፴፪፣ ፲፴፫፡፭)።

እጆቹ የነጹ፡ ልቡም ንጹሕ የሆነ ወደ ጌታ ተራራ ይወጣል፣ መዝ. ፳፬፡፫–፭።

ማንንም ሰው ተራ ወይም ርኩስ ብላችሁ አት ጥሩ፣ የሐዋ. ፲፡፲፩–፳፳።

በንፁህ ልባችሁና በንፁህ እጃችሁ እግዚአብ ሔርን ለመመልከት ትችላላችሁ፣ አልማ ፭፡፲፱።

ጌታ ፅዩን ንጹህ እስክትሆን ድረስ ይገስጻታል፣ ት. እና ቃ. ፶፡፴፯። የጌታን ዕቃ የምትሸከሙ ንፁሃን ሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፫፡፩–፭፣ ፲፩ (ኢሳ. ፶፪፡፲፩፣ ፲፩)።

ንጹህነት። *ደግምም ማመንዘር፣ ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ በጎነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

የወንዶች እና የሴቶች ወሲባዊ ንጹህነት።

ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስትን መገፋፋት ተቋቋመ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፣ ፯–፳፩ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፩፡፣ ፶፱፡፯)። አታመንዝር፣ ዘፀአ. ፳፡፲፩። ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት፣ ምሳ. ፲፪፡፬ (ምሳ. ፴፩፡፣)።

ሥጋችሁ . . . የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፲፯–፲፱። በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን፣ ፩ ጢሞ. ፬፡፲፪።

ማንኛውም እርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖር አይቻለውም፣ ፩ ኔፊ ፲፡፳፩። እኔ ጌታ አም ላክ በሴቶች ንጹህነት እደሰታለሁ፣ ያዕቆ. ፪፡፳፯። ወሲባዊ ኃጢያት እርኩሰት ነው፣ አልማ ፴፱፡፩–

፲፫። ድንግልነት እና ምግባረ ጥሩነት ከሁሉም ነገሮች በላይ የተወደሰና ውድ ናቸው፣ ሞሮኒ ፱፡፱።
በንጹህነት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፫።

ንፍታሌም። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

ከያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ስድስተኛው እና የራሄል ገረድ ባላ ሁለተኛ ልጅ ነበር (ዘፍጥ. ፴፡፣ ፯–፰)። ንፍታሌም አራት ወንድ ልጆች ነበሩት (፩ ዜና ፯፡፲፫)።

የንፍታሌም ጎሳዎች፣ ያዕቆብ ለንፍታሌም የሰጠው በረከቶች በአሪት ዘፍጥረት ፵፱፡፳፩ ውስጥ ተመዝግበዋል። ሙሴ ለጎሳው የሰጠው በረከት በአሪት ዘዳግም ፴፫፡፳፩ ውስጥ ተመዝግቧል።

ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ። *ደግምም መርከብ፣ ቀስተ ዳመና፣ የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ፣ ገብርኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የላሜሕ ልጅ እና ከአዳም ጀምሮ አስረኛው የአባቶች አለቃ (ዘፍጥ. ፭፡፳፱–፴፪)። ስለክርስቶስ መሰከረ እናም ለኃጢያተኛ ትውልዶች ንስሀ መግባትን ሰበከ። ህዝቡ መልእክቱን ሲያስወግዱ፣ እግዚአብሔር ምድር ክፉዎችን ለማጥፋት በምትጥለቀለቅበት ጊዜ ቤተሰቡን እና የምድር ሁሉ እንስሳት እንዲኖሩበት መርከብ እንዲገነባ አዘዘው (ዘፍጥ. ፮፡፲፫–፳፪፣ ሙሴ ፰፡፲፯–፴)። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ኖኅ መላእኩ ገብርኤል እንደሆነ እና የደህንነትን ቁልፎች በመያዝ ከአዳም ተከታይ እንደሆነ አስተማረ።

እርሱ እና ልጆቹ ያፌት፣ ሴም፣ እና ሀም፣ እናም ባለቤቶቻቸው በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሰረት መርከብን ሲገነቡ ድነው ነበር፣ ዘፍጥ. ፮–፰ (ዕብ. ፲፩፡፯፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፳)። ጌታ ከሔኖክ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ከኖህ ጋር አደሰ፣ ዘፍጥ. ፱፡፩–፲፯ (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፱፡፲፩፣ ፳፩–፳፩፣ ሙሴ ፯፡፴፱–፵፪)።

ኖኅ በአስር አመቱ ወደ ክህነት ስልጣን በማቱሳላ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፵፪።

ሰዎች እርሱን ለመግደልም ፈለጉ፣ ነገር ግን የጌታ ሀይልም አዳነው፣ ሙሴ ፰፡፲፰። የጻድቅ ሰባኪ ሆነ እናም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አስተማረ፣ ሙሴ ፰፡፲፱፣ ፳፫–፳፬ (፪ ጴጥ. ፪፡፭)።

ኖኅ፣ የዜኒፍ ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የነበረ ኃጢያተኛ ንጉስ። በኔፊ ምድር ውስጥ ኔፋውያንን መራ።

ኖኅ ብዙ ኃጢያቶችን ሰራ፣ ሞዛያ ፲፩፡፭–፲፭። ነቢዩ አቢናዲ እንዲገደል አዘዘ፣ ሞዛያ ፲፫፡፭ (ሞዛያ ፲፯፡፭፣ ፭–፰)። ኖኅ በእሳት ሞተ፣ ሞዛያ ፲፱፡፳።

አህዛቦች

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙበት፣ *አህዛብ* የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። አንዳንድ ጊዜ ይህም የእስራኤል ዘር ያልሆኑ ህዝቦችን፣ አንዳንድ ጊዜ የአይሁዳ ዘር ያልሆኑ ህዝቦችን፣ እናም ምንም እንኳን በመካከላቸው የእስራኤል ደም ቢኖርም፣ አንዳንድ ጊዜ ወንጌሉ የሌላቸው ሀገሮች ንም ይጠቁማል። የኋለኛው የቃል ጥቅም በመፅሐፈ ሞርሞንና በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የሚጠቀሙበት ትርጉም ነው።

እስራኤላውያን እስራኤላውያን ያልሆኑትን አያገቡም (አህዛብ)፣ ዘዳግ. ፯፡፩–፫። ጌታ ለአሕዛብም ብርሃን ለመሆን ይመጣል፣ ኢሳ. ፵፪፡፮።

ጴጥሮስ ወንጌሉን ወደ አህዛብ እንዲወስድ ታዘዘ፣ የሐዋ. ፲፡፱–፴፭። እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ንስሐን ሰጣቸው፣ የሐዋ. ፲፩፡፲፰። አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን በአንድ ቤተክርስቲያን ተጠምቀናልና፣ ፩ ቆሮ. ፲፪፡፲፫። በወንጌል አሕዛብ አብረው በክርስቶስ ወራሾች መሆን ይገባቸውል፣ ኤፌ. ፫፡፮።

መፅሐፈ ሞርሞን የተጻፈው በአህዛብ ነው፣ የመፅሐፈ ሞርሞን ርዕስ ገፅ (ሞር. ፫፡፲፯)። ከአህዛብ መካከል አንድ ሰው በብዙ ውኃዎች ላይ ሄደ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፲፪። ሌሎች መፅሀፎች ከአህዛብ መጡ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴፱። የወንጌል ሙሉነት ወደ አህዛብ ይመጣል፣ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፫ (፫ ኔፊ ፲፮፡፮፣ ት. እና ቃ. ፳፡፱)። ይህ ምድር ለአህዛብ የነፃነት ምድር ይሆናል፣ ፪ ኔፊ ፲፡፲፩። አህዛብ ከወይራ ዛፍ ጋር ይመሳሰላል፣ ያዕቆ. ፭።

ወንጌሉ በአህዛብ ጊዜ ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳፰ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯)። ቃል እስከ ምድር ዳርቻ፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ፣ እና ከዚያም ወደ አይሁድም ይዞራሉ፣ ት. እና ቃ. ፶፡፳–፲። ሰባዎቹ ለአህዛብ በሙሉ ልዩ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭። መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ከዚያም ወደ አይሁዶች፣ ሁሉንም ሀገሮች እንዲጠሯቸው የቤተክርስቲያኔን ሽማግሌዎች ላኩ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፳።

አለማመን። *ደግምም እምነት፣ ማመን ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር እና በወንጌሉ እምነት ማጣት።

በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም፣ ማቴ. ፲፫፡፶፰። በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም፣ ማቴ. ፲፯፡፲፱–፳፩። አለማመኔን እርዳው፣ ማር. ፱፡፳፫–፳፬። ኢየሱስ ተነሥቶም ያዩትን ስላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ፣ ማር. ፲፯፡፲፬። የማያምኑ ቢኖሩ አለ

ማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራ ልን፣ ሮሜ ፫፡፫።

አንድ አገር እምነት በማጣት ከሚመነምንና ከሚ ሞት አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል፣ ፮ ኔፊ ፱፡፲፫። የሚከዱበት ቀን ከመጣ፣ እንዲበተኑ እና እንዲጠፉ ያደርጋል፣ ፪ ኔፊ ፭፡፲–፲፩ (ት. እና ቃ. ፫፡፲፰)። ባለማመናቸው የእግዚአብሔርን ቃል ሊረዱት አል ቻሉም ነበር፣ ሞዛያ ፳፯፡፩–፭። ስለማያምኑ እን ደዚህ የሆነ ታላቅ ተአምራት ላሳያቸው አልቻል ኩም፣ ፫ ኔፊ ፲፱፡፴፭።

አዕምሮአችሁ ባለማመን ምክንያት ጨልሞባችሁ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፴፩–፴፰።

አለማዊነት። *ደግሞም ሀብቶች፣ ከንቱ፣ ከንቱነት፣ ኩራት፣ ገንዘብ ተመልከቱ*

መንፈሳዊ ነገሮችን በመተው ለምድራዊ ሀብ ቶች እና ለንብረቶች ያለ ጻድቅ ያልሆነ ፍላጎት እና ጥረት።

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐ ድል ምን ይጠቅመዋል፣ ማቴ. ፲፮፡፳፮።

ልባቸውን በዓለም ከንቱ ነገሮች ላይ ያሳረፉ፣ አልማ ፬፡፰ (አልማ ፴፭፡፳፯)።

የዚህን አለም ነገሮች ወደጎን ትተዋያለሽ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፲። ሰዎች ልባቸውን የአለም ነገ ሮች ላይ ያደርጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፴፭።

አለም። *ደግሞም ምድር፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ባቢሎን ተመልከቱ*

ምድር፣ ስጋዊ ሰው የሚፈተንበት ቦታ። በም ሳሌም፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የማያከብሩ ሰዎች።

ምድራዊ ህይወት፣ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለ ባችሁ፣ ዮሐ. ፲፮፡፴፫።

እስከሞትም አትፍሩ፣ በዚህ አለም ደስታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፴፯።

ትእዛዛትን የማያከብሩ ሰዎች፣ ዓለሙን ስለ ክፉ ታቸው እቀጣለሁ፣ ኢሳ. ፲፫፡፲፩ (፪ ኔፊ ፳፫፡፲፩)።

ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፰–፲፱።

ትልቁና ሰፊው ህንፃ የዓለም ኩራት ነው፣ ፮ ኔፊ ፲፩፡፴፯።

አለም በሃጢያት እየበሰለ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፮። ከአለም ነገሮች ራስህን ንጹህ እና ነውር የሌለበት አድርግ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፱። ታማኝ የሆነው እና የሚጸናውም አለምን ያሸንፋል፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፯። በአለም አይነት ኑሮ መኖር አይገባችሁም፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፲፫።

የአለም መጨረሻ፣ አዲስ አዲስ ምድር እፈጥራ ለሁ፣ የቀደሙትም አይታሰቡም፣ ኢሳ. ፳፭፡፲፯ (ራዕ. ፳፩፡፩፣ ኢ.አ. ፩፡፲)።

እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፣ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፣ ማቴ. ፲፫፡፴፣ ፴፱ (ሚል. ፬፡፩፣ ያዕቆ. ፮፡፣ ፫)።

የወይኑን ስፍራዬን በእሳት እንዲቃጠል አደርገ ዋለሁ፣ ያዕቆ. ፭፡፫–፮ (ት. እና ቃ. ፰፬፡፰፫–፰፬)።

ጌታ ሰይጣንን እና ስራዎቹን በአለም መጨ ረሻ ያጠፋል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፫። ምድር ብትሞ ትም፣ እንደገናም ህይወት ይሰጣታል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፭–፳፮።

ጌታም ለሔኖክ እስከ አለም መጨረሻ ድረስ አሳ የው፣ ሙሴ ፯፡፳፯።

አለት። *ደግሞም ራዕይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወንጌል ተመልከቱ*

በምሳሌ፣ ጠንካራ መሰረት እና መደገፊያ የሆኑት ኢየሱስ ክርስቶስ እና ወንጌሉ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፬፣ ፴፫፡፲፪–፲፫)። አለት ደግሞም እግዚአብሔር ወን ጌሉን ለሰው የሚያሳውቅበት ራዕይ መሆንም ይች ላል (ማቴ. ፲፮፡፲፭–፲፰)።

እርሱ አምላክ ነው፣ ሥራውም ፍጹም ነው፣ ዘዳግ. ፴፪፡፬። እግዚአብሔር ዓለቴ ነው፣ በእር ሱም እታመናለሁ፣ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፪–፫። እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈነቀለ፣ ዳን. ፪፡፴፬–፴፭።

በዓለት ላይም ተመሰርቷል፣ ማቴ. ፯፡፳፭ (፫ ኔፊ ፲፬፡፳፭)። ኢየሱስ ክርስቶስ የተናቀው ድን ጋይ ነው፣ የሐዋ. ፬፡፲–፲፩። ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፩–፬ (ዘፀአ. ፲፯፡፮)።

በአለት ላይ የሰራ እውነትን ይቀበላል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፰። አይሁዶች የሚገነቡበት አለት [ክርስ ቶስን] አይቀበሉም፣ ያዕቆ. ፬፡፲፭–፲፯። በቤዛነት ዓለታችን ላይ ነው መሰረታችንን መገንባት ያለ ብን፣ ሔሊ. ፭፡፲፪። በክርስቶስ ትምህርት የሚገነባ በአለቱ ላይ ይገነባል እናም የጥፋት ውሀው ሲመጣ አይወድቅም፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፴፱–፴፣ (ማቴ. ፯፡፳፬–፳፯፣ ፫ ኔፊ ፲፳፡፲፪–፲፫)። ጠቢብ ሰው ቤቱን በአ ለት ላይ ሰራ፣ ፫ ኔፊ ፲፬፡፳፬።

በእኔ ዐለት ላይ ከተገነባችሁ ሊቋቋሟችሁ አይች ሉም፣ ት. እና ቃ. ፯፡፴፭። በዚህ አለት ላይ የተመ ሰረተም አይወድቅም፣ ት. እና ቃ. ፹፡፴፭።

እኔ የፅዮን ንጉስ፣ የሰማይ ዓለት፣ መሲሕ ነኝ፣ ሙሴ ፯፡፹፫።

አሉባልታ። *ደግሞም ክፉ መናገር፣ ወሬ ተመልከቱ*

ከእዚያ ሰው ፍቃድ ሳይኖር ስለ ሌላ ሰው የግለ ሰብ ተጨባጭ ነገሮችን ወይም መረጃዎችን መካ ፈል።

ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ መልስ ይሰጡበታል፣ ማቴ. ፲፪፡፴፮። ቅዱሳን የማይገባ

ውንም እየተናገሩ፣ ለፍላፊዎችና በነገር ጣልቃ ገቢ ዎች እንዳይሆኑ ተገስጸዋል፣ ፩ ጢሞ. ፭፡፣ ፲፩–፲፡፡

በባልጀራህ ላይ እርኩሰትን አትናገር፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፣ ፳፯፡፡ በንግግርህ በሙሉ ወንድ ሞችህን አጠናክር፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፣ ፲፡

አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ። *ደግሞም ሽማግሌው አልማ፤ አሙሌቅ፤ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የኔፋውያን ህዝቦች የመጀመሪያ ዋና ዳኛ እና ነቢይ። በወጣትነቱ ቤተ ክርስትያኗን ለማጥፋት ፈለገ (ሞዛያ ፳፯፡፣ ፳–፲)። ነገር ግን፣ መላእክት ተገለጸለት እና ወደ ወንጌሉም ተቀየረ (ሞዛያ ፳፯፡፣ ፳–፳፱፤ አልማ ፴፯፡፣ ፯–፳፯)። በኋላም የዋና ዳኛ ሀላፊነቱን ህዝቦችን ለማስተማር ዘንድ ተወው (አልማ ፩፡፲፩–፳)።

መፅሐፈ አልማ፣ የነብያት አልማ፣ የአልማ ልጅ፣ እና የእርሱም ልጅ ሔለማን ፅሁፎች በእጥ ረት ተፅፎበት ያለ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የተ ለየ መፅሐፍ። በመፅሐፉ ውስጥ የሚገለጹት ድርጊ ቶች የደረሱት በግምት ከ ፣፲፩ እስከ ፵፪ ም.ዓ. ነበር። መፅሀፉ ፳፫ ምዕራፎች አሉት። ምዕራፍ ፩–፬ የኔሆር እና የአምሊካይ ተከታዮች በኔፋውያን ላይ ያመጹ በትን ይገልጻሉ። የዚህ ውጤት ጦርነት በኔፋው ያን ታሪክ ውስጥ ከነበሩት በላይ የሚያጠፋ ነበር። ምዕራፍ ፭–፲፯ የአልማን የመጀመሪያ የሚስዮን ጉዞዎች፣ በተጨማሪም የጥሩው እረኛ ስብከቱን (አልማ ፭) እና ከአሙሌቅ ጋር በአሞኒያሀ ውስጥ የሰበከውን ፅሁፍ ይዘዋል። ምዕራፍ ፲፯–፳፯ የሞዛያ ወንድ ልጆችን እና በላማናውያን መካከል ስላደረ ጉት አገልግሎት ፅሑፍ ይዘዋል። ምዕራፍ ፳፰–፴፪ የአልማ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የነበሩትን አንዳ ንድ ስብከቶች ይዘዋል። በምዕራፍ ፴፪ ውስጥ አልማ ቃልን ከዘር ጋር አነጻጸረ፣ በምዕራፍ ፴፯ ውስጥ ለልጁ ሔለማን የቅያሬ ታሪኩን ነገረው። ምዕራፍ ፴፱–፴፪ አልማ በስነምግባር መተላለፍ ተካፋይ ለነ በረው ለልጁ ቆሪያንተን የሰጠውን ምክር ይመዘግ ባሉ፣ ይህ አስፈላጊ ስብከት ፍትህን፣ ምህረትን፣ ትንሳኤን፣ እና የኃጢያት ክፍያን ይገልጻል። ምዕ ራፍ ፴፭–፴፫ የዛ ጊዜ የኔፋውያን ጦርነቶችን እና በሀጋዝ ዘመን ስደቶችን ይገልጻሉ። እንደ ሻምበል ሞሮኒ፣ ቴአንከም፣ እና ሊሀይ አይነት ታላቅ መሪ ዎች በብርቱ እና ጊዜአዊ ስራዎቻቸው ኔፋውያንን ለመጠበቅ ረዱ።

አልሳዕ

የሰሜን እስራኤል መንግስት የብሉይ ኪዳን ነቢይ እና የሀገሯ የተለያዩ ንጉሶች የታመነ አማካሪ።

ኤልሳዕ አለቃው ኤልያስ የታወቀበት የሚን በለበል ጉጉት ሳይኖረው፣ የረጋና አፍቃሪ ጸባይ የነበረው ነበር። የእርሱ የሚጠቀሱት ታምራቶቹ (፪ ነገሥ. ፪–፭፣ ፰) በኤልያስ ምትክ ነቢይ ሲሆን (፪ ነገሥ. ፪፡፣ ፱–፲፪) በእውነትም የኤልያስን ሀይል እንደተቀበለ የሚመሰክሩ ነበሩ። ለምሳሌ፣ የሚ መር ምንጭ ውሀን ፈወሰ፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሀ ዎችን ከፋፈለ፣ የባልቴት ዘይትን አባዛ፣ ወንድ ልጅን ከሞት አስነሳ፣ ሰውን ከለምጽ ፈወሰ፣ የብ ረት ምሳር በውሀ ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገ፣ እናም ሶሪያውያኖቹን አይነ ስውር አደረጋቸው (፪ ነገሥ. ፪–፮)። በኢዩራም፣ በኢዩ፣ በኢዮአካዝ፣ እና በኢዮአስም ንግስና ጊዜ ከሀምሳ አመት በላይ አገ ለገለ።

የኤልያስን መጐናጸፊያ ተቀበለ፣ ፪ ነገሥ. ፪፡፣ ፲፫። የባልቴት ዘይትን አባዛ፣ ፪ ነገሥ. ፬፡ ፩–፯። የሱነማይቱን ወንድ ልጅ ከሞት አስነሳ፣ ፪ ነገሥ. ፬፡ ፣፴–፴፯። ሶሪያውያኑን ናዕማንን ፈወሰ፣ ፪ ነገሥ. ፭፡ ፩–፲፬። የሶሪያውያን ወታደ ሮች አይነ ስውር አደረጋቸው፣ እና የአገልጋዩን አይኖች ከፈተ፣ ፪ ነገሥ. ፮፡ ፳–፳፫፡፡

አልዓዛር። *ደግሞም ማርታ፤ የቢታንያ ማርያምን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የማርታና የማርያም ወን ድም። ኢየሱስ ከሞት አስነሳው (ዮሐ. ፲፩፡ ፩–፴፬፣ ፲፪፡ ፩–፪፣ ፱–፲፩)። ይህም ኢየሱስ በምሳሌ ባስተ ማረው ውስጥ የነበረው ለማኙ አልዓዛር አይደለም (ሉቃ. ፲፮፡ ፲፱–፴፩)።

አልፋ እና ኦሜጋ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

አልፋ የግሪክ ፊደል የመጀመሪያ ፊደል ነው፤ ኦሜጋ የመጨረሻው ነው። እነዚህ ለኢየሱስ ክር ስቶስ የተሰጡ ስሞች እና ክርስቶስ መጀመሪያ እና መጨረሻ እንደሆነ እንዲያሳዩ የሚጠቀሙባቸው ምልክቶች ናቸው (ራዕ. ፩፡ ፣፳፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፩)።

አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት። *ደግሞም መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት፤ ማምለክ ተመልከቱ*

ከእግዚአብሔር ከተቀበልነው በረከቶች የምን ሰጠው ምስጋና። ምስጋናን መግለፅ እግዚአብሔ ርን ያስደስታል፣ እናም እውነተኛ ማምለክ ምስጋና በተጨማሪ አለው። ለጌታ ለሁሉም ነገሮች ምስጋና መስጠት ይገባናል።

እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፣ መዝ. ፣፶፪፡ ፩። በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፣ መዝ. ፣፺፭፡ ፩–፪። አመስግኑት፡ ስሙንም ባርኩ፣ መዝ. ፻።

ማመስገንን አትተው፣ ኤፌ. ፭፡ ፲፭–፲፯። የም ታመሰግኑም ሁኑ፣ ቄላ. ፫፡ ፣፲፭። በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም

ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፣ ራዕ. ፯፡፲፪።

በረከትና ክብር ምስጋናም ውዳሴም ለአምላካችን ይሁን፣ ሞዛያ ፪፡፲፱–፳፩። በየቀኑ በምስጋና ኑሩ፣ **አልማ** ፴፩፡፴፰። ጠዋት ከመኝታህ በምት ነቃበት ጊዜ ልብህ ሁሉ እግዚአብሔርን በማመስገን ይሞላ፣ **አልማ** ፴፯፡፴፯።

ሁሉንም ነገሮች በጸሎትና በምስጋና አድርጉ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፯። ምስጋናዎችን ለእግዚአብሔር መስጠት አለባችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፪። ምስጋና በመስጠት እነዚህን ነገሮች አድርጉ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፭–፳፩። ከጌታ እጅ ለሁሉም ነገሮች ምስጋና ባለው ልብ በረከትን ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፯። ሁሉንም ነገሮች በምስጋና የሚቀበል ባለ ክብር ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፫፳፡፲፱። በሁሉም ነገሮች ምስጋናዎች ስጡ፣ ት. እና ቃ. ፶፳፡፩ (፩ ተሰ. ፭፡፲፳)። ጌታን በምስጋና ጸሎትና በምስጋና አምልኩ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፳፯።

አመራር። ቀዳሚ አመራር *ተመልከቱ*

አመጽ። *ደግሞም ኃጢያት፤ ማጉረምረም፤ ክህደት፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

በእርሱ የተመረጡትን መሪዎች ለመከተል እምቢ በማለት እና ትእዛዛቱን በፈቃደኝነት ባለ ማክበር የጌታን ትእዛዝ መጣስ ወይም እርሱን መቃወም።

በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ፣ ዘኁል. ፲፬፡፱። ክፉ ሰው ዓመፃን ብቻ ይሻል፣ ምሳ. ፲፯፡፲፩። ለዓመፀኞች ልጆች ወዮላቸው፣ ኢሳ. ፴፡፩።

ጌታም በእርሱ ላይ ያመፀውንና በኃጢያት የሞተውን አያድንም፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፯። አምሊኪውያን በእግዚአብሔር ላይ አመጹ፣ **አልማ** ፫፡፲፳–፲፱።

አመጸኞች በብዙ ሐዘን ይወጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፫። የጌታ ቁጣ በአማጸኞቹ ላይ ነዷል፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፩ (ት. እና ቃ. ፳፫፡፩–፯)።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀ፣ **ሙሴ** ፬፡፫።

አሙሌቅ። *ደግሞም አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የአልማ ልጅ አልማ ሚስዮን የጉዞ ጓደኛ።

በመላእክት ተጎብኝቶ ነበር፣ **አልማ** ፰፡፳፣ ፲፡፯። አልማን በቤቱ ተቀበለ፣ **አልማ** ፰፡፳፩–፳፯። ለአሞኒያሃ ህዝቦች በሀይል ሰበከ፣ **አልማ** ፰፡፳፱–፴፪፣ ፲፡፩–፲፩። የኔፊ፣ የሌሂ፣ እና የም ናሴ ተወላጅ ነበር፣ **አልማ** ፲፡፪–፫። ስለእውነት መሰከረ፣ **አልማ** ፲፡፬–፲፩። ህዝቦችን ንስሀ እን ዲገቡ ጠራቸው እና ተወገደ፣ **አልማ** ፲፡፲፪–፴፪። ከዚዝሮም ጋር ተከራከረ፣ **አልማ** ፲፩፡፳–፳፮። ከሞት ስለመነሳት፣ ስለፍርድ፣ እና ዳግሞ መመለስ አስተማረ፣ **አልማ** ፲፩፡፳፯–፳፭። የሚያምኑትን ሰማእትነትን ለማቆም ፈለገ፣ **አልማ** ፲፬፡፱–፲። ከአልማ ጋር ታስሮ ነበር፣ **አልማ** ፲፬፡፲፬–፳፫። በወህኒ ቤቱ የታሰረበትን ሲባጎ በእምነት በጠሰ፣ **አልማ** ፲፬፡፳፩–፳፱። ስለኀጢያት ክፍያ፣ ስለም ህረት፣ እና ስለፍትህ መሰከረ፣ **አልማ** ፴፩፡፳–፲፯። ስለጸሎት አስተማረ፣ **አልማ** ፴፩፡፲፯–፳፳። ንስሀ መግባታቸውን እንዳያዘገዩ ሰዎችን አበረታታ፣ **አልማ** ፴፩፡፴–፴፭። የአልማ እና የአሙሌቅ እምነት የወህኒ ቤቱ ግድግዳ እንዲወድቅ አደረጉ፣ **ኤተር** ፲፪፡፲፫።

አማላጅ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር አማላጃችን ነው (ሞሮኒ ፯፡፳፳) እና ከእርሱም ጋር ምክንያታችንን ይለምንልናል፡ የሚማለድ ወይም መካከለኛ። ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የሚማለድ ነበር። የእርሱ የኃጢያት ክፍያ ሰዎች ለኃጢያታቸው ንስሀ ለመግባት እና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ የሚቻልበት መንገድ ሰራ።

በኢየሱስ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፣ **ዮሐ.** ፲፬፡፮። በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፭። ክርስቶስ በኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን በዚያ ልክ እጅግ የሚሻል ነው፣ ዕብ. ፰፡፮ (ዕብ. ፱፡፲፭፣ ፲፪፡፳፬፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፲፱)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ አማላጃችን ነው፣ ፩ **ዮሐ.** ፪፡፩ (ት. እና ቃ. ፻፲፡፱)።

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሁሉ ይማለዳል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፱ (ዕብ. ፯፡፳፭)። ቅዱሱ መሲህ ለሰው ልጆች ሁሉ ያማልዳል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፱ (ኢሳ. ፶፫፡፲፪፣ ሞዛያ ፲፭፡፲፪)። በታላቁ አማላጅ ተመኩ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯–፳፳። ኢየሱስ በሞት ላይ ድልን አገኘ፣ ለሰው ልጆች እንዲማልድ ኃይልን ሰጠው፣ ሞዛያ ፲፭፡፳።

ከአብ ዘንድ አማላጃችሁ ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፭። ኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያታችሁን ይማጸንላቸኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፫–፭። የአዲስ ኪዳን አማላጅ በሆነው ኢየሱስ ፍጹም ሆነናል፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፳፱።

አማሌቃዊ (ብሉይ ኪዳን)

በፋራን በሀር ውስጥ በአራባ እና በሜድትሬኒያን መካከል የኖሩ የአረብ ግንድ። ከእብራውያን ጋር ከመሴ ጀምሮ (ዘፀአ. ፲፯፡፰) እስከ ሳኦል እና ዳዊት ዘምን (፩ ሳሙ. ፲፭፡፣ ፳፯፡፰፣ ፴፣ ፪ ሳሙ. ፰፡፲፩–፲፪) ድረስ ሁልግዜም በጦርነት ይዋጉ ነበር።

አማሌቅያውያን (መፅሐፈ ሞርሞን)

ላማናውያን ከኔፋውያን ጋር እንዲዋጉ የመሩ

ሀይማኖትን የከዱ ኔፋውያን (አልማ ፳፭–፳፱፤ ፴፫)።

አማኑኤል። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ከኢየሱስ ክርስቶስ ስሞች አንዱ። ይህም “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር” የሚል ትርጉም ካለው የዕብራውያን ቃል የመጣ ነው።

አማኑኤል እንደ እግዚአብሔር ቤዛነት ምልክት የተሰጠ ስም-ርዕስ ነው (ኢሳ. ፯፡፲፬)። ኢሳይያስ የጠቀሰው አማኑኤል እንደ ኢየሱስ በስጋ መወለድ ትንቢት በማቴዎስ ተጠቁሟል (ማቴ. ፩፡፲፰–፳፫)። ስሙም በኋለኛው ቀን ቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ታይቷል (፪ ኔፊ ፲፯፡፲፬፣ ፲፰፡፰፣ ት. እና ቃ. ፲፳፰፡፳፪)።

አሜን። *ደግምም ጸሎት ተመልከቱ*

“ይህም ይሁን” ወይም “እንዲህም ነው” ማለት ነው። አሜን የሚባለው ልባዊ ወይም የተከበረ ተቀባይነት እና ስምምነትን (ዘዳግ. ፳፯፡፲፬–፳፮) ወይም እውነትነት (፩ ነገሥ. ፩፡ ፴፯) ለማሳየት ነው። ዛሬ በጸሎቶች፣ በምስክርነቶች፣ እና ንግግሮች መጨራሻ ላይ፣ ጸሎትን ወይም ምልዕክትን የሰሙት ተቀባይነት እና ስምምነትን ለማሳየት በደንብ የሚሰማ አሜን ይላሉ።

በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች፣ ሰው መሃላ ሲገባ አሜን ማለት ነበረበት (፩ ዜና ፲፮፡፣ ፴፭–፴፮፣ ነህ. ፭፡፲፫–፲፫፣ ፰፡፪–፯)። ክርስቶስ “አሜን የሆ ነው፡ የታመነውና እውነተኛው ምስክር” ተብሎ ተጠርቷል (ራዕ. ፫፡፲፬)። በነቢያት ትምህርት ቤት አሜንም ደግሞ እንደ ቃል ኪዳን ምልክት አገልግሏል (ት. እና ቃ. ፹፰፡፪፣ ፪፴፫–፪፴፭)።

አምሊካያህ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በላማናውያን መካከል ሀይል ያገኙ እና በኔፋውያን ላይ የመሩአቸው የኔፋውያን ከዳተኞች (አልማ ፴፯–፴፩)።

አምሊካይ፣ አምሊካውያን

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በዳኛዎች ዘመነ መንግስት ንጉስ ለመሆን ፍላጎት የነበራቸውን ኔፋውያንን ይመራ የነበረ ሰው። አምሊካውያን ተብለው የተጠሩት እነዚህ ኔፋውያን በእግዚአብሔር ላይ በግልፅ አመጹ፣ ለዚህም ተረግመው ነበር (አልማ ፪–፫)።

አምላክነት። *ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ፣ ከፍተኛነት፣ የዘለዓለም ህይወት ተመልከቱ*

አምልኮ። *ማምለክ ተመልከቱ*

አምስቱ መጻህፍት። *ደግምም ሙሴ፣ ብሉይ ኪዳን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘዳግም፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘፍጥረት ተመልከቱ*

ለብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ አምስት መፅሐፎች፣ ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘዳግም፣ የተሰጡ ስሞች። አይሁዶች እነዚህን መፅሐፎች ቶራ ወይም የእስራኤል ህግ ብለው ይጠሯቸዋል። በሙሴ ተፅፈው ነበር (፩ ኔፊ ፭፡፣–፣፩)።

አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ። *ደግምም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ አንቲ-ኔፊ-ሌሂ፣ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞዛያ ወንድ ልጅ። አሞን ትጋታዊ ጥረቱ ብዙ መንፈሶችን ወደ ክርስቶስ ለመቀየር እንደረዳ ሚስዮን አገለገለ።

ቤተክርስትያኗን ለማጥፋት የፈለገ አረመኔ ነበር፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡–፣፣ ፴፱። ለእርሱ እና ለጓደኞቹ መላእክት ተገለጠላቸው፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፣፩። ንስሀ ገባ እና የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ጀመረ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፴፪–፳፰፡፡። በንጉስነት ለመመደብ እንቢ አለ እና በምትኩ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ወደ ላማናውያን ምድር ሄደ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፣–፣፩። ለመመሪያ ጾመ እና ጸለየ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፡–፣፩። ታስሮ ወደ ንጉስ ላሞኒህ ተወሰዶ ነበር፣ **አልማ** ፣፣፯፡፳–፳፩። የላሞኒህን መንጋዎች አዳነ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፳፩–፴፴። ለላሞኒህ ሰበከ፣ **አልማ** ፣፣፡፡፡–፣፣፩፡፣፣፫። እግዚአብሔርን አመሰገነ እና በደስታ ተሸነፈ፣ **አልማ** ፣፣፩፡፣፣፩። በእርሱ የተቀየሩት በምንም አልከዱም፣ **አልማ** ፳፫፡፣፯። ሺዎችን ወደ እውነት ለማምጣት በእግዚአብሔር እጆች መሳሪያ ስለሆነ ተደሰተ፣ **አልማ** ፳፯፣፡–፡ (አልማ ፳፯)። የአንቲ-ኔፊ-ሌሂ ህዝቦችን መራ፣ **አልማ** ፳፯። ከአልማ ጋር በመገና ኘቱ ታላቅ ደስታ ተሰማው፣ **አልማ** ፳፯፡፣፣፣–፣፡፡።

አሞን፣ የዛራሔምላ ትውልድ። *ደግምም ሊምሂ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ከሌሂ-ኔፊ ምድር ወደ ዛራሔምላ ጉዞን የመራ ጠንካራ እና ሀያል ሰው (ሞዛያ ፯፡ ፩–፣፣)። የጥንት ፅሁፎችን አሳዩት እና ባላራዕይ ምን እንደሆነ ገለጸ (ሞዛያ ፡፡ ፣–፣፡)። በኋላም ንጉስ ሊምሒን እና ህዝቦቹን ከላማናውያን ነጻ ለማድረግ እና ወደ ዛራሔምላ መልሶ ለማምጣት ረዳ (ሞዛያ ፳፪)።

አሞፅ

በግምት ከ፯፻፣፣፪ እስከ ፯፻፣፣ ም.ዓ. በአይሁድ ንጉስ ኡዝያ እና በእስራኤል ንጉስ ኢዮርብዓም ዘመናት የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ።

ትንቢተ አሞፅ፣ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ የአሞፅ ትንቢያት እስራኤልን እና ጎረቤቷ አገሮችን ወደ ጽድቅ እንዲመለሱ አስጠንቅቀዋል።

ምዕራፍ ፩–፮ እስራኤልን እና ጎረቤቷ አገሮችን ንስሀ እንዲገቡ ይጠራሉ። ምዕራፍ ፮ ጌታ ምስጢሮቹን ለነብያቱ እንደሚገልፅ እና በመተላለፍ ምክንያት እስራኤል በጠላት እንደምትደመሰስ ያስረዳል። ምዕራፍ ፯–፱ አሶር ከመውረሯ ከብዙ አመቶች በፊት ስለእስራኤል መውደቅ ተነበየ። ምዕራፍ ፱ እስራኤል ወደምድሯ ዳግማ እንደምትመለስ ተነበየ።

አሳ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይሁዳ ሶስተኛ ንጉስ። ቅዱሣት መጻህፍት “ልብ ግን በዘመኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ነበረ” ብለው ተፅፈዋል (፩ ነገሥ. ፲፭፡፲፬)። በዘመነ መንግስቱ ጦር ሰራዊትን በብቃት አዘጋጀ፣ የኢትዮጵያን ቀንበር ጣለ፣ የሀሰት ጣኦቶችን አስወጣ፣ እና ህዝቦች ያህዌህን ለመፈለግ ቃል ኪዳን እንዲገቡ ጋበዘ (፩ ነገሥ. ፲፭–፲፮፣ ፪ ዜና ፲፬–፲፮)። ነገር ግን፣ እግሮቹ ሲታመሙ፣ የጌታን እርዳታ አልፈለገም እና ሞተ (፩ ነገሥ. ፲፭፡፳፫–፳፱፣ ፪ ዜና ፲፮፡፲፪–፲፫)።

አሴር

ደግምም እስራኤል፤ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ባርያ የዘለፋ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፲–፲፣ ፴)፣ እና ሙሴ የአሴርን ትውልዶች ባረከ (ዘዳግ. ፴፫፡፳–፳፭)። እነዚህ ትውልዶች “ጽኑዓን ኃያላን ሰዎች” ተብለው ተጠርተው ነበር (፩ ዜና ፯፡፴)።

አስሩ ቃላት

ደግምም ሙሴ፤ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተመልከቱ

በነቢዩ ሙሴ በኩል የስነምግባር ጸባይን ለመቆጣጠር እግዚአብሔር የሰጣቸው አስር ቃላት።

በዕብራውያን ቋንቋ የእነዚህ ስም “አስር ቃላት” ነው። እነዚህም ቃል ኪዳን (ዘዳግ. ፬፡፲፫) ወይም ምስክር ተብለው ተጠርተዋል (ዘፀአ. ፳፭፡፳፭፤ ፴፪፡፲፭)። እግዚአብሔር አስሩን ቃላት ለሙሴ እና በእርሱም በኩል ለእስራኤል ሰጠ፣ በዘፀአ. ፲፱፡፱–፳፡፳፣ ፴፪፡፲፣ ፴፬፡፲–፲፱፣ ፴፩፡፩ ውስጥም ተገልጸዋል። ትእዛዛቱ የተቀረጹት በሁለት የድንጋይ ጽላት ላይ ነበር፣ እነዚህም በታቦት ውስጥ ተቀመጡ፤ ከዚህም ጀምሮ ታቦቱ የኪዳን ታቦት ተብለው ተጠርተዋል (ዘኁል. ፲፡፴፫)። ጌታ ከዘዳግ. ፮፡፬–፭ እና ከዘሌዋ. ፲፱፡፲፰ በመጥቀስ አስሩን ቃላት “በሁለቱ ትእዛዛት” አሳጥሮ በማጠቃለል ሰጥቷል (ማቴ. ፳፪፡፴፯–፴፱)።

አስሩ ቃላት በኋለኛው ቀን ራዕያት ውስጥ ደግመው ተሰጥተዋል (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአ. ፴፬፡፩–፪፣ ፲፬ [ተጨማሪ]፤ ሞሣያ ፲፪፡፴፪–፴፯፣ ፲፫፡፲፪–፳፬፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፰–፳፰፣ ፹፱፡፩–፲፫)።

አስሩ ጎሳዎች

እስራኤል ተመልከቱ

አስራት፣ አስራት መክፈል

ደግሞም በኩራት፤ ገንዘብ ተመልከቱ

በቤተክርስቲያን በኩል ለጌታ የሚሰጥ የሰው በአመት አንድ አስረኛ እድገት። የአስራት ገንዘቦች ቤተክርስቲያናትን እና ቤተመቅደሶችን ለመገንባት፣ የሚሰዮን ስራን ለመደገፍ፣ እና የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለመገንባት ይጠቀሙባቸዋል።

አብርሐም የንብረቱን ሁሉ አስራት ለመልከጼዴቅ ሰጠ፣ ዘፍጥ. ፲፡፡፲፰–፳ (ዕብ. ፯፡፩–፪፣ ፱፣ አልማ ፲፫፡፲፭)። የምድርም አሥራት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፣ ዘሌዋ. ፳፯፡፴–፴፡፡ ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ፣ ዘዳግ. ፲፡፡፳፪፣ ፳፫፡ የሁሉንም አሥራት አብዝተው አቀረቡ፣ ፪ ዜና ፴፩፡፭ ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላ ችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው፣ ሚል. ፫፡፰–፲፩ (፫ ኔፊ ፳፬፡፰–፲–፲፩)።

አስራትን የሚከፍልም በሚመጣበት ጊዜ አይ ቃጠልም፣ ት. እና ቃ. ፭፬፡፳፫ (ት. እና ቃ. ፻፲፭፡፫)። የጌታ ቤት በህዝቦቹ አስራት ይሰራ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፲፩–፲፪። ጌታ የአስራት ህግን ገለጸ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፱። አስራት በሽንጎ ይከፋፈላል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፡

አስቀድሞ መወሰን

ቀድሞ መመረጥ ተመልከቱ

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩

ደግሞም መግለጫ፤ ውድሩፍ፣ ውልፈርድ፤ ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ

በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች በመጨረሻ ገጾች ላይ የታተሙት፣ የአስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ የመጀመሪያ ክፍል መግለጫም ተብሎ ይታወቃል። የተሰጠውም በፕሬዘደንት ውልፈርድ ውድሩፍ ነበር እናም በጥቅምት ፯፣ ፲፰፻፶፯ (እ.አ.አ.) በአጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ ለቤተክርስቲያኗ አባላት ቀረበ። ከ፲፰፻፶፰ (እ.አ.አ.) ጀምሮ፣ የተለያዩ ህግጋት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ህገወጥ አደረጉት። ጌታ በራዕይ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ካላቆሙ በቅዱሳን ላይ ምን እንደ ሚደርስ ለውልፈርድ ውድሩፍ አሳየ። መግለጫው

ከአንድ ሚስት በላይ ማጋባት እንደቆመ ማስታወቂያ ሰጠ።

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪። *ደግምም* ኪምባል፣ ስፔንሰር ደብሊው፤ *ክህነት ተመልከቱ*

አሁን በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች በመጨረሻ ገጾች ላይ የታተሙት፣ ማን ክህነትን ለመያዝ እንደሚችል በሚመለከት የተሰጠ የትምህርት መረጃ። በሰኔ ፲፱፻፹፫ (እ.አ.አ.)፣ ጌታ ክህነት ለቤተክርስቲያና ብቁ አባላት በሙሉ እንዲሰጥ ለፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል ገለጸ። ይህም የቆዳ ቀለማቸውንም ይሁን ዘራቸውን ሳይመለከት ክህነትን ብቁ ለሆኑ ወንዶች ለመስጠት እና የቤተመቅደስ በረከቶችንም ብቁ ለሆኑ አባላት በሙሉ ለመስጠት የሚቻል አስደረገ። በመስከረም ፴፣ ፲፱፻፹፯ (እ.አ.አ.)፣ ይህ አዋጅ ለቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ጉባኤ ቀርቦ ነበር እናም ባንድ ድምፅ ተቀባይነት አገኘ።

አስቴር

ታላቅ እምነት የነበራት እና በመፅሐፈ አስቴር ውስጥ ዋና ባለታሪክ።

መፅሐፈ አስቴር፣ ህዝቦቿን ከጥፋት ለማዳን ንግስት አስቴር የነበራት ታላቅ ብርቱነትን የሚያሳይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ መፅሐፍ።

ምዕራፍ ፩–፪ የአይሁዳ ሴትና መርዶክዮስ የሚባለው የአይሁዳ ሰው በጉዲፈቻ ያሳድጋት የነበረችው ሴት ልጅ በውበቷ ምክንያት የፋርስ ንግስት እንድትሆን እንዴት እንደተመረጠች ይነግራሉ። *ምዕራፍ ፫* በንጉሱ ቤት ዋና አለቃ የነበረው ሀማን መርዶክዮስን እንደጠላና የአይሁዳ ህዝቦችን በሙሉ ለመግደል አዋጅ እንዳገኘ ይገልጻል። *ምዕራፍ ፬–፮* አስቴር፣ እራሷን በአደጋ ላይ በመጣል፣ ዜግነቷን ለንጉሱ እንዴት እንደገለጸችና የአዋጁን ለውጥ እንዳመጣች ይናገራሉ።

አስጸያፊ፣ አስከፊ፣ አሰቃቂ፣ ርኩሰት። *ደግምም ኃጢያት ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ለጻድቅ እና ንጹሁ ጽያፊ እና ጥላቻ የሚያመጣ።

ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አሰጸያፊ ነው፣ *ምሳ.* ፲፪፡፳፪።

ኩራት በጌታ ፊት የርኩሰት ነው፣ *ያዕቆ.* ፪፡፲፫–፳፪። ክፉዎች በራሳቸዉ እርኩሰት ሁኔታ ይመደባሉ፣ *ሞዛያ* ፫፡፳፭። ንጹህ አለመሆን ደም ከማፍሰስ ወይንም መንፈስ ቅዱስን ከመካድ በቀር ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ይበልጥ አስከፊ ነው፣ **አልማ** ፴፱፡፣–፴።

የጌታ ቁጣ በርኩሰታቸው ላይ ተቀጣጥሏልና፣ *ት. እና ቃ.* ፶፯፡፳፡።

አሶር

በብሉይ ኪዳን ዘመናት ውስጥ በሙሉ፣ ከተወዳዳሪዋ ባብሎን ጋር፣ ሶርያን እና ፍልስጥኤምን የገዛች የጥንት ግዛት። ምንም እንኳን አሶራውያን ከ፲፪ኛው ሺህ ም.ዓ. ግማሽ እስከ ፯ኛው ሺህ ም.ዓ. መጨረሻ ድረስ ታላቅ ሀይል የነበሩ ቢሆኑም፣ የረጋ የፖለቲካ ድርጅት ለመገንባት በምንም አልቻሉም ነበር። በፍርሀት፣ ጠላቶቻቸውን በእሳት እና በጎራዴ በመደምሰስ ወይም የጠላቶቻቸውን ህዝቦች ታላቅ ክፍልን ወደ ግዛቶቻቸው ሌላ ክፍሎች በመላክ ደካማ እንዲሆኑ በማድረግ ይገዙ ነበር። በአሶራውያን ተገዢነት ስር የነበሩት ህዝቦች ከመንግስት ጋር ሁልጊዜም ይታገሉ ነበር። (፪ ነገሥ. ፲፰–፲፱፣ ፪ ዜና ፴፪፣ ኢሳ. ፯፡፲፯–፳፣ ፲፣ ፲፱፣ ፴፯ ተመልከቱ።)

አርማጌዶን። *ደግምም ማጎግ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፣ ጎግ ተመልከቱ*

የአርማጌዶን ስም “የሚጎዶ ተራራ” የሚል ትርጉም ካለው ከእብራውያን *ሀር ሚጎዶ* መንጭ የመጣ ነው። የሚጎዶ ሸለቆ በኤስድራኤሎን ሜዳ ምስራቃዊ ክፍል ውስጥ፣ ከሰሜን ኢየሩሳሌም ሀምሳ ኪሎ ሜትር አልፎ ያለ ነው፣ እና በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች ብዙ በጣም ወሳኝ የሆኑ ጦርነቶች የነበረበት ቦታ ነው። በጌታ ዳግም ምፅዓት ቅርብ ጊዜ የሚመጣው ታላቅ እና የመጨረሻው ጦርነት የአርማጌዶን ጦርነት የሚባልበት ምክንያት በዚያ አካባቢ ስለሚጀምር ነው። (ሕዝ. ፴፱፡፲፩፣ ዘካ. ፲፪–፲፬፣ በልዩም ፲፪፡፲፩፣ ራዕ. ፲፮፡፲፬–፳፩።)

አሮናዊ ክህነት። *ደግምም* አሮን፣ የሙሴ ወንድም፤ *ክህነት*፤ *የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

አነስተኛው ክህነት (ዕብ. ፯፡፲፩–፲፪፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፣–፲፱)። ሀላፊነቶቹም ኤጲስ ቆጶስ፣ ካህን፣ አስተማሪ፣ ዲያቆን ናቸው (ት. እና ቃ. ፴፬፡፴፣ ፲፯፡፲፣ ፲፱–፲፭፣ ፴፯–፴፰)። በጥንት፣ በሙሴ ህግ በታች፣ ሊቀ ካህናት፣ ቄሶች፣ እና ሌዋውያኖች ነበሩ። የጥንት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ፣ ሙሴ እና ቅዱስ ክህነት ከእነርሱ ተወሰዱ እናም አነስተኛው ክህነት ቀጠለ። ለመቀደስ እና የመልከ ጼዴቅ ክህነትንና ስነስርዓቶቹን ለመቀበል እምቢ ብለው ነበር። (ት. እና ቃ. ፴፬፡፳፡፳፫–፳፮ ተመልከቱ።) የአሮናዊ ክህነት በጊዜአዊ እና በህግ እና ወንጌል ውጪአዊ ስርዓቶችን ያስተዳድራል (፩ ዜና ፳፫፡፳፯–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፳፡፳፮–፳፯፣ ፲፯፡፲፣ ፴)። የመልአክትን አገልግሎት፣ እና የንስሃ ወንጌልን እና የመጥመቅ ቁልፎችን ይዟል (ት. እና ቃ. ፲፫)። የአሮናዊ ክህነት በዚህ ዘመን ፍጻሜ ላይ በ፲፭ ግንቦት ፲፰፻፹፭ (እ.አ.አ.) ወደ ምድር ደግሞ ተመለሰ። መጥምቁ ዮሐንስ በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ አጠገብ ይህን

በጀሴፍ ስሚዝ እና በኦሊቨር ካውደሪ ላይ አረጋ ገጠ (ት. እና ቃ. ፲፫፣ ጀ.ስ.—ታ. ፩፡፳፰–፳፱)።

ለእርሱም ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይሆን ለታል፣ ዘኁል. ፳፭፡፲፫። የሌዊንም ልጆች ያጠ ራል፡ ያነጥራቸዋልም፣ ሚል. ፫፡፫ (፫ ኔፊ ፳፬፡፫)።

ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም፣ ዕብ. ፭፡፬። በሌዊ ክህነት ፍጹምነት አይመጣም፣ ዕብ. ፯፡፲፩።

የሌዊ ልጆች እንደገና መሰዋዕት ለጌታ እስኪያ ቀርቡ ድረስ ክህነት ከምድር ላይ ዳግመኛ በፍጹም አይወሰድም፣ ት. እና ቃ. ፲፫። ጀሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ በአሮናዊ ክህነት ተሹመው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፡ ፳። አነስተኛው ክህነት የመል አክትን አገልግሎት ቁልፍ ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯፲፮ (ት. እና ቃ. ፲፫)። በስም መልክ ጴጴቅ እና አሮናዊ የሚባሉ፣ ሁለት የክህነት ባለስልጣኖች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩። ሁለተኛው ክህነት አሮ ናዊ ክህነት ተብሎ ይጠራል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፫።

አሮን፣ የሙሴ ወንድም። *ደግሞም ሙሴ፤ አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሌዊ ነገር የእንበረምና የዮካብድ ወንድ ልጅ (ዘፀአ. ፮፡፲፯–፳)፤ የሙሴ ታላቅ ወንድም (ዘፀአ. ፯፡፯)።

የእስራኤል ልጆችን ከግብፅ ለማምጣት ሙሴን እንዲረዳ እና የእርሱ ቃል ተቀባይ እንዲሆን በጌታ ተመድቦ ነበር፣ ዘፀአ. ፬፡፲–፲፯፣ ፳፯–፴፩፣ ፭፡፩–፲፪፡፲፩። በሲና ተራራ ላይ፣ ሙሴ ስለአሮንና አራት ወንዶች ልጆቹ ወደ አሮናዊ ክህነት መመደብ መመ ሪያ ተቀበለ፣ ዘፀአ. ፳፰፡፩–፬። ህዝቦች ስለጠየቁት የወርቅ ጥጃ ሰራ፣ ዘፀአ. ፴፪፡፩–፮፣ ፳፭፣ ፴፬፣ ፴፭። በየ፳፫ኛ አመቱ በሆር ተራራ ላይ ሞተ፣ ዘኁል. ፳፡፳፫–፳፱ (ዘኁል. ፴፫፡፡ ፴፰–፴፱)።

ጌታ ክህነትን በአሮን እና በዘሩ ላይ አረጋገጠ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፲፰፣ ፳፯–፳፰፣ ፴። የክህነት ጥሪ ያቸውን የሚያጎሉ የሙሴ እና የአሮን ልጆች ይሆ ናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፴፫–፴፴።

አሮን፣ የሞዛያ ልጅ። *ደግሞም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞዛያ ወንድ ልጅ አሮን በሚስዮን ሲያገለግል ትጉህ ጥረቱ ብዙ ነፍሶችን ወደ ክርስቶስ ቀየር።

ቤተክርስትያኗን ለማጥፋት የፈለገ የማያምን ነበረ፣ ሞዛያ ፳፯፡፡ ፳–፲፣ ፴፩። ለእርሱና አብ ረውት ለነበሩት መላእክት ታያቸው፣ ሞዛያ ፳፯፡፲፩። ንስሀ ገባ እና የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ጀመረ፣ ሞዛያ ፳፯፡፴፪–፳፳፡ ፳። እንደ ንጉስ ለመመደብ እምቢ ብሎ እና ወደላማናው ያን ምድር የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ሄደ፣ አልማ ፲፯፡፮–፱። ለመመሪያ ጾመም ጸለየም፣ አልማ ፲፯፡ ፳–፲፩። የንጉስ ላሞኒህ አባትን አስ ተማረ፣ አልማ ፳፪፡፩–፳፯። ለዞራማውያን ለመ ስበክ ሄደ፣ አልማ ፴፩፡፮–፯።

አቡቃለምሲስ። *ደግሞም የዮሐንስ ራዕይ ተመልከቱ*

የአዲስ ኪዳን የመጨረሻው መፅሐፍ፣ የራ ዕይ መፅሐፍ፣ ማንኛውም ትርጉም ያለው ራዕይ ማለትም ሊሆን ይችላል፣ ከግሪክ ቃል “የተገለጸ” ወይም “የተገለጠ” ማለት ነው።

አቢናዲ። *ደግሞም ሰማዕት፣ ሰማዕትነት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፋውያን ነቢይ።

ንስሀ ካልገቡ እግዚአብሔርን የክፉን ንጉስ ኖኅን ህዝቦች እንደሚቀጣ ተነበየ፣ ሞዛያ ፲፩፡፳–፳፭። የንጉስ ኖኅን እና የህዝቦቹን መደምሰስ ስለተነበየ ታሰረ፣ ሞዛያ ፲፪፡፩–፲፯። የንጉስ ኖኅን ክፉ ቁሶች ስለሙሴ እና ስለክርስቶስ ህግ አስተማረ፣ ሞዛያ ፲፪–፲፯። ሽማግሌው አልማ አመነው እና ቃላቶቹን ጻፈ፣ ሞዛያ ፲፯፡፪–፴። በንጉስ ኖኅ በእሳት ተገ ደለ፣ ሞዛያ ፲፯፡፳።

አቤል። *ደግሞም ቃየን፣ አዳም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአዳም እና የሔዋን ልጅ።

ለእግዚአብሔር ከወንድሙ ቃየን ካደረገው ይልቅ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ መስዋዕት አቀረበ፣ ዘፍጥ. ፬፡፡ ፬–፭ (ዕብ. ፲፩፡፡ ፬፣ ሙሴ ፭፡ ፲፯–፳፩)። በቃየን ተገደለ፣ ዘፍጥ. ፬፡ ፰ (ሙሴ ፭፡ ፴፪)።

ክህነትን ከአዳም ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፲፯።

ሰይጣን ከቃየን ጋር አቤልን ለመግደል የሚስጥር እቅድ ሰራ፣ ሙሴ ፭፡ ፳፰–፴፩ (ሔስ. ፮፡ ፳፯)።

አብራም። *አብርሐም ተመልከቱ*

አብርሐም። *ደግሞም የአብርሐም ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

ከለዳውያን ዑር ውስጥ የተወለደ፣ የታራን ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፲፩፡፡ ፳፯፣ ፴፩፣ ፲፯፡፡ ፳)። የምድር ህዝ ቦች ሁሉ የሚባረኩበት ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ጌታ የገባለት የጌታ ነቢይ። አብርሐም በመጀመሪያ አብ ራም ተብሎ ይጠራ ነበር።

ወደ ሐራን ተሰደደ፣ በዛም ታራን ሞተ፣ ዘፍጥ. ፲፩፡ ፴፩–፴፪ (አብር. ፪፡ ፩–፳)። ወደ ከነዓን እን ዲጓዝ እና መለኮታዊ ቃል ኪዳን እንዲቀበል በእ ግዚአብሔር ተጠራ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፩–፳ (አብር. ፪፡ ፱፣ ፲፭–፲፯)። ወደ ግብፅ ተጓዘ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፱–፳ (አብር. ፪፡ ፳፩–፳፭)። በኬብሮን ውስጥ ሰፈረ፣

ዘፍጥ. ፲፫፡፲፰። ሎጥን አዳነ፣ ዘፍጥ. ፲፱፡፩–፲፯። ከመልከ ጼዴቅ ጋር ተገናኘ፣ ዘፍጥ. ፲፱፡፲፰–፳። አጋር ልጁን እስማኤልን ወለደች፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፲፭–፲፯። ስሙ ወደ አብርሐም ተቀየረ፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፩። ጌታ አብርሐም እና ሳራ ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ ነገራቸው፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፲፭–፳፪፣ ፲፰፡፩–፲፩። ሳራ ወንድ ልጁን ይስሐቅን ወለደች፣ ዘፍጥ. ፳፩፡፪–፫። ይስሐቅን እንዲሰዋ ታዘዘ፣ ዘፍጥ. ፳፪፡፩–፲፰። ሳራ ሞተች እና ተቀበረች፣ ዘፍጥ. ፳፫፡፩–፪፣ ፲፱። አብርሐም ሞተ እና ተቀበረ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፰–፲።

አብርሃም ይስሀቅን ለመስዋዕት በማቅረብ ታዛዥ ነቱ የእግዚአብሔርና ከአንድያ ልጁ ጋር አምሳልነት ያለው ነው፣ ያዕቆ. ፡፡፡–፡፡ ለመልከ ጼዴቅ አስራት ከፈለ፣ አልማ ፲፫፡፲፭። የክርስቶስ መምጣትን አስ ቀድሞ ተመለከተም መሰከረም፣ ሔለ. ፡፡፡፲፭–፲፯።

ክህነትን ከመልከ ጼዴቅ ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡። ታማኝ የአብርሐም ዘር ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡ (ገላ. ፫፡፳፯–፳፱)። ሁሉ ንም ነገሮች በራዕይ ተቀበለ እናም ዘለአለማዊነትን ተቀብሏል፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡።

የአባቶችን በርከቶች እና የክህነት ምደባን ፈለገ፣ **አብር.** ፩፡፩–፡፡። በከላውዴዎ የሀሰት ቁሶች ተሰ ደደ፣ **አብር.** ፩፡፩–፲፭። በጌታ ዳነ፣ **አብር.** ፩፡፲፯–፳። ስለጸሀይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦች ተማረ፣ **አብር.** ፫፡፩–፲፡። ስለምድር በፊት ህይወት እና ፍጥረት ተማረ፣ **አብር.** ፫፡፳፪–፳፳።

መፅሐፈ አብርሐም፣ በ፲፳፻፡፳ (እ.አ.አ.) ወደ ቤተክርስቲያኗ እጅ የገባ በአብርሐም የተጻፈ የጥ ንት መዝገቦች። መዝገቦቹ እና አንዳንድ አስከሬ ኖች በግብፅ መቃብሮች ውስጥ በአንቶኒዮ ሌቦሎ ተገኝተው ነበር፣ እነዚህንም ለማይክል ቻንድለር በኑዛዜ ቃል ተወለት። በ፲፳፻፡፳ (እ.አ.አ.) ቻንድ ለር እነዚህን በዩናትድ ስቴት ውስጥ ለእይታ አቀ ረባቸው። አንዳንድ የጀሴፍ ስሚዝ ጓደኞች ገዙአ ቸው እና ለነብዩ ሰጡት፣ እርሱም ተረጎማቸው። ከእነዚህ አንዳንድ ፅሁፎችም በየታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ ይገኛሉ።

ምዕራፍ ፩ አብርሐም ክፉ ቁሶች ሊሰዉት በሞ ከሩበት በከላውዴዎ ዑር ውስጥ ስለነበረው አጋ ጣሚዎች ይመዘግባል ምዕራፍ ፪ ስለከነዓን ጉዞው ይናገራል። ጌታም ታየው እና ቃል ኪዳን ከእርሱም ጋር ገባ። ምዕራፍ ፫ አብርሐም ሁለንተናን እንዳየ እና በሰማያዊ ሰውነቶች መካከል ያለውን ግንኙነ ቶች እንደተመለከተ መዝግቧል። ምዕራፍ ፡፡–፡ የፍ ጥረት ሌላ መዝገቦች ናቸው።

የአብርሐም ዘር፣ ለህግጋት እና ኢየሱስ ክርስ ቶስ ወንጌል ስነስርዓቶች ታዛዥ በመሆን እግዚአ ብሔር ለአብርሐም የገባውን የተስፋ ቃላትና ቃል ኪዳኖች የሚቀበሉ ህዝቦች። ወንዶች እና ሴቶች የእውነት የአብርሐም ዝርያ ከሆኑ ወይም ወንጌልን በመቀበል እና በመጠመቅ ወደ ቤተሰቡ በጉዲፈቻ ከተወሰዱ እነዚህን በረከቶች ይቀበላሉ (ገላ. ፫፡፳፯–፳፱፣ ፡፡፡–፡፡፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡)። ለአብርሐም የእ ውነት ዘሮች በረከቶቻቸውን ታዛዥ ባለመሆን ለማ ጣት ይችላሉ (ሮሜ ፡፡፡፣ ፡፡–፡–፡)።

አብደናጎ። *ደግሞም ዳንኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ እና አብደናጎ ከዳንኤል ጋር ወደ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት የተወሰዱ ሶስት የእስ ራኤል ወጣቶች ነበሩ። የአብደናጎ ዕብራውያን ስም ዓዛርያስ ነበር። አራቱ ወጣት ሰዎች የንጉሱን ስጋ እና ወይን በመብላት እና በመጠጣት እራሳቸውን ለመበከል እምቢ አሉ (ዳን. ፩)። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ እና አብደናጎ ወደሚነደው ወደ እቶን እሳት ተጣሉ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልጅ በተአምራት ተጠብ ቀው ነበር (ዳን. ፫)።

አብድዩ

ስለኤዶም መጥፋት አስቀድሞ የተናገረ የብ ሉይ ኪዳን ነቢይ። የተነበየው ምናልባት ኢዮራም በነገሰበት ጊዜ (፳፻፵፯–፳፻፵፭ ም.ዓ.) ወይም በ፳፻፲፮ ም.ዓ. ውስጥ ባቢሎን በወረረችበት ጊዜ ነበር።

ትንቢተ አብድዩ፣ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። አንድ ምዕራፍ ብቻ ነበረው። በውስጡም፣ አብ ድዩ ስለኤዶም መጥፋት ጻፈ እናም በፅዮን ተራራ ላይ አዳኞች እንደሚቆሙ ተነበየ።

አንቲ-ኔፊ-ሌሂ። *ደግሞም* አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ፣ የሔለማን ልጆች፣ የሞዛያ ልጆች *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በሞዛያ ወንድ ልጆች ለተቀየሩ ላማናውያን የተሰጠ ስም። ከተቀ የሩ በኋላ፣ እነዚህ የአሞን ህዝቦች ተብለው የተጠሩ ህዝቦች በህይወቶቻቸው በሙሉ ታማኝ ነበሩ (አልማ ፳፫፡፱–፣ ፲፭–፲፯፣ ፳፯፡፳–፳፰)።

አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች የሚል ስም ወሰዱ፣ **አልማ** ፳፫፡፲፭–፲፯፣ ፳፱፡፩። ደም ለማፍሰስ እምቢተ ኞች ሆኑ እናም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ቀበሩ፣ **አልማ** ፳፱፡፯–፣ ፲፱። ልጆቻቸው ለጦርነት ተዘጋጁ እናም ሔለማንን እንደ መሪያቸው መረጡ፣ **አልማ** ፶፫፡፲፭–፲፱፣ ፶፭–፶፰። (ደግሞም እነዚህ ፳፪ ወጣት ጦረኞች ተብለው ይታወቃሉ።)።

አንደበት። ምላስ *ተመልከቱ*

አንድ። አንድነት፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ *ተመልከቱ*

የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ

አንድ ሺህ አመት ፯፲

አንድ ሺህ አመት። *ደግምም ሲያል፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ተመልክቱ*

ክርስቶስ በምድር ላይ ለመንገስ በሚመጣበት ጊዜ የሚጀምረው የ አንድ ሺህ አመት ጊዜ (እ.አ. ፩፡፲)።

ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም፣ ኢሳ. ፪፡፬ (ሚክ. ፬፡፫፣ ፪ ኔፊ ፲፪፡፬)። ባድማ የነበረች ይህች ምድር እንደ ዔድን ገነት ሆናለች፣ ሕዝ. ፴፮፡፴፭።

ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ፡ ራዕ. ፳፡፬።

በህዝቦቹ ፅድቅ ምክንያት ሰይጣን ኃይል የለ ውም፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳፯።

በጽድቅም ከሰዎች ጋር በምድር ላይ ለአንድ ሺ አመታት እኖራለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፩። አንድ ሺ አመት ሲጠናቀቅ፣ መሬትን የምተዋት ለትንሽ ጊዜ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፪። ታላቁ አንድ ሺህ ዘመን ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፸፫፡፴። ልጆችም ወደ ደህንነት ያለሀጢያት ያድጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፸፭፡፻፳። ልጆች እድሜአቸው እስኪገፋ ድረስም ያድጋሉ፣ ሽማግሌዎችም በቅጽበት ዓይንም ይቀ የራሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፻፩። በሰባት ሺ አመቶች መጀመሪያ ላይ ጌታ አምላክ ምድርን ይቀድሳል፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፪። ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈ ጸም ድረስ፣ በሕይወት አይኖሩም፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፩። ሰይጣንም ለአንድ ሺህ ለሚሆን ዘመ ንም አይፈታም፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፲። አንድ ሺህ አመት በግልፅ ተዘርዝሯል፣ ት. እና ቃ. ፻፩፡፳፫–፴፩።

ለአንድ ሺ አመቶችም ምድር ታርፋለች፣ ሙሴ ፯፡፳፬፡፩።

አንድነት። *ደግምም እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልክቱ*

በሀሳብ፣ በፍላጎት፣ እና በአላማ በመጀመሪያ ከሰማይ አባታችንና ከኢየሱስ ጋር፣ እና ከእዚያም ከሌሎች ቅዱሳን ጋር አንድ መሆን።

ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው፣ መዝ. ፻፴፫፡፩።

እኔና አብ አንድ ነን፣ ዮሐ. ፲፡፴ (ት. እና ቃ. ፶፡፳፫)። ኢየሱስ እርሱ እና አባቱ አንድ እንደሆኑ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ ጸለየ፣ ዮሐ. ፲፯፡፲፩–፳፫ (፫ ኔፊ ፲፱፡፳፫)። ሁላችሁ የተባበራችሁ እንድት ሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን እለ ምናችኋለሁ፣ ፩ ቆሮ. ፩፡፲።

በአንድ ሀሳብና በአንድ ልብ ሁኑ፣ በሁሉ ነገ ሮች ተስማሙ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፳፭። ቅዱሳን ልባቸው በአንድ ላይ በአንድነት ይጣበቁ፣ ሞዛያ ፲፰፡፳፭። ኢየሱስ በኔፋውያን ደቀ መዛሙርት መካከል አንድ ነት እንዲኖር ጸለየ፣ ፫ ኔፊ ፲፱፡፳፫። ደቀ መዛሙ ርቱ በብርቱ ፀሎታቸው እና ያማቸው አንድ ሆነው ነበር፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፩።

አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፯–፳፰ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፪፣ ፻፡፻፫)። ከእውነት ቤተክርስቲያን ጋር አንድ መሆን ሀላፊነታችሁ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፯። እንደ ትእ ዛዜ በጸሎት አንድ ሆናችሁ በእምነት የምትጠይ ቁትን ማንኛውንም ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፮። አንድ ካልሆናችሁ የእኔ አይደላችሁም፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡፳፯።

እነርሱ የአንድ ልብ እና የአንድ አእምሮ ስለ ነበሩ፣ ጌታ ህዝቡን ፅዮን ብሎ ጠራቸው፣ ሙሴ ፯፡፲፰።

አንድያ ልጅ። *ደግምም መወለድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልክቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስም። እርሱ የአብ አንድያ ልጅ ነው (ሉቃ. ፩፡፳፯–፴፭፣ ዮሐ. ፩፡፲፬፣ ፫ ፡፲፣ ፩ ኔፊ ፲፣ ፲፡–፳፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፬፣ አልማ ፯፡፲፣ ፲፪፡፴፫፣ ሙሴ ፯፡፳፪)።

አዕምሮ

የአዕምሮ ሀይል፣ የህሊና ሀሳብ ሀይሎች።

በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው፣ ፩ ዜና ፳፰፡፱፡፪።

ጌታ አምላክህን በፍጹም ነፍስህም ውደድ፣ ማቴ. ፳፪፡፴፯።

ስለ ዓለም ማሰብ ሞት እንደሆነና፣ ስለመንፈሳዊ ነገር ማሰብ ዘለዓለማዊ ህይወት ነው፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴፱። የጌታ ድምፅ በአዕምሮዬ መጣ፣ ኢኖስ ፩፡፲። ቃሉ ታላቅ ዝንባሌ ስላለው ከጎራዴ የበለጠ በአዕምሮ አቸው ላይ ውጤት ይኖረዋል፣ አልማ ፴፭፡፪፡፫።

በአዕምሮህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪። በአ እምሮህ ውስጥ ልታጠናው ይገባል፣ ት. እና ቃ. ፱፡፳። የዘለአለም ማስተዋልም በአዕምሮዎቻችሁ ላይ ይረፉ፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፩። ከዚህ በፊት አዕምሮአችሁ ጨልሞባችሁ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፲፡፲፩። ወደ መኝታችሁ በጊዜ ሂዱ፣ ሰውነቶቻ ችሁ እና አዕምሮዎቻችሁ እንዲነቃቁ ዘንድ በማ ለዳም ተነሱ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፳፩።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሀሳብ አያውቅም፣ ሙሴ ፩፡፮። እነርሱ አንድ ልብ እና አንድ አእ ምሮ ስለነበሩ፣ ጌታ ህዝቡን ፅዮን ብሎ ጠራቸው፣ ሙሴ ፯፡፲፰።

አክሊል። *ደግምም የዘለዓለም ህይወት ተመልክቱ*

በመሪዎች ጭንቅላት ላይ የሚቀመጥ ክብ ጌጣጌጥ። ይህም የሰለስቲያል ሀይል፣ ግዛት፣ እና አምላክነት ምልክት ሊሆንም ይችላል። የእግዚአብ ሔርን ትእዛዛት ሁሉ በማክበር የሚጸኑት የዘለአለም

ህይወት ዘውድን ይቀበላሉ። (ት. እና ቃ. ፳፡፲፡፡ ሙሴ ፯፡፹፯፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፩ ተመልከቱ።)

ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፰። የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ፣ ፩ ጴጥ. ፭፡፬።

በእኔ የሞቱት ሙታን የጽድቅን አክሊል ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፫። በአባቴ ቤት ውስጥ አክሊል ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፪። ጌታ ቅዱሳንን ለተዘጋጀላቸው አክሊል እንዲመጡ ያዘጋጃቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፭። ጌታ ለቅዱሳኑ በቀኝ እጁ በኩል የክብር አክሊል ኪዳን ገብቶላቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፲።

አክዓብ። *ደግምም ኤልዛቤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሰሜን እስራኤል ከሁሉም በላይ ክፉ እና ሀይለኛ ንጉስ ከሆኑት አንዱ። የሲዶንን ልዕልት ኤልዛቤልን አገባ፣ በእርሷም ተፅዕኖ በኩል የበኣልን እና የአስታሮት ማምለክን በእስራኤል ውስጥ መሰረተ (፩ ነገሥ. ፲፮፡፳፱–፴፫፣ ፪ ነገሥ. ፫፡፪)፡ እና ነብያትን እና ያህዌህን ማምለክ ለማስወገድ ጥረት ተደርጎ ነበር (፩ ነገሥ. ፲፰፡፲፫)።

በእስራኤል ላይ በሰማሪያ ሀያ ሁለት ዓመት ነገሠ፣ ፩ ነገሥ. ፲፮፡፳፱ (፩ ነገሥ. ፲፮–፳፪)። ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፣ ፩ ነገሥ. ፲፮፡፴። በጦርነትም ተገደለ፣ ፩ ነገሥ. ፳፪፡፳፱–፴።

አይሁዶች። *ደግምም እስራኤል፣ ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ ተመልከቱ*

አይሁዶች (፩) ከያዕቆብ አስራ ሁለት ወንድ ልጆች መካከል አንዱ የይሁዳ ትውልድ፣ (፪) የጥንቱ የደቡብ የይሁዳ መንግስት ህዝቦች፣ ወይም (፫) የይሁዳነት ሀይማኖት፣ የህይወት አኗኗር፣ እና ባህል የሚከተሉ፣ ነገር ግን በተወለዱበት አይሁዳ ለመሆን ወይም ላለመሆን የሚችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የያዕቆብ ትውልዶችን በሙሉ ለመጠቆም ይሁዳ በሚባለው ቃል መጠቀም ባህል ሆኗል፣ ነገር ግን ይህ ስህተት ነው። ይህ ለይሁዳ መንግስት ወይም በተለይ ዛሬ የይሁዳ ጎሳዎችን እና ከእነርሱ ጋር የተገናኙትን ለመጠቆም የተወሰነ መሆን ይገባዋል።

በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም. . . ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፲።

የኢየሱስ ወንጌል አስቀድሞ ለአይሁዳዊ፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው፣ ሮሜ ፩፡፲፮።

ጌታ እግዚአብሔር ከአይሁዶች መካከል ነቢይን፣ እንዲሁም መሲሁን ያስነሳል፣ ፩ ኔፊ ፲፡፱። መፅሐፉ ከአይሁድ አፍ በወጣበት ጊዜ ነገሮች ግልፅና የጠሩ ነበሩ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፳–፳፫። አይሁዶች በሀገር ሁሉ መካከል ይበተናሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፮። አይሁዶች የጥንት የቃል ኪዳን ህዝቦቼ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲። የተበተኑት አይሁዶች ደግሞ በክርስቶስ ማመን ይጀምራሉ፣ ፪ ኔፊ ፴፡፯። አይሁዶች የደህንነት መሰረት የሚያገኙበትን አለቱን አይቀበሉም፣ ያዕቆ. ፱፡፲፱–፲፯። አይሁዶች ኢየሱስ የጥንቱ ክርስቶስ እንደሆነ ሌላ ምስክር ይኖራቸዋል፣ ሞር. ፣፡፳–፳፭።

ሁለት ነቢያት ለአይሁዶች እንዲተነቢዩ በአይሁድ ሀግሮች ይነሳሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፭። መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ከዚያም ወደ አይሁዶች፣ ሁሉንም ሀገሮች ይጥሯቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፣፡፳። በዚያን ጊዜ ታላቅ ስቃይ በአይሁዶች ላይ ይደርሳል፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፲፰።

አይነ አፋርነት። *መጠነኛነት ተመልከቱ*

አይን፣ አይኖች

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ አይን የእግዚአብሔርን ብርሀን ለመቀበል ሰው እንዳለው ችሎታ ምሳሌ በብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ነው። በምሳሌም፣ የሰው አይን የመንፈሳዊ ጉዳይን እና የእግዚአብሔር ነገሮችን ማስተዋልን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል፣ መዝ. ፲፱፡፰። ሰነፎች ዓይን እያላችሁ አታዩም፣ ኤር. ፭፡፳፩ (ማር. ፰፡፲፰)።

የሰውነት መብራት ዓይን ናት፣ ማቴ. ፮፡፳፪ (ሉቃ. ፲፩፡፴፬፣ ፣ ኔፊ ፲፣፡፳፪፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፯)። የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ብፁዓን ናቸው፣ ማቴ. ፲፣፡፲፮። የማስተዋላችሁ አይኖች ብሩህ ይሆናሉ፣ ኤፌ. ፩፡፲፯–፲፰።

በራሳቸው ዐይን ብልህና አስተዋይ ለሆኑት ወዮላቸው፣ ፪ ኔፊ ፲፭፡፳፩ (ኢሳ. ፭፡፳፩)። የህዝቡም ዐይን እንዲከፈት፣ መፀለይ እናም መዖም ጀመሩ፣ ሞዛያ ፳፯፡፳፪። ሰይጣን አሳውሮአቸዋል፣ ፣ ኔፊ ፪፡፪። ለእግዚአብሔር ክብሩ በቀናነት ካላደረገ በስተቀር ማንም መፅሐፈ ሞርሞንን ለማምጣት ሀይል አይኖረውም፣ ሞር. ፰፡፲፭።

፲፪ በመንፈስ ሀይልም፣ አይኖቻችን ተከፈቱ እናም እውቀቶቻችንም ብሩህ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪። አይኖቻችሁን የሚያበራው ብርሀንም በእርሱ በኩል ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፩። ለክብሬ ዐይናችሁ ቀና ብትሆን፣ ሰውነታችሁ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፯።

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም። *ደግምም ፅዮን ተመልከቱ*

ቅዱሳን የሚሰበሰቡበት እና ክርስቶስ በአንድ ሺህ አመት ዘመን እራሱ የሚነግስበት ቦታ። ፅዮን (አዲሲቱ ኢየሩሳሌም) በአሜሪካ ክፍል አህጉራት ውስጥ ትመሰረታለች፣ ምድርም ትታደሳለች እናም እንደ ገነት አይነት ክብር ትቀበላለች (እ.አ. ፩፡፲)። ይህም

በአንድ ሺህ ዘመን ጊዜ ከሰማይ የምትወርደውን ቅዱስ ከተማን ይጠቁማል።

ከጽዮን ሕግ ይወጣል፣ ሚክ. ፬፡፪።

የጌታ ከተማ ስም አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ነው፣ ራዕ. ፲፡፲፪። ዮሐንስ ቅዱስ ከተማዋን፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም አየ፣ ራዕ. ፳፩፡፩–፫።

ይህን ህዝብ በዚህች ምድር እመሰርታለሁ፤ እርሷም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች፣ ፲ ኄፊ ፳፡፳፪። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በአሜሪካ ትመሰረ ታለች፣ ኤተር ፲፫፡፲–፲፯፣ ፲።

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማ ትዘጋጃለች፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፱፣ ፴፭፣ ፴፪–፴፱። ቅዱሳን ይሰ ብሰቡ እናም አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ይመስርቱ፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፴፫–፴፭። አዲስቱ ኢየሩሳሌም በምዙሪ ተመሰረታለች፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፩–፫ (ት. እና ቃ. ፶፯፡፩–፲)። በጉ በፅዮን ተራራ ላይና በቅዱስ ከተማ፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ላይ ይቆ ማል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፶፯።

ድንኳኔም ፅዮን፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ተብላ ትጠራለች፣ ሙሴ ፯፡፴፪።

አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን። *ደግምም ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሙላት (ት. እና ቃ. ፴፯፡፪)። ከክህደት ጊዜ በኋላ እንደ አዲስ በሚ ገለጽበት ጊዜ ሁሉ አዲስ ነው። ይህም ዘለአለ ማዊ የሚሆነው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለሆ ነና ሰዎች ይህን ለመቀበል ፈቃደኛ በሆኑበት በእ ያንዳንዱ የወንጌል ዘመን ይደሰቱበት የነበረ ስለ ሆነ ነው። አዲሱ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን በኢ የሱስ ክርስቶስ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል እንደ ገና በምድር ላይ ለሰዎች ተገለጸ። ይህም በክህነት ስልጣን በኩል የሚከናወኑ ለሰው ደህንነት፣ ህያ ውነት፣ እና ዘለአለማዊ ህይወት ዝግጅት የሚያቀ ርቡ እንደ ጥምቀት እና የቤተመቅደስ ጋብቻ አይ ነት ቅዱስ ስነስርዓቶችን የያዘ ነው። ሰዎች ወንጌ ልን ሲቀበሉ እና የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለማ ክበር ቃል ሲገቡ፣ እግዚአብሔር የአዲስ እና የዘ ለአለም ቃል ኪዳን በረከቶችን ለእነርሱ ለመስጠት ቃል ኪዳን ይገባል።

ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አቆማ ለሁ፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፯። ለእርሱ ክህነት ቃል ኪዳን ይሆንለታል፣ ዘኁል. ፳፭፡፲፫። ሰዎች ሥርዓቱ ንም ለውጠዋልና፥ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍ ርሰዋል፣ ኢሳ. ፳፬፡፭ (ት. እና ቃ. ፭፡፲፭)። የዘላ ለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ፣ ኢሳ. ፶፭፡፣ (ኤር. ፴፪፡፴)። የዘላለምም ቃል ኪዳን ይሆ ንላቸዋል፣ ሕዝ. ፴፯፡፳፯።

ጌታ አዲስ ቃል ኪዳን ሰራ፣ እናም አዲሱን አስረጅታል፣ ዕብ. ፰፡፲፣ ኢየሱስ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ነው፣ ዕብ. ፲፪፡፳፬ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፱)።

ይህ አዲስ እና ዘለአላለማዊ ቃል ኪዳን ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፩። ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን ወደ አለም ላኩኝ፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፱ (ት. እና ቃ. ፵፱፡፱)። ጌታ የወንጌሌን ሙሉነት፣ የዘለአለም ቃል ኪዳኑን ላከ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፪ (ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፶፯)። ከፍተኛውን የሰለስቲያል ክብር ለማግ ኘት፣ ሰው ወደ አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን መግባት አለበት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፩–፪። አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን የተመሰረተው ለጌታ ክብር ሙላት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፯፣ ፲፴።

አዲስ ኪዳን። *ደግምም መፅሐፍ ቅዱስ፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

ስለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለሐዋሪያት፣ እና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ህይወት እና አገልግ ሎት የሚገልጹ (በግሪክ ቋንቋ በመጀመሪያ የተ ጻፉ) የተነሳሱ ጽሁፎች። አዲስ ኪዳን በወንጌሎች፣ በሐዋርያት ስራ፣ በጳውሎስ መልእክቶች፣ አጠ ቃላይ መልእክቶች፣ እና በራዕይ መፅሐፍ የተከ ፋፈሉ ናቸው።

አራቱ ወንጌሎች፣ የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉ ቃስ፣ እና የዮሐንስ መፅሐፎች የክርስቶስ ህይወት ታሪኮች ናቸው። የሐዋርያት ስራ የቤተክርስቲያኗን እና የሐዋሪያትን፣ በልዩም ከክርስቶስ ሞት በኋላ የጳውሎስን የሚስዮን ጉዞ ታሪክ ይመዘግባል። የጳ ውሎስ ደብዳቤዎች የቤተክርስቲያኗን መሪዎችና አባላት ያስተምራል። ሌሎቹ ደብዳቤዎች የተጻ ፉት በሌሎች ሐዋሪያት ነበር እናም የመጀመሪያ ቅዱሳንን ተጨማሪ ምክር የሚሰጥ ነበር። በሐዋሪ ያው ዮሐንስ የተጻፈው የዮሐንስ ራዕይ ስለመጨ ረሻ ቀናት ትንቢቶችን የያዘ ነው።

አዳም። *ደግምም ሔዋን፤ ሚካኤል፤ አዳም-አንዳይ-አማን፤ ዓድን፤ የመላእክት አለቃ፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት ተመልከቱ*

በምድር ላይ የተፈጠረ የመጀመሪያ ሰው።

አዳም የምድር ሰው ዘር አባት እና የአባቶች አለቃ ነው። በዓድን ገነት ውስጥ የተላለፈው (ዘፍጥ. ፫፤ ት. እና ቃ. ፳፪፡፵–፵፪፤ ሙሴ ፩) “እንዲወድቅ” እና ሟች ሆነ፣ ይህም የሰው ዘር በዚህ ምድር ላይ እድገት እንዲኖራቸው አስፈላጊ የሆነ ደረጃ ነበር (፪ ኔፊ ፪፡፲፩–፳፭፤ አልማ ፲፪፡፳፭–፳፯)። ስለዚህ አዳም እና ሔዋን የዘለአለማዊ እድገት እንዲኖረን ስላስቻሉን ለስራ ክፍላቸው መከበር ይገባቸዋል። አዳም በዘመናት የሸመገለውም እና ሚካኤል ተብሎ የሚታወቀው ነው (ዳን. ፯፤ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፤ ፲፯፡፹–፹፩፤ ፲፲፯፤ ፲፴፯፡፴፯)። እርሱም የመላ

እክት አለቃ ነው (ት. እና ቃ. ደ፯፡፹፱) እና እንደ ሰው ቤተሰብ የአባቶች አለቃ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ዝግጅት እንደገና ወደ ምድር ይመ ጣል (ት. እና ቃ. ፲፲፯)።

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፯–፳፰ (ሙሴ ፪፡፳፯–፳፰፣ አብር. ፬፡፳፯–፳፰)። እግዚአብሔር ሰውን በሁሉም ነገሮች ላይ ገዝነት ሰጠው እና እንዲባዛ እና ምድርን እንዲ ሞላ አዘዘው፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፰–፴፩ (ሙሴ ፪፡፳፰–፴፩፣ አብር. ፬፡፳፰–፴፩)። እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን በዔድን ገነት ውስጥ አኖራቸው እና መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውን ዛፍ እንዳ ይበሉም ከለከላቸው፣ ዘፍጥ. ፪፡፮–፱፣ ፲፭–፲፯ (ሙሴ ፫፡፮–፱፣ ፲፭–፲፯፣ አብር. ፭፡፮–፲፣)። አዳም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ ስም አወጣላቸው፣ ዘፍጥ. ፪፡፲፱–፳ (ሙሴ ፫፡፲፱–፳፡ አብር. ፭፡፳–፳፩)። አዳም እና ሔዋን በእግዚአብሔር ተጋቡ፣ ዘፍጥ. ፪፡፲፳–፳፫ (ሙሴ ፫፡፲፳–፳፫፣ አብር. ፭፡፲፱–፳፩)። አዳም እና ሔዋን በሰይጣን ተፈ ተኑ፣ የተከለከለውን ፍሬ በሉ፣ እና ከዔድን ገነ ትም ወጡ፣ ዘፍጥ. ፣ (ሙሴ ፱)። አዳም ሲሙት እድሜው ፱፻፴ ነበር፣ ዘፍጥ. ፭፡፭ (ሙሴ ፮፡፲፪)።

አዳም የመጀመሪያ ሰው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፲፮። ከመሞቱ በፊት አዳም ጻድቅ ዘሮቹን በአ ዳም-ኦንዳይ-አማን ውስጥ ሰበሰበ እና ባረካቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፫–፹፯።

አዳን መስዋዕት አቀረበ፣ ሙሴ ፭፡፱–፳። አዳም ተጠመቀ፣ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ፣ እና ለክህነት ስልጣን ተሾመ፣ ሙሴ ፮፡፶–፳፫።

አዳም-ኦንዳይ-አማን። *ደግምም አዳም ተመልከቱ*

ከመሞቱ ሶስት አመት በፊት አዳም ዘሮቹን የባ ረከበት (ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፫–፹፯) እና ከዳግም ምፃት በፊት እንደገና የሚመጣበት ቦታ (ት. እና ቃ. ፲፲፯)።

አዳኝ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

የሚያድን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በኃጢያት ክፍያ በኩል፣ ለሰው ዘር ቤዛነት እና ደህንነትን አቀረበ። “አዳኝ” የኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና ርዕስ ነው።

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፣ መዝ. ፳፯፡፩ (ዘፀአ. ፲፭፡፩–፪፣ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፪–፫)። እኔ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ ከእኔ ሌላም የሚያ ድን የለም፣ ኢሳ. ፵፫፡፣፩ (ት. እና ቃ. ፷፯፡፩)።

እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፣ ማቴ. ፩፡፳፩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል፣ ሉቃ. ፪፡፲፩ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፣ ዮሐ. ፫፡፲፯–፲፯ ከክርስቶስ በስተ ቀር ሰው የሚዳንበት ምንም ሌላ ስም የለም፣ የሐዋ. ፬፡፲–፲፪ (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፣ ሞዛያ ፫፡፲፣ ፭፡፳፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፳፫፣ ሙሴ ፮፡፶፪)። ከሰማይ መድ ኃኒትን፣ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፣ ፊልጵ. ፫፡፳። አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን ላከው፣ ፩ ዮሐ. ፬፡፲፬።

ጌታ እግዚአብሔር መሲሁን፣ የዓለምን መድ ኃኒት ያስነሳል፣ ፩ ኔፊ ፲፡፬። የእግዚአብሔርም በግ የአለም አዳኝ እንደሆነ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴። የአ ዳኞችን እውቀት በሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ እና ህዝብ መካከል ይሰራጫል፣ ሞዛያ ፫፡፳። ደህን ነት እንዲመጣ ክርስቶስ መሞት ይገባዋል፣ ሔሌ. ፲፬፡፲፭–፲፯።

በአዳኞችን በኩል የሚገኘው ጽድቅነትና ቅድስና ትክክል እና እውነተኛ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴–፴፩። እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የአለም አዳኝ ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፴፱።

አንድያ ልጁም አዳኝ ነው፣ ሙሴ ፩፡፮። በወ ልድ ያመኑትና ለኃጥያታቸው ንስሀ የገቡት ሁሉ ይድናሉ፣ ሙሴ ፭፡፲፭።

አድናቆት። *አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት፣ ክብር ተመልከቱ*

አገልጋይ መላእክት። *መላእክት ተመልከት*

አገልግሎት። *ደግምም በጎ ድርጊት፣ ክህነት፣ ፍቅር ተመልከቱ*

የጌታን ስራ በምድር ላይ ማከናወን። ለእግዚ አብሔር እና ለሌሎች ጥቅም የተሰጠ እንክብካቤ ወይም የተፈጸመ ስራ። ሌሎችን ስናገለግል፣ እግ ዚአብሔርንም ማገልገላችን ነን። የጌታ የተመረጡ አገልጋዮች በስራው ውስጥ ለማገልገል በእግዚአ ብሔር መጠራት አለባቸው። እውነተኛ አገልጋ ዮች የጌታን ፍላጎት ሲያከናውኑ፣ በዋና ሀላፊነታ ቸው ጌታን ይወክላሉ እናም እንደ እርሱ ወኪሎችም ይሰራሉ (ት. እና ቃ. ፳፬፡፳፩)፣ በዚህም ለሰው ደህ ናነት አስፈላጊ ስራዎችን ያከናውናሉ። ጌታ ሐዋሪ ያት፣ ነቢያት፣ ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሊቀ ካህናት፣ ሰባዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ካህናት፣ አስተማሪዎች፣ ዲያቆኖች፣ ረዳቶች፣ እና አስተ ዳዳሪዎች ቅዱሳንን ፍጹም ለማድረግ እና ለአገል ግሎት ስራ ሰጥቷል (፩ ቆሮ. ፲፪፡፲፪–፳፰፣ ኤፌ. ፬፡፲፩–፲፮፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯)።

በእግዚአብሔር ስም ያገለግል ዘንድ አምላክህ መረጠው፣ ዘዳግ. ፲፰፡፭። የምታገለግሉትን ዛሬ ምረጡ፣ ኢያ. ፳፬፡፲፭። ሰዎቹም የአምላካችን አገልጋዮች ብለው ይጠሩአችኋል፣ ኢሳ. ፰፩፡፮።

የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፣ ማቴ. ፳፡፳፭–፳፰። ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ

ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል፣ **ማቴ.** ፳፭፡፡፴–፴፭። ለአ ንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁ፣ **የሐዋ.** ፳፮፡፲፮–፲፰። ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያ ሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ፣ **ሮሜ** ፲፪፡፩። በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪ ያዎች ሁኑ፣ **ገላ.** ፭፡፲፫። እግዚአብሔር፡ ቅዱሳ ንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአ ቸው፡ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁ ትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና፣ **ዕብ.** ፮፡፲። ማንም ሰው የሚያገለግልም ቢሆን፡ እግዚ አብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፣ **፩ ጴጥ.** ፬፡፣–፲፩።

ቀናትህን አምላክህን በማገልገል ታሳልፋለህ፣ **ፍ ኔሬ** ፪፡፫። እናንተ ሰዎችን በምታገለግሉበት ጊዜ እግዚአብሔርን ብቻ እያገለገላችሁ ናችሁ፣ **ሞዛያ** ፪፡፲፯። አንዳቸው ሌላኛውን አገለገሉ፣ እናም አስ ተማሩ፣ **ፍ ኔሬ** ፳፮፡፲ፀ። የቃል ኪዳን ምድርን የሚ ይዙ እግዚአብሔርን ማገልገል ወይም ተጠርገው መውጣት አለባቸው፣ **ኤተር** ፪፡፯–፲፪።

እናንተ በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ መሳ ተፍ የጀመራችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ እንደምታገ ለግሉት አረጋግጡ፣ **ት. እና ቃ.** ፬፡፪። ጌታ እግ ዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲያገለግሉ ትእዛዞች ሰጣቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፣–፲፱። በኢየሱስ ክር ስቶስ ስም አገልግለው፣ **ት. እና ቃ.** ፶፱፡፭። እኔ ጌታ ለየሚያገለግሉኝንም ለማክበር እደሰታለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፯፡፭። ወንጌል ሰባኪዎችን መሾም የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፴፱–፴፯። ሊቀ ካህን በስጋዊ ነገሮች ለማስተዳደር መለ የት ይቻላል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፹፭–፹፪። እነዚህ ሰባዎች ተጓዥ አገልጋዮች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፣፲–፣፯። ሽማግሌዎች የተሾሙት የቤተክ ርስቲያኗ የማይጓዙ አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፬፡፲፴፯።

እግዚአብሔርን አምልክ፣ እርሱን ብቻም አገል ግል፣ **ሙሴ** ፭፡፣፲፭።

አጋር። *ደግሞም አብርሐም፤ እስማኤል፣ የአብርሐም ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሳራ ግብጻዊ ገረድ። የአብርሐም ባለቤት እና የእስማኤል እናት ሆነች (ዘፍጥ. ፣፯፤ ፳፭፡፣፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፣፡ ፳፭)። ጌታ ከልጇ ታላቅ ህዝብ እንደሚመጡ ለአ ጋር ቃል ገባላት (ዘፍጥ. ፳፩፡፱–፳፩)።

አጋንንት። *ዲያብሎስ ተመልከቱ*

አግሪጳ። *ደግሞም ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የመጀመሪያው ሔሮድስ አግሪጳ ወንድ ልጅ እና የበርኒቄ እና የድሩሲላ ወንድም። በሊባኖስ ውስጥ በሚገኘው፣ የቻልስስ ንጉስ። ሐዋሪያው ጳውሎስን ሰማ እና ክርስትያን ወደመሆን ለማመን ቀርቦ ነበር (የሐዋ. ፳፭–፳፮፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፬)።

አጠቃላይ ባለስልጣኖች። *ሐዋሪያ፤ ሰባ፤ ቀዳሚ አመራር፤ የኤጲስ ቆጶስ አመራር ተመልከቱ*

አጥቢያ ኮከብ። *ደግሞም ሲያል፤ አፍራሽ፤ የክርስቶስ ተቃዋሚ፤ የጥፋት ልጆች፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ስሙ "የሚበራው" ወይም "ብርሀን ያዝው" ማለት ነው። እርሱ የንጋት ልጅ ተብሎ ይታወ ቃል። አጥቢያ ኮከብ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ ነበር እናም በቅድመ ምድር ህይወት አመፅን መራ። የአጥቢያ ኮከብ ስም በመፅሐፍ ቅዱስ የሚገኘው አንድ ጊዜ ብቻ ነው (ኢሳ. ፲፬፡፲፪)። የኋለኛው ቀን ራዕይ ስለአጥቢያ ኮከብ መውደቅ ተጨማሪ ዝርዝር ይሰጣል (ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፭–፳፱)።

አጥቢያ ኮከብ በቅድመ ምድር ህይወት ወደቀ፣ **ኢሳ.** ፲፬፡፣፲፪ (ሉቃ. ፣፡፣፰፣ ፪ ኔሬ ፳፬፡፣፲፪)።

ከወደቀ በኋላ ሰይጣን እና ዲያብሎስ ሆነ፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፳፭–፳፱ (ሙሴ ፬፡፩–፬)።

አጥፊ። *አፍራሽ ተመልከቱ*

አፅናኝ። *ደግሞም መንፈስ ቅዱስ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ቅዱሣት መጻህፍት ስለሁለት አፅናኞች ይናገ ራሉ። የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. ፲፬፡፳፭–፳፯፤ ሞሮኒ ፯፡፳፯፤ ት. እና ቃ. ፳፭፡፱፤ ፵፪፡፲፣፤ ፣፡፣፩)። ሁለተኛው አፅናኝ ጌታ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. ፲፬፡፲፣፡ ፳፭፤ ፳፫)። አንድ ሰው ሁለተኛውን አፅናኝ ሲያገኝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጊዜ ወደጊዜ ለእርሱ ይታየዋል፣ አብን ይገልፅለታል፣ እናም ፊት ለፊትም ያስተምረዋል (ት. እና ቃ. ፲፱፡፣–፣)።

አፍራሽ። *ደግሞም ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ሰይጣን አጥፊው ነው።

እግዚአብሔር አጥፊው ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም፣ **ዘፀአ.** ፲፪፡፳፫።

አጥፊው በውሀው ላይ ይንሳፈፋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡፲፱። ጠባቂው የወይን ስፍራዬን ከአጥፊው ሊያድኑት ይችሉ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፶፭–፶፩።

አፖክሪፋ። *ደግሞም መፅሐፍ ቅዱስ፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

በእብራውያን መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጨ

መሩት ነገር ግን በአንዳንድ የክርስትያን ቤተክርስ ትያናት ውስጥ የሚገኙት የአይሁድ ህዝቦች ቅዱሣት መጻህፍት። እነዚህ መጽሀፎች በብዙ ሁኔታዎች ብሉይ እና አዲስ ኪዳኖችን ለማያያዝ ጠቃሚ ናቸው እና በቤተክርስትያኗ ውስጥ እንደ ጠቃሚ ምንባብ አስተያየት ይሰጣቸዋል።

አፖክርፋ በብዙ ጊዜ በትክክል የተተረጎሙ ናቸው ነገር ግን ትክክል ያልሆነ ጣልቃዎች ገብ ተውባቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፯፩፡፩–፫። አፖክርፋ በመንፈስ የተብራሩትን ለመጠቀም ይችላል፣ ት. እና ቃ. ፯፩፡፱–፲፮።

ኡሪም እና ቱሚም። *ደግሞም ባለራዕይ፤ የደረት ኪስ ተመልከቱ*

ሰውን ራዕይን ለማግኘት እና በቋንቋዎች ለመተ ርጎም በእግዚአብሔር የተዘጋጀ መሳሪያ። በእብራ ውያን ቋንቋ ቃላቶቹ “ብርሀኖች እና ፍጹምነቶች” ማለት ነው። ኡሪም እና ቱሚም በብር ቀሰት ላይ የተቀመጥ ሁለት ድንጋዮች ያሉበት እናም አንዳንድ ጊዜም ከጥሩር ጋር ይጠቀሙበት ነበር (ት. እና ቃ. ፲፯፡፩፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፭፣ ፴፪፣ ፴፪)። ይህች ምድር በተቀደሰችበት እና በአለሟችነት ሁኔታዋ ታላቅ ኡሪም እና ቱሚም ትሆናለች (ት. እና ቃ. ፲፴፡፲–፱)።

በፍርዱ በደረት ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሚ ምን ታደርጋለህ፣ **ዘፀአ.** ፳፰፡፴፡፴።

ድል ለነሣው ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፣ ራዕ. ፪፡፣ ፲፯።

እርሱ የሚመለከትበት ለመተርጎም የሚችል በት አለው፣ **ሞዛያ** ፰፡፲፫። እነዚህን ሁለት ድን ጋዮች እሰጥሃለሁ፣ **ኤተር** ፫፡፳፫–፳፭፣ ፳፡፳ (ኤተር ፭፡፩)።

ጆሴፍ ስሚዝ በኡሪም እና ቱሚም በኩል ራዕ ዮችን ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ክፍሎች ፯፣ ፲፩፣ ፲፬–፲፯ መግቢያዎች። በኡሪም እና ቱሚም አማካኝነት እንድትተረጉም ኃይል ተሰጥተውሀል፣ ት. እና ቃ. ፲፡፩። ሶስቱ ምስክሮች ለያሬድ ወንድም የተሰጡ ትን ኡሪም እና ቱሚም ይመለከታሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩። እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታምታላቅ ኡሪም እና ቱሚም ነው። ነጩ ድንጋይ ለሚቀበ ሉት ግለሰቦች ሁሉ ኡሪም እና ቱሚም ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፮–፲፩።

እኔ፣ አብርሐም፣ ኡሪም እና ቱሚም ነበረኝ፣ **አብር.** ፫፡፩፣ ፱።

ኢሊያ። *ደግሞም ኤልያስ ተመልከቱ*

ኤልያስ የሚባለው ስም ወይም ርዕስ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የተለያዩ ጥቅም ነበራቸው።

ቀደምትነት ያለው፣ ኤልያስ ቀደምትነት ላለው የተሰጠ ርዕስም ነው። ለምሳሌ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኤልያስ የነበረው ለኢየሱስ መንገድን እንዲያዘጋጅ ስለተላከ ነው (ማቴ. ፲፯፡፲፪–፲፫)።

ደግሞ የሚልክ፣ የኤልያስ ርዕስ እንደ ባለራዕዩ ዮሐንስ አይነት ልዩ ሚስዮንን ለሚያሟሉት ተሰ ጥቷል (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፱) (ሉቃ. ፩፡፲፩–፳፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፮–፯፣ ፲፲፡፲፪)።

በአብርሐም ዘመን የነበረ ሰው፣ በአብርሐም ቀናት ይኖር የነበረ ኢሳይያስ ወይም ኤልያስ ተብሎ የተጠራ ነቢይ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፲፩–፲፫፣ ፲፲፡፲፪)።

ኢሳይያስ

ከ፯፻፵–፯፻፩ ም.ዓ. ድረስ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። እንደ ንጉስ ሕዝቅያስ ዋና አማካሪ፣ ኢሳይ ያስ ታላቅ የሀይማኖትና የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበረው። ኢሳይያስ በአብርሐም ቀናት ይኖር የነበረ ነቢይ ነበር (ት. እና ቃ. ፳፯፡፣ ፹፬፡፲፫)።

ኢየሱስ ኢሳይያስን ከሌሎች ነቢያት በላይ ጠቅሶ ነበር። ደግሞም ኢሳይያስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ እና ጳውሎስ ተጠቅሷል። መፅሐፈ ሞርሞንና ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ተጨማሪ ጠቅሶች ከሌሎች ነቢያት በላይ ከኢሳ ይያስ አሏቸው እናም ኢሳይያስን ለመረዳት ብዙ እርዳታዎችን ያቀርባሉ። ኔፊ ከኢሳይያስ ጽሁፎች ህዝቡን አስተማረ (፪ ኔፊ ፲፪–፳፱፣ ኢሳ. ፪–፲፱)። ጌታ ለኔፋውያን “የኢሳይያስ ቃላት ታላቅ ናቸው” እናም ኢሳይያስ የተነበያቸው ሁሉም ነገሮች እን ደሚሟሉ ነገራቸው (፫ ኔፊ ፳፫፡፩–፫)።

መፅሐፈ ኢሳይያስ፣ የብሉይ ኪዳን መፅሀፍ። ብዙዎቹ የኢሳይያስ ትንቢቶች ስለአዳኝ መምጣት፣ ስለምድራዊ አገልግሎቱና (ኢሳ. ፱፡፮) በመጨረሻ ቀን እንደ ታላቅ ንጉስ መምጣቱ (ኢሳ. ፳፫) የሚና ገሩ ነበሩ። ደግሞም ስለእስራኤል ወደፊት ሁኔታም ብዙ ተነበየ።

ምዕራፍ ፩ መፅሐፉን በሙሉ ማስተዋወቂያ ነው። ኢሳይያስ ፯፡፲፬፣ ፱፡፮–፯፣ ፲፩፡፩–፭፣ ፶፫፡፲–፲፩ የአዳኝ ተልዕኮን አስቀድመው ይናገራሉ። ምዕራፍ ፪፣ ፲፩፣ ፲፪፣ እና ፴፭ ወን ጌሉ ዳግም በሚመለስበት፣ እስራኤል በምትሰበሰ ብበት፣ እና የጠግው ምድር እንደ ጽጌ ረዳም በሚ ያብብበት በጓለኛው ቀናት ስለሚሆኑ ጉዳዮች ይናገ ራሉ። ምዕራፍ ፳፱ ስለመፅሐፈ ሞርሞን መምጣት ትንቢት የያዘ ነው (፪ ኔፊ ፳፯) ምዕራፍ ፴–፴፮ ስለ ያህዌህ እንደ እውነተኛ አምላክ የጣዖት አምላኪዎች አምልክት በላይ ታላቅነት የሚያውጁ ነበሩ። የሚ ቀሩት ምዕራፍ፣ ፴፯–፴፯፣ ስለእስራኤል የመጨ ረሻ ዳግም መመለስ እና ጌታ በህዝቡ መካከል በመ ኖር ስለፅዮን መመስረት ይናገራሉ።

ኢሮስ፣ የያዕቆብ ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የጻለየና በክርስቶስ

እምነቱ በኩል ለኃጢያቶቹ ስርየትን ያገኘ የኔፋ ውያን ነቢይና መዝገብ ጠባቂ (ኢኖስ ፩፡፩–፰)። ጌታ ከኢኖስ ጋር መፅሀፈ ሞርሞንን ለናማናውያን ለማምጣት ቃል ኪዳን ገባ (ኢኖስ ፩፡፲፭–፲፯)።

መፅሐፈ ኢኖስ፣ ኢኖስ ወደ ጌታ ለግል ምህረት፣ ለህዝቦቹና፣ ለሌሎችስለጸለየበት የሚነግር በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኝ መፅሐፍ። ጌታ መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚጠበቅ እና በወደፊት ቀን ላማናውያን እንዲያገኙት እንደሚደረግ ጌታ ቃል ገባለት። ምንም እንኳን መፅሐፉ አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ቢሆንም፣ አምላኩን በጸሎት ስለፈለገ፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥ በመሆን ስለኖረ፣ እናም ከመሞቱ በፊት በቤዛው እውቀት ስለተደሰተ ሰው ሀይለኛ ታሪክ መዝግቧል።

ኢየሱስ ክርስቶስ። *ደግምም* ህሊና፣ ህያው ውሀ፣ መለወጥ—የክርስቶስ መለወጥ፣ መልካሙ እረኛ፣ መሰቀል፣ መሲህ፣ መስቀል፣ መስዋዕት፣ መንገድ፣ መወለድ፣ መድኃኒት፣ መጀመሪያ፣ መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፣ መፍጠር፣ ፍጥረት፣ ሙሽራ፣ ማለቂያ የሌለው፣ ማርያም፣ የኢየሱስ እናት፣ ቅዱስ ቁርባን፣ በኩር፣ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት፣ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ ትንሳኤ፣ አለት፣ አልፋ እና ኦሜጋ፣ አማላጅ፣ አማኑኤል፣ አዳኝ፣ አፅናኝ፣ እምነት፣ ማመን፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ ወንጌሎች፣ ወደ ሰማይ ማረግ፣ የኃጢያት ስርየት፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ የህይወት እንጀራ፣ የማዕዘን ድንጋይ፣ የሰው ልጅ፣ የቤዛነት ዕቅድ፣ የተራራ ስብከት፣ የተቀባው፣ የናስ እባብ፣ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፣ የእግዚአብሔር በግ፣ ያህዌህ፣ ያለና የሚኖር፣ ደም፣ ጌታ፣ ጎልጎታ፣ ጸጋ *ተመልከቱ*

(የግሪክ ቃል የሆነው) *ክርስቶስ* እና (የዕብራዊ ያን ቃል የሆነው) *መሲህ* “የተቀባ” የሚል ትርጉም አላቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ በመንፈስ የበኩር ልጅ ነው (ዕብ. ፩፡፮፣ ት. እና ቃ. ፯፲፡፳፩)። እርሱም በስጋ የአብ አንድያ ልጅ ነው (ዮሐ. ፩፡፲፬፣ ፫፡፲፮)። እርሱም ያህዌህ ነው (ት. እና ቃ. ፴፲፡፫–፴)፡ እናም ለታላቁ ጥሪው ምድር ከመፈጠሯ በፊት ቀድሞ የተመረጥ ነበር። በአብ አመራር ስር፣ ኢየ ሱስ ምድርን እና በላዩዋ ያሉትን ሁሉ ፈጠረ (ዮሐ. ፩፡፫፣ ፲፬፡ ሙሴ ፩፡፴፭–፴፫)። በቤተሌሔም ከማ ርያም ተወለደ፣ ኃጢያት የሌለው ህይወት ኖረ፣ እናም ደሙን በማፍሰስ እና ህይወቱን በመስቀል ላይ አሳልፎ በመስጠት ለሰው ዘር ፍጹም የኃጢ ያት ክፍያን አደረገ (ማቴ. ፪፡፩፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡፲፫–፴፫፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፫–፲፯፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፵–፵፪)። ከሞት ተነሳ፣ በዚህም የሰው ዘር ሁሉ ከሞት እን ደሚነሳ አረጋገጠ። በኢየሱስ የኃጢያት ክፍያ እና ትንሳኤ፣ ለኃጢያታቸው ንስሀ የሚገቡት እና የእ ግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚያከብሩ ከኢየሱስ እና ከአብ ጋር ለዘለአለም ለመኖር ይችላሉ (፪ ኔፊ ፱፡፲–፲፪፣ ፳፩–፳፪፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፶–፶፣ ፳፪)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ላይ ከተወለዱት ሁሉ በላይ ታላቅ ነው። ህይወቱም የሰው ዘር ሁሉ መኖር ያለበት ፍጹም ምሳሌ ነው። ሁሉም ጸሎቶች፣ በረ ከቶች፣ እና የክህነት ስነስርዓቶች በእርሱ ስም መከ ናወን ይገባቸዋል። እርሱም የጌቶች ጌታ፣ የንጉ ሶች ንጉስ፣ ፈጣሪ፣ አዳኝ፣ እና የምድር ሁሉ አም ላክ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሺህ አመት በሀይልና በክብር በምድር ላይ ለመንገስ እንደገና ይመጣል። በመ ጨረሻም ቀን፣ የሰው ዘርን ሁሉ ይፈርድባቸዋል (አልማ ፲፩፡፶–፶፩፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩)።

የህይወቱ ማጠቃለያ (በድርጊቶች ተከታታይ ነት)፣ የኢየሱስ መወለድ እና ተልዕኮ አስቀድሞ ተነ ግሮ ነበር፣ ሉቃ. ፩፡፳፯–፴፰ (ኢሳ. ፯፡፲፬፣ ፱፡፮–፯፣ ፩ ኔፊ ፲፩)። ተወለደ፣ ሉቃ. ፪፡፩–፯ (ማቴ. ፩፡፲፰–፳፭)። ተገረዘ፣ ሉቃ. ፪፡፳፩። በቤተመቅ ደስ ውስጥ ቀረበ፣ ሉቃ. ፪፡፳፪–፴፰። በሰብአ ሰገል ተጎበኘ፣ ማቴ. ፪፡፩–፲፪። ዮሴፍ እና ማርያው ወደ ግብፅ ሸሹ፣ ማቴ. ፪፡፲፫–፲፰። ወደ ናዝሬት ተወ ሰደ፣ ማቴ. ፪፡፲፱–፳፫። በእስራ ሁለት አመቱ ቤተ መቅደስን ጎበኘ፣ ሉቃ. ፪፡፵፩–፶። ወንድሞችና እህቶች ነበሩት፣ ማቴ. ፲፫፡፶፭–፶፮ (ማር. ፮፡፫)። ተጠመቀ፣ ማቴ. ፫፡፲፫–፲፯ (ማር. ፩፡፱–፲፩፣ ሉቃ. ፫፡፳፩–፳፪)። በዲያብሎስ ተፈተነ፣ ማቴ. ፬፡፩–፲፩ (ማር. ፩፡፲፪–፲፫፣ ሉቃ. ፬፡፩–፲፫)። ደቀ መዛ ሙርቱን ጠራ፣ ማቴ. ፬፡፲፰–፳፪ (ማቴ. ፱፡፱፣ ማር. ፩፡፲፯–፳፡ ፪፡፲፬–፲፯፣ ሉቃ. ፭፡፩–፲፩፣ ፳፯–፳፰፣ ፮፡፲፪–፲፯)፣ ዮሐ. ፩፡፴፭–፶፩)። አስራ ሁለቱን ሾመ፣ ማቴ. ፲፡፩–፬ (ማር. ፫፡፲፫–፲፱፣ ሉቃ. ፮፡፲፪–፲፮)። የተራራ ስብከትን ሰጠ፣ ማቴ. ፭–፯። ስለእራሱ ሞትና ትንሳኤ አስቀድሞ ተና ገረ፣ ማቴ. ፲፮፡፳፩ (ማቴ. ፲፯፡፳፪–፳፫፣ ፳፡፲፯–፲፱፣ ማር. ፰፡፴፩፣ ፱፡፴–፴፪፣ ፲፡፴፪–፴፬፣ ሉቃ. ፱፡፳፪–፳፮)። ተለወጠ፣ ማቴ. ፲፯፡፩–፱ (ማር. ፱፡፪–፰፣ ሉቃ. ፱፡፳፰–፴፮)። ሰባዎ ችን ላከ፣ ሉቃ. ፲፡፩–፳። ወደ ኢየሩሳሌም በድል ገባ፣ ማቴ. ፳፩፡፩–፲፩ (ማር. ፲፩፡፩–፲፩፣ ሉቃ. ፲፱፡፳፱–፴፣ ዮሐ. ፲፪፡፲፪–፲፭)። ቅዱስ ቁርባንን መሰረተ፣ ማቴ. ፳፮፡፳፮–፳፱ (ማር. ፲፬፡፳፪–፳፭፣ ሉቃ. ፳፪፡፲፱–፳)። በጌቴሴማኒ ውስጥ ተሰቃየ እና ጸለየ፣ ማቴ. ፳፮፡፴፯–፴፮ (ማር. ፲፬፡፴፫–፴፮፣ ሉቃ. ፳፪፡፵፩–፴፮)። ተካደ፣ ተያዘ፣ እና ተተወ፣ ማቴ. ፳፮፡፴፯–፶፮ (ማር. ፲፬፡፴፫–፶፫፣ ሉቃ. ፳፪፡፵–፶፪፣ ዮሐ. ፲፰፡፪–፲፫)። ተሰቀለ፣ ማቴ.

ፍጹ፡ ፍፁ–ፍፁ (ማር. ፲፫፡ ፍ–ፍፁ፣ ሉቃ. ፍ፮፡ ፍ፯–ፍፍ፣ ፍፀ–ፍፁ፣ ዮሐ. ፲፱፡ ፲፯–ፍ)። በትንሳኤ ተነሳ፣ **ማቴ.** ፍፍ፡ ፍ–ፍ (ማር. ፲፯፡ ፩–፰፡ ሉቃ. ፍፀ፡ ፩–፲፪፣ ዮሐ. ፍ፡ ፩–፲)። ከትንሳኤው በኋላ ታየ፣ **ማቴ.** ፍፍ፡ ፱–ፍ (ማር. ፲፯፡ ፱–፲፡ ሉቃ. ፍፀ፡ ፲፫–ፍፍ፣ ዮሐ. ፍ፡ ፲፩–ፍፀ፣ የሐዋ. ፩፡ ፫–ፍ፡ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፭–ፍ)። ወደ ሰማይ አረገ፣ **ማር.** ፲፯፡ ፲፱–ፍ (ሉቃ. ፍፀ፡ ፻፩–፻፫፣ የሐዋ. ፩፡ ፱–፲፪)።

በኔፋውያን ታየ፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፩–፲፯ (፫ ኔፊ ፲፩–ፍ፯)።

በጆሴፍ ስሚዝ ታየ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፭–ፍ።

ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ምት ትንቢ ቶች፣ ድንግል ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅም ትወል ዳለች፣ **ኢሳ.** ፯፡ ፲፬ (፩ ኔፊ ፲፩፡ ፲፫–ፍ)። ከቤተ ልሔም በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣል ኛል፣ **ሚክ.** ፭፡ ፪።

ላማናውያን ሳሙኤል ስለአንድ ቀን፣ ምሽት፣ እና ቀን ብርሀን፣ አዲስ ኮከብ፣ እና ሌሎች ምልክ ቶች ተነበየ፣ **ሔሌ.** ፲፬፡ ፪–፯። ላማናውያን ሳሙኤል ስለጭለማ፣ ስለነነድጎዶች እና መብረቆች፣ እናም ስለምድር መንቀጥቀት ተነበየ፣ **ሔሌ.** ፲፬፡ ፭–ፍ፯። የኢየሱስ መወለድ ምልክቶች ተፈጸሙ፣ ፫ ኔፊ ፩፡ ፲፭–ፍ፩። የኢየሱስ ሞት ምልክቶች ተፈጸሙ፣ ፫ ኔፊ ፰፡ ፭–ፍ፫።

ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ምስክር፣ ጳውሎስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ መሰከረ፣ **የሐዋ.** ፲፰፡ ፭። ክፉው መንፈሶችም ኢየሱስን እናውቃ ለን ብለው መሰከሩ፣ **የሐዋ.** ፲፱፡ ፲፭። በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ አይችልም፣ ፩ ቆሮ. ፲፪፡ ፫። እያንዳንዱ ጎል በት ይንበረከካል መላስም ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክራል፣ **ፊልጵ.** ፪፡ ፣–፲፩።

ስለክርስቶስ እንናገራለን፣ በክርስቶስ እንደሰ ታለን፣ ስለክርስቶስ እንሰብካለን፣ ስለክርስቶስ ትንቢት እንናገራለን፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳፯። መፅሐፈ ሞርሞን አይሁዶችን እና አህዛብን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለማሳመን የተጻፈ ነው፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፪ (የመፅሐፈ ሞርሞን ርዕስ ገፅ)። ነቢያት እና ቅዱሣት መጻህፍት ስለክርስቶስ ይመሰክራሉ፣ *ያዕቆ.* ፯፡ ፲፩፣ ፲፱። ነቢያት እና ሐዋሪያት የፃፉ ለትን ይህንን ኢየሱስን ፈልጉ፣ **ኤተር** ፲፪፡ ፻፩።

አይተነዋልና፣ እናም እርሱ የአብ አንድያ ልጅ እንደሆነም ሲመሰክር ድምፅ ሰምተናል፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡ ፳–ፍፀ። ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፡ ፳ፀ።

በዘለአለማዊ አባት እግዚአብሔር፣ እና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፣ **እ.አ.** ፩፡ ፩። ክር ስቶስ እራሱ በምድር ላይ እንደሚነግስ እናምና ለን፣ **እ.አ.** ፩፡ ፲።

ስልጣን፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፱፡ ፮ (፪ ኔፊ ፲፱፡ ፮)።

ኢየሱስ ስልጣን እንዳለው አስተማረ፣ **ማቴ.** ፯፡ ፳፱–ፍ፱ (ማር. ፩፡ ፳፪)። በምድር ላይ ኃጢአ ትን ያስተሰርይ ዘንድ የሰው ልጅ ሥልጣን አለው፣ **ማቴ.** ፱፡ ፮። ኢየሱስ በሥልጣን ርኵሳን መናፍ ስትን አዘዘ፣ እነርሱም ታዘዙለት፣ **ማር.** ፩፡ ፳፯ (ሉቃ. ፱፡ ፴፫–፴፮)። ኢየሱስ አስራ ሁለትን ስል ጣን እንዲኖራቸው ሾመ፣ **ማር.** ፫፡ ፲፡–፲፭። ኢየ ሱስ ቃሉ በሥልጣን ነበር፣ **ሉቃ.** ፬፡ ፴፪። አብ ፍር ድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው፣ **ዮሐ.** ፭፡ ፳፪፣ ፳፯። እግዚአብሔር ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስና በኃ ይልም ቀባው፣ **የሐዋ.** ፣፡ ፴፰። ክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር በፊት አስቀድሞ ታወቀ፣ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፳ (ኤተር ፫፡ ፲፬)። ክርስቶስ የሞትና የሲኦልም መክ ፈቻ አለው፣ *ራዕ.* ፩፡ ፣፲።

ሁሉም ሰዎች ለክርስቶስ ይገዛሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፭። የእግዚአብሔርን ልጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የሰማ ይና የምድር አባት፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነው፣ **ሔሌ.** ፲፬፡ ፲፪።

ክርስቶስ የመጣው በአብ ፈቃድ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡ ፳፭። ኢየሱስ የአብን ክብር ሙሉነት ተቀበለ፣ እናም ሁሉንም ሀይል ተቀበለ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፫፡ ፫–፱፣ ፲፯–፲፯ (ዮሐ. ፫፡ ፴፭–፴፯)።

ክርስቶስ ከሚችነት በኋላ መገለጡ፣ ኢየሱስ በተነሣ ጊዜ፡ አስቀድሞ ለማርያም ተገለጠ፣ **ማር.** ፲፯፡ ፱ (ዮሐ. ፳፡ ፲፩–፲፯)። ኢየሱስ በኤማሁስ መን ገድ ላይ ከሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር ሄደ እናም ተነጋገረ፣ **ሉቃ.** ፳፬፡ ፲፫–፴፪። ኢየሱስ እጆቹን እና እግሮቹን ለነኩት ሐዋሪያት ተገለጠ፣ **ሉቃ.** ፳፬፡ ፴፯–፴፫ (ዮሐ. ፳፡ ፲፱–፳)። ኢየሱስ ለቶማስ ተገለጠ፣ **ዮሐ.** ፳፡ ፳፬–፳፱። ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠ፣ **ዮሐ.** ፳፩፡ ፩–፲፡፡ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ለአርባ ቀን አገለገለ፣ **የሐዋ.** ፩፡ ፪–፫። እስጢፋኖስ ኢየሱስ ንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ፣ **የሐዋ.** ፯፡ ፶፭–፶፮። ኢየሱስ ለሳዖል ተገለጠ፣ **የሐዋ.** ፱፡ ፩–፳ (ጆ.ስ.ት.፣ የሐዋ. ፱፡ ፣፡ የሐዋ. ፳፯፡ ፱–፲፣)። ክር ስቶስ ከፍ፲ በላይ ሰዎች ታየ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፫–ፍ።

ኢየሱስ እራሱን ለኔፊ ህዝቦች ገለጠ፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፩–፲፯። ፪ ሺህ ፭፻ ሰዎች ኢየሱስን አዩ እናም ሰሙ፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡ ፲፯–ፍ፭። ሞርሞን በጌታ ተጎ በኘ፣ **ሞር.** ፩፡ ፲፭።

ጆሴፍ ስሚዝ እና ስድኒ ሪግደን ኢየሱስን በእግ ዚአብሔር በኩል ቀኝ አዩት፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡ ፳፪–ፍ፫። ጆሴፍ ስሚዝ እና ስድኒ ሪግደን ጌታን በከርት ላንድ ቤተመቅደስ ውስጥ አዩ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፲፡ ፩–፱።

ጆሴፍ ስሚዝ ኢየሱስን አየ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፭–፲፯።

የቤተክርስትያኗ ራስ፣ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው፣ **ኤፌ.** ፭፡፳፫ (ኤፌ. ፩፡፳፪፣ ፬፡፲፭)። እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፣ **ቄላ.** ፩፡፲፰።

ይህች የእኔ ቤተክርስቲያን ናት፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፳፪ (ሞዛያ ፳፯፡፲፫)። ክርስቶስ የእምነታቸው ደራሲ እና ፈፃሚ ነው፣ **ሞሮኒ** ፯፡፩–፬።

ይህችን ቤተክርስቲያን መስርቻታለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፫፡፭ (፫ ኔፊ ፳፯፡፫–፳)።

የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፣ እኔ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ፣ **ዮሐ.** ፲፫፡፲፭። እኔ መንገድና እውነት ሕይወ ትም ነኝ፣ **ዮሐ.** ፲፬፡፮። ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከ ራን ተቀብሎአል፣ **፩ ጴጥ.** ፪፡፳፩።

የህያው እግዚአብሔርን ልጅ ምሳሌን በመከተል ሰው እስከመጨረሻው የማይፀና ከሆነ፣ መዳን አይ ችልም፣ **፪ ኔፊ** ፴፩፡፲፮። እንደ እኔ ፍፁም እንድ ትሆኑ እፈልጋችኋለሁ፣ **፫ ኔፊ** ፲፪፡፴፳። እኔ እን ዳደረግሁትም ቢሆን፣ ይህንን ሁል ጊዜ በቀጣይነት አድርጉ፣ **፫ ኔፊ** ፲፳፡፮። ለእናንተ ምሳሌም ትቼላ ችኋለሁ፣ **፫ ኔፊ** ፲፳፡፲፮። እኔ ስሰራው ያያችሁትን ስራ እናንተም ደግሞ ስሩ፣ **፫ ኔፊ** ፳፯፡፳፩፣ ፳፯፡፯። የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች ልክ እርሱ እንደሆነ ይሆናሉ፣ **ሞሮኒ** ፯፡፴፳።

የክርስቶስ ምሳሌዎች እና ምልክቶች፣ አቤልም ከበጎቹ በኩራትና አቀረበ፣ **ዘፍጥ.** ፬፡፬ (ሙሴ ፭፡፳)። አንድ ልጅህን ይስሐቅን ውሰድ፣ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው፣ **ዘፍጥ.** ፳፪፡፩–፲፫ (ያዕቆ. ፬፡፭)። ጌታ የእስራኤል ልጆችን እንከን የሌለበት በግ እንዲሰዉ አዘዛቸው፣ **ዘፀአ.** ፲፪፡፭፣ ፳፭፣ ፴፯ (ዘኁል. ፱፡፲፪፣ ዮሐ. ፩፡፳፱፣ ፲፱፡፴፫፣ ፩ ጴጥ. ፩፡፲፱፣ ራዕ. ፭፡፮)። ትበሉት ዘንድ እግ ዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ ነው፣ **ዘፀአ.** ፲፮፡፪–፲፭ (ዮሐ. ፮፡፶፩)። ዓለቱንም ትመታለህ፣ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል፣ **ዘፀአ.** ፲፯፡፮ (ዮሐ. ፱፡፮–፲፱፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፩–፬)። መተላለፋቸው ንም ሁሉ በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል፣ **ዘሌዋ.** ፲፮፡፳–፳፪ (ኢሳ. ፶፫፡፲፩፣ ሞዛያ ፲፡፲፩፣ ፲፫፡፲፫–፱)። የተመለከቱት ይድኑ ዘንድ፣ ሙሴም የናሱን እባብ ሰቀለ፣ **ዘኁል.** ፳፩፡፰–፱ (ዮሐ. ፫፡፲፬–፲፭፣ አልማ ፴፫፡፲፱፣ ሔለ. ፰፡፲፬–፲፭)። ዮናስም ለሦ ስት ቀንና ለሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበረ፣ **ዮና.** ፩፡፲፯ (ማቴ. ፲፪፡፴)።

ይህ ነገር በጸጋና በእውነት የተሞላው የአብ አን ድያ ልጅ መስዋዕት አምሳል ነው፣ **ሙሴ** ፭፡፬–፰።

የክርስቶስ ቅድመ ምድራዊ ህይወት፣ እግዚአ ብሔርም ለአብራም ተገለጠለት፣ **ዘፍጥ.** ፲፪፡፯ (ዘፍጥ. ፲፯፡፩፣ ፲፰፡፩፣ አብር. ፪፡፯–፰)። እግዚ አብሔርም ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር፣ **ዘፀአ.** ፴፫፡፲፩ (ዘዳግ. ፴፬፡፣ ሙሴ ፩፡፩–፪)። ጌታን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ አየሁት፣ **ዓሞ.** ፱፡፩።

በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብ ሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ፤ እናም በእኛ አደረ፣ **ዮሐ.** ፩፡፩፣ ፲፬ (፩ ዮሐ. ፩፡፩–፫)። አብ ርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ፣ **ዮሐ.** ፰፡፶፰። ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራ ስህ ዘንድ አክብረኝ፣ **ዮሐ.** ፲፯፡፭።

ኢሳይያስ በእውነት መድኃኒቴን፣ እኔ እና ወን ድሜ ያዕቆብ እንዳየነው፣ አይቶታል፣ **፪ ኔፊ** ፲፩፡፪–፫። በሚቀጥለውም ቀን . . . ወደ ዓለም እመጣለሁ፣ **፫ ኔፊ** ፩፡፲፪–፲፰። ክርስቶስ ከአለም በፊት ነበረ፣ **፫ ኔፊ** ፳፯፡፭ (ዮሐ. ፮፡፳፪)። በመ ንፈስ ለአንተ እንደታየሁት ለህዝቤም በሥጋ እታያ ለሁ፣ **ኤተር** ፫፡፲፰–፲፯።

ሔኖክ ጌታን አየ እናም አካሄዱን ከእርሱ ጋር አደረገ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡፴፰–፴፱።

ውዱና ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የተመረጠው ተወዳጁ ልጄ፣ **ሙሴ** ፱፡፪። ጌታ እንዲህ አለ፡ ማንን ልስደድ? እና አንዱም እንደ ሰው ልጅ መለሰ፡ እዚህ አለሁ፣ እኔን ስደደኝ፣ **አብር.** ፫፡፳፯።

የክርስቶስ ክብር፣ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ፣ **ዘፀአ.** ፴፡፴፭–፴፰። ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች፣ **ኢሳ.** ፮፡፫ (፪ ኔፊ ፲፮፡፫)። የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻል፣ **ኢሳ.** ፷፡፩–፪።

የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ይመጣል፣ **ማቴ.** ፲፮፡፳፯። ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ፣ **ዮሐ.** ፲፯፡፭።

የእስራኤል ቅዱስ በታላቅ ክብር የሚነግስበት ጊዜ በፍጥነት ይመጣል፣ **፩ ኔፊ** ፳፪፡፳፱። የክብሩ ተስፋ ነበረን፣ *ያዕቆ.* ፱፡፱። የእግዚአብሔር ልጅ በክብሩ ይመጣል፣ **አልማ** ፭፡፶። ከመጀመሪያው ጀምሮ በክብሩ እስከሚመጣ ድረስ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች አብራራላቸው፣ **፫ ኔፊ** ፳፯፡፫።

ሐዋሪያቶቹ እንደ እኔ በክብር ይቆማሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፱)። የወ ልድን ክብር፣ በአብ ቀኝ በኩል ተመለከትን፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፲፱–፳፫። ዮሐንስ አየና ስለክ ብሬ ሙላት መሰከረ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፫፡፯ (ዮሐ. ፩፡፲፬)። ፊቱም ከጸሀይ ብርሀን በላይ የሚበራ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፶፣፡፫።

ክብሩ እኔ ላይ ነበር፣ እና ፊቱን አየሁኝ፣ **ሙሴ** ፩፡፩–፲፩። ስራዬ እና ክብሬ ይህም ነው፣ **ሙሴ** ፩፡፴፱።

የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት፣ አለቅነ ትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፱፡፯ (፪ ኔፊ ፲፱፡፯)። መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁ፣ ይላል እግ ዚአብሔር፣ **ዘካ.** ፪፡፲–፲፪ (ዘካ. ፲፡፡–፱)።

እግዚአብሔር ለኢየሱስ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ ሉቃ. ፩፡፡ ፴–፴፫። ክርስቶስ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል፣ ራዕ. ፲፩፡፡ ፲፭። ቅዱሳን ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሳሉ፣ ራዕ. ፳፡፡ ፬ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፡ ፳፫)።

በህዝቦቹ ፅድቅ ምክንያት ሰይጣን ኃይል አይኖ ረውም፣ ፮ ኔፊ ፳፪፡፡ ፳፯ (ራዕ. ፳፡፡ ፩–፫)።

በጽድቅነት ከሰዎች ጋር በምድር ላይ ለአ ንድ ሺ አመታት እኖራለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፡ ፲፩ (ት. እና ቃ. ፶፫፡፡ ፳፱–፴)። ለመንገስ መብት ያለው እስኪነግስ ድረስ፣ ባሉት ባለስልጣናት ተመሩ፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፡ ፳፪ (ሮሜ ፰ ቆሮ. ፲፭፡፡ ፳፭)።

ክርስቶስ እራሱም በምድር ላይ ይነግሳል፣ ኢ.አ. ፩፡፡ ፲ (ኢሳ. ፴፪፡፡ ፩)።

የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ፣ እንድ ንበት ዘንድ የሚገባን ስም ሌላ የለም፣ የሐዋ. ፬፡፡ ፲፪ (፪ ኔፊ ፴፩፡፡ ፳፩)። ሐዋሪያት ስለ ስሙ ለመናቅ ብቁ በመሆናቸው ተደሰቱ፣ የሐዋ. ፭፡፡ ፴፫–፴፪። ትእ ዛዞቱም ይህች ናት፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ፣ ፮ ዮሐ. ፫፡፡ ፳፫።

በጥምቀት የክርስቶስን ስም ለእራሳችሁ ለመ ውሰድ ፈቃደኛ እንደሆናችሁ መስክሩ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፡ ፲፫። የክርስቶስን ስም እንድትወስዱ እፈል ጋለሁ፣ ሞዛያ ፭፡፡ ፯–፲፪ (ሞዛያ ፩፡፡ ፲፩)። ማንኛ ውም የክርስቶስን ስም በእራሱ ለመውሰድ የፈ ለገ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያናት አባል ይሆ ናል፣ ሞዛያ ፳፭፡፡ ፳፫። የክርስቶስ እውነተኛ አማ ኞች የነበሩት በሙሉ የክርስቶስን ስም በእራሳቸው ወሰዱ፣ አልማ ፴፯፡፡ ፲፭። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለሚያምኑ፣ የሰማይ በር ለሁሉም ክፍት ነው፣ ሔለ. ፫፡፡ ፳፰። በመጨረሻው ቀን ለስሜ ታማኝ ሆኖ የሚ ገኝ የተባረከ ነው፣ ኤተር ፬፡፡ ፲፱። እነርሱ የወልድን ስም በላያቸው ላይ ለመውሰድ ፈቃደኞች ናቸው፣ ሞሮኒ ፬፡፡ ፣ (ት. እና ቃ. ፳፡፡ ፷፯)።

የክርስቶስ ስም በላያችሁ ላይ ውሰዱ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፡ ፳፩–፳፭።

ዳኛ፣ እርሱም ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳታል፣ መዝ. ፱፡፡ ፰ (፣ ኔፊ ፳፯፡፡ ፲፯)። በምድር ላይ ሊፈ ርድ ይመጣል፣ መዝ. ፺፯፡፡ ፲፣። በጻድቃንና በኃጢ አተኛ ላይ እግዚአብሔር ይፈርዳል፣ መክ. ፣፡፡ ፲፯። በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፣ ኢሳ. ፪፡፡ ፬ (ሚክ. ፬፡፡ ፣ ፪ ኔፊ ፲፪፡፡ ፬)። ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፣ ኢሳ. ፲፩፡፡ ፪–፬።

አብ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው፣ ዮሐ. ፭፡፡ ፳፪። እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው፣ ዮሐ. ፰፡፡ ፲፯። ሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብ ሔር የተወሰነ ነበር፣ የሐዋ. ፲፡፡ ፴፪ (፪ ጢሞ. ፬፡፡ ፩)። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ዘንድ የተ ሰወረውን ይፈርዳል፣ ሮሜ ፪፡፡ ፲፯። ሁላችን በክር ስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን፣ ሮሜ ፲፡፡ ፲ (፪ ቆሮ. ፭፡፡ ፣ አልማ ፲፪፡፡ ፲፪፣ ሞር. ፣፡፡ ፳፡ ፣፡፣ ኤተር ፲፪፡፡ ፴፰፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፡ ፭)።

ሁሉም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይመጣሉ፣ በውስጡ ባለው እውነትና ቅድስና መሰረት እንዲ ፈረድባቸው በፊቱ ይቆማሉ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፡ ፣፡ በስራ ዎች መሰረት በእግዚአብሔር ፊት ሊፈረድበት ይቆ ማሉ፣ አልማ ፭፡፡ ፲፭ (አልማ ፲፪፡፡ ፲፭፣ ፴፣፡፡ ፳፪፡፡ ፣ ኔፊ ፳፯፡፡ ፣፴)።

እግዚአብሔር እና ክርስቶስ ሁሉንም ይፈርዳሉ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፡ ፳፰።

ኢየሩሳሌም

በእዚህ ዘመን እስራኤል ውስጥ የምትገኝ ከተማ። በታሪካዊ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታላቅ አስፈላጊ ነት የነበራት ከተማ ናት። ለክርስቲያኖች፣ ለአይ ሁዶች፣ እና ለእስላሞች ከሁሉም የሚበልጡ አን ዳንድ ቅዱስ ቦታዎች በእዚህች ከተማ ውስጥ ይገ ኛሉ እናም በታማኝ አማኞች በየጊዜው ይጎበኛሉ። ብዙም ጊዜ ቅዱስ ከተማ ተብሎ ይጠራል።

አንድ ጊዜ ሳሌም ተብላ ትታወቅ የነበረችው (ዘፍጥ. ፲፬፡፡ ፲፰፣ መዝ. ፷፯፡፡ ፪)፣ ኢየሩሳሌም በዳዊት እስከተያዘች ድረስ የኢያቡሳውያን ከተማ ነበረች (ኢያ. ፣፡፡ ፣፣ ፲፭፡፡ ፰፣ ፪ ሳሙ. ፭፡፡ ፮–፯)። እስከዚያም ድረስ ከባህር በላይ ፳፪ ሜትር ከፍ ያለች እንደ ተራራ መሸሸጊያ የምትጠቅም ነበ ረች። ከሰሜን በስተቀር በሁሉም በኩል በጥልቅ ሸለቆዎች የተከበበች ነበረች።

በኢየሩሳሌም ንጉስ ዳዊት በነገሰበት ዘመን፣ የእ ንጨት ቤተመንግስት ውስጥ ይኖር ነበር። ነገር ግን፣ በሰለሞን ዘመን መንግስት፣ ህዝቡ ከተማዋን ለማስ ዋብ የንጉስን ቤተመንግስት እና ቤተመቅደስ ከመገ ንባት በተጨማሪ ብዙ ነገሮች አደረጉ።

የእስራኤል እና የይሁዳ መንግስቶች ከተከፋ ፈሉ በኋላ፣ ኢየሩሳሌም የይሁዳ ዋና ከተማ ነበ ረች። በሚወርሩ ሰራዊቶች ብዙ ጊዜ ተጠቅታ ነበር (፩ ነገሥ. ፲፬፡፡ ፳፭ ፪ ነገሥ. ፲፡፡ ፣፣ ፣፣ ፣፣ ፣፣–፣፱ ፳፩፡፡ ፣ ፳፭)። በሕዝቅያስ ስር፣ ኢየሩ ሳሌም የሀይማኖት ማምለኪያ ዋና ቦታ ሆነች ነገር ግን በ፣፣ ዓ.ዓ.፣ በ፣፳፯ ዓ.ዓ.፣ እና በ፳፭ ዓ.ዓ. በግማሽ ተደምስሳ ነበር። ሄሮድስ ግድግዳውን እና ቤተመቅደስን እንደገና ገነባ፣ ነገር ግን በ፷ ዓ.ም. በሙሉ ተደመሰሰች።

መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ ነበረ፣ ዘፍጥ. ፲፡፡ ፲፰ (ዕብ. ፯፡፡ ፩–፪)። ኢሳይያስ ኢየሩሳሌምን ጌጠኛ ልብሷን ልበሺ አላት፣ ኢሳ. ፶፪፡፡ ፩። ከኢ የሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣል፣ ሚክ. ፬፡፡ ፪።

ክርስቶስ ስለኢየሩሳሌም እጣ ፈንታ አዘነ፣ ማቴ. ፳፫፡፡ ፴፯–፴፱ (ሉቃ. ፲፣፡፡ ፴፩)። ኢየሩሳሌም የሕ ያው እግዚአብሔር ከተማ ነች፣ ዕብ. ፲፪፡፡ ፳፪።

ኢዮኤል

ኢየሩሳሌም ንስሀ ካልገባች ትጠፋለች፣ ፤ ፤ ፤

መፅሐፈ ኢዮብ፣ ምንም እንኳን ይህ መፅሐፍ ስለ ኢዮብ ስቃይ ቢሆንም፣ ለምን ኢዮብ (ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው) እንደሚሰቃይ እና ቤተሰቡን ወይም ንብረቱን እንደሚያጣ ሙሉ መልስ አይ ሰጥም። መፅሐፉም የሚሰቃየው ሰው ኃጢያተኛ ሰው እንዳልሆነም ይገልጻል። ጌታ ስቃይን አጋጣሚ ለመስጠት፣ ለመገሰጽ፣ ለማስተማር እናም ለመቅ ጣት ይጠቀምበታል (ት. እና ቃ. ፤ ፤)።

መፅሐፉ በአራት ክፍሎች ለመከፋፈል ይች ላል። ምዕራፍ –ፀ በኢዮብ እና በሶስት ጓደኞቹ መካ ከል ስለነበሩት ንግግሮች ይገልጻሉ። ምዕራፍ –ፀ የመጀመሪያ ሶስቱ ጓደኞቹ ከወቀሱበት ምክን ያት ሌላ ኢዮብን የኮነነው የአራተኛ ጓደኛው የኢሊ ዮን ንግግሮች የያዙ ናቸው። ምዕራፍ –ፀ መፅ ሐፉ ኢዮብን የህይወት መንገዱ ከመጀመሪያ ጀምሮ ጥሩ እንደሆነ በማረጋገጥ ይፈፅማል።

መፅሐፈ ኢዮብ ሰው የእግዚአብሔር ትክክል እውቀት ካለው እና በእግዚአብሔር ተቀባይነት ባለው ህይወት ከኖረ፣ በእርሱ ላይ የሚመጡትን ፈተናዎች በመልካም ለመቋቋም እንደሚችል ያስ ተምራል። የኢዮብ የማይወድቅ እምነት "ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ" በሚለው አባባል ይገለጻል (ኢዮብ ፤ ፤)። ኢዮብ በሕዝ ቅኤል ፤ ፤ በየያዕቆብ ፤ ፤ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፤ ፤ ውስጥ ተጠቅሷል።

ኤሊ። *ደግሞም ሳሙኤል፣ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ተመልከቱ*

ጌታ ሳሙኤልን ነቢይ እንዲሆን በጠራበት ጊዜ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሊቀ ካህን እና ዳኛ የነበረው (ፀ ሳሙ. ፤)። ጌታ የወንድ ልጆቹን ክፋት በመታገስ ስለተቀበለ ገሰጸው (ፀ ሳሙ. ፤ ፤–፤ ፤ ፤ ፤)።

ኤልሳቤጥ። *ደግሞም መጥምቁ ዮሐንስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የዘካሪያስ ባለቤት፣ የመ ጥምቁ ዮሐንስ እናት፣ እና የማሪያም ዘመድ (ሉቃ. ፀ፣ ፀ–፤)።

ኤልዛቤል። *ደግሞም አክዓብ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከፊኦኒካ ምድር የመጣች ክፉ ሴት። ኤልያስ ነቢይ በነበረበት ጊዜ የነገሰው የእስራኤል ንጉስ አክዓብ ባለቤት ነበረች (ፀ ነገሥ. ፤ ፤–፤)።

ከሌላው አንድ ድርጊት ሁሉ በላይ የኤልዛቤል ከአክዓብ ጋር መጋባቷ የሰሜን የእስራኤል መን ግስት ውድቀት ምክንያት ነበር፤ ኤልዛቤል እስ ራኤልን ያህዌህን ከማምለክ ከሁሉም በላይ መጥፎ የሆነ የጣዖት አምልኮትን አስተዋወቀች። (ፀ ነገሥ. ፤ ፤ ፤ ፤)።

ኤልዛቤልም ብዙ የእግዚአብሔርን ነቢያት አስገ ደለች፣ ፀ ነገሥ. ፤ ፤ ፤ ፤። ኤልዛቤል ኤልያስን ለመ ግደል ሞከረች፣ ፀ ነገሥ. ፤ ፤ ፤–፤። የኤልዛቤል ክፋት በመጥፎ ሞቷ ተፈጸመ፣ ፤ ነገሥ. ፤ ፤ ፤–፤ ፤ ፤

ሚልክያስ እርሱ እንደገና በኋለኛው ቀናት ስለመ መለሱ ተነበየ፣ ሚል. ፬፡፭–፮ (ቮ ኔፊ ፳፭፡፭)።

በ፲፰፻፯ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ቤተመቅ ደስ ውስጥ መጣ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲ቮ–፲፮።

ኤሎኽም። *እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ የሰማይ አባት ተመልከቱ*

ኤርምያስ። *ደግሞም ሰቆቃመ ኤርምያስ ተመልከቱ*

በካህናት ቤተሰብ ውስጥ የተወለደ እና በይሁዳ ውስጥ ከ፮፻፳፯ እስከ ፮፻፲፮ ም.ዓ. ድረስ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። በታላቆቹ ነቢያት፣ በሌሂ፣ በህዝቅኤል፣ በሆሴዕ፣ እና በዳንኤል ዘመን አቅራ ቢያ የኖረ ነበር።

በቅድመ ምድር ህይወት ነቢይ እንዲሆን ተሹሞ ነበር (ኤር. ፩፡፡–፭)። ወደ አርባ አመታት በሆኑት የነቢይነት አገልግሎት ጊዜዎቹ፣ ጣዖት ማምለ ክን እና ምግባረ መጥፎ የሆኑትን ከአይሁዳ ህዝ ቦች መካከል ስለማስወገድ አስተማረ (ኤር. ፲፡፩–፭፣ ፯፡፳–፲)። በየጊዜውም ተቃራኒ መሆንን እና ስድቦችን መፅናት ነበረበት (ኤር. ፳፡፪፣ ፴፮፡፣ ፲፰–፲፱፣ ፴፰፡፡)። ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ፣ ወደ ግብፅ ያመለጡት አይሁዶች ኤርምያስን ይዘውት ሄዱ (ኤር. ፵፫፡፩–፯)፣ በባህል መሰረትም በእዚያ ወግረው ገደሉት።

መፅሐፈ ኤርምያስ፣ ምዕራፍ ፩–፮ በኢዮስ ያስ ዘመነ መንግስት የሰጣቸው ትንቢቶችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፯–፳ የኢዮአቄም ዘመን ትንቢ ቶች ነበሩ። ምዕራፍ ፳፩–፴፰ ስለሴዴቅያስ ዘመነ መንግስት ይናገራሉ። ምዕራፍ ፴፱–፴፱ ትንቢቶ ችን የያዙና ኢየሩሳሌም ከወደቀች በኋላ ስለነበሩት ታሪካዊ ድርጊቶች ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፴፭ የጸሀ ፊው ባሮክ ህይወት እንደሚጠበቅ ለባሮክ የተሰጠ ውን ቃል ኪዳን ይይዛል። በመጨረሻም፣ ምዕራፍ ፴፮–፴፩ በውጪ ሀገሮች ላይ የተተነበዩ ትንቢቶች ናቸው። ምዕራፍ ፴፪ የታሪካዊ መጨረሻ ነው። አን ዳንዶቹ የኤርምያስ ትንቢቶች ኔፊ ከላባን ባገኘውን በነህስ ሰሌዳ ውስጥ ነበሩ (፩ ኔፊ ፭፡፣–፲፣)። ኤርም ያስም በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠ ቅሷል (፩ ኔፊ ፯፡፲፣ ሔሊ. ፰፡፳)።

መፅሐፈ ኤርምያስ ደግሞም የሰውን ቅድመ ምድራዊ ህይወት እንዳለ ይቀበላል እና ስለኤር ምያስ ቀድሞ መመረጥ ይናገራል (ኤር. ፩፡፡–፭)፣ እስራኤል ከመበተናቸው ስለመመለስ፣ አንደኛ ስለ ከተማና ሁለተኛ ስለቤተሰቡ፣ እስራኤልና ይሁዳ በደህንነት እና በሰላም ለመኖር በሚችሉበት አስደ ሳች መሬት ወደሆነችው ወደፅዮን የመሰብሰብ ትን ቢትን የያዘ (ኤር. ፲፡፲፪–፲፱)፤ እናም ብዙ “ዓሣ አጥማጆች” እና “አዳኞች” በመላክ ጌታ እስራ ኤልን ከሰሜን ሀገሮች የመሰብሰቡ ትንቢትን የያዘ ነው (ኤር. ፲፮፡፣፲፡–፳፩)። ይህ የኋለኛው ቀን ድር ጊት ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ካወጣበት በላይ ታላቅ የሆነ ድርጊት ይሆናል (ኤር. ፲፮፡፣፲፣–፲፭፣ ፳፣፡፣)።

ኤተር። *ደግሞም ያሬዳውያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የመጨረሻው የያሬዳ ውያን ነቢይ (ኤተር ፲፪፡፣ ፩–፪)።

መፅሐፈ ኤተር፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የያ ሬዳውያን ታሪክ መዝገብን የያዘ መፅሐፍ። ያሬዳው ያን ከሌሂ ህዝቦች ከብዙ መቶ አመቶች በፊት በምዕ ራብ ክፍለ አለም ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች። መፅ ሐፈ ኤተር በሊምሒ ህዝቦች ከተገኙት ሀያ አራት ሰሌዳዎች የተወሰዱ ነበሩ (ሞዛያ ፰፡፡–፱)።

ምዕራፍ ፩–፪ ያሬዳውያን በባቢሎን ግንብ መገ ንባት ጊዜ ቤታቸውን ትተው አሁን የአሜሪካ ክፍለ አህጉር ተብሎ ወደሚታወቀው እንዴት እንደሄዱ ይናገራሉ። ምዕራፍ ፫–፮ የያሬድ ወንድም የቅ ድመ ምድራዊ አዳኝን እንዳየና ያሬዳውያን በስ ምንት ጀልባዎች እንደተጓዙ ይገልጻል። ምዕራፍ ፯–፲፩ የያሬዳውያን ታሪክ ውስጥ በብዛት የሚገኘ ውን የክፋትነት ታሪክን ቀጠሉ። የኤተር መዝገብን ያዘጋጀው ሞሮኒ ምዕራፍን ፲፪–፲፫ን በእምነት ስለ ተደረጉ ታምራቶች እና ስለ ክርስቶስ እና ስለምት መጣው አዲስቷ ኢየሩሳሌም ጻፈ። ምዕራፍ ፲፬–፲፭ ያሬዳውያን እንዴት ታላቅ ሀገሮች እንደሆኑ ነገር ግን በኃጢያተኝነት ምክንያት በመጣ ህዝባዊ ጦር ነት እንደተደመሰሱ ይናገራሉ።

ኤጲስ ቆጶስ። *ደግሞም አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ*

“አለቃ”፣ የሀላፊነት ስፍራ ወይም ስልጣን ማለት ነው። ኤጲስ ቆጶስ በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የተ ሾመ ሀላፊነት ነው (ት. እና ቃ. ፳፡፡፲፣ ፲፯፡፣ ፲፱–፲፳)፣ እና ኤጲስ ቆጶስ የእስራኤል ዋና ዳኛ ነው (ት. እና ቃ. ፲፯፡፣ ፳፪፣ ፳፬)።

መንፈስ ቅዱስ እናንተን አልቃ አድርጓል፣ የሐዋ. ፳፡፣ ፳፡፡። የኤጲስ ቆጶሳት የመሆን ብቃት ተዘርዝረዋል፣ ፩ ጢሞ. ፫፡፣ ፩–፯ (ቲቶ ፩፡፣ ፯)።

ኤጲስ ቆጶስ ይሾም፣ ት. እና ቃ. ፳፡፡፡። ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እንደ ቤተክርስቲያና ኤጲስ ቆጶስ ሊያገለግል ነበር፣ ት. እና ቃ. ፴፩፡፣ ፱። ኤጲስ ቆጶስ የመንፈስ ስጦታዎችን ይገንዘብ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፣ ፳፣፣ ፡ ሊቀ ካህን በኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነት ለማስተዳደር ይችላል፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡፡፡፣ ፲፱ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፣ ፲፯)። ኤጲስ ቆጶስ በጌታ የተመ ደበ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፪። ኤጲስ ቆጶስ ደሀዎ ችን ይንከባከብ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፣ ፲፲፪። ኤጲስ ቆጶስ ስጋዊ ነገሮችን ሁሉ ያስተዳድር፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፣ ፡፡፡። ኤጲስ ቆጶስ የአሮናዊ ክህነት ፕሬዘደንት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፣ ፲፲–፲፡፡።

ኤፍሬም። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፤ ምናሴ፤ እስራኤል፤ ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የዮሴፍና የአስናት ሁለ ተኛ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፤፳፡፱–፴፤፳፡፳)። በባህል የሚደረገውን በመቃረን፣ ምሳሌ ሳይሆን ኤፍሬም የብኩርነት በረከትን ተቀበለ (ዘፍጥ. ፴፤፳፡፲–፳)። ኤፍሬም የኤፍሬም ጎሳ አባት ሆነ።

የኤፍሬም ጎሳ፣ ኤፍሬም የእስራኤል ብኩርና ተሰጠው (፩ ዜና ፭፡፩–፪፤ ኤር. ፴፩፡፱)። በመጨ ረሻው ቀናት እድላቸው እና ሀላፊነታቸው ክህነትን ለመሸከም፣ ዳግም የተመለሰውን ወንጌል በአለም ለመውሰድ፣ እና ለተበተነው እስራኤል ምልክት ማንሳት ነው (ኢሳ. ፲፩፡፲፪–፲፫፤ ፪ ኔፊ ፳፩፡፲፪–፲፫)። በመጨረሻው ቀናት ከሰሜን ሀገሮች የሚመ ለሱትን የኤፍሬም ልጆች የክብር አክሊል ይሰጧ ቸዋል (ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፳፯–፴፪)።

የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር፣ በ ፯፻ ም.ዓ. ከኢየሩሳሌም ወደ አሜሪካ ተመርተው የሄዱ ከኤፍ ሬም ጎሳዎች ቡድን አንዱ መዝገብ። ይህ የቡድን መዝገብ የኤፍሬም ወይም የጆሴፍ በትር፣ ወይም መፅሐፈ ሞርሞን ተብሎ ይጠራል። ይህ እና የይ ሁዳ በትር (መፅሐፍ ቅዱስ) የጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስን፣ የትንሳኤውን፣ እና በእነዚህ ሁለት የእስራ ኤል ቤት ክፍሎች መካከል የነበረ መለኮታዊ ስራ ውን በአንድነት ምስክር ይሰጣሉ።

ቅርንጫፍም ይሰበራል፣ እና ወደ ሩቅ አገርም ይወሰዳሉ እናም ሌላ የክርስቶስ ምስክር ይፅፋሉ፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፶፡ ፳፩–፳፯፣ ፴–፴፩። የይሁዳ በትር እና የዮሴፍ በትር አንድ ይሆናሉ፣ ሕዝ. ፴፯፡፲፭–፲፱።

በይሁዳ እና በዮሴፍ የተጻፈው በአንድነት ያድ ጋሉ፣ ፪ ኔፊ ፫፡፲፪። ጌታ ለብዙ ሀገሮች ተናገረ፣ ፪ ኔፊ ፳፱።

የኤፍሬም በትር ጽሁፍ ቁልፎች ለሞሮኒ ተሰጡ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፭።

እሁድ። የሰንበት ቀን *ተመልከቱ*

እህት። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ ሴት፣ ሴቶች፤ ወንድሞች፣ ወንድም ተመልከቱ*

እንደ ሰማይ አባታችን ልጆች፣ ሁሉም ወንዶች እና ሴቶች የመንፈስ ወንድሞችና እህቶች ናቸው። በቤተክርስቲያኗውስጥ፣ ሴት አባላት እና የቤተክ ርስቲያኗ ጓደኞች በብዙ ጊዜ እንደ እህት ነው የሚ ጠሩት።

የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወን ድሜ እኅቴም እናቴም ነው፣ ማቴ. ፲፪፡፡፶ (ማር. ፫፡፴፭)።

በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ወንድሞችን እና እህቶ ችን ለኃጢያታቸው መናዘዝን የሚመሩት ህግጋት ተዘርዝረዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡፲፫–፲፮።

እምነት፣ ማመን። *ደግሞም መታመን፤ ተስፋ፤ አለማመን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በአንድ ነገር ወይም በአንድ ሰው ላይ ማመን፤ በሰው ላይ ማመን ወይም አንድ ነገርን እንደ እው ነት መቀበል። ሰው በእግዚአብሔር መንግስት ለመ ዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን አለበት፣ (ት. እና ቃ. ፳፡፳፱)። በቅዱሣት መጻህፍት ላይ በብዙ ጊዜ እን ደሚጠቀሙበት፣ እምነት ለእርሱ ታዛዥ ለመሆን የሚመራ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነትን መጣል ነው። ሰውን ወደ ደህናነት ለመምራት እን ዲችል እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መመስረት አለበት። ደግሞም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን በአብ እግ ዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በክህነት ስልጣን ሀይል፣ እና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ በዳግም በተ መለሰው ወንጌል አስተያየት ላይ እምነት አላቸው።

እምነት ለማናያቸው፣ ቢሆንም እውነት ለሆኑት ነገሮች ተስፋ መጣልንም ይጠቃልላል (ዕብ. ፲፩፡ ፩፣ አልማ ፴፪፡፳፩፤ ኤተር ፲፪፡፮)። እምነት የሚነሳ ሳውም በእግዚአብሔር ስልጣን ተሰጥቷቸው በተ ላኩ ወንጌሉ ሲያስተምሩ በመስማትም ነው (ሮሜ ፲፡፲፬–፲፯)። ታምራቶች እምነትን አይፈጥሩም፣ ነገር ግን ጠንካራ እምነት የሚያድገው ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ታዛዥ በመሆን ነው። በሌላ አባ ባልም፣ እምነት የሚመጣው በጽድቅ ነው (አልማ ፴፪፡፳–፳፫፤ ኤተር ፲፪፡፱፣ ፮፣ ፲፪፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፱–፲፪)።

እውነተኛ እምነት ታምራቶችን፣ ራዕዮችን፣ ህልሞችን፣ መፈወስን፣ እና እግዚአብሔር ለቅ ዱሳኑ የሚሰጣቸውን ሁሉ ስጦታዎችን ያመጣል። በእምነት አንድ ሰው የኃጢያት ስርየትን እናም በመ ጨረሻም በእግዚአብሔር ፊት የመኖር ችሎታን ያገኛል። እምነት ማጣት ሰውን በኃጢያት ምክን ያት ወደሚመጣው ተስፋ መቁረጥ ይመራል (ሞሮኒ ፲፡፳፪)።

በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ፣ በነቢ ያቱም እመኑ፣ ፪ ዜና ፳፡፳። ዳንኤል አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ያልተጎዳው በእግዚአብሔር በማ መኑ ምክንያት ነው፣ ዳን. ፮፡፳፫። ጻድቅ ግን በእ ምነቱ በሕይወት ይኖራል፣ እንባ. ፪፡፬።

እንዳመንህ ይሁንልህ፣ ማቴ. ፰፡፲፫። እምነትሽ አድኖሻል አላት፣ ማቴ. ፱፡፳፪ (ማር. ፭፡፴፬፣ ሉቃ. ፯፡፶)። እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ፣ ማቴ. ፱፡፳፱። የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እም ነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁም ነገር የለም፣ ማቴ. ፲፯፡፳ (ሉቃ. ፲፯፡፮)። አምናችሁም በጸሎት የም ትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ፣ ማቴ. ፳፩፡፳፪። እመን ብቻ እንጂ አትፍራ፣ ማር. ፭፡፴፮። ለሚያ

ምን ሁሉ ይቻላል፣ ማር. ፱፡፳፫–፳፬። ያመነ የተ ጠመቀም ይድናል፣ ማር. ፲፮፡፲፮ (፪ ኔፊ ፪፡፱፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፴፫–፴፭)። እኔ ግን እምነትህ እንዳይ ጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፣ ሉቃ. ፳፪፡፴፪። በወ ልድ የሚያመን የዘላለም ሕይወት አለው፣ ዮሐ. ፫፡፲፮፣ ፲፰፣ ፴፮ (ዮሐ. ፭፡፳፬፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡፶)። እኛስ አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ አምነ ናል አውቀናልም፣ ዮሐ. ፮፡፳፱። የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፣ ዮሐ. ፲፩፡፳፭–፳፮። በክርስቶስ ስም በኩል የሆነው እምነት ይህን ሰው አጠናከረው፣ የሐዋ. ፫፡፲፮። እምነት የሚመ ጣው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ነው፣ ሮሜ ፣፡፣፲። ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፲፱። በፍቅር የሚሠራ በእ ምነት ነው፣ ገላ. ፭፡፮። ጻጋው በእምነት አድኖአ ችኋል፣ ኤፌ. ፪፡፰ (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫)። የእምነትን ጋሻ አንሡ፣ ኤፌ. ፮፡፲፮ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፮)። ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፯። እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገ ባለን፣ ዕብ. ፬፡፫። እምነትም ተስፋ ስለምናደር ገው ነገር የሚያስረግጥ ነው፣ ዕብ. ፲፩፡፩። ያለ እምነትም እርሱን ደስ ማሰኘት አይቻልም፣ ዕብ. ፲፩፡፮። ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው፣ ያዕ. ፪፡፲፯–፲፰፣ ፳፪። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ፣ እርስ በርሳችን እንዋደድ፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፳፫።

ጌታ ያዘዘኝንም ነገሮች አደርጋለሁ፣ ፩ ኔፊ ፫፡፯። ጌታ ለሰዎች ልጆች፣ በእርሱ ታማኝ እስ ከሆኑ ድረስ፣ ሁሉንም ነገሮች በፈቃዱ ለማድረግ ይችላል፣ ፩ ኔፊ ፯፡፲፪። በኳሱ ላይ ያሉት አመል ካቾች የሚሰሩት፣ ለእነርሱ በምንሰማቸው እምነት ነበር፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፳፰። መሲህ በእርሱ የሚያምኑ ትን አንዳቸውንም አያጠፋም፣ ፪ ኔፊ ፮፡፲፱። በእ ስራኤል ቅዱስ ፍፁም የሆነ እምነት ኖሯቸው ንስሀ ግቡና፣ በእርሱ ስም ተጠመቁ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፳፫። አይ ሁዶች ለማመን እስኪገደዱም ድረስ ይሰደዳሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፯። ክርስቶስ እንደ እምነታቸው በሰው ልጆች መካከል አስደናቂ ተአምራትን ይሰራል፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፣ (ኤተር ፲፪፡፲፪፣ ሞሮኒ ፯፡፳፯–፳፱፣ ፴፬–፴፮)። የኢኖስ ኃጢያት በክርስቶስ ባለው እም ነት ምክንያት ተሰረየ፣ ኢኖስ ፩፡፫–፰። ደህንነት በንስሃ እና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ካልሆነ በቀር አይመጣምና፣ ሞዛያ ፫፡፲፪። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካመናችሁ መፈፀማችሁን አረጋግጡ፣ ሞዛያ ፬፡፣፡። ልባችሁ በስሙ በማመን ተለውጧል፣ ሞዛያ ፭፡፯። በእምነታቸው መሰረት የእግዚአብሔር አገ ልጋዮቹ ፀሎት መልስ ያገኛል፣ ሞዛያ ፳፯፡፲፬። ወልድ በስሙ ለሚያምኑት መተላለፋቸውን በእ ራሱ ላይ ይወስዳል፣ አልማ ፲፩፡፴። በክርስቶስ ባለን እምነታችን መሰረት ጥንካሬን ስጠን፣ አልማ ፲፬፡፳፯። እግዚአብሔርን በእምነት ጥራ፣ አልማ ፳፪፡፲፯። ሳይገደድ በእግዚአብሔር ቃል ያመነ የተባረከ ነው፣ አልማ ፴፪፡፲፯። እምነት ስለ ነገ ሮች ፍፁም የሆነ እውቀት አለ ማለት አይደለም፣ አልማ ፴፪፡፳፩ (ኤተር ፲፪፡፮)። ከማመን በላይ የበ ለጠ ለመፈለግ ባትችሉም፣ . . . ይህ ፍላጎት በእና ንተ እንዲሰራ አድርጉ፣ አልማ ፴፪፡፳፯። ማደግ በጀመረ ጊዜ በእምነታችሁ ተንከባከቡት፣ አልማ ፴፫፡፳፫ (አልማ ፴፪፡፳፳)። የተጠበቁበት በእግ ዚአብሔር ሀይል ባላቸው ታላቅ እምነት የተነሳ እን ደነበር አስረድቷል፣ አልማ ፶፯፡፳፭–፳፮። በእም ነት የእግዚአብሔርን ልጅ ቢመለከቱ ሀያው ይሆ ናሉ፣ ሔሌ. ፰፡፲፭። በክርስቶስ ስም ካመናችሁም ንስሀ ትገባላችሁ፣ ሔሌ. ፲፩፡፲፫። በክርስቶስ የሚ ያምኑት ደግመው በአብ ያምናሉ፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፴፭። እናንተን እንድፈውላችሁ እምነታችሁ በቂ ነው፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፰። ማንም የያሬድ ወንድም እንዳደረ ገው በጌታ ያመነ አልነበረም፣ ኤተር ፫፡፲፭። እም ነት ተስፋ የምናደርጋቸው ነገሮች ነገር ግን የማና ያቸው ናቸው፣ ኤተር ፲፪፡፯። ተአምራትን ያመ ጡት ሁሉ እነዚህን ያመጡት በእምነት ነው፣ ኤተር ፲፪፡፲፪–፲፰። በእኔም እምነት ካላቸው፣ ከዚያም ደካማ የሆኑትን ለእነርሱ ጠንካራ እንዲሆኑ አደር ጋለሁ፣ ኤተር ፲፪፡፳፯–፳፰፣ ፴፯። ሞሮኒ ስለእ ምነት፣ ተስፋ፣ እና ልግስና አስተማረ፣ ሞሮኒ ፯። እንዲያምኑ ለማሳመን የሚያደርግ ሁሉም ነገር የተ ላከው በክርስቶስ ኃይል ነው፣ ሞሮኒ ፯፡፲፣፲፯–፲፱። በስሜ ትክክል የሆነውን ማንኛውንም ነገር በእም ነት እናገኛለን በማለት አብን ከጠየቃችሁት፤ እነሆ ለእናንተ ይሰማችኋል፣ ሞሮኒ ፯፡፳፯። በክርስቶስ እምነት ያላቸውን መልካሙን ነገር በሙሉ ይይ ዛሉ፣ ሞሮኒ ፯፡፳፰። በክርስቶስ አምናችሁ ከጠ የቃችሁት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እውነቱን ይገል ፅላችኋል፣ ሞሮኒ ፣፡፴።

በጌታ ቃላት የሚያምኑ ሁሉ በመንፈስ መገ ለጥ ይሰጣቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፮። ያለ እም ነት ምንም ማድረግ አትችልም፤ ስለዚህ በእምነት ጠይቅ፣ ት. እና ቃ. ፰፡፣፡። በጸሎታቸው ባላቸው እምነት መጠን ሊሰጣቸው ይገባል፣ ት. እና ቃ. ፣፡፴፯፣ ፴፪። በጌታ ስም የሚያምኑት የእግዚአብ ሔር ልጆች ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፴ (ዮሐ. ፩፡፲፪)። ሁሉም ሰዎች በእርሱ ስም እስከመጨረ ሻው መጽናት አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፭፣ ፳፱። በእምነት ጸሎት መንፈስ ቅዱስ ይሰጣች ኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፰። ለሌሎችም በሌሎች ቃላት እንዲያምኑ ተሰጥቷቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፰። የሚያምኑትን ምልክቶች ይከተሏቸ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፳፭ (ት. እና ቃ. ፳፫፡፯–፲፪)። እምነት የሚመጣው በምልክቶች አይደ ለም፣ ነገር ግን ምልክቶች የሚያምኑትን ይከተ ላል፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፱–፲፪። ወላጆች ልጆችን በክ ርስቶስ እምነት ያስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፭።

እውቀትን ፈልጉ፣ እንዲሁም በጥናትና ደግሞም በእምነት፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡፲፰።

የሚያምኑ፣ ንስሀ የሚገቡ፣ እና የሚጠመቁ መን ፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ፣ ሙሴ ፮፡፶፪። በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት የወንጌሉ የመጀመሪያ መሰረታዊ መመሪያ ነው፣ ኢ.ኦ. ፩፡፬።

እሳት። *ደግምም መንፈስ ቅዱስ፤ ምድር—ምድርን ማፅዳት፤ ሲያል፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ ተመልከቱ*

የማፅዳት፣ የማጥራት፣ ወይም የመቅደስ ምል ክት። እሳት እንደ እግዚአብሔር በቦታው እንደመ ገኘቱ ምልክት ሊያገለግል ይችላል።

አምላክህ እግዚአብሔር የሚበላ እሳት ነው፣ ዘዳግ. ፬፡፳፬። መላእክቱን አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል፣ መዝ. ፻፬፡፬። የሠራዊት ጌታ በምትበላም በእሳት ነበልባል ይጐበኛታል፣ ኢሳ. ፳፱፡፮ (፪ ኔፊ ፳፯፡፪)። ጌታ ከእሳት ጋር ይመ ጣል፣ ኢሳ. ፳፮፡፲፭። እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳት፣ ሚል. ፫፡፪ (፫ ኔፊ ፳፬፡፪፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፳፬)።

እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃች ኋል፣ ማቴ. ፫፡፲፩ (ሉቃ. ፫፡፲፮)።

ፃድቃናች ከእሳትም እንኳን ቢሆን ይድናሉ፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፯። በደለኞችን በእሳት ይጠፋሉ፣ ፪ ኔፊ ፴፡፲። ኔፊ እንዴት የእሳት እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንደምንቀበል ገለጸ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፲፫–፲፬ (፫ ኔፊ ፱፡፳፣ ፲፪፡፩፣ ፲፱፡፲፫፣ ኤተር ፲፪፡፲፬፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፩)።

በጥምቀት እናም በእሳት ሃጢያት እንደሚሰረይ አውጅ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፩። ታላቋና የርኩሰት ቤተክርስቲያን ወደ ሚንቀለቀል እሳት ትጣላለች፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፩። ምድርም በእሳትም እንኳን ቢሆን ትጠፋለች፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፴፪። የጌታ መገኘትም እሳት እንደሚያቀልጥ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፴፩።

አዳም በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል፣ ሙሴ ፮፡፳፮።

እሴይ። *ደግምም ዳዊት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የዳዊት አባት እና የክር ስቶስና የይሁዳ ንጉሶች ሁሉ ትውልድ።

የሩት ልጅ ኢዮቤድ የእሴይ አባት ነበር፣ ሩት ፬፡፲፯፣ ፳፪። የእሴይ ትውልዶች እስከ ይሁዳ ድረስ ተቆጥረዋል፣ ፩ ዜና ፪፡፲–፲፪ (ማቴ. ፩፡፭–፮)።

እስማኤል፣ የኔፊ አማች። *ደግምም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

የሌሂ ቤተሰብ ወደ ቃል ኪዳን ምድር በሚጓዙ በት ጊዜ አብሮ ከቤተሰቡ ጋር የተጓዘ የመፅሀፈ ሞር ሞን ሰው።

ኔፊና ወንድሞቹ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ እናም እስማኤልና ቤተሰቡ ሌሂንና ቤተሰቡን ወደ ቃል ኪዳን ምድር አብረዋቸው እንዲሄዱ አሳመኑ፣ ፩ ኔፊ ፯፡፪፣ ፪–፭። ሁለቱም ቤተሰቦች በጋብቻ ተጣ መሩ፣ ፩ ኔፊ ፲፮፡፲፣ ፲። እስማኤል ሞተ በምድረ በዳ ሞተ፣ ፩ ኔፊ ፲፮፡፴፬።

እስማኤል፣ የአብርሐም ልጅ። *ደግምም አብርሐም፤ አጋር ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአብርሐምና የሣራ ግብጻዊ ገረድ አጋር ልጅ (ዘፍጥ. ፲፮፡፲፩–፲፯)። ጌታ ለአብርሐምና ለአጋር እስማኤል የታላቅ ሀገሮች አባት እንደሚሆን ቃል ገባላቸው (ዘፍጥ. ፳፩፡፲–፳፩)።

ቃል ኪዳኑ የመጣው በእስማኤል ሳይሆን በይስ ሐቅ ነው፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፲፱–፳፩ (ገላ. ፬፡፳፪–፭፡፩)። እግዚአብሔር ፍሬያማ እንዲሆን እስማኤ ልን ባረከው፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፳። እስማኤል አብርሐ ምን ለመቅበር ረዳ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፯–፱። የእስማኤል አስራ ሁለት ወንድ ልጆች ስም ተሰጥተዋል፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፲፪–፲፮። እስማኤል ሞተ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፲፯–፲፰። ዓሳው የእስማኤል ሴት ልጅ ማዕሌትን ሚስት ትሆነው ዘንድ አገባ፣ ዘፍጥ. ፳፰፡፱።

እስራኤል። *ደግምም አብርሐም—የአብርሐም ዘር፤ የራስ ማድረግ፤ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ጌታ የእስራኤልን ስም ለይስሐቅ ልጅ እና ለአብርሐም የልጅ ልጅ ያዕ ቆብ ሰጠው (ዘፍጥ. ፴፪፡፳፰፣ ፴፭፡፲)። የእስራ ኤል ስም ያዕቆብን፣ ትውልዶቹን፣ ወይም በብ ሉይ ኪዳን ዘመናት እነዚያ ትውልዶች የነበራቸ ውን መንግስት ለመጠቆም የሚቻል ነው። (፪ ሳሙ. ፭፡፳፬፣ ፳፫፡፣ ፲)። ሙሴ የእስራኤል ልጆችን ከግ ብፅ ባርነት መርቶ ካስወጣ በኋላ (ዘፀአ. ፲–፲፱)፣ ለሶስት መቶ አመታት በመሳፍንት ተመርተው ነበር። ከንጉስ ሳኦል ጀምሮ፣ ንጉሶች አንድ የነ በረችውን እስራኤል አስሩ ጎሳዎች ከሮብዓም በማ መፅ የተለያየ ሀገር እስከ መሰረቱበት እስከ ሰለሞን ሞት ድረስ ገዙ። የእስራኤል መንግስት ከተከፋፈለ በኋላ፣ የሰሜን ጎሳዎች እንደ ትልቅነታቸው የእስ ራኤልን ስም ጠበቁ፣ የደቡብ መንግስት ግን ጅሁዳ ተብሎ ተጠራ። የከነዓን ምድርም ዛሬ እስራኤል ተብሎ ይጠራል። በሌላ አባባል፣ እስራኤል ማለት እውነተኛ የክርስቶስ ታማኞች ናቸው (ሮሜ ፲፡፩፣ ፲፩፡፯፣ ገላ. ፮፡፲፮፣ ኤፌ. ፪፡፲፪)።

የእስራኤል አስራ ሁለት ጎሳዎች፣ ስሙ ወደ እስ ራኤል የተቀየረው የአብርሐም የልጅ ልጅ ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ነበሩት። የእነርሱም ትውል ዶች የእስራኤል አስራ ጎሳዎች ወይም የእስራኤል

ልጆች ተብለው ተጠርተዋል። አስራ ሁለቱ ጎሳዎች እነዚህ ናቸው፥ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ እና ዛብሎን (የያዕቆብ እና የልያ ወንድ ልጆች)፤ ዳን እና ንፍታሌም (የያዕቆብ እና የባላ ወንድ ልጆች)፤ ጋድ እና አሴር (የያዕቆብ እና የዘ ልፋ ወንድ ልጆች)፤ ዮሴፍ እና ቢንያም (የያዕ ቆብ እና የራሔል ወንድ ልጆች) (ዘፍጥ. ፴፱፡ ፴፪–፴፡ ፴፰፣ ፴፭፡ ፲፯–፲፰)።

ያዕቆብ ለእያንዳንዱ የጎሳ መሪ ከመሞቱ በፊት በረከት ሰጠ (ዘፍጥ. ፵፱፡ ፩–፳፰)። ለዚህ ተጨ ማሪ ማስረጃ፣ የእያንዳንዱን የያዕቆብን ልጆች ስም ተመልከቱ።

የያዕቆብ የመጀመሪያ ባለቤት ልያ የበኩር ልጅ ሮቤል የበኩር በረከቱን እና የውርሱን ሁለት እጥፍ በስነ ምግባር ጉድለት አጣ (ዘፍጥ. ፴፱፡ ፫–፬)። ከእዚያም በኩርነትም ወደ ያዕቆብ ሁለተኛ ባለ ቤት ራሔል የበኩር ልጅ ዮሴፍ ሄደ(፩ ዜና ፭፡ ፩–፪)። ጎሳው እንደ ክህነት ስልጣን አገልጋዮች ለማገ ልገል የመረጡት ሌዊ በጎሳዎች ሁሉ መካከል ለማ ገልገል በነበራቸው ልዩ ጥሪ ምክንያት ውርስን አል ተቀበለም። ይህም የዮሴፍ ሁለት እጥፍ ክፍል እን ደተለያዩ ጎሳዎች በተቆጠሩት (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፴፰፡ ፭–፮ [ተጨማሪ]) በዮሴፍ ልጆች በኤፍሬም እና በምናሴ መካከል ተከፋፈለ። (፩ ዜና ፭፡ ፩፣ ኤር. ፴፩፡ ፱)።

የይሁዳ ጎሳዎች አባላት መሲህ እስከሚመጣ ድረስ ገዢዎች ነበሩ (ዘፍጥ. ፵፱፡ ፲፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፶፡ ፳፫)። በመጨረሻው ቀናት የኤፍሬም ጎሳ ዳግም የተመለሰውን ወንጌል ወደ አለም ለመውሰድ እና የተበተኑትን እስራኤል የመሰብሰብ እድል አላ ቸው (ዘዳግ. ፴፫፡ ፲፫–፲፯)። በኢየሱስ ክርስቶስ ወን ጌል ኤፍሬም የእስራኤል ጎሳዎችን አንድ ለማድረግ የመሪነት ሀላፊነት የሚኖርበት ጊዜ ይመጣል (ኢሳ. ፲፩፡ ፲፪–፲፫፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡ ፳፯–፴፩)።

የተበተኑት እስራኤል፣ ጌታ አስራ ሁለቱ ጎሳ ዎችን ጻድቅ ባለመሆናቸውና በማመጻቸው ምክ ንያት በተናቸው እናም አሰቃያቸው። ነገር ግን፣ ጌታ ይህን የተመረጡትን ህዝቦቹን በአለም ሀገ ሮች መካከል በመበተን እነዚያን ሀገሮች ለመባ ረክ ተጠቀመበት።

እናንተንም ከአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፣ ዘሌዋ. ፳፮፡ ፴፫። እግዚአብሔርም ብድአሕዛብ ሁሉ መካከል ይበትንሃል፣ ዘዳግ. ፳፰፡ ፳፭፣ ፴፯፣ ፳፱፡ ፲፬። በምድር መንግሥታት ሁሉ ዘንድ ለመበተን አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፣ ኤር. ፳፱፡ ፲፰–፲፱። የእስ ራኤልን ቤት በአሕዛብ ሁሉ መካከል እበትናለሁ፣ ዓሞ. ፱፡ ፱ (ዘካ. ፲፡ ፱)።

ኢየሱስ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች ተል ኳል፣ ማቴ. ፲፭፡ ፳፬። ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፣ ዮሐ. ፲፡ ፲፮።

እስራኤል በምድር ገፅ ላይ በሙሉ ትበተናለች፣ ፮ ኔፊ ፳፪፡ ፫–፳። ያዕቆብ ያን የለማው እና የጹር የወይራ ዛፍ ምሳሌ ዘረዘረ፣ ያዕቆ. ፭–፮። በተበ ተኑት ነገዶችም መካከል የአብ ስራ ይጀመራል፣ ፫ ኔፊ ፳፭፡ ፳፮።

የእስራኤል መሰብሰብ፣ የእስራኤል ቤት ክር ስቶስ ከመምጣቱ በፊት በመጨረሻው ቀን አብ ረው ይሰበሰባሉ (እ.አ. ፩፡ ፲)። ጌታ ህዝቡ እስራ ኤልን በሚቀበሉት ጊዜ እና ትእዛዛቱን ሲያከብሩ ይሰበሰባቸዋል።

ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል፥ ይመጣሉ፣ ኢሳ. ፭፡ ፳፮። በታላቅም ምሕረት እሰበስብሻ ለሁ፣ ኢሳ. ፶፬፡ ፯። እስራኤልና ይሁዳ ወደ ተሰ ጣቸው ምድር ይመለሳሉ፣ ኤር. ፴፡ ፫። ጌታ የእ ስራኤልን ቤት ከተበተኑባቸው አሕዛብ ዘንድ ይሰ በስባል፣ ሕዝ. ፳፯፡ ፳፭።

በዘመን ፍጻሜ ሁሉንም ነገሮች በክርስቶስ ይጠ ቀልላል፣ ኤፌ. ፩፡ ፲።

እስራኤል ከተበተበነ በኋላ፣ ይሰበሰባሉ፣ ፮ ኔፊ ፲፭፡ ፲፪–፲፯። ጌታ የእስራኤልንም ቤት በሙሉ ይሰ በስባል፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡ ፲፯ (ቮ ኔፊ ፲፯፡ ፭)። ከጨለ ማና ከጭጋግ ይወጣሉ፤ እና ጌታ አዳኛቸውና ቤዛ ቸው መሆኑን ያውቃሉ፣ ፮ ኔፊ ፳፪፡ ፲፪። እግዚአ ብሔር ልጆቹን ይሰበስባል እናም ይቆጥራል፣ ፮ ኔፊ ፳፪፡ ፳፭። የአህዛብ ሀገሮች እስራኤልን ወደ ርስ ታቸው ይሰበስባሉ፣ ፪ ኔፊ ፲፡ ፳ (ቮ ኔፊ ፲፯፡ ፱)። ህዝቤ እና ቃሌ እንደ አንድ ይሰበሰባሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፱፡ ፲ቮ–፲፱።

ሽማግሌዎች የተመረጡትን ለመሰብሰብ ተጠር ተዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፯ (ት. እና ቃ. ፴፱፡ ፲፭)። ምርጦቼን እሰበስባለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴ቮ፡ ፮። ህጌን እሰጣችሁ እና የመንፈስ ስጦታ እሰጣችሁ ዘንድ ተሰብሰቡ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፴፭–፴ቮ። የእስራ ኤል ቤት የሆኑትን ህዝቦቼን እንዲመለሱ አደርጋ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡ ፲፭። ቅዱሳንም ይመጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፶፮። ሙሴ የመሰብሰቢያ ቁልፎ ችን ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፲፣ ፡ ፲፭።

ጻቅነትና እውነት መሬትን ያድሳሉ እናም የጌታ ምርጥን ይሰበስባሉ፣ ሙሴ ፯፡ ፲ቮ። መሰብሰብ ቆሪ ቶች ባሉበት አሞራም ከሚሰበሰቡበት ጋር ተነጻ ጽሯል፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡ ፳፯።

የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች፣ የእስራኤል አስር ጎሳዎች የሰሜን የእስራኤል መንግስት የሰሩ ነበሩ እናም በ፯፻፲፪ ም.ዓ. በአሶር በምርኮ ተወሰዱ። በእዚያ ጊዜ ወደ “ሰሜን ሀገሮች ሄዱ” እናም ከሌ ሎች እውቀቶችም ጠፉ። በመጨረሻው ቀናትም ይመለሳሉ።

ሰሜንን መልሰህ አምጣ እለዋለሁ፣ ኢሳ. ፵፫፡ ፮። እነዚህ ከሰሜን ይመጣሉ፣ ኢሳ. ፵፱፡ ፲፪ (፩ ኔፊ

ፍ፩፡፲፪)። ይሁዳ እና እስራኤል በአንድም ሆነው ከሰሜን ምድር ይመጣሉ፣ **ኤር.** ፫፡፲፰። ከሰሜን ምድር እስራኤልን የሚያመጣው ጌታ ህያው ነው፣ **ኤር.** ፲፮፡፲፡–፲፯። ከሰሜን አገር አመጣቸዋለሁ፣ **ኤር.** ፴፩፡፰።

ኔፋውያን እና አይሁዶች የጠፉት የእስራኤል ጎሳዎችን ቃላት ያገኛሉ፣ ፪ **ኔፊ** ፳፱፡፲፪–፲፫። ራሴን ለጠፉት የእስራኤል ነገዶች ለማሳየት እሄዳለሁ፣ ፫ **ኔፊ** ፲፯፡፭። ወንጌሉ ለሚቀሩት ለእስራኤል ቤቶች ሲሰበክ፣ የጠፉት ጎሳዎች ወደ ቤት ወደ ርስት ምድር ይሰበሰባሉ፣ ፫ **ኔፊ** ፳፩፡፳፯–፳፱።

ሙሴ የእስራኤልን መሰብሰቢያ ቁልፎችን ለጆሴፍ ስሚዝና ለኦሊቨር ካውደሪ ሰጠ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፫፡፲፩። በሰሜን ሀግሮች ያሉት ጌታን ያስታውሳሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፫፡፳፯–፴፪።

ስለእስራኤል መሰብሰብ እናምናለን፣ **እ.አ.** ፩፡፲።

እስጢፋኖስ

እስጢፋኖስ በአዲስ ኪዳን ጊዜ ለአዳኝ እና ለቤተክርስቲያኑ ሰማዕት የነበረ ነበር። የእርሱ ስብከት፣ እስጢፋኖስ ሳንሀድሪን ፊት ሲከራከር በነበረበት ጊዜ እዚያ ለነበረው ጳውሎስ ታላቅ ስራ አስቀድሞ ያስመለከተ እና ምናልባት ተፅዕኖ የነበረው ነበር (የሐዋ. ፰፡፩፣ ፳፪፡፳)።

እስጢፋኖስ አስራ ሁለቱን ሐዋሪያት እንዲረዱ ከተመደቡት ሰባት ሰዎች አንዱ ነበር፣ **የሐዋ.** ፮፡፩–፰። እስጢፋኖስም ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር፣ **የሐዋ.** ፮፡፰። እስጢፋኖስ ከአይሁዶች ጋር ይከራከር ነበር፣ **የሐዋ.** ፮፡፱–፲። ተከሰሰ፣ እናም በሳንሀድሪን ፊት ለፍርድ ቀረበ፣ **የሐዋ.** ፮፡፲፩–፲፭። እስጢፋኖስ መከራከሪያውን አቀረበ፣ **የሐዋ.** ፯፡፪–፶፫። መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ፣ አብና ወልድን በራዕይ አያቸው፣ **የሐዋ.** ፯፡፶፭–፶፮። ለምስክሩም እስጢፋኖስ ሰማዕት ሆነ፣ **የሐዋ.** ፯፡፶፩–፰።

እረኛ። *ደግምም መልካሙ እረኛ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በምሳሌ፣ የጌታን ልጆች የሚንከባከብ ሰው።

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣ **መዝ.** ፳፫፡፩። እረኞች በጎችን ያሰማሩ፣ **ሕዝ.** ፴፬፡፪–፫።

እረፍት። *ደግምም ሰላም፣ የሰንበት ቀን ተመልከቱ*

ከእስቸጋሪ ሀሳብ እና ብጥበጣ በሰላምና በነጻነትን መደሰት። ጌታ በእዚህ ህይወት ጊዜ ለታማኝ ተከታዮቹ እንዲህ አይነት እረፍት እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቷል። ለእነርሱም በሚቀጥለው ህይወት የእረፍት ቦታ አዘጋጅቶላቸዋል።

እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፥ አሳርፍህማለሁ፣ **ዘፀአ.** ፴፫፡፲፬።

እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ፣ **ማቴ.** ፲፩፡፳፰–፳፱።

ወደ እረፍቱም ይገቡ ዘንድ በትጋት ሠራን፣ **ያዕቆ.** ፩፡፲ (ዕብ. ፱፡፩–፲፩)። ንስሃ የሚገቡ በእረፍቴ ይገባሉ፣ **አልማ** ፲፪፡፴፱። ንጹህ የሆኑ፣ እናም ወደ ጌታ እረፍት የገቡ በጣም ብዙ ነበሩ፣ **አልማ** ፲፫፡፲፪–፲፯። ገነት የእረፍት ቦታ ናት፣ **አልማ** ፴፡፲፪ (አልማ ፳፡፲፫)። በደሜ ልብሳቸውን ካጠቡት በስተቀር በእረፍቱ የሚገባ ማንም የለም፣ ፫ **ኔፊ** ፳፯፡፲፱።

ከእነሱ ጋር በአባቴ መንግስት አብረህ ታርፍ ዘንድ ለዚህ ህዝብ ንስሃን አውጅ፣ አሜን፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፲ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፲)። የሞቱትም ከሁሉም ስራዎቻቸው ያርፋሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፶፱፡፪ (ራዕ. ፲፡፡፲፫)። የጌታ እረፍት የክብሩ ሙላት ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፹፬፡፳፯።

እርሻ። *ደግምም አለም፣ የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ለማሳደጊያ ወይም ለመጋጫ የሚጠቀሙበት ምድር። ብዙ ጊዜም ይህ አለምንና ህዝቦቿን ያመለክታል።

እርሻውም ዓለም ነው፣ **ማቴ.** ፲፫፡፴፰። መን ግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፣ **ማቴ.** ፲፫፡፴፩።

ትልቅና ሰፊ የሆነን ሜዳ ተመለከትኩ፣ ፪ **ኔፊ** ፳፡፲፣ ፳፡ እርሻው ተዘጋጅቷል፣ **አልማ** ፳፯፡፭።

የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ ለመከር ዝግጁ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፬፡፬ (ት. እና ቃ. ፯፡፫፣ ፲፭፡፫፣ ፲፪፡፫፣ ፲፬፡፫፣ ፴፭፡፬፣ ፴፫፡፫፣ ፶)። እርሻው አለም ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፹፯፡፭–፪። እነዚህን መንግስቶች መሬት እንዳለው ሰው አመሳስላለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፳፡፶፭።

እርካታ። *ደግምም የተራራ ስብከት ተመልከቱ*

በተራራ ስብከት ውስጥ የተነጠረ እና መንፈሳዊ ጸባይን በመግለፅ ኢየሱስ የሰጣቸው የተከታተሉ ትምህርቶች (ማቴ. ፭፡፫–፲፪፣ ሉቃ. ፮፡፳–፳፫)። ክርስቶስ ስለተባረኩት የተናገራቸው አረፍተ ነገሮች የተዘጋጁት እያንዳንዱ አባባል ከዚያ በኋላ በሚመጣው ላይ እየገነባ በሚሄድበት መንገድ ነው። ክርስቶስ ስለተባረኩት የተናገራቸው አረፍተ ነገሮች በፍጹም እና በትክክለኛነት በ፫ **ኔፊ** ፲፪ ውስጥ ይገኛሉ።

እርግማን፣ እርግማኖች። *ደግምም ማራከስ፣ ኩነኔ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ እርግማን ጻድቅ ባለመሆን ምክንያት በነገሮች፣ በሰዎች፣ ወይም በህዝቦች ላይ ፍርዶችንና የእነዚህን ውጤቶች ሚያመ

ጣን መለኮታዊ ህግ መጠቀም ማለት ነው። እርግ ማኖች የእግዚአብሔር መለኮታዊ ፍቅርና ፍተህ መግለጫ ነው። እነዚህም በእግዚአብሔር እራሱ የሚነገሩ ወይም በባለስልጣን አገልጋዮቹ የሚታ ወቁ ናቸው። አንዳንዴ፣ የእርግማኑ ሙሉ ምክንያት የሚታወቁት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። በተጨማ ሪም፣ የተረገመ ሁኔታ የሚያጋጥማቸው እግዚአ ብሔርን በፈቃደኝነት በማይታዘዙት ነው እና በዚ ህም ከእግዚአብሔር መንፈስ እራሳቸውን ያርቃሉ።

ግለሰቦች ወይም ህዝቦች በኢየሱስ ክርስቶስ ባላ ቸው እምነትና ለወንጌሉ ህግጋትና ስነስርዓቶች ታዛዥነታቸው ምክንያት ጌታ እርግማንን ለማን ሳት ይችላል (አልማ ፳፫፡፲፯–፲፰፣ ፫ ኔፊ ፪፡፲፡–፲፯፣ እ.አ. ፩፡፫)።

እግዚአብሔር እባቡን አዳምና ሔዋንን በማታ ለሉ ረገመው፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፲፫–፲፭ (ሙሴ ፬፡፲፱–፳፩)። ለአዳም እና ሔዋን ጥቅም ምድሩ ተረገመ፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፲፯–፲፱ (ሙሴ ፬፡፳፫–፳፭)። ጌታ ቃየን አቤልን ስለገደለው ረገመው፣ **ዘፍጥ.** ፬፡፲፩–፲፯ (ሙሴ ፭፡፳፪–፳፬)። ጌታ ከነዓንን እና ትውል ዶቹን ረገመ፣ **ዘፍጥ.** ፱፡፳፭–፳፯ (ሙሴ ፯፡፮–፰፣ አብር. ፩፡፳፩–፳፯)። እስራኤል ለእግዚአብ ሔር ታዛዥ ከሆነች ትባረካለች፣ ታዛዥ ካልሆነች ትረገማለች፣ **ዘዳግ.** ፳፰ (ዘዳግ. ፳፱፡፲፰–፳፰)። ግያዝና ትውልዶቹ በናዕማን የለምጽ ደዌ ተረገሙ፣ ፪ ነገሥ. ፭፡፳–፳፯። ጌታ የጥንት እስራኤል ሀገ ርን አስራት እና ቁርባን ባለማቅረቧ ረገማት፣ **ሚል.** ፫፡፮–፲።

ኢየሱስ የወራት ዛፍን ረገማት እርሷም ሞተች፣ **ማር.** ፲፩፡፲፩–፲፬፣ ፳–፳፩። ኢየሱስ የኮራዚ፣ የቤተ ሳይዳን፣ እና የቅፍርናሆምን ከተማዎች ረገመ፣ **ሉቃ.** ፣፡፣–፲፫።

ላማናውያን ጌታን ስለማያዳምጡ፣ ከጌታ ፊት ተለዩ እናም ተረገሙ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፳–፳፬። ሁሉም ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ ተጋብዘዋል፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፴፫። ጌታ ዝሙትን የሚፈፅሙትን ሁሉ ይረ ግማል፣ **ያዕቆ.** ፪፡፴፩–፴፫። ኔፋውያን ንስሀ ካል ገቡ በስተቀር ከላማናውያን በላይ የሆነ እርግማን ያገኛሉ፣ **ያዕቆ.** ፫፡፫–፮። ጻበኛ ህዝቦች በእራሳ ቸው ላይ እርግማን ያመጣሉ፣ **አልማ** ፫፡፲፰–፲፱ (ዘዳግ. ፲፩፡፳፯–፳፰)። ቆሪሆር ህዝብን ከእግዚአ ብሔር መርቶ በመውሰዱ ተረገመ፣ **አልማ** ፴፡፴፫–፴። በህዝቦች እርኩስነት ምክንያት ጌታ የኔፋውያ ንን ምድሮችና ሀብቶች ረገመ፣ **ሔሌ.** ፲፫፡፳፪–፳፫ (፪ ኔፊ ፭፡፲፣ አልማ ፴፯፡፴፭)። ጌታ የያሬዳውያ ንን ክፉነት ረገመ፣ **ኤተር** ፱፡፳፰–፴፭። የክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ የአዳም እርግማንን ከትንሽ ልጆች ወሰደ፣ **ሞሮኒ** ፰፡፰–፲፪።

ከጌታ ዞር የሚሉ ይረገማሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፵፭፡፩። በአባቶች እና ልጆች መካከል በአንዳንድ የሚያስ ተሳስር ግንኙነት ከሌለ ምድር በእርግማን ትመታ ለች፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፰፡፲፰ (ሚል. ፬፡፩–፮)።

ስድብት፣ እርግማን የብልግና፣ የስድብ፣ ወይም የንቀት ቋንቋን መጠቀም ነው።

ሰዎች አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን አይስደቡ፣ **ዘፀአ.** ፳፩፡፲፯ (ማቴ. ፲፭፡፬)። የሕዝብህንም አለቃ አትርገመው፣ **ዘፀአ.** ፳፪፡፳፰ (መክ. ፣፡፳)። ወን ዶችና ሴቶች እግዚአብሔርን አይርገሙ፣ **ዘሌዋ.** ፳፬፡፲፫–፲፮።

ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደሚያውቅ ሲክድ ተራገመ፣ **ማቴ.** ፳፮፡፳፱–፴፬።

ክፉዎች ኔፋውያን እግዚአብሔርን ረገሙ እናም ለመሞት ፈለጉ፣ **ሞር.** ፪፡፲፬።

እናት። *ደግምም* ሔዋን፣ ቤተሰብ፣ ወላጆች *ተመልከቱ*

ልጆችን ለወለደች ወይም በጉዲፈቻ ለምታሳ ድግ ሴት የተሰጠ ቅዱስ ስም። እናቶች ለእግዚአ ብሔር መንፈሳዊ ልጆች ስጋዊ ሰውነት በመስጠት የእግዚአብሔርን አላማ ይረዳሉ።

አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ፥ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፳ (ሙሴ ፬፡፳፯)። አባትህንና እናትህን አክብር፣ **ዘፀአ.** ፳፡፲፪ (ኤፌ. ፮፡፩–፫፣ ሞዛያ ፲፫፡፳)። የእናት ህንም ሕግ አትተው፣ **ምሳ.** ፩፡፰። ሰነፍ ልጅ ግን እናቱን ይንቃል፣ **ምሳ.** ፲፭፡፳ (ምሳ. ፣፡፩)። እና ትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት፣ **ምሳ.** ፳፫፡፳፪። ልጆችዋ ይነሣሉ፥ ምስጋናዋንም ይናገራሉ፤ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል፣ **ምሳ.** ፴፩፡፳፰።

የኢየሱስ እናት በመስቀል አጠገብ ቆመች፣ **ዮሐ.** ፲፱፡፳፩–፳፮።

ሁለት ሺህ የላማናውያን ጀግናዎች በእናቶ ቻቸውም ተምረዋል፣ **አልማ** ፶፮፡፲፯ (አልማ ፶፯፡፳፩)።

በእዚህ ታላቅ የጻድቆች ስብሰባ ከተሰበሰቡት ታላቅ እና ሀይለኛ ከሆኑት መካከል የእኛ ግርማዊዋ እናት ሔዋን ነበረች፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፯፡፴፯–፴፱።

እንክርዳድ

እንደ ስንዴ የሚመስል ሳር ወይም መርዛዊ አረም። በሙሉ እስከሚያድግ ድረስ ከስንዴ መካ ከል ለመለየት አይቻልም (ማቴ. ፲፫፡፳፭–፴፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፩–፯)።

እንድርያስ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የስምዖን ጴጥሮስ ወን ድም እና በስጋዊ አገልግሎቱ ጊዜ ኢየሱስ ከተራ ቸው አስራ ሁለት ሐዋሪያት አንዱ (ማቴ. ፬፡፲፰–፲፱፣ ማር. ፩፡፲፯–፲፰፣ ፳፱)።

እውቀተኛነት፣ እውቀተኛዎች። *ደግምም መንፈስ፣ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ እውነት ተመልከቱ*

የመረዳት ችሎታ (እውቀተኝነት) ብዙ ትርጉሞች አሉት፣ ሶስቱም እነዚህ ናቸው፥ (፩) በሁለን ተና ውስጥ ላሉ ነገሮች በሙሉ ህይወት እና ብርሀን የሚሰጥ የእውነት ብርሀን ነው። ሁልጊዜም የኖረ ነው። (፪) እውቀተኛዎች የሚባለው ቃልም ስለእግዚአብሔር ልጆች መንፈስ የሚናገር ነው። (፫) ቅዱሣት መጻህፍት እውቀተኛነትን (የመረዳት ችሎታን) እኛ እንደመንፈስ ልጆች ከመፈጠራችን በፊት ስለነበሩት የመንፈስ መሰረታዊ ነገር ይና ገሩበታል።

እውቀተኛ ከእውቀተኛ ጋር ይጣበቃል፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፣ ፴። የመረዳት ችሎታ፣ የተፈጠረ ወይም የተሰራ አይደለም፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፱። እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ተፅዕኖ አካባቢያቸው ሁሉም የመረዳት ችሎታዎች እራሳቸውን የቻሉ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴። የእግዚአብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፯–፴፯። በዚህ ህይወት የምናገኘው ማንኛውም የመረዳት ችሎታ ደረጃ፣ ይህም ከሞት ስንነሳ አብሮን ይነ ሳል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፲፭–፲፱።

ጌታ እውቀተኛዎችን በሙሉ ይመራል፣ አብር. ፫፡፳፭። ጌታ አብርሐምን አለም ከመመሰረቱ በፊት የነበሩትን እውቀተኛዎችን አሳየው፣ አብር. ፫፡፳፪።

እውቀት። *ደግምም ማስተዋል፣ እውነት፣ ጥበብ ተመልከቱ*

በልዩም እንደሚያስተምረው ወይም እንደሚ ያረጋግጠው፣ እውነትን የማስተዋል እና የመረ ዳት ችሎታ።

እግዚአብሔር አዋቂ ነው፣ ፮ ሳሙ. ፪፡፫። ጌታ በእውቀት ፍጹም ነው፣ ኢዮብ ፴፯፡፲፮። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ምሳ. ፩፡፯። ጥቂት ቃልን የሚናገር አዋቂ ነው፣ ምሳ. ፲፯፡፳፯። ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላ ለች፣ ኢሳ. ፲፩፡፱ (፪ ኔፊ ፳፩፡፱፣ ፴፡፲፭)።

እውቀትን መክፈቻ ወሰዳችሁ፣ ሉቃ. ፲፩፡፶፪። የክርስቶስን ፍቅር እውቀትን ያሳልፋል፣ ኤፌ. ፫፡፲፱። ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ ፪ ጴጥ. ፩፡፭።

ኔፊ የእግዚአብሔርን ቸርነት ታላቅ ዕውቀት ነበ ረው፣ ፩ ኔፊ ፩፡፩። መድኃኒታቸውንም ያውቃሉ፣ ፪ ኔፊ ፯፡፲፩። ጻድቃንም ጻድቅነታቸው ፍፁም እውቀት ይኖራቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፡፡ መንፈስ እውቀት ይሰጣል፣ አልማ ፲፯፡፴፭። እውቀታችሁ በእዚያ ነገር ፍፁም ነው፣ አልማ ፴፪፡፴፡፡ ላማና ውያን ወደ አዳኛቸው እውነታዊ እውቀት ይመ ጣሉ፣ ሔለ. ፲፭፡፲፫። ይህ ከእግዚአብሔር መሆ ኑን ፍፁም በሆነ ዕውቀት ታውቃላችሁ፣ ሞሮኒ ፯፡፲፩–፲፯።

ቅዱሳን ታላቅ የእውቀት ሀብት ያገኛሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፲፡፡ ንጹህ እውቀት ነፍስን በታ ላቅ ያሳድጋል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡፴፪። የቅዱስ የክ ህነት ቁልፎችን የያዘ እውቀቶችን ለማግኘት ችግር አይኖረውም፣ ት. እና ቃ. ፻፳፯፡፲፩። ሰው እው ቀት በዚህ ህይወት ካገኘ፣ በሚመጣው አለም ውስጥ ተጨማሪ የተሻለ ሁኔታ ይኖረዋል፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡፲፡፡ በደንቆሮነት ለመዳን ለሰው አስቸጋሪ ነው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፭፡፯።

እውነት። *ደግሞም ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ እውቀተኛነት፣ እውቀተኛዎች፣ እውቀት ተመልከቱ*

ነገሮችን እንዳሉ፣ እናም እንደነበሩ፣ እናም እን ደሚሆኑ ማወቅ (ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፱)። እውነት ደግሞም ከሰማይ የሚመጣን ብርሀን እና ራዕይን ያጠቁማል።

እውነት ከምድር በቀለች፣ መዝ. ፹፭፡፲፩ (ሙሴ ፯፡፳፪)።

እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወ ጣችኋል፣ ዮሐ. ፰፡፴፪። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ ዮሐ. ፲፬፡፮። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፣ ፩ ዮሐ. ፩፡፰።

ጥፋተኞች እውነትን ከባድም አድርገው ይወስዱ ታል፣ ፩ ኔፊ ፲፮፡፪። ጻድቆች እውነትን ይወዳሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴። መንፈስ እውነቱን ይናገራል እንጂ አይዋሽም፣ ያዕቆ. ፬፡፲፫። አንተ የእውነት አምላክ ነህና፣ ለመዋሸት አትችልም፣ ኤተር ፫፡፲፪። የሁ ሉንም ነገር እውነታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታው ቁታላችሁ፣ ሞሮኒ ፲፡፭።

እውነት ለዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል፣ ት. እና ቃ. ፩፡፴፱። ፲በእውነት መንፈስ መረዳትን አግኝተሀል፣ ት. እና ቃ. ፮፡፲፭። መጽሐፈ ሞር ሞን እውነትን እና የእግዚአብሔርን ቃል ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯። አፅናኚ እውነትን ለማስተማር ተልኳል፣ ት. እና ቃ. ፯፡፲፡፡ በእውነት መንፈስ በኩል ቃልን የሚቀበል የሚቀበለው በእውነት መን ፈስ እንደሚሰበክ ነው፣ ት. እና ቃ. ፯፡፲፯–፳፪። በሰጠኋችሁ ራዕዮች በኩል እውነቶችን አውጁ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፫–፴። እውነት የሆነውም ብርሀን ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፴፭። የክርስቶስ ብርሀን የእ ውነት ብርሀን ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፮–፯፣ ፴፡ መንፈሴም እውነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፳፮። የመረዳት ችሎታ፣ ወይም የእውነት ብርሀን፣ የተ ፈጠረ አይደለም፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፱። የእግዚ አብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፣ ት. እና ቃ.

፯፲፡ ፴፯። ልጆቻችሁን በብርሀን እና በእውነት እን
ድታሳድጓቸው አዛችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፯፲፡ ፴።
አንድያ ልጄም በጸጋና በእውነት ተሞልቷል፣
ሙሴ ፭፡ ፮።

እዳ። *ደግምም ይቅርታ ማድረግ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደተጠቀሙ
በት፣ ለሌላ በገንዘብ ወይም በንብረት ባለእዳ መሆን
ተበዳሪን በባሪያነት እንደሆነ አይነት ያደርገዋል።
በሌላ አመላካከት፣ ኢየሱስ የበደሉንን ይቅር ካልን
በኋላ በደላችንን ይቅር እንዲያደርግልን፣ ወይም
በኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል ለኃጢ
ያታችን ክፍያ ከማድረግ እንዲለቀን እንድንጠይቅ
አስተምሯል (ማቴ. ፮፡ ፲፪፣ ፲ ፡ ፲፫፡ ፲፩)።

ኃጢአተኛ ይበደራል አይከፍልምም፣ መዝ.
፴፯፡ ፳፭። ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው፣ ምሳ.
፳፪፡ ፯።

ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፣ አንተስ ደግሞ ርህራሄ
አይኖርህም፣ ማቴ. ፲፰፡ ፳፫–፴፭። እርስ በርሳ
ችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፣
ሮሜ ፲፫፡ ፰።

ለሰማይ አባታችሁ ለዘለአለም እዳ አለባችሁ፣
ሞዛያ ፪፡ ፳፭–፳፱፣ ፴፡ ማንም ከጎረቤቱ የተበ
ደረ የተበደረውን ነገር በስምምነቱ መሰረት መመ
ለስ አለበት፣ ሞዛያ ፬፡ ፳፰፡ ፳፰።

የገባኸውን እዳ ክፈል፣ እናም ከባርነት ራስህን ነፃ
አውጣ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡ ፴፭። በጠላታችሁ በኩል
እዳ መግባታችሁ የተከለከለ ነው፣ ት. እና ቃ.
፳፬፡ ፳፯። እዳችሁን ሁሉ ክፈሉ፣ ት. እና ቃ.
፲፬፡ ፫፳፡ ፡ የጌታን ቤት ለመገንባት እዳ አትግቡ፣
ት. እና ቃ. ፲፲፭ ፡ ፲፫።

እድፍ፣ እድፍነት። *ደግምም ኃጢያተኛ፣ አመፃ፣ ኃጢያት፣ ንጹህ እና ርኩስ፣ እግዚአብሔርን የሚጠላ፣ ክፉ፣ ክፋት ተመልከቱ*

ለእግዚአብሔር በፈቃደኝነት ታዛዥ ባለመሆን
ምክንያት መንፈሳዊ ርኩስነት።

ጌታም የጽዮንን ቄነጃጅት እድፍ ያጥባል፣ ኢሳ.
፬፡ ፬ (፪ ኔፊ ፲፬፡ ፬)።

የእግዚአብሔር መንግስት የረከሰ አይደለም፣
፩ ኔፊ ፲፭ ፡ ፴፬ (አልማ ፯፡ ፳፭)። የረከሱትም አሁ
ንም ርኩሳን ይሆናሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፯ (ሞር. ፱፡ ፲፬)።
ልብሳችሁ በቆሻሻ ተበክሎ በእግዚአብሔር የፍርድ
ወንበር ፊት የምትቆሙ ከሆነ ማንኛችሁም ምን ይሰ
ማችኋል፣ አልማ ፭፡ ፳፪።

የረከሱት ረክሰው መቅረት አለባቸው፣
ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፴፭።

መቼ አርፋለሁ፣ እና ከእኔ ውስጥ ከወጡት እድፍ
እነጻለሁን፣ ሙሴ ፯፡ ፴፰።

እጅን መጫን። *ደግምም ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፣ መለየት፣ መሾም፣ ሹመት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተመልከቱ*

እንደ ክህነት ስነስርዓት ክፍል፣ እጆችን በሰው
ራስ ላይ መጫን። እንደ ሹመቶች፣ በረከቶች፣ ለታ
መሙት አገልግሎት የመስጠት፣ የቤተክርስቲያን
አባልነትን የማረጋገጥ፣ እና መንፈስ ቅዱስን የመ
ስጠት እይነት ብዙ የክህነት ስነስርዓቶች የሚከና
ወኑት እጆችን በመጫን ነው።

ሙሴ ጌታ እንዳዘዘው፣ እጁን በኢያሱ ራስ ላይ
ጫነ፣ ዘኁል. ፳፯፡ ፲፰፣ ፳፫–፳፫ (ዘዳግ. ፴፬፡ ፱)።
ኢየሱስም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ
ፈወሰ፣ ማር. ፮፡ ፭ (ሞር. ፱፡ ፳፬)። ሐዋሪያት
ሰባቶቱ ረዳቶቻቸው ላይ እጃቸውን ጫኑ፣ የሐዋ.
፮፡ ፭–፮። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው እጅን በመ
ጫን ነበር፣ የሐዋ. ፰፡ ፲፬–፲፯። ሐናንያ በሳውል
ላይ እጁን ጫነ እና አይኑ እንዲያይ አደረገ፣ የሐዋ.
፱፡ ፲፪፣ ፲፯–፲፰። ጳውሎስም እጁንም በላዩ ጭኖ
ፈወሰው፣ የሐዋ. ፳፰፡ ፰። ጳውሎስ ስለ ጥምቀቶ
ችና እጆችንም ስለ መጫን አስተማረ፣ ዕብ. ፮፡ ፪።

አልማ እጁን በመጫን ካህናትን እና ሽማግሌ
ዎችን ሾመ፣ አልማ ፮፡ ፩። ኢየሱስ ደቀ መዛሙ
ርቱ እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ለመስ
ጠት ኃይል ሰጣቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፴፯–፴፯። እጃ
ችሁን በምትጭኑበት ላይ መንፈስ ቅዱስን ለመስ
ጠት ስልጣን ይኖራችኋል፣ ሞሮኒ ፪፡ ፪።

ሽማግሌዎችም እጆቻቸውን ልጆቹ ላይ ይጫኑ፣
ት. እና ቃ. ፭፡ ፫። እጆችን በመጫን መንፈስ ቅዱ
ስን ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፮ (እ.አ. ፩፡ ፱)።
ሽማግሌዎች እጆቻቸውን በታመሙት ላይ ይጫኑ፣
ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፵፬ (ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፱)። ልጆ
ችም ከጥምቀት በኋላ የእጆችን ጭነት ይቀበሉ፣
ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፳፯። ክህነት ለመቀበል የሚቻ
ለው እጅን በመጫን ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡ ፯–፲፯።

እግዚአብሔር፣ አምላክ። *ደግምም መንፈስ ቅዱስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የሰማይ አባት፣ ጌታ ተመልከቱ*

በአምላክ ውስጥ ሶስት የተለያዩ ግለሰቦች አሉ፥
እግዚአብሔር፣ የዘለላለም አባት፣ ልጁ ኢየሱስ
ክርስቶስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ። በእያንዳንዱም እና
ምናለን (እ.አ. ፩፡ ፩)። ከኋለኛው ቀን ራዕይ አብና
ወልድ ለመዳሰስ የሚቻል የስጋና የአጥንት ሰው
ነት እንዳላቸው እና መንፈስ ቅዱስ የስጋና የአጥ
ንት ሰውነት የሌለው የመንፈስ ሰው እንደሆነ ተም
ረናል (ት. እና ቃ. ፻፴፡ ፳፪–፳፫)። እነዚህ ሶስት
ሰዎች በፍጹም ህብረት እና በአላማና በትምህርት
ስምምነት የተዋህዱ ናቸው (ዮሐ. ፲፯፡ ፳፩–፳፫፣
፪ ኔፊ ፴፩፡ ፳፩፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፳፯፣ ፴፯)።

እግዚአብሔር አብ፣ ይህም በአጠቃላይ በእግ

ዚአብሔር ርዕስ የሚጠቀስ አብ፣ ወይም ኤሎሂም ነው። አብ ተብሎ የተጠራበት ምክንያት የመ ንፈሳችን አባት ስለሆነ ነው (ዘኁል. ፲፮፡፳፯፤ ፳፯፡፲፮፣ ሚል. ፪፡፲፣ ማቴ. ፮፡፱፤ ኤፌ. ፬፡፮፤ ዕብ. ፲፪፡፱)። እግዚአብሔር አብ የሁለንተና ታላቅ መሪ ነው። እርሱም ሀያል (ዘፍጥ. ፲፰፡፲፬፤ አልማ ፳፯፡፴፭፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፩–፫)፣ ሁሉን የሚያ ውቅ፣ (ማቴ. ፮፡፰፤ ፪ ኔፊ ፪፡፳፬)፣ እናም በመን ፈሱም በሁሉም ቦታ የሚገኝ ነው (መዝ. ፻፴፱፡፯–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፹፰፡፭–፲፫፣ ፵፭)። ሰውን ከተ ፈጠሩት ሌሎች ነገሮች ሁሉ የሚለየው ልዩ አይ ነት ግንኙነት በሰው ዘርና በእግዚአብሔር መካከል አለ፥ ወንዶች እና ሴቶች የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች ናቸው (መዝ. ፹፪፡፮፤ ፩ ዮሐ. ፫፡፩–፫፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፯–፲፰)።

አብ እግዚአብሔር ወደ ሰው መጥቶ የታየ በት ወይም የተናገረበት የተመዘገቡ ጥቂት ጊዜ ዎች አሉ። ቅዱሣት መጻህፍት ከአዳም እና ከሔ ዋን ጋር ተነጋገረ (ሙሴ ፬፡፲፩–፴፩) እናም ኢየሱ ስን በተለያዩ ሁኔታዎች አስተዋወቀ ይላሉ (ማቴ. ፫፡፲፯፣ ፲፯፡፭፣ ፡ ዮሐ. ፲፪፡፳፭–፳፱፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፫–፯)። በእስጢፋኖስ (የሐዋ. ፯፡፶፭–፶፮) እና በጆሴፍ ስሚዝ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯) ታየ። በኋላም ለጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን ታየ (ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፣ ፳፫)። እግዚአብሔርን ለሚወዱና እራሳቸውን ለሚ ያጸዱ፣ እግዚአብሔር እንዳንዴ የማየትና ለእራሳ ቸው እግዚአብሔር እንደሆነ የማወቅ እድል ይሰጣል (ማቴ. ፭፡፳፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፳፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፲፯–፲፲፣ ፶፫፡፩)።

አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ፣ ማር. ፲፭፡፴፬። እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው፣ የሐዋ. ፲፯፡፲፯። እኛ የእግዚአብሔር ዘመ ዶች ነን፣ የሐዋ. ፲፯፡፳፱–፳፱።

ቅዱስ ቁርባንህን ለልዑልህ ለማቅርብ አስታ ውስ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲–፲፪።

ሔኖክ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን መንፈሶች አየ፣ ሙሴ ፮፡፴፮። ስሙ የቅድስና ሰው ነው፣ ሙሴ ፮፡፶፯።

እግዚአብሔር ወልድ፣ ያህዌህ ተብሎ የሚ ታወቀው አምላክ ወልድ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ኢሳ. ፲፪፡፪፣ ፵፫፡፲፩፣ ፵፱፡፳፯፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፩–፬፣ ፩ ጢሞ. ፩፡፩፣ ራዕ. ፩፡፳፣ ፪ ኔፊ ፳፪፡፪)። ኢየሱስ በአብ አመራር ስር ይሰራል እናም ከእር ሱም ጋር በፍጹም ስምምነት ላይ ነው። የሰው ዘር በሙሉ የእርሱ ወንድሞችና እህቶች ናቸው፣ ምክ ንያቱም እርሱ ለኤሎሂም መንፈስ ልጆች ታላቅ ነውና። አንዳንድ ቅዱሣት መጻህፍት እርሱን እግ ዚአብሔር ብለው ይጠሩታል። ለምሳሌ፣ ቅዱሣት መጻህፍት “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ” (ዘፍጥ. ፩፡፩) ይላል፣ ነገር ግን ፈጣሪው በእግዚአብሔር አብ አመራር ስር ኢየ ሱስ ነበር (ዮሐ. ፩፡፩–፫፣ ፲፣ ፲፬፣ ዕብ. ፩፡፩–፪)።

ጌታ እራሱን እንደ እኔ አስተዋወቀ፣ ዘፀአ. ፫፡፲፣–፲፭። እኔ፥ እኔ እግዚአብሔር [ያህዌህ] ነኝ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም፣ ኢሳ. ፵፣፡፲፩ (ኢሳ. ፵፭፡፳፩)።

እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፣ ዮሐ. ፰፡፲፪። አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ፣ ዮሐ. ፰፡፶፰።

ጌታ በሰዎች መካከል በጭቃ ሰውነቱ ያገለግላል፣ ሞዛያ ፫፡፭–፯። አቢናዲ ክርስቶስ አብና ወልድ እን ደሆነ ገለጸ፣ ሞዛያ ፲፭፡፩–፬ (ኤተር ፫፡፲፬)። ጌታ ለያሬድ ወንድም ታየ፣ ኤተር ፫። የጌታህን እናም የአምላክህን የክርስቶስን ቃል አድምጥ፣ ሞሮኒ ፰፡፰። ያህዌህ ለህያዋን እና ለሙታን ዘለዓለማዊ ዳኛ ነው፣ ሞሮኒ ፣፡፴፬።

ኢየሱስ ለጆሴፍ ስሚዝና ለስድኒ ሪግደን ተታየ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፣ ፳፫። ጌታ ያህዌህ በክርትላንድ ቤተመቅደስ ታየ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፩–፴።

ያህዌህ ለአብርሐም ተናገረ፣ አብር. ፩፡፲፯–፲፱። ኢየሱስ ለጆሴፍ ስሚዝ ታየ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነው እናም ከሌሎች ስሞችና ርዕሶች መካከል፣ መንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ፣ እና የእግዚ አብሔር መንፈስ ተብሎ ይጠራል። በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ፣ ሰው የእግዚአብሔር አብን ፍላጎት ለማ ወቅ እና ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ለማወቅ ይችላል (፩ ቆሮ. ፲፪፡፫)።

መንፈስ ቅዱስ ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተ ምራችኋል፣ ሉቃ. ፲፪፡፲፪። መንፈስ ቅዱስ አፅ ናኝ ነው፣ ዮሐ. ፲፬፡፳፯ (ዮሐ. ፲፯፡፲–፲፭)። ኢየ ሱስ ለሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ትእዛዛትን ሰጣ ቸው፣ የሐዋ. ፩፡፪። መንፈስ ስለእግዚአብ ሔርና ስለክርስቶስ ይመሰክራል፣ የሐዋ. ፭፡፳፱–፴፪ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፫)። መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ይመ ሰክርልናል፣ ዕብ. ፣፡፣–፣፯።

የሁሉንም ነገር እውነታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታውቁታላችሁ፣ ሞሮኒ ፣፡፭።

መንፈስ ቅዱስ የራዕይ መንፈስ ነው፣ ት. እና ቃ. ፰፡፪–፫ (ት. እና ቃ. ፰፰፡፴)።

እግዚአብሔርን የሚጠላ፣ *ደግሞም*

ኃጢያተኛ፣ አመፃ፣ ኃጢያት፣ እድፍ፣ እድፍነት፣ ክፉ፣ ክፋት *ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር ፍላጎት ወይም ትእዛዛት መሰ ረት ያልሆነ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር፣ ክፉ እና ያልተቀደሰ።

የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች፣ መዝ. ፩፡፮። ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ፣ ፩ ጴጥ. ፬፡፲፰።

ኃጢአተኝነትን በሙሉ ለእራሳችሁ ካዱ፣ ሞሮኒ ፲፡ ፴፪።

በጎጥያተኞቹ ላይ በቀል በቶሎ መጥቷል፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፳፪። እግዚአብሔርን በሚጠሉት መካከል ድምጹ አለተነሳም፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፳።

አሜጋ። አልፋ እና አሜጋ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

አምነር። *ደግምም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞዛያ ልጅ። አምነር ከወንድሞቹ ጋር ለላማናውያን ለመስበክ ሄደ (ሞዛያ ፳፯፡ ፲–፲፭፣ ፴፡–፴፯፣ ፳፯፡ ፭–፱)።

አምኒ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በ፲፻፲፰ ም.ዓ. ውስጥ የተጻፈ የኔፋውያን መዝገብ ጠባቂ (ዮሪም ፭፡ ፲፭፣ አምኒ ፩፡ ፩–፲)።

መፅሐፈ አምኒ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ከኔፊ ትንሽ ሰሌዳዎች የተተረጎመ መፅሐፍ። በኔፋውያን እና በላማናውያን መካከል ስለነበረው ጦርነት ታሪክ የሚነግረው መፅሀፍ አንድ ምዕራፍ ብቻ ነበረው። አምኒ የመፅሀፉን የመጀመሪያ ሶስት ቁጥሮችን ብቻ ጽፏል። ከእዚያም ሰሌዳዎቹ ወደ አማሮን፣ ቼሚሽ፣ አቢናዶም፣ እና በመጨረሻም አማሌቂ ተሰጥተው ነበር። አማሌቂ ሰሌዳዎችን የዛራሔምላ ንጉስ ለሆነው ንጉስ ቢንያም አሳልፎ ሰጠ።

አሪት ዘጉልቁ። *ደግምም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን አራተኛ መፅሐፍ። ሙሴ አሪት ዘጉልቁን ጽፏል። አሪት ዘጉልቁ ከሲና ተራራ እስከ ከነዓን ድንበር በሞአብ ሜዳዎች የእስራኤልን ጉዞ ታሪክ ይነግራል። የሚያስተምረው አንዱ አስፈላጊ ትምህርት ቢኖር የእግዚአብሔር ህዝብ በውጤታ ማነት ለመቀጠል በእምነት፣ የእርሱን ቃል ኪዳን በማመን መሄድ እንዳለባቸው ነው። ትእዛዝን ባለ ማክበር እግዚአብሔር እስራኤልን ስለቀጣበት ይና ገራል እናም ስለእስራኤል ህግጋት መረጃዎች ይሰ ጣል። የመፅሐፉ ስም የመጣው በአጠቃላይ የህዝቡ ቆጠራ ላይ በነበሩት የህዝቡ ቁጥሮች ነው (ዘጉል. ፩–፪፣ ፳፮)።

ምዕራፍ ፩–፲ ስለእስራኤላውያን ከሲና ለመሄድ ዝግጅት ይናገራሉ። ምዕራፍ ፲፩–፲፬ ጉዞውን፣ ወደ ከነዓን ሰላዮችን ስለመላክ፣ እና እስራኤል ወደ ቃል ኪዳን ምድር ለመግባት እምቢ ስለማለታቸው ይገ ልጻሉ። ምዕራፍ ፲፭–፲፱ የተለያዩ ህግጋትን እና የታ ሪክ ድርጊቶችን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፳–፴፮ ህዝቡ በምድረበዳ ያሳለፉበት የመጨረሻ አመት ታሪክ ናቸው።

አሪት ዘሌዋውያን። *ደግምም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

በእስራኤል ውስጥ ስላሉት የካህናት ሀላፊነቶች የሚነግር የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። የእግዚአብሔ ርን ቅዱስነት እናም ህዝቦቹ ቅዱስ ለመሆን በሚ ችሉበት ህግ ላይ ያተኩራል። አላማውም የሙሴን ህግ የስነምግባር አስተያየት እና ሀይማኖታዊ እው ነቶችን በቅድመ ተከተል ለማስተማር ነው። ሙሴ አሪት ዘሌዋውያንን ጽፏል።

ምዕራፍ ፩–፯ የመስዋዕት ስነስርዓቶችን ይገ ልጻሉ። ምዕራፍ ፰–፲ ካህናትን ለመቀደስ የሚደ ረጉትን ቅድመ ተከተል ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፲፩ ምን መበላት እንደሚቻልና እንደማይበላ እናም ምን ንጹህ እንደሆነና እንዳልሆነ ይገልጻል። ምዕ ራፍ ፲፪ ሴቶች ልጆች ከወለዱ በኋላ ስለሚያደር ጉት ይወያያል። ምዕራፍ ፲፫–፲፭ ከርኩስነት ስነስ ርዓቶች ጋር ስለሚገናኙ ህግጋት ይናገራሉ። ምዕ ራፍ ፲፮ በማስተስረያ ቀን ስለሚከናወኑት ቅድመ ተከተል ያይዘ ነው። ምዕራፍ ፲፯–፳፮ ስለሀይማኖ ታዊ እና ማህበራዊ ስነስርዓት ጋር የተገናኙ የህግጋት ደንቦችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፳፯ እስራኤልን ምርታቸውን፣ መንጋዎቻቸውን፣ እና ከብቶቻቸ ውን ለጌታ እንዲቀድሱ ጌታ ያዘዛቸውን ይገልጻል።

አሪት ዘዳግም። *ደግምም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን አምስተኛ መፅሐፍ።

አሪት ዘዳግም የሙሴን የመጨረሻ ሶስት ንግግ ሮችን ይይዛል፣ እነዚህንም የሰጣቸው በሞአብ ሜዳ ላይ ከመቀየሩ በፊት ነበር። የመጀመሪያው ንግግር (ምዕራፍ ፩–፬) ማስተዋወቂያ ነው። ሁለተኛው ንግ ግር (ምዕራፍ ፭–፳፮) ሁለት ክፍሎች አሏቸው፥ ምዕራፍ ፭–፲፩—አስሩ ትእዛዛትና በእነርሱ እንዴት በየቀኑ እንደሚጠቀመባቸው፤ እናም ምዕራፍ ፲፪–፳፮። ሶስተኛው ንግግሮች (ምዕራፍ ፳፯–፴) በእስ ራኤልና በእግዚአብሔር መካከል የተገባው የክብር ቃል ኪዳን የታደሰበትን እና ታዛዥነትን የሚከተሉ በረከቶችንና ታዛዥ አለመሆንን የሚከተሉ እርግ ማንን ይይዛል። ምዕራፍ ፴፩–፴፡ ህጉ ለሌዋውያን የተሰጠበትን፣ የሙሴን መዝሙርና የመጨረሻ በረ ከት፣ እና የሙሴ መሄድን ይገልጻል።

አሪት ዘፀአት። *ደግምም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እስራኤላዊያን ከግብፅ የወ ጡበትን የሚገልፅ በሙሴ የተጻፈ መፅሐፍ። በአሪት ዘጸዓት ውስጥ በመጀመሪያ የተጻፉት የእስራኤል ታሪክ በሶስት ክፍሎች ለመከፋፈል ይችላሉ፥ (፩) የህዝቦቹ ለግብፅ ባሪያነት፣ (፪) በሙሴ አመራር ስር ከግብፅ የወጡበት፣ እና (፫) በሀይማኖት ህይወታ

ቸው እና በፖለቲካ ህይወታቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ስለወሰኑበት።

የመጀመሪያው ክፍል፣ ዘጸአት ፩፡፩–፲፭፡፳፭፣ እስራኤል በግብፅ መጨቆንን፤ የሙሴ የመጀመሪያ ታሪክ እና ጥሪ፤ ተነቅለው መሄዳቸው እና የፋሲካ መጀመር፤ እናም ወደ ቀይ ባህር ጉዞአቸው፣ የፈርዖን ሰራዊት ጥፋት፣ እና የሙሴ የድል መዝሙር።

ሁለተኛው ክፍል፣ ምጽአት ፲፭፡፳፪–፲፰፡፲፯፣ ስለእስራኤል ቤዛነት እና ከቀይ ባህር ወደ ሲና በተጓዙበት የደረሱ ነገሮች፤ የማራ ውሀዎች መራራ ነት፣ ድርጭቶች እና መና መሰጠታቸው፣ የሰም በት መከበር፣ በራፊዲም የተሰጠው የተአምራት የውሀ ስጦታ፣ እና ከአማሌቂውያን ጋር የተዋጉ በትን፤ ዮትር ወደሰፈሩበት መሄዱ እና ስለህዝባዊ መንግስት ስለነበረው ምክር ይናገራሉ።

ሶስተኛው ክፍል፣ ምዕራፍ ፲፱–፳፣ እስራኤል በሲና በነበራቸው የክብር ድርጊቶች ለእግዚአብ ሔር አገልግሎት ስለመቀደሳቸው ይናገራሉ። ጌታ ህዝቡን እንደ ካህናትና ቅዱስ ሀገሮች መንግስት ከፋፈላቸው፤ አስሩን ቃላት ሰጣቸው፤ እናም ስለ ታቦት፣ ስለእቃዎቹ፣ እና በእዚያም ውስጥ ስለ ማምለክ መመሪያ ሰጠ። ከእዚያም ህዝቦቹ የወርቅ ጥጃዎች በማምለክ ኃጢያት የሰሩበት ታሪክ ይቀ ጥላል፣ እናም በመጨረሻም የታቦት መሰራት እና ለአገልግሎቱ ዝግጅት ታሪክ አለ።

ኦሪት ዘፍጥረት። *ደግሞም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

ኦሪት ዘፍጥረት የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ መፅ ሐፍ ነው እናም በነቢዩ ሙሴ የተጻፈ ነበር። ስለ ምድር መፈጠር፣ እንስሳትና ሰው በምድር ላይ መደረግ፣ የአዳምና የሔዋን ውድቀት፣ ለአዳም ስለተገለጸው የጎሳዎችና የዘሮች መጀመሪያ፣ የተ ለያዩ ቋንቋዎች በባቢሎን የተጀመሩበት፣ እናም ወደ እስራኤል ቤት መመስረት የመራው የአብር ሐም ቤተሰብ መጀመሪያ አይነት ብዙ የመጀመሪ ያዎች ታሪክ ይሰጣል። የጀሴፍ የእስራኤል አዳኝ ሀላፊነት በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ አፅንኦት ተሰ ጥቶታል።

የኋለኛው ቀን ራዕይ የኦሪት ዘፍጥረት ታሪኮችን ያረጋግጣል እናም ይገልጻል (፩ ኔፊ ፭፣ ኤተር ፩፣ ሙሴ ፩–፰፣ አብር. ፩–፭)።

በኦሪት ዘፍጠርት ውስጥ፣ ምዕራፍ ፩–፬ የአለም መፈጠርን እና የአዳም ቤተሰብ እድገት ታሪክን ይነ ግራሉ። ምዕራፍ ፭–፲ የኖህን ታሪክ ይመዘግባሉ። ምዕራፍ ፲፩–፳ እስከ ይስሐቅ ድረስ ስለ አብርሐ ምና ቤተሰቡ ይነግራሉ። ምዕራፍ ፳፩–፴፭ የይስሐ ቅን ቤተሰብ ይከተላሉ። ምዕራፍ ፴፮ ስለ ዔሳውና ቤተሰቡ ይናገራል ምዕራፍ ፴፯–፶ ስለ ያዕቆብ ቤተ ሰብና ወደ ግብፅ ስለተሸጠው ዮሴፍ እና የእስራኤል ቤትን ለማዳን ስላለው ሀላፊነት ታሪክ ይናገራሉ።

ከሞት መነሳት። ትንሳኤ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

ከነዓናውያኑ ስምዖን

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ የመ ጀመሪያ ሐዋሪያት አንዱ (ማቴ. ፲፡፪–፬)።

ከነዓን፣ ከነዓናውያን

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የካም አራተኛ ልጅ (ዘፍጥ. ፱፡፳፪፤ ፲፡፭፣ ፮) እና የኖኅ የልጅ ልጅ። *ከነዓናውያን* ከነዓን በመጀመሪያ ከኖረበት ምድር የመጣ ሰው እና የእርሱ ትውልዶች የሚጠሩበት ነው። *ከነዓናውያንም* በፍልስጥኤም በሜዲትሬን ያን ባህር ዳር አካባቢ ቆላ ውስጥ ለሚኖሩት ህዝ ቦች የተሰጠ ስም ነው። ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ ባለ ሀገር፣ ግሪኮች ፊኖሺያን ብለው የሚጠሩአቸ ውን እስራኤላውያን ያልሆኑ ነዋሪዎችን አንዳንዴ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ስም ነበር።

ከንቱ፣ ከንቱነት። *ደግሞም አለማዊነት፤ ኩራት ተመልከቱ*

ውስልት ወይም ውሸት፤ ኩራት ወይም ትዕቢት። *ከንቱ* እና *ከንቱነት* ደግሞም ባዶ ወይም ምንም ዋጋ የሌለው ማለት ሊሆንም ይችላል።

ነፍሱን ለከንቱ ያላነሣ በጌታ ቅዱስ ቦታ ላይ ይቆ ማል፣ **መዝ.** ፳፬፡፫–፬።

ስትጸልዩ በከንቱ አትድገሙ፣ **ማቴ.** ፮፡፯።

ከንቱ ሀሳብ እና ኩራት ትልቅ አስፈሪ ገደል ነው፣ **ፊ ኔፊ** ፲፪፡፲፰። ልባችሁን በከንቱ ምድራዊ ነገሮች እንዲሁም በሀብት ላይ ማድረጋችሁን አሁንም ትቀ ጥላላችሁን፣ **አልማ** ፭፡፶፫። የዚህን ዓለም ከንቱ ነገሮች አትፈልግ፤ ከአንተም ጋር ይዘሀቸው ለመ ሄድ አትችልም፣ **አልማ** ፴፬፡፲፭።

ከንቱነት እና ያለማመን ቤተክርስቲያኗን ሁሉ በፍርድ ላይ አድርገዋታል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፬፡፹–፹፭። ኩራታችንን ከንቱ ፍላጎታችንን ለማርካት ስን ሞክር፣ ሰማያት እራሳቸውን ይለያሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፭፡፴፯።

ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት። *ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ*

ከአንድ ሚስት በላይ የማግባት ባህል። *ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ*

ከፍተኛ ሸንጎ

የአስራ ሁለት ሊቀ ካህናት ሸንጎ።

በቤተክርስቲያኗ ዳግም መመለስ መጀመሪያ ቀኖች፣ *ከፍተኛ ሸንጎ* ሁለት የተለያዩ የአመራር ክፍሎችን የሚጠቁም ነበር፡ (፩) የቤተክርስቲያኗ

ከፍተኛነት

አስራ ሐለት ሐዋሪያት ቡድን (ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፫፣ ፴፰) እና በእያንዳንዷ ካስማዎች ውስጥ የሚያገለ ግሉ ከፍተኛ ሽንጎዎች (ት. እና ቃ. ፲፪፤ ፲፯፡፴፯)።

ከፍተኛነት። *ደግምም ሰው፣ ሰዎች— የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ፤ አክሊል፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የሰለስቲያል ክብር፤ የዘለዓለም ህይወት ተመልከቱ*

በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ታላቁ የደስታና የክብር ሁኔታ

ከፊትህ ጋር ደስታ፣ መዝ. ፲፮፡፲፩።

እነርሱ አማልክቶች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው—ስለዚህ፣ ሁሉም ነገሮች የእ ነርሱ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፰፯፡፶፫–፶፱። ቅዱ ሳንም ውርሳቸውን ይቀበላሉ እና ከእርሱም ጋር እኩል ይደረጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፯። እነዚህ መላእክቶች በህጎቼ አልኖሩም፤ ስለዚህ፣ ተለያይ ተው እና በብቸኝነት፣ ያለዘለአለማዊነት ይቆያሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፲፯። ወንዶች እና ሴቶች ዘለአ ለማዊነትን ለማግኘት በእግዚአብሔር ህግ መሰረት መጋባት አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፲፱–፳። ወደ ዘለአለማዊነት መቀጠል የሚወስደው ደጅ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፪–፳፫። አብርሐም ይስሀቅ፣ እና ያዕቆብ ወደ ዘለአ ለማዊነታቸው ገብተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፩፣ ፴፯። ዘለአለማዊነትህን አትምብሀለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፱።

ከፍተኛው ክህነት። *የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

ኩራት። *ደግምም ሀብቶች፤ ትሁት፣ ትሕትና፤ አለማዊነት፤ ከንቱ፣ ከንቱነት፤ ገንዘብ ተመልከቱ*

ትሕትና ወይም የመማር ችሎታ የሌለው። ትዕ ቢት ሰዎችን እርስ በራስ እና ከእግዚአብሔር ጋር የተቃረኑ እንዲሆኑ ያደርጋል። ትዕቢተኛ ሰው በአ ካባቢው ከሚገኙት እራሱን ከፍ ያደርጋል እናም የእግዚአብሔርን ፍላጎት ሳይሆን የእራሱን ፍላጎት ይከተላል። ጉረኝነት፣ ቅናት፣ ልበ ደንዳናነት፣ እና ኩራተኝነት የትዕቢተኛ ሰው ጸባይ ናቸው።

እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ፣ ልብህ እንዳይጓደድ፣ ዘዳግ. ፰፡፲፩–፲፭። ትዕቢትንና እብሪትን እጠላለሁ፣ ምሳ. ፰፡፲፣ (ምሳ. ፮፡፲፮–፲፯)። ትዕቢት ጥፋትን ይቀድማል፣ ምሳ. ፲፮፡፲፰። የእግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛው ላይ ይሆናል፣ ኢሳ. ፪፡፲፩–፲፪ (፪ ኔፊ ፲፪፡፲፩–፲፪)። የልብህ ትዕ ቢት አታልሎሃል፣ ኦብድ. ፩፡፣ የ። ትዕቢተኞች ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፣ ሚል. ፬፡፩ (፮ ኔፊ ፳፪፡፲፭፣ ፣ ኔፊ ፳፭፡፩፣ ፩፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፱)።

ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ ማቴ. ፳፣ ፡ ፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፴፪)። እግዚአብሔር ትዕ ቢተኞችን ይቃወማል፣ ፮ ጴጥ. ፭፡፭።

ትልቁና ሰፊው ህንፃ የዓለም ኩራት ነው፣ ፮ ኔፊ ፲፩፡፴፯ (፮ ኔፊ ፲፪፡፲፣ ፲፣)። በተማሩ ጊዜ ራሳቸ ውን እንደብልህ ይቆጥራሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፳፭–፳፱። በልባችሁ ኩራት ከፍ ብላችኋል፣ ያዕቆ. ፪፡፣ ፣ ፲፯ (አልማ ፬፡፣ ፣–፣ ፣)። ከኩራታችሁስ ተገፍፋች ኋልን፣ አልማ ፭፡፣ ፣ ፣

(እ.አ.አ.) እንደ ፕሬዘደንት አገለገሉ። የተወለዱት በ፲፰፻፶፭ (እ.አ.አ.) ነበር እና በ፶ አመታቸው በ፲፱፻፹፫ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

በሰኔ ፲፱፻፹፰ (እ.አ.አ.)፣ ቀዳሚ አመራር የክህነት መብትን እና የቤተመቅደስ በረከቶችን ብቁ ለሆኑ ወንዶች ሁሉ የሚዘረጋ ራዕይ ፕሬዘደንት ኪምባል እንደተቀበሉ አስታወቀ፣ **አ.አ.** ፪።

ኪሩቤል

የሰማይ ፍጥረቶችን የሚወክሉ ቅርጾች፣ ትክክለኛው አመለካከታቸው አይታወቅም። ኪሩቤል ቅዱስ በታዎችን ለመጠበቅ ተጠርተዋል።

ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልን አስቀመጠ፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፳፬ (አልማ ፲፪፡፳፭–፳፱፣ ፵፪፡፪–፫)። በምህረት መቀመጫ ላይ በምሳሌ የሚወክሉ ኪሩቤል ተቀምጠው ነበር፣ **ዘፀአ.** ፳፭፡፲፰፣ ፳፪ (፩ ነገሥ. ፮፡፳፫–፳፰፣ ዕብ. ፱፡፭)። ኪሩቤል በሕዝቅኤል ራዕዮች ውስጥ ተጠቅሰዋል፣ **ሕዝ.** ፲፣ ፲፩፡፳፪።

ኪዳን። ብሉይ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳን *ተመልከቱ*

ካህን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት። *ደግሞም* ሊቀ ካህን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት *ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር በፊት የሀይማኖት ስርዓትን ለሌሎች የሚያከናውን ሰው። በብዙ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ካህናት እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት ሊቀ ካህናት ናቸው (አልማ ፲፫፡፪)። ከት ንሳኤ በኋላ የእግዚአብሔርን ክብር ሙሉነት የሚቀበሉት በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ካህናትና ንጉሶች ይሆናሉ።

መልከ ጼዴቅም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ፣ **ዘፍጥ.** ፲፬፡፲፰። እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ፣ **መዝ.** ፻፲፡፬ (ዕብ. ፭፡፮፣ ፯፡፲፯፣ ፳፩)።

ክርስቶስ ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድንሆን አደረገ፣ **ራዕ.** ፩፡፮ (ራዕ. ፭፡፲፣ ፳፡፮)።

ጌታ እግዚአብሔር ካህናት እንደ ቅዱስ ስርዓቱ እንደሾመ አስታውሱ፣ **አልማ** ፲፫፡፩–፳።

በጻድቅ ትንሳኤ የሚመጡት ካህናት እና ንጉሶች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፣ ፶፭–፳።

ካህን፣ የአሮናዊ ክህነት። *ደግሞም* ሊቀ ካህን፣ አሮናዊ ክህነት፣ አሮን፣ የሙሴ ወንድም *ተመልከቱ*

በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የሚገኝ ሀላፊነት። በጥንት፣ በሌዋውያን ክህነት ውስጥ በአሮንና በትውልዶቹ ይያዙ የነበሩ ከፍተኛ ሀላፊነቶች። ክርስቶስ የሙሴ ህግን ሲያሟላ፣ ይህ ገደብ ተነስቷል።

ዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የካህናት ሀላፊነቶች ተገልጸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፶–፶፪።

ካሌብ

ከስደት ከሁለት አመት በኋላ የከነዓንን ምድር እንዲፈትሽ በሙሴ ከተላኩት አንዱ። እርሱ እና ኢያሱ ብቻ ስለምድሩ እውነተኛ ሀተታ አመጡ (ዘኁል. ፲፫፡፮፣ ፴፣ ፲፬፡፮–፴፰)። ከግብፅ ከወጡት እነርሱ ብቻ በምድረበዳው ውስጥ ለአርባ አመታት ተረፉ (ዘኁል. ፳፮፡፳፭፣ ፴፪፡፲፪፣ ዘዳግ. ፩፡፴፮) እናም ወደ ከነዓን ገቡ (ኢያ. ፲፬፡፮–፲፭፣ ፲፭፡፲፫–፲፱)።

ካም። *ደግሞም* ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የኖህ ሶስተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፭፡፴፪፣ ፮፡፲፣ ሙሴ ፰፡፲፪፣ ፳፯)።

ኖህ፣ ወንድ ልጆቹ፣ እና ቤተሰቦቻቸው ወደ መርከቡ ገቡ፣ **ዘፍጥ.** ፯፡፲፫። የካም ልጅ ከነዓን ተረገመ፣ **ዘፍጥ.** ፱፡፲፰–፳፭።

የካም መንግስት ከአባት ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፍ ነበር እናም በምድራዊ ነገሮችና በጥበብ ቢባረክም በክህነት ስልጣን የተባረከ አልነበረም፣ **አብር.** ፩፡፳፭–፳፯። የካም ባለቤት፣ ግብፅዎስ፣ የቃየን ትውልድ ነበረች፣ የሴት ልጃቸው ግብፅዎስ ወንድ ልጆች በግብፅ ውስጥ ሰፈሩ፣ **አብር.** ፩፡፳፫፣ ፳፭ (መዝ. ፻፭፡፳፫፣ ፻፯፡፳፭–፳፱)።

ካሳ፣ ዳግም መመለስ። *ደግሞም* የወንጌል ዳግም መመለስ *ተመልከቱ*

ተወስዶ የነበረ ወይም የጠፋ ነገር ወይም ሁኔታ መመለስ።

መንፈስና ሰውነት በፍጹም ሁኔታ ደግመው ይገናኛሉ፣ **አልማ** ፲፩፡፴፫–፴፬። ዳግም መመለስ ክፉን ለክፉ፣ ጻድቅን ለጻድቅ ማምጣት ነው፣ **አልማ** ፴፩፡፲–፲፭።

በአስሩ ጎሳዎች ዳግም መመለስ እናም ምድርም ታድሳ እንደገነነት አይነት ክብር እንደምትቀበልም እናምናለን፣ **እ.አ.** ፩፡፲ (ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፳፫–፳፬)።

ካስማ

ከኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች እና ማስተዳደሪያ ክፍል አንዱ። ካስማ በብዙ ዎርዶች ወይም ቅርንጫፎች የተሰራ ነው። በኢሳይያስ ፶፬፡፪ ውስጥ "አውታሮ ችሽን አስረዝሚ ካስሞችሽንም አጽኚ" በማለት የድንኳን ምስልን እንደገለጸው፣ ይህም የተመደበ የቦታዎች ገደብ ያለው ነው። ካስማ ለተበተኑት እስ

ራኤል ቅሪዎች መሰብሰቢያ ቦታ ነው (ት. እና ቃ. ፲፪፡፲፫–፲፬፣ ፤ ፤ ፲፯–፳፩)።

ካስማዎችሽን አጥብቂ እናም ወሰንሽንም ለዘለዓለም አስፊ፣ ሞሮኒ ፤ ፡ ፤ ፤ (ት. እና ቃ. ፲፪፡፲፬)።

ከዚህ በላይ ሌላ ካስማ በፅዮን እንድትመድብ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በፅዮን ምድርና በካስማዎቿ ላይ አብሮ መሰብሰቡ ለመሸሸጊያ እንዲሆን ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤)። ለካስማዎች ሌሎች ቦታዎች ይመደባሉ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የሊቀ ካህናት ቡድን ፕሬዘደንቶች የሚመደቡት የካስማ ፕሬዘደንት እንዲሆኑ የሚመደቡትን ብቁ ለማድረግ ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፡ ፤ ። ካስማዎቿ እንደጠናከሩ ዘንድ፣ ወደ ፅዮን ምድር ሂዱ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ።

ካውደሪ፣ ኦልቨር

ዳግም የተመለሰችው ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ካህን እና ለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ ስረ ነገርና እውነተኛነት ምስክር ከሆኑት ከሶስቱ አንዱ። ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ከወርቅ ሰሌዳዎች ሲተረጎም እንደ ጸሀፊ አገለገለ (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤–፤ ፤)።

ስለመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም እውነትነት ምስክር ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፤ ፡ ፤ ።

በመጥቁዑ ሶሐንስ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፤ ። (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፤ ። ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤–፤ ፤ ። የቁጥር ፤ ፤ ማስታወሻን ተመልከቱ)። እውነትን ካገኘህ እና በአይኖችህ ካየሀቸው በኋላ፣ እንዳየሀቸው ትመሰክራለህ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በመንፈሴ የጻፍካቸው እውነት እንደሆኑ ለአንተ ገልጬልሀለሁ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በራዕያት ላይ ከመጋቢዎቹ አንዱ እንዲሆን ተመድቧልም ተሾሟልም፣ ት. እና ቃ. ፤ ። ከጆሴፍ ስሚዝ ጋር የክህነት ቁልፎችን ተቀብሏል፣ ት. እና ቃ. ፤ ።

ኬብሮን

ከኢየሩሳሌም በሰላሳ ሁለት ኪሎ ሜትር ወደ ደቡብ አልፎ የሚገኝ የጥንት የይሁዳ ከተማ። የአብርሐም እና የቤተሰቡ መቃብር ቦታ ነበር (ዘፍጥ. ፡ ፤–፡ ፤)። በዳዊት የመጀመሪያ ዘመነ መንግስት ዋና ከተማውም ነበረ (፤ ሳሙ. ፤ ፡ ፤–፤)።

ክህነት

ደግምም ሀይል፣ መሾም፣ ሹመት፣ ስልጣን፣ አሮናዊ ክህነት፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን፣ የክህነት ቁልፎች ተመልከቱ

ለሰው ደህንነት በሁሉም ነገሮች ሰዎች ለመስራት እንዲችሉ እግዚአብሔር ለሰው የሚሰጠው ስልጣን እና ሀይል (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤)። የክህነት ባለስልጣን የሆኑ የቤተክርስቲያኗ ወንድ አባላት በቡድኖች ተደራጅተዋል እናም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ስነስርዓቶችንና ማስተዳደሪያ ስራዎችን ለማከናወን ስልጣን አላቸው።

መቀባታቸውም ለዘላለም ክህነት ይሆንላቸዋል፣ ዘፀአ. ፡ ፤ ፤ (ዘኁል. ፤ ፡ ፤ ፤)።

ሾምኋችሁ፣ ዮሐ. ፤ ፡ ፤ ። ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ፣ ፤ ጴጥ. ፤ ፡ ፤ ። እናንተ የጠራችሁን ትውልድ የንጉሥ ካህናት ናችሁ፣ ፤ ጴጥ. ፤ ፡ ፤ (ዘፀአ. ፤ ፡ ፤)።

በእምነታቸው እና በታላቅ ስራቸው ምክንያት ሰዎች እንደ ሊቀ ካህናት ተጠርተዋል፣ ኦልማ ፤ ፡ ፤–፤ ። እንድታጠምቅ ስልጣንን እሰጥሃለሁ፣ ፤ ኔፊ ፤ ፡ ፤ ። መንፈስ ቅዱስንም ለመስጠት ስልጣን ይኖራችኋል፣ ሞሮኒ ፤ ፡ ፤ ።

በኤሊያስ እጅ ክህነትን እገልጽላችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤)። ጌታ ክህነትን በአሮን እና በዘሮቹ ላይ አረጋገጠ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። ይህም ታላቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። ሙሴን፣ እናም ደግሞም ቅዱስ ክህነትን፣ ከመካከላቸው አወጣ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን ተገልጿል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤ ። በአባቶቻችሁ ዘር ክህነት ቀጥለዋል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ ሁለት የክህነት ባለስልጣኖች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የመጀመሪያው ክህነት፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስርዓት ቅዱስ ክህነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤ ። የክህነት መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በማሳመን እና ግብዝነት በሌለው ፍቅር ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ሀይል ወይም ተጽዕኖ በክህነት ስልጣን ዘዴ ሊደገፍ አይቻልም ወይም አይገባም፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። እያንዳንዱ ታማኝ፣ ብቁ ወንድ የቤተክርስቲያኗ አባል ክህነትን ይቀበላል፣ ኢ.ኢ. ፤ ።

ወንድ በእግዚአብሔር መጠራት አለበት፣ ኢ.ኢ. ፤ ፡ ፤ ።

ክህደት

ደግምም አመጽ፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ

በግለሰቦች፣ በቤተክርስትያን፣ ወይም በሕዝቦች ሁሉ ከእውነት ዞር ማለት።

ታላቅ ክህደት፣ እስራኤል ከጌታ ልቦቻቸው ከሚያስቱት ይጠብቁ፣ ዘዳግ. ፡ ፤ ፤ ። ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ምሳ. ፡ ፤ ፤ ። የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋል፣ ኢሳ. ፡ ፤ ። ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፣ ወደቀም፣ ማቴ. ፤ ፡ ፤ ። ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፣ ገላ. ፤ ፡ ፤ ።

በጥሩ መንገድ ጉዞ ጀመሩ፣ ነገር ግን መንገዳቸውን በጭጋግ ውስጥ ሳቱ፣ ፤ ኔፊ ፡ ፤ ፤ (፤ ኔፊ ፤ ፡ ፤ ፤)። ፍሬውን ከቀመሱ በኋላ አፈሩ፣ ወደ ተከ

ለከለውም መንገድ ገቡና ጠፉ፣ ፤ ኔሬ ፯፡፯፯፡፡ የኔፋውያን ክህደት ለማያምኑት መደናቀፊያ ሆነ፣ አልማ ፱፡፤–፲፪፡፡ የቤተክርስቲያና አባላት በኩራት ተወጠሩ እናም ሌሎች አባላትን አሳደዱ፣ ሔሌ. ፫፡፴፫–፴፱ (ሔሌ. ፱፡፲፭–፲፫፣ ፭፡፪–፫)። ጌታ ህዝቡን ሲያበለፅግ፣ አንዳንዴ እነርሱ ልባቸውን ያጠጥራሉ እናም ይረሱታል፣ ሔሌ. ፲፪፡፪፣ ፲፫፡፴፯፡፡ ኔፋውያን ልባቸውን አደነደኑ እናም በሰይጣን ሀይል ስርም ወደቁ፣ ፫ ኔሬ ፪፡፭–፫። ሞሮኒ ስለመጨረሻው ቀናት ክህደት ተነበየ፣ ሞር. ፯፡፯፯፣ ፴፭–፴፭።

ከዳግም ምፅዓት በፊት ክህደት ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፫–፲፮።

የመጀመሪያ የክርስትያን ቤተክርስትያን ክህደት፣ ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፣ ኢሳ. ፳፱፡፣ ፲፫። ጨለማ ምድርን ይሸፍናል፣ ኢሳ. ፮፡፪። ጌታ የእግዚአብሔርን ቃላትን የመስማት ራብን ይልካል፣ ዓሞ. ፰፡፲፭።

ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፣ ማቴ. ፳፬፡፳፬። ጨካኞች ተኩላዎች በመካከላችሁ ይገባሉ፣ የሐዋ. ፳፡፳፱። ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፣ ገላ. ፩፡፮። ከዳግም ምፅአት በፊት ክህደት አስቀድሞ ይመጣል፣ ፪ ተሰ. ፪፡፫። አንዳንዶች ስለ እውነት ይስታሉ፣ ፪ ጢሞ. ፪፡፲፰። አንዳንዶች የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ይክዳሉ፣ ፪ ጢሞ. ፫፡፪–፭። እውነት ትምህርትን የማይጸኑበት ጊዜ ይመጣል፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፫–፬። ሐሰተኞች ነቢያት እና ሐሰተኞች በህዝቡ መካከል፣ ፪ ጴጥ. ፪፡፩። አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ብቻውን ያለውን ንጉሳችንን እና ጌታችንን ይክዳሉ፣ ይሁዳ ፩፡፬። አንዳንድ ሰዎች ሐዋርያት ነን ይላሉ እና አይደሉም፣ ራዕ. ፪፡፪።

ኔሬ የታላቋና የርኩሰቱን ቤተክርስቲያን መመስረትን አየ፣ ፤ ኔሬ ፲፫፡፳፯። አህዛብ ተሰናክለዋል እና በዚህም ብዙ ቤተክርስቲያኖች ሰርተዋል፣ ፪ ኔሬ ፳፯፡፳።

ከስርዓቴ እርቀዋል፣ እናም የዘላለማዊ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፭። ጭለማ ምድርን፣ እና ታላቅ ጭለማም የህዝቦችን አዕምሮ ሸፍኗል፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፳፫።

ጆሴፍ ሁሉም ቤተክርስቲያናት ስህተተኛ እስ ደሆኑ ተነገረው፣ ልባቸውም ከእግዚአብሔር የራቁ ነበሩ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፱።

ክርስቲያኖች። *ደግሞም ቅዱሳን፣ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የተሰጠ ስም ምንም እንኳን ይህ ስም በአለም ውስጥ ሁሉ የሚ ጠቀመበት ቢሆንም፣ ጌታ የክርስቶስ ተከታዮችን እንደ ቅዱስን መድቧቸዋል (የሐዋ. ፱፡፲፫፣ ፴፪፣ ፴፩፣ ፩ ቆሮ. ፩፡፪፣ ት. እና ቃ. ፲፲፭፡፬)።

ደቀ መዛሙርትም ክርስቲያኖች ተባሉ፣ የሐዋ. ፲፩፡፳፮። ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል አይፈር፣ ፩ ጴጥ. ፬፡፲፮።

በቃል ኪዳን ምክንያት እናንተ የክርስቶስ ልጆች ትባላላችሁ፣ ሞዛያ ፭፡፯። በእውነት የሚያምኑት በቤተክርስቲያና አባል ባልሆኑት ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ፣ አልማ ፴፯፡፲–፲፮።

ክርስቶስ። ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

ክርስቶስ ስለተባረኩ የተናገራቸው አረፍተ ነገሮች። *እርካታ ተመልከቱ*

ክብር። *ደግሞም መቆጠር፣ ማክበር፣ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ እውነት፣ የክብር ደረጃዎች ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ክብር ስለእግዚአብሔር ብርሀንና እውነት የሚያመለክት፣ ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር አምልኮን ማሳየት ነው። ይህም ደግሞ ስለ ሙገሳ ወይም ክብር እናም ስለዘ ለአለማዊ ህይወት አንዳንድ ጉዳዮች ወይም ስለእ ግዚአብሔር ክብር ያመለክታል።

አባትህንና እናትህን አክብር፣ ዘፀአ. ፳፡፲፪ (፤ ኔሬ ፲፯፡፹፭፣ ሞዛያ ፲፫፡፳)። እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፣ ምሳ. ፫፡፱። ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞል ታለች፣ ኢሳ. ፮፡፫ (፪ ኔሬ ፲፯፡፫)።

የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል፣ ዮሐ. ፲፪፡፳፮። እኛም ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፣ ፪ ቆሮ. ፫፡፲፰። ባሎች ለሚስቶቻቸው ክብር ይስጧቸው፣ ፤ ጴጥ. ፫፡፯።

በከንፈሮቻቸውም ጌታን አከበሩ፣ ፪ ኔሬ ፳፯፡፳፭ (ኢሳ. ፳፱፡፲፫)። በክብር ከእርሱ ጋር እንድኖር በመጨረሻው ቀን ያስነሳኛል፣ አልማ ፴፯፡፳፯። የዓለምን ክብር አይደለም የምፈልገው፣ አልማ ፲፡፴፡፡

ኃይሌ የሆነውን ክብርህን ስጠኝ በማለት ዲያ ብሎስ በእኔ ላይ አመጸ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯። ታማኝ በክብር ዘውድ አክሊልም ይጫንላችኋል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፭ (ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፭)። ጌታ የሚያገለግሉትንም ለማክበር ይደሰታል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፭። በትንሳኤ የምንቀበለው ክብር በጽድቅ መሰረት ይለያያል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፱–፲፲፱። ፴፭ የእግዚአብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፭። ያልተመረጡት በሰዎች ለመከበር ስለሚነሳሱ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፴፪–፴፭።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥ ቶም ማሳለፍ የእግዚአብሔር ስራ እና ክብር ነው፣

ሙሴ ፩፡፴፱። ብርሀናቸውና ክብራቸው የሚገለጽበት ሁሉ ብቁ ያልሆነ፣ ሁለት ሰዎች በአየር ከእኔ በላይ ቆመው አየሁ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯። ህግን በማክበርና በመደገፍ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፴፰፡፯)።

ክንድ

በዕብራውያን መካከል የርዝመት መመዘኛ፣ በመጀመሪያ ከክርን እስከ ጣቶች ጫፍ ያለው ርዝመት ነበር።

ክፉ፣ ክፋት። *ደግሞም ኃጢያተኛ፣ አመፃ፣ ኃጢያት፣ መንፈሳዊ ጭለማ፣ እድፍ፣ እድፍነት፣ እግዚአብሔርን የሚጠላ ተመልከቱ*

ክፋት፣ ኃጢያት፣ ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥ አለመሆን።

እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፯–፱። እግዚአብሔር ከጎጥአን ይር ቃል፣ የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል፣ ምሳ. ፲፭፡፳፱። ጎጥአን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ሕዝብ ያለ ቅሳል፣ ምሳ. ፳፱፡፪ (ት. እና ቃ. ፣፲፰፡፱)።

በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት፣ ፩ ቆሮ. ፭፡፲፫። መጋደላችን ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው፣ ኤፌ. ፣፡፲፪።

ከክፉዎች ውጡ እናም ተለዩ፣ እናም የጎ ደፉ ነገሮቻቸውን አትንኩ፣ **አልማ** ፭፡፲፯–፲፯ (ት. እና ቃ. ፴፣፡፣)። የኃጢአተኞች የመጨረሻ ሁኔታ ይህ ነው፣ **አልማ** ፴፬፡፴፭ (አልማ ፣፡፣–፣፡)። ክፋት በፍፁም ደስታ ሆኖ አያውቅም፣ **አልማ** ፣፡፣፡፣። ኃጥአን የሚቀጡት በኃጢአተኞች ነው፣ **ሞር.** ፬፡፭ (ት. እና ቃ. ፣፣፡፡፡፴)።

በእዚያም ሰዓት ጻድቃኖችን ከጎጥያተኞቹ በሙሉ የሚለያዩበት ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፣፣፡፡፡፣፡።

እንደዚህም የክፉዎች መጨረሻ ይመጣል፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፣፣፩።

ክፉ መናገር። *ደግሞም ሐሰት፣ አሉባልታ፣ ወሬ፣ ጸብ ተመልከቱ*

ትክክል ያልሆኑ፣ የሚጎዱ፣ እና ክፉ የሆኑ ነገሮችን መናገር። በብዙ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደዚህ አይነት ንግግር የሚደረገው በሰው ላይ ጉዳት ለማምጣት ነው።

አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ መዝ. ፴፬፡፲፫ (፩ ጴጥ. ፫፡፣)። ምናምንቴ ሰው ክፋትን ይም ሳል፣ ምሳ. ፲፣፡፣፭፣። ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፣ ማቴ. ፭፡፲፩ (፫ ኔፊ ፲፪፡፲፩)። ከልብ ክፉ አሳብ ይወጣል፣ ማቴ. ፣፭፡፣፣ (ማር. ፣፡፣፭፩)። በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትና ገር፣ የሐዋ. ፳፫፡፭። ክፉ ንግግሮች ሁሉ ከእና ንተ ዘንድ ይወገድ፣ ኤፌ. ፬፡፴፩። እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፣ ያዕ. ፬፡፣፩።

መተማማት፣ ወይም ክፉ መነጋገር እንዳይኖር ይጠበቅ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፣፬።

ክፉ መንፈሶች። *መንፈስ—ክፉ መንፈሶች ተመልከቱ*

ወሊድ መቆጣጠሪያ። *ደግሞም ቤተሰብ፣ ጋብቻ፣ መጋባት ተመልከቱ*

ፅንስን በመቆጣጠር ወይም በመከላከል ለተጋቡት የሚወለዱትን ልጆች ቁጥር መቆጣጠር።

ብዙ፡ ተባዙ፡ ምድርንም ሙሉአት፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፰ (ሙሴ ፪፡፳፰)። ልጆች የእግዚአብሔር ቅርስ ናቸው፣ መዝ. ፲፳፯፡፣–፫።

የሌሒ ቤተሰብ ለጌታ ዘር ያሳድጉ፣ ፩ ኔፊ ፣፡፩።

ጋብቻ ለሰው በእግዚአብሔር የተመደበ ነው፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡፣፭–፣፣። ከፍ ከፍ ያሉት ሙሉ ነትን እና የዘር ቀጣይነትን ለዘለአለም ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፣፱፣ ፣፣፫።

ወላጆች። *ደግሞም ሚች አባት፣ እናት ተመልከቱ*

አባቶችና እናቶች። በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ በትክክለኛው ስርዓት በጋብቻ የተሳሰሩ ብቁ ባሎች እና ሚስቶች የወላጅነት ሀላፊነታቸውን በዘለአለም ሁሉ ያሟላሉ። “ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር እና በጽድቅ የማሳደግ፣ ስጋዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን የማሟላት፣ እና እርስ በራስ እንዲዋደዱና እንዲያገለግሉ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንዲያከብሩ፣ እና በሚኖሩበት በማንኛውም ቦታ ህግን የሚያከብሩ ዜጋዎች እንዲሆኑ የማስተማር ቅዱስ ሀላፊነት አላቸው” (“ቤተሰብ፡ ለአለም የተላለፈ አዋጅ”፣ *Ensign,* ህዳር ፳፻፲ [እ.አ.አ.]፣ ፲፳፱)።

ልጆች ሆይ፡ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፣ ኤፌ. ፣፡፩–፫ (ቁላ. ፫፡፳)።

አዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ወላጆች ናቸው፣ ፩ ኔፊ ፭፡፣፩። እርግማኑ በወላጆቻችሁ ራስ ላይ ይመለስ፣ ፪ ኔፊ ፬፡፣። ወላጆች ንሰሃ መግባት እናም መጠመቅ እንዳለባቸው አስተምራቸው፣ ሞሮኒ ፰፡፣።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወንጌል እንዲያስተምሩ ታዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፰፰፡፰፭። ሁሉም ልጆች በወላጆቻቸው ላይ የመደገፍ መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡፬።

የወላጆች ኃጢያት በልጆች ጭንቅላት ላይ አይ መለስም፣ ሙሴ ፮፡፱፬።

ወራሽ

ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመውረስ መብት ያለው ሰው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ቅዱሳን እግዚአብሔር ላለው ሁሉ ወራሽ እንደ ምሚሆኑ ቃል ተገብቶላቸዋል።

አብርሐም ወራሽን ፈለገ፣ ዘፍጥ. ፲፭፡፪–፭።
አብርሃም የዓለምም ወራሽ የሆነው በእምነት ጽድቅ ነው፣ ሮሜ ፬፡፲፫። የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፣ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፡ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፣ ሮሜ ፰፡፲፮–፲፯ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፴፰)። ልጅ ነህ፣ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ፣ ገላ. ፬፡፯። እግዚአብሔር ልጁን የሁሉን ወራሽ አደረገ፣ ዕብ. ፩፡፪።
ለኃጢአታቸው ስርየት ያንን ቀን የሚጠብቁ፣ የእግዚአብሔርን መንግስት ወራሾች ናቸው፣ ሞዛያ ፲፭፡፲፩። ሰዎች በአንድነት የክርስቶስ ልጆች፣ እናም የእግዚአብሔርንም መንግስት ወራሾች ነበሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፲፯።
ይህን ወንጌል ሳያውቁ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር ሰለስቲያል መንግስት ወራሾች ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፣–፰። ንስሀ የገቡ ሙታን የደህንነት ወራሾች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፱፰–፱፱።
አብርሐም በጽድቅ መብት ያለው ወራሽ ሆነ፣ አብር. ፩፡፪።

ወሬ። *ደግሞም አሉባልታ፤ ክፉ መናገር ተመልከቱ*

አንዳንዴም በግማሽ እውነት፣ ህዝብን ከእግዚአብሔር እና ከሁሉም ጥሩ ነገሮች ለማዞር ሰይጣን ወሬን እና ጸብን ያባዛል (ሔሌ. ፲፮፡፳፪፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፩)። የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት አንደኛው ምልክት ሰዎች ስለጦርነቶች እና ስለጦርነቶች ወሬ መስማታቸው ነው (ማቴ. ፳፬፡፮፤ ት. እና ቃ. ፵፭፡፳፮፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፳፫)

ወንድሞች፣ ወንድም። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ ሴት፣ ሴቶች፤ እህት ተመልከቱ*

እንደ ሰማይ አባታችን ልጆች፣ ወንዶች እና ሴቶች ሁሉ መንፈሳዊ መንድሞችና እህቶች ናቸው። በቤተክርስትያኗ ውስጥ፣ ወንድ አባላት እና የቤተክርስትያኗ ጓደኞች ብዙ ጊዜ ወንድም ተብለው ይጠራሉ።

አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና፣ ሉቃ. ፳፪፡፴፪። ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፲–፲፯።

ወንድሞቻችሁን እንደ እራሳችሁ አስቡባቸው፣ ያዕቆ. ፪፡፣፲፯።
እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን እንደ እራሱ ይመልከት፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፳፬–፳፭። በንግግራችሁ በሙሉ ወንድሞቻችሁን አጠናክሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፣፯።

ወንጀል። በደል *ተመልከቱ*

ወንጌል። *ደግሞም ዘመን፤ የቤዛነት ዕቅድ፤ የክርስቶስ ትምህርት ተመልከቱ*

በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል እንዴቻል የሆነ የእግዚአብሔር የደህንነት አላማ። ወንጌል ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመመለስ የሰው ዘር የሚያስፈልጋቸውን የዘለአለም እውነቶች ወይም ህግጋት፣ ቃል ኪዳኖች፣ እና ስርዓቶች ያጠቃልላል። እግዚአብሔር በ፲፱ኛው መቶ አመት ውስጥ በነቢዩ ጆሴ ስሚዝ በኩል ሙሉ ወንጌልን በምድር ላይ በዳግም መለሰ።

ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ስበኩ፣ ማር. ፲፮፡፣፲፭።
ግልፅና እጅግ የከበረው የበጉ ወንጌል ክፍል ወደ ኋላ ተያዙ፣ ፩ ኔፊ ፲፣፡፣፴፪። ይህ ወንጌሌ ነው፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፣፲፣–፳፩ (ት. እና ቃ. ፴፱፡፣፯)።
መፅሐፈ ሞርሞን ሙሉ ወንጌልን ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፳፡፣፳–፱ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፣፲፪)። ይህ ወንጌል ነው፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፣፣–፵፣፣። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፣፲፱። የወንጌል ሙላትን በእራሱ ልሳን እያንዳንዱ ሰው ይሰማል፣ ት. እና ቃ. ፣፡፣፲፩። ወልድ ወንጌልን ለሙታን መንፈሶች ሰበከ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፣፲፳–፳፭፣ ፳፳–፴፣፯።
ወንጌሉ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ መሰበክ ጀመረ፣ ሙሴ ፩፡፣፲፳። የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆችና ስነስርዓቶች ተገልጸዋል፣ ኤ.አ. ፩፡፲።

ወንጌል ሰባኪ። *ደግሞም የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ፤ የፓትሪያርክ በረከቶች ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መልካም ዜናን የሚያውጅ ወይም የሚወስድ ሰው። ጆሴፍ ስሚዝ ወንጌል ሰባኪ ፔትሪያርክ እንደሆነ አስተምሯል። ፔትሪያርኮች የተጠሩና በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት አመራር መሰረት የፔትሪያርክ በረከቶች ተብለው የሚጠሩ ልዩ በረከቶችን ለመስጠት የሚሾሙ ናቸው።

ጌታ አንዳንዶቹን ሐዋርያት፣ ሌሎቹን ነቢያት፣ ሌሎቹን ወንጌልን ሰባኪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፣ ኤፌ. ፬፡፲፩። የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፭።
በሀዋርያት፣ በነቢያት፣ በሚኒስትሮች፣ በአስተ

ማሪዎች፣ በወንጌል ሰባኪዎች እናምናለን፣ ኤ.አ. ፩፡፲፤

ወንጌሎች። *ደግሞም ሉቃስ፤ ማርቆስ፤ ማቴዎስ፤ ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ምድራዊ ህይወት እና የአገልግሎቱ ድርጊቶች ምስክሮችን የያዙ በአዲስ ኪዳን የመ ጀመሪያ አራት መፅሐፎች ውስጥ የሚገኙ አራት መዝገበች። የተጻፉትም በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ፣ እና በዮሐንስ ነው፣ እነዚህም ስለክርስ ቶስ ህይወት የተመዘገቡ ምስክሮች ናቸው። በመ ፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኘው ፫ ኔፊ መፅሐፍ በብዙ መንገዶች ከእነዚህ አዲስ ኪዳን ወንጌሎች ጋር የተመሳሰለ ነው።

የአዲስ ኪዳን መፅሐፎች በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነበር። በግሪክ ቋንቋ *ወንጌል* ማለት "መልካም ዜና" ማለት ነው። መልካሙም ዜና የሰው ዘርን በሙሉ ከሞት ለማዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያት ዋጋ መክፈሉ እና እያንዳንዱን ለስራው ደመወዝ ናቸው። (ዮሐ. ፫፡፲፮፤ ሮሜ ፭፡፲–፲፩፤ ፪ ኔፊ ፱፡ሸ፲፤ አልማ ፴፪፡ፀ፤ ት.እና ቃ. ፳፯፡ሸ–ሸ፱)

የወንጌሎች ስምምነትን በተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ተመልከቱ።

ወኪል። *ለሙታን ደህንነት፤ ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት ተመልከቱ*

ወደ ሰማይ ማረግ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ተመልከቱ*

ከትንስኤው አርባ ቀናት በኋላ፣ አዳኝ ከምድር የሄደበት። ወደ ሰማይ ማረጉ የነበረው በደቀ መዛ ሙርቶች ፊት ለፊት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ነበር (ማር. ፲፮፡፲፱፤ ሉቃ. ፳፬፡ፀ፲ሸ)። በእዚያም ጊዜ ከሰማይ የመጡ ሁለት መላእክቶች ጌታ ወደ ፊት "እንዲሁ" ይመለሳል ብለው መሰከሩ (የሐዋ. ፩፡፱–፲፪)።

ወደ ሮሜ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ጳውሎስ በሮሜ ላሉት ቅዱሳን የጻፈው ደብዳቤ። አደጋ ቢኖርበትም፣ ኢየ ሩሳሌምን ለመጎብኘት እያሰበ ነበር። በህይወቱ ካመ ለጠ፣ ከእዚያም በኋላ ሮሜን ለመጎብኘት ተስፋ ነበ ረው። ደብዳቤውን የጻፈው፣ እርሱ ሲመጣ እርሱን ለመቀበል በእዚያ ያለችው ቤተክርስቲያን እንድት ዘጋጅ ነበር። ይህም ክርክር የነበረባቸውን እና አሁን ጳውሎስ በመጨረሻ ተመስርተዋል ብሎ የተመለ ከታቸውን የአንዳንድ ትምህርቶች መረጃ እንደያዘ ሊታይበትም ይችላል።

ምዕራፍ ፩ ጳውሎስ ለሮሜ የላከውን ሰላምታ የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፲፩ የእምነት፣ ስራዎች፣ እና ጸጋ ትምህርት ብዙ አዋጆችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፲፪–፲፮ የፍቅር፣ የሀላፊነት፣ እና የቅዱስነት ትም ህርቶችን የያዙ ናቸው።

ወደ ቁላስይስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ይህ በመ ጀመሪያ ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤጳፍራ ከተጎ በኘ በኋላ ለቁላስይስ የጻፈው ደብዳቤ ነበር (ቁላ. ፩፡፣–፤)። ኤጳፍራ ጳውሎስን ቁላስይስ በከባድ ስህተት ውስጥ እየወደቁ እንዳሉ ነገረው—አን ዳንድ የውጪ ስነስርዓቶችን በጥንቃቄ ስለሚከ ተሉ (ቁላ. ፪፡፣–፲፮)፣ አንዳንድ ስጋዊ ፍላጎታቸ ውን ከእራሳቸው ስለሚያስወግዱ፣ እና መላእክ ትን ስለሚያመልኩ (ቁላ. ፪፡፲–ሸ)እነርሱ ከሌሎች ሰዎች የተሻሉ ይመስላቸው ነበር። እንዚህ ድር ጊቶች ቁላስይስን የተቀደሱ እንደሆኑ እንዲሰማ ቸው አደረጉአቸው። እነርሱም የሁለንታን ሚስ ጥሮች ከሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ይበልጥ እንደሚገባቸው ይሰማቸው ነበር። ቤዛነት የሚ መጣው በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ እነርሱን በማ ስተካከል እና እኛ ጥበበኛ መሆን እንደሚገባን እና እንድናገለግለው በደብዳቤው ውስጥ ጳው ሎስ አስተማራቸው።

ምዕራፍ ፩ ጳውሎስ ለቁላስይስ የሰጠው ሰላምታ ነው። ምዕራፍ ፪–፫ ትምህርት የያዙ እናም ስለክር ስቶስ ቤዛነት፣ ስለሀሰት አምልኮ አደጋ፣ እና ስለ ትንሳኤ አስፈላጊነት መግለጫዎችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፬ ቅዱሳን በሁሉም ነገሮች ጠበበኛ መሆን እንዳለባቸው ያስተምራል።

ወደ ቆሮንቶስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት መፅሐፎች። እነዚህ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለሚገኙት ቅዱሳን በመካከላ ቸው ያለውን ረብሻ ለማስተካከል የጻፈው ደብዳቤ ዎች ነበሩ። ቆሮንቶስ የኖሩት ክፉ በሆኑ ህብረተሰ ቦች ውስጥ ነበር።

መጀመሪያይቱ ቆሮንቶስ፣ ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታና አንድ ስለመሆን የገሰጸባቸውን ይይዛል። ምዕራፍ ፪–፮ የቆሮንቶስ ቅዱሳን ስህተት ጳውሎስ ያስተካከላቸው ናቸው። ምዕራፍ ፯–፲፪ለአንዳንድ ጥያቄዎች የጳውሎስን መልስ የያዙ ናቸው። ምዕ ራፍ ፲፫–፲፭ በልግስና፣ በመንፈሳዊ ስጦታዎች፣ እና በትንሳኤ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ምዕራፍ ፲፮ በእም ነት ጠንክረው እንዲቆሙ የጳውሎስን ምክር የያዙ ናቸው።

ሁለተኛይቱ ቆሮንቶስ፣ ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን

ሰላምታና የመጽናናት መልእክት ይይዛል። ምዕራፍ ፤ ለቲቶ የግል ምክርን የያዘ ነው። ምዕራፍ ፫–፮ ወንጌል በቅዱሳንና በመሪዎቻቸው ህይወቶች ውስጥ ስላለው ሀይል ይናገራሉ። ምዕራፍ ፯–፱ ቅዱሳንን ለደህዎች በደስታ እንዲሰጡ ይመክራሉ። ምዕራፍ ፣–፲፤ ጳውሎስ ስለሐዋሪያነቱ የሚናገርባቸው ናቸው። ምዕራፍ ፲፫ ፍጹም ስለመሆን በትህትና የሚያስጠነቅቅ ነው።

ወደ ተሰሎንቄ መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሁለት መጻህፍት። እነዚህ ጳውሎስ በ፶ ም.ዓ. አካባቢ አውሮፓን በጎበኘበት ጊዜ በቆሮንቶስ ውስጥ እያለ በመጀመሪያ ለተሰሎንቄ የጻፋቸው ደብዳቤዎች ነበሩ። በተሰሎንቄ የነበረው ስራ በ የሐዋርያት ስራ ፲፯ ውስጥ ተዘርዝረዋል። ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ለመመለስ ፈለገ ነገር ግን ይህን ለማድረግ አልቻለም ነበር (፩ ተሰ. ፪፡፣፲፰)። ስለዚህ የተቀየሩትን እንዲያስደስት እና እንዴት እንደሆኑ መልእክት እንዲያመጣለት ጢሞቴዎስን ላከ። ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈው በጢሞቴዎስ መመለስ ምስጋና ስለተሰማው ነበር።

መጀመሪያይቱ ተሰሎንቄ፣ ምዕራፍ ፩–፪ የጳውሎስን ሰላምታ እና ለቅዱሳን ያለውን ጸሎት የያዙ ነበሩ፤ ምዕራፍ ፫–፭ ስለመንፈሳዊ እድገት፣ ፍቅር፣ ንጹህነት፣ ትጋት፣ እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት መመሪያዎች የሚሰጡ ነበሩ።

ሁለተኛይቱ ተሰሎንቄ፣ ምዕራፍ ፩ ለቅዱሳን የነበረውን ጸሎት የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪ ስለሚመጣው ክህደት ተናግሯል። ምዕራፍ ፫ ለመንጌሉ ምክንያት ድል ማግኘት የነበረውን የጳውሎስ ጸሎትን የያዘ ነበር።

ወደ ቲቶ መልእክት። *ደግምም ቲቶ፤ የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

ጳውሎስ ለጊዜ ከሮሜ እስር ቤት ወጥቶ እያለ፣ መልእክቱን በቀርጤስ ለነበርው ጢቶ ጻፈ። ደብዳቤው ስለቤተክርስቲያኗ ድርጅት እና በውስጧ ስላለው ቅጣቶች ስለነበሩት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነበር።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ምን አይነት ብቁነት እንደሚያስፈልግና መመሪያዎችን የያዘ ነበር። ምዕራፎ ፪–፫ አጠቃላይ ትምህርቶችን እና የቀርጤስ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ቡድኖችን እንዴት መቋቋም እንደሚችል ለቲቶ የላከውን የግል መልዕክት የያዙ ናቸው። ጳውሎስ ቅዱሳንን ባለጌነትን እንዲያቆሙ፣ ራስን ተቆጣጣሪና ታማኝ፣ እናም መልካም ስራን የሚቀጥሉ እንዲሆኑ አበረታታ።

ወደ ኤፌሶን መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በሐዋሪያ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን የጻፈው መልእክት። መልእክቱ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ጳውሎስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸውን ይዟል።

ምዕራፍ ፩ እንደ በፊቱ አይነት ሰላምታን ይዟል። ምዕራፍ ፪–፫ የቤተክርስቲያኗ አባላት በሚሆኑበት ጊዜ በሰዎች ላይ የሚመጣውን ቅያሬ ይገልጻል—ከቅዱሳን፣ ከአህዛባች እና ከአይሁድ ጋር በአንድ ቤተክርስቲያን በመተባበር ዜጋዎች ይሆናሉ። ምዕራፍ ፬–፮ የሐዋሪያትን እና የነቢያትን ሀላፊነቶች፣ ስለአንድነት አስፈላጊነት፣ እና የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር እቃ የመልበስ አስፈላጊነትን ይገልጻሉ።

ወደ ዕብራውያን መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው አይሁድ የሆኑትን የቤተክርስቲያን አባላት አብዛኛዎቹ የሙሴ ህግ በክርስቶስ እንደተሟላ እና የክርስቶስ ታላቁ የወንጌል ህግ ይህን እንደተካ ለማሳመን ነበር። ከሶስተኛው ሚስዮኑ መጨረሻ ላይ (በ፶ ም.ዓ. አካባቢ) ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ፣ ብዙዎቹ የቤተክርስቲያኗ አይሁድ አባሎች የሙሴን ህግ እያከበሩ እንዳሉ አገኛቸው (የሐዋ. ፳፩፡፣፳)። ይህም በኢየሩሳሌም የነበረው የቤተክርስቲያኗ ጉባኤ አንዳንድ የሙሴ ህግ ስነስርዓቶች ለአህዛብ ክርስቲያኖች አስፈላጊ እንዳልሆነ ከተወሰነ ከአስር አመት በኋላ ነበር። ጳውሎስ ከዚህ በኋላ በእራሳቸው ቅዱሣት መጻህፍት እና ግልፅ ምክንያት በመስጠት የሙሴን ህግ ከዚህ በኋላ ለምን መከተል እንደማያስፈልጋቸው ወደ ዕብራውያን እንደጻፈ ግልፅ ነው።

ምዕራፍ ፩ እና ፪ ኢየሱስ ከመላእክት በላይ ታላቅ እንደሆነ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፫–፮ ኢየሱስን ከሙሴና ከሙሴ ህግ ጋር ያነጻጽራሉ እናም እርሱ ከሁለቱም ታላቅ እንደሆነ ይመሰክራሉ። የመልከጼዴቅ ክህነት ከአሮናዊ ክህነት ታላቅ እንደሆነም ያስተምራሉ። ምዕራፍ ፯–፱ የሙሴአዊ ስነስርዓቶች ሰዎችን ለክርስቶስ አገልግሎት እንዴት እንደሚያዘጋጁና ክርስቶስ እንዴት የአዲሱ ቃል ኪዳን አማላጅ እንደሆነ ይገልጻሉ (አልማ ፴፯፡፣፴፯–፴፰፤ ት. እና ቃ. ፹፬፡፣፳፩–፳፬)። ምዕራፍ ፲ ለትጉነትና ታማኝነት የሚገፋፋ ነው። ምዕራፍ ፲፩ የእምነት ፅሁፍ ነው። ምዕራፍ ፲፪ ግሰጻን እና ሰላምታን ይሰጣል። ምዕራፍ ፲፫ ስለጋብቻ ክብር እን ስለታዛዥነት አስፈላጊነት ይናገራል።

ወደ ገላትያ መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። በገላትያ

ውስጥ ለሚኖሩት ቅዱሳን ሐዋሪያው ጳውሎስ የጻፈው ደብዳቤ ነበር። የዚህ ደብዳቤ ጭብጥ መልእክት እውነተኛ ነጻነት ለመገኘት የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመኖር ነው የሚል ነበር። ቅዱሳን የሙሴን ህግ መከተል አለባቸው የሚሉት የአይሁዳ ክርስቲያን ትምህርቶችን ከወሰዱ፣ በክርስቶስ ያገኙትን ነጻነት ይገድባሉ ወይም ያጠፉሉ። መልእክቱ ውስጥ ጳውሎስ የሐዋሪያ ሀላፊነቱን አረጋገጠ፣ የጽድቅ በእምነት ትምህርትን ገለጸ፣ እናም የመንፈሳዊ ሀይማኖት ታላቅ ዋጋን አረጋገጠ።

በምዕራፍ ፩ እና ፪፣ ጳውሎስ በገላትያ መካከል ስላለው ክህደት በተቀበለው ዜና ሀዘኑን ገለጸ እናም በሐዋሪያት መካከል ስላለው ቦታ ገለጸ። ምዕራፍ ፫ እና ፬ የእምነትና የስራ ትምህርቶችን ይወያያሉ። ምዕራፍ ፭ እና ፮ የእምነት ትምህርት ውጤቶች ስብከትን የያዙ ናቸው።

ወደ ጢማቴዎች መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጢሞቴዎስ፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት መፅሐፎች። ሁለቱም በቅድሚያ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፋቸው ደብዳቤዎች ነበሩ።

፩ ጢሞቴዎስ፣ ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈው ለመጀመሪያ ጊዜ ከታሰረ በኋላ ነበር። ጢሞቴዎስን በኋላ እንደገና ለመመለስ እያሰበ፣ በኤፌሶን ትቶት ሄዶ ነበር (፩ ጢሞ. ፫፡፲፬)። ነገር ግን፣ ጳውሎስ የሚዘገይ እንደሆነ ስላሰበ፣ ምናልባት ከመቄዶንያ፣ ምክር ለመስጠት እና ሀላፊነቱን ለማሟላት ለማበረታታት ወደ ጢሞቴዎስ ጻፈ (፩ ጢሞ. ፩፡፣ ፫)።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ደግሞም በቤተክርስቲያኗ ለመገኘት ስለጀመሩት የሞኝነት ግምቶች መመሪያ የሰጠበትን የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፫ ስለህዝባዊ አምልኮ እና ስለአገልጋዮች ጸባይ እና አሰራር መመሪያ የሚሰጡ ነበሩ። ምዕራፍ ፬–፭ የኋለኛው ቀን ክህደትን መግለጫ እና የሚመራቸውን እንዴት ለማገልገል እንደሚችል ለጢሞቴዎስ የተሰጠን መመሪያ የያዙ ነበሩ። ምዕራፍ ፮ ታማኝ ለመሆን እና የአለም ሀብቶችን እንዲያስወግዱ የሚያበረታታ ነበር።

፪ ጢሞቴዎስ፣ ጳውሎስ ሁለተኛውን ደብዳቤ የጻፈው በታሰረበት በሁለተኛ ጊዜ፣ እና በስማዕቱ ከትንሽ ጊዜ በፊት ነበር። ይህም የሐዋርያውን የመጨረሻ ቃላት የያዘ እና ሞትን እንዴት በአስደናቂ ጉብዝና እና እምነት እንደተቋቋመ የሚያሳይ ነው።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ለ ጢሞቴዎስ የሰጠውን ሀላፊነት የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፫ የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች እና መመሪያዎች፣ ወደፊት የሚመጡትን አደጋዊች ለመቋቋም ሀላፊነት የሚሰጡ ነበሩ። ምዕራፍ ፬ የሚክዱትን ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ምክር የሰጠውን የያዘ የጳውሎስ ጓደኞች የተላከውን መልእክት የያዘ ነበር።

ወደ ፊልሞና መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በጳውሎስ ከተጻፈው ደብዳቤ የተወሰደ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ወደ ፊልሞን ሰዎች የላከው መልእክት ጌታውን ስለዘረፈው እና ወደ ሮሜ ስለሸሸው ባሪያ አናሲሞስ በሚመለከት ለፊልሞን የላከው የግል ደብዳቤ ነበር። ጳውሎስ በቄላስይስ ወደሚገኘው ጌታው የጳውሎስ ደብዳቤ ወደ ቄላስይስ ከወሰደለት ከቲኪቆስ ጋር መልሶ ላከው። ጳውሎስ አናሲሞስ ይቅርታ እንዲሰጠው እና እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀበለው ጠየቀ። ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው ለመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ እስር ቤት እያለ ነው።

ወደ ፊልጵስዮስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

ጳውሎስ በፊልጵስዮስ ውስጥ ላሉት ቅዱሳን ለመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ ውስጥ በእስር ቤት እያለ የጻፈው ደብዳቤ ነበር። አሁን ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወደ ኢልጵስዮስ መልእክት የሚባል መፅሐፍ ነው።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ስለአንድነት፣ ትሁትነት፣ እና ስለመፅናት የሚሰጠው መመሪያን የያዘ ነው። ምዕራፍ ፪ ሁሉም ለክርስቶስ እንደሚሰግዱ እና እያንዳንዱ ሰው የእራሱን ደህንነት ለመፈጸም እንደሚገባቸው ትኩረት ይሰጣል። በምዕራፍ ፫ ውስጥ፣ ጳውሎስ ሁሉንም ነገሮች ለክርስቶስ መስዋዕት እንዳደረገ ይገልጻል። በምዕራፍ ፬ ውስጥ፣ ጳውሎስ የፊልጵስዮስ ቅዱሳንን ለእርዳታቸው ያመሰግናል።

ዊትመር፣ ዴቪድ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ስለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ መንጭ እና እውነትነት ምስክር ከሆኑት ሶስት ምስክሮች አንዱ (ት. እና ቃ. ፲፩፣ ፲፯–፲፰)። ጌታ ለእርሱ የግል መመሪያ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፲፩ እና ፴፡፩–፬ ውስጥ ሰጠው።

ዊትመር፣ ጆን

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ከስምንቱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች አንዱ። “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርን” በመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጾች ውስጥ ተመልከቱ። ወንጌልን ለመስበክ ተጠርቶ ነበር (ት. እና ቃ. ፴፡፩–፲፩)።

ዊትመር፣ ፒተር ዳግማዊ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ከስምንቱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች አንዱ። “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርን” በመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጾች ውስጥ ተመልክቱ። ጌታ ለእርሱ የግል መመሪያ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፲፮ እና ፴፡፩–፳ ውስጥ ተሰጠው።

ዊትኒ፣ ኒውል ኬ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ። ኒውል ኬ ዊትኒ የከርትላንድ ኦሀዮ (ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ) ኤጲስ ቆጶስ ነበር እና በኋላም እንደ ቤተክርስቲያና ኤጲስ ቆጶስ አመራር አገለገለ (ት. እና ቃ. ፳፪፡፩–፳፣ ፲፱፣ ፲፲፯)።

ውህደት። የሚስጥር ስብሰባ *ተምልከቱ*

ውልያምስ፣ ፍሬድሪክ ጂ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ከፍተኛ የክህንነ ስልጣን አመራር አማካሪ ያገለገለ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ (ት. እና ቃ. ፴፩፣ ፶፡፮፣ ፲፱፣ ፲፳፡፲)።

ውድሩፍ፣ ውልፈርድ። *ደግምም መግለጫ፤ አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ ተመልከቱ*

በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ወንጌሉ በዳግም ከተመለሰ በኋላ አራተኛው የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት የነበሩት። የተወለዱት በ፲፰፻፲፯ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በ፲፰፻፲፯፳፰ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

በአስራ ሁለቱ ሸንጎ ውስጥ ሀላፊነትን እንዲያሟሉ ተጠሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፰፡፮። በዘመን ሙላት ለመምጣት ከተጠበቁት ምርጥ መንፈሶችም መካከል ነበሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፭፰፡፱፲። በቤተክርስቲያን ውስጥ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን እንዲቆም ራዕይን ተቀበሉ፣ አ.አ. ፩።

ውግዘት። *ደግምም አመጽ፤ ክህደት ተመልከቱ*

ማውገዝ ቤተክርስቲያኗ ከምትቀጣበት መንገድ በጣም ጥብቅ የሆነው ነው። የተወገዘ ሰው የቤተክርስቲያን አባል አይደለም። የቤተክርስቲያን ባለስልጣኖች የጌታ ትእዛዛትን በመቃረን ለመኖር የሚመርጠውን እና በዚህም በቤተክርስቲያኗ አባል ለመሆን ብቁነትን የሚያጣውን ሰው ያወግዛሉ።

የብዙዎች ልብ ጠጥሯል፣ ስማቸው ተደምስሷል፣ አልማ ፩፡፳፬ (አልማ ፮፡፫)። ንሰሃ ካልገባ፣ ከህዝቦቼ መካከል አይቆጠርም፣ ፫ ኔፊ ፲፰፡፴ (ሞዛያ ፳፯)።

የሚያመንዝር፣ እናም ንሰሃ የማይገባ፣ ወደ ውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፬። ኃጢያትን የሚሰራና ንስሃ የማይገባ ወደ ውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፰። አስፈላጊ የሆኑ ችግሮችን የማስተካከያ ስነስርዓቶች ተሰጥተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፪ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፲–፲፫)። ኤጲስ ቆጶስ የእስራኤል ዳኛ እንዲሆን ተመድቧል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፷፪። ጻድቅ ህብረተሰቦች ሁሉ አባሎቻቸው በሚረብሹበት ጊዜ ለመቅጣት መብት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፬፡፲።

ዐይነ-እርግብ

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ (፩) የታቦትን ወይም የቤተመቅደስን ክፍሎች የሚያለያይ መከፋፈያ፣ (፪) የእግዚአብሔር እና የሰው መለያየት ምልክት፣ (፫) ሰዎች ፈታቸውን ወይም ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙበት ጨረቅ ወይም (፬) የሰዎችን የቅድመ ምድር ህይወት ትዝታን የሚዘጋ በእግዚአብሔር የተሰጠ ዝንጉነት።

መጋረጃውም በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ ይሁናችሁ፣ ዘፀአ. ፳፮፡፴፫።

የቤተ መቅደስ *መጋረጃ* ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፣ ማቴ. ፳፯፡፶፩ (ማር. ፲፭፡፴፰፣ ሉቃ. ፳፫፡፴፭)። ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደ ምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፣ ፩ ቆሮ. ፲፫፡፲፪።

እርሱም ያለማመን ጥቁር *መጋረጃው* ከአዕምሮው እንደተወሰደ ያውቅ ነበር፣ **አልማ** ፲፱፡፯። የያሬድ ወንድም በ*መጋረጃው* ውስጥ ከመመልከት ሊጠበቅ አልቻለም፣ ኤተር ፫፡፲፱ (ኤተር ፲፪፡፲፱)።

መጋረጃውም ይገፈፋል እናም አይታችሁኝ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲ (ት. እና ቃ. ፴፳፡፳)። ቤተ መቅደሴን የሚሸፍነው *መጋረጃ* ይወልቃል፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፫። *መጋረጃው* ከአዕምሮዎቻችን ተወገደ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፩።

የጭለማም *መጋረጃ* ምድርን ይሸፍናል፣ ሙሴ ፯፡፳፩።

ዑር

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የከለዳውያን ዑር የአብራም የመጀመሪያ ቤት ነበር (ዘፍጥ. ፲፩፡፳፯–፳፰፣ ፴፩፡፲ ፲፭፡፯፣ ነህ. ፱፡፯፣ አብር. ፪፡፩፣ ፱)።

ዔሳው። *ደግምም ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ፣ ይስሐቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይስሀቅ እና የርብቃ የመጀመሪያ ልጅ እና የያዕቆብ መንታ ወንድም። ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ወንድሞች ይፎካከሩ ነበር (ዘፍጥ. ፳፭፡፲፱–፳፯)። የዔሳው ትውልዶች፣ ኤዶማውያን፣ እና የያዕቆብ ትውልዶች፣ እስራኤላውያን፣ የሚፎካከሩ ሀገሮች ሆኑ (ዘፍጥ. ፳፭፡፳፫)።

ዔድን

ዔሳው ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፴፫ (ዕብ. ፲፪፡፲፮–፲፯)። ዔሳው ወላጆቹን በማሳዘን የኬጢ ሚስቶች አገባ፣ ዘፍጥ. ፳፮፡፴፬–፴፭። ያዕቆብ እና ዔሳው ታረቁ፣ ዘፍጥ. ፴፫።

ዔድን። *ደግሞም ሔዋን፣ አዳም ተመልከቱ*

የመጀመሪያ ወላጆቻችን፣ አዳምና ሔዋን፣ ቤት (ዘፍጥ. ፪፡፰–፲፡፳፬፣ ፴፡፲፯፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፱–፳፭፣ ሙሴ ፣–፴፣ አብር. ፭)፣ ይህም በስተምስራቅ ዔድን እንደገነት ተመድቦ ነበር። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላና ሟች ከሆኑ በኋላ ከዔድን እንዲወጡ ተደረጉ (ሙሴ ፪፡፳፭–፳፱)። የኋለኛው ቀን ራዕይ የመፅሐፍ ቅዱስ የዔድን ገነት ታሪክን አረጋግጧል። ገነት ይገኝበት የነበረው አሁን የሰሜን አሜሪካ በሚባለው ክፍለ አህጉር ውስጥ እንደነበረ አስፈላጊ መረጃ ጨምሯል።

ዕብራይስጥ። *ደግሞም እስራኤል ተመልከቱ*

የእስራኤል ልጆች የሚናገሩት የሴም ቋንቋ።

ከባቢሎን ምርኮ እስከሚመለሱ ድረስ እስራኤል ዕብራይስጥ ቋንቋ ይናገሩ ነበር፣ በዚያም ጊዜ አራሚኛ የየቀኑ የንግግር ቋንቋ ሆነ። በኢየሱስ ዘመን፣ ዕብራይስጥ የተማሩት፣ የህግ፣ እና የሀይማኖት መፅሐፎች ቋንቋ ነበር።

ዕንባቆም

በይሁዳ ውስጥ ምናልባት በዮአኪን አገዛዝ ዘመን ስለህዝቡ ኃጢያተኛነት የተናገረ የብሉይ ኪዳን ነቢይ (በ፲፯ ም.ዓ. አካባቢ)።

ትንቢተ ዕንባቆም፣ ምዕራፍ ፩ በኤርምያስ ፲፪ እና በትምህርት እና ቃል ኪዳን ፻፳፩ ውስጥ እን ደሚገኙት አይነት በጌታ እና በነቢዩ መካከል የነበረ ውይይት ነው። በምዕራፍ ፪ ውስጥ ጌታ ዕንባቆምን ትዕግስተኛ እንዲሆን መከረው—ጻድቅ ሰው በእምነት ለመኖር ይማራል። ምዕራፍ ፣ የእግዚአብሔርን ፍትህ የተቀበለበትን የዕንባቆምን ጸሎት መዝግቧል።

ዕዝራ

አንዳንድ አይሁዶችን ከባቢሎን ምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው የብሉይ ኪዳን ካህንና ጸሀፊ (ዕዝ. ፯–፲፣ ነህ. ፰፣ ፲፪)። በ፱፻፹፮ ም.ዓ. ከፋርስ ንጉስ አርጤክስስ ለመሄድ የሚፈልገውን ማንኛውንም የአይሁድ ስደተኛ ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ ፈቃድ አገኘ (ዕዝ. ፯፡፲፪–፳፭)።

ከዕዝራ ጊዜ በፊት፣ “ህግ” ተብለው የሚጠሩትን የተጻፉ ቅዱሣት መጻህፍትን በማንበብ ላይ ካህናት ሙሉ ስልጣን ነበራቸው። ዕዝራ ቅዱስ መጻህፍቱ ለሁሉም አይሁዶች ለመገኘት እንዲችሉ ረዳ። “የህጉ መፅሐፍ” መነበብ የአይሁዳ ሀገር ህይወት ዋና ክፍል ሆነ። ከዕዝራ ትምህርቶች ታላቁ ቢኖር የጌታን ህግ ለመፈለግ፣ ለማክበር፣ እና ለሌሎች ለማስተማር ልቡን ያዘጋጀበት የእራሱ ምሳሌ ነበር (ዕዝ. ፯፡፣)።

መፅሐፈ ዕዝራ፣ ምዕራፍ ፩–፯ ዕዝራ በኢየሩሳሌም ከመድረሱ ከስልሳ እስከ ሰማኒያ አመት በፊት የነበሩትን፣ በ፩፻፱፻፯ ም.ዓ. የቂሮስ አዋጅ እና በዘሩባቤል ስር የአይሁዳ መመለስ አይነት ድርጊ ቶችን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፯–፲ ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት እንደተመለሰ ያሳያሉ። እርሱ እና ከእርሱ ጋር የሚጓዙት ለጥበቃ ጾሙም ጸለዩም። በኢየሩሳሌም በዘሩባቤል ስር ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱና ከቃል ኪዳን ውጪ ሴቶችን ያገቡና በዚህም እራሳቸውን ያረከሱ ብዙ አይሁዶችን አገኙ። ዕዝራ ለእነርሱ ጸለየ እና ባለቤቶቻቸውን እንዲፈቱ በቃል ኪዳን ስር አደረጋቸው። የዕዝራ የኋለኛ ታሪክም በመፅሐፈ ነህምያ ውስጥ ይገኛል።

ዕጣ

የተለያዩ ምርጫዎችን የሚመረጥበት ወይም የሚወገድበት መንገድ፣ በብዙም ጊዜ የሚደረገው አንድ ወረቀትን ወይም እንጨትን ለብዙዎች መካ ከል በመምረጥ ነው። ይህም እጣ መጣል ይባላል።

ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ፣ ማቴ. ፳፯፡፣፲፰ (መዝ. ፳፪፡፲፰ ማር. ፲፭፡፳፬፣ ሉቃ. ፳፫፡፴፬፣ ዮሐ. ፲፱፡፳፬)። ዕጣም ተጣጣሉላ ቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀ፣ የሐዋ. ፩፡፳፫–፳፮።

ማን ወደ ላባን ቤት መሄድ እንዳለበት ዕጣ ተጣ ጣልን፣ ፩ ኔፊ ፣፡፲፩።

ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን

ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን። ቃል ኪዳን፣ አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን *ተመልከቱ*

ዘለአለማዊ አባት

ዘለአለማዊ አባት። እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ የሰማይ አባት *ተመልከቱ*

ዘለዓለማዊነት

ዘለዓለማዊነት። ከፍተኛነት *ተመልከቱ*

ዘመን

ዘመን። *ደግሞም ክህነት፣ ወንጌል፣ የክህነት ቁልፎች፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ*

የወንጌል ዘመን ጌታ በምድር ላይ የቅዱስ ክህነት ቁልፍ ያለው አንድም የሚሆን ባለስልጣን በምድር ላይ የነበረበት ጊዜ ነው።

አዳም፣ ሔኖክ፣ ኖህ፣ አብርሐም፣ ሙሴ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እና ሌሎች አዲስ የወንጌል ዘመንን እያንዳንዳቸው ጀምረዋል። ጌታ ዘመንን ሲያደራጅ፣ የእዚያ ዘመን ህዝቦች በወደ ፊቱ ዘመን ለደህንነት አላማ እውቀት የሚመኩ እን ዳይሆኑ ወንጌሉን እንደ አዲስ ይገለጻል። በጆሴፍ

ስሚዝ የተጀመረው ዘመን “የዘመን ፍጻሜ” ተብሎ ይታወቃል።

የሰማይ አምላክ መንግሥት ያስነሣል፣ ዳን. ፪፡፵፬ (ት. እና ቃ. ፰፩)።

በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፣ የሐዋ. ፪፡፲፯ (ኢዩ. ፪፡፳፰)። ገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ክርስቶስን ይቀበለው ዘንድ ይገባል፣ የሐዋ. ፫፡፳፩። በዘመን ፍጻሜ፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በክርስቶስ ይጠቀልላል፣ ኤፌ. ፩፡፣። ቤተክርስቲያኔን በእነርሱ መካከል እመሰርታ ለሁ፣ ፫ ኔፊ ፳፩፡፳፪።

ጌታ ለመጨረሻው ጊዜ የዘመነ ፍጻሜን ወን ጌልና የመንግስቱን ቁልፎች ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፫። የዘመን ቁልፎች በእጆቻችሁ ተሰጥተ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፣፡፲፪–፲፯። የድሮ ዘመን ቁል ፎች በሙሉ በዘመን ፍጻሜ በዳግም ተመልሰዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፳፡፲፳–፳፩።

ዘሩባቤል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ቂሮስ ለአይሁዶች ወደ ፍልስጥኤም እንዲመለሱ ፈቃድ ሲሰጣቸው፣ ዘሩባቤል እንደ አስተዳዳሪ ወይም እንደ አይሁዳ ልውል ቤት ወኪል ተመድቦ ነበር። የፋርሳዊው ስም ሰሳብሳር ነበር (ዕዝ. ፩፡፰)። የኢየሩሳሌም ቤተመ ቅደስን በመገንባትም ተሳታፊ ነበር (ዕዝ. ፫፡፪፣ ፳፣ ፭፡፪)።

ዘካሪያስ፡ ደግሞም መጥምቁ ዮሐንስ፤ ኤልሳቤጥ *ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ አባት። ዘካሪያስ የካህን ሀላፊነት ነበረው እናም በቤተመቅ ደስ ውስጥ አገለገለ።

ዘካሪያስ በቤተመቅደሱ እና በመሰዊያው መካከል ተገደለ፣ ማቴ. ፳፫፡፴፭ (ሉቃ. ፲፩፡፶፩)። መል ዓኩ ገብርኤል ዘካሪያስን እና ሚስቱ ኤልሳቤጥን ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ ቃል ገባላቸው፣ ሉቃ. ፩፡፭–፳፭ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፣)። ምላሱ ተፈታ፣ ሉቃ. ፩፡፶፱–፷፬።

ዘይት፡ *ደግሞም ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፤ መቀባት፤ የወይራ ዛፍ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ዘይት ሲጠቀስ፣ ብዙ ጊዜ የወይራ ዛፍ ዘይት ማለት ነው። ከብሉይ ኪዳን ዘመናት ጀምሮ፣ የወይራ ዛፍ ዘይት ለቤተመቅደስ እና ለድንኳን ስርዓት፣ ፋኖስ ለማብራት፣ እና ለም ግብ የሚጠቀሙበት ነው። የወይራ ዘይት አንዳንዴ ለንጹህነት እና ለመንፈስ ቅዱስና ለእርሱ ተጽዕኖ ምልክት ነው (፩ ሳሙ. ፲፡፩፣ ፲፣ ፲፮፡፲፫፣ ኢሳ. ፷፩፡፩–፫)።

ካህኑም በእጁ ውስጥ ካለው ዘይት የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ ላይ ያስነካዋል፣ ዘሌዋ. ፲፬፡፳፭–፳፱። በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንድትሆን እቀባህ ዘንድ እግዚአብሔር ላከኝ፣ ፪ ሳሙ. ፲፮፡፩። ዘይቱም ከባልቴቷ ማሰሮው አል ጎደለም፣ ፪ ነገሥ. ፲፣፡፣–፲፯። ጌታ ራሴን በዘይት ቀባህ፣ መዝ. ፳፫፡፩።

ብዙ ድውዮችንም ዘይት ቀቡ፣ ማር. ፮፡፲፫። ሽምግሌዎች እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፣ ያዕ. ፭፡፲፫–፲፭።

መብራታችሁን አስተካክላችሁ ለኩሱ እና ዘይታ ችሁን ያዙ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፣ (ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫)።

ዚኖስ

ስለክርስቶስ ተልዕኮ የተነበየ በብሉይ ኪዳን ዘመን በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ ብቻ የተጠቀሰ የእስራ ኤል ነቢይ።

ስለክርስቶስ መቀበር እና ስለሶስት ቀን ጭለማ ተነበየ፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡፣፣ ፲፪። ስለእስራኤል መሰብ ሰብ ተነበየ፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡፲፯። ያዕቆብ ከዚኖስ ስለለ ማው እና ስለዱር የወይራ ዛፍ ታሪክ ጠቀሰ፣ ያዕቆ. ፭። ያዕቆብ የዚኖስን ምሳሌ አብራራ፣ ያዕቆ. ፮፡፩–፣። ጸሎትን እና አምልኮን በሚመለከት አስተማረ፣ አልማ ፴፫፡፣–፲፩። ቤዛነት የሚመጣው በወልድ በኩል እንደሆነ አስተማረ፣ አልማ ፴፬፡፮። ለደ ፋር ምስክሩ ተገደለ፣ ሔሌ. ፭፡፲፱። ስለላማናው ያን ዳግም መመለስ ተመለሰ፣ ሔሌ. ፲፭፡፲፩። በክ ርስቶስ ሞት ስለሚመጣው ጥፋት መሰከረ፣ ፫ ኔፊ ፣፡፲፭–፲፯።

ዚኤዝሮም

በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በአሞኒሀ ከተማ ውስጥ የነበረ ጠበቃ። አልማ እና አሙሌቅ በመንፈስ በኩል ዚኤዝሮም እንደዋሸ ለመመልከት ቻሉ። በኋ ላም ወደ ክርስቶስ ወንጌል ተቀየረ (አልማ ፲፩፡፳፩–፳፯፣ ፲፭፡፩–፲፪)።

ዛራሔምላ፡ *ደግሞም ሙሌቅ፤ አሞን፣ የዛራሔምላ ትውልድ ተመልከቱ*

በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ዛራሔምላ (፩) የሙሌቅ ግዛትን የሚመራን ሰው፣ (፪) ከእርሱ ስም የተጠራ ከተማ፣ (፫) የዛራሔምላ ምድር፣ ወይም (፬) እርሱን የሚከተሉ ሰዎችን የሚጠቁም ነው።

ጌታ ኔፋውያንን ስለላከ ዛራሔምላ እጅግ ተደ ሰተ፣ ኦምኒ ፩፡፲፬። ዛራሔምላ የአባቶቹን ትው ልድ ሐረግ ሰጠ፣ ኦምኒ ፩፡፲፰። አሞን የዛራሔምላ ትውልድ ነበር፣ ሞዛያ ፯፡፫፣ ፲፫። ቤተክርስቲ ያኗ በዛራሔምላ ከተማ ተመሰረተች፣ አልማ ፩፡፪። ፃድቃን በሆኑት ምክንያት ነው ዛራሔምላ

የዳነችው፣ ሔሌ. ፲፫፡፲፪። በክርስቶስ ሞት ጊዜ የዛራሔምላ ከተማ ተቃጠለ፣ ፫ ኔፊ ፰፡፰፣ ፳፩።

ዛብሎን። *ደግሞም* እስራኤል፣ *ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፲፱–፳)።

የዛብሎን ጎሳ፣ ያዕቆብ የዛብሎን ጎሳን ባረከ (ዘፍጥ. ፵፱፡፲፫)። የዛብሎን ጎሳ ከዲቦራ እና ከባርቅ ጋር ከእስራኤል ጠላቶች ጋር ለመዋጋት ተባበረ (መሳ. ፬፡፭–፮፣ ፣)። እነርሱም ከጌዴዎን ጋር ተባብሮ ከምድያማውያን ጋር ተዋጋ (መሳ. ፮፡ ፡፲–፳)።

ዛካርያስ

በ፭፻፳ ም.ዓ. አካባቢ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። ነቢዩ ሐጌ በኖረበት ጊዜ የሚኖር ነበር(ዕዝ. ፭፡፩፣ ፮፡፲፬)።

ትንቢተ ዛካርያስ፣ መፅሐፉ ስለክርስቶስ የም ድር አገልግሎት እና ስለዳግም ምፅዓቱ ስላለው ትንቢቶች የታወቀ ነው (ዘካ. ፱፡፱፣ ፲፩፡፲–፲፣ ፲፪፡፲፣ ፲፣ ፲፣ ፲፡፲)። ምዕራፍ ፩–፰ ስሌማዚአብሔር ህዝቦች ወደፊት ራዕዮችን የያዙ ነበሩ። ምዕራፍ ፱–፲፬ ስለመሲህ፣ ስለመጠረሻው ቀናት፣ ስለእስራ ኤል መሰብሰብ፣ ስለመጠረሻው ታላቅ ጦርነት፣ እና ስለዳግም ምፅዓት ራዕዮችን የያዙ ናቸው።

ዜኒፍ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ወደ ኔፊ ምድር የተመለሱትን ቡድኖች የመራ ሰው፣ የእነርሱ ንጉስ ሆነ እናም በጻድቅ መራቸው (ሞዛያ ፱–፣)።

ዜና ማዋእል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ሁለት መጻህፍቶች። እነዚህም ከፍጥረት ጀምሮ አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ እስከታወጀበት ድረስ የነበሩትን ድርጊቶች አጭር ታሪክ ይዘረዝራሉ።

ዜና ማዋእል ቀዳማዊ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ከአዳም እስከ ሳኦል የነበሩትን ትውልዶች ይዘረዝራሉ። ምዕራፍ ፣ የሳኦል ሞትን ይዘረዝራል። ምዕራፍ ፲፩–፳፱ የዳዊት ግዛት ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ይገልጻል። ምዕራፍ ፳፫–፳፯ ሰለሞን እንደነገሰና ሌዋውያን በስነስርዓት እንደተደራጁ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፳፰ ዳዊት ለሰሞንን ቤተመቅደስ እንዲ ገነባ እንዳዘዘው ይገልጻል። ምዕራፍ ፳፱ የዳዊት ሞትን ይመዘግባል።

ዜና ማዋእል ካልዕ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ከሰለሞን ግዛት ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ይገልጻል። ምዕራፍ ፣–፲፪ አንድ የነበረው የእስራኤል መንግስት ወደ ሰሜንና ደቡብ ግዛት ስለተከፋፈለበት ስለሰለሞን ልጅ ሮብዓም ግዛት ይናገራሉ። ምዕራፍ ፲፫–፴፮ ናቡከደነፆር የአይሁድን መንግስት በምርኮ እስከ ሚይዝበት ድረስ የነበሩትን የተለያዩ ንጎሶች ይገ ልጻል። መፅሐፉም ቂሮስ በምርኮ የተያዙት የአይ ሁድ ልጆች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ በሚያ ውጅበት ይፈጸማል።

ዜኖቅ

በብሉይ ኪዳን ዘመን በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ብቻ የተጠቀሰ የእስራኤል ነቢይ።

ስለክርስቶስ ሞት ተነበየ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፣። ስለእግ ዚአብሔር ልጅ ተናገረ፣ **አልማ** ፴፫፡፲፩ (**አልማ** ፴፴፡፯)። ለእውነት ሰማዕት ነበር፣ **አልማ** ፴፫፡፲፯። ስለመሲሕ መምጻት ተነበየ፣ ሔሌ. ፰፡፳፰።

ዝሙት መፈጸም

ደግሞም ማመንዘር፣ ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ ንጹህነት ተመለከቱ

ባልተጋቡ ሰዎች ወከከል የሚፈጸም ህጋዊ ያል ሆነ ፍትወተ ስጋ ግንኙነት። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ይህም እንደ ክህደት ምሳሌ የሚጠቀሙበት አንዳንድ ጊዜዎች አሉ።

ከዝሙት የራቃችሁ ሁኑ፣ **የሐዋ.** ፲፭፡፳፱። ሰውነት ለጌታ እንጂ ለዝሙት አይደለም፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፲፫–፲፰። ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣ ፩ ቆሮ. ፯፡፪–፫። ይህ የእግዚአ ብሔር ፈቃድ ነው፣ ከዝሙት እንድትርቁ፣ ፩ ተሰ. ፬፡፫።

ያዕቆብ ህዝቡን ከዝሙትና አስጠነቀቀ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፪። በመግደላችሁ፣ እናም ዝሙት በመፈፀማ ችሁ እንዲሁም በክፋታችሁ ለዘለዓለማዊው ጥፋት በስላችኋል፣ ሔሌ. ፲፡፳፯።

ዝሙት ፈጻሚዎች የቤተክርስቲያኗ አባል ለመ ሆን ንስሀ መግባት አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳–፳፯።

ዞራም፣ ዞራማውያን

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ወደ ቃል ኪዳን ምድር ለመምጣት ከኔፊ እና ከሌሂ ጋር የተባበረ የላ ባን አገልጋይ (፩ ኔፊ ፬፡፴–፴፭)። በዞራም ታማ ኝነት ምክንያት፣ ሌሂ ከሌሂ ልጆች ጋር አብሮ ባረ ከው (፪ ኔፊ ፩፡፴–፴፪)። ትውልዶቹ ዞራማውያን ተብለው ይታወቁ ነበር (ያዕቆ. ፩፡፲፫)።

የህይወት እንጀራ

ደግሞም ቅዱስ ቁርባን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ

ኢየሱስ ክርስቶስ የህይወት እንጀራ ነው። የቅዱስ ቁርባን እንጀራ (ዳቦ) የክርስቶስን ሰውነት በምሳ ሌነት ይወክላል።

